www.abyssinialaw.com

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት

www.abyssinialaw.com

## መግቢያ

የወንጀል ሕግ የአንድን አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ለማስጠበቅ የሚያስችል፣ የግለሰቦችን መብትና ነፃነት የሚያስከብር መሆን እንደሚገባው ይታመናል። በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣውና አሁን የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በጊዜና በተለያዩ ምክንያቶች ሕጉ ከወጣ በኋላ ያለውን የዕድገት የአስተሳሰብና ሌሎች ሁለንተናዊ ለውጦችን በተሟላ ሁኔታ ያገናዘበ አይደለም።

በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ፀድቆ በሥራ ላይ በዋለው ሕገ-መንግሥት ከተካተቱትና አገሪቱ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ከተመለከቱት መብቶችና ነፃነቶች ጋር መጣጣም ይኖርበታል።

በዚህም መሠረት የተወካዮች ምክር ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ያሻሻለ ሲሆን ይህ ማብራሪያ ተሻሽሎ በቀረበው የወንጀል ሕግ /ከቁጥር.፩-፰፻፷/ በዋናነት ለውጥና ማሻሻያ በተደረገባቸው ድንጋጌዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

ማብራሪያው ቀደም ሲል ያልነበሩ አዳዲስ አስተሳሰቦች እንዲካተቱ የተደረገበትን ምክንያት በዝርዝር የሚያሳይ ሲሆን ማሻሻያ የተደረገባቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ድንጋጌዎች በቅርጽና በይዘት ከነባር ሕጉ በምን እንደሚለዩ ያመለክታል። በአንፃሩ ከነባሩ ሕግ እንዲወጡ የተደረጉ ድንጋጌዎች የተሰረዙበት ምክንያትም ተመልክቷል።

www.abyssinialaw.com



# የ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የወንጀል ሕግ
# ሐተታ ዘምክንያት

## መጀመሪያ ታላቅ ክፍል
## ጠቅላላ ክፍል

## አንደኛ መጽሐፍ
## ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊው

### ርዕስ አንድ
### የወንጀል ሕግና የአፈጻጸሙ ወሰን

#### ምዕራፍ አንድ
#### የሕጉ ተፈጻሚነት ወሰን

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ የሕጉ ስያሜ "የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ" የሚል ሲሆን ይህ መሆኑ ቀርቶ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ" በሚል አገላለጽ ተስተካክሏል:: በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር የተዘረዘረ ሲሆን በተለይ በንዑስ አንቀጽ ፭ ላይ ምክር ቤቱ "የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያወጣል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ይኖራቸዋል::" ተብሎ ተደንግጓል::

ከዚህ ንዑስ አንቀጽ መረዳት እንደሚቻለው የአገሪቱ ሉዓላዊ ሕግ አውጪ አካል የሚያወጣው ሕግ የሚጠራው የፌዴራል የወንጀል ሕግነቱን በሚያሳይ ስያሜ ነው:: የፌዴራል የወንጀል ሕጉ ለክልሎች ሁሉ ተፈፃሚነት ቢኖረውም በየክልሉ ሊኖር የሚችለውን የወንጀል ጉዳይ ሁሉ በማይሸፍንበት ጊዜ ክልሎች የየራሳቸውን ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ:: በአ... በተወሰነ ጊዜ የሚወጣ ሕግ በጊዜው ያለውን የመንግሥት አስተዳደር ዓይነት ማካተቱ የተለመደ ነው:: ስለዚህ ከላይ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የወንጀል ሕጉ ስያሜ ተለውጦ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፩ ዓላማና ግብ

ይህ አንቀጽ ሁለት ፓራግራፎች ያሉት ሲሆን፣ በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ የሚከተለው ለውጥ ተደርጓል::

"State" የሚለው የእንግሊዚኛ ቃል የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግሥታቱን እንዲሁም ጠቅላላ የሀገሪቱን ገጽታ ስለሚያካትት "የመንግሥትን" በሚለው ቃል ምትክ የአገሪቱን መንግሥት የሚለው ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል::

ሕገ መንግሥቱ ለብሔር ብሔረሰቦች እና ለህዝቦች ከፍተኛ ጥበቃ ያደረገላቸው በመሆኑ የወንጀል ሕጉ ይህንን ሊያንፀባርቅና ሕጉ ነዋሪዎችን በግለሰብነታቸው ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ኅብረት በተቋቋሙበት ሁኔታ ጥበቃ ሊያደርግላቸው እንደሚገባ ግልጽ ነው፣ ሆኖም በሕግ ፊት እኩል ስለመሆን በሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፭ ላይ የተመለከተውን መሠረት አድርጎ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ~~ሁለት~~ (፪) ላይ "ብሔሮች" እና "ብሔረሰቦች" የተጠቀሱ-

www.abyssinialaw.com

በመሆናቸው "ሕዝቦች" የሚለው አጠቃላይ ቃል ብቻ በአንቀጽ አንድ (፩) ላይ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

ዜጐች ከማለት ይልቅ "ነዋሪዎች" የሚለው ዜጐችንም ሆነ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የውጭ አገር ሰዎች ስለሚያጠቃልልና የወንጀል ህግ ጥበቃ የሚያደርገው ለሰዎች ሁሉ ስለሆነ በ"ዜጎች" ፈንታ "ነዋሪዎች" የሚለው ቃል ገብቷል፡፡

በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የሚከተለው ለውጥ ተደርጓል፡፡ "It aims at the prevention of offences" የሚለው የእንግሊዝኛ ሀረግ መኖር እጅግ አስፈላጊ ሲሆን በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የአማርኛ ቅጂ ላይ ስለሌለ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የወንጀል ሕግ ዓላማውን ከግቡ የሚያደርሰው ወንጀል እንዳይፈፀም በመከላከል በመሆኑ እና በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ዘዴዎች ወንጀል እንዳይፈፀም ለመከላከል የሚያገለግሉ እንጂ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ግቦች ባለመሆናቸው ነው፡፡

ቅጣት ወንጀል አድራጊዎችን ለማረም እስካገለገለ ድረስ እንጂ ራሱን ችሎ እንደ አንድ ግብ ሊጠቀስ ስለማይገባና የወንጀል ህጉ አንድ ግብ መቅጫ እንደሆነ በተሻረው ህግ ላይ መገለጹ ስላልተደገፈ "የወንጀለኞች መቅጫ" የሚለው ሀረግ ቀርቶ "ወንጀል አድራጊዎች ተቀጥተው እንዲታረሙ በማድረግ" የሚለው የተሻለ በመሆኑ በዚሁ ተተክቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ "ከጥፋትና ከወንጀል እንዲወገዱ ማድረጊያ ነው" የሚል ሀረግ በቁጥር ፩ ፓራግራፍ ሁለት መደምደሚያ ላይ ይገኛል፡፡ እንግሊዝኛው "Measures to prevent the commission of further offfences" ስለሚል የአማርኛውን አነጋገር ከዚህ ጋር ለማጣጣም "ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በማድረግ" በሚል ተተርጉሟል "ማስወገድ" የሚለው ቃል የጭካኔን አስተሳሰብ የሚያመለክት ስለሚመስል ተሰርዟል፡፡

አንቀጽ ፪ <u>የሕጋዊነት መርህ</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪ ስያሜ "የሕግነቱ መሠረት" የሚል ነበር፡፡ ስያሜው በውስጡ ያለውን ይዘት በሚገባ የሚያንጸባርቅ ስላልሆነና "Principle of Legality" ከሚለው እንግሊዝኛ ቅጂ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ይህንኑ ለማንጸባረቅ ሲባል የዚህ ረቂቅ አንቀጽ ፪ ስያሜ "የሕጋዊነት መርህ" ተብሎ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

በዚህ ረቂቅ ውስጥም በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ መሠረቱ በማለት የተጠቀሰው "መርህ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል፡፡

ይዘቱንም በተመለከተ በ፲፱፻፵፱ኙ ሕግ በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው መስመር ላይ "የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ" በማለት የተጻፈው ከላይ በአንቀጽ (፩) በተነገረው መሠረት ወጥነት (Consistency) እንዲኖረው በማሰብ "የወንጀል ሕግ" በሚል ተተክቷል፡፡ እንዲሁም "ጥንቃቄዎች" በማለት የተጠቀሰው ግልጽነት የሚጐለው በመሆኑ "የጥንቃቄ እርምጃዎች" ተብሎ እንዲጻፍ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ሌላ በነባሩ ሕግ ቁጥር ፪ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር አንዳንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪

www.abyssinialaw.com



የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል:: የነባሩ ሕግ የቁጥር ፪ የሁለተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ሆኖ ገብቷል:: እንዲሁም ፍርድ ቤት የሚወስነው በሕጉ ላይ የተደነገገውን ቅጣት ነው ማለቱ ብቻ ስለማይበቃ "የቅጣቶቹ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈፃጸምም በሕግ ከተመለከተው ውጪ መሆን አይችልም" የሚል አዲስ አሳብ ተጨምሮበት የፓራግራፉ ሁለተኛ ዓረፍተ-ነገር ሆኖ ገብቷል::

በተጨማሪም በዚሁ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የተመለከተው ፍሬ አሳብ ግልጽነት እንዲኖረው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል::

በነባሩ ሕግ ንዑስ ቁጥር (፪)ን በተመለከተ "ሕግ ሰጪው" የሚለው ሐረግ ሕግ አውጭውን ለማመልከት ስለሆነ በዚህ ሕግ ውስጥ "ሕግ አውጪው" በሚል ተስተካክሏል::

ከዚህ በተረፈ ንዑስ ቁጥሩ በነባሩ ሕግ የያዘውን ፍሬ አሳብ እንደጠበቀ ሆኖ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ከተደረገበት በኋላ የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ገብቷል::

የነባሩ ሕግ ቁጥር ፪ ንዑስ ቁጥር (፫)ንም በተመለከተም አንድ ሰው ሁለት ጊዜ እንደማይቀጣ ይደነግጋል ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፫ ላይ ሁለት ጊዜ መቀጣትን ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ መከሰስንም ጭምር የሚከለክል በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ "ማንም ሰው በሕግ መሠረት ተከሶ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ በተወሰደበት ወይም ነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" ተብሎ በተሻሻለው ሕግ አንቀጽ ፪/፭/ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል:: በሕገ-መንግስቱ ላይ "በወንጀል ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት" የሚለውንም ሐረግ በማሳጠር "በሕግ መሠረት" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል::

አንቀጽ ፫ <u>ሌሎች የሚያስቀጡ ሕጎች</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፫ ስያሜ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫ ስያሜ ሆኖ ገብቷል::

በመጀመሪያው ፓራግራፍ ሥር "ደንብ" የሚለው ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ውስጥ የሚገኘውን የደንብ ተላላፊዎች ሕግን የሚመለከት ሳይሆን ከዚህ ሕግ ውጭ ሊደነገጉ የሚችሉ ሌሎች ደንቦችን በመሆኑ ይህንኑ በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ ተደንግጓል::

የቁጥር ፫ የሁለተኛው ፓራግራፍ አነጋገር በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ተሻሽሎ የቀድሞውን አሳብ እንደያዘ እንዲቀጥል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬ <u>በሕግ ፊት እኩል መሆን</u>

የ፲፱፻፵፱ኙ የወንጀል ሕግ የቁጥር ፬ ስያሜ "በሕግ ፊት ትክክል ስለመሆን" የሚል ነበር ሆኖም ከይዘቱ መረዳት እንደሚቻለው ሕግ ሁሉንም በእኩል እንደሚያይ እንጂ እንደሚያስተካክል የሚደነግግ አይደለም፡፡

ስለዚህም ስያሜው ይዘቱን በሚገባ ማንፀባረቅ እንዲችል እና ከእንግሊኛው ቅጂ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ እንዲኖረው በማሰብ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬ ስያሜ "በሕግ ፊት እኩል መሆን" ተብሏል፡፡

በነባሩ ሕግ ቁጥር ፬ የመጀመሪያ ፓራግራፍ ላይ ሕጉ ልዩነት እንዳይደረግባቸው ከሚዘረዝራቸው በተጨማሪ በብሔር ብሔረሰብ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሐይማኖት እንዲሁም በፖለቲካ አመለካከት ወዘተ... የመሳሰሉት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት ውስጥ የተዘረዘሩ ጉዳዮችን በማካተት ከሕገ-መንግስቱ ጋር ተጣጥሞ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬ የመጀመሪያ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል፡፡

የቁጥር ፬ ሁለተኛውን ፓራግራፍ ስንመለከት ልዩነት የሚደረግባቸውን ጉዳዮች በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም "በመንግሥት ሕግና በሕገ-መንግሥት" የታወቁ የማይደፈሩ መብቶችን የሚለው ሐረግ የሐገራችንን ሕግ ብቻ የሚያመለክት መስሎ ስለሚታይ በዓለም-አቀፍ ሕግ መሠረት የተሰጡ የማይደፈሩ መብቶችንም ማካተት ይቻል ዘንድ በነባሩ ሕግ ውስጥ የሚገኘው "የመንግስት ሕግ" የሚለው ሐረግ እንዲወጣ ተደርጎ "የዓለም አቀፍ ሕግ" የሚል ሐረግ "ሕገ-መንግሥት" ከሚለው ሐረግ በፊት እንዲገባ ከተደረገ በኋላ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ በማድረግ በዚህ ሕግ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>የሕጉ አፈጻጸም ወሰን</u>
<u>ክፍል አንድ</u>
<u>ጊዜን የሚመለከቱ ሁኔታዎች</u>

"የጊዜ ሁኔታ" ይል የነበረው የቀድሞው ስያሜ ተሻሽሎ ከላይ በተመለከተው መሠረት ተስተካክሏል፡፡

አንቀጽ ፭ <u>የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ</u>

አንቀጽ ፭ ሦስት ንዑስ አንቀጾች እንዲኖሩት የተደረገው፣ የተሻረው ሕግ ይሰራበት በነበረ ጊዜ ተፈጽሞ አዲሱ ሕግ እስከፀናበት ጊዜ ድረስ ግን ውሳኔ ያላገኘ ድርጊትን በሦስት መልክ ከፍሎ ማሣየት ስለሚያስችል ነው፡፡ ይኸውም፡- ንዑስ አንቀጽ (፩) በሁለቱም ሕጎች ወንጀል የሆነ ድርጊትን ይመለከታል፤ ንዑስ አንቀጽ (፪) በአዲሱ ሕግ ወንጀልነቱ ተደንግጐ በተሻረው ሕግ ግን እንደወንጀል ስላልተቆጠረ ድርጊት ይደነግጋል፤ ንዑስ አንቀጽ (፫) ደግሞ በተሻረው ሕግ እንደወንጀል ተቆጥሮ የነበረ በአዲሱ ግን ወንጀልነቱ የቀረ ድርጊትን ይሸፍናል፡፡

www.abyssinialaw.com



የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭/፩/ "ይህ ሕግ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ማንም ሰው ሕግን የጣሰ እንደሆነ የሚፈረደው በዚሁ ሕግ ድንጋጌዎች ነው:: ወንጀሉ የተሠራው የቀድሞ የወንጀል መቅጫ ደንብ ይሰራበት በነበረ ጊዜ የሆነ እንደሆነ ፍርዱ የሚፈረደው በዚያው በቀድሞው ሕግ በተመለከተው መሠረት ነው::" የሚል ሲሆን የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አለመስራቱን ስለማያሳይ ከአንቀፁ ስያሜ ጋር አይጣጣምም:: በተጨማሪም አዲሱ የወንጀል ሕግ ከግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና እንደሚሆንና የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንደተሻረ በአዲሱ ሕግ መግቢያ ላይ ስለተገለጸ፣ የቁጥር ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር አስፈላጊ አይደለም:: በመሆኑም የቁጥር ፭ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለት ዓረፍተ-ነገሮችን በአንድ ዓረፍተ-ነገር በማካተት ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ተቀርጿል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭/፪/ የሆነው የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር "ይህ ሕግ እንዲፀና ከመደረጉ በፊት የተሰራ ሥራ ሲኖርና ሕግን እንደመጣስ ያልተቆጠረ ሲሆን በዚህ ሕግ ሊያስቀጣ አይችልም" የሚል ሲሆን ድርጊቱ በዚህ ሕግ መሠረት ወንጀል መሆን አለመሆኑ ግልጽ አይደለም:: ሆኖም በሁለቱም የወንጀል ሕጎች እንደወንጀል ያልተቆጠረ ድርጊት አያስቀጣም ብሎ መደንገጉ ስለማያስፈልግ ድርጊቱ በተሻረው ሕግ የማያስቀጣ በዚህ ሕግ ግን እንደወንጀል የተቆጠረ መሆን ይኖርበታል:: በዚህ መሠረት አነጋገሩ ተሻሽሎ ተቀርጿል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭/፪/ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር "እንዲሁም የሕግ መጣስ ነገር በተደረገበት ጊዜ ባልተጻፈ ቅጣት ሊፈረድ አይቻልም" የሚል ሲሆን የዚህ ዓይነቱ አሳብ ስለሕጋዊነት መርህ በተፃፈው በአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተካተተ በመሆኑ ከዚህ አንቀጽ ተሰርዟል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል:: ይኸውም "ይህ ሕግ እንዲፀና ከመደረጉ በፊት የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ሕግ ግን እንደ ወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል::" የሚል ነው:: አንቀጽ ፱/፩/ የተጀመረ ክስን ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ቅጣትን ሲያስቀር ስላልተጀመረ ክስ የሚደነግገው ነገር የለም:: በመሆኑም ይህንን ሁኔታ አንቀጽ ፭/፫/ እንዲሸፍን ተደርጓል::

አንቀጽ ፮ <u>የተለየ ሁኔታ፣ የተሻለውን ሕግ ተፈፃሚ ማድረግ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፮ ስያሜ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ስያሜ ሆኖ ገብቷል:: ይዘቱንም በተመለከተ በሁለቱ ፓራግራፍ ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

አንቀጽ ፯ <u>የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈፃፀም</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፯ ላይ የተመለከተው ስያሜ ውስጥ "ደንቦች" በሚል ቃል ምትክ "እርምጃዎች" የሚለው ቃል ገብቷል፤ ምክንያቱም "Measures" ለሚለው ቃል "የጥንቃቄ እርምጃዎች" የሚለው ሐረግ የተሻለ ትርጉም በመሆኑ ነው::

የአንቀፁን ይዘት በሚመለከት "ባለፈው ሕግ ቅጣትን የሚያስከትሉ ቢሆኑም" የሚለው ሐረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ዶ/ር ግራቨን በመጽሐፋቸው ላይ እንደገለፁት የ፲፱፻፷፫ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለ ጥንቃቄ እምርጃዎች የማይደነግግ ሲሆን በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከተደነገጉት የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዳንዶቹ በቅጣት

 www.abyssinialaw.com

መልክ በ፲፱፻፳፫ በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተካትተው ነበር:: በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በዚህ ሕግ ግን የጥንቃቄ እርምጃዎች ጥፋተኛውን ወደ ሰላማዊ ኑሮ ለመመለስና የሕብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች እንጂ እንደ ቅጣት አይቆጠሩም::

ከዚህም በላይ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በሚመለከት ይህ ሕግ ከ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የተለየበት ምክንያት በመኖሩና የጥንቃቄ እርምጃዎች ለጥፋተኛውም ሆነ ለሕብረተሰቡም ጥቅም የሚውሉ በመሆናቸው በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚፈረድበት ሰውም ቢሆን የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰዱበት በዚህ በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት መሆን ይገባዋል::

ስለዚህ የአንቀጽ ፯ ስያሜና ይዘት ከላይ በተገለፀው መሠረት ተሻሽሎ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፰ <u>የይርጋ ዘመን አፈፃፀም</u>

"የግል ከሳሹ" የሚለው ሀረግ ዓቃቤ ሕግን ተክቶ በፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብና የሚከታተል ተበዳይ ሲሆን ሀረጉ በዚህ ቦታ አግባብነት ስለሌለው በምትኩ "አቤቱታ አቅራቢ" የሚለው ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: ከዚህ በስተቀር ድንጋጌው ከአንዳንድ የቃላት ለውጦች ጋር ባለበት ሁኔታ እንዲቀጥል ተደርጓል::

አንቀጽ ፱ <u>በተሻረው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም</u>

የቁጥር ፱ ስያሜ "አዲሱ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በተሰጡት ፍርዶች ላይ የዚህ ሕግ አፈፃፀም" የሚል ሲሆን አገላለፁ ስሕተት ነው:: ምክንያቱም ፍርድ የሚሰጠው በተሻረው ሕግ መሠረት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ፍርድ የተሰጠው ግን ይህ ሕግ ከፀና በኋላም ሊሆን ስለሚችል ነው:: በዚህ መሠረት የእንግሊዝኛው "judgments passed under legislation repealsed by this code" እንደሚለው ተስተካክሎ "በተሻረው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች አፈፃፀም" በሚል ስያሜ ተተክቷል::

የቁጥር ፱/፩/ ሁለተኛው ፓራግራፍ ከመጀመሪያው ፓራግራፍ ጋር ይሄን ያህል የጠበቀ ግንኙነት አለው ለማለት ስለማያስደፍር አገላለጹ ተሻሽሎ ራሱን የቻለ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ተረቅቋል::

የቁጥር ፱/፪/ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር "በፍርድ የተወሰኑ ቅጣቶች አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት ይህ ሕግ በሥራ ላይ እንደዋለ ወዲያውኑ በዚህ ሕግ በተመለከተው ድንጋጌና ፎርም ይፈፀማል" ይላል:: ፍርድ የተሰጠው በተሻረው ሕግ መሠረት መሆኑ ግልጽ ነው:: ነገር ግን ፍርዱ የተሰጠው ይህ ሕግ ከፀና በኋላ ይሁን ወይም ከዚያ በፊት የተሰጠውን ፍርድ የሚጨምር ለመሆኑ ግልጽ አይደለም በሁለቱም ጊዜ የተሰጠውን ፍርድ ቅጣት ሊያካትት እንደሚገባ ይታመናል:: ለምሣሌ የግርፋት ቅጣት በአዲሱ ሕግ ስለተሻረ አዲሱ ሕግ ከመጽናቱ በፊትም ሆነ በኋላ ግርፋት የተወሰነበት ሰው ግርፋቱ ሊቀርለት ይገባል:: በዚህ ምክንያት አንቀጽ ፱/፫/ የመጀመሪያው ዓረፍተ.ነገር መግቢያ "ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊትም ሆነ በኋላ በተሰጡ ወይም በሚሰጡ ፍርዶች የተወሰኑ ቅጣቶች አፈፃፀም" በሚል ተተክቷል::

ቁጥር ፱/፪/ -እና /፫/ አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎባቸው ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንዲሆኑ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፲ የወንጀለኞች ሪኮርድ መሰረዝንና መሰየምን በማመለከት የዚህ ሕግ አፈፃፀም

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ ከእንግሊዝኛውና ከፈረንሳይኛው ቅጂ ጋር ሲነፃፀር አገላለጹ ስህተት ነው:: የአንቀጹ ይዘት የቀድሞው ሕግ የፍርድ ሪኮርድ የሚሰረዘውና ወንጀለኛው የሚሰየመው በዚህ ሕግ መሠረት ነው ለማለት እንጂ ሪኮርድ የሚሰረዝበትና ወንጀለኛው የሚሰየምበት ፍርድ በቀድሞው ሕግ መሠረት ተሰጥቷል ለማለት አይደለም:: በዚህ ምክንያት እንዲስተካከል ተደርጐ ተረቅቋል::

## ክፍል ሁለት
## በታን የሚመለከቱ ሁኔታዎች
## ንዑስ ክፍል አንድ
## ዋና አፈጻጸም

"የቦታ ሁኔታ" የሚለው የቀድሞው ስያሜ ተሰርዞ ከላይ በተጸፈው ዓይነት ተስተካክሎአል::

አንቀጽ ፲፩ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚደረጉ ወንጀሎች፣ መደበኛ ሁኔታ

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፩ ስያሜ "በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት የሚደረጉ ወንጀሎች ደንበኛ ሁኔታ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ ስያሜ ከዚህ የወንጀል ሕግ ጋርና ከወቅቱም ሁኔታ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ እንዲሁም ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በትርጓሜ ማጣጣም በማስፈለጉ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፩ ስያሜ "በኢትዮጵያ ግዛት የሚደረጉ ወንጀሎች፣ መደበኛ ሁኔታ" በሚል ተስተካክሏል::

የተሻረው ሕግ ቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ በስያሜው በተሰጡት ምክንያቶች ስያሜው የዚህ ይዘት ወጥነት እንዲኖረውና ከስያሜው ጋር እንዲጣጣም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል::

የዚሁ ሕግ ቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፩) የሁለተኛውን ፓራግራፍ ይዘት በተመለከተ ከስያሜው ጋር ለማጣጣም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከመደረጉም በላይ የኢትዮጵያ ግዛት በቀድሞው ሕግ ባህሩንም እንደሚጨምር የሚደነግገው፣ አገሪቱ በአሁኑ ጊዜ ባህር የሌላት በመሆኑ ነገር ግን ሌሎች ከአጎራባች አገሮች ጋር የሚያገናኙን የውሃ አካላትን በዚህ ምትክ መተካት ስለአስፈለገ "የባህሩ" የሚለው ሐረግ እንዲወጣ ተደርጎ " የውሃ አካላት" በሚል ሐረግ ተስተካክሎአል::

እንዲሁም በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ በመንግሥቱ ሕግ የተወሰነው ነው የሚለው ሀረግ የግዛቱን ስፋት በየትኛው ሕግ እንደተወሰነ ግልጽ ባለመሆኑ ይህንኑ በግልጽ ለማመልከት ሲባል "የግዛቱም ስፋት በሕገ-መንግሥቱ እንደተወሰነው ነው::" በሚል እንዲስተካከል ከተደረገ በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ሆኖ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፪ ላይ ከሰፈረው አሳብ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፪) "ከውጭ አገር በግልጽ ስለተላኩ ሰዎች በኢንተርናሲዮናል ሕግ የተደነገጉት የማይደፈሩ መብቶች የተጠበቁ ናቸው" ተብሎ የተደነገገው መብቱ ለውጭ አገር ሰዎች ብቻ እንጂ የኢትዮጵያ ዜግነት ኖሮአቸው በአለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች የማያካትት ስለሚያስመስለው የነዚህን ዜጎች መብት ለማስጠበቅ ይረዳ ዘንድ በማሰብ ይኸው ንዑስ አንቀጽ በዚህ ሕግ ውስጥ "በአለም`አቀፍ ሕግ የማይደፈሩ መብቶች ስላሉቸው ሰዎች የተደነገጉት የተጠበቁ ናቸው:: "በሚል ተስተካክሎ የሕጉ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

የነባሩ ሕግ ቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፫) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ ፍሬ-አሳቡ እንዳለ ተቀባይነት ስላገኘ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቶአል::

## አንቀጽ ፲፪ ልዩ ሁኔታ፣ውክልና መስጠት

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፲፪ ስያሜ ይዘቱን በትክክል የሚያንጸባርቅ ሆኖ በመገኘቱ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፲፪ ስያሜ ሆኖ ገብቶአል::

ሆኖም ቁጥር ፲፪/፩/ ላይ የተጠቀሰው የውጭ አገር ዜጋ ተላልፎ ሊሰጥ የማይችለው የተጠጋበት አገር ዜጋ በመሆኑ ምክንያት ስለመሆኑ ብቻ ስለሚያስመስለው ይኸው ይዘት ተለይቶ በማናቸውም አገር ውስጥ ተጠግቶ ተላልፎ ሊሰጥ ያልቻለውን የውጭ አገር ሰው ሁሉ የሚመለከት እንዲሆን በማሰብ "ይልቁንም የሸሸበት አገር የትውልድ አገሩ ሆኖ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ወንጀለኛው ተፈርዶበት ቅጣቱን ሳይፈጽም ከአገር ወጥቶ በሌላ አገር ጥገኝነት ስር ያለ ስለሚያስመስለው፣ ግለሰቡ ሳይፈረድበትም ሊያመልጥ እንደሚችል ከግምት በማስገባት በዚህ ሕግ ውስጥ "ሳይከሰስ ወይም ሳይቀጣ የቀረ እንደሆነ" በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል:: ከዚህ ሌላ ቁጥር ፲፪ ንዑስ ቁጥር (፩) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል::

ቁጥር ፲፪/፪/ን በሚመለከት በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ "ወንጀለኛው" የሚል ቃል የተጠቀመ ሲሆን ይህ ቃል የሚያመለክተው ፍርድ ቤት ቀርቦ ቅጣት የተወሰነበትን ሰው ነው:: ሆኖም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ የተመለከተው ግን ተከሶ ነፃ የወጣ እንዲሁም ተፈርዶበት ምህረት ያገኘን ሰው ስለሆነ ወንጀለኛ የሚለው ቃል ትክክል ሆኖ አልተገኘም ስለዚህ ሁሉንም የሚያጠቃልል "የውጭ አገር ዜጋው" በሚለው አባባል ተተክቷል::

በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ሥር ምህረት ብቻ ሳይሆን ይቅርታም ጭምር እንዲካተት ተደርጓል፣ ምክንያቱም ከሁለቱ ባንዱ ምክንያት ቅጣቱ ሊቀርለት ይችላልና::

የተከሳሽ ቅጣት በይርጋ ስለመቅረቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ላይ ተጠቅሷል:: ሁለት ጊዜ መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም:: አንድ ጊዜ ከተጠቀሰ ግን ቦታው ንዑስ አንቀጽ (፪) እንጂ ንዑስ አንቀጽ (፫) አይደለም፣ ምክንያቱም በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ተከሳሹ በኢትዮጵያ ሊቀጣ ስለማይችልባቸው ሁኔታዎች የደነገገ በመሆኑና አንዱ የማይቀጣበት መንገድ የቅጣት ይርጋ በመሆኑ ስለይርጋ መገለጽ ያለበት በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ነው::

www.abyssinialaw.com


ከዚህም ሌላ በቁጥር ፲፪ በንዑስ ቁጥር (፪) መጨረሻ ላይ "..... በዚሁ ወንጀል ሁለተኛ አይቀጣም...." የሚለው ሀረግ ከቅጣት በፊት ያለውን መከሰስ ሊያስቀር ስለማይችል ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፫ ጋር በማጣጣም "አይቀጣም" የሚለው ቃል መግባቱ ቀርቶ "አይከሰስም" እንዲል ተደርጓል::

በዚህ መልክ የድንጋጌው አቀራረጽ ተሻሽሎ ከተዘጋጀ በኋላ የዚሁ ሕግ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል:: የቁጥር ፲፪ ንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌን በሚመለከት የማያስፈልጉ ቃላት ከተሰረዙና አንዳንድ የቃላት ለውጥ ከተደረገ በኋላ አንቀጽ ፲፪/፫/ ሆኖ ገብቷል::

## አንቀጽ ፲፫ በኢትዮጵያ ላይ ከግዛቷ ውጭ የሚደረግ ወንጀል

የቀድሞው ህግ የቁጥር ፲፫ ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን፣ በተለይም "በውጭ አገር" በሚለው ምትክ "ከግዛቷ ውጭ" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት፣ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ ወንጀል ሊፈጸም የሚችለው የውጭ አገር መንግሥት በሚያስተዳድረው የግዛት ክልል ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ በሆነ የባህር ወይም የውቅያኖስ ክልል ጭምር ሊፈጸም ስለሚችል፣ ሁለቱንም ሁኔታዎች እንዲያካትት ታስቦ ስያሜው ከላይ በተጻፈው ዓይነት ተስተካክሏል::

ይዘቱን በተመለከተ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን፣ በተለይም "ንጉሠ ነገሥት" እና "ነጋሲ" የሚሉት ቃላት፣ አሁን ኢትዮጵያ ከምትከተለው የፖለቲካ ሥርዓት ጋር የሚጣጣሙ ባለመሆኑ ተሰርዘዋል:: በምትካቸውም "ርዕሰ ብሔር" የሚለው ቃል ያልገባ ሲሆን፣ ይህ የሆነበት ምክንያት በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፹፬/፩/ሠ በአጠቃላይ ለባለሥልጣኖች የተሰጠው ጥበቃ በቂ ስለሆነ ለርዕሰ-ብሔር የተለየ የሕግ ጥበቃ እዚህ ማስቀመጡ አስፈላጊ ባለመሆኑ ነው::

## አንቀጽ ፲፬ የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ በውጭ አገር ሆኖ የሚያደርጋቸው ወንጀሎች

በነባሩ ሕግ ቁጥር ፲፬ ንዑስ ቁጥር (፩) "በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ መንግሥት የዲፕሎማቲክና የቆንሲል አባሎች የሆኑ የመንግሥት መልዕክተኞችና ወኪሎች" በሚለው ሀረግ "የሆኑ" የሚለው ቃል የመንግሥት ወኪሎችና መልዕክተኞች ሁሉ ዲፕሎማቲክና የቆንሲል አባሎች ብቻ እንደሆኑ በማስመሰል ለአጭር ጊዜ ተልዕኮ የሚላኩትን ስለማይጨምር "የሆኑ" የሚለው ቃል ተሰርዞ አንዳንድ የቃላትና የስርዓተ ነጥብ ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፬/፩/ ሆኖአል::

ንዑስ አንቀጽ (፩) "ሊፈረድባቸው" የሚለው ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ድንጋጌ ላይ ተካትቷል:: ይህ ትክክል ባለመሆኑ "ሊከሰስ የማይችል እንደሆነ" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: ምክንያቱም ጉዳዩ እንዲታይ ይደረግ እንጂ ተከሣሽ የሚፈረድበት ወይም በነፃ የሚለቀቅ መሆኑ የሚታወቀው ክሱ ከተሰማ በኋላ ነው:: ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ "እንዲፈረድበት" ማለቱ ስሕተት ነው::

በዚህ ቁጥር በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተነገሩት ነጥቦች ልዩነት የሌላቸው በመሆኑ የፊደል (ሀ) እና (ለ) አከፋፈል ተሰርዞ በአንድነት ተካትተዋል:: በቀድሞው ህግ በፊደል (ሀ)

መጨረሻ የሚገኘው፣ "ስለሆነም" በሚለው ቃል የሚጀምረው ዓረፍተ-ነገር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ ቁጥር (፪) ይዘት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል::

## ቀጽ ፲፭ የኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ሠራዊት አባል በውጭ አገር ሆኖ የሚያደገርው ወንጀል

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር አስራ አምስት ስያሜ ከወቅቱ ጋር የማይጣጣሙ ቃላት ተሰርዘውና የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፲፭ ስያሜ ሆኖ ገብቶአል::

በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፲፭ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "የወል ሕግ" የሚለው ሀረግ "Ordinary law" የሚለውን የእንግሊዝኛ ሀረግ የሚወክል ሲሆን፣ ሆኖም "የወል ሕግ" የሚለው ሀረግ "International law" የሚለውን የእንግሊዘኛ ሀረግ የሚተካ ስለሚያስመስለው በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ "መደበኛ ሕግ" በሚል ሀረግ ተለውጧል::

በዚሁ በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፲፭ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "እጁም ተላልፎ ያልተሰጠ እንደሆነ" የሚለው ሀረግ ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ሰው ምንግዜም ቢሆን እጁ ተላልፎ እንዲሰጥ የሕገሪቱ ሕግ ስለማይፈቅድ ነው:: በዚሁ ፓራግራፍ ላይ የሚገኘው "በዚሁ ሕግ መሠረት" የሚለው ሀረግ በመጀመሪያው ፓራግራፍ "... በዚያው አገር ሕግና..." ከሚለው ሀረግ ጋር ሲነበብ የውጭ አገር ሕግን የሚያስመስል መልዕክት ስለሚያስተላልፍ "በዚሁ ሕግ መሠረት ይፈረድበታል ቁጥር ፳፩(፪)::" የሚለው ሀረግ ወጥቶ "በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፳፩(፪) መሠረት ይከሳሳል" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፭ ንዑስ ቁጥር (፪) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና ለአመቺነቱ ሲባል የአጣቃሽ አንቀጾች አቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቶአል::

## ቀጽ ፲፮ በውጭ አገር የተሰጡ ፍርዶች ውጤት

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፮ ስያሜ "በውጭ አገር ስለተሰጠ ፍርድ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር ለማጣጣምና ይዘቱም ይበልጥ ገላጭ እንዲሆን በማሰብ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፮ ስያሜ "በውጭ አገር የተሰጡ ፍርዶች ውጤት " ተብሏል::

በነባሩ ሕግ ቁጥር ፲፮ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ " ተላልፎ ካልተሰጠ" የሚል ሀረግ ይገኝበታል:: ነገር ግን ተከሳሹ ተላልፎ ካልተሰጠና እዚህም ካልተገኘ ተከሰ እንዲፈረድበት ማድረግ አጥጋቢ ውጤት አያመጣም:: ስለዚህም በእንግሊዘኛው ቅጂ እንደተመለከተው ለኢትዮጵያ ተላልፎ ከተሰጠ የሚለው አገላለጽ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ-አንቀጽ (፩) "ተላልፎ ካልተሰጠ" የሚለው ወጥቶ "በኢትዮጵያ ከተገኘ ወይም ተላልፎ ከተሰጠ" በሚል ሐረግ ተተክቷል:: በተጨማሪም በዚሁ ንዑስ

www.abyssinialaw.com



ቁጥር ከተጠቀሱት ቁጥሮች ውስጥ "፲፬/ሀ" የሚለው ፲፬/፩/ ማለቱ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ በዚህ አኳኋን ተስተካክሏል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፮ ንዑስ ቁጥር (፪) አገላለጹ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፲፮ ንዑስ ቁጥር (፫) አነስተኛ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>ምትክ አፈጻጸም</u>

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ክፍሉ ስያሜ "ተከታይ አፈጻጸም" የሚል ሲሆን "ምትክ አፈጻጸም" በሚል ሀረግ ተተክቷል፤ ምክንያቱም "Subsidiary Application" ለሚለው የእንግሊዘኛ ሀረግ የኋለኛው የአማርኛ ሀረግ በይበልጥ ተስማሚ በመሆኑ ነው::

አንቀጽ ፲፯ <u>በዓለም አቀፍ ሕግና ሥርዓት ላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ወንጀሎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፯ ስያሜ "በማህበራዊ መብት ላይ ወይም በመላው አለም ፀጥታ ላይ..." የሚል ሀረግ ይገኝበታል:: ይህ ሀረግ ግልጽነት የሚጎለው በመሆኑና ከእንግሊዝኛው ቅጂም ጋር የማይጣጣም ስለሆነ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "በዓለም አቀፍ ሕግና ስርዓት ላይ" በሚል ተስተካክሏል:: "በውጭ አገር" የሚለውም "ከኢትዮጵያ ውጭ" እንዲል ተደርጓል፤ ምክንያቱም ከማንኛውም መንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆነን ባህር ወይም ውቅያኖስ ጭምር እንዲያካትት ነው::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፲፯ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ማንም ሰው" ከሚለው ሀረግ በኋላ ጉዳዩን ይዘረዝር ነበር:: ይሁን እንጂ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ሲባል በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ማንም ሰው ከሚለው ቀጥሎ "በውጭ አገር ሆኖ" የሚል ሀረግ እንዲጨመርበት ከተደረገና አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፲፯ ንዑስ ቁጥር (፪) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

አንቀጽ ፲፰ <u>ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ሌሎች ወንጀሎች</u>

በቀድሞው ህግ ድንጋጌ ስያሜ ላይ "በውጭ አገር" ይል የነበረው ተሻሽሎ "ከኢትዮጵያ ውጭ" ተደርጓል ይህም የሆነው፣ ከማንኛውም መንግሥት ቁጥጥር ውጭ በሆነ ባሕር ወይም ውቅያኖስ የሚፈጸምን ወንጀል እንዲያጠቃልል ነው::

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፲፰ ንዑስ ቁጥር (፩) በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የሚፈጸመውን ወንጀል አድራጊው የት ሆኖ እንደሚፈጽመው በግልጽ የሚያመለክት አልነበረም:: ስለዚህም ይህንኑ ግልጽ ለማድረግ ሲባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ላይ "ማንም ሰው" ከሚለው ቀጥሎ "በውጭ አገር" የሚል ሀረግ ተጨምሮአል:: እንዲሁም ይኸው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፰ ንዑስ ቁጥር (፩) መንደርደሪያ "ሳይቀጣ በመቅረቱ" የሚል ሀረግ

www.abyssinialaw.com



ነበረው:: ነገር ግን የዚህ የወንጀል ሕግ ዓላማ ሁልጊዜ ለመቅጣት ሳይሆን ተገቢ በሆነ የፍርድ ሂደት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በመሆኑና የእንግሊዝኛውም ቅጂ ቢሆን "ሳይቀጣ" ሳይሆን የሚለው "ሳይከሰስ" የሚል በመሆኑ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ "ሳይቀጣ በመቅረቱ" የሚለው ተሰርዞ "ሳይከሰስ ከቀረ" በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል::

በተጨማሪም በንዑስ ቁጥር (፩) በ(ሀ)ና በ(ለ) የተመለከቱት ፍሬ ሃሳቦች እንዳለ ተቀባይነትን ካገኙ በኋላ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎባቸው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) እና (ለ) ሆነው ገብተዋል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፲፰ ንዑስ ቁጥር (፪) የተቀመጠው ፍሬ ነገር ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

ቀጽ ፲፱ <u>ይህ ሕግ በምትክነት የሚፈፀምበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፱ ስያሜ "ይህ ሕግ በሌላ አገር ሕግ ፈንታ ስለሚፈጸምበት ሁኔታ" የሚል ሲሆን "Conditions for subsidiary application" ከሚለው ከእንግሊዝኛ ስያሜ ጋር በማጣጣም በዚህ ድንጋጌ ላይ "ይህ ሕግ በምትክነት የሚፈጸምበት ሁኔታ" ተብሎ እንዲሻሻል ተደርጓል::

በቁጥር ፲፱/፩/ ላይ ከአሁኑ የፖለቲካ ሥርዓት ጋር የማይጣጣሙ ቃላት ተሰርዘውና አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) የገባ ሲሆን፣ "በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፲፯ እና በአንቀጽ ፲፰ (፪) የተደነገጉትን የወንጀል ዓይነቶች በሚመለከት፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል "ሀ" እና "ሐ" የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የግዴታ መሟላት አይኖርባቸውም::" በማለት ይደነግጋል::

ይህ ንዑስ አንቀጽ እንዲገባ ያስፈለገበት ምክንያት፣ ከየትኛውም የውጭ አገር መንግሥት ቁጥጥር ውጭ በሚገኝ ዓለም አቀፍ ባህር ወይም ውቅያኖስ ላይ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፲፯ እና ፲፰ የተመለከቱት ወንጀሎች በሚፈጽሙበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) ላይ እንደተገለጸው፣ ወንጀሎቹ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጡ መሆን አለመሆናቸው ሊነሳ አይችልም:: በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) እንደተመለከተውም በውጭ አገር ህግ መሠረት ወንጀሎቹ በይቅርታ የታለፉ ወይም ክሶቹ በይርጋ የታገዱ መሆን አለመሆናቸው ሊታይ አይችልም፤ ተፈጻሚ የሚሆን የውጭ አገር ህግ የለምና::

ከዚህም ሌላ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፲፯(፩)(ሀ) የተመለከቱት ወንጀሎች በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፳፰ መሠረት የክስ ይርጋ የሌላቸውና ይቅርታም ሆነ ምህረት የማይደረግላቸው በመሆኑ፣ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፲፰(፩) (ሐ) እንደተመለከተው በውጭ አገር ህግ መሠረት ክሶቹ በይርጋ የታገዱ ወይም በይቅርታም ሆነ በምህረት የታለፉ ስለመሆናቸው የሚነሳ ጥያቄ አይኖርም:: ይህም፣ የሆነው፣ የማንኛውም አገር መንግሥት በተጠቀሱት ወንጀሎች ረገድ ክሳቸውን በይርጋ የሚያስቀር ህግ ሊያወጣም ሆነ ይቅርታ ወይም ምህረት ሊያደርግባቸው አይችልም፤ ይቅርታ ወይም ምህረት ቢያደርግም ወይም ክሳቸው በይርጋ የሚታገድበት ህግ ቢያወጣም ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም::

ስለዚህ የዚህ ህግ የአንቀጽ ፲፱ (፩) (ሀ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የማይሆኑባቸው ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ፣ ይህንን የሚመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሊገባ ችሏል:: በተለይም በዓለም አቀፍ ባሕር ወይም ውቅያኖስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ የሚሸፍናቸው የውጭ አገር ህግ ስለሌለ ጉዳያቸው የሚታየው በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ብቻ ነው ማለት ነው::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) በመግባቱ፣ የቀድሞው የቁጥር ፲፱ (፪) ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖአል:: በዚሁ በቀድሞው ቁጥር ፲፱ (፪) ላይ "ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የክስ ጥያቄ የሚያቀርበው በጉዳዩ ከፍርድ ሚኒስትር ጋራ ከተስማማበት በኋላ ነው" የሚል ሲሆን "ዓቃቤ ሕግ ክሱን ከማቅረቡ በፊት የፍትህ ሚኒስትሩን ማማከር ይኖርበታል" ተብሎ ተሻሽሎአል:: ይህ የሆነበት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣን ከፍትህ ሚኒስትሩ ሥልጣን ጋር የተዋሃደ በመሆኑ ክስ ማቅረብ ተግባሩ የሆነው ዓቃቤ ሕግ በዚህ ዓይነቱ ተግባር ላይ ክስ ከማቅረቡ በፊት ከፍትህ ሚኒስትሩ መመሪያ እንዲጠይቅ ግዴታ መጣሉ አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

ቁጥር ፲፱ (፫) ተሸጋሽጎ አንቀጽ ፲፱ (፬) የተደረገ ሲሆን በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) ሥር የውጭ አገር ሲባል በኢትዮጵያ የታወቀ አገር መሆኑን ስለሚያመለክት "መንግሥትነቱ በታወቀበት አገር" የሚለው አነጋገር አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዟል::

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) አነጋገሩ ተሻሽሎ ከሁለቱ አገር ሕግ ተከሳሹን የሚጠቅመው ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጐ ተረቅቋል:: ከዚህ በተጨማሪ በአንቀጹ ላይ አስፈላጊ የሆነ የቃላት ለውጥ ተደርጓል::

አንቀጽ ፳ <u>በውጭ አገር የተሰጠ የፍርድ ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳ ስያሜ "በውጭ አገር ስለተሰጠ ፍርድ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ ይዘቱ የሚገልጸው ስለፍርዱ ሳይሆን በውጭ አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ስለሚኖረው ውጤት ነው:: ስለዚህም ከላይ በተገለጸው ምክንያትና ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በማጣጣም የዚህ አንቀጽ ስያሜ "በውጭ አገር የተሰጠ የፍርድ ውጤት" በሚል ተስተካክሏል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፳ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ፈንታ" የሚል ቃል ይገኝበታል:: ይህ ቃል ከላይ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው በ "ምትክ" እንዲተካ ከመደረጉም በላይ በቀድሞው ሕግ ተመሳሳይ ቁጥር እና ንዑስ ቁጥር ላይ "አድራጊው" በማለት የተጻፈውን ግልጽ ለማድረግ ሲባል ከዚህ ቃል ፊት "ወንጀል" የሚል እንዲጨመር ተደርጎ ከተስተካከለ በኋላ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል::

ንዑስ ቁጥር (፪) የቃላትና የማጣቀሻ አንቀጾች አቀማመጥ ማስተካከያ ተደርጎበት ግልጽ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ ፍሬ ሐሳቡ እንዳለ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com


ንዑስ ክፍል ሦስት
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

ንቀጽ ፳፩ አሳልፎ መስጠት

በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፳፩ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "በወል ሕግ መብት" ላይ የሚል ሀረግ ይገኝበታል:: ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸው "የወል ሕግ" የሚለው ሀረግ "መደበኛ የወንጀል ሕግ" በሚል ሐረግ እንዲተካ ተደርጎ እንዲሁም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) በመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ላይ "ጥፋት በተደረገ ጊዜ" የሚል ሀረግ የነበረው ይሁን እንጂ ሀረጉ የዜጎች መብት በእኩልነት እንዳይጠበቅ የሚያደርግ ክፍተትን ስለሚፈጥርና ከጥፋት በፊትም ሆነ ከጥፋት በኋላ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ሰው በእኩል እንዲታይ ማድረጉ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት ጥፋት በተደረገ ጊዜ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዜጋ የነበረውን" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ወንጀሉ በተደረገ ጊዜም ሆነ ወይም የአድራጊው እጅ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚያሳስብ ጥያቄ በቀረበበት ጊዜ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነውን" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: በተጨማሪም የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፳፩ ንዑስ ቁጥር (፫) የተገለጸው ፍሬ አሳብ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

ንቀጽ ፳፪ ለውጭ አገር ፍርዶች እውቅና መስጠት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፪ ስያሜ "የውጭ አገርን ፍርዶች ስለማወቅ" ይል ነበር:: ሆኖም ሐረጉ የተፈለገውን አሳብ በግልጽ የማያስተላልፍ እና፣ "Recognition of Foreign Sentences" የሚለውን የእንግሊዝኛ ሀረግ ትክክለኛ ትርጉም ያልያዘ በመሆኑ፣ "ለውጭ አገር ፍርዶች እውቅና መስጠት" በሚል ተስተካክሏል::

የንዑስ ቁጥር (፩) የእንግሊዝኛው አተረጓጎም ትክክል አለመሆኑ ስለታመነበት በእንግሊዝኛው እና በፈረንሳይኛው ቅጂ መሠረት አገላለጹ ተሻሽሎ ተረቅቋል:: ዝርዝር ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው::

"antecedents" የሚለውን ቃል "ቀድመው ስለተሰጡ ውሳኔዎች" ብሎ ከመተርጎም ይልቅ "የተከሳሹን ያለፈ የሕይወት ታሪክ" የሚለው ትርጉም የተሻለ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል:: "aggravating circumstances" የሚለውም "ቅጣትን ስለሚያከብዱ ፍርዶች" በሚል መተርጎሙ ቀርቶ "ቅጣት የሚያከብዱ ምክንያቶች" እንዲል ተደርጓል:: "ስለ ፀጥታ አጠባበቅ የማረጋገጫ ደንብ" ከሚለው ሀረግ ይልቅ "የደህንነት ማረጋገጫ እርምጃዎች" የሚለው፣ "the enforcement of safety measures" ተብሎ የተጻፈውን የእንግሊዝኛ ሀረግ በተሻለ ሁኔታ የሚገልጸው በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል:: "የፍትሐብሔር ጉዳይ ነክነት ስላላቸው ነገሮችና የተወሰዱ ዕቃዎች ስለመመለስ" የሚለው አገላለጽ፣ የተወሰደን ንብረት መመለስ ከፍትሐብሔር ነክነት ጉዳዮች ውስጥ እንደሆነ ያስቆጥራል:: ሆኖም የተወሰደን ንብረት መመለስ ከፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ ግልጽ ነው:: በመሆኑም "የተወሰዱ ዕቃዎችን መመለስን እና ሌሎች

www.abyssinialaw.com



የፍትሐብሔር ነክነት ያላቸውን ነገሮች" ተብሎ በእንግሊዘኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል። በመጨረሻም "በዚህ ሕግ ላይ" በሚለው ሀረግ ውስጥ "ፍትሐውያን የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው ቅጂ ላይ የሌለ በመሆኑና አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል።

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፤ የማያስፈልጉ ሀረጎችም ተሰርዘዋል።

## ርዕስ ሁለት
## ወንጀልና አፈፃፀሙ
### ምዕራፍ አንድ
### የወንጀል ድርጊት

**አንቀጽ ፳፫ የሚያስቀጣ ወንጀል**

የአንቀጹ ስያሜ "የሚያስቀጡ ወንጀሎች" የሚል ሲሆን ከዚህ ሀረግ ይልቅ "የሚያስቀጣ ወንጀል" የሚለው ይመረጣል፣ ምክንያቱም ቃሉ በየንዑስ አንቀጹ ላይ በነጠላ ቁጥር እንጂ በብዙ ቁጥር ያልተገለፀ በመሆኑ ነው።

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፳፫ (፩) ድንጋጌ፣ "ያስቀጣል ተብሎ በሕግ የተደነገገውን መሥራት ወይም እንዲሠራ የታዘዘውን አለመስራት የከባድነቱ ደረጃ ማናቸውም ዓይነት ቢሆን ወንጀል ነው።" የሚል ሲሆን በዚህ ሕግ ላይ፣ "ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገውን ድርጊት መፈፀም ወንጀል ነው።" ተብሎ አገላለፁ ተሻሻሎ እንዲገባ ተደርጓል። ቀጥሎም፣ "በዚህ ሕግ ውስጥ ድርጊት ማለት በሕግ የተከለከለውን ማድረግን ወይም የታዘዘውን አለማድረግ ነው።" የሚል አነጋገር ታክሎበታል። ንዑስ አንቀፁ በዚህ መልክ መቀረፁ የሕጉን አሳብ በይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል። "የተከለከለውን ማድረግ ወይም የታዘዘውን አለማድረግ" የሚለውን ሐረግ በየቦታው ከማስገባት ይልቅ "ድርጊት" በሚለው ቃል ብቻ መጠቀሙ ይመረጣል።

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፫ ንዑስ ቁጥር (፪) አነጋገር ግልጽነት የሌለው በመሆኑ፣ "አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው።" ተብሎ እንደ እንግሊዘኛው ቅጂ አጠር ባለና ግልጽ በሆነ መልኩ ተቀምጦ የተሻለ አገላለጽ እዲኖረው ተደርጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) የተፃፈው ድንጋጌ ቢኖርም የአእምሮ አስተሣሰብ የሌለው ወይም ግዑዝ የሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን መቻሉን የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ገብቷል።

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፳፫/፫/ አገላለጽ ተሻሽሎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል።

**አንቀጽ ፳፬ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት**

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜና ይዘት ላይ የአገላለጽና የቃላት ለውጦች ከመደረጉም በተጨማሪ አንዳንድ የአሳብ ለውጥ እንደሚከተለው ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

በአንቀጽ ፳፬ ላይ "አድራጊ" ከሚለው ቃል ይልቅ "ተከሣሽ" በሚለው መጠቀሙ ይመረጣል:: አንቀጽ ፳፬ መሠረት አድርጐ ሊይዝ የሚገባው አንድን ውጤት ያስከተለውን ማንኛውንም አድራጊ ሳይሆን ወደ ሕግ ፊት ቀርቦ ተጠያቂ የሚሆነውን ሰው ነው:: በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት አለ ወይም የለም ብሎ መመርመሩ አስፈላጊ የሚሆነው፣ የተከሰሰ ሰው ሲኖር ነው:: የዚህ ዓይነቱም ሰው ግልጽና ትክክለኛ መጠሪያው ተከሳሽ እንጂ አድራጊ የሚለው አይደለም፣ አድራጊ የሚለው ቃል ያልተያዘውንም ሆነ ያልተደረሰበትን ወንጀል አድራጊ ያካትታልና::

የዓለም ኑሮ እጅግ ውስብስብ በሆነበት በአሁኑ ዘመን ምክንያቶች ከሚያጋጥሙበት ጊዜ አንፃር የተደራረቡና ጣልቃ ገብ ምክንያቶች በማለት በሁለት ክፍል ብቻ መድቦ ማየቱ ትክክል ሆኖ አይታይም:: የመጀመሪያው ምክንያት የተከሳሹ ድርጊት ላይሆን ይችላል:: ከእርሱ ድርጊት በኋላ ውጤትን ማስከተል የሚችል ጣልቃ ገብ ምክንያት ሊኖር የመቻሉን ያህል ከእርሱ ድርጊት አስቀድሞ የደረሰ የሌላ ሰው ድርጊት ወይም ሌላ ምክንያት ሊያጋጥም ይችላል:: በሕግ ረገድም ምክንያቶችን ከጊዜ አንፃር በሦስት ደረጃ ከፍለው የሚያዩ የወንጀል ሕጐች አሉ:: ለምሣሌ የ፲፱፻፴ዓ.ም የኢጣሊያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ ፵፩ ምክንያቶች "pre-existing"፣ "simultaneous" እና "supervening" ሊሆኑ እንደሚችሉ ይደነግጋል:: የልዩ ልዩ ሰዎች ድርጊትም በሦስቱ የጊዜ ደረጃ ሊከሰት እንደሚችል ይኸው የኢጣሊያ የወንጀል ሕግ ያሳያል፤ /የሕጉ ይዘት ግን ከዚህ አንቀጽ መደምደሚያ አሳብ የተለየ ነው::/

በዚህ መሠረት አንቀጽ ፳፬ (፪) አስቀድሞ የደረሰ ምክንያትን እንዲያጠቃልል ተደርጐ ተረቅቋል:: ለተከሳሹ እንግዳ ከሆኑት፣ በሦስቱ የጊዜ ደረጃ ከደረሱት ልዩ ልዩ ምክንያቶች አንዱ ራሱን ችሎ፣ ማለት የተከሳሹ ድርጊት ምንም እገዛ ሣያደርግለት፣ አንድን ወጤት ማስከተሉ ከተረጋገጠ በተከሳሹ ድርጊትና በውጤቱ መካከል ሊኖር ይችል የነበረው ግንኙነት ይቋረጣል ማለት ነው:: ይህንን በሚያሳይ መልክ የንዑስ አንቀጽ (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሻሽሏል::

ልዩ ልዩ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው አንድን ውጤት ማምጣት ባይችሉም ተጣምረው አንድ ውጤት ካስገኙ ሁሉም ለውጤቱ ምክንያቶች ናቸው ብሎ መደንገጉ ትክክል መሆኑ ይታመንበታል:: ይህም በፍትሐብሔር ተጠያቂ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ጋር አንድ አይነት ነው ተብሎ ይታመናል:: በመሆኑም አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) በዚህ መልክ ተቀርጾ ገብቷል::

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ነጥብ የተከሳሹ ድርጊት በተደራቢነት ለውጤቱ አስተዋጽኦ ማድረጉ ብቻ በወንጀል ተጠያቂ የማያደርገው መሆኑ ነው:: ተከሳሽ በወንጀል የሚጠየቀው ሞራላዊ ፍሬ ነገር ጭምር ሲሟላ ነው፤ ማለት ድርጊቱን አስቦ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው::

## ቀጽ ፳፭ ወንጀል የተደረገበት ጊዜና ቦታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፭ ሥያሜ "ሕግ መጣስ ስለተደረገበት ሥፍራና ጊዜ" የሚል ሲሆን አገላለፁ ተሻሽሎ "ወንጀል የተደረገበት ጊዜና ቦታ" እንዲል ተደርጓል::

ንዑስ ቁጥር (፩) እና ንዑስ ቁጥር (፪) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ንዑስ አንቀጽ (፩) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆነው ገብተዋል::

www.abyssinialaw.com



ይህ አንቀጽ ወንጀል ስለሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ በሁለት ከፍሎ ይደነግጋል:: ንዑስ አንቀጽ (፩) በአንድ ጊዜና በአንድ ሥፍራ ስለሚደረግ ወንጀል የሚደነግግ ሲሆን፣ ንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ በአንድ ጊዜና ቦታ የማይፈፀሙ ወንጀሎችን /non-instantaneous offence/ ይመለከታል፣ ይህም ድርጊቱና ውጤቱ በአንድ ጊዜና በአንድ ቦታ ስለማይገኝበት የወንጀል አይነት ነው:: ሆኖም በአንድ ጊዜና ቦታ የማይፈፀሙ ሌሎች የወንጀል ዓይነቶችም አሉ:: በአንቀጽ ፳፭ ላይ በተለያየ ጊዜና ቦታ ተፈጽመው እንደአንድ ነጠላ ወንጀል ስለሚቆጠሩ ወንጀሎች ተደንግጎ ይገኛል:: እነዚህም ወንጀሎች የተቀሳቀሱ /አንቀጽ ፳፭ (፩) ወይም ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ ወይም ተራዝመው የቆዩ አንቀጽ ፳፭ (፪) ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ የወንጀል ድርጊቶች በየበኩላቸው እንደ አንድ ነጠላ ወንጀል የሚቆጠሩ ተደጋጋሚ ወይም ተከታታይ ድርጊቶችን ያጠቃልላሉ:: በዚህ መሠረት አንድን ነጠላ ወንጀል ከሚያቋቁሙት ድርጊቶች አንዱ ወይም ከፊሉ የተደረገበት ቦታና ጊዜ፣ ወንጀሉ እንደተደረገበት ቦታና ጊዜ የሚቆጠር መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>የወንጀል አፈፃጸም ደረጃ</u>

አንቀጽ ፳፮ <u>የማሰናዳት ተግባሮች</u>

አንቀጹን ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊው የቃላት ለውጥ ተደርጎበት ተረቅቋል::

አንቀጽ ፳፯ <u>ሙከራ</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፳፯ ንዑስ ቁጥር (፩) እና ንዑስ ቁጥር (፪) ይዘት እንዳለ ተቀባይነትን አግኝቶ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ ቅደም ተከተላቸውን እንደጠበቀ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆነው እንዲገቡ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፫) መንደርደሪያ ላይ "በዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚል ሀረግ እንዲጨመርበት ተደርጓል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት ዳኞች በሙከራ የወንጀል ድርጊት የሞት ውሳኔ እንዳይወስኑ ለማስታወስ በማሰብ ነው:: በተጨማሪም ንዑስ ቁጥሩ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና ለአመቺነቱም ሲባል የአጣቃሽ አንቀጽ የአቀማመጥ ለውጥ በማድረግ የቀድሞ ሕግ ቁጥር ፳፯ ንዑስ ቁጥር (፫) ተስተካክሎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

አንቀጽ ፳፰ <u>መተውና መፀፀት</u>

በተሻረው ሕግ የቁጥር ፳፰ ስያሜ "ስለመተውና ስለመፀፀት ተግባር" የሚል ነበር:: ነገር ግን በዚህ ሕግ ውስጥ የአንቀጽ ፳፰ ስያሜ የእንግሊዝኛውን ቅጂ ተከትሎ "መተውና መፀፀት" የሚል ሆኗል::

በዚህ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ሰው አንድን ወንጀል ሞክሮ በራሱ ፈቃድ ሲተው በቅጣት አወሳሰን ረገድ ሶስት ልዩ ልዩ ሁኔታዎች አሉ፤ ይኸውም፣ አድራጊው ወንጀሉን የተወበት ምክንያት እየታየ ቅጣቱ በመጠኑ ወይም እጅግ በጣም ሊቃለልለት ከመቻሉም በላይ፣ የተወው በሀቀኝነት ሲሆን በነፃ ይሰቀቃል:: በቀድሞው የአማርኛ ቅጂ ግን ቅጣቱ በመጠኑ የሚቃለልበት ድንጋጌ (ቀጥር ፻፹፬) ብቻ የተጠቀሰ

www.abyssinialaw.com

ሲሆን የተጠቀሰውም "..... ነፃ ያደርገዋል" ከሚለው ዓረፍተ-ነገር መጨረሻ ላይ ነው:: የቁጥር ፻፹፩ ድንጋጌ በመጠኑ ቅጣት ማቅለያ እንጂ ነፃ ማድረጊያ ስላልሆነ አጠቃቀሱ ስህተት ነው::

ይሁን እንጂ በራሱ አነሳሽነት የወንጀል ድርጊትን ለተወ ሰው በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ እንደተመለከተው እንደነገሩ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በሕግ በተፈቀደው መሠረት፣ ማለት በመጠኑ (ቁጥር ፻፹፩) ወይም በመሰለው ማለት እጅግ በጣም (ቁጥር ፻፹፭) ቅጣቱን ሊያቃልል እንደሚችል መደንገጉ አግባብነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል:: በመሆኑም በዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ላይ ቁጥር ፻፹፩ (በአሁኑ አንቀጽ ፻፸፱) እና ቁጥር ፻፹፭ (በአሁኑ አንቀጽ ፻፹) በአማራጭነት እንዲገቡ ተደርጓል:: በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አንቀጾች መሠረት ቅጣት ለማቅለል የሚያስችሉ ተገቢ ምክንያቶች ከተገኙ ፍርድ ቤት ቅጣቱን እንደፈለገው ሊያቃልልም ሆነ ላያቃልል በሚችል መልኩ መደንገጉ ትክክል ባለመሆኑ ቅጣቱ ማቃለሉ አስገዳጅ መሆኑን አንቀጹ እንዲደነገግ ተደርጎ ተቀርጿል::

በተሻረው ሕግ በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ውጤቱ "እንዳይደርስ እርዳታ የሰጠ" ከሚለው አነጋገር ይልቅ "ውጤቱ እንዳይደርስ ያደረገው አስተዋጽኦ መልካም ፍሬ ያስገኘ እንደሆነ" በሚል ተተክቷል:: ይህም የሆነበት ምክንያት "እርዳታ" የሰጠው የሚለው አነጋገር እርዳታ መስጠቱን እንጂ በዚሁ በሰጠው እርዳታ መነሻ ድርጊቱ ሊያስከትል ይችል የነበረው ውጤት መቅረቱን በግልጽ ስለማያሳይ ነው በመሠረቱ ግን የሰጠው እርዳታ ፍሬ ካላስገኘ በአንቀጽ ፻፹ መሠረት ቅጣቱ አይቃለልለትም:: በዚህ ምክንያት እንዲስተካከል ተደርጓል::

የተሻረው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) እና (፫) ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆኖ ገብቷል::

ቀጽ ፳፱ <u>ሊፈፀም የማይቻል ወንጀል</u>

በመጀመሪያው ፓራግራፍ በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ ያለው "or" የሚለው ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የሌለ በመሆኑና በግልጽ መኖሩ አስፈላጊ በመሆኑ "ወይም" የሚል ቃል እንዲጨመር ተደርጓል::

ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "...ጉዳት ለማድረስና የወንጀል ውጤት ለመስጠት በማይችል ..." ይላል:: ሆኖም "ጉዳት ለማድረስ በማይችል" የሚለው አነጋገር በቂ ስለሆነ "የወንጀል ውጤት ለመስጠት በማይችል" የሚለው ሀረግ ተሰርዟል::

የተሻረው ሕግ ቁጥር ፳፱፣ ሊፈፀም ለማይቻል ወንጀል አድራጊ የተደነገገውን ቅጣት በተመሳሳይ ሁኔታ የዚሁ ዓይነት ወንጀል እንዲፈፀም ላነሣሣና ለተባበረ ሰውም ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት በማመን በቀድሞው ሕግ ይዘት ከመጨረሻው ፓራግራፍ ቀጥሎ".....በወንጀል አነሳሽ ወይም አባሪ ላይ በተመሣሣይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል" የሚል አዲስ ሦስተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል:: በዚህ መልክ ተሻሽሎ አንቀጽ ፳፱ ሆኗል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፴ ከሙከራ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፴ ስያሜ "የተለየ የወንጀል ሙከራ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ ስያሜውና ይዘቱ የተጣጣሙ ባለመሆናቸው ይልቁንም ይዘቱ የተለየ ሙከራን የሚያሣይ ሣይሆን የወንጀል ሙከራው በውስጡ ራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል አጠቃልሎ በሚይዝበት ወይም በሚያካትትበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ በግልጽ ለማመልከት በመሆኑ ከላይ የተመለከተው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴ ስያሜ ተለውጠ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "ከሙከራ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች " እንዲል ተደርጓል:: በይዘቱም ረገድ በቀድሞው ሕግ የተደነገገው የቁጥር ፴ ፍሬ ሃሣብ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴ የተሻለ አገላለጽ ተደርጐበታል::

አንቀጽ ፴፩ የዳኛ አስተያየት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፩ ስያሜ "የዳኛ ግምት" የሚል ነበር:: ነገር ግን ይዘቱ የሚገልፀው ፍሬ ሃሣብ የዳኛን አስተያየት የሚመለከት በመሆኑ ከላይ የተመለከተው የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፴፩ ስያሜ ተለውጠ "የዳኛ አስተያየት" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

ይዘቱ እንዳለ ተቀባይነትን አግኝቶ አንዳንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ አንቀጽ ፴፩ እንዲሆን ተደርጓል::

ምዕራፍ ሶስት
በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ መሆን

አንቀጽ ፴፪ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ መሆን

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፴፪ ስያሜ "ስለዋና ወንጀል አድራጊውና ስለ ግብረ አበሮቹ" የሚል ሲሆን አሁን ግን የአንቀጽ ፴፪ ስያሜ "በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ መሆን" ብቻ እንዲል ተደርጓል:: ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት "ስለዋና ወንጀል አድራጊውና ስለ ግብረ አበሮቹ" የሚለው የቁጥር ስያሜ ስህተት በመሆኑ ነው:: የቀድሞው ሕግ ድንጋጌ ስያሜ፣ አንድ ቀንደኛ ወንጀል አድራጊ እንዳለና ሌሎቹ ግን ከርሱ ያነሰ ሚና ያላቸው ረዳቶች እንደሆኑ ያሳያል:: ሆኖም የንዑስ ቁጥር አንድ መግቢያ እንደሚያስረዳው በፊደል (ሀ) (ለ) እና (ሐ) የተዘረዘሩት ወንጀል አድራጊዎች ሁሉ እንደ ዋና ወንጀል አድራጊ እንጂ አንዱን እንደ ኡብይ ወንጀለኛ፣ ሌሎቹን ግን እንደ አነስተኛ ወንጀለኞች የሚቆጥር አይደለም::

ከዚህም ሌላ ሁሉም ዋና ወንጀል አድራጊዎች በወንጀሉ አፈፃፀም ላይ በግብር ወይም በድርጊት ሳይሳተፉ ይችላሉ:: አንዳንዶቹ በቀጥታ በድርጊት ተካፋይ ቢሆኑም ሌሎቹ አሳብ ወይም መመሪያ በመስጠት ብቻ የወንጀሉ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ግብረ አበሮች የሚለው ቃል ግን በግብር ወይም በድርጊት ተካፋይ የሆኑትን ብቻ ያመለክታል::

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰውን ችግር ለማስቀረት "ግብረ አበሮች" ወይም "ግብረ አበርነት" የሚለው ቃል ከስያሜውም ላይ እንዲሰረዝ ተደርጐ "ዋና ወንጀል አድራጊነት" ወይም
... የሚለው ቃል በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ እንዲገባ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

ቁጥር ፴፪ (፩) ንዑስ (ሐ) "አእምሮ የሌለውን አሳዋቂ" የሚል ሀረግ ይገኝበታል። ሀረጉ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ አእምሮ ያልተፈጠረበት ሰው አስመስሎ ያሳያል። ስለዚህም አገላለፁ የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ በማሰብ "አእምሮ ያልተስተካከለውን ሰው" በሚል ተስተካክሏል። እንዲሁም አእምሮው የተስተካከለ ሰው እንኳ ቢሆን በልዩ ልዩ ምክንያት የወንጀሉን ድርጊት ሳይገነዘብ ወይም ሳያውቅ መሣሪያ ሊሆን ስለሚችል ይኸው ፍሬ ሀሣብ በዚህ ሕግ ውስጥ "ሁኔታውን ያልተገነዘበው ሰው" በሚል እንዲገለጽ ተደርጓል። ሕፃናትም በመሣሪያነት ሊያገለግሉ ስለሚችሉ "ህፃን" የሚል ቃል ገብቷል። በተጨማሪም በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፴፪ ንዑስ ቁጥር (ሐ) ውስጥ "እንስሳት ወይም ግዙፋዊ ኃይል" የሚለው ሃረግ በዚሁ ቁጥር እና በንዑስ ቁጥር (ሀ) የተገለፀ በመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

በቁጥር ፴፪ (፪) ላይ "የሚቀጣው" የሚለው አግባብ ባለመሆኑ ከእንግሊዝኛው "shall be tried" ከሚለው ጋር በሚስማማ ሁኔታ "ጉዳዩ የሚታየው" በሚል ተተክቷል።

በቁጥር ፴፪ (፫) ላይ "ብዙዎች" የሚለው ቃል ስህተት ስለሆነ "ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ" በሚል ተተክቷል።

ከዚህም በላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ታክሎበት አንቀጹ ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፴፫ <u>በልዩ ወንጀል ተካፋይ መሆን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፫ ስያሜ "ልዩ ወንጀል በሚሰራበት ጊዜ ተካፋይ ስለመሆን" የሚል ሲሆን አገላለጹ ተሻሽሎ "በልዩ ወንጀል ተካፋይ መሆን።" እንዲል ተደርጓል።

በድንጋጌው ላይ ስለግብረ አበርነት የተደነገገው አግባብነት የለውም፤ ምክንያቱም ይህ አንቀጽ ስለዋና ወንጀል አድራጊነት ተጨማሪ ሀሣብ የያዘ እንደመሆኑ መጠን በአንቀጽ ፴፪ ስያሜ ላይ በተገለጸው መሠረት መስተካከል ስለሚገባው ነው። ስለዚህ ስለግብረአበር የተደነገገው ተሰርዞ "ዋና ወንጀል አድራጊነት" በሚል ተተክቷል።

ከዚህም ሌላ አንቀጹን ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊው የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፴፬ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

በሕግ የሰውነት መብት ያላቸው ድርጅቶች የመንግሥት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ በወንጀል እንደሚከሰሱ እና ቅጣቱም መቀጮ እንደሚሆን በማመልከት አዲስ አንቀጽ ፴፬ እንዲገባ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የድርጅቱ የወንጀል ተካፋይነት በዋና ወንጀል አድራጊነት፤ በአባሪነት ወይም በአነሳሽነት ደረጃ ሊሆን እንደሚችል፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ አንድ ድርጅት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የሚቀጣው ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ፣ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም ወንጀል ሲያደርግ እንደሆነ፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ቅጣቱ በአንቀጽ ፺ መሠረት መቀጮ እንደሚሆንና ካስፈለገም ድርጅቱ ሊታገድ፣ ሊዘጋ ወይም ሊፈርስ እንደሚችል፤ በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የድርጅቱ መከሰስና መቀጣት ወንጀሉን

www.abyssinialaw.com



የፈጸሙትን ግለሰቦች ከመክሰስና ከመቅጣት እንደማያስቀር ተደንግጓል፡፡ በንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ ደግሞ የድርጅት ትርጉም እንዲካተት ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፴፰ <u>በሕብረት የሚፈጸም ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፬ ድንጋጌ `የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፰ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የአንቀጹ ስያሜ እንደሚያመለክተው፣ ወንጀሉ የሚፈፀመው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም የወንጀል አድራጊዎች ብዛት ከአንድ በላይ በሆነ ቁጥር ይህ አንቀጽ አግባብነት ሊኖረው እንዴት እንደሚችል በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡ ጥቂት ሰዎች ተስማምተው የግድያ፣ የዘረፋ ወይም ማናቸውንም ሌላ አይነት ወንጀል ሲፈጽሙ በእያንዳንዳቸው ላይ ማስረጃ አቅርቦ የማስቀጣቱ ተግባር የዐቃቤ ሕግ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በዚህ መልክ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተቀርጿል፡፡ እንደ አድማ፣ አምባ ጓሮ፣ ግርግር ወይም ሕገ ወጥ ሰልፍ በመሳሰሉት ወንጀሎች ግን ዐቃቤ ሕግ ማስረዳት ያለበት እያንዳንዱ ሰው በህብረቱ ውስጥ መገኘቱን እንጂ ምን ምን እንዳደረገ የማስረዳቱ ሸክም የእርሱ ግዴታ መሆን የለበትም፡፡ በጊዜውና በቦታው በህብረቱ ውስጥ መገኘቱን የማስረዳት ሸክም የዐቃቤ ህግ ቢሆንም አስቦ የወንጀሉ ተካፋይ አለመሆኑን ማስረጃ ማቅረብ ያለበት እያንዳንዱ ተከሳሽ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መልክ አንዳንድ ምሳሌ በማስገባት ሁለተኛው ፓራግራፍ ተቀርጿል፡፡

አንቀጽ ፴፱ <u>ማነሳሳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፱ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የቀድሞው ስያሜ "ለወንጀል ሥራ ስለማነሳሳት" የሚል የነበረ ሲሆን "ማነሳሳት" ብቻ እንዲል ተደርጓል፤ ምክንያቱም የማነሳሳት ወንጀል እንዲፈፀም ለማድረግ እንደሆነ ግልጽ በመሆኑ ነው፡፡

የአንቀጹን አቀራረጽ በተመለከተ የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ ራሱን የቻለ አሳብ የያዘ በመሆኑ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደረገ ሲሆን ንዑስ ቁጥር (፪) እና (፫) የነበሩት ድንጋጌዎች ደግሞ ተሸጋሽገው ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነው ገብተዋል፡፡

የቁጥር ፴፭ ንዑስ ቁጥር (፩) ይዘትን በሚመለከት አንድ ሰው ወንጀል እንዲፈጽም በገንዘብ ስጦታ ሊያግባባ እንደሚችል ይደነግጋል ይሁን እንጂ ከገንዘብ ሌላም በሌላ አይነት ስጦታ ወንጀል እንዲፈፀም ማነሳሳት ስለሚቻልና በእንግሊዝኛው ቅጅ ይኸው ፍሬ አሳብ የተንፀባረቀ በመሆኑ በገንዘብ ስጦታ የሚለው ቀርቶ "በገንዘብ፣ በስጦታ" በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

የቁጥር ፴፭ (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ መጨረሻ ላይ አንድ ሰው አነሳሸ የሚባለው ተነሳሸውን "ወንጀልን እንዲሠራ ያደረገው እንደሆነ ነው" ተብሏል፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፤ ምክንያቱም በእንግሊዝኛውም ሆነ በፈረንሳይኛው ቅጂ መሠረት ወንጀሉ ከመሞከሩ በፊት አነሳስቷል ማለት ስለሚቻል ነው፡፡ ወንጀል እንዲፈፀም ሌላውን ሰው ካግባባው የማነሣሣቱ ድርጊት በዚሁ ደረጃ ፍፃሜ አግኝቷል፡፡ ወንጀሉ እስኪፈፀም፣ እስኪሞከር

www.abyssinialaw.com



ወይም ወንጀሉን ለመፈፀም ዝግጅት እስኪደረግ ድረስ አላነሳሳም የሚባልበት ምክንያት የለም:: በዚህ መሠረት አንቀጽ ፴፭ (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሻሽሏል::

ከዚህም ሌላ በዚህ ንዑስ አንቀጽም ሆነ በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ አንቀጹ ተሻሽሏል::

ንቀጽ ፴፮ <u>አባሪነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፮ የተደረገ ሲሆን፣ አንቀጹን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በተለይም የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች ግልጽነት ያነሳቸውና ውስብስብነት ያላቸው በመሆኑ፣ ከላይ ስለአነሳሽነት በተደነገገው አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ፣ (፫) እና (፬) መሠረት ተሻሽለው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) እና (፭) ሆነው እንዲገቡ ተደርጓል::

ንቀጽ ፴፯ <u>ወንጀል ለማድረግ ማደም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፮ ድንጋጌ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፯ ሆኖ ገብቷል::

በተለይም በቁጥር ፴፮ (፩) ላይ "ግብረአበርነት" የሚለው ቃል የሚገኝ ሲሆን በእንግሊዝኛው እና በፈረንሳይኛው ቅጅ ላይ ግን "participation" የሚለውን ቃል ተጠቅመውበታል:: ተካፋይነቱ በዋናም ቢሆን በሁለተኛ ደረጃ ወንጀል አድራጊ ተካፋይነቱ ሁሉንም ይመለከታል:: በመሆኑም "ግብረአበርነት" ወይም "ዋና ወንጀል አድራጊነት" ከሚለው ቃል ይልቅ "የወንጀል ተካፋይነት" የሚለው አነጋገር የተሻለ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል::

ንቀጽ ፴፰ <u>ወንጀልን አለማስታወቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፰ ሆኖ የገባ ሲሆን፣ አንዳንድ የቃላት ለውጦች ተደርጎበታል::

ቀጽ ፵ <u>ወንጀል ከተደረገ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵ የተደረገ ሲሆን የድንጋጌው ስያሜ "ወንጀለኛን ስለመርዳት" ከሚል ይልቅ "ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳት" የሚለው አገላለጽ ይበልጥ ተስማሚ በመሆኑ በዚሁ መልክ ተስተካክሏል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቁጥር ፴፱ መግቢያ "ዋና ወንጀል አድራጊውን ረድቶ" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል:: የቃላት ለውጥም ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፵፩ <u>የግል ምክንያቶች ለሌላ የማይተላለፉ መሆናቸው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፩ ሆኖ ገብቷል። በድንጋጌው ላይ "ብዙ" የሚለው ቃል ቀርቶ "ሁለት እና ከሁለት በላይ" በሚል ቃል ተተክቷል።

እንዲሁም "በዋናነት" የሚለው አገላለጽ አሻሚ እንዳይሆን በማሰብ "በዋና ወንጀል አድራጊነት" በሚል ተስተካክሏል። ከዚህ ሌላ አንዳንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አራት
## በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ መሆን

የምዕራፍ አራት ስያሜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት "ታትመው በሚወጡ ጽሁፎች በሚሠራ ወንጀል ተካፋይ መሆን" የሚል ሲሆን "በመገናኛ ብዙሀን አማካይነት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተካፋይ መሆን" በሚል ተተክቷል:: ይህ የሆነበት ምክንያት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፳፱ (፫) ላይ "መገናኛ ብዙኃን" የሚለው ሀረግ የህትመት ሥራንም ሆነ ሌላውን የማሠራጫ ዘዴ የሚያካትት ስለሆነ ነው:: በሁለት አማራጭ ሀረጎች ከመጠቀም ይልቅ በአንድ ሀረግ መጠቀሙ ስለሚመረጥ በዚህ ምክንያት ተስተካክሏል:: በየአንቀጹም ሥር እንደአስፈላጊነቱ ይኸው ሀረግ ጥቅም ላይ ውሏል::

ይህ አራተኛው ምዕራፍ ስለመደበኛ የወንጀል ተካፋይነት ከሚደነግገው ከሶስተኛው ምዕራፍ የሚለይባቸው አበይት ነጥቦች አሉ:: እንዲሁም በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ረገድ በአዲሱ የወንጀል ሕግና በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይታያል:: በዚህ ምዕራፍ ስር ስለሚገኙት አንቀፆች ስለእያንዳንዳቸው ማብራሪያ ከመስጠቱ በፊት፣ በሁለቱ ምዕራፎችም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግና በተሻረው ሕግ ድንጋጌዎች መካከል ስላሉት ዋና ዋና ልዩነቶች አጭር አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል::

፩ መደበኛ የወንጀል ተካፋይነትን በሚመለከት (ከአንቀጽ ፴፪ እስከ ፵፩) በአንድ ወንጀል አፈፃፀም በማናቸውም ደረጃ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ሁሉ፣ ወንጀሉ ከመደረጉ በፊትም ሆነ በሚደረግበት ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት እና በአባሪነት ድርጊቱን ሲፈፅሙ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናሉ:: ወንጀሉ ከተፈፀመ በኋላም ዋና ወንጀል አድራጊው ከመከሰስም ሆነ ከመቀጣት እንዲያመልጥ የሚረዱ ግለሰቦች ሁሉ በወንጀል ሊቀጡ ይችላሉ:: በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ግን የሚከሰሱት እና የሚቀጡት፣ ሁሉም ተካፋዮች አይደሉም:: ለወንጀሉ ሐላፊ ናቸው ተብለው ተጠያቂ የሚሆኑት የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው:: ለዚህም ተጠያቂ መሆን የሚገባቸውን ሰዎች ዝርዝር በቅደም ተከተል ሕጉ ያስቀምጠ ሲሆን፣ በዝርዝሩ ቅደም ተከተል ከተቀመጡት ውስጥ አንዱ ከተቀጣ ሌሎቹ በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆኑም::

፪ ከአንቀጽ ፴፪ እስከ ፵፩ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ፖሊስ የማስናዳት ተግባር መከናወኑን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ክትትል ሊያደርግ ይችላል፤ ወንጀሉ እስኪሞከር ወይም እስኪፈፀም ድረስ መጠበቅ የለበትም:: ከአንቀጽ ፵፪ - ፵፯ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ግን ጽሑፉ እስኪታተም ወይም ተፈላጊው ነገር እንደ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን በመሳሰሉት እስኪሰራጭ ድረስ ፖሊስ ምንም ክትትል ሊያደርግ ወይም እርምጃ ሊወስድ አይችልም:: ይህንን ሁኔታ አዋጅ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፹፭ በይበልጥ ግልጽ አድርጎ ያስቀምጠዋል:: አንድ ጽሑፍ ከመታተሙ ወይም የፕሬስ ውጤት ከመሰራጨቱ በፊት መንግሥት ቁጥጥር (ሳንሱር) ያደርግ የነበረ ቢሆንም ከተጠቀሰው አዋጅ ወዲህ ቁጥጥር ማድረጉ ቀርቷል:: በዚህ መሠረት ከሕትመት ሥራ ወይም ከስርጭት በፊት ምንም-ማድረግ አይቻልም ማለት ነው:: የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፩ የመጨረሻው አነጋገር በአማርኛው ቅጂ ላይ ባይደነግግም በእንግሊዘኛውና በፈረንሣይኛው ቅጂዎች መሰረት ከሕትመት ስራ ወይም የፕሬስ ውጤቱ ከመሠራጨቱ በፊት ወንጀሉ ተፈፅሟል አይባልም:: በዚህ የወንጀል ሕግ

www.abyssinialaw.com

በአንቀጽ ፵፪ መጨረሻ ላይም በሁለቱ የውጭ አገር ቋንቋዎች መሰረት ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል፡፡

፫ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚደረጉ ወንጀሎችን በሚመለከት በቀድሞው ሕግና በዚህ በአዲሱ ሕግ መካከል ያሉ ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የስዊዘርላንድ የወንጀል ህግን የሚከተለው የቀድሞው ህጋችን ለመገናኛ ብዙኃን ወንጀሎች ዋና ኃላፊ የሚያደርገው ደራሲውን ወይም አመንጪውን ነው (ቁ.፵፪)፡፡ አዘጋጁንና አሳተሚውን የመሳሰሉት ሰዎች በምትክ ኃላፊነት የሚጠየቁ ሲሆን ይህም የሚቻለው ደራሲው ወይም አመንጪው በልዩ ልዩ ምክንያት በማይከሰስበት ጊዜ ነው (ቁ.፵፫)፡፡

በአዲሱ የወንጀል ህግ ግን ሁኔታው ተለውጧል፤ በመደበኛ ኃላፊነት የሚጠየቁት አዘጋጁ፣ አሳታሚው ወዘተ .... ናቸው (አንቀጽ ፵፫)፡፡ ደራሲው ወይም አመንጪው የአገሪቱን የህዝቡንና የመንግሥቱን ጉዳይ በሚመለከት ከሚፈጸሙ ወንጀሎች በቀር (አንቀጽ ፵፬)፣ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ስራ(አንቀጽ ፵፫/፩) ወይም እንደ ሬዲዮ በመሳሰሉ የመገናኛ ብዙኃን በሚደረግ ስርጭት (አንቀጽ ፵፫/፫) በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም፤ በየጊዜው በማይወጣ (Non periodical) የህትመት ስራ በሚፈጸም ወንጀልም አዘጋጁ ወይም አመንጪው የሚጠየቀው አልፎ አልፎ ነው (አንቀጽ ፵፫/፪)፡፡

ለ/ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፪ መሠረት ደራሲው ወይም አመንጪው በወንጀል የሚቀጣ ከሆነ አዘጋጁ ፣ አሳታሚው ወይም ለወንጀሉ ኃላፊ የሆነ ሌላ ሰው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም፡፡ በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ ፵፬ ግን የአገሪቱን፣ የህዝቡን ወይም የመንግሥቱን ጥቅም በሚጎዳ ሁኔታ ወንጀል ሲፈጸም፣ በወንጀል የሚጠየቀው ደራሲው ወይም አመንጪው ብቻ ሳይሆን አሳታሚውም ጭምር ነው፡፡

ሐ) የአንድን ደራሲ ወይም አመንጪ ማንነት ስለመግለጽ፣ የቀድሞውም ሆነ አዲሱ የወንጀል ህግ የሚመሳሰሉበት ሁኔታ ቢኖርም ከፍተኛ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ በአገር ወይም በመንግሥት ላይ የተቃጡ ወንጀሎችን በተመለከተ አዘጋጁ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሌላ ሰው በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ህግ መሠረት የደራሲውን ወይም የአመንጪውን ስም የመግለጽ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ በሌሎች ወንጀሎች ረገድ ግን የደራሲውን ማንነት ለመግለጽም ሆነ ላለመግለጽ አዘጋጁ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሌላ ሰው በቀድሞው ህግ መሠረት መብት የነበረው ሲሆን (ቁ.፵፬/፩)፡ በአዲሱ የወንጀል ህግ ግን የደራሲውን ወይም የአመንጪውን ስም መግለጽ የተከለከለ ነው (አንቀጽ ፵፭ (፩)፡፡ አዲሱ ህግ በዚህ መልክ የተቀረጸበት ምክንያት ደራሲዎች ሃሳባቸውን ያለመገታት እንዲገልጹ የሚያበረታታና፣ ይህም በበኩሉ በህገ መንግሥቱ ለተደነገገው የፕሬስ ነፃነት ዋስትና የሚሰጥ መሆኑ በመታመኑ ነው፡፡

መ) በቀድሞው ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑት ግለሰቦች ብቻ ናቸው፡፡ በአዋጅ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፹፭ እና በዚህ የወንጀል ሕግ መሠረት ግን

www.abyssinialaw.com

የሕትመት ስራውን ወይም ስርጭቱን ያከናወነው ድርጅት ምንጊዜም በወንጀሉ ተጠያቂ ይሆናል።

ከዚህ ቀጥሎ በምዕራፉ ድንጋጌዎች በእያንዳንዳቸው ላይ አጭር ማብራሪያ ይሰጣል።

## አንቀጽ ፵፪ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፪ ሆኖ ገብቷል።

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፵፩ አገላለጽ ልዩ ልዩ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ እንዲገባ

ተደርጓል።

በዚህ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ በገባው በቀድሞው ንዑስ ቁጥር ሁለት የሁለተኛው ፓራግራፍ የእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ "... and are committted only where publication is completed" ይል የነበረው ሀረግ በአማርኛው ቅጂ ላይ አልተካተተም ነበር። ሆኖም ይህ የእንግሊዝኛ ሀረግ መኖሩ፣ በመገናኛ ብዙሃን ወንጀል ተፈፀመ የሚባለው በመሰናዳት ደረጃ ላይ ሳይሆን የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ በተገለፀ ጊዜ መሆኑን ግልጽ ያደርገዋል። በመሆኑም "ወንጀሉ ተፈፀመ የሚባለውም በነዚሁ ዘዴዎች ለሕዝብ በተገለፀ ጊዜ ነው" የሚል ዓረፍተ-ነገር እንዲገባ ተደርጓል። በአዋጅ ቁጥር 34/1985 መግቢያ በአራተኛው ፓራግራፍ ላይ፣ "ፕሬስ ይህንን ተግባሩን ሊያከናውን የሚችለው የቅድሚያ ምርመራ (ሴንሰርሺፕ) እና ሌላም ተመሳሳይ ገደብ ሳይደረግበት በነጻና በኃላፊነት ስሜት ሊንቀሳቀስ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ሲፈጠርለት" ነው ተብሎ የተጻፈውም ይህንኑ ሁኔታ ያረጋግጣል።

## አንቀጽ ፵፫ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በሚፈጸሙ ወንጀሎች ያለው ኃላፊነት*

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፫ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፫ ሆኖ ገብቷል።

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፵፫ ስያሜ "ሕትመቱ በሚገለፁ ጽሁፎች በሚደረጉ ወንጀል ምክትል ሀላፊ ስለመሆን" የሚል ነበር። ሆኖም ምክትል ኃላፊዎች የነበሩ ሰዎች ዋና ኃላፊዎች ... የመሰሰሉት የማስራጨያ ዘዴዎችም በዚህ ... በሕትመትም ይሁን በሌሎች ልዩ ልዩ ለሕዝብ መግለጫ በሆኑ መንገዶች የሚፈፀሙትን ወንጀሎች ማንፀባረቅ እንዲችልና የቀድሞው ምክትል ኃላፊዎች ሳይሆኑ ኃላፊዎች መሆናቸውን እንዲያገኙ፣ ስያሜው ... ተደርጓል።

የተሻረው ሀግ የቁጥር ፵፫ ንዑስ ቁጥር አንድ ፊደል (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ከፍተኛ ለውጥ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነው ገብተዋል። ከዚህም ሌላ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገቡ የፕሬስ ውጤቶችን በሚመለከት አስገቢው ወይም

* በወንጀል ሕግ በአንቀጽ ፵፫(፩) በፊደል (መ) ላይ "የሚያሟላ" የሚለው ቃል "የማያሟላ" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

አሰራጪው ተጠያቂ መሆን እንዳለበት በዚህ ህግ የተደነገገ ሲሆን፤ በየጊዜው ታትሞ የሚወጣ ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሰ)፣ በየጊዜው ታትሞ የማይወጣ ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (፪) (ሰ) ስር እንዲገባ ተደርጓል::

በቀድሞው ህግ በቁጥር ፶፰ እንደፊልም፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ስለመሳሰሉት መገናኛ ብዙኃን ተደንግጎ የነበረው ተሻሽሎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል:: አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የገባ ሲሆን፣ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) በተመለከተው መሠረት ለመገናኛ ብዙኃን ውጤት በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊ የሆነው ሰው በሀገር ውስጥ የመኖሪያ ስፍራው ካልታወቀ ወይም የመኖሪያ አድራሻውን ለማረጋገጥ ካልተቻለ ከእርሱ ቀጥሎ የተመለከተው ሰው በኃላፊነት ይጠየቃል::" የሚል ነው:: የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዓላማ በሰስቱ ንዑሳን አንቀጾች በየንዑስ ፊደሉ ላይ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ የተጠቀሰውን ሰው አድራሻ ማወቅ ወይም ማረጋገጥ ካልተቻለ፣ በቅደም ተከተሉ ዝርዝር ላይ የሚገኘው ቀጥሎ ያለው ሰው ለወንጀሉ ኃላፊ የሚደረግበትን ሁኔታ ለመግለጽ ነው::

ከላይ በንኡስ አንቀጽ (፬) ውስጥ እንደተገለፀው በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊ የሚሆነው ሰው ከተጠያቂነት የሚድነውና ከእርሱ ቀጥሎ ያለው ሰው በኃላፊነት የሚጠየቀው፣ የመጀመሪያውን ተጠያቂ የመኖሪያ አድራሻ ማወቅ ወይም ማረጋገጥ በማይቻልበተ ጊዜ ነው:: አድራሻው አለመታወቁ ወይም አለመረጋገጡ ለሃላፊነቱ መዛወር እንደብቸኛ አማራጭ ተደርጎ መወሰዱ ችግር ያስከትላል:: ለምሣሌ አንድ አዘጋጅ በሕጋዊ መንገድ ለህጋዊ አላማ ወደ ውጭ አገር በሄደበት ጊዜ ሕገወጥ ጽሑፍ ቢታተም፣ በአገር ውስጥ ያሉትና ከእርሱ ቀጥሎ ያሉት ሰዎች ተጠያቂ ሳይሆኑ ነውን? ሌሎች ምክንያቶችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ፤ ከፊሎቹ ከአንቀጽ ፶፫(፭) ጋር በማያያዝ ተጠቅሰዋል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭)፣ "በዚህ አንቀጽ በመገናኛ ብዙኃን ውጤቶች አማካይነይት በተፈጸመ ወንጀል ኃላፊነትን ለመወሰን ሲባል የውጤቱ ይዘት ኃላፊነት ባለበት ሰው ሙሉ ዕውቀትና ፈቃደኛነት እንደገባ፣ እንደታተመ ወይም እንደተሰራጨ ይቆጠራል::" ተብሎ የተደነገገ ሲሆን፣ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፶፫ (፫) ከተመለከተው ጋር የሚጣጣም አይደለም:: የቀድሞው ድንጋጌ የፕሬስ ውጤቱን ይዘት ያሳተምሁት ወይም ያሰራጨሁት ህገወጥነቱን እያወቅሁ አይደለም ብሎ አዘጋጁ፣ አሳታሚው ወይም አሰራጪው የቀረበበትን ክስ መከላከል ይችል እንደነበር ያሳያል:: በአዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ግን ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ሰዎች ድርጊቱን አውቀው ወይም አስበው እንደፈጸሙት ይቆጠራል::

ከዚህም አልፎ የአዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፭) ሁለተኛው ፓራግራፍ ፣"በዚህ ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ማስረጃ እንዲቀርብ አይፈቀድም::" የሚል በመሆኑ እንደሁኔታው አዘጋጁ፣ አሳታሚው፣ አታሚው፣ አሰራጩ ድርጊቱን የፈጸመው አውቆ ወይም አስቦ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ከተከሰሰበት ወንጀል ነጻ ሊወጣ አይችልም::

ይህ አስተሳሰብ የወንጀል ህግን መርሆች የሚጻረር መምሰሉ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው አስቦ ወይም በቸልተኛነት አንድን ህገ ወጥ ድርጊት ሲፈጽም በመሆኑ ነው:: በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት በሚፈጸሙ ወንጀሎች ረገድ ግን ዶክተር ፊሊፕ ግራቨን በታወቀው መጽሐፋቸው* ላይ እንደገለጹት፣ ከፍ ብሎ

* በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው የዶክተር ግራቨን መፅሐፍ እ.ኤ.አ በ1965 የተጻፈው፣"an Introduction to Ethiopian Penal Law" የተሰኘው ነው::

www.abyssinialaw.com

በተጠቀሱት መንገዶች ወይም ዘዴዎች በሚፈጸሙ ወንጀሎች የሚከሰሰውና የሚቀጣው ተካፋይ የሆነ ሰው ሁሉ አይደለም:: አስቦ ወይም በቸልተኛነት ድርጊቱን ቢፈጽምም ባይፈጽምም መከሰስና መቀጣት የሚገባው ሰው ግን እንዲኖር ያስፈልጋል:: ይህም አስተሳሰብ በብዙ በሰለጠኑት አገሮች የወንጀል ህግ የተደገፈ ነው፤ ለቀድሞው ህጋችን በአብዛኛው መሠረት የሆነው የስዊዘርላንድ የወንጀል ህግ ሳይቀር ይህንን መርህ እንደሚከተል ከዶክተር ግራቬን መጽሐፍ መረዳት ይቻላል::

አዲሱ የወንጀል ህግ ይህንን አቋም መውሰዱ የሚያስገርም አይሆንም:: አንድ አዘጋጅ፣ አሳታሚ፣ አታሚ ወይም አሰራጭ እንደሁኔታው በወንጀል ሐላፊ በሚሆንበት ጊዜ ሕገወጡን ድርጊት የፈጸምሁት አውቄ ወይም አስቤ አይደለም በማለት መከላከያ ማስረጃ እያቀረበ ከክስ እና ከቅጣት የሚድን ከሆነ፣ ለህትመት ወይም ለስርጭት የሚቀርበውን የፕሬስ ወይም የሌላ የመገናኛ ብዙኃን ውጤት በጥንቃቄ ላለማንበብ ወይም ላለመመልከት መቆጣጠሪያ የሌለው በር ይከፍታል:: በዚህ ዓይነቱ መንገድ በሚፈጸም ወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው ሁሉ እንዲቀጣ አለማድረጉ የፕሬስ ነጻነትን ለማረጋገጥ ይረዳል ተብሎ መታመኑ የሚደገፍ ቢሆንም አንድም ሰው የማይቀጣበትን መንገድ መክፈቱ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት የሚደረገውን ወንጀል መከላከል የማያስችል ሁኔታን ይፈጥራል::

የዚህ ዓይነቱ አተረጓጎም ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል:: ተከሳሹ ምን ጊዜም ቢሆን ማፍረሻ ማስረጃ ማቅረብ አይችልም ማለቱ አጠያያቂ ነው:: የህትመቱ ስራ ወይም ስርጭቱ የተከናወነው፣ ተከሳሽ ነገሩን ለመከታተል ወይም ለመቆጣጠር የማያስችል፣ ፍጹም ከአቅሙ በላይ የሆነ ድንገተኛ ነገር ባጋጠመው ጊዜ ለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ከተረጋገጠ በወንጀል ይቀጣ ማለቱ ትክክል መስሎ አይታይም:: ለምሳሌ የመገናኛ ብዙኃን ውጤት ለህትመት ወይም ለስርጭት የቀረበው ኤዲተሩ ወይም ኃላፊነቱ የሚመለከተው ሌላ ሰው ከባድ ህመም ይዞት በሀኪም ቤት በመተኛቱ ወይም በፖሊስ ተይዞ በቁጥጥር ስር በመዋሉ ምክንያት ከስራ ቦታው እርቆ በሚገኝበት ጊዜ ከሆነ፣ እነዚህን መሠረት አድርጎ ቢከራከርና መከላከያ ማስረጃ ቢያቀርብ ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይገባልን? የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ውድቅ መደረግ ያለበት ተከሳሹ ወኪል ሳይኖረው ከስራ ቦታው ላይ እየጠፋ በስራ ቦታው ላይ እያለ ጉዳዩን አላየሁትም ወይም በጥንቃቄ አልመረመርኩትም የሚል ምክንያት ሲያቀርብ እና ሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሊሆን ይገባል:: ባጭሩ ጉዳዩ የሚቀርብለት ፍርድ ቤት በጥልቀት እየመረመረ ተከሳሹ ማፍረሻ ማስረጃ በማቅረብ መከላከል የሚገባው መሆን አለመሆኑን ሊወስን ይገባል::

ከላይ የተመለከቱት የንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ድንጋጌዎች አነጋገር ለትርጉም በር አይከፍትም የሚባል ከሆነ፣ በቁጥር ፴፬/፲፱፻፷፯ የወጣውን የፕሬስ አዋጅ የሚተካ አዲስ አዋጅ በመረቀቅ ላይ በመሆኑ፣ በእነዚህ ንዑስ አንቀጾችና በሌሎችም ተዛማጅ ነጥቦች ላይ አዲሱ ህግ ያሉበትን እጥረቶች በሚያሟላ ሁኔታ ሊቀረፅ ይገባል::

## አንቀጽ ፵፬ የደራሲው፣ የአመንጪው ወይም የአሳታሚው ልዩ የወንጀል ኃላፊነት

ይህ ድንጋጌ ከቀድሞው ህግ ከቁጥር ፵፪ ይዘት ጋር በጥቂቱ ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፣ አንድ ደራሲ ወይም አመንጪ በተሻረው ህግ እንደተደነገገው የሚጠየቀው በዋና ኃላፊነት ሳይሆን በልዩ ኃላፊነት መሆኑን ይደነግጋል:: ቀደም ሲል በተሰጠው አጭር አስተያየት ላይ እንደተገለጸው፣ ደራሲው ወይም አመንጪው በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው ህገርን

www.abyssinialaw.com

ወይም መንግሥትን በሚመለከቱ ከባድ ወንጀሎች ብቻ ነው:: ከደራሲው ወይም ከአመንጪው ጋርም አሳታሚው በጣምራ በወንጀል እንደሚቀጣ የአንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ ያሳያል::

## አንቀጽ ፵፫ የመረጃ ምንጭን በሚስጢር መጠበቅ

ይህ አንቀጽ በጥቂቱም ቢሆን ከተሻረው ህግ የቁጥር ፵፬ ድንጋጌ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: በሁለቱ ህጎች መሠረት የአገርን ወይም የመንግሥትን ጥቅም የሚነኩ ወንጀሎችን በሚመለከት የደራሲን ወይም የአመንጪን ማንነት መግለጽ ግዴታ ነው:: በሌሎች ወንጀሎች ግን የአንድን ደራሲ ወይም አመንጪ ስም መግለጽ የተከለከለ ነው፤ የዜና ወይም የመረጃ ምንጩንም እንዲገልጽ አሳታሚ ወይም አዘጋጅ አይገደድም:: በተሻረው ህግ በቁጥር ፵፬(፩) መሠረት የደራሲውን ወይም የአመንጪውን ማንነት የመግለጽም ሆነ ያለመግለጽ መብት የአሳታሚው፣ የአዘጋጁ ወይም በኃላፊነት የሚጠየቀው የሌላ ሰው መብት ነበር::

### የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፭ ድንጋጌ መሰረዝ

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፵፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፪ (፪) ሆኖ ስለገባ ከዚህ ተሰርዟል::

## አንቀጽ ፵፮ ድርብ ኃላፊነትን ማስቀረት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ሁለተኛ ኃላፊነትን ስለማስቀረት" የሚለው አገላለጽ የተፈለገውን መልዕክት በሚገባ የሚያስተላለፍ መስሎ ስለማይታይ ይህ ስያሜ ተሰርዞ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፮ ስያሜ "ድርብ ኃላፊነትን ማስቀረት" ተብሏል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፮ ይዘት አገላለፁ የተሻለ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፮ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆኗል::

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ድርጅት በዋናም ሆነ በምክትል ሀላፊነት በወንጀል ከሚጠየቁት ሰዎች ጋር ምንጊዜም በተደራቢነት መጠየቅ እንዳለበት የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፹፬ የአንቀጽ ፲፬ አነጋገር የዚህ አንቀጽ ሁለተኛው ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል::

## አንቀጽ ፵፯ የማይደፈር መብት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፯ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ፣ "በጽሁፍ ጉዳይ ስለማይደፈር መብት" ይል የነበረ ሲሆን "የማይደፈር መብት" በሚለው ሀረግ ተተክቶ የዚህ አንቀጽ ስያሜ ሆኗል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ጉዳዩ የሚመለከተው ጽሁፍን ብቻ ሳይሆን ሌሎች መገናኛ ብዙሀንን ጭምር በመሆኑ ነው::

የአንቀጹን ይዘት በሚመለከት ከእንግሊዝኛው አነጋገር ጋር የሚጣጣም አገላለጽና ይዘት እንዲኖረው ተደርጎ ተረቅቋል::

www.abyssinialaw.com

ርዕስ ሶስት
ወንጀል አድራጊውን የሚያስቀጡ ሁኔታዎች
ምዕራፍ አንድ
የወንጀል ኃላፊነት
ክፍል አንድ
መደበኛ ኃላፊነት

## አንቀጽ ፵፰ የወንጀል ኃላፊነትና ፍፁም ኢ-ኃላፊነት

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፰ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጽ ፵፰ ስያሜ "ለወንጀል ሀላፊ ስለመሆንና ስላለመሆን" ከሚል ይልቅ የወንጀል ሀላፊነትና ፍጹም ኢ-ኃላፊነት" ማለቱ ይሻላል ተብሎ ስለታመነበት በዚሁ መሠረት ተለውጧል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፵፰ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፖራግራፍ ላይ የባዮሎጂካዊ ምክንያቶችን ዝርዝር ገድቦ ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ አልታየም:: በቁጥር ፵፰ የተጠቀሱት ምክንያቶች ፍፁም የወንጀል ኢ-ኃላፊነትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የታወቀ ነው:: በጀርመን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይም ፍፁም የወንጀል ኢ-ኃላፊነትን ያስከትላሉ ተብለው በምክንያትነት ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም ዶክተር ፍሊፕ ግራቨን በመጽሐፋቸው ላይ በሰጡት አስተያየት በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፱ (፩) የተዘረዘሩት ምክንያቶችም ከፊል ኃላፊነትን ብቻ ሳይሆን ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ማስከተል እንደሚችሉ የታወቀ መሆኑን ገልጸዋል::

ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ማስከተል የሚችሉ ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ሊኖሩ ወይም ሊከሰቱ እንደሚችሉ መገመት አዳጋች አይሆንም። በመሆኑም የአንቀጽ ፵፰ን ባዮሎጂካዊ ምክንያቶች ገዛ ከማድረግ ይልቅ በሳይንስ ዕድገት ሊደረስባቸው የሚችሉ ሌሎች ምክንያቶች ሊታከሉበት ይገባል ተብሎ ይታመናል።

ስለዚህ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፰(፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ከተዘረዘሩት ስነሕይወታዊ ምክንያቶች በተጨማሪ፣ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፱ ከተጠቀሱት ስነሕይወታዊ ምክንያቶች አንዱ ወይም "ማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ስነሕይወታዊ ምክንያት" ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ሊያስከትል እንደሚችል የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተቀርጿል።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፵፰ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ፣ ".....የተግባሩን ዓይነትና ውጤት ለሠገሠት ወይም በዚህ ግምት መሠረት ለመረመድ ያልቻለ ሲሆን" የሚል አነጋገር ይገኝበታል:: ሆኖም "መገመት" ወይም "ግምት" የሚሉት ቃላት ትክክል ባለሆኑ "ለማወቅ" "ለመገንዘብ" ወይም "ግንዛቤ" በሚሉት ቃላት ተተክቷል:: "ለመፈጠሙ" [illegible] ቃል ተተክቷል:: እንዲሁም [illegible] በኢማፈጭነት ማስቀመጡ፣ "ግለት" "እና" የሚለው ቀርቶ "ወይም" መግባቱ ይመረጣል:: ይህም በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ ላይ የተገለፀ ሲሆን አሳቡም ምክንያት ያለው ነው::

www.abyssinialaw.com

ስለዚህ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፰(፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ከተዘረዘሩት ስነሕይወታዊ ምክንያቶች በተጨማሪ፣ በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፱ ከተጠቀሱት ስነሕይወታዊ ምክንያቶች አንዱ ወይም "ማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ስነሕይወታዊ ምክንያት" ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ሊያስከትል እንደሚችል የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተቀርጿል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፵፰ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ፣ ".....የተግባሩን ዓይነትና ውጤት ለመገመት ወይም በዚህ ግምት መሠረት ለመራመድ ያልቻለ ሲሆን" የሚል አነጋገር ይገኝበታል:: ሆኖም "መገመት" ወይም "ግምት" የሚሉት ቃላት ትክክል ስላልሆኑ "ለማወቅ" "ለመገንዘብ" ወይም "ግንዛቤ" በሚሉት ቃላት ተተክቷል:: "ለመራመድ" የሚለው ቃልም "ለመቆጣጠር" በሚል ቃል ተተክቷል:: እንዲሁም የተግባሩ ዓይነትና ውጤት ከማለት ይልቅ ሁለቱን ነገሮች በአማራጭነት ማስቀመጡ፣ ማለት "እና" የሚለው ቀርቶ "ወይም" መግባቱ ይመረጣል:: ይህም በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ ላይ የተገለፀ ሲሆን አሳቡም ምክንያት ያለው ነው::

የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ንዑስ አንቀጽ (፪) አነጋገሩ በመጠኑ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

ኀጽ ፵፱ ከፊል ኃላፊነት

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፵፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፱ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ህግ በቁጥር ፵፰(፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የተዘረዘሩት ስነሕይወታዊ ምክንያቶች ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ከፊል ኃላፊነትን የሚያስከትሉበት ጊዜ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ዶክተር ግራቨን በመፅሐፋቸው ላይ አስተያየት የሰጡበት ጉዳይ ነው:: ከፊል ኃላፊነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ስነ ሕይወታዊ ምክንያቶች ሊያጋጥሙ ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ:: በመሆኑም የቀድሞው የቁጥር ፵፱(፩) ድንጋጌ እነዚህን ለውጦች በማካተት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፵፱(፩) ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) የእንግሊዝኛው ቅጂ "In addition to a penalty.." ይላል:: ስለዚህ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል::

ኆጽ ፶ በስካር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረ ኢ-ኃላፊነት የሚደረጉ ወንጀሎች

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው "ከኃላፊነት እድናለሁ በማለት ዘዴን መፍጠር" ይል የነበረ ሲሆን ይዘቱን በሚገባ ስለማያመለክት "በስካር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረ ኢ-ኃላፊነት የሚደረጉ ወንጀሎች" እንዲል ተደርጓል::

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ "ቀጥተኛ አሳብን" ብቻ በሚያመለክት አነጋገር የተደነገገ ሲሆን ሁኔታው ግን ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብን በተጨማሪ ማካተት እንደለበት ግልጽ በመሆኑ ሁለቱን አይነት አሳብ እንዲያካትት ተደርጓል:: ይኸውም፣ "አንድን ወንጀል ለመፈጸም በማቀድ ወይም ሲፈጽም እንደሚችል እያወቀ...... አስቦ" በሚለው ጥገኛ ሀረግ ውስጥ "ለመፈጸም በማቀድ" የሚለው ሀረግ ቀጥተኛ ሃሳብን

www.abyssinialaw.com


የሚያመለክት ሲሆን "ሊፈጽም እንደሚችል እያወቀ" የሚለው ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብን ያሳያል።

በተጨማሪም የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል።

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በማጣጣም አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል።

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ ወንጀል አድራጊው በገዛ ራሱ ጥፋት ወንጀሉን እንደፈጸመ አስመስሎ አቅርቦታል። ሆኖም በገዛ ራሱ ጥፋት ወደ ፍጹም ኢ-ኃላፊነት ራሱን ማስገባቱን እንጂ ወንጀሉ በራሱ ጥፋት መፈጸሙን የእንግሊዝኛው ቅጂ ስለማያሳይ እና ትክክለኛውም አሳብ ይኸው ስለሆነ በዚህ መሠረት ንዑስ አንቀጽ (፫) ተስተካክሏል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተጨመረ ሲሆን ምንም ጥፋት ሳይኖረው ወይም ተገድዶ በመጠጥ፣ በአደንዛዥ ዕጽ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ነገር ወደ ፍጹም ኢ-ኃላፊነት ውስጥ ገብቶ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ወንጀል ቢፈጽም ተጠያቂ ሊሆን እንደማይገባ የሚደነግግ ነው። አድራጊው የሚገደደው በስካር መንፈስ ወደ ፍጹም ኢ-ኃላፊነት እንዲገባ ለማድረግ እንጂ በአንቀጽ ፶፰ እና ፶፱ እንደተደነገገው በቀጥታ ወንጀል እንዲፈጽም ባለመሆኑ የድንጋጌው መኖር አስፈላጊ ነው። ስለዚህም ሊካተት ችሏል።

አንቀጽ ፶፩ <u>አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚደረግ የልዩ ዐዋቂ ምርመራ</u>

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፩ ሆኖ ገብቷል።

የቁጥር ፶፩ ስያሜ "አጠራጣሪ ሁኔታ" የሚል ነበር። ዳሩ ግን በዚሁ ቁጥር የተደነገገው ስለተከሳሾች አጠራጣሪ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን አጠራጣሪ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የልዩ ዐዋቂውን አሳብ መጠየቅ ግዴታው ስለመሆኑ ጭምር ስለሆነ የድንጋጌው ስያሜ በዚሁ አኳኋን ተሻሽሎአል።

በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፶፩ ንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው ይዘት መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጎበታል። እንዲሁም በዚሁ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው መስመር ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ሙሉ በሙሉ ሁሉን የሚያካትቱ ሳይሆኑ በምሳሌነት የተቀመጡ መሆናቸው ስለታመነበት ፓራግራፉ ሲጀምር "በተለይ" በሚል ቃል እንዲሆን ተደርጓል። በተጨማሪም በዚሁ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "በድንቁርና መስማትና መናገር በዲዳነት" የሚለውን አገላለጽ ጺያፍነትን ለማስወገድ ሲባል "መስማትና መናገር በዲዳነት" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል። ከዚህ ሌላ በዚህ ንዑስ ቁጥር ላይ "በመጠጥ የሚሳነው" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል። ከዚህ ሌላ በዚህ ንዑስ ቁጥር ላይ "በመጠጥ የሚሳነው" የሚለው አገላለጽ ውስንነት ያለው መስሎ አዘውታሪነት በሽታ የተለከፈ እንደሆነ" የሚለው አገላለጽ ውስንነት ያለው መስሎ ስለሚታይ ለምሳሌም በሌሎች የአደንዛዥ ዕጽ አዘውታሪነት (ተጠቃሚነት) የሚከሰት የአእምሮ በሽታን እንዲጨምር ለማድረግ በማሰብ "በመጠጥ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር አዘውታሪነት በሽታ የተለከፈ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል።

በቁጥር ፶፩ ንዑስ ቁጥር (፩) የተገለጸው ፍሬ አሳብ ከላይ በተገለጸው አኳኋን ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኗል።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ የተደነገገው ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር ተቀባይነትን አግኝቷል። በዚህ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "በተከሳሹ ሁኔታ" ሳይ የሚለው አገላለጽ የተከሳሹን ሁኔታ ሲመረምር ልዩ አዋቂው መመልከት ያለበት ወንጀሉ በተፈጸመ ጊዜ ያለው ሁኔታ መሆን ስለአለበት ተከሳሹ በሚመረመርበት ወይም ለፍርድ ቤት በሚቀርብበት ጊዜ ያለው ሁኔታ በወንጀል ስነ-ስርአት ሕግ ሊሸፈን ስለሚገባ ይህንኑ ለማሳየት ሲባል "ተከሳሹ ወንጀሉን ባደረገበት ጊዜ" በሚል ተገልጿል።

ንዑስ ቁጥር (፫) ይዘት መጠነኛ ማሻሻል ተደርጎበት የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኗል።

## ክፍል ሁለት
## ህፃናትና ለአካለመጠን ያልደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች

### ቶጽ ፶፪ በህፃናት ላይ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ አለመሆን

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፶፪ ስያሜ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፪ ስያሜ ሆኗል።

በተሻረው ሕግ ቁጥር ፶፪ በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ፣ ስለ ተቀጪነትና ስለወንጀል ኃላፊነት የሚደነግጉት ሁለት ዓረፍተ-ነገሮች ቅደም ተከተላቸው እንዲለዋወጥ ተደርጓል፤ ምክንያቱም የወንጀል ኃላፊነት ከተቀጪነት በቅድሚያ ሊጠቀስ ስለሚገባው ነው። በዚሁ ቁጥር በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ እንደተመለከተው ወንጀል ባደረጉ ህፃናት ላይ ስልጣን ያላቸው ቤተዘመዶቻቸውና አስተማሪዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ አሳዳሪዎቻቸውና ሌሎችም በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህንኑ ለማመልከት "አስተማሪዎቻቸው" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "አሳዳሪዎቻቸው ወይም ሌሎች አካላት" የሚል ሀረግ እንዲጨመር ሆኗል።

ቁጥር ፶፪ ከላይ በተነገረው አኳኋን ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፪ ሆኖ ገብቷል።

### ቀጽ ፶፫ በወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚፈጸሙ ልዩ ድንጋጌዎች

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፶፫ ስያሜ ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር ተቀባይነትን አግኝቶ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፫ ስያሜ ሆኗል።

የቁጥር ፶፫ ንዑስ ቁጥር (፩) ይዘት የተሻለ አገላለጽ ይኖረው ዘንድ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር (፪) ወጣት ጥፋተኞች የቅጣትና የዲሲፒሊን ስርዓት የሚፈጸምባቸው በፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ እንደሆነ መሆኑን ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ወጣቶቹ ፍፁም ኢ-ኃላፊ ቢሆኑ ወይም ኃላፊነታቸው የተቀነሰ ቢሆን በአንቀጽ ፶፰ እና በአንቀጽ ፶፱ የሚወሰደው ዓይነት የጥንቃቄ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ የሚጠቅሰው ነገር ባለመኖሩ በአፈጻጸም ረገድ ሊነሳ የሚችለውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በንዑስ ቁጥር (፪) ከመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ቀጥሎ "ሆኖም ወጣት ጥፋተኛው ኃላፊነት የሌለው በሆነ ጊዜ የዚህ አንቀጽ ፻፶፱-፻፷፫ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል" የሚል ዓረፍተ-ነገር ተጨምሯል።

በዚህ መሰረት የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፻፫ ከላይ በተገለጸው አኳኋን እንዲሻሻል ተደርጎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፫ ሆኗል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፬ እና ፻፭ ድንጋጌዎች የአቀማመጥ ለውጥ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቁጥር ፻፬ እና ፻፭ ድንጋጌዎች አቀማመጥ እንዲለዋወጥ ተደርጓል:: የቁጥር ፻፬ ድንጋጌ ስለ ፍርድ ቤት ቅጣት አወሳሰን፣ የቁጥር ፻፭ ድንጋጌ ደግሞ ስለማጣራት የሚደነግግ ሲሆን ማጣራት ከውሳኔ መቅደም ስለሚገባው አቀማመጣቸው ተለዋውጧል::

አንቀጽ ፻፬ <u>የልዩ ዐዋቂ ምስክርነትና ማጣራት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፬ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ማጣራት ስለ ልዩ ምርመራና ስለማናቸውም ምርመራ" የሚል ነበር:: ዳሩ ግን የድንጋጌው ይዘት ፍርድ ቤቱ ስለወጣት ጥፋተኛ አስተዳደግና ኑሮ እንዲሁም ስለጠባዩ ለማጣራት የወጣቱን ጥፋተኛ ዘመዶች እና የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣኖች ጠይቆ ጉዳዩን ማጣራት እንደሚያስፈልገው እንዲሁም ልዩ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች አሳብ መጠየቅ እንደሚገባው የሚደነግግ ነው:: የልዩ አዋቂው ሳይንሳዊ ግኝቶችንም በሚመለከት ረገድ ፍርድ ቤቱ ምን ማድረግ እንዳለበት በዚህ ቁጥር ተደንግጓል:: ስለዚህ በዚህ ቁጥር የተመለከተውን ድንጋጌ ለመግለጽ የሚችል ተስማሚ ስያሜ እንዲሆን በማሰብ የነበረው ስያሜ ተሰርዞ "የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማጣራት" በሚል ተተክቷል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፭ ሶስት ንዑስ ቁጥሮች ቦታቸውን እንደያዙ በእንግሊዘኛው ቅጂ መሠረት ከተስተካከሉ በኋላ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ሶስት ንዑሳን አንቀጾች ሆነው ገብተዋል::

አንቀጽ ፻፭ <u>የቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ እርምጃው አወሳሰን</u>

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፭ ሆኖ ገብቷል::

የሕጉ ስያሜ "ስለ ዳኛ ግምት" ይል የነበረ ቢሆንም በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ የድንጋጌው ስያሜ "Assessment of Sentence" የሚል በመሆኑና "Sentence" የሚለው ቃል የቅጣትንም ሆነ የጥንቃቄ እርምጃ አወሳሰንን አጠቃልሎ የሚይዝ በመሆኑ ስያሜው "የቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ እርምጃው አወሳሰን" እንዲል ተደርጓል::

ይዘቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የጥንቃቄ እርምጃን ብቻ ሳይሆን ቅጣትንም ጭምር በመሆኑ፣ በዚህ መልክ አንቀጹ ተሻሽሏል:: ሌሎችም የቃላት ማስተካከያ ተደርገውበታል::

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፶፮ <u>ከ፲፭ ዓመት በላይ፣ ከ፲፰ ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፮ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፶፮ ስያሜ "አካለ መጠን ከማድረስ አስቀድሞ ያለው መካከለኛ ጊዜ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጠው አገላለጽ የትኛውን የዕድሜ ክልል እንደሚሸፍን ለመረዳት አስቸጋሪ በመሆኑና ይዘቱንም በትክክል እንዲያንፀባርቅ ለማድረግ በማሰብ የቀድሞ ስያሜ ተሰርዞ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፮ ስያሜ "ከ፲፭ ዓመት በላይ፣ ከ፲፰ ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች" ተብሏል::

በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ቅጣቱ የሚወሰንበት" የሚለው ሀረግ፣ "ጉዳዩ የሚታየው"፣ በሚል ሀረግ ተተክቷል::

በንዑስ ቀጥር (፪) ላይ "እንደስሜቱ መጥፎነት" የሚለው የአማርኛ ቅጂ በእንግሊዝኛው ቅጂ incorrigible የሚለውን አያሳይም:: የዚህ ተቀራራቢ ትርጉም መታረም ያለመቻል ነው:: ስለዚህም የወጣትነት ዕድሜ መጠን ከሚለው ቀጥሎ "ሊታረም ያለመቻሉ እና አደገኛነቱን" በሚል ተተክቷል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በወንጀል ጥፋተኛ መሆን</u>
<u>ክፍል አንድ</u>
<u>አሳብ፣ ቸልተኛነትና ድንገተኛ ነገር</u>

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የምዕራፍ ሁለት ስያሜ "በወንጀል ስራ አጥፊ ስለመሆን" የሚል ነበር:: "አጥፊ" የሚለው ቃል ትክክል ባለመሆኑ "Criminal Guilt" ከሚለው የእንግሊዝኛ ሀረግ ጋር በማጣጣም "በወንጀል ጥፋተኛ መሆን" በሚል ሀረግ ተስተካክሏል::

ቀጽ ፶፯ <u>መርህ፣ የወንጀል ጥፋትና ድንገተኛ ነገር</u>

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፯ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያ ፓራግራፍ ላይ "አጥፊነት" የሚለው "ጥፋተኛነት" በሚል ተተክቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "በፈቃዱ" የሚለው "አስቦ" በሚለው ተተክቷል፣ ምክንያቱም "Intentionally" ለሚለው ቃል የተሻለው ትርጉም "አስቦ" የሚለው በመሆኑ ነው::

የንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን ሁለተኛው ፓራግራፍ ስለፍትሐብሔር ተጠያቂነት የሚደነግግ በመሆኑና ስለዚህ ጉዳይ የመደንገጉ ተግባር የፍትሐብሔር ሕግ ስለሆነ ይህ ፓራግራፍ ተሰርዟል::

www.abyssinialaw.com

## ንዑስ ክፍል አንድ
## በነጠላ ወንጀል ጥፋተኛ መሆን

### አንቀጽ ፶፰ አስቦ ወንጀል መፈፀም

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "አውቆ ስለማጥፋት" ይል የነበረው፣ "አስቦ ወንጀል መፈጸም" እንዲል ተደርጓል፤ "Intentionally" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል "አውቆ" "ሆነ ብሎ" ወይም "አስቦ" በማለት በተለያየ ቃል ከመተርጎም ይልቅ "አስቦ" በሚለው ቃል ብቻ መጠቀሙ ይመረጣል:: "ማጥፋት" የሚለውም ቃል "ወንጀል መፈጸም" በሚለው ሀረግ ተተክቷል::

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ በቀድሞው ሕግ መሰረት በሁለት ፓራግራፍ የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ፓራግራፍ ስለቀጥተኛ አሳብ፣ ሁለተኛው ፓራግራፍ ቀጥተኛ ስላልሆነ አሳብ ይደነግግ ነበር:: ሆኖም የሁለቱን ዓይነት አሳብ ልዩነት በቀላሉ መረዳት እንዲቻል በይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ አነጋገሩን ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በመሆኑም "ማንም ሰው አስቦ ወንጀል ፈጸመ የሚባለው" የሚል አገላለጽ ከገባ በኋላ በፊደል "ሀ" ላይ ስለቀጥተኛ አሳብ፣ በፊደል "ለ" ላይ ደግሞ ቀጥተኛ ስላልሆነ አሳብ እንዲደነገግ ተደርጓል::

ከዚህም ሌላ የንዑስ ቁጥር (፩)፣ (፪) እና (፫) አነጋገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ አካል ሆነው ገብተዋል::

### አንቀጽ ፶፱ በቸልተኛነት ወንጀል መፈፀም

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፱ ሆኖ ገብቷል::

የተሻረው ሕግ የንዑስ ቁጥር አንድ የመጀመሪያው ፓራግራፍ የአማርኛው ትርጉም ስለሁለቱ ዓይነት ቸልተኝነት በግልጽ ስለማይደነግግ በይበልጥ ግልጽ ነው ተብሎ በታመነበት አነጋገር ተረቅቋል:: በአንቀጽ ፶፰ (፩) ላይ በመጀመሪያ ስለቀጥተኛ አሳብ፣ ቀጥሎ ቀጥተኛ ስላልሆነ አሳብ እንደተደነገገው ሁሉ በዚህም አንቀጽ ሥር እንደቸልተኝነቱ የክብደት ደረጃ አስቀድሞ ስለታወቀ ቸልተኝነት /advertent negligence/፣ በፊደል (ሀ) ከዚያም ስላልታወቀ ቸልተኝነት /inadvertent negligence/ በፊደል "ለ" በግልጽ አጋገር ተረቅቋል::

የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር አንድ የሁለተኛው ፓራግራፍ መግቢያ፣ "በግል ኑሮው አቀማመጥ" የሚለው ሀረግ በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ መሠረት "የአድራጊው የግል ሁኔታ" ተብሎ ተስተካክሏል::

የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር ሁለት አገላለጽም መጠነኛ የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በተደራራቢ ወንጀሎች እና በደጋጋሚነት ረገድ ጥፋተኛ መሆን

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የንዑስ ክፍል ሁለት ስያሜ፣ "ወንጀሎች ወይም የሕግ ድንጋጌዎች አንድነት ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ስላለ ጥፋተኛነት" የሚል ሲሆን "በተደራራቢ ወንጀሎችና በደጋጋሚነት ረገድ ያለው ጥፋተኛነት" በሚል ተተክቷል:: የደጋጋሚነትን ጉዳይ ማካተት ያስፈለገበት ምክንያት፣ የአንድ አድራጊ የጥፋተኛነቱ ክብደት የሚለካው ተደራራቢ ወንጀሎችን በሚፈጽምበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋጋሚ በሚሆንበት ጊዜ ጭምር በመሆኑ ነው::

ከተደራራቢ ወንጀሎች ይልቅ ደጋጋሚነት የአድራጊውን የጥፋተኛነት ደረጃ በይበልጥ ስለሚገልጽ ስለደጋጋሚነት የሚደነግግ አንቀጽ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ከተደነገጉት አንቀጾች ቀጥሎ ገብቷል::

### አንቀጽ ፷ ተደራራቢ ወንጀሎች

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፷፩ እና ፷፪ የልዩ ልዩ ተደራራቢ ግዙፍ ወጀሎችን ዓይነት ይደነግጋሉ::

የተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ትርጉም ግን የሚገኘው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፹፪ (፩) (ሀ) መጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ላይ ነው::

ቁጥር ፷፫ ላይ ስለ አንዱ ዓይነት የወንጀሎች መጣመር /Notional Concurrence/ የሚደነግግ ሲሆን የቁጥር ፹፪ (፩) (ሀ) ሁለተኛ ዓረፍተ-ነገር ላይ ደግሞ ስለሌላው ዓይነት የወንጀሎች መጣመር /Notional Concurrence/ ይተረጉማል:: ስለሁለቱም ዓይነት የወንጀሎች መጣመር /Notional Concurrence/ ቅጣት የሚወስነው ቁጥር ፻፺፪ ነው:: ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ድንጋጌ አወጣጥ ሥርዓት ያለውና የተቀናጀ ነው ማለት ስለማይቻል፣ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ዓይነትና ቅጣት ከሚደነግጉት አንቀጾች በፊት፣ የተደራራቢ ወንጀሎችን ትርጉም የሚያሣየው የቀድሞው የቁጥር ፹፪ (፩) (ሀ) አነጋገር ተሻሽሎ እዚህ መግባቱ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ አንቀጽ ፷ (ሀ) እና (ለ) ሆኖ ገብቷል::

ከዚህም በላይ እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊያስቀጡ ሲገባ እንደነጠላ ወንጀል የተቆጠሩባቸው ሁኔታዎች ያጋጥማሉ:: አንድ ሰው አስቦ በአንድ ጥይት ሁለት ሰዎችን ቢገድል አሁን ባለው ሕግ መሠረት የሚጠየቀው በአንድ ነጠላ ወንጀል ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን ፈጽሟል እንዳይባል የፈፀመው አንድ ድርጊት /አንድ ጥይት መተኮሱ/ ብቻ ነው:: ጣምራ ወንጀሎችን /Notional Concurrence/ ፈጽሟልም እንዳይባል የተጣሰው አንድ የሕግ ድንጋጌ ብቻ ነው:: በሌላ በኩል አንድ ሰው በአንድ ጥይት አስቦ አንድ ሰው ቢገድል፣ በዚያው ጥይት ደግሞ ሌላ ሰው በቸልተኝነት ቢገድል ተደራራቢ ወንጀሎችን ፈጽሟል ተብሎ ይጠየቃል:: ይህ ግን ሲደገፍ አይገባውም አንደኛውን አስቦ፣ ሁለተኛውን ግን በቸልተኝነት መግደሉ በሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ሲያስጠይቀው ሁለቱን አስቦ ሲገድል ግን በአንድ ነጠላ ወንጀል ብቻ ተጠያቂ መሆኑ በሕግም ሆነ በፍትህ ረገድ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም:: ዶክተር ፊሊፕ ግራቨን የዚህ ዓይነቱን አስተሳሰብ ያልደገፉት መሆኑን በመጽሐፋቸው ላይ የገለፁ ሲሆን አስተያየታቸው የሚደገፍ ነው::

www.abyssinialaw.com

ስለዚህ አንድ ሰው በአንድ ዓይነት የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈፀመው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ድንጋጌ የአንቀጽ ፳(ሐ) አካል ሆኖ ገብቷል።

አንቀጽ ፳፩ <u>ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፩ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ሀብት" ይል የነበረው "መብት" በሚለው ቃል ተተክቷል። ምክንያቱም የድንጋጌው ዓላማ ሀብትን (ንብረትን) ብቻ ሳይሆን በሕይወት፣ በአካል ወይም በሌላ ነገር ሰው ያለውን አጠቃላይ መብት ለመጠበቅ በመሆኑ ነው። በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይም የተቀመጠው (Right) የሚለው ቃል ነው። በተጨማሪም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ ወንጀሎችን እንደ አንድ ድርጊት ለመቁጠር ወይም እንደተደራራቢ ወንጀል ለመቁጠር ከፍተኛ ችግር ነበረው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከነበሩት መለኪያዎች በተጨማሪ ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ከሆነ የሚል ሦስተኛ መለኪያ ተጨምሮበታል። ይህ ማለት በአንድ የወንጀል ድንጋጌ የማይሸፈኑ ድርጊቶች ከሆኑ እንደ ተደራራቢ ወንጀሎች ይቆጠራሉ ማለት ነው።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ንብረት" የሚለው "መብት" በሚል ተተክቷል። "አንድ ግብ ለማግኘት" የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል። ምክንያቱም በአንድ በኩል የቀጥተኛ አሳብ ትርጉም ይህንን አነጋገር የሚያካትት በመሆኑና በሌላ በኩል የቸልተኛነት ትርጉም ይህንን ሀረግ የሚያጠቃልል ባለመሆኑ በሁለቱም ረገድ የሀረጉ መግባት አስፈላጊ ስላልሆነ ነው።

አንቀጽ ፳፩ ንዑስ ቁጥር (፪) አዲስ ተጨማሪ ፓራግራፍ ገብቶለታል። አድራጊው ድርጊቶችን ደጋግሞ ወይም አከታትሎ መፈፀሙ የአንድ ተራ ወንጀል ማቋቋሚያ ጠባይ ለመሆኑ ወይም ወንጀል መፈፀምን እንደልማድ ወይም ሞያ አድርጎ መያዙ ቅጣትን እንደሚያከብድ አንድ ወንጀል ተቆጥሮ በሕግ ተደንግጎ ሲገኝ፣ አንድ ነጠላ ወንጀል እንጂ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን እንደፈፀመ አይቆጠርም። ይህን በግልጽ የሚያመለክት ተጨማሪ ፓራግራፍ ተቀርጿል።

የንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌም የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ ሦስት ሆኗል።

አንቀጽ ፳፪ <u>አዲስ ቅጣት የሚያስከትል ወንጀልን መደጋገም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፩ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፪ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜው ላይ "ጥፋት" የሚለው "ወንጀል" በሚል ተተክቷል። በዚሁ ድንጋጌ ይዘት ላይ አንዳንድ የቃላት ለውጦች ተደርጎበት ተሻሽሎ ተረቅቋል።

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፷፫ <u>የተዛመዱ ወንጀሎች በተደረጉ ጊዜ ያለው ጥፋተኛነት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፷፪ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፫ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቀጥር ፷፪ ስያሜ "የተቀራረበ ወንጀል በተሰራ ጊዜ ስላለው ጥፋተኝነት" የሚል ቢሆንም ይዘቱ የሚገልጸው ስለተዛማጅ ወንጀሎች እንጂ ስለተቀራረቡ ወንጀሎች ባለመሆኑ "የተቀራረበ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "የተዛመዱ" በሚል እንዲተካና አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የአንቀጹ ስያሜ ሆኗል::

ይዘቱም የተሻለ አገላለጽ እንዲኖረው ተደርጎ ተቀርጿል፤ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል::

ቀጽ ፷፬ <u>ሌሎች ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሲደረጉ ያለው ጥፋተኛነት</u>

አንቀጽ ፷፩ እና ፷፪ ልዩ ልዩ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ቢሆንም ከሁለቱ አንቀጾች ውጭ የሚፈፀሙ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ ኃይሉ ለገሰን ይዘርፈዋል፤ በሌላ ጊዜ አበበን ይገድለዋል ከዚያም በኋላ በሰለሞን ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያደርሳል:: ሦስቱም ያልተዛመዱ እና ተመሣሣይነት የሌላቸው ወንጀሎች በመሆናቸውና በአንቀጽ ፷፪ ወይም ፷፫ የማይሸፈኑ በመሆኑ፣ እነዚህን የሚሸፍን ድንጋጌ አንቀጽ ፷፬ ሆኖ ተቀርጿል::

ቀጽ ፷፭ <u>የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ በሚደረጉ ጣምራ ወንጀሎች ያለው ጥፋተኛነት</u>

ሁለቱ ዓይነት ጣምራ ወንጀሎች (Notional Concurrence) ተራርቀው በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፷፫ እና ፹፪/፩/ (ሀ) ተለያይተው ከሚቀመጡ ይልቅ በሁለት ተከታታይ አንቀጾች ተቀርጸው መግባት ይገባቸዋል:: ስለዚህ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ስለሚፈፀሙ ጣምራ ወንጀሎች የሚደነግግ ራሱን የቻለ አንቀጽ ፷፭ የተቀረፀ ሲሆን ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎችን በሚመለከት የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፫ ድንጋጌ አንቀጽ ፷፮ ሆኖ ገብቷል::

የሁለቱ ዓይነት ጣምራ ወንጀሎች ልዩነት የሚከተለው ነው::

የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ጣምራ ወንጀሎች ተደራራቢ መሆናቸው የሚታወቀው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች ሲታዩ ብቻ ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ትዳር ያለው ሰው የአክስቱን ልጅ አስገድዶ ቢደፍር በአብዛኛው ሰው ዘንድ የሚታወቀው አንድ ወንጀል መፈጸሙ ብቻ ነው፤ ይኸውም አስገድዶ መድፈሩ ነው:: በሕጉ መሠረት ግን አድራጊው በተጨማሪ የቤሰኝነት ወይም የዝሙትን ወንጀልና የስጋ ዝምድናን የመጣስ ወንጀል በመፈጸሙ በሦስት ተደራራቢ ወንጀሎች ሊቀጣ ይችላል ማለት ነው::

በአንቀጽ ፷፮ የተመለከቱት ጣምራ ወንጀሎች ተደራራቢ መሆናቸው ለአብዛኛው ሰው ግልጽ ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ክብሪት ጭሮ የሌላውን ሰው ቤት ይለኩሳል:: ቃጠሎ ተፈጥሮ ቤቱ ይወድማል፤ በውስጡ ካሉት ሰዎች ከፊሎቹ ሲሞቱ ከፊሎቹ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ይደርስባቸዋል፤ በበረት ውስጥ የነበሩ እንስሳትም በቃጠሎ ይሞታሉ:: አድራጊው የፈጸመው አንድ ድርጊት፣ ማለትም ክብሪት ጭሮ ቤት መለኮሱ ብቻ

www.abyssinialaw.com



ቢሆንም ሰዎችን በመግደሉና ልዩ ልዩ የአካል ጉዳት በማድረሱ እንዲሁም ንብረት በማውደሙ በተደራራቢ ወንጀሎች ሊቀጣ ይችላል ማለት ነው::

ሁለቱን ዓይነት ጣምራ ወንጀሎች የሚመለከቱ ግልጽ ድንጋጌዎች በተከታታይ ማስቀመጥ ያስፈለገውም ሁለቱን ዓይነት ጣምራ ወንጀሎች ለይቶ ማወቅ እንዲያስችል ነው:: በቅጣት አወሳሰንም ረገድ ከፍተኛ ልዩነት ስላላቸው (አንቀጽ ፻፹፯) ሁለቱ ዓይነት ጣምራ ወንጀሎች ተለይተው በግልጽ እንዲቀመጡ ማድረጉ ጠቃሚነቱ አያጠያይቅም::

አንቀጽ ፷፮ <u>ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎችን በሚመለከት ያለው ጥፋተኛነት</u>

የአንቀጽ ፷፫ ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ስያሜ "የተቀላቀለ ወንጀል በተሠራ ጊዜ ስላለ ጠ ጥፋተኛነት" የሚል ሲሆን ከአንቀጹ ይዘት ጋር በይበልጥ እንዲስማማ ለማድረግ፣ "ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎችን በሚመለከት ያለው ጥፋተኛነት" በሚል ተተክቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ አነጋገር ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን መጠነኛ የቃላት ለውጥ ተደርጐበታል::
የንዑስ አንቀጽ (፪) የፊደል "ሀ" እና "ለ" አነጋገር እንዲሻሻል ተደርጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር በቸልተኝነት የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት በቸልተኝነት የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል ሲያስከትል እንደተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች ተቆጥሮ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጓል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ አንዳንድ የቃላት ለውጥ የተደረገ ሲሆን በተለይም "የይዋጣልን ፉክክር" የሚለው ሀረግ ቀርቶ በዚህ ሕግ "አምባጓሮ" የሚለው ቃል ገብቷል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የይዋጣልን ፉክክር በሕይወት ወይም በአካል ላይ ጉዳት ሲያስከትል ባደረሰው ጉዳት መነሻ አንድ ነጠላ ወንጀል እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ሲሆን፣ አምባጓሮ ግን ሞትን ወይም የአካል ጉዳትን ካስከተለ በአምባጓሮና በደረሰው ጉዳት ምክንያት ተደራራቢ ወንጀሎች እንደተፈጸሙ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፭፻፹ (፩) ስለሚደነግግ ነው::

አንቀጽ ፷፯ <u>ደጋጋሚነትን በሚመለከት ያለው ጥፋተኛነት</u>

"ደጋጋሚነትን በሚመለከት ያለው ጥፋተኛነት" በሚል ስያሜ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፸፬ (፩) (ለ)ን አሳብ የያዘ አዲስ አንቀጽ ከአንቀጽ ፷፮ ቀጥሎ ገብቷል:: ሆኖም በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፸፬ (፩) (ለ) ይዘት ላይ አንዳንድ ለውጥ ተደርጓል፤ ይኸውም:-

ሀ/ አድራጊው ከዚህ ቀደም የፈፀመው ወንጀል በስዊዝ የወንጀል ሕግ እንደተመለከተው በእሥራት የሚያስቀጣ መሆን አለበት:: የመጀመሪያው ወንጀል በመቀጮ ወይም በግዴታ ስራ የሚያስቀጣ ከሆነ ለደጋጋሚነት ማሟያ ነጥብ መሆን አይገባውም::

ለ/ በቀድሞ ሕግ በቁጥር ፸፬ (፩) (ለ) ላይ አንድ ጥፋተኛ ደጋጋሚ ነው የሚባልበት አንዱ ምክንያት "በምህረት ወይም በአዋጅ ምህረት ከተማረበት ቀን ጀምሮ" በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ አዲስ ወንጀል አስቦ ያደረገ እንደሆነ ነው::

www.abyssinialaw.com

"ምህረት" በሚለው ቃል ምትክ "ይቅርታ" (pardon) የሚለው ቃል የገባ ሲሆን "የአዋጅ ምህረት"(amnesty) የሚለው ሀረግ ተሰርዟል:: ይህ የሆነበት ምክንያት የአዋጅ ምህረት ከተሰጠበት ቀን አንስቶ አድራጊው በወንጀል ከመከሰስ ወይም ከመቀጣት ነጻ ከመሆኑም በላይ በተወሰነበት ቅጣት ምክንያት ሪኮርድ ስለማይያዝበትና እንደ ንፁህ ሰው ስለሚቆጠር ነው::

ሐ/ እንደገና የሚፈጸመው ወንጀል ከብደት እጁ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚያደርግ መሆን እንዳለበት የሰፈረው ድንጋጌ አልተደገፈም፣ ምክንያቱም አጠቃላይ እጁ ተላልፎ የሚሰጥበት ሕግ ስላልወጣ አንቀጹ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም እንደገና የሚፈፀመው ወንጀል መነሻው ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆን እንዳለበት ተደርጐ ተቀርጿል:: ይህም ሲባል፣ ፍርድ ቤት በየወንጀሉ ላይ የሚፈርደውን መነሻ ቅጣት እንጂ በህጉ ልዩ ክፍል ለየወንጀሉ የተደነገገውን መነሻ ቅጣት እንደሚያመለክት ተደርጎ ሊተረጎም አይገባም:: ዝርዝር ምክንያቱ የሚከተለው ነው::

በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ ፷፯ ላይ፣ "መነሻ ቅጣቱ ስድስት ወር የሆነ ቀላል እስራት ማስቀጣት የሚችል አዲስ ወንጀል" የሚለው ሀረግ ግልጽ ነው ማለት አይቻልም:: በሕጉ ልዩ ክፍል የሚገኙ ማስቀጫ አንቀጾች ለአዲሱ ወንጀል የሚደነግጉትን መነሻ ቅጣት ያመለክታል እንዳይባል፣ የአንቀጽ ፷፯ ድንጋጌ በዚህ መልክ አልተቀረፀም:: ፍርድ ቤት ለአዲሱ ወንጀል የሚወስነው ዝቅተኛ ቅጣት ነው እንዳይባልም፣ የድንጋጌው አነጋገር ይህንን አስተሳሰብ በግልጽ አያሣይም:: የስድስት ወሩ መነሻ ቅጣት ለአዲሱ ወንጀል የሕጉ ልዩ ክፍል የሚደነግገው ወይም ፍርድ ቤት የሚወስነው ዝቅተኛ ቅጣት መሆኑን አንቀጽ ፷፯ በግልጽ ካልደነገገም፣ ከሕግ አውጭው የቅጣት ዓላማ ጋር የሚጣጣመውን አስተሳሰብ መከተሉ ግድ ይሆናል:: ከሁለቱ አስተሳሰቦች ውስጥ የህግ አውጭውን ዓላማ ተግባራዊ የሚያደርገው የትኛው እንደሆነ ማወቅ እንዲቻልም፣ ሁለቱ ዓይነት አስተሳሰብ ወይም አተረጓጎም በቅጣት አወሳሰን ላይ የሚያመጣውን ልዩነት በቅድሚያ መመርመሩ አስፈላጊ ነው::

የስድስት ወሩ ቀላል እስራት በህጉ ልዩ ክፍል የተደነገገው መነሻ ቅጣት ነው ከተባለ፣ ብዙ ወንጀሎች እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ቢያስቀጡም መነሻ ቅጣታቸው አስር ቀን ወይም ሶስት ወር ከሆነ እነዚህን ወንጀሎች የፈጸሙ ሰዎች በአንቀጽ ፷፯ መሠረት ደጋጋሚ ወይም ልማደኛ ተብለው ሳይቀጡ ሊቀሩ ነው:: ለምሳሌ በአዲሱ የወንጀል ህግ መሠረት ተራ ስርቆት (አንቀጽ ፮፻፷፭) እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ቢያስቀጣም መነሻ ቅጣቱ አስር ቀን ነው:: በዚህ መሠረት ተራ ሌባ ምንጊዜም ደጋጋሚ ነው ሳይባል ነው፤ ደጋጋሚ ነው ካልተባለም ልማደኛ ሌባ ነው የሚባልበት ጊዜ አይኖርም:: በሌላ አነጋገር አንድ ሌባ ቀን በቀን ከሜዳ ላይ በሬ በመስረቁ የተፈረደበትን የቀላል ወይም የጽኑ እስራት ቅጣት ከጨረሰ በኋላ አምስት ዓመት ሳይሞላው ከታክሲ ተሳፋሪ ላይ ዘጠኝ መቶ ብር ቢሰርቅ ደጋጋሚ ሌባ ሊባል አይችልም፤ ምክንያቱም የተራ ስርቆት መነሻ ቅጣት አስር ቀን እንጂ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ባለመሆኑ ነው:: በዚህ መልክ አምስት ወይም ከአምስት የሚበልጥ የስርቆት ሬኮርድ ያለበት ሌባ ልማደኛ ሌባ ሊባል አይችልም ማለት ነው:: ይህ አተረጓጎም ግን የኢትዮጵያን ሕዝብና የህግ አውጭውን ሃሳብ ይጻረራል፤ የሁለቱም ዓላማ የተጠቀሰው ዓይነት ሌባ ደጋጋሚ ወይም ልማደኛ እየተባለ ከባድ ቅጣት እንዲወሰንበት ነው::

www.abyssinialaw.com

በአዲሱ የወንጀል ህግ በአንቀጽ ፷፯ ላይ የተመለከተው የስድስት ወር ቀላል እስራት በፍርድ ቤት የሚወሰነው ዝቅተኛ ቅጣት ነው የሚለው አተረጓጎም ግን ደጋጋሚንም ሆነ ልማደኛ ሌባን በአግባቡ መቅጣት የሚያስችል ነው፡፡ በተራ ስርቆት ከስድስት ወር ቀላል እስራት በታች በተደጋጋሚ የሚፈረድበት ሰው በአንቀጽ ፷፯ መሠረት ደጋጋሚ ነው ተብሎ በአንቀጽ ፩፻፹፰ መሠረት ባይቀጣም የስድስት ወር እና ከዚያ በላይ ቀላል እስራት የሚወሰንበት ከሆነ ደጋጋሚ ሌባ ነው ይባላል፡፡ በደጋጋሚነት በስርቆት ብዙ ጊዜ ከተቀጣም ልማደኛ ሌባ ነው ተብሎ ከባድ ቅጣት ሊወሰንበት ይቻላል፡፡ ልማደኛ ሌባ ከሆነም የተፈረደበትን ቅጣት በሙሉ ከሚጨርስ በቀር በአመክሮ የመፈታት ዕድል አይኖረውም፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከህግ አውጭው ዓላማ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡

ከላይ ከተሰጠው አስተያየት ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ነጥብ አለ፡፡ በቀድሞው ህግ መሠረት ልማደኛ ሌባም ሆነ ሌሎች ንብረት ነክ ወንጀሎችን በተደጋጋሚ የሚፈጽም ሰው ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ሊፈረድበት አይችልም፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ በተራ ሌብነት፣ እምነት ማጉደል፣ አታላይነት ወዘተ.... የሚቀጣ ግን በቀድሞው ህግ በቁጥር ፩፻፺፫ መሠረት ከአስር ዓመት ፅኑ እስራትም አልፎ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊፈረድበት ይችላል፡፡ እነዚህን እርስ በርስ የሚቃረኑ ድንጋጌዎች ለማስቀረት በማሰብ ልማደኛ ሌብነትን፣ ልማደኛ ወንበዴነትን፣ ልማደኛ አታላይነትን ወዘተ..... የሚመለከቱ የቀድሞው ህግ ድንጋጌዎች ተሰርዘው ወጥነት ባለው መንገድ ቅጣት መወሰን እንዲቻል፣ የቀድሞው ህግ የቁጥር ፩፻፺፫ ድንጋጌ ተሻሽሎ አንቀጽ ፩፻፹፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብና ህግ አውጭው ባሰቡት መሠረት እንደ ስርቆት የመሳሰሉ ወንጀሎች በደጋጋሚ ወይም በልማደኛ ጥፋተኞች ሲፈጸሙ በአግባቡ መቅጣት የሚያስችለውን ትርጉም መከተሉ የሚደገፍ ነው፡፡ ይኸውም በአንቀጽ ፷፯ የተመለከተው የስድስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ቅጣት በህጉ ልዩ ክፍል ለየወንጀሉ የተደነገገው ዝቅተኛ ቅጣት ሳይሆን ፍርድ ቤት በየወንጀሉ የሚፈርደው ዝቅተኛ ቅጣት ነው ብሎ መተርጎሙ ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች፣ የማያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች</u>
### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
### <u>በሕግ የተፈቀዱ ድርጊቶች</u>

አንቀጽ ፷፰ <u>በሕግ የታዘዙ ወይም የተፈቀዱ ድርጊቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፬ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፷፬ ፊደል (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) አነጋገር አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፷፱ <u>የሙያ ሥራ ግዴታ</u>

የተሻረው ሕግ ቁጥር ፷፭ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፱ ሆኖ የገባ ሲሆን የመጀመሪያው ፓራግራፍ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ሁለተኛው ፓራግራፍ ባለሙያ የሚፈጽመው ስህተት በፍትሐብሔር ስለሚያስጠይቅበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን ይህን መደንገግ የፍትሐብሔር ሕግ እንጂ የወንጀል ሕግ ተግባር ባለመሆኑ ተሰርዟል::

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>የማያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች</u>

ቀጽ ፸ <u>የተበዳይ ፈቃድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፷፮ "ስለተበዳይ ፈቃድ" በሚል ስያሜ ስር አድራጊው የሰራው ተግባር በሕጉ ልዩ ደንብ የተከለከለና የሚያስቀጣ ከሆነ፣ "ተጎጂው ወይም ስለእርሱ መብት ያለው የተስማማበት ጉዳይ ቢሆንም ባይሆንም ቅጣት አይቀርለትም" በሚል የተደነገገው፣ የግል አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ በሚያስቀጡ ወንጀሎችና የግል አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ በሚያስቀጡ ወንጀሎች መካከል ምንም ልዩነት አያደርግም::

አድራጊው የፈጸመው ወንጀል በግል አቤቱታ ሊያስቀጣ የሚችለው በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ ከሆነና የግል ተበዳዩ ወይም ስለእርሱ በሕግ ስልጣን ያለው የፈቀደው ድርጊት ከሆነ አድራጊው እንዲቀጣ ማድረጉ ተገቢ አይደለም:: በሌላ በኩል ደግሞ አድራጊው የሰራው ወንጀል የግል አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ የሚያስቀጣ ወንጀል ከሆነ የግል ተበዳዩ ወይም ስለእርሱ በሕግ ስልጣን ያለው የፈቀደው ድርጊት ቢሆንም እንደዚህ ያለው ወንጀል የህብረተሰቡን ጠቅላላ ደህንነት የሚመለከት ስለሆነ ከቅጣት አይድንም::

ስለዚህ የቁጥር ፸ ድንጋጌ ተስተካክሎ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣና የግል ተበዳዩ ወይም ስለእርሱ በሕግ ስልጣን ያለው የፈቀደው ድርጊት ከሆነ አድራጊው እንደማይቀጣ በንዑስ አንቀጽ (፩)፣ በግልጽ እንዲደነገግ ተደርጓል:: ከዚህ አገላለጽ መረዳት እንደሚቻለው የግል አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ በሚያስቀጡ ወንጀሎች ረገድ የተበዳይ ፈቃድ ከቅጣት እንደማያድን ግልጽ በመሆኑ ይሄንን የሚያሳይ ዓረፍተ-ነገር በሕጉ ላይ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም::

ነገር ግን የተበዳይ ፈቃድ የማያስቀጣበትን ልዩ ሁኔታ የያዘ አዲስ አሳብ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ እንዲገባ ተደርጓል:: ይኸውም፤ ማንም ሰው የንግድ ዓላማ ሳይኖረው በሕይወቱ እያለ በሚያደርገው ውል፣ አካሉን፣ የአካሉን ክፍል ወይም የአካሉን አንዱን ብልት ለሚያስፈልገው ሰው ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር በሕይወቱ ወይም ከሞቱ በኃላ እንዲሰጥ ቢስማማ፣ ተቀባዩ በወንጀል እንደማይጠየቅ የሚደነግግ ነው:: ድርጊቱ የተፈጸመው በንግድ ዓላማ ከሆነ ግን ሰጪውም ሆነ ተቀባዩ በወንጀል እንዲቀጡ የሚያደርግ አዲስ አንቀጽ (፭፻፸፫) እንዲገባ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፷፩ ፍጹም የሆነ መገደድ

በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፷፯ ፍጹም የሆነ መገደድን አካላዊና ሞራላዊ በሆነ መንገድ በሁለት ከፍሎ አካላዊ የሆነውን ለመቋቋም የማይቻል፣ ሞራላዊ የሆነውን ደግሞ ለመቋቋም የሚቻል አስመስሎ አቅርቦታል:: ስለዚህ ለመቋቋም የሚቻለው አካላዊም ሆነ ሞራላዊ በቁጥር ፷፪ የተሸፈነ ስለሚሆን በቁጥር ፷፩ ላይ አካላዊና ሞራላዊ ብሎ መከፈል ሳያስፈልግ ጠቅለል ባለ መልኩ ፍጹም የሆነ መገደድ በሚል ተስተካክሏል::

የቀድሞው የቁጥር ፷፯ ድንጋጌ ለፍጹም መገደድ በቂ መለኪያ ባለማስቀመጡ "ሊደርስበት ከነበረው ጉዳት በማይበልጥ ሁኔታ" የሚል አዲስ ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፰ የሁለተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌም ለመለኪያነት ስለሚያገለግልና በይበልጥ ተስማሚ ቦታው እዚህ መሆኑ ስለታመነበት የዚህ አንቀጽ ሁለተኛው ፓራግራፍ ሆኗል::

አንቀጽ ፷፪ ለማሸነፍ የሚቻል መገደድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፰ ስያሜውና ይዘቱ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ አገላለጹ ተስተካክሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፪ ሆኖ ገብቷል:: ከፍ ብሎ እንደተገለጸውም የሁለተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌ ከዚህ ተሰርዞ የአንቀጽ ፷፩ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኗል::

አንቀጽ ፷፫ የትዕዛዝ ሰጪ ተጠያቂነት

በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፷፱ ስያሜ ላይ "ኃላፊነት" የሚለው "ተጠያቂነት" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

ይዘቱንም በተመለከተ "ቁርጠኛ ትዕዛዝ" የሚለው ሀረግ ፍጹም የሆነ የመገደድ ባህሪን የሚያሳይ ስለሆነ ከላይ በአንቀጽ ፷፯ ከተገለጸው ፍሬ አሳብ ጋር እንዳይምታታ ሲባል የሕጉን የእንግሊዝኛ ሀረግ "express order" የሚለውን ትርጉም ተከትሎ "ግልጽ ትዕዛዝ" በሚል ተተክቶአል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፷፱ ድንጋጌ ከላይ በተመለከተው አኳኋን ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፫ ሆኗል::

አንቀጽ ፷፬ የትዕዛዝ ፈፃሚው ተጠያቂነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፬ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የድንጋጌው ስያሜ "የትዕዛዝ ፈጻሚው ኃላፊነት" የሚል ነበር:: ሆኖም "ኃላፊነት" የሚለው ቃል በአንቀጽ ፶፰ እና ፶፱ ከተገለጸው ጋር እንዳይምታታ ሲባል ቃሉ ተሰርዞ "ተጠያቂነት" በሚል ከተካተተ በኋላ የዚህ አንቀጽ ስያሜ ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ ቁጥር (፩)ን የመጀመሪያው ፓራግራፍ ይዘት በተመለከተ "በህዝብ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ ወይም በህብረት መብት ላይ" በማለት የተገለጸው ግልጽነት የሚጎለው

www.abyssinialaw.com


በመሆኑ ከሕጉ የእንግሊዝኛ ትርጉም ቅጂ ጋር ከተነጻጸረ በኋላ ሀረጉ ተሰርዞ "በሕብረተሰቡ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ ወይም በአለም አቀፍ ሕግ ላይ" የሚል ሀረግ እንዲገባና የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ተደርጓል።

በተለይም የቁጥር ፸ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ከፊሉ ተሻሽሎ ተቀርጿል። ምክንያቱም ሦስት ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በዚህ ፓራግራፍ ላይ የተጠቀሱ ሲሆን በሦስቱም ምክንያቶች ረገድ ፍርድ ቤት የማቅለል መብት እንዳለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ያሣያል። እንደ እንግሊዝኛው ቅጂ ግን በሦስተኛው ምክንያት ረገድ ፍርድ ቤት ቅጣት የማቅለል ግዴታ ተጥሎበታል። ይህ የሚደገፍ ነው። ትዕዛዙ አስገዳጅ ከሆነ ቅጣት ማቅለሉ ግዴታ ሊሆን ስለሚገባ በዚሁ መሠረት ተረቅቋል። "ትእዛዝ ፈጻሚው ሥነ-ሥርዓትን የመጠበቅና የመታዘዝ ስሜት አድሮበት ትእዛዙን የፈፀመ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል /አንቀጽ ፻፹/፣ በተለይም ትእዛዙ አስገዳጅ ሲሆን ፍርድ ቤቱ እንደመሰለው ቅጣቱን ያቃልልለታል።" በሚል አነጋገር ተስተካክሏል።

ይህም ፓራግራፍ ከተሻሻለ በኋላ ከንዑስ ቁጥር (፩) ወጥቶ የንዑስ አንቀጽ (፪) መጀመሪያ ፓራግራፍ ሆኗል። የቀድሞ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ደግሞ የንዑስ አንቀጽ (፪) ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሁለቱም ፓራግራፎች ተቀራራቢ አሳብ ያላቸው በመሆኑ ነው።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ መጠነኛ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ሆኖ ገብቷል።

ጽ ፸፭ <u>አስገዳጅ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፭ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የቁጥር ፸፩ ስያሜ "አስፈላጊ የሆነውን አድራጎት መተላለፍ" የሚል ነበር። ዳሩ ግን በዚህ ቁጥር ስር የተደነገገው አስፈላጊ የሆነውን አድራጎት ስለመተላለፍ ሳይሆን፣ ከሁኔታው አስገዳጅነት የተነሳ ሌላ አማራጭ ሳይኖር ሲቀር አስገዳጅ ሁኔታው በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት ቢያስከትልም የማያስቀጣ መሆኑን ነው። ስለዚህም የቁጥር ፸፩ ስያሜ ተሰርዞ " አስገዳጅ ሁኔታ" በሚል ስያሜ ተተክቷል።

የድንጋጌውን ይዘት በሚመለከት በመጀመሪያው አዲስ ፓራግራፍ ላይ ወንጀል የተሰራው ምን አይነት አደጋ ሲያጋጥም መሆኑን አይገልጽም። አደጋው በቅርቡ መድረሱ የማይቀርና አስጊ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር፣ ወይም የሌላውን ሰው መብት ለማዳን ነው በማለት ወንጀል ቢሰራ ከቅጣት ነጻ ለመሆን አይቻልም። ስለዚህ በዚህ ቁጥር በተመለከተው ድንጋጌ "በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ" በሚል ሀረግ እንዲጀምር ተደርጓል። በዚሁ ፓራግራፍ በቀረው ክፍል የተመለከተው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተሻሽሎአል።

ይህ አንቀጽ አዲስ ተጨማሪ ፓራግራፍ እንዲገባለት ተደርጓል። ይኸውም የሰውን ሕይወት ወይም ደህንነት የመጠበቅ ልዩ የሙያ ኃላፊነት የተጣለባቸው ሰዎች "እንደመርከብ ካፒቴን" የመሳሰሉት በሙያቸው ምክንያት ሊጠብቋቸው የሚገባቸውን ሰዎች ደህንነት ለአደጋ በማጋለጥ ራሳቸውን ቢያድኑ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ሊደግፋቸው

www.abyssinialaw.com



አይገባም:: ምንጊዜም የራሳቸውን መብት እንዲሰው ይጠበቅባቸዋል:: ይህንን ጥሰው ቢገኙ ግን በዚህ አንቀጽ በመጀመሪያው ፓራግራፍ መሠረት ከቅጣት ነፃ መሆናቸው ቀርቶ በአንቀጽ ፸፮ እና ፸፱ መሰረት ቅጣታቸው ሊቃለልላቸው ይችላል::

አንቀጽ ፸፮ <u>የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን መተላለፍ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፪ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፮ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፪ ስያሜ "አስፈላጊ ግዴታ የሆነውን የመብት ወሰን ስለመተላለፍ" የሚል ነበር:: ይሁን እንጂ ከላይ በአንቀጽ ፸፭ ስያሜ ላይ የተደረገው ለውጥ በዚህም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲደረግ በማስፈለጉ የዚህ አንቀጽ ስያሜ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ እንዲሻሻል ተደርጓል:: ይዘቱም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፪ ሁለተኛው ፓራግራፍ የሚደነግገው ስለ ፍትሐብሄር ሕግ ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ላይ መግባቱ አስፈላጊ አይደለም:: ይልቁንም በቁጥር ፸፪ ቀርቶ በቁጥር ፸፩ መሠረትም እንኳ በፍትሐብሄር ከመጠየቅ እንደማይድን የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር ፪ሺ፷፮ ስለሚደነግግ የቁጥር ፸፪ ሁለተኛው ፓራግራፍ መካተቱ ስሕተት ስለሆነ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፸፯ <u>ወታደራዊ አስገዳጅ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፯ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለወታደራዊ አስፈላጊ ሁኔታ" የሚል ነበር:: ሆኖም ከላይ በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፸፩ እና በቁጥር ፸፪ ስያሜ ላይ በተደረገው ለውጥ መሰረት "አስፈላጊ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "አስገዳጅ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) የተገለጸውም እንዳለ ተቀባይነትን ያገኘ ሲሆን በንዑስ ቁጥር (፪) "ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ሊያቃልልለት ይችላል" የሚለው አገላለጽ የሚፈለገው ነገር የተሟላ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ ካልፈለገ ቅጣቱን ሊያቃልልለት እንደማይችል የሚያመለክት መስሎ ስለሚታይ ከላይ የተገለጸው አባባል ተሰርዞ የሕጉን የእንግሊዝኛ ቅጂ ትርጉም ተከትሎ "ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ያቃልልለታል" በሚል ተስተካክሏል::

አንቀጽ ፸፰ <u>ሕጋዊ መከላከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፰ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን "ይልቁንም ያደጋውን ከባድነትና የተጠቂውን መብት ከፍተኛነት በማመዛዘን" የሚለው አነጋገር በምሳሌነት ከማገልገል በቀር የሚጨምረው አዲስ አሳብ ስለሌለና መኖሩ በአማርኛው ትርጉም ላይ ወደስሕተት ስለሚያመራ ተሰርዟል::

www.abyssinialaw.com

ጽ ፸፱ <u>ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፱ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፰ ስያሜ በቁጥር ፸፱ ስያሜ ላይ በተደረገው ማስተካከያ መሠረት እንዲስተካከል ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥም ከላይ በቁጥር ፸፱ የሕጉን የእንግሊዝኛ ትርጉም በማነጻጸር የተደረጉት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በዚህ ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ ተደርጓል:: እንዲሁም በዚሁ ንዑስ ቁጥር የማስረያው አንቀጽ ላይ "በመሰለው ቅጣትን ለማቃለል ይችላል" የሚለው አገላለጽ በንዑስ ቁጥሩ ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች ቢሟሉም እንኳን ቅጣትን ለማቃለል ወይም ላለማቃለል ለፍርድ ቤቶች ምርጫ የተተወ እንዳያስመስል የሕጉን የእንግሊዝኛ ቅጂ ተከትሎ ማሰሪያ አንቀጹ "ያቃልልለታል" በሚል ተተክቶ ንዑስ ቁጥሩ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ተስተካክሎ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ከላይ በቁጥር ፸፱ እና በቁጥር ፸፰ ንዑስ ቁጥር (፩) የተደረጉት አይነት የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በላይ "ይቅርታ ሊያስገኝ በሚችል" የሚለው ሀረግ ለደም ፍላት እና ለቁጣ ብቻ ስለሆነ ለፍርሃትም ለድንገተኛ ድንጋጤም እንዲያገለግል ተደርጎ ከተሻሻለ በኃላ ድንጋጌው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፸፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል::

በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) ላይ ያለው ስለ ፍትሐብሄር ጉዳይ የሚደነግግ ስለሆነ ተሰርዟል::

ጽ ፹ <u>በፍሬ ነገር መሣሣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹ የተደረገ ሲሆን በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፱ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፸፱ ላይ ያለው አሳብ በአንቀጽ ሁለት ላይ የተካተተ በመሆኑ ተሰርዟል::

ጽ ፹፩ <u>በሕግ ላይ መሣሣትና ሕግን አለማወቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፩ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፹ ንዑስ ቁጥር (፩) ማንም ሰው ከጥፋት ነፃ ለመውጣት ሕግን አለማወቁን ምክንያት ለማድረግ አይችልም በሚል ቢደነገግም ከጥፋት ነፃ ለመውጣት ሕግን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን በሕግ ላይ መሣሣትንም ምክንያት ለማድረግ ስለማይቻል "በሕግ ላይ መሣሣቱን ወይም" የሚለው ሀረግ "ሕጉን አለማወቁን" ከሚለው ሀረግ በፊት እንዲገባ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

በቁጥር ፸፰ ንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የተገለጸው ፍሬ አሳብ ለብቻው ራሱን ችሎ በንዑስ አንቀጽ ተከፍሎ መቀመጥ ያለበት በመሆኑ ፓራግራፉ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል::

በቁጥር ፸፰ ንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ የተገለጸው ይዘት ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና መጠነኛ የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ ንዑስ ቁጥር (፫) ሕግ አለማወቅ ወይም በሕግ መሣሣት በሚያስከትለው ጉዳት በፍትሐብሄር ስለሚያስጠይቅበት ሁኔታ ይደነግጋል:: ነገር ግን ይህ የፍትሐብሄር ሕግ እንጂ የወንጀል ሕግ ተግባር ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች</u>

### አንቀጽ ፹፪ <u>ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፪ ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ ቁጥር (፩) መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር ፍርድ ቤቱ በሕጉ ከተደነገገው ውሳኔ ሳያልፍ ቅጣትን ለማቃለል እንደሚችል ተደንግጎ የቅጣት ማቃለያ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል:: እያንዳንዱ ምክንያት ቅጣትን ለማቃለል በቂ ስለሆነ ከእነዚሁ ምክንያቶች አንዱ ወይም ከአንድ የበለጠ ያጋጠመ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ለማቃለል ሌላ አማራጭ አይኖረውም:: ስለዚህ "ለማቃለል የሚችለው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የሚያቃልለው" በሚል ተተክቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሀ) የተመለከተው ፍሬ ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ለ)ያለው ድንጋጌ በእንግሊዝኛ ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል::

በቁጥር ፸፱ ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሐ) ውስጥም "የአካል ወይም የመንፈስ ስቃይ" የሚለው ሀረግ ግልጽነት የሚጎለው በመሆኑ ከሕጉ የእንግሊዝኛው ቅጂ ትርጉም ጋር ተነጻጽሮ "ከፍተኛ የቁሳዊ እጦት ወይም ከፍተኛ የህሊና ስቃይ" በሚል ሀረግ እንዲስተካከል ተደርጓል::

በቁጥር ፸፱ ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (መ) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ እና መጠነኛ የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል::

በቁጥር ፸፱ ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሠ) እንደሕጉ የእንግሊዝኛው ቅጂ ትርጉም ወንጀል ፈጻሚው ከወንጀሉ ድርጊት በኋላ በእውነት መፀፀቱን የሚያሳይ ምሳሌ ቢቀመጥ እንደሚሻል በማመን "ወንጀለኛው ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ በእውነት የተፀፀተ መሆኑን" የሚለው ሀረግ መንደርደሪያ ሆኖ "በተለይም" በሚል ምሳሌዎቹ እንዲዘረዘሩ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

እንዲሁም "ለፍርድ ባለሥልጣን" የሚለው ሀረግ ጠባብ በመሆኑ ሀረጉ ተሰርዞ "ለፍትህ አካላት" በሚል ተተክቷል::

ከዚህም በላይ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ቀርቦ የክስ ማመልከቻ ከተነበበለት በኋላ ክሱን ሳይቃወም በክስ ማመልከቻው ላይ የተቀመጠውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ የዐቃቤ ህግም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች እንዲቀርቡ ሳይደረግና ረዥም ጊዜ ሳይወስድ ፍርድ ቤቱ ፍርድ ለመስጠት ስለሚያስችለውና ተከሳሾች እውነቱን እንዲናገሩ ስለሚያበረታታ፣ ይህ ሁኔታ እንደቅጣት ማቅለያ ምክንያት እንደሚቆጠር የሚደነግግ አዲስ ሀረግ በተራ ፊደል (ሠ) መጨረሻ ላይ እንዲገባ ተደርጓል::

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፸፱ ንዑስ ቁጥር (፪) ይዘት ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና የተሻለ አቀራረብ እንዲኖረው ተደርጓል::

ቀጽ ፹፫ <u>ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች፤ ዝምድናና የጠበቀ ወዳጅነት፡</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፫ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጹን ስያሜ በሚመለከት የአንቀጽ ፹ ስያሜ "ጠቅላላ የቅጣት ማቃለያ ምክንያቶች" የሚል ከሆነ የአንቀጽ ፹፫ ስያሜም በንጽጽር ሲታይ "ልዩ ቅጣት ማቃለያ ምክንያቶች" ሊል ይገባዋል:: ይህ አንቀጽ "በዝምድና ወይም ጥብቅ በሆነ ወዳጅነት ስለተሳሰረ ግንኙነት" ብቻ የሚደነግግበት ምክንያት የለም:: ይህ ግንኙነት ከልዩ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አንዱ መሆኑን አንቀጽ ፹፫ ማሳየት እንጂ ይህንን ነጥብ ብቻ እንደልዩ ማቅለያ ምክንያት አድርጎ ሊደነግግ አይገባም:: በመሆኑም በአንቀጽ ፻፹ መሠረት ቅጣት እንዲቃለል የታዘዘባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ልዩ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሆናቸውን በማካል አንቀጽ ፹፫ ስለዝምድና እና ስለጠበቀ ወዳጅነት ብቻ ሳይሆን እነዚህንም ተጨማሪ ማቅለያ ምክንያቶች በአጭሩ እንዲያጠቃልል ተደርጎ ተቀርጿል::

ቀጽ ፹፬ <u>ቅጣትን የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች፤</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹፩ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፬ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ሕግ ቁጥር ፹፩ ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሀ) ውስጥ ጥላቻ ከሚለው ቀጥሎ በሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጂ ትርጉም "ስግብግብነት" የሚል ቃል በመኖሩ ይኸው ተጨምሮ ከሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጂ ጋር በሚጣጣም መልክ የሌሎችም ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የተሻለ አገላለጽ እንዲኖረው ተደርጓል::

በዚሁ ንዑስ ቁጥር (፩) ፊደል (ለ) ላይ የሚገኘው ይዘት ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር ተቀባይነትን አግኝቷል::

የዚሁ ንዑስ ቁጥር (፩) ፊደል (ሐ) ግልጽነት ስለሚጎለው ይዘቱን በሚገባ ማንጸባረቅ ይቻል ዘንድ የቃላት ማስተካከያም ሆነ የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል::

---

ዑስ አንቀጽ (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ "እንደሆነ" ከሚለው ቃል በፊት "ሆነ" የሚለው "የሆነ" ተብሎ ነብ::

www.abyssinialaw.com


በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (መ) የተመለከተው ከሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጂ ጋር ሲወዳደር ብዙ ነገሮች እንደሚጎድሉት በመረጋገጡ እነዚሁ የጎደሉት ነገሮች ተሟልተውና የአንዳንድ ቃላት ለምሳሌም "ወንበዴ" የሚለው ቃል የሕጉን መንፈስ እንዳያጠበው በማሰብ ቃሉ ተሰርዞ "ወንጀል ለመስራት ከተቋቋመ ቡድን" በሚል እንዲተካ ተደርጎ የተሻለ አቀራረብና ይዘት እንዲኖረው ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሠ) "ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ወይም ወደላይ የሚቆጠር ወላጅ በሆነ ሰው" የሚለው ሀረግ የሕጉን የአተረጓጎም መንፈስ ሊያጠበው ስለሚችል ሀረጉ ተሰርዞ "በቅርብ ዘመዱ" በሚል ሐረግ እንዲተካ ተደርጓል:: እንዲሁም የኃይማኖት ባለሥልጣን በሆነ" የሚለው ሐረግ መንግሥት ከሌሎች ሰዎች የተለየ ጥበቃ ለኃይማኖት ባለሥልጣን የማያደርግ በመሆኑ ሀረጉ ተሰርዟል:: ከዚህም ሌላ "በሕገ መንግሥት በተቋቋመ ሥልጣን" የሚለው አገላለጽ ሕገ መንግሥት በደረጃው ከፍ ያለ ሕግ ከመሆኑ በቀር "ሕግ" በሚለው ቃል ስለሚሸፈን ተሰርዞ "በሕግ" በሚል ንዑስ ሀረግ ተተክቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ግልጽ ባለመሆኑ የተሻለ አቀራረብ ተደርጎበታል::

## አንቀጽ ፹፭ <u>ልዩ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች፤ የወንጀሎች መደራረብና ደጋጋሚነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹፪ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (፩) "ሀ" እና "ለ" ቀደም ሲል ስለተደራራቢ ወንጀሎች እና ስለደጋጋሚነት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷ እና ፷፯ ተቀርጾ ስለገባ እዚህ ላይ በድጋሚ መጻፍ አላስፈለገም:: ነገር ግን አንቀጽ ፹፬ ስለጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት የደነገገ እንደመሆኑ መጠን የዚህ አንቀጽ ስያሜ በንጽጽር ስለልዩ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች እንዲል ሆኖ ተደራራቢ ወንጀሎችን መፈጸምና ደጋጋሚነት ልዩ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሆናቸውን በሚያሳይ መልክ ተቀርጿል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፹፪(፪) አድራጊው ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሆኖ በተደራረቡ ወንጀሎች ጥፋተኛ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ስለተደራረቡት ወንጀሎች ቅጣትን ይወስናል የሚል ሲሆን ሙሉ በሙሉ የቅጣት ስሌት አወሳሰንን የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ ይልቅ በሁለተኛው መጽሐፍ ሥር ከአንቀጽ ፻፹፰ (፪) እንዲካተት ተደርጓል::

## አንቀጽ ፹፮ <u>ሌሎች ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹፫ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለሌሎች አጋጣሚ ምክንያቶች" ይል የነበረው "ሌሎች ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች" በሚል ተተክቷል:: ምክንያቱም የአንቀፁ ይዘት ሁለቱን ምክንያቶች ብቻ ሊያካትት የሚገባ በመሆኑ ነው::

ሕጉ በግልጽ ካስቀመጣቸው ከተደራራቢ ወንጀሎችና ከደጋጋሚነት በቀር ሌሎች ልዩ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ፍርድ ቤቶች እንዲፈጥሩ ሕጉ ይፈቅድላቸዋል ተብሎ ስለማይታመን ይህ አንቀጽ ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶችን ብቻ እንዲያካትት ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹፩ ድንጋጌ የቦታ አቀማመጥ ለውጥ</u>

ይህ ድንጋጌ በይበልጥ ተስማሚ ቦታው የቅጣት አወሳሰንን በሚመለከተው ምዕራፍ ውስጥ በመሆኑ ከዚህ ወጥቶ አንቀጽ ፻፹፱ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል::

## ሁለተኛ መጽሐፍ
## የወንጀል ቅጣትና አፈጻጸሙ
## ርዕስ አንድ
## ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች፣ እንዲሁም አፈፃፀማቸው
## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

የዚህ ምዕራፍ ስያሜ አዲስ ሲሆን በርዕሱ ስር የሚገኙትን ሦስት አጠቃላይ አንቀጾች የሚመለከት ነው:: የርዕሱ መግቢያ አንቀጾች በቀድሞው ሕግ ላይ በነበሩበት ሁኔታ ከሚቀመጡ ይልቅ ራሱን በቻለ ምዕራፍ ስር እንዲገቡ ማድረጉ በአቀራረጽ ሥርዓት ደንብ መሠረት ተገቢ መሆኑ ይታመንበታል:: የዚህ ዓይነቱ የምዕራፍ አከፋፈልም ለግልጽነት እንደሚረዳ ይገመታል::

ቀጽ ፹፯ <u>መርህ</u>

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፯ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ ስያሜ "መሠረቱ" የሚለው፣ "መርህ" በሚለው ቃል ተተክቷል::

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ በአንድ ፓራግራፍ የተጠቃለሉት ሁለት ዓረፍተ-ነገሮች በሁለት ፓራግራፎች እንዲከፈሉ ተደርጓል:: ይህም የሆነው፣ እያንዳንዱ ዓረፍተ-ነገር ራሱን የቻለ ፍሬ ሃሳብ ስለያዘ ነው::

ይዘቱን በተመለከተ አንዳንድ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል:: እንዲሁም "በዚህ ሕግ የተመለከቱት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች፣ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን አላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈጸም አለባቸው" ለሚለው ለመጀመሪያው ፓራግራፍ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበው አላማ በሕጉ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ስለሆነ ይኸው አንቀጽ (፩) ተጠቅሷል::

ቀጽ ፹፰ <u>የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን</u>

የተሻረው ሕግ የቁጥር ፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "በፍርድ ቤት የሚወሰን ቅጣት" የሚል ነበር:: ይህ አገላለጽ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እንደቅጣት የሚቆጥር በመሆኑ አገላለጹ ተሻሽሎ "የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን" በሚል ተተክቶአል::

ይዘቱንም በተመለከተ በ፲፱፻፵፱ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሁለት ፓራግራፎች ተከፍለው የተደነገጉት በሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲከፈሉ ከተደረገ በኋላ ግልጽ

www.abyssinialaw.com



ለማድረግ አንዳንድ የቃላት እና የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ማሻሻያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነው ገብተዋል::

ይህ አንቀጽ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲታከሉበት የተደረገ ሲሆን የንዑሳን አንቀጾቹ ይዘት እንደሚከተለው ነው:: አዲሱ የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ፣ "የዚህ ህግ የልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት ይወስናል::" የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቶች እያንዳንዱን ጉዳይ በጥልቀት እያዩ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲወስኑና ያለአግባብ ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ቅጣት እንዳይጥሉ መመሪያ የሚያስቀምጥ ነው::

የአዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ደግሞ፣ "የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) ያወጣል::" በማለት የሚደነግግ ነው::

አንቀጽ ፹፱ <u>በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፱ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "እጅግ ቀላል ስለሆኑ ጉዳዮች" ይል ነበር:: ሆኖም በይበልጥ ተስማሚ መሆኑ በሚታመንበት ሀረግ "በጣም ቀላል የሆኑ ወንጀሎች" በሚል ተተክቷል::

ድንጋጌው አዲስ ሁለተኛ ፓራግራፍ ታክሎበታል::

በተግሳጽ፣ በማስጠንቀቂያ ሊታለፍ የሚገባው ጥፋተኛ በጣም ቀላል ወንጀል የፈጸመ ብቻ ሊሆን ይገባል:: አንድ ወንጀል ግን በጣም ቀላል መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ለፍርድ ቤቶች ከመተው ይልቅ ሕግ አውጪው ቢወስን የተሻለ መሆኑ ታምኖበታል:: በዚህ መሠረት እስከ ሰስት ወር ድረስ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በጣም ቀላል ወንጀሎች እንደሆኑ በመቁጠር በተግሳጽ ወይም በማስጠንቀቂያ ሊታለፉ መቻላቸውን በግልጽ መደንገጉ ጠቃሚ ስለሆነ በዚህ መሠረት ተቀርጿል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>ለአካለመጠን በደረሱ ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ መደበኛ ቅጣቶች</u>

ይህ ምዕራፍ በቀድሞው ሕግ ምዕራፍ አንድ ነበር:: ሆኖም ከአንቀጽ ፹፯-፹፱ ያሉት ድንጋጌዎች በምዕራፍ አንድ ስር እንዲሆኑ በመደረጉ የዚህ ምዕራፍ ቁጥር ተሸጋሽጎ ምዕራፍ ሁለት ሆኗል::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል አንድ
## ዋና ቅጣቶች
## ንዑስ ክፍል አንድ
## የገንዘብ ቅጣቶች
## ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ
## መቀጮ፣ንብረትን መውረስና መያዝ

### ቀጽ ፹፰ መቀጮ፣ የመቀጮ አወሳሰን መርሆዎች

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "መቀጮ፣ መሠረቱ" የሚል ነበር፡፡ የውስጥ ይዘቱ የሚያመለክተው የመቀጮ አወሳሰን እንዴት መሆን እንዳለበት ስለሆነና ቀደም ሲልም "መሠረቱ" የሚለው "መርህ" በሚል የተተካ በመሆኑ እንዲሁም የመቀጮ አወሳሰን መርሆች ከአንድ በላይ በመሆናቸው ስያሜው ይዘቱን በተሻለ ሁኔታ እንዲገልጽ በማሰብ "መቀጮ፣ የመቀጮ አወሳሰን መርሆዎች" በሚል እንዲተካ ተደርጓል፡፡

ድንጋጌው በሶስት ፓራግራፍ ተጽፎ የነበረ ሲሆን በዚህ ሕግ በአራት ንዑስ አንቀጾች እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

በቀድሞ ሕግ በቁጥር ፹፮ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓረፍተ-ነገሮች የተደነገገው ፍሬ ነገር እንዳለ ተቀባይነት አግኝል፡፡ በሶስተኛው ዓረፍተ-ነገር "ሕጉ ተቃራኒ ውሳኔ ካልደነገገ በቀር" የሚለው ሀረግ በዚህ የወንጀል ሕግ ብቻ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ መስሎ ስለሚታይና በሌሎች ሕጎችም ተቃራኒ ድንጋጌ ሊኖር ስለሚችል ሐረጉ "ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር" በሚል ተተክቶአል፡፡ እንዲሁም በዚሁ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ "ካንድ የኢትዮጵያ ብር እስከ አምስት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ለመድረስ ይችላል" በማለት የተደነገገው የቅጣቱ መነሻም ሆነ መድረሻ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ጥፋተኛው ግለሰብ ሲሆን "ከብር አስር እስከ ብር አስር ሺህ" ጥፋተኛው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ደግሞ "ከአንድ መቶ ብር እስከ አምስት መቶ ሺህ" ሊደርስ ይችላል በሚል ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሆኗል፡፡

የሶስተኛ ፓራግራፍ አሳብ በሁለተኛው ፓራግራፍ የተካተተ በመሆኑ ሶስተኛው ፓራግራፍ ተሰርዟል፡፡ በመሆኑም የሁለተኛው ፓራግራፍ አነጋገር በመጠኑ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል፡፡

አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሦስት ተጨምሯል፡፡ ይኸውም የሕጉ ልዩ ክፍል የእስራትን ቅጣት አስቀምጦ መቀጮን በአማራጭ በሚደነግግበትና ተቀጪው የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ እስራቱ ወደ መቀጮ የሚለወጥበትን ሁኔታ የሚያመላክት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት እስከ አምስት አመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አስር ሺህ፣ እስከ አምስት አመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃያ ሺህ ብር፣ ከአምስት እስከ አስር አመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ሃምሳ ሺህ ብር፣ ከአስር አመት ጽኑ እስራት በላይ ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ሆኖ ተመልክቷል፡፡---

www.abyssinialaw.com



ከላይ እንደተመለከተው የእስራቱ ጊዜ ርዝመት ከመቀጮ መጠን ጋር እየተነጻጸረ ሊለወጥ የቻለው በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፭፻፲ እና ፭፻፳፯ የተደነገጉትን የእስራትና የመቀጮ መጠን በማስተያየት እንዲሁም የአሁኑን የገንዘብ ዋጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው::

ከዚህም በላይ በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ መቀጮ ብቻ በተደነገገ ጊዜ እና ተቀጪው የሕግ ሰውነት ያለው አካል በሆነ ጊዜ አወሳሰኑ የተመለከተውን መቀጮ አምስት እጥፍ በማድረግ እንደሚሆን የተመለከተበት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ገብቷል::

አንቀጽ ፺፩ <u>መቀጮን ከእሥራት ጋር ማጣመር</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፹፱ ድንጋጌ አንቀጽ ፺፩ ሆኖ የገባ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

ስያሜው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት "መቀጮን ከእስራት ጋር ማጣመር" እንዲል ተደርጓል::

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፹፱ የመጀመሪያው ፓራግራፍ መቀጮ እና እስራት በልዩ ክፍሉ ውስጥ በጣምራነት ተደንግገው እንደሆነ የሚል መልዕክት ያስተላልፋል:: ነገር ግን የፈረንሳይኛውና የእንግሊዝኛው ቅጂዎች መቀጫና እስራት በአማራጭነት ተደንግገው በሚገኙ ጊዜ ለማለት በመሆኑ "ከግል ነጻነት የመወሰን ቅጣትና የገንዘብ መቀጮን በማረጋገጥ ደንግጎ እንደሆነ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "መቀጮንና እስራትን በአማራጭ የደነገገ እንደሆነ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

የሁለተኛው ፓራግራፍ ይዘት ግን በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ የተካተተ በመሆኑ በድጋሚ ሊፃፍ ስለማይገባው ተሰርዟል::

አንቀጽ ፺፪ <u>አፍቅሮ ንዋይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መሆኑ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፺ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፪ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞ ስያሜው "ቅጣትን ስለማክበድ በአፍቅሮ ንዋይ ስሜት ገንዘብ ስለማግኘትና የወንጀልን ሥራ ሞያ ስለማድረግ" የሚል ነበር:: ነገር ግን የውስጥ ይዘቱ የሚገልጸው አፍቅሮ ንዋይ የቅጣት ማክበጃ የሚሆነው የወንጀል ድርጊቱን እንደ ሙያ በመያዙ ወይም በመደጋገሙ ብቻ ሳይሆን የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ስሜት ተነሳስቶ በሚሆንበት ጊዜ ጭምር ስለሆነ "አፍቅሮ ንዋይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መሆኑ" በሚል ስያሜ ተተክቷል::

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) የተገለጸው በሶስት ፓራግራፎች የተከፈለው ፍሬ ነገር በሁለት ፓራግራፎች ብቻ ሙሉ አሳቡን ማስተላለፍ ስለሚቻል በሁለተኛው ፓራግራፍ ውስጥ የነበረው ፍሬ ነገር የንዑስ አንቀጹ መንደርደሪያ እንዲሆን በማሰብ "በተለይ ከፍ ያለ ቅጣት የሚወስኑት የልዩ ድንጋጌ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው "በሚል እንዲጀምር ተደርጓል:: እንዲሁም መቀጮው እስከ አስር ሺህ ብር ይል የነበረው ለአንዳንድ ወንጀለኞች ቅጣቱ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ በመሰለው

www.abyssinialaw.com


ጊዜ ሁሉ እነዚህን ወንጀለኞች ለመቅጣት የሚያስችል ሰፋ ያለ ስልጣን መስጠት እንደሚያስፈልግ በማመን "እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ የሚደርስ መቀጮ ሊወሰንበት ይችላል::" በሚል ተሻሽሎአል:: በተጨማሪም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ ሦስተኛ ፓራግራፍ የነበረው ሁለተኛ ፓራግራፍ እንዲሆን ተደርጎ መቀጮው የሚወሰነው በወንጀል ደርጊት ከተገኘው ንብረት መውረስ በተጨማሪ መሆኑን በግልጽ እንዲያመለክት ተደርጎአል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ፍሬ ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፲፫ መቀጮን ማስገባት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፫ ሆኖ የገባ ሲሆን እንደሚከተለው ተስተካክሏል::

የድንጋጌው ስያሜ "የመቀጮ ገንዘብን ስለ ማስገባት" ይል የነበረ ሲሆን "መቀጮን ማስገባት" በሚል ተስተካክሏ፤ ምክንያቱም "መቀጮ" የሚለው ቃል በገንዘብ የሚከፈል ቅጣትን እንደሚያመለክት ግልጽ በመሆኑ ነው::

ይዘቱን በተመለከተ የሚከተለው ማሻሻያ ተደርጎበታል::

መቀጮ ወዲያውኑ መከፈል እንዳለበት የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል:: የመቀጮውም የመክፈያ ጣራ የሦስት ወር ጊዜ ባንዳንድ ሁኔታ ላይ ሊያንስ ስለሚችል ወደ ስድስት ወር ከፍ እንዲል ተደርጓል::

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሦስት እንዲሆን ተደርጓል:: የመክፈያው የሁለት ዓመት ጣራ ጊዜም ባንዳንድ ሁኔታ ላይ እስከ ሶስት ዓመት ሊራዘም እንደሚችል ተደንግጓል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፪ እና ፲፫ ድንጋጌዎች የቦታ አቀማመጥ መለዋወጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፪ እና የቁጥር ፲፫ ድንጋጌዎች የነበሩበት ቦታ እንዲለዋወጥ ተደርጓል:: የቁጥር ፲፪ ስያሜ "የመቀጮውን ገንዘብ በሥራ ስለማስከፈል" የቁጥር ፲፫ ስያሜ ደግሞ "የግዴታው ዋስትና" የሚል ሲሆን መቀጮ መክፈል ያቃተው ጥፋተኛ መቀጮ በስራ በተለወጠ ጊዜ ይህንን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ የዋስትና ግዴታ እንዲገባ ወይም ንብረቱ እንደሚያዝ ወይም እንደሚሸጥ የሚደረግ መሆኑን ድንጋጌዎቹ ያስረዳሉ ይህ ግን ትክክል ሆኖ አይታይም:: ስራ በመስራት ሂሳቡ እየተተመነለት መቀጮውን በዚህ መልክ መክፈል የተቀጪውን ሰብአዊ ነፃነት እንደሚነካ የታወቀ ነው:: የዋስትና ግዴታ መግባቱና ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲሸጥ ማድረጉ ግን ከንብረቱ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው:: አንድ ሰው በንብረት ላይ ባለው መብት ረገድ ከሚቀጣ ይልቅ ሰብአዊ ነፃነቱን ማ

ነዑስ አንቀጽ (፫) በፊደል (መ) "በአስተዳዳሪነት፣ ሥራ አስኪያጅ" የሚለው ቃል "በአስተዳዳሪነት፣ በሥራ ...ያጅ" ተብሎ ይነበብ::

www.abyssinialaw.com


ጣቄ ይብስበታል። ስለዚህ ቅደም ተከተላቸውን ማለዋወጡ አስፈላጊ በመሆኑ የንብረትን መብት በሚመለከት የተደነገገው የቁጥር ፺፫ ድንጋጌ አንቀጽ ፺፬ እንዲሆን፣ ሰብአዊ ነፃነትን የሚያሳጣው የቁጥር ፺፪ ድንጋጌ ደግሞ አንቀጽ ፺፭ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፺፬ ወዲያውኑ መቀጮ በማይከፈልበት ጊዜ ፍርድ ቤት የሚወስደው እርምጃ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፺፫ ድንጋጌ ስያሜና ይዘት ማሻሻያ ተደርጎባቸው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፬ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ የዋስትና ግዴታን ብቻ ሳይሆን የንብረት መያዝን ወይም መሸጥን እንዲያጠቃልል ስለተደረገ "የዋስትና ግዴታ" የሚለው የቀድሞው ስያሜ ተሰርዞ ከላይ የተመለከተው እንዲሆን ተደርጓል።

ይዘቱን በተመለከተ የቀድሞው ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎባቸው ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት ሆነው ገብተዋል።

ጥፋተኛው በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተደነገገው መሠረት ያልፈጸመ እንደሆነ ባልከፈለው መቀጮ መጠን ንብረቱ በሕግ መሠረት ተይዞ እንዲሸጥ ፍርድ ቤቱ እንዲወስንና የንብረቱም ሽያጭ በሚፈጸምበት ጊዜ በዚህ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ ፺፰ (፫) የተደነገገው ተፈጻሚ እንደሚሆን የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ገብቷል።

አንቀጽ ፺፭ መቀጮውን በስራ መለወጥ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፺፪ ድንጋጌ ስያሜና ሁለት ፓራግራፎች ማሻሻያ ተደርጎባቸው ድንጋጌው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፭ ሆኖ ገብቷል። መቀጮውም በስራ ሲለወጥ ለተቀጪው የሚተመንለት የቀን ሂሳብ ከአንድ ብር አያንስም የሚለው ቀርቶ "የመቀጮውን መጠን ከግምት በማስገባት መቀጮው ተከፍሎ የሚያልቅበትን ጊዜም ይወስናል" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል። በተጨማሪም የሚወሰነው ጊዜ ከሁለት ዓመት እንዳይበልጥ ተደርጎ ተቀርጿል።

የተቀጪው የቀን ገቢ እየተተመነ መቀጮው በጉልበት ወይም በአእምሮ ስራ እየተለወጠ በዚሁ ስሌት መሠረት ጥፋተኛው የሚሰራበት ጊዜ የሚወሰን ከሆነ በዚህ ዓይነት ውሳኔ የሚጎዳው የቀን ገቢው አነስተኛ የሆነ ሰው ነው። በቀን ሶስት መቶ እና አራት መቶ ብር የሚያገኝ ሰው የተወሰነበትም መቀጮ በስራ በማገልገል እንዲከፍል ሲወሰንበት በዕለት ገቢው መጠን ስለሆነ የተጣለበት መቀጮ ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ በጥቂት ወሮች ውስጥ ስራ በመስራት መቀጮውን ከፍሎ ሊጨርስ ይችላል። ነገር ግን የቀን ገቢው ብር አስር እና ብር አስራአምስት የሆነ ሰው በዚሁ መሠረት እየተተመነለት በጉልበቱ እያገለገለ የተጣለበትን መቀጮ ይክፈል ቢባል፣ ብዙ ዓመታት ሊወስድበት የሚችል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህ አንቀጽ ከፍተኛ ለውጥ የተደረገበት ምክንያት የዚህ ዓይነቱን ኢ-ፍትሐዊ ልዩነት ለማስቀረት ነው።

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፺፬ ድንጋጌ መሰረዝ

አንድ ጥፋተኛ የተወሰነበትን መቀጮ መክፈል ባልቻለ ጊዜ ወደ እስራት እንዴት እንደሚለወጥ በድንጋጌው ላይ ተመልክቶ ነበር። ነገር ግን መቀጮ ተወስኖበት በልዩ ልዩ

www.abyssinialaw.com



መንገድ እንዲከፍል የተደረገው ጥረት ፍሬ ባላስገኘ ጊዜ መቀጮው በእስራት እንዲለወጥ ማድረጉ ፍትሐዊ አይደለም። ገንዘብ ካላቸው ሰዎች ይልቅ ድሃውን ወገን የሚጎዳ የቅጣት አፈጻጸም ነው። በመሆኑም ድንጋጌው ሊሰረዝ ችሏል።

ጽ ፺፮ <u>መቀጮን በግዴታ ሥራ መለወጥ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቁጥር ፺፮ ድንጋጌ አንቀጽ ፺፮ ሆኖ የገባ ሲሆን ከፍተኛ ለውጥ ተደርጎበታል። በቀድሞው ድንጋጌ መሠረት የግዴታ ስራ እንዲሰራ የሚወሰንበት ሰው ጥፋቱ ቀላል ሲሆን ነው። በዚህ አንቀጽ መሠረት ግን ጥፋቱ ቀላልም ይሁን ከበድ ያለ፣ የመቀጮውም መጠን አነስተኛ ይሁን ከፍ ያለ፣ መቀጮውን መክፈል ያቃተው ሰው በአንቀጽ ፻፫ እና ፻፬ ዓይነት የግዴታ ስራ እንዲሰራ ሊፈረድበት ይችላል። ፍርድ ቤቱም የጊዜውን ልክ መግለጽ ያለበት ሲሆን፣ የሚወሰነው ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል። አንቀጹ በዚህ መልክ ሊቀረጽ የቻለው፣ የጥፋተኛው ጉልበት ወይም አእምሮ ለረዥም ጊዜ ያለአግባብ እንዳይበዘበዝ ከማድረጉም በላይ የተለያየ የገንዘብ ማግኘት አቅም ባላቸው ሰዎች ማካከል ያለውን ልዩነት የተቻለውን ያህል ለመቅረፍ ታቅዶ ነው።

ጽ ፺፯ <u>የግዴታ ስራ አፈጻጸምን ማቆም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፺፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፯ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ ከቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ቢሆንም በይዘት ረገድ እንደ አዲስ የሚቆጠር ነው። በቀድሞው ድንጋጌ መሠረት መቀጮ ወደ ቀላል እስራት ከተለወጠ በኋላ በአንዳንድ ምክንያት ቅጣቱ በአንቀጽ ፻፺፪ መሠረት ሊታገድ እንደሚችል ተደንግጎ ነበር። ይህ አንቀጽ የሚደነግገው ግን መቀጮው ወደ ግዴታ ስራ ከተለወጠ በኋላ በድህነቱ፣ ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ባለበት ኃላፊነት፣ በጤንነቱ ወይም በማናቸውም ተገቢ በሆነ ምክንያት ቅጣቱን መቀጠል ካልቻለ የግዴታው ስራ አፈጻጸም ሊያቆም እንደሚችል ነው። ይህም አስተሳሰብ ፍትሐዊ ስለሆነ ይደገፋል።

ከዚህም በላይ የግዴታ ስራ በመፈጸም ላይ የሚገኝ ጥፋተኛ ቢታመም፣ የግዴታ ስራው ስለሚታገድበት እና ከህመሙ ሲድን ስለሚወሰደው እርምጃ የዚህ ህግ የአንቀጽ ፻፭ ድንጋጌ ለዚህ አንቀጽም ተገቢነት ስለሚኖረው፣ "የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፻፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል።

ቶጽ ፺፰ <u>ንብረት መውረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፰ ሆኖ ገብቷል።

የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል።

በቁጥር ፺፰ (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የሰፈረው ፍሬ-ነገር ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ የተካተተ በመሆኑ ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል እንዲሰረዝ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com


በሁለተኛው ፓራግራፍ የሰፈረው ፍሬ-ነገር ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል።
በንዑስ ቁጥር (፫) (ሀ) ላይ " ፍጹም አስፈላጊ የሆኑ" የሚለው ሀረግ "አስፈላጊ የሆኑ" በሚል ተተክቷል።

በንዑስ ቁጥር (፫) (ለ)" ቢበዛ ለሶስት ወር ጊዜ" ይል የነበረው በአንዳንድ ሁኔታዎች ከላይ የተገለጸው ጊዜ እጅግ ሊያንስ ስለሚችል "ለስድስት ወር ጊዜ" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፫) (ሐ) የሰፈረው ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

በቁጥር ፲፯ (፫) (መ) ንጹህ የሆነው የወንጀለኛው ባለቤት ከማይወረሱበት ንብረቶች ውስጥ አንዱ ከጋራ ሀብታቸው ግማሹን የሚመለከት አነጋገር ስለሌለው ይኸው አሳብ እንዲካተት ተደርጓል።

"የልጆቹና የሚስቱ...." ይል የነበረውም ከወንጀሉ ንጹህ የሆነውን የባል ንብረት የማይጠብቅ በመሆኑ እንዲሁም ምንጊዜም ቢሆን ወንጀለኛ ሊሆን የሚችለው ባል ነው የሚለውን አሳብ የሚያስተላልፍ መስሎ የሚታይ በመሆኑ ተሻሽሎ "የወንጀለኛው ባለቤት፣ ወይም ልጆች..." በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

በተጨማሪም የሌሎች ንጹሃን ሰዎች ንብረት መወረስ እንደሌለበት በፊደል (መ) ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል።

አንቀጽ ፲፱ <u>ንብረትን መያዝ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ንብረትን ስለማስያዝ" የሚል ነው። ሆኖም ይዘቱ እንደሚያመለክተው ንብረቱን የሚያሲዘው ወንጀለኛው ሳይሆን የሚይዝበት ሌላ ሕጋዊ አካል በመሆኑ ስያሜው ይዘቱን ማመልከት እንዲችል "ንብረትን መያዝ" እንዲል ተደርጓል።

ይዘቱን በተመለከተ በቁጥር ፲፰ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ውስጥ "ማንም ሰው" ከሚለው ቀጥሎ "በንጉሠ-ነገሥቱ ግዛት ላይ ወይም በንጉሠ-ነገሥቱ ላይ" የሚሉት ሀረጎች እንዲሰረዙ ተደርጎ በምትኩ አሁን ካለው ሁኔታ ጋር በማጣጣም "በአገሪቱ ሕገ መንግስታዊ ስርአት ወይም በውስጥና በውጭ ደህንነት ላይ" በሚሉ ሀረጎች እንዲተኩና አንዳንድ ሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቀርጿል።

<u>ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶች</u>

አንቀጽ ፳ <u>ለመንግሥት ገቢ ሊሆን የሚገባው ሀብት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳ ሆኖ ገብቷል።
በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ሊሰጠው የታቀደው "የሚል ሀረግ እንዲገባ ሆኖአል።

www.abyssinialaw.com

ይህም ምንም እንኳን ጥቅሙ ወንጀሉን በፈጸመው ሰው እጅ ባይገባም ለወንጀል ማስፈጸሚያ አላማ ታቅዶ ገቢራዊ ያልሆነውን ጥቅም ለመውረስ ያስችላል ተብሎ ነው:: እንዲሁም "የስጦታ ገንዘብ" የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምክንያቱም በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለው ሀረግ ማናቸውም ጥቅም ሁሉ በሚለው ሀረግ ሊሸፈን ስለሚችል ነው::

የንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍም ቢሆን ከላይ በመጀመሪያው ፓራግራፍ በተሻሻለው አኳኋን ሆኖ "የተባለውም ንብረት" የሚለው የፓራግራፉ የመጀመሪያ ዐረፍተ-ነገር ተሰርዞ "የተሰጠው ወይም ሊሰጠው የታቀደው ጥቅም" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

ከዚህ በተጨማሪ የቁጥር ፲፱ ንዑስ ቁጥር (፪) ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ ሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲሆን ተደርጓል::

የተያዘው ንብረት የሚበላሽ ከሆነ ተሸጦ ገንዘቡ የሚቀመጥበትን ሁኔታ የሚደነግግ አዲስ ዓረፍተ-ነገር በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ገብቷል::

ቶጽ ፲፩ <u>ንብረትን መተካት ወይም የጉዳት ካሣና ኪሣራን መክፈል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ ጉዳት ካሣ" የሚል ነው:: ነገር ግን ይዘቱ የሚያመለክተው ስለ ጉዳት ካሣ ብቻ ሳይሆን ንብረትን ስለመተካትና ስለ ኪሳራም ጭምር በመሆኑ ስያሜው ይዘቱን የሚያመለክት እንዲሆን ተሻሽሎ "ንብረትን ስለመተካት ወይም ስለጉዳት ካሣና ኪሣራ" ተብሏል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲ ድንጋጌ፣ የፍትሐብሔር ሕግ ገና ባለመውጣቱ የፍትሐብሔር ነክ ነገሮችን በዝርዝር አስቀምጦ ነበር:: አሁን ግን የፍትሐብሔር ሕግ እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የታወጀ በመሆኑ ስለዝርዝሩ መደንገጉ አስፈላጊ አይደለም:: በመሆኑም በወንጀል ምክንያት ልዩ ልዩ ጉዳት የደረሰበት ተበዳይ ወይም የተበዳዩ ባለመብት የፍትሐብሔር ክስን ከወንጀሉ ጋር አጣምሮ ማቅረብ እንዲችልና ሁኔታውም በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደሚመራ የሚደነግግ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል::

ቶጽ ፲፪ <u>ለተበዳይ የሚሰጠው ካሣ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፪ ሆኖ ገብቷል::

በቁጥር ፲፩ ንዑስ ቁጥር (፩) በዳዩ ወይም ስለእርሱ መብት ያላቸው ለተበዳዩ ሊከሱ በማይችሉ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሊያዝባቸው ከሚችሉት አማራጮች ውስጥ "በዋስትና መያዣ ስም ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ" ከሚለው ሀረግ በተጨማሪ "ከመቀጮው ውስጥ" የሚል ሀረግ ተጨምሯል:: ይህም ተበዳዩ ሊካስበት የሚችለውን አማራጭ መንገድ ከፍ እንዲያደርግለት ያስችላል በማለት ነው::

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ስለካሣ መጠን አወሳሰን የሚመለከት የፍትሐብሔር ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ የወንጀል ሕግ ውስጥ ተሰርዟል::

www.abyssinialaw.com



በንዑስ ቁጥር (፫) ተደንግጎ የነበረው ፍሬ-ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ፻፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>የግዴታ ሥራ እና ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች</u>

የንዑስ ክፍል ሁለት ስያሜ "የግል ነፃነትን የሚቀንሱና የሚያሳጡ ቅጣቶች" የሚል ነበር። ሆኖም በግዳጅ ሥራ ላይ ነፃነት የማይገደብበት ሁኔታ ስላለ የግዳጅ ሥራ ጽንሰ አሳብ ስያሜው ሁለቱን አስተሳሰቦች አጠቃሎ ይዟል። ስለዚህ ስያሜው ተሻሽሎ "የግዴታ ሥራና ነፃነትን ስለሚያሳጡ ቅጣቶች" በሚል ተስተካክሎ ተረቅቋል። ምክንያቱም ልቅ የሆነ ነፃነት የትም ቢሆን የለም አስፈላጊ የሆነ ቁጥጥርም ነፃነትን እንደመገደብ አያስቆጥርም። በአንድ አይነት የግዳጅ ሥራ ላይም ቁጥጥር መኖሩ ነፃነትን እንደመገደብ አያስቆጥርም ተብሎ ስለሚታመን ነው።

## <u>ዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ</u>
## <u>የግዳጅ ሥራ</u>

የንዑስ ክፍል ሁለት የዝቅተኛ ንዑስ ክፍል አንድ ስያሜን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "የገንዘብ መቀጮ የሚያስከፍሉና ነፃነትን የሚያሳጡ የተቀላቀሉ ወንጀሎች" የሚል ነው። ይህ ስያሜ አልተደገፈም። ምክንያቱም ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ነፃነት የማይገደብበት የግዴታ ሥራ አለ። እንዲሁም የግዴታ ሥራ ሲባል ጥፋተኛው ሰርቶ ገቢ የሚያደርገውን ገንዘብ የሚያመለክት በመሆኑ አነጋገሩ አጠር ብሎ "የግዳጅ ሥራ" በሚል ተስተካክሏል።

### አንቀጽ ፻፫ <u>ከግዴታ ሥራ ከሚገኘው ገቢ ተቀንሶ ለመንግሥት የሚከፈል ገንዘብ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፪ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፫ ሆኗል።

የድንጋጌው ስያሜ ግልጽ እንዲሆንና ከእንግሊዝኛው ቅጂም ጋር እንዲጣጣም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ይዘቱንም በተመለከተ በቁጥር ፻፪ ንዑስ ቁጥር (፩) "ከፍ ያለ ከባድነት የሌለው ሆኖ" የሚለው ሀረግ ወንጀሉ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ ከተገለጸ "ከፍ ያለ ከባድነት" የሌለው መሆኑ የታወቀ ስለሆነ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዞአል። "ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት የሆነ እንደሆነ" በሚለው ሀረግ ውስጥ ከሶስት ወር በማይበልጥ የሚያስቀጣ ወንጀል በጣም አነስተኛ ክብደት ያለው ወንጀል መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ተሻሽሎ ይህ ሐረግ ሲነበብ "ወንጀሉ የሚያስከትለው ቅጣት ከስድስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት የሆነ እንደሆነ" የሚል ሆኖአል።

www.abyssinialaw.com


"ጥፋተኛውም... አደገኛ የማይመስል ሲሆን" የሚለው ሀረግ የጥፋተኛው አደገኛነት ለማን መሆኑን ስለማይገልጽ "ለህብረተሰቡ" የሚል ንዑስ ሐረግ አደገኛ ከሚለው ቃል በፊት እንዲገባ ተደርጓል።

በዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛው ላይ ሊወስንበት የሚችለው የግዴታ ስራ ቅጣት ከአንድ ቀን እስከ ሶስት ወር ሊደርስ የሚችል የሥራ ጊዜ ብቻ ሲሆን የግዴታው ስራ የቅጣት ጣሪያ አነስተኛ መስሎ ስለሚታይ "እስከ ሶስት ወር ሊደርስ የሚችል" በሚለው ሀረግ "ሶስት" የሚለው ቃል "ስድስት" በሚል ቃል እንዲተካ ተደርጎአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የተመለከተው ፍሬ ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገው "ከተቀጪው የድካም ዋጋ ወይም በስራ ፍሬ ከሚያገኘው ጥቅም እስከ አራት አንድ እጅ ሊደርስ የሚችል ሂሳብ እየተያዘ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል።" የሚል ነው። ከተቀጪው የድካም ዋጋ ወይም በስራው ፍሬ ከሚያገኘው ጥቅም እየተያዘ ለመንግሥት ገቢ የሚደረገው ሂሳብ ከፍተኛው ከአራት በአንድ እጅ ብቻ ቢወሰን በአንድ በኩል ወንጀለኞቹ በግዴታ ስራ ከሚያገኙት ገቢ ለመንግሥት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ ዘግይቶ እንዲገባ ማድረግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተቀጪው ወንጀለኛ በግዴታ ስራ ከድካም ዋጋ ወይም ከስራ ፍሬ የሚያገኘውን ጥቅም ከአራት ሶስት እጅ ይኸውም ከመቶ ሰባ አምስት ሳያንስ ለራሱ እንዲቀርለትና ከግዴታ ስራ ከሚያገኘው ጥቅም መክፈል የሚገባውን መቀጮ ያለመጠን ረጅም በሆነ ጊዜ ቀስ ብሎ እንዲከፍል ቢደረግ የመቀጮው ቅጣት እምብዛም ስለማይሰማው እስከ አራት አንድ እጅ የሚለው ሐረግ ተሰርዞ እስከ አንድ ሶስተኛ /ሲሶ/ በሚል ሐረግ ተተክቶአል። "እየተያዘ" የሚለውም ቃል "እየተቀነሰ" እንዲል ተደርጓል። ንዑስ ቁጥሩ በዚህ መልክ ተሻሽሎ ንዑስ ቀንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል።

በቁጥር ፴፪ ንዑስ ቁጥር (፫) የተደነገገው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑሰ አንቀጽ (፫) ሆኗል።

ዐጽ ፴፬ <u>የግል ነፃነትን ከመገደብ ጋር የሚወሰን የግዴታ ስራ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፴፫ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፬ ሆኖ ገብቷል።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፴፫ ስያሜ "የግል ነፃነትን ከመቀነስ ጋራ የሚወሰን የግዴታ ስራ" የሚል ነው። ሆኖም "የግል ነጻነትን ከመቀነስ ጋራ" ከማለት ይልቅ ገላጭነት እንዲኖረውና ከእንግሊዝኛውና ከፈረንሳይኛው ቅጂዎች ጋር ለማጣጣም ስያሜው ተሻሽሎ "የግል ነፃነትን ከመገደብ ጋራ የሚወሰን የግዴታ ስራ" በሚል ተተክቶአል።

ይዘቱንም በተመከለተ በንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑ በተጨማሪ ተቀጪው በአንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጣለበትን ግዴታ ባያሟላ በዚህ ንዑስ ቁጥር የተደነገገ ባለመኖሩ "በተለይም" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "በአንቀጽ ፴፫ (፩) መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ወይም" የሚል ተጨማሪ አሳብ ታክሎበታል።

www.abyssinialaw.com


በንዑስ ቁጥር (፪) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቀባይነት አግኝል።

በንዑስ ቁጥር (፫) በተመለከተው ድንጋጌ ውስጥ "በእስራት ይለወጣል" የሚለው የዓረፍተ-ነገሩ ማሰሪያ የእስራቱን ዓይነት እንዲያመለክት "እስራት" ከሚለው ቃል በፊት "ወደ ቀላል" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል።

አንቀጽ ፻፭ <u>በሕመም ጊዜ የግዴታ ሥራ ቅጣት የሚታገድበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፬ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፭ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ ድንገተኛ ህመም" የሚል ነበር። ሆኖም ይዘቱ የሚያሳየው ከድንገተኛ ሕመም ይልቅ ተቀጪው በግዴታ ሥራ ላይ እያለ ቢታመም የሚወሰደውን እርምጃ ስለሆነ ስያሜው ይህን የውስጥ ይዘቱን እንዲያንጸባርቅ ለማድረግ ተሻሽሎ "በሕመም ጊዜ የግዴታ ሥራ ቅጣት የሚታገድበት ሁኔታ" እንዲል ተደርጓል።

ይዘቱንም በተመለከተ ጥፋተኛው ከህመሙ ሲድን የግዴታ ስራውን እንዲቀጥል፤ ይህም ካልተቻለ ከግል ጤንነቱና ሁኔታው ጋር ተስማሚ የሆነ ማናቸውንም ስራ እንዲሰራ ከሚደረግ በቀር፣ የግዴታ ስራውን ወደ መቀጮ ወይም ወደ እስራት መለወጥ ትክክል ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም የቀድሞው ድንጋጌ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ተሰርዞ ከፍ ብሎ በተገለጸው መልክ ተቀርጿል።

ጥፋተኛው ከግል ጤንነቱና ሁኔታው ጋር ተስማሚ የሆነ ሌላ ስራ እንዲሰራ ቢታዘዝም፣ "የዚህ ዓይነቱን ትዕዛዝ መስጠት ወይም ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለ ፍርድ ቤቱ በተቀጪው ላይ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ቅጣት አይወስንም።" የሚል ዓረፍተ ነገር ገብቶአል። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ተቀጭው የተወሰነበትን መፈጸም ባልቻለ ጊዜ ምንም እርምጃ እንዳይወሰድበት ህግ አውጭው መደንገጉ ለተቀጪው ከፍተኛ አስተያየት ማድረጉን ያሳያል።

ከዚህም ሌላ የግዴታ ስራ ቅጣት እንዲታገድ የሚደረገው በህመም ብቻ ሳይሆን በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺፯ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ጭምር ሲያጋጥሙ መሆን ስለሚገባው፣ በአንቀጽ ፻፭ መግቢያ ላይ፣ "በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺፯ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ" የሚል ሐረግ እንዲካተት ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com


## ሁለተኛ ንዑስ ክፍል ሁለት
## የግል ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች

### ጽ ፻፮ ቀላል እስራት

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፭ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ ፻፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው "ስለ እሥራት" የሚል ነበር፡፡ ሆኖም "እስራት" የሚለው ቃል የትኛው የእስራት አይነት? የሚለውን ጥያቄ የማይመልስ በመሆኑ ይህን በግልጽ ለማመልከት ስያሜው ተሻሽሎ " ቀላል እስራት" እንዲል ሆኖአል፡፡

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ የተደነገገው ከላይ በስያሜው ላይ የተደረገ ማሻሻያና የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የሰፈረው ፍሬ-ነገር የወንጀል ሕግ ዓላማን በያዘው በአንቀጽ ፩ የተካተተ በመሆኑ ድግግሞሹን ለማስቀረት ሲባል እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ቁጥር ሦስተኛው ፓራግራፍ ላይ የሰፈረው የቀላል እስራት ጊዜ "ከአስር ቀን እስከ ሶስት አመት" በማለት የተደነገገው ባለበት እንዲቀጥል የተደረገ ሲሆን የንዑስ አንቀጽ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል፡፡

በአንቀጽ ፩፻፮(፩) ሦስተኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር የተገለፀው በተደጋጋሚ የመቀጣቱ ሃሳብ፣ በአንቀጽ ፷፮ ከተመለከተው በደጋጋሚ የመቀጣቱ ሃሳብ፣ ሰፋ ተደረጎ ሲተረጎም ይገባል፡፡ በአንቀጽ ፲፻፮(፩) መሠረት በተደጋጋሚ (Repeatedly) የተቀጣ ጥፋተኛ በአንቀጽ ፷፮ እና ፩፻፹፰ መሠረት በደጋጋሚነት (Recidivism) ቢያንስ ሦስት ጊዜ የተቀጣውን ጥፋተኛ እንደሚጨምር አያከራክርም፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው በልዩ ልዩ ወንጀሎች ሦስት ጊዜ ቢያንሰ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ቀላል እስራት በአንቀጽ ፷፮ በተገለፀው ሁኔታ ቢቀጣ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ተብሎ በአንቀጽ ፩፻፹፰ መሠረት ቅጣቱ ይከብድበታል፡፡ በአንቀጽ ፩፻፮ መሠረት አንድ ሰው ከተቀጣ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሌላ ወንጀል እየፈፀመ በዚህ መልክ ከአስር ቀን በማያንስ ከስድስት ወር በታች በሆነ ቀላል እስራት ሦስት ጊዘ ቢቀጣ በደጋጋሚነት (Recidivism) ተቀጥቷል ባይባልም በተደገጋሚ (Repeatedly) ተቀጥቷል የማይባልበት ምክንያት የለም፡፡ አንቀጽ ፩፻፮(፩) ሦስተኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገረ የተቀረፀው ሁለቱንም ሃሳሶቦች እንዲያጠቃልል ታቅዶ ነው፡፡ በመሆኑም "በተደጋጋሚ ሲቀጣ" የሚለው አነጋገር የስድስት ወር እና ከዚያ በላይ ወይም ከስድስት ወር በታች የሆነ ቀላል እስራት የሚወሰንበትን ጥፋተኛ ይመለከታል፡፡

የቅጣቱን ስሌት በተመለከተ ግን በአስር ቀን እና በስድስት ወር መካከል ቀላል እስራት በተደጋጋሚ የሚቀጣ ሰው በአንቀጽ ፩፻፮ (፩) ሦስተኛ ፓራግራፍ መሠረት ቀጣቱ እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት እንዴት ሊደርስ እንደሚችል በተጠቀሰውም ሆነ በሌላ አንቀጽ አልተደነገገም፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ጥፋተኛ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ ፩፻፹፰ መሠረት ቅጣቱን ማስላት የሚችል መሆኑ ወይም አለመሆኑ ያከራክራል፡፡ በአንድ በኩል "በሕግ ግልጽ ባልተደነገገ ጉዳይ ተከሳሽን የሚጎዳ የቅጣተ ስሌት መጠቀም አይገባም፤ በአንቀጽ 106 መሠረት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት መቅጣት የሚቻለው የስድሰት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ ወንጀል በደጋጋሚነት (Recidivism) ፈጽሞ

www.abyssinialaw.com

የተገኘውን ሰው እንጂ ከስድስት ወር በታች ቀላል እስራት በተደገጋሚ የሚቀጣውን ሰው አይደለም፤" የሚል ሃሳብ ሊቀርብ ይችላል:: በሌላ በኩል "በቀላል እስራት በተደጋጋሚ የሚቀጣ ሰው እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት ቅጣቱ ሊጨምርበት ይችላል የሚለው የአንቀጽ ፩፻፺(፩) አሳብ ስድስት ወር እና ከዚያ በላይ ለሚቀጡ፣ ማለትም የአንቀጽ ፹፮ እና ፩፻፹፰ ሁኔታዎችን ለሚያሟሉ ደጋጋሚ ጥፋተኞች ብቻ መሆኑን አያመላክትም:: ካላመላከተም ከስድስት ወር በታች በተደጋጋሚ የሚቀጡ ጥፋተኞችም እስከ አምስት ዓመት ቀላል እስራት ቅጣቱ ከፍ ሊልባቸው ይችላል ማለት ነው:: ወደዚህ ጣሪ ቅጣት መድረስ የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌ ከሌለ፣ ስለደጋጋሚነት የተደነገገው የአንቀጽ ፩፻፹፰ የቅጣት ስሌት በተመሳሳይነተ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል" የሚል አስተያየት ሊቀርብ ይችላል:: ፍርድ ቤት ያመነበትን አተረጓጎም ተግባራዊ የማድረግ ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እልባት ሊያገኝ ይችላል:: ነገር ግን ልማደኛ ደጋጋሚ በአመክሮ የመፈታት እድል እንደሌለው የሚገልፀው የአንቀጽ ፪፻፪(፪) አነጋገር በተደገጋሚ ከስድስት ወር በታች የሚቀጡ ጥፋተኞች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፤ ምክንያቱም ክልከላው በግልጽ የተቀመጠው ከበድ ያለ ወንጀል እየፈፀሙ በደገጋሚነት (Recidivism) ለሚቀጡና የአንቀጽ ፩፻፹፰ ድንጋጌን ትርጉም ለሚያሟሉ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ነው:: የዚህ ዓይነቱን ክልከላ በግልጽ ሳልተደነገገ ጉዳይ በተመሳሳይነት ተፈፃሚ ይሁን ማለቱ አግባብ አይሆንም::

በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር አዲስ ሦስተኛ ፓራግራፍ የገባ ሲሆን በቀላል እስራት የሚያስቀጣው የወንጀል ዓይነት ክብደት ሲኖረው ወይም አድራጊው በቀላል እስራት የሚያስቀጣው ተደራራቢ ወንጀሎችን ሲፈጽም ወይም በዚሁ የእስራት ዓይነት በሚያስቀጡ ወንጀሎች በተደጋጋሚ ሲቀጣ የእስራቱ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል የሚደነግግ አዲስ ዓረፍተ-ነገር ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፮ <u>ቀላል እስራትን በግዴታ ስራ መተካት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፮ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ለአጭር ጊዜ የተወሰነውን ቅጣት በሌላ ስለመተካት" የሚል ነበር:: ዳሩ ግን ለአጭር ጊዜ የተወሰነውን ቅጣት ሲባል ቀላል እስራትን መሆኑን እንዲሁም "በሌላ" የተባለው ለግዴታ ስራ መሆኑን በድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ስለሚቻል ስያሜውን በድንጋጌው ይዘት መሠረት በማስተካከል "ቅጣት" ከሚለው ቃል በፊት "ቀላል እስራት" የሚል ሀረግ እንዲገባ እንዲሁም "በሌላ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "በግዴታ ስራ" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል::

ይዘቱንም በተመለከተ "እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የእስራት ቅጣት" የሚለው ጊዜው አነስተኛ መስሎ ስለሚታይ በማሻሻል "ሶስት" የሚለው ተሰርዞ "ስድስት" በሚለው ተተክቶአል:: እንዲሁም በሁለተኛው ፓራግራፍ የተመለከተው ፍሬ-ነገር ግልጽነት ስለሚጎድለው ግልጽ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል::

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፻፰ <u>ጽኑ እስራት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፯ ድንጋጌ አንዳንድ ማሻሻያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "በተለይ አደገኞች በሆኑት" የሚለው ሀረግ አደገኝነታቸው ለማን መሆኑን የሚያመለክት ባለመሆኑ "በተለይም" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ለህብረተሰቡ አደገኛ በሆኑ" የሚል ሀረግ ገብቷል፡፡ በዚህ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የሰፈረው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቀባይነትን ከማግኘቱም በላይ ጽኑ እስራት ከቀላል እስራት የከበደ መሆኑን በአጽንኦት ማመልከቱ አስፈላጊ በመሆኑ "የጽኑ እስራት ቅጣት የአፈጻጸም ሁኔታ ከቀላል እስራት የአፈጻጸም ሁኔታ በይበልጥ ይከብዳል፡፡" የሚል አዲስ ሁለተኛ ፓራግራፍ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

ቀጽ ፻፱ <u>የወል ድንጋጌዎች</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፰ ድንጋጌ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፰ ድንጋጌ በይበልጥ ግልጽነት እንዲኖረው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ቀጽ ፻፲ <u>እሥረኞችን መለያየት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፱ ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "በእስር ቤት ወንድንና ሴትን ስለ መለያየትና በየተወሰነላቸው ስፍራ ነጥሎ ስለ ማኖር፡፡" የሚል ነው፡፡ ሆኖም ከይዘቱ መረዳት እንደሚቻለው ተለያይተው መቀመጥ ያለባቸው እስረኞች ወንድና ሴት ብቻ ሳይሆኑ አደገኛ አዋኪ ያልሆኑና ለመጀመሪያ ጊዜ የታሰሩ እንዲሁም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ጥፋተኞች ተለይተው በተዘጋጀላቸው ስፍራ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህም ስያሜው የጠቅላላ ይዘቱን ሁኔታ ማካተት እንዲችል "እስረኞችን መለያየት" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ አንዳንድ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ ጽኑ እስራት የሚፈረድበት ሰው በጣም አደገኛ በመሆኑ /አንቀጽ ፻፰/፣ የጥፋተኛውን አደገኛነት ለማሳየት የገቡት ሌሎች ቃላት ተሰርዘዋል፡፡ እንዲሁም ጽኑ እስራት ከተፈረደባቸው ሰዎች ጋር አብረው መታሰር የሌለባቸው በመጀመሪያ ጥፋት በቀላል እስራት የተቀጡ ለአካለ መጠን የደረሱ እስረኞች ብቻ ሳይሆኑ ለአጭር ጊዜ በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን ፈጽመው በተደጋጋሚ ይኸው ቅጣት የተፈረደባቸው ሰዎች ጭምር መሆን አለባቸው፡፡ በመጀመሪያ ጥፋትም ሆነ በተደጋጋሚ ለአጭር ጊዜ ቀላል እስራት የተፈረደበት ሰው ይህን ያህል

www.abyssinialaw.com



አደገኛ ስላልሆነ በጽኑ እስራት ከተቀጣ ሰው ጋር መታሰር የለበትም:: በመሆኑም" በመጀመሪያ ጥፋት" የሚለው ቃል ተሰርዟል::

በንዑስ ቁጥር (፫) የሰፈረው ድንጋጌ ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በተጨማሪ "በዕዳ ምክንያት ተይዘው የታሰሩ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም ከመንግሥት ሥራ ግዴታቸው የተነሳ ከእስረኞች ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሆነው በወንጀል ወይም በዕዳ ምክንያት የታሰሩ ሰዎች" የሚል ሀረግ እንዲገባ ሆኖአል:: ይህም በስራቸው የተነሳ ቀደም ሲል ባደረጉት ድርጊት የመንግሥት ሠራተኞች በታሳሪዎቹ ሊደርስባቸው የሚችለውን ስነ ልቦናዊና ሞራላዊ ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል::

## አንቀጽ ፻፲፩ የመስራት ግዴታና የስራው ዋጋ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ እስረኛው የግዴታ ሥራና ስለ ሥራው ዋጋ::" የሚል ነው:: ሆኖም ይዘቱ የሚያመለክተው በአንቀጽ ፻፫ እና ፻፬ የተመለከተውን ዓይነት የግዴታ ስራ ሳይሆን እስረኛው በእስር ቤት ሆኖ የሚሰጠውን ማናቸውንም ዓይነት ስራ ለማመልከት ነው:: ስለዚህም ስያሜው ይዘቱን ማንፀባረቅ እንዲችል "የመስራት ግዴታና የሥራው ዋጋ::" እንዲል ተደርጎ ተሻሽሎአል::

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር አንድም ሆነ በንዑስ ቁጥር ሁለት የሰፈሩት ድንጋጌዎች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

## አንቀጽ ፻፲፪ የእስራቱን ሁኔታ መለዋወጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፪ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የተቀጪውን የእስራቱን ደረጃ ስለመለዋወጥ::" የሚል ነው:: ሆኖም ይዘቱ እንደሚያመለክተው የሚለዋወጠው የእስራቱ ደረጃ ሳይሆን የተቀጪው የእስራቱ ሁኔታ በመሆኑ ስያሜው ይህንኑ እንዲያንፀባርቅ "የእስራቱን ሁኔታ መለዋወጥ" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል::

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩)፣ ንዑስ ቁጥር (፪) እና (፫) ላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

## አንቀጽ ፻፲፫ በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፫ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞ ሕግ ላይ የድንጋጌው ስያሜ "አስቀድሞ በአመክሮ ስለመፈታት" ይል ነበር:: ሆኖም "Conditional release" ለሚለው የድንጋጌው የእንግሊዘኛ ስያሜ "በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታት" የሚለው ሐረግ በይበልጥ ተስማሚ በመሆኑ በዚህ መልክ ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com



ይዘቱን በተመለከተ በሁለቱም ንዑሳን ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል:: በተለይ በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ " ተቀጪው ከተወሰነበት የእስራት ጊዜ ውስጥ ከሶስት እጅ ሁለቱን እጅ የፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም የዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደበት ሲሆን ሃያ ዓመት የታሰረ እንደሆነ" የሚለው ጥገኛ ሐረግ ከዚህ ተሰርዞ በአንቀጽ ፪፻፪ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል:: ይህ ሊደረግ የቻለበት ምክንያት የአንቀጽ ፪፻፪ ስያሜ "ለመለቀቅ የሚያበቁ ሁኔታዎች" የሚል ሲሆን ከላይ በተጠቀሰው ጥገኛ ሐረግ ላይ የተቀመጠው አሳብ ለመለቀቅ ከሚያበቁት ምክንያቶች አንዱን የያዘ በመሆኑና ሁሉን ማሟያ ነጥቦች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ማስፈሩ የተሻለ በመሆኑ ነው::

ቀጽ ፻፲፬ <u>በወታደሮች ላይ የማወሰን የቅጣት አፈጻጸም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፬ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ጠቅለል ያለ አሳብ እንዲይዝ ተደርጎ እንዲሻሻል ሆኖአል::

ይዘቱም ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፻፲፭ <u>ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የተያዘበትን ጊዜ መቁጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፭ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ለመጠበቂያ እጁ ተይዞ የቆየበትን ጊዜ ስለመቁጠር::" የሚል ነበር:: ሆኖም ስያሜው ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ይዘቱ የሚያመለክተው ውሳኔ እስኪያገኝ ያለውን ጊዜ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ስያሜው ተሻሽሎ "ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የተያዘበትን ጊዜ መቁጠር::" እንዲል ሆኖአል::

ይዘቱንም በተመለከተ ንዑስ ቁጥር (፩) ከመጀመሩ አስቀድሞ "ነፃነትን የማሳጣት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ" የሚለው ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጻፈ በኋላ ቢሆን እንደሚሻል ስለታመነበት የቦታ አቀማመጥ ለውጥ ተደርጓል:: በተጨማሪም ንዑስ ቁጥሩ ግልጽ ይሆን ዘንድ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የሰፈረው ድንጋጌም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፻፲፮ <u>የታመመ እሥረኛ ወደ ሀኪም ቤት ሲገባ ሆስፒታል የቆየበትን ጊዜ መቁጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የታመመውን እሥረኛ ወደ ሀኪም ቤት ለማስገባትና የታመመበትን ጊዜ ስለመቁጠር" የሚል ሲሆን አሳቡን በይበልጥ ግልጽ በሚያደርግ መልክ "የታመመ እሥረኛ ወደ ሀኪም ቤት ሲገባ ሆስፒታል የቆየበትን ጊዜ መቁጠር" እንዲል ተደርጎ ተቀርጿል::

የንዑስ ቁጥር (፩) የአንደኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው ዐረፍተ-ነገር፣ አንድ እሥረኛ በመታመሙ ሀኪም ቤት ገብቶ የሚታከምበት ጊዜ ሊፈጽመው ከሚገባው ቅጣት ጋር እንደሚታሰብለት የሚደነግግ ሲሆን በሀኪም ቤት ገብቶ የታከመው ከመታሰሩ በፊት

www.abyssinialaw.com

ባደረበት ህመም ወይም ሌላ ምክንያት ከሆነ ይህ ጊዜ ከእስራቱ ዘመን ውስጥ ሳይታሰብለት እንደሚችል የንዑስ ቁጥር አንድ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ይደነግጋል:: ሆኖም ህመሙ የደረሰበት በራሱ ጥፋት ካልሆነ በሀኪም ቤት የቆየበት ጊዜ ከሚፈጽመው ቅጣት ጋር በሙሉ ሊታሰብለት ይገባል:: በዚህ መሠረት የመጀመሪያው ፓራግራፍ የሁለተኛው ዐረፍተ-ነገር ይዘት ተሻሽሎ ራሱን የቻለ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኗል::

የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል::

የንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያውና ሁለተኛው ፓራግራፎችም ግልጽነት እንዲኖራቸው አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎባቸው በንዑስ አንቀጽ (፫) ስር ተካትተዋል::

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የሞት ቅጣት

### አንቀጽ ፻፲፯ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፯ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፩፻፲፮ ስያሜ "መሠረቱ" የሚል ነበር:: ነገር ግን ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት ተለውጦ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "መርህ" ተብሏል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የሞት ቅጣት ሊወሰን የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በመዘርዘር በአሉታ የተጻፈውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በአዎንታ ተጽፎ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖአል:: በዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ "Offences which are completed" የሚለው ሀረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "የተፈፀመው ወንጀል" ተብሎ ተተርጉሟል፤ ሆኖም በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የተሞከሩ ወንጀሎች ሳይሆኑ ፍፃሜ ያገኙ ወንጀሎች ናቸው:: ስለዚህም ንዑስ አንቀጹ ይህንን አሳብ በግልጽ በሚያሳይ መንገድ ተሻሽሎ ተረቅቋል:: በተጨማሪም በዚሁ አዲስ መስመር የሞት ቅጣት የመጨረሻው ከፍተኛ ቅጣት በመሆኑ "የተፈጸመው ወንጀል እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑ እና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ" የሚሉ ሁለት የሁኔታ መለኪያዎች እንዲገቡ ተደርጓል:: ከዚህም ሌላ የሞት ፍርድ የሚፈረድበት ሰው፣ ወንጀሉን በሚፈጽምበት ጊዜ ቢያንስ ፲፰ ዓመት የሞላው መሆን እንዳለበት ተገልጿል::

በቀድሞው ህግ በንዑስ ቁጥር (፪) "የሞት ፍርድ ግርማዊ ንጉሠ-ነገሥት ካላጸኑት በቀር ሊፈፀም አይችልም::" በሚል ተደንግጎ ነበር:: ሆኖም አገሪቱ በአሁኑ ጊዜ በምትከተለው ሥርዓት ውስጥ የንጉሣዊ አገዛዝ የሌለ በመሆኑ ዓረፍተ-ነገሩ እንዳለ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የሞት ፍርድን የማጽናት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ ተለይቶ ለአንድ አካል ያልተሰጠ ቢሆንም ካለው ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው ሶስት የተለያዩ አካላት የሞት ፍርድን የማጽናት ሥልጣን ያላቸው ይመስላል:: እነዚህም:-

፩ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በአዋጅ ቁጥር ፭፯/፳፰ መሠረት፣

www.abyssinialaw.com

፪ ማዕከላዊ መንግሥትና
፫ የክልል መንግሥታት በሕገመንግስቱ አንቀጽ ፶፪(፩) መሰረት ናቸው::

ሆኖም የሞትን ቅጣት ማጽናት ያለበት የአገሪቱ ርዕሰ-ብሔር ብቻ መሆኑ ስለታመነበት በተሰረዘው ዓረፍተ-ነገር ፈንታ "በአገሪቱ ርዕሰ-ብሔር ፍርዱ ካልፀና በቀር ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም::" በሚል እንዲተካ ተደርጓል:: እንዲሁም በዚሁ ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ላይ "በምህረት ወይም በአዋጅ ምህረት" የሚለው ሀረግ በእንግሊዘኛው "Pardon" እና "Amnesty" ከሚሉት ቃላት ጋር ለማጣጣም እና ልዩነታቸውንም አጉልቶ ለማሳየት በሚያስችል መልክ መግለጹ የተሻለ ስለሆነ ሀረጉ ተሰርዞ "በይቅርታ ወይም በምህረት" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል::

የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት፣ በአደባባይ በስቅላት ወይም በሌላ ኢሰብአዊ በሆኑ ዘዴዎች መፈጸም እንደሌለበት ስለታመነበት የቀድሞው ህግ የቁጥር 116 የንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሰርዞ በምትኩ ተሻሽሎ የተጻፈው ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል:: የአፈጻጸሙ ዘዴም ጉዳዩ በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ማረሚያ ቤት የበላይ ሕግ አስፈጻሚ አካል እንዲወሰን ተደርጓል:: ይህም የሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው የበላይ ህግ አስፈጻሚ አካል በየአካባቢው ባሉት ሁኔታዎች መሠረት አቅም በፈቀደ መጠን ሰብዓዊ በሆነ መንገድ የሞት ፍርድ ቅጣት የሚፈጸምበትን ዘዴ እንዲወስን ለማስቻል ታስቦ ነው::

የቀድሞው ህግ የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሁለተኛ ፓራግራፍ የተደረገ ሲሆን የሞት ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት በተቀጪው ላይ ስቃይ ማድረስ የተከለከለ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

የቀድሞው ህግ ድንጋጌ የንዑስ ቁጥር (፫) ሶስተኛው ፓራግራፍ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ የገባ ሲሆን የሞት ቅጣቱ ከተፈጸመ በኋላ አስከሬን እንዲሰጠው ቤተሰቡ ከጠየቀ እንደሚሰጠው ቢደነገግም ጠያቂ ቤተሰብ ካልተገኘ አስከሬኑ ምን እንደሚደረግ የተገለጸ ነገር ስለሌለ "ጠያቂ ቤተሰብ ካልተገኘ አስከሬኑ በተገቢው ሥነ-ሥርዓት ይቀበራል::" የሚል አዲስ ዓረፍተ-ነገር ገብቶአል::

## ቶጽ ፻፲፰ የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ እስከሚፈጸም የሚቆይበት ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ሞት የተፈረደበት ሰው ቅጣቱ እስኪፈጸም የሚቆይበት ሁኔታ" የሚል ነበር:: ሆኖም ሞት የሚፈረደው እንዲሁ ሳይሆን ለቅጣት ተብሎ በመሆኑ ይህንኑ እንዲያንፀባርቅ ተብሎ ስያሜው የሞት ቅጣት በሚል እንዲጀምር ተደርጎ ተሻሽሏል::

በመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ "ሞት የተፈረደበት ሰው" የሚለው አገላለጽ ከላይ ለስያሜው በተሰጠው ምክንያት እንዲሻሻል ተደርጎ "የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው" በሚል እንዲነበብ ተደርጓል::

በሁለተኛው ፓራግራፍ "አስፈላጊም ሲሆን ማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ክፍል ልዩ የጥንቃቄ ጥበቃ ሊያደርግበት ይችላል::" የሚለው ዓረፍተ-ነገር አስፈላጊ ሲሆን የጥንቃቄ ጥበቃ

www.abyssinialaw.com


ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የማረሚያ ቤት አስተዳደር ክፍል ምርጫ መሆን ስለሌለበት "ሊያደርግበት ይችላል" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ያደርግበታል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል፡፡

በሦስተኛው ፓራግራፍ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፻፲፱ <u>የሞት ቅጣት አፈጻጸም ታግዶ የሚቆይበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፲፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

የአንቀፁ ስያሜ "የሞት ቅጣት ከመፈጸም ስለሚቆይበት ሁኔታ" የሚል ነበር፡፡

የሞት ቅጣት የሚወሰንበትን ሁኔታ አንቀጽ ፻፲፯ የሚደነግግ ሲሆን በውስጠ ታዋቂ የሞት ቅጣት የማይወሰንበትንም ሁኔታ ይደነግጋል ማለት ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በአንቀጽ ፻፲፰(፩) እድሜው ፲፰ ዓመት ባለመሙላቱ ምክንያት የሞት ቅጣት አይወሰንበትም የሚለው አሳብ በአንቀጽ ፻፲፯(፩) ላይ በአዎንታዊ አገላለጽ እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ የሞት ቅጣት የማይወሰንበትን ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ስር መደንገጉ አላስፈለገም፡፡

እንዲሁም ህይወት ያለው ልጅ የወለደች እርጉዝ ሴት ልጁን ማሳደግ በሚኖርባት ጊዜ የሞት ቅጣት እንደማይፈፀምባትና ቅጣቱ በዕድሜ ልክ እስራት እንደሚለወጥላት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር በአንቀጽ ፻፳ ላይ የተደነገገው በአንቀጽ ፻፲፰(፩) እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ የሞት ቅጣት ስለማይፈፀምበት ሁኔታ ከዚህ ይዘትም ውስጥ ላይ ተሰርዟል፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ የአንቀጽ ስያሜ የሞት ቅጣት ታግዶ የሚቆይበት ሁኔታ እንዲል ተደርጎ ተረቅቋል፡፡

ከላይ በተገለጸው መሠረት የማያስፈልጉ ሐረጎች በመሰረዝ የአንቀጹ ይዘት እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

ህይወት ያለው ልጅ በወለደች እርጉዝ ሴት ላይ የሞቱ ቅጣት በእድሜ ልክ እሥራት ስለሚለወጥበት ሁኔታ በቁጥር ፻፲፰ በሁለተኛው ፓራግራፍ በሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ላይ የተደነገገው አንቀጽ ፻፳(፩) ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በቁጥር ፻፲፰ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ፓራግራፎች ላይ ስለአእምሮ ህመምና ስለሌላ ጽኑ ህመም እንዲሁም ስለእርጉዝ ሴት የተደነገገውን በማሻሻል ይህ አንቀጽ አንድ ፓራግራፍ ብቻ እንዲኖረው ተደርጎ ተረቅቋል፡፡

አንቀጽ ፻፳ <u>የሞት ቅጣትን መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፲፱ ድንጋጌ አስፈላጊ መሻሻሎች ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳ ሆኖ ገብቷል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአንቀጽ ፻፲፰ የሁለተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል፡፡

www.abyssinialaw.com


የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፻፲፱ ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል:: ሁለቱ ሁኔታዎች በአንድ አንቀጽ ሥር የተካተቱበት ምክንያት በሁለቱም በኩል የሞቱ ቅጣት በሌላ ቅጣት ስለሚለወጥበት ሁኔታ የሚደነግግ በመሆኑ ነው::

## ክፍል ሁለት
## ተጨማሪ ቅጣቶች

ቁጽ ፻፳፩ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፳ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፩ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፳ ስያሜ "መሠረቱ" የሚል ነው:: ነገር ግን ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት ተለውጦ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "መርህ" ተብሏል::

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ የቀድሞው ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን ይህ አንቀጽ ሶስት ፓራግራፎች እንዲኖሩት ተደርጓል::

የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሦስተኛው ዓረፍተ-ነገር ራሱን የቻለ አሳብ ስላለው ሁለተኛ ፓራግራፍ የተደረገ ሲሆን የቀድሞው የሁለተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌ ሦስተኛ ፓራግራፍ ሆኗል:: በይዘትም ረገድ የአሳብ መቃናትና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

የቁጥር ፻፳ (ሀ) ድንጋጌ መሠረዝ

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ ፻፳(ሀ) ላይ ግርፋት ለአንዳንድ ከባድ ወንጀሎች እንደተጨማሪ ቅጣት የተደነገገ ሲሆን በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩትን መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች የሚፃረር ስለሆነ ተሰርዟል::

ቁጽ ፻፳፪ በጥፋተኛው ላይ የሚደረግ ማስጠንቀቂያ፣ ወቀሳ ፣ተግሳጽ፣ጥፋተኛው የሚጠይቀው ይቅርታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፳፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፪ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ ከወቀሳ በፊት ተግሳጽ ገብቶ የነበረ ሲሆን ቅደም ተከተላቸው እንዲለዋወጥ ተደርጓል:: ይህም የሆነው በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ከመገሰጽ በፊት መውቀስ ተጠቅሶ በመገኘቱ ነው::

ይዘቱን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ፍርድ ቤቱ በገመተ ጊዜ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ" የሚል ገብቷል፤ ምክንያቱም በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ እርምጃው የሚወሰደው ዋናውን ቅጣት በመተካት እንደሆነ መደንገጉ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ቅጣቱ የሚወሰነው ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ መሆኑን ስለሚያሳይ ነው::

www.abyssinialaw.com



እንዲሁም "በችሎትና በፍርዱ ላይ ..." በማለት የተመለከተው በአማራጭ ቢፃፍ የሚሻል በመሆኑ ተሻሽሎ "...በችሎት ወይም በፍርዱ ላይ..." በሚል እንዲሻሻል ሆኖአል:: በተጨማሪም ንዑስ ቁጥሩ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተመለከተው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላትና የአጣቃሽ አንቀጾች አቀማመጥ ማስተካከያ እንዲደረግበት ሆኖአል::

አንቀጽ ፻፷፫ <u>ከመብት መሻር</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፫ ሆኖ ገብቷል::

አሳቡን ግልጽ ለማድረግ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የተቀረፀ ሲሆን በተለይ በፊደል "ለ" ላይ ከመብት የሚሻሩት እናትና አባት ሁለቱም ሊሆኑ ስለሚችሉ "የአባትነት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "የወላጅነት" በሚል ተተክቷል::

አንቀጽ ፻፷፬ <u>ቅጣቱ የሚቆይበት ዘመንና አወሳሰኑ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፬ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ ለጊዜው ብቻ የሆነ ከመብት የመታገድ ወይም የመከልከል ውሳኔዎች ከአንድ አመት አያንስም ተብሎ የተደነገገው የጊዜ ገደብ በጣም ረጅም ስለሆነ "ከአንድ አመት የሚለው" ሀረግ ተሰርዞ "ከስድስት ወር" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: በዚህ ንዑስ ቁጥር ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የሚገኘው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ".ምህረት የማግኘት መብት". የሚል ሀረግ ይገኝበታል:: ሆኖም "ምህረት" (Mercy) ችሮታ እንጂ መብት ስለአልሆነ "መብት" የሚለው ቃል ተሰርዟል:: በሌላ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ስለይቅርታ ሳይጠቀስ ታልፏል፤ ሆኖም ሊካተት ይገባል:: ስለመሰየምም ከአንቀጽ ፻፷፰ ይልቅ ስለ መሰየም በዝርዝር የሚደነግጉት አንቀጽ ፪፻፴፪-፪፻፴፯ ተብሎ ቢጠቀስ ይሻላል:: በዚህ መሠረት ንዑስ ቁጥሩ ተስተካክሎ ተቀርጿል::

ከዚህም ሌላ በድንጋጌው ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ተረቅቋል::

አንቀጽ ፻፷፭ <u>ከመብት የመሻሩ ቅጣት የሚፀናበት ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፭ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የተሰጠው ውሳኔ ስለሚያስገኘው ውጤት" የሚል ነበር:: ሆኖም የመብት መሻሩ ውሳኔ የሚፀናው ከምን ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ለማመልከት በመሆኑ ከቀድሞ ሕግ ስያሜ ይልቅ ከላይ የተቀመጠው ስያሜ ይመረጣል::

የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ የንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የተደረገ ሲሆን፣ የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ፓራግራፎች የንዑስ አንቀጽ (፪) ሁለተኛው እና ሶስተኛው ፓራግራፍ ሆነው ገብተዋል::

www.abyssinialaw.com

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ከመብት የመሻሩ ቅጣት የሚጸናበት ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበት አንዱ ሁኔታ ጥፋተኛው "ከተማረበት" ቀን አንስቶ እንደሆነ ተደንግጓል:: "ከተማረበት" የሚለው ቃል የገባው ይቅርታን "pardon" ወይም ምህረትን "amenesty" ወይም ሁለቱን ለማመልከት እንደሆነ ግልጽ አይደለም:: ሆኖም ምህረት "amnesty" የተደረገለት ሰው ከተማረበት ቀን አንስቶ ምንም ወንጀል እንዳልፈጸመ ንጹህ ሰው ስለሚቆጠር ይህ ድንጋጌ በዚህ ዓይነት ሰው ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም:: ይቅርታ የተደረገለት ጥፋተኛ ግን የወንጀለኛነቱ ሪከርድ ስለማይሰረዝለትና ይህ ድንጋጌ ለዚህ ዓይነቱ ሰው አግባብነት ስላለው "ከተማረበት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ቅጣቱ በይቅርታ ከተሻረበት" በሚል ሀረግ ተተክቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: እንዲሁም የአጣቃሽ አንቀጾቹ አቀማመጥ ሊያመለክቱ በተፈለገው አሳብ አንጻር እንዲገቡ ተደርጓል::

ቀጽ ፻፳፮ መብትንና ክብርን መመለስና መሰየም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፳፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፮ ሆኖ ገብቷል:: አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፻፳፯ ከመከላከያ ሠራዊት ማስወገድ፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፳፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፯ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞ ሕግ በቁጥር ፻፳፮ ድንጋጌ ስያሜና ይዘት ላይ "የጦር ሠራዊት" የሚለው "የመከላከያ ሠራዊት"፣ "ማዕረግ መግፈፍ" (Reduction Rank) የሚለው "ከደረጃ ዝቅ ማድረግን" "ይፈርድበታል" የሚለው "ሊፈርድበት ይችላል" በሚሉት ሀረጎች ተተክተዋል:: የሌሎች የቃላት ለውጥም ተደርጎበታል::

ቀጽ ፻፳፰ ውሳኔው የሚጸናበት ሁኔታ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፳፯ ስያሜ "ውሳኔው ስለሚያስገኘው ውጤት::" የሚል ነው:: ሆኖም ይዘቱ ውሳኔው ስለሚያስገኘው ውጤት ከመግለጽ ይልቅ ውሳኔው ስለሚጸናበት ሁኔታ የሚያሳይ በመሆኑ ይህን ይዘቱን እንዲያንጸባርቅ ለማድረግ ስያሜ ተሻሽሎ "ውሳኔው የሚጸናበት ሁኔታ::" ተብሏል::

ይዘቱም "ከጦር ሠራዊት" የሚለው ሀረግ "ከመከላከያ ሰራዊት" በሚል ተተክቶአል:: እንዲሁም "የመወገድና የማዕረግ መገፈፍ" በማለት በ"ና" የተጣመሩት ሀረጎች በአንድነት ከሚወሰኑ ይልቅ በአማራጭነት ቢወሰኑ የሚሻል በመሆኑ "ና" በሚለው መስተፃምር ፈንታ "ወይም" በሚል ተሻሽሏል:: "የማዕረግ መገፈፍ" የሚለውም፣ "ከደረጃ ዝቅ የመደረግ" በሚል ሐረግ ተለውጧል::

www.abyssinialaw.com



## የጽኑ ግዞትን የጥንቃቄ እርምጃ በሚመለከት ከቁጥር ፻፷፰-፻፸፪ የተጻፉት የቀድሞ የሕግ ድንጋጌዎች መሰረዝ፤

ጽኑ ግዞት የሚወሰነው በልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ላይ ሲሆን ለድርጊቱ ይመጥነዋል ተብሎ የሚወሰን ቅጣት ሳይሆን ህብረተሰቡን ለመጠበቅ ሲባል ወንጀለኛው በተወሰነ ቦታና ሁኔታ ተገልሎ እንዲቀመጥ የሚደረግበት የጥንቃቄ እርምጃ ነው (ቁጥር ፻፷፰ እና ፻፷፱):: በስዊዝ አገር ሕግ መሠረት ወንጀለኛው የፈጸመው የመጨረሻው ወንጀል ይህን ያህል ከባድ ባይሆንም እንኳ ወንጀለኛው ጠባዩን እስካላሻሻለ ድረስ ዕድሜ ልኩን በጽኑ ግዞት እንዲቀመጥ ሊደረግ ይችላል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ወንጀለኛው በደጋጋሚነቱ እየተፈረደበት ቅጣት ያላረመው በመሆኑ ነው::

በአገራችን ሕግ ግን የሰፈረው ተቃራኒ አሳብ ነው:: ጽኑ ግዞት የሚቆይበት ጊዜ ፈጽሞ ከአስር ዓመት አይበልጥም (ቁጥር ፻፸):: ዶ/ር ግራቨን እንደሚሉት የዚህ ዓይነቱ የጥንቃቄ እርምጃ በቀላል እስራት ለሚቀጣ ልማደኛ ወንጀለኛ ያገለግል እንደሆነ እንጂ እየደጋገመ ለብዙ ዓመታት በጽኑ እስራት በተቀጣ ወንጀለኛ ሲሆን አይችልም:: ጽኑ ግዞት የሚቆይበት ጊዜ ብዙ ዓመት እየታሰረ ሊታረም ያልቻለ ወንጀለኛ በፈጸመው ወንጀል ሊታሰር ይገባ ከነበረው ጊዜ የረዘመ እንጂ እጅግ ያጠረ ሲሆን አይገባም:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት የረዥም ጊዜ እስራት ያላስተካከለውን ጠባይ የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ ከሚቆይበት ረጅም ጊዜ የተነሳ ያርመዋል ተብሎ በመታመኑ ነው:: የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ግን ለዚህ ጉዳይ በቂ ምላሽ የለውም:: እንዲኖረው ማድረግም አይቻልም::

በመሆኑም ይህ የጥንቃቄ እርምጃ ከወንጀል ሕጉ እንዲሰረዝ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል:: ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው::

፩ የቁጥር ፻፷፰ የእንግሊዝኛውና የአማርኛው ትርጉም እርስ በርስ የሚፋለስ ከመሆኑም በላይ የጽኑ ግዞት ውሳኔ በፍርድ ቤቶች ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም:: ጽኑ ግዞት የሚወሰንበት ጥፋተኛ በመሰረቱ ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲሆን አንድ ጥፋተኛ ደጋጋሚ ነው የሚባለውም (ቁጥር ፻፷፰ (፩) (ለ) የመጨረሻውን ወንጀል ሆነ ብሎ የፈጸመ እንደሆነ ነው:: በቁጥር ፻፷፰ (፪) የእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ "Internment may be ordered where the new offence is intentional...." የሚለው አነጋገር በንዑስ ቁጥር አንድ የተመለከተው የወንጀል አፈጻጸም በቸልተኛነት መሆን መቻሉን ያሳያል:: ይህ ግን ፍጹም ስህተት ነው:: ከዚህም በላይ በንዑስ ቁጥር ሁለት መሰረት ፍርድ ቤቶች የጽኑ ግዞት ውሳኔ እንዲወስኑ መብት የሚሰጥ እንጂ የሚያስገድዳቸው አይደለም::

፪ በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው የጽኑ ግዞት መሰረተ አሳብ በጣም ከባድ ወንጀል በተደጋጋሚ እየፈጸሙ ለተቀጡ አደገኛ ወንጀለኞች እንጂ አደገኞች ሳልሆኑ በቀላል እስራት ለተቀጡ ወንጀለኞች መሆን የለበትም:: የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፻፷፰ (፩) ግን የሚያገለግለው እስከ አምስት ዓመት እስራት ብቻ ለተፈረደበት ወንጀለኛ ነው:: የሚቆይበት ጊዜም ከአስር ዓመት አይበልጥም:: ይህ ሁኔታ ዓላማውን የሳተ ሆኖ ይታያል፤ ዕድሜ ልክ በግዞት ማቆየት ከሚያስችለው የስዊዝ አገር ልምድ ለምን እንደተለየም ግልጽ አይደለም::

፫ ጽኑ ግዞት በስዊዘርላንድና በስዊድን አገሮች ከሚሰራበት በቀር ሌሎች አገሮች የሚያውቁት አይመስልም:: የብላክ የሕግ መዝገበ ቃላትም "internment " የአሜሪካ መንግሥት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከጃፓን መንግሥት ጋር ሲዋጋ በዘራቸው

www.abyssinialaw.com



ጃፓናውያን በዜግነታቸው ግን አሜሪካውያን የሆኑትን ሰዎች አግቶ ያቆየበት ሁኔታ መሆኑን ከሚገልጽ በቀር ፍርድ ቤቶች በሕግ መሰረት በየትኛውም አገር የሚሰጡት ውሳኔ መሆኑን አይጠቁምም::

፬ ጽኑ ግዞት የሚፈጸምበት ቦታና ሁኔታ በኢትዮጵያ ተመቻችቶ አያውቅም:: ከዚህ በኋላም በቁጥር ፻፰፱ መሰረት ለማደራጀት አቅሙ አላት ተብሎ አይታመንም:: በአሁኑ ጊዜ ጽኑ እስራትና ቀላል እስራት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች በተለያየ ቦታ ወይም ሁኔታ መታሰር ሲገባቸው በአንዳንድ በጣም ከባድ በሆነ ወንጀል ካልሆነ በቀር አብረው እንደሚታሰሩ የታወቀ ነው:: ደምብ ተላላፊዎችም የሚወሰንባቸው የማረፊያ ቤት እስራት ከቀላል እስራትም የቀለለ ወይም ያነሰ ከመሆኑም የተነሳ የተለየ ሁኔታ ሊደራጅለት ሲገባ እስከአሁን ድረስ የተከናወነ ነገር የለም:: መደበኛ የሆኑትን ነጻነት የሚያሳጡ ቅጣቶችን ማስፈጸሚያ የሌላት አገር፣ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተግባራዊ ሆኖ የማያውቀውንና በሕጉ መሠረት ተግባራዊ ሊሆን የማይችለውን የጥንቃቄ እርምጃ የምታስፈጽምበት ቦታና ሁኔታ ታቋቁም ማለቱ አግባብ አይሆንም::

ከዚህ በላይ በተሰጡት ምክንያቶች መሰረት የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ በህጋችን እንዲኖር ማድረጉ አስፈላጊ ባለመሆኑና ስራ ላይም የሚውል ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

## ምዕራፍ ሦስት
## ለአካለ መጠን በደረሱ ጥፋተኞች ላይ የሚፈጸሙ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ምዕራፍ በቀድሞው ሕግ መሠረት ምዕራፍ ሁለት የነበረ ሲሆን ከዚህ ቀደም በተደረገው የምዕራፎች ሽግሽግ መሠረት ምዕራፍ ሦስት እንዲሆን ተደርጓል::

የምዕራፉን ስያሜ በተመለከተ ለአካለ መጠን በደረሱ ጥፋተኞች ላይ የሚወሰዱትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በተለየ ሁኔታ (ከቁጥር ፻፳፰-፻፴፯) እና ጠቅላላ ደንቦች (ቁጥር ፻፴፰-፻፵) ብሎ በሁለት ምዕራፎች ከመክፈል ይልቅ ሁሉንም የጥንቃቄ እርምጃዎች ባከተተ መልክ በአንድ ምዕራፍ ስር እርምጃዎችን ሁሉ ማስቀመጡ የተሻለ ስለሆነ በዚሁ መሠረት የምዕራፉ ስያሜ ተስተካክሏል::

## ክፍል አንድ
## ኃላፊነት በሌላቸውና ከፊል ኃላፊነት ባላቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ በተለየ ሁኔታ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ክፍል በቀድሞው ሕግ መሠረት ክፍል ሁለት የነበረ ሲሆን ስለ ጽኑ ግዞት የተደነገገው የመጀመሪያ ክፍል ስለተሰረዘ ክፍል አንድ ሆኗል:: በቀድሞው ስያሜ ላይም "በተለየ ሁኔታ" የሚል ሀረግ እንዲታከልበት ተደርጓል:: ይህም የሆነው፣ በዚህ ክፍል የሚወሰደው የጥንቃቄ እርምጃ በአብዛኛው ጥፋተኛ ላይ ተፈጻሚ ስለማይሆን ነው::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፻፳፱ <u>መርሀ</u>[*]

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፳፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፴፫ ስያሜ "መሠረቱ" የሚል ነው፡፡ ሆኖም ይህን ቃል ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት ወጥነት ይኖረው ዘንድ ተሻሽሎ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "መርሕ" ተብሎአል፡፡

ይዘቱም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በተጨማሪ የአጣቃሽ አንቀጾችም አቀማመጥ ማመልከት ከሚገባቸው ፍሬ ነገሮች አጠገብ እንዲቀመጡ ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

አንቀጽ ፻፴ <u>ለጥንቃቄ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥና እንዲታከም ማድረግ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴ ሆኖ ገብቷል፡፡

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፴ ስያሜ "የጥንቃቄ ግዞት" የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ይዘቱ የሚያመለክተው በቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፻፳፰-፻፴፪ በተደነገገው አኳኋን የሚደረገውን የግዞት የጥንቃቄ እርምጃ የሚያመለክት ሳይሆን ለጥንቃቄ በአንድ በተወሰነ ስፍራ ማስቀመጥን የሚያመለክት በመሆኑ በዚህ ቦታ መታከም የሚችልበት ሁኔታ በመኖሩ የአንቀጹ ስያሜ ተሻሽሎ "ለጥንቃቄ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥና እንዲታከም ማድረግ" እንዲል ሆኗል፡፡

ይዘቱን በተመለከተ ኃላፊነት የሌለው ሰው ወይም ከፊል ኃላፊነት ያለው ወንጀል አድራጊ አብሮት ለሚኖረው ሰው አደገኛ ሊሆን ስለሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር ፻፴፬ በንዑስ ቁጥር (፩) "ሁከትን የሚያደርስ መስሎ የታየ እንደሆነ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም አብረውት ለሚኖሩት" የሚል ሀረግ ገብቶ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በቀር ወይም "ከመታከሚያ ቤት" የሚለው ሀረግ ስለ ህክምና በአንቀጽ ፻፴፩ የተሸፈነ ስለሆነ ተሰርዞአል፡፡

አድራጊው ህክምና የሚያስፈልገው መሆኑ ሲታወቅ ህክምናውን በዚያው ባለበት ስፍራም ሆነ በአንቀጽ ፻፴፩ በተደነገገው መሠረት በተገቢው ሥፍራ ተዛውሮ እንዲታከም በሚደረግበት ጊዜ ለራሱ ለአድራጊው እና ለህብረተሰቡ ደህንነት ሲባል ስለአጠባበቁ ተገቢ የሆኑት የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲፈጸሙ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት በንዑስ ቁጥር (፪) መጨረሻ ላይ "ስለመልካም አጠባበቁም ተገቢ የሆኑት የጥንቃቄ እርምጃዎች ይፈጸማሉ፡፡" የሚል ዓረፍተ-ነገር ገብቷል፡፡

አንቀጽ ፻፴፩ <u>ሕክምና</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፭ ድንጋጌ በሁለቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

---

[*] በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 129 "ከፊል ኃላፊነቱ" የሚለው ቃል "ከፊል ኃላፊነት" ተብሎ ይነበብ፡፡

www.abyssinialaw.com



ቀጽ ፻፴፪ <u>የህክምናው እና የጥበቃው ውሳኔ የሚቆይበት ጊዜ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፪ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ አጠቃላይ ድንጋጌዎች፤ ውሳኔው ስለሚቆይበት ጊዜ" ይል የነበረ ሲሆን "አጠቃላይ ድንጋጌዎች" የሚል ሀረግ በእንግሊዝኛው ቅጂ ባለመኖሩና መኖሩ አስፈላጊ ባለመሆኑ የአንቀጹ ስያሜ "የሕክምናው እና የጥበቃው ውሳኔ የሚቆይበት ጊዜ" ብቻ እንዲል ተደርጓል፡፡

ይዘቱን በተመለከተ በአንቀጽ ፻፴ በተገለጸው መሠረት "ግዞት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ" የተባለ ሲሆን ሶስቱ ንዑስ ቁጥሮች በይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡

ቀጽ ፻፴፫ <u>የተቀነሰ ሀላፊነትና በቅጣት ላይ ያለው ውጤት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፫ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "በቅጣቱና በተቀነሰው ኃላፊነት መካከል ስላለው ግንኙነት" ይል የነበረ ሲሆን በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ ግን " Effect of Limited Responsibility upon Penalty" የሚል በመሆኑ፣ በዚህ መሠረት ስያሜው ተስተካክሏል፡፡

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) "የተቀነሰ ኃላፊነት ያለበት አጥፊው ሲሆን በመደቡ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ሊያቀል የሚችለውን በሕግ የተወነውን ቅጣት ይፈርዳል (ቀጥር.፵፱)" የሚለው የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ግልጽነት ስለሚጎድለው ዓረፍተ-ነገሩ "ከፊል ኃላፊነት ስላለባቸው ሰዎች የቅጣት አወሳሰን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ (አንቀጽ ፵፱) ...." በሚል እንዲሻሻል ሆኖአል፡፡ እንዲሁም በዚህ ንዑስ ቁጥር "የጥንቃቄ አጠባበቅ" የሚለው ሀረግ ምን አይነት ጥንቃቄ እንደሆነ አያስረዳም፡፡ የጥንቃቄ እርምጃዎች በቁጥር ፻፴ እና ፻፴፩ የተገለጹት የመከላከልና የመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲሁም የመታከም ሥርዓት ስለሆነ ይኸው ተዘርዝሮአል፡፡ አንቀጾቹም ተጠቅሰው ገብተዋል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ፣ አድራጊው በተቀነሰ ኃላፊነት ምክንያት በህኪም ቤት የቆየበት ጊዜ ከቅጣቱ ጋር ሊቆጠር የሚችል መሆን አለመሆኑ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ አድራጊው ህመሙን ያስከተለው በራሱ ጥፋት ከሆነ በህኪም ቤት የቆየበት ጊዜ ከቅጣቱ ጋር ሊታሰብለት ስለማይገባ፣ በሌላ በኩል ህመሙ የመጣው የራሱ ጥፋት ባልሆነ በሌላ ምክንያት ከሆነ ሊቆጠርለት ስለሚገባ ይህንን ለማመልከት እንዲቻል "....በአንቀጽ ፻፲፮ መሠረት ይወሰናል፡፡....." የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) በሁለተኛው ፓራግራፍ በመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ "ሰላማዊ ሰው ሊሆን የሚሰጠውን ዋስትና" የሚለው ሀረግ ሰላማዊ ሰው ለመሆን ዋስትና ለመስጠት አዳጋች ከመሆኑም በቀር ዋስትናነቱም አስተማማኝ ሊሆን ስለማይችል ፍርድ ቤቱ ከዚህ በፊት ጥፋተኛውን ለመከላከልና ለመጠበቅ በአንድ ቦታ ተወስኖ የቆየበት፣ ወይም በህክምና ያሳለፈው ጊዜ—ገና ሊፈጸምበት ከሚገባው ለጊዜው ታግዶለት ከነበረው ቅጣት ላይ በምን ሁኔታ ሊቀነስለት እንደሚገባው ለመወሰን መሠረት አድርጎ ከሚከተላቸው ነጥቦች አንዱ ጥፋተኛው ሰላማዊ ሰው ለመሆን የሚያሳየው አዝማሚያ ነው፡፡ ስለዚህም

www.abyssinialaw.com



"ሰላማዊ ሰው ለመሆን ስለሚሰጠው ዋስትና" ከሚለው ሀረግ ውስጥ "ሊሆን የሚሰጠውን ዋስትና" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ" ለመሆን የሚያሳየውን አዝማሚያ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፫) የቅጣቱ መፈጸም ከጥቅሙ ይልቅ የሚጎዳ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በተገነዘበ ጊዜ አፈጻጸሙን ማቆየት እንደሚችል የተደነገገው ቅጣቱ የሚጎዳ እስከሆነ ድረስ የሚቆይበት ምክንያት ባለመኖሩ ንዑስ ቁጥሩ ተሻሽሎ "ወንጀል አድራጊው ቀሪውን ቅጣት እንዲፈጽም ማድረጉ ጠቃሚ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት የቅጣቱን መፈጸም ያስቀርለታል" በሚል አስገዳጅነት እንዲደነገግ ተደርጓል::

## ክፍል ሁለት
## የመከላከልና የአጠባበቅ አጠቃሳይ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ክፍል በቀድሞው ሕግ መሠረት ምዕራፍ ሦስት ነበር:: ሆኖም ከዚህ በፊት ስላለው ስለ ክፍል አንድ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ለአካለ መጠን በደረሱ ጥፋተኞች ላይ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች በሁለት ልዩ ልዩ ምዕራፎች ስር ከማስቀመጥ ይልቅ፣ ሁሉም በአንድ ምዕራፍ እንዲጠቃለሉና እንደአስፈላጊነቱ በክፍሎችና በንዑሳን ክፍሎች እንዲመደቡ ማድረጉ ስለሚመረጥ በዚህ ምክንያት ክፍል ሁለት ሊሆን ችሏል::

### አንቀጽ ፻፴፩ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "መሠረቱ" የሚል ነበር:: ሆኖም ቀደም ሲል በተደረገው ማሻሻያ መሠረት ተሰርዞ "መርሕ" በሚል ቃል ተተክቶአል::

ይዘቱንም ግልጽ ለማድረግ የሕጉን የፈረንሳይኛ ቅጂ በመመልከት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ንብረት ነክ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ንዑስ ክፍል በቀድሞ ሕግ መሠረት ክፍል አንድ ነበር:: ነገር ግን ክፍሉ የሚገኝበት ምዕራፍ ወደ ክፍል ሲለወጥ፣ ክፍል የነበረው ዝቅ ተደርጎ ንዑስ ክፍል ሆኗል::

### አንቀጽ ፻፴፪ የመልካም ጠባይ ዋስትና መርህ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፱ ስያሜ "የመልካም ጠባይ ዋስ መሰረቱ" የሚል ነበር:: ዳሩ ግን በዚህ አንቀጽ እንደተደነገገው የማረጋገጫ ግዴታ የሚሰጠው እንደነገሩ ሁኔታ በመያዣ፣ በሰው ዋስትና ወይም በራሱ ዋስትና ነው:: ስለዚህ በዚህ ቁጥር ስር የተደነገገው ስለመልካም ጠባይ ዋስ ስለሚሆነው ግለሰብ ሳይሆን ስለዋስትናው ስለሆነ፣ "መሠረቱ" የሚለውም ስያሜ "መርሕ" በሚል ቃል የተተካ ስለሆነ፣ ስያሜው ተሰርዞ "የመልካም ጠባይ ዋስትና መርሕ" በሚል ተተክቷል::

www.abyssinialaw.com



ይዘቱን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ "በቂ የሆነ ዋስ" የሚለው ሀረግ ቀደም ሲል በስያሜው ላይ እንዲሻሻል በተገለጸው ምክንያት ተሰርዞ "በቂ የሆነ ዋስትና" በሚል ተተክቶአል:: በተጨማሪም ንዑስ ቁጥሩ ግልጽ እንዲሆን ሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ "የማረጋገጫውም ግዴታ የሚሰጠው እንደነገሩ ሁኔታ በመያዣ ወይም በሰው ዋስትና ነው::" ተብሎ ተደንግጎአል:: ዳሩ ግን የማረጋገጫ ግዴታ በራስ ዋስትናም ሊሰጥ ስለሚችል በሰው ዋስትና ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም በራስ ዋስትና" የሚል ሀረግ በተጨማሪ ገብቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፫) "የቃል መግባቱን ጊዜና ለመያዝ የሚገባውንም የጥንቃቄ ከፍተኛነት" የሚለው ሀረግ ግልጽ ስላልሆነ ተሰርዞ "የማረጋገጫው ቃል የሚቆይበትን ጊዜና የመያዣውን ወይም የዋስትናውን መጠን::" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

ቀጽ ፻፴፮ <u>የማረጋገጫ ቃል ወይም ዋስትና መስጠትን እንቢ ማለት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ቃል መግባትን ወይም ዋስ መስጠትን እንቢ ስለማለት" የሚል ነበር:: የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፴፱ ስያሜን ለማሻሻል በተሰጠው ምክንያት ላይ እንደተገለጸው ወንጀል ይሰራል ተብሎ የሚያሰጋው ሰው የሚሰጠው የማረጋገጫ ግዴታ የሰው "ዋስትና" ብቻ ሳይሆን መያዣ ወይም የራስ ዋስትናም ሊሆን ስለሚችል በቁጥር ፻፵ ስያሜ ውስጥ "ዋስ" የሚለው ቃል ተሰርዞ ዋስትና በሚል ቃል ተተክቶአል:: በስያሜው መጀመሪያ "ቃል መግባትን" የሚለው ሀረግም በአንቀጽ ፻፴፰ በተመለከተው ድንጋጌ "የማረጋገጫ ቃል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ "በክፉ ልቦና ላይ በመመስረት" ከሚለው አነጋገር ቀጥሎ "የራስ ወይም የሰው ዋስትና ያልሰጠ እንደሆነ" የሚል ሐረግ ገብቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፪) የሁለተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር "በአይነቁራኛ እየተጠበቀ ለጊዜው እንዲፈታ "የሚለው ቀርቶ" ተፈትቶ ቁጥጥር እየተደረገበት" በሚል ተስተካክሏል::

የንዑስ አንቀጽ (፪) የሁለተኛው ፓራግራፍ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር "ይህም የመታደሱ ጊዜ" የሚለው ቀርቶ "ሆኖም በማረፊያ ቤት ተይዞ የሚቆይበትጊዜ" በሚል ተተክቷል::

ቀጽ ፻፴፯ <u>የውሳኔው ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵፩ ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፯ ሆኖ ገብቷል::

ቀጽ ፻፴፰ <u>ዋስትና ወይም መያዣ ስመስጠት አለመቻል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር-፻፵፪ ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፰ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፻፴፱ <u>የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔን መደጋገም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "የጥንቃቄውን ውሣኔ ስለመደጋገም" የሚለው፣ "የጥንቃቄ እርምጃ ውሣኔን መደጋገም" በሚል ተተክቷል"

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩)"... ሰውየው እንደገና ዋስ እንዲጠራ ውሳኔ ከመስጠት ፍርድ ቤቱ አይታገድም፡፡" የሚለው ሀረግ ስለመልካም ጠባይ ዋስትና የተደነገገው በአንቀጽ ፻፴፰ ስለሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ላይ ይኸው የአንቀጹ ቁጥር እንዲጠቀስ ተደርጓል፡ በተጨማሪም ንዑስ ቁጥሩ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል፡፡ በተጨማሪም አዲስ ሁለተኛ ፓራግራፍ የገባ ሲሆን ጥፋተኛው ለፈጸመው ዛቻ በአንቀጹ መሠረት የጥንቃቄ እርምጃ የሚወሰድበት ብቻ ሳይሆን፤ በወንጀል ሊከሰስ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ ነው፡፡

አንቀጹ አሳቡን ይበልጥ ግልጽ በሚያደርግ መልኩ ተረቅቋል፡፡

አንቀጽ ፻፵ <u>አደገኛ የሆኑ ነገሮችን መውረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፵ ሆኖ ገብቶአል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "አደገኛ የሆኑ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ያለው "ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን" የሚለው ሀረግ ተሻሽሎ ሰፋ ባለ አኳኋን "ነገሮች" በሚል ተተክቶአል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ንብረቶቹ ከሦስተኛ ወገኖች እጅ በአታላይነት፣ በስርቆት ወዘተ ስለተወሰዱበት ሁኔታ በዝርዝር ይገልፃል፡፡ የንፁህ ሦስተኛ ወገኖች መብት የተጠበቀ መሆኑ ከተደነገገ ንብረቶቹ የተወሰዱበትን ዝርዝር ሁኔታ ማስፈሩ አስፈላጊ ባለመሆኑ ዝርዝሩ ተሰርዟል፡፡ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑም ንዑስ ቁጥሮቹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡

አንቀጽ ፻፵፩ <u>የወል ድንጋጌ፣ ለጥንቃቄ የሚደረግ ጠቅላላ አፈፃፀም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፵፩ ሆኖ ገብቶአል፡፡

በቀድሞ ሕግ በቁጥር ፻፵፭ ስያሜ መጀመሪያ ላይ "አጠቃላይ ድንጋጌ" በማለት የተመለከተው ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት ተሰርዞ "የወል ድንጋጌ" በሚል ከተተካና ከተከታዩ ጋር ተያይዞ እንዲነበብ ከተደረገ በኋላ የዚህ አንቀጽ ስያሜ ሆኖ ገብቶአል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ ያሉት ሁለት ፓራግራፎች አገላለጽ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ድንጋጌ ፍሬ-አሳብ ከወንጀል ሕጉ ይልቅ በወንጀል ሥነ-ሥርአት ሕግ የሚደነገግ ስለሆነ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

ስለዚህ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ከተሰረዘ በኋላ አንቀጹ በንዑስ ቁጥሮች ሳይከፋፈል ሁለት ፓራግራፎች ብቻ እንዲኖሩት ተደርጎ ተቀርጿል::

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የሥራ እንቅስቃሴን በመገደብ የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ንዑስ ክፍል ሁለት በቀድሞ ሕግ ክፍል ሁለት ነበር:: ይሁን እንጂ ክፍሉ የሚገኝበት ምዕራፍ ወደ ክፍል ዝቅ እንዲል ስለተደረገ ክፍሉ በዚሁ መሠረት ንዑስ ክፍል ሆኗል::

### ቀጽ ፻፺፩ ፈቃድን ማገድና መልሶ መውሰድ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፺፮ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፩ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠባቸውን የሥራ ዝርዝሮች መጥቀሱ አላስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ዝርዝራቸው ተሰርዟል:: ነገር ግን ፈቃድ የማገዱና የመሰረዙ ውሳኔ የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የሕግ ሰውነት ያለውንም አካል ጨምሮ እንዲካተት ተደርጓል::

በሁለተኛው አዲስ መስመር በተመለከተው ዓረፍተ-ነገር "እንዲያውም" የሚለው ቃል አስፈላጊ ባለመሆኑ ከተሰረዘ በኋላ ራሱን ችሎ በአዲስ ፓራግራፍ መጻፍ ስላለበት ሶስተኛ አዲስ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቶአል::

### ቀጽ ፻፺፪ ድርጅትን መከልከልና መዝጋት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፪ የተደረገ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

### ቀጽ ፻፺፫ ውሳኔውን አለማክበር የሚያስከትለው ውጤት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ከመጠነኛ የቃላት ማስተካከያ በስተቀር እንዳለ ተቀባይነት አግኝቷል::

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) ሆነ (፪) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተሻሽሏል::

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የግል ነፃነትን በመገደብ የሚፈጸሙ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ይህ ንዑስ ክፍል በቀድሞ ሕግ ላይ የተቀመጠው በክፍል ደረጃ ነበር:: ክፍሉ የሚገኝበት ምዕራፍ ግን ወደ ክፍል ደረጃ ዝቅ ስላለ፣ ክፍሉም በተዋረድ ንዑስ ክፍል እንዲሆን ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፻፴፭ <u>ጥፋተኛው ባንዳንድ ስፍራ እንዳይደርስ መከልከል</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፭ የተደረገ ሲሆን በአንቀጹ ይዘት ላይ የአሳብና የቃላት ማስተካከያ ተደርጐ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፻፴፮ <u>በአንድ በተወሰነ ቦታ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር መከልከል</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፮ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ "ተመሳሳይ ምክንያት" የሚለው ሀረግ ቀርቶ በአንቀጽ ፻፴፭ ላይ እንደተገለፀው "ለጥበቃው ፍፁም አስፈላጊ የሆነ ተመሣሣይ ምክንያት ሲገኝ" በሚል ሀረግ ተተክቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "ክልከላው" ለዘወትር /ዕድሜ ልክ/ ሊቆይ እንደሚችል ተደንግጓል።

ሆኖም እንዲህ አይነት ክልከላ ዕድሜ ልክ እንዲቆይ መደረጉ በተከለከለው ሰው ነፃነት እና ለመታረም ባለው ዕድል ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ይህ ቀርቶ እገዳው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ ሊሆን እንደሚችል ተደርጎ ተረቅቋል።

አንቀጽ ፻፴፯ <u>በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ የመኖር ግዴታ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ በአንድ ቦታ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ወይም አካባቢ የሚል ሀረግ ተጨምሮበት ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ሆኖ ተሻሽሏል።

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው ፍሬ ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በተጨማሪ አሳስፈላጊ የሆኑ ድግግሞሾች እንዲወጡ ተደርጎ ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፻፴፰ <u>ጥፋተኛው ላይ ቁጥጥር ማድረግ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፴፰ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ "አጥፊው በተጠባባቂ እንዲጠበቅ" የሚለው ቀርቶ "አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤት የተለቀቀውን እሥረኛ በፖሊስ ቁጥጥር እየተደረገበት እንዲጠበቅ ሊያደርገው ይችላል" በሚል ሀረግ ተስተካክሏል።

ንዑስ ቁጥር (፩) እና (፫) የቃላት ማስተካከያ ተደርጐባቸው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆነዋል።

www.abyssinialaw.com

ቶጽ ፻፵፱ <u>ተፈቅደው የተሰጡትን ወረቀቶች ለጊዜው መልሶ መውሰድ</u>♦

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፶፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፵፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "በግልጽ የተሰጡትን ወረቀቶች ስለ መውሰድ።" የሚል ነው። ሆኖም ይዘቱ እንደሚያመለክተው ወረቀቶቹ የተሰጡት ወይም የሚሰጡት ተፈቅደው በመሆኑ እና በኋላም ጥፋተኛ ከተባለው ሰው ተመልሰው የሚወሰዱ በመሆናቸው ይህን ይዘቱን በሚገባ ለማንፀባረቅ እንዲቻል ስያሜው "ተፈቅደው የተሰጡትን ወረቀቶች ለጊዜው መልሶ መውሰድ።" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

ይዘቱም አንዳንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቶጽ ፻፶ <u>ወንጀለኛውን ከአገር ማስወጣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፶፬ ድንጋጌ በሚከተለው አኳኋን ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ወንጀለኛው በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት እንዳይኖር ስለመከልከልና ካገር ስለማስወጣት" ይል ነበር። የማያስፈልጉ ቃላት እንዲሰረዙ የተደረገ ሲሆን በአገር እንዳይኖር መከልከልና ማስወጣት ሁለቱም ሀሳቦች ተመሳሳይ በመሆናቸው ድግግሞሽን ለማስቀረት በማሰብ፣ ስያሜው "ወንጀለኛውን ከአገር ማስወጣት" እንዲል ተደርጓል።

ይዘቱንም በሚመለከት በንዑስ ቁጥር አንድ መግቢያ ላይ "ተከሳሽ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ተቀጪው" በሚል ተተክቷል።

በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያውና ሶስተኛው ፓራግራፍ ላይ ከአሁኑ የፖለቲካ ስርዓት ጋር የማይጣጣሙ ቃላት እንዲሰረዙ ተደርጓል። በዚሁ ንዑስ ቁጥር በሁለተኛው ፓራግራፍ "ወይም ልማደኛ በመሆኑ ጽኑ ግዞት በተወሰነበት" የሚለው ሀረግ፣ የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ ከወንጀል ሕጉ እንዲወጣ በመደረጉ ተሰርዟል። ኃላፊነት የሌለው ወይም ኃላፊነቱ ከፊል የሆነው ሰው አደገኛ የሚሆነው ለማን እንደሆነ ባለማመልከቱ ለህዝብ ደህንነት የሚል ሀረግ ተጨምሮበትና አፃፃፉም ተቃንቶ ተዘጋጅቶአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የፖለቲካ መምሪያና ያስተዳደር ክፍሎችን የሚለው ሀረግ ቢወጣ "ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች" በሚለው ሀረግ መሠረት ሐሳብ ሊሸፈን እንደሚችል በመገመት ተሰርዟል። በሁለተኛውም ፓራግራፍ "ይህን ስለመሰሰው አጋጣሚ ነገር የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ግዛት ገብቶ በሚቀመጥበት ጊዜ" የሚለው ሀረግ ቢወጣ የሚያጎድለው ፍሬ-ነገር ባለመኖሩ ተሰርዟል። ከላይ ከተገለጹት ማሻሻያዎች በተጨማሪ ንዑስ አንቀጹ የተሻለ አገላለጽ እንዲኖረው የአንዳንድ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

---

ንጀል ሕጉ በአንቀጽ 149 "ጠሰፖርቶች" የሚለው ቃል "ፓስፖርቶች" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com



በንዑስ ቁጥር ሦስትም "የቅጣቱ ውሳኔ" የሚለው ሀረግም ከአገር የማስወጣት ውሳኔ የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ እንጂ የቅጣት ውሳኔ ነው ለማለት ስለማይቻል ተሰርዞ "የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

በተጨማሪም ድንጋጌው የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ተቀርጿል::

አንቀጽ ፻፶፩ አፈፃፀሙ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፶፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፩ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) "አጋጣሚው ሁኔታ ይህ ሆኖ ሲገኝ ከቅጣቱ ከተማረ በኋላ ነው::" የሚለው አገላለጽ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆንና አሳስፈላጊ የሆኑ ቃላት እንዲወጡ ለማድረግ "ከቅጣቱ በይቅርታ ወይም በምህረት ከተለቀቀ በኋላ ነው::" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

የንዑስ ቁጥር (፫) የመጀመሪያው ፓራግራፍ የእንግሊዝኛው ቅጂ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የአማርኛው ቅጂ ጋር አንድ አይነት አይደለም:: የእንግሊዝኛው ትርጉም "In the case of an offender whose resposibility is limited and when circumstances so justify the penalty may be first inforced and expultion substituted for the ordinary measures of treatment or safety (Art. 134 or 135) " የሚል ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለተሰመረበት ሀረግ የሰጠው ትርጉም "ከአገር የመውጣቱም ውሳኔ በመታከም ወይም ስለፀጥታ አጠባበቅ በጥንቃቄ አፈፃፀም በተለመደው ደንብ ይለወጥለታል:: /ቁጥር ፻፴፬ እና ፻፴፭/::" የሚል ነው:: በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት "ህክምናውና በተወሰነ ቦታ መቀመጡ ቀርቶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል" የሚል ሲሆን የአማርኛው ትርጉም ግን "ከአገር እንዲወጣ መደረጉ ቀርቶ እንዲታከም ወይም በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ ይደረጋል" የሚል ነው:: ትክክለኛው አሳብ የእንግሊዝኛው ሆኖ ይታያል:: ከፊል ኃላፊነት ያለው ሰው ቅጣቱን ከጨረሰ በኋላ መታከም ወይም በተወሰነ ቦታ መቀመጡ መደበኛ ሁኔታ ነው:: ይህን ማድረጉ ከአገሪቱ የሚጠበቅ ነው:: ነገር ግን በቂ ምክንያቶች ሲኖሩ ሕክምናው ወይም በተወሰነ ቦታ መቀመጡ ቀርቶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል ለማለት ነው::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ግን ከአገር ማስወጣቱ መደበኛ እርምጃ ሆኖ ካስፈለገ እንዲታከም ወይም በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት የሚል ነው:: በዚህ ምክንያት በእንግሊዝኛው አይነት ተሻሽሎ ተረቅቋል::

የቁጥር ፻፶፭/፫/ ፓራግራፍ ሁለት ፍፁም ኢ-ኃላፊ የሆነን ጥፋተኛ የሚመለከት ሲሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "እንዲሁም በሙሉ ኃላፊነት በማይጠየቅ ጥፋተኛ ላይ የሚደረገው ውሳኔ ከክሱ ውጭ ያደረገው እንደሆነ ወይም ፍርዱ በሙሉ ነፃ ያደረገው እንደሆነ" የሚለው ሀረግ ስህተት ነው::

ሳደረገው ወንጀል ፍፁም ኢ-ኃላፊ የሆነ ሰው ጥፋተኛ ሊባል ስለማይችል ምን ጊዜም ከክስ ውጭ ወይም ከፍርዱ ነፃ እንደሆነ ግልጽ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ አነጋገር ተሰርዞ ፓራግራፉ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

www.abyssinialaw.com

### ቀጽ ፻፶፪ የጥንቃቄ እርምጃን ለሙከራ ለጊዜው ማገድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ በመነሻው ላይ "የተሰጠውን ውሳኔ" የሚለው ሀረግ ውሳኔው ስለምን እንደሆነ የማያመለክት በመሆኑ ይዘቱ ደግሞ የሚገልጸው የጥንቃቄ እርምጃ ለሙከራ ለጊዜው የሚቋረጥበትን ሁኔታ በመሆኑ ርዕሱ ይህን ይዘቱን እንዲገልጽ "የተሰጠውን ውሳኔ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የጥንቃቄ እርምጃን" በሚል ተተክቶ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ሆኖ ተሻሽሎአል::

ይዘቱም በአንድ ስፍራ ከመድረስ ወይም ከመኖር በተጨማሪ ውሎ ማደርም በጥንቃቄ እርምጃው ውስጥ ሊካተት ስለሚችልና ይህም ለሙከራ ሊታገድ ስለሚችል "ውሎ ከማደር" የሚል ሀረግ እንዲጨመርበት ሆኖአል:: በተጨማሪም ግልጽ እንዲሆን የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተሻሽሏል::

### ቀጽ ፻፶፫ የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔዎች ሲጣሱ የሚወሰን ቅጣት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ ፀጥታ አጠባበቅ የተወሰነውን ደንብ በመጣስ የሚደረግ የቅጣት ውሳኔ::" የሚል ነበር:: ነገር ግን ይዘቱ የሚያመለክተው የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔዎች ሲጣሱ ስለሚወሰነው ቅጣት በመሆኑ ስያሜው ተሻሽሎ ይዘቱን በሚያመለክት መልክ "የጥንቃቄ እርምጃ ውሳኔዎች ሲጣሱ የሚወሰን ቅጣት::" በማለት እንዲነበብ ተደርጓል::

ይዘቱም "የንጉሠ-ነገሥቱ ግዛት" የሚለው ሀረግ ከላይ በተደረጉት ማሻሻያዎች ውስጥ በተገለጸው ምክንያት ተሰርዞ "ወደ" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ኢትዮጵያ ግዛት" የሚል ሀረግ ተተክቶአል:: በተጨማሪም ድንጋጌውን ግልጽ ለማድረግ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተረድጎአል::

## ንዑስ ክፍል አራት
## የማሳወቅ እርምጃዎች

ይህ ንዑስ ክፍል በቀድሞው ሕግ ላይ የተመደበው በክፍል ደረጃ ነበር:: በዚህ ሕግ ግን ክፍሉ ያለበት ምዕራፍ ወደ ክፍል ስለተለወጠ ክፍል የነበረው በንዑስ ክፍል ደረጃ እንዲቀመጥ ተደርጓል::

### ቀጽ ፻፶፬ ለሚመለከተው ባለሥልጣን ማሳወቅ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፬ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፻፶፰ ስያሜ መጀመሪያ ላይ "ለደንበኛው" የሚለው ቃል ግልጽ ባለመሆኑ ተሰርዞ "ለሚመለከተው" በሚል ቃል ተተክቶአል:: እንዲሁም በዚሁ ስያሜ መጨረሻ ላይ "ስለሚሰጥ ማስታወቂያ" በማለት የተመለከተው "ማሳወቅ" በሚል ቢተካ ሊተላለፍ የተፈለገውን--መልዕክት በሚገባ የሚገልጽ በመሆኑ በዚሁ ቃል እንዲተካ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

ይዘቱም በመጀመሪያ ፓራግራፍ "የክፍሉ ባለሥልጣን" በማለት የተመለከተው ግልጽ ባለመሆኑ ተሰርዞ "ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሥልጣን" በሚል እንዲተካ ሆኖአል:: እንዲሁም በዚሁ ፓራግራፍ የሚመለከተው ባለሥልጣን ጉዳዩን ብቻ እንዲያወቀው ሳይሆን እንዲያስፈጽም ወይም እንዲቆጣጠር አስፈላጊ ሊሆን ስለሚችል "እንዲያውቀው ከሚለው" ቃል በኋላ "እንዲያስፈጽም ወይም እንዲቆጣጠር" የሚል ሀረግ ተጨምሮአል:: በዚሁ ፓራግራፍ "ለአስተዳደር፣ ለብሔራዊ (ለባሳገር) ... ወዘተ ከሚሉት መዘርዝሮች ውስጥ "ለብሔራዊ (ባሳገር)" የሚለው ሀረግ ግልጽ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: በምትኩም በዚሁ ፓራግራፍ

መጨረሻ ላይ ሳይጠቀሱ ሊቀሩ የሚችሉ ዝርዝር ባለሥልጣናትን ለማካተት እንዲያስችል "አግባብ ላለው ሌላ አካል" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጎበታል:: ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፶፰ <u>ፍርድን ለህዝብ መግለጽ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፰ ሆኖ ገብቷል::

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ የተመለከተው ግልጽ እንዲሆን የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: በሁለተኛው ፓራግራፍ "በቀጥታ እንዲገለጽ ፍርድ ቤቱ ያዛል::" የሚለው ሀረግ "ፍርድ ቤቱ ለህዝብ መገናኛ በሆኑ ዘዴዎች እንዲገለጽ ያዛል" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

በዚህ ንዑስ ቁጥር በሦስተኛው ፓራግራፍ የተደነገገው ፍሬ-ነገር በወንጀል ሕግ ከሚካተት ይልቅ በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቢካተት የተሻለ እንደሆነ በማመን እንዲሰረዝ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፪) በመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ የተሰጡትን አማራጮች ሰፋ ለማድረግ እንዲያስችል "በማናቸውም የመገናኛ ብዙኃን ዘዴ በማሰራጨት" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጎአል:: በተጨማሪም የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፶፱ <u>በፍርድ መመዝገቢያ ላይ መመዝገብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፱ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷ ስያሜ "ፍርድን በግል የፍርድ ሰሌዳ ላይ መመዝገብ::" የሚል ነው:: ነገር ግን በዚሁ ርዕስ ስያሜ በግል የፍርድ ሰሌዳ የሚለው ሀረግ ግልጽ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጎ "በፍርድ መመዝገቢያ" በሚል ሀረግ ተተክቶ ከተሻሻለ በኋላ ስያሜው "በፍርድ መመዝገቢያ ላይ መመዝገብ" በማለት እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱንም በሚመለከት በንዑስ ቁጥር (፩)ም ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገጉት ፍሬ ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አራት
## ለአካለመጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ የጥንቃቄ እርምጃዎችና ቅጣቶች
## ክፍል አንድ
## ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ያለው አካለመጠን ያልተደረሰበት ዘመን
### ንዑስ ክፍል አንድ
### መደበኛ የጥንቃቄ እርምጃዎች

ቁ. ፻፶፯ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ፻፶፯ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በላይ አግባብነት ያላቸው አጣቃሽ አንቀጾች ተገቢ በሆኑ ስፍራዎች እንዲገቡ ተደርጓል::

ቁ. ፻፶፰ ሕክምና ወደሚደረግበት ተቋም መላክ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርጎበታል::

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ "ዕውቀቱ ሙሉ ከመሆን የዘገየ" የሚለው ሀረግ ግልጽነት የሚጎድለው ስለሆነና ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የአእምሮ ዕድገቱ የዘገየውን ወጣት ጥፋተኛ ለማመልከት በመሆኑ ሀረጉ ተሰርዞ "የአእምሮ ዕድገቱ የዘገየ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል:: እንዲሁም በዚሁ ፓራግራፍ "አእምሮው የተበላሸ" የሚለው አገላለጽ ፀያፍ በመሆኑ" አእምሮው የታመመ" በሚል ተተክቶአል:: ከዚህም በተጨማሪ ዕውር፣ ዲዳ፣ ደንቆሮ የሚሉት ዝርዝሮች ዐይነ-ስውርነት ወይም መስማትና መናገር አለመቻል በራሳቸው የወንጀል መንስኤዎች እንደሆኑ አስመስሎ የሚያሳይ በመሆኑ ከዝርዝሩ ውስጥ እንዲወጡ ተደርጓል::

በዚህ የመጀመሪያ ፓራግራፍ መጨረሻ ላይም ሌሎች ለወንጀለኛነት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉና ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች "በናርኮቲክ ወይም በሌሎች በሚያፈዙ ዕጽዋት የተመረዘ" የሚሉ በመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ እንዲገቡ ተደርጓል::

ድንጋጌው ሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቁ. ፻፶፱ ቁጥጥር በማድረግ የሚሰጥ ትምህርት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፶፱ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ "... ታማኝነት ላለው ራሱን ለቻለ ጨዋ ሰው ሞግዚት ወይም ሥራ አልማጅ ቤተዘመድ ወይም ህፃናትን ለመጠበቅ ለማስተማር ለቆመ ቤት" በሚለው ሀረግ ጠባቂ የሚሆነውን ሰው ታማኝ መሆኑ ወይም ራሱን የቻለ ጨዋ

www.abyssinialaw.com


ሰው መሆኑ ብቻ ለጠባቂነት ብቁ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ ጠባቂ የሚሆነው ሰው ከተዘረዘረው በላይ ብዙ ነገሮችን አሟልቶ የሚገኝ ሰው መሆን ስላለበት በደፈናው "ብቁ ለሆነ ሰው" ቢባል የተሻለ ይሆናል፡፡

ህፃናትን ለመጠበቅና ለማስተማር የሚቋቋመው ቤት ሳይሆን ድርጅት ስለሆነ "ሕፃናትን ለመጠበቅና ለማስተማር ለተቋቋመ" የሚል ሀረግ "ድርጅት" ከሚለው ቃል በፊት ገብቶ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ተደርጓል፡፡

ጠባቂዎች በአደራ የተሰጣቸው ወጣት ወንጀለኛ መልካም አስተዳደግና ትምህርት ማግኘቱን ሁልጊዜ ሳይከታተሉ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ያለ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ የቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸሙንና የአፈጻጸሙንም ሥርዓት መልካም ፍሬ እንዲያስገኝ የሚረዳው የጥበቃው ባልደረባ ስለሆነ (አንቀጽ ፪፻፰) በጠባቂዎች ላይ ቁጥጥር ቢደርግ የወጣት ወንጀለኛው አስተዳደግና ትምህርት መልካም ፍሬ ሊያስገኝ ይችላል በሚል ግምት በንዑስ ቁጥሩ የመጨረሻ ፓራግራፍ ላይ የነበረው አገላለጽ ይህን አሳብ በተሻለ ሁኔታ እንዲያንጸባርቅና እንዲገልጽ ተደርጎ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) በመጀመሪያው ፓራግራፍ የተገለጸው ፍሬ-ነገር ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ በዚህ ንዑስ ቁጥር በሁለተኛው ፓራግራፍ "ስለ ጠባዩ ዋስ" የሚለው ሀረግ አካለመጠን ያላደረሰውን ወጣት ጥፋተኛ ብቁ ለሆነው ሰው የሚሰጠውን ዋስ እንዲሆነው ሳይሆን ጠባዩን እንዲቆጣጠረውና እንዲጠብቀው በመሆኑ ከላይ በትእምርተ ጥቅስ የተቀመጠው ሀረግ ተሰርዞ "ለጠባዩ ጠባቂ" በሚል ተተክቶአል፡፡ በተጨማሪም ፓራግራፉ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፫) የተገለጸው ፍሬ-ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

## አንቀጽ ፻፷ ተግሳጽና ወቀሳ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፩ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷ ሆኖ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ "እንዲህ ያለው አሠራር ተገቢና ውጤት የሚሰጥ መስሎ በታየው ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጥፋታቸውን በተግሳጽና በወቀሳ ያልፈዋል፡፡" የሚለው አገላለጽ አካለመጠን ያልደረሰውን ጥፋተኛ የግድ ሁልጊዜ ተግሳጽም ወቀሳም ይደርስበታል ብሎ ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ለአካለመጠን ያልደረሰውን ጥፋተኛ በተግሳጽ ወይም በወቀሳ ስለሚያልፈው በዚህ ንዑስ ቁጥር ተግሳጽና ወቀሳ "ና" በሚል መጣመራቸው ቀርቶ "ወይም" በሚል በአማራጭ ተጽፈዋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ንዑስ ቁጥር ላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎአል፡፡

የንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያው ፓራግራፍ አገላለጽ በፈረንሳይኛው ቅጂ መሠረት የተስተካከለ ሲሆን ሁለተኛው ፓራግራፍ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## አንቀጽ ፻፷፩ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ማድረግ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፮ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

www.abyssinialaw.com



የድንጋጌው ስያሜ "በትምህርት ቤት ወይም በቤቱ ስለ ማገድ" የሚል ነው:: ሆኖም "ስለማገድ" የሚለው አገላለጽ ግልጽ ባለመሆኑና ዓላማውም ወጣት ጥፋተኛው በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ የሚቆይበትን ሁኔታ ለማመልከት በመሆኑ ስያሜው ተሻሽሎ "በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ማድረግ::" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱም ለአካለመጠን ያልደረሰው ወጣት ጥፋተኛ በቀላሉ የሚታረም መስሎ ሲታይ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤቱ ተወስኖ ሳይወጣ በዕረፍት ጊዜው የተወሰነ ሥራ በግዴታ እንዲሰራ መደረግ ያለበት ለዕድሜውና ለኑሮው ተስማሚ የሆነውን ሥራ ነው:: ይህ ካልሆነ የግዴታው ስራ ለወጣት ጥፋተኛው የሚፈለገውን መልካም ውጤት ያስገኛል ብሎ ለመገመት አዳጋች ነው:: ስለዚህ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፻፷፭ በመጀመሪያው ፓራግራፍ"... በዕረፍት ሰዓቱ ወይም በዕረፍት ቀኖቹ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ለዕድሜው በሚስማማና በተወሰነ ሥፍራ እንዲሰራ" የሚል ሀረግ ተጨምሮ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ሆኖ ተዘጋጅቷል::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ፓራግራፎች የተደነገጉት ፍሬ-ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

ቀጽ ፻፷፪ <u>ወደጠባይ ማረሚያ ተቋም መላክ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፶፮ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፪ ሆኖ ገብቷል::

በመጀመሪያው ፓራግራፍ "ከዚህ በላይ የተመለከተው ውሳኔ" በማለት የተገለጸው ግልጽ ባለመሆኑና ከላይ የተመለከቱት ውሳኔዎች ሳይሆኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች በመሆናቸው ይህንኑ ለማመልከት ከላይ የተገለጸው ሀረግ ተሰርዞ "ፍርድ ቤቱ የወጣት ወንጀል አድራጊውን ፀባይ ወይም የቀድሞ ታሪኩን መጥፎነት" በሚል አገላለጽ እንዲጀምር ተደርጓል:: በተጨማሪም ፓራግራፉ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ፓራግራፎች የተገለጹት ድንጋጌዎች ግልጽ እንዲሆኑ ያንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

ቀጽ ፻፷፫ <u>የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፯ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ውሳኔው የሚቆይበት ጊዜ" የሚል ነበር:: ሆኖም ይዘቱ የሚያመለክተው የጥንቃቄ እርምጃዎቹ የሚቆዩበትን ጊዜ በመሆኑ ይህንኑ በግልጽ ለማመልከት ሲባል ስያሜው "የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ" በሚል ተሻሽሏል::

ይዘቱን በተመለከተ ንዑስ ቁጥር (፩) የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያና የተሻለ የአጣቃሽ አንቀጾች የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com



በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፻፷፬ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መለወጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፫ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፬ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ውሳኔዎችን ስለመለወጥ።" የሚል ነበር። ሆኖም የሚለወጡት ውሳኔዎች በግልጽ ያልተመለከቱ በመሆናቸው ይዘቱ ደግሞ እንደሚያመለክተው ተለዋጮቹ የጥንቃቄ እርምጃዎች በመሆናቸው ስያሜው ይዘቱን ያንፀባርቅ ዘንድ ተሻሽሎ "የጥንቃቄ እርምጃዎችን መለወጥ።" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል።

ይዘቱም ፍርድ ቤቱ ስለወጣት ወንጀለኛው የተሰጠውን ትዕዛዝ በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ የሚችለው "በመሥሪያ ቤቱ መኖሪያ ክፍል ወይም በተጠባባቂው ባለሥልጣን ራፖር መሠረት" እንደሆነ ተደንግጓል። "በመሥሪያ ቤቱ መኖሪያ ክፍል" የሚለው ሀረግ የጠባይ ማረሚያውን ተቋም ለማለት የገባ ሀረግ ይመስላል። ለማናቸውም ይህ ሀረግ ግልጽ ካለመሆኑም በቀር እንዲህ ያለውን ራፖር የሚያቀርበው የጠባይ ማረሚያ ተቋም ኃላፊ ወይም የጥበቃው ባልደረባ ስለሆነ "በመሥሪያ ቤቱ መኖሪያ ክፍል" የሚለው ሃረግ ተሰርዞ "የተቋሙ አስተዳደር" በሚል ሃረግ ተተክቶአል። ከዚህም በቀር በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፻፷፫ የተመለከተው ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቃንቷል። አቀራረቡም ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፻፷፭ የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጋዊ ውጤት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፷፬ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፭ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ሕጋዊያን ውጤቶች።" የሚል ነበር። ሆኖም ህጋዊ ውጤቶቹ የምን እንደሆኑ ስያሜው ስለማያመለክትና ይዘቱ የሚገልጸው የጥንቃቄ እርምጃዎችን ህጋዊ ውጤት በመሆኑ ይህንኑ እንዲያንፀባርቅ ስያሜው "የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጋዊ ውጤት።" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

ይዘቱም ህክምና፣ ትምህርት ወይም የጠባይ ማረም የጥንቃቄ እርምጃዎች እንጂ "ቅጣቶች" ስላልሆኑ ቅጣቶች የሚለው ቃል ተሰርዞ "የጥንቃቄ እርምጃዎች" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። ከዚህም በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>ቅጣቶች</u>

ቀጽ ፻፷፮ <u>መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፮ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ላይ ከቁጥር ፻፶፰ እስከ ፻፷፪ የተመለከቱት የጥንቃቄ እርምጃዎች ስለሆኑ "የተመለከቱት ውሳኔዎች ተሰጥተው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የተደነገጉት የጥንቃቄ እርምጃዎች" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። "አስፈላጊው ምርመራ ከተደረገ በኋላ" የሚለው አነጋገር ምን ዓይነት ምርመራን ለማመልከት እንደሆነ ግልጽ አይደለም። በሕጉ በፈረንሳይኛው ቅጂ ግን ምርመራውን አስመልክቶ ቁጥር ፶፰ (በዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፩) ስለተጠቀሰ ምርመራው፣ የልዩ አዋቂዎችን ምርመራ ለማመልከት እንደሆነ ግልጽ ነው። በመሆኑም "አስፈላጊው ምርመራ ከተደረገ በኋላ" የሚለው ተሰርዞ "አስፈላጊ ከሆነም የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ምርመራዎች እንዲደረጉ ካዘዘ በኋላ (አንቀጽ ፶፩)" በሚል ሀረግ ተተክቷል። በተጨማሪም ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፻፷፯ <u>መቀጮ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፩ ድንጋጌ መጠነኛ መሻሻያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፯ ሆኖ ገብቷል።

ይዘቱም ንዑስ ቁጥር (፩) "ፍርድ ቤቱ እንደጥፋቱ ከባድነትና እንደችሎታው መጠን መቀጮውን እንዲከፍል ይፈርድበታል።" የሚለው ሐረግ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘውም ጊዜ ለአካለመጠን ያልደረሰው ጥፋተኛ መቀጮ እንዲከፍል መፍረድ እንዳለበት የሚደነግግ ነው። ዳሩ ግን ለአካለመጠን ያልደረሰው ጥፋተኛ መቀጮ መክፈሉ ቅጣት ሆኖ የሚሰማው የሚያስተምረውና የሚመልሰው መሆኑን ለማመዛዘን ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤቱ ስለሆነ ሁኔታዎችን አመዛዝኖ ለአካለመጠን ያልደረሰው ጥፋተኛ መቀጮ እንዲከፍል ፍርድ የመስጠት ምርጫው የፍርድ ቤቱ መሆን ስለሚገባ "ይፈርድበታል" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ሊፈርድበት ይችላል።" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። ንዑስ ቁጥሩ የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ግልጽ እንዲሆን የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በሁለተኛው ፓራግራፍ "ቅጣቱን ፍርድ ቤቱ በሚቆርጠው ልክ በማረፊያ ቤት እስራት ሊለውጠው ይችላል።" የሚል ሀረግ ይነበባል። ከሀረጉም መጨረሻ ቁጥር ፻፷፰ ተጠቅሶአል። ቅጣቱ ሲባል የመቀጮውን ቅጣት ለማለት ስለሆነ "ቅጣቱን" የሚለው ቃል ተሰርዞ "በመቀጮው ምትክ" የሚል ሀረግ ተተክቶአል። ፍርድ ቤቱ የሚቆርጠውም የጊዜ ልክ ነው። ስለዚህ "የጊዜ" የሚል ንዑስ ሀረግ "ልክ" ከሚለው ቃል በፊት ገብቶአል። "በማረፊያ ቤት እስራት ሊለውጠው ይችላል።" የሚለውን ሀረግ በሚመለከትም የተጠቀሰው ቁጥር ፻፷፰ ስያሜ "በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ስለማድረግ" በሚል ስለተሻሻለ "በማረፊያ ቤት እሥራት ሊለውጠው ይችላል" የሚለው ሀረግ ተሠረዞ "በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ

www.abyssinialaw.com

እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል::" በሚል ሀረግ ተተክቶ በተከታዩ ከተጠቀሰው አንቀጽ ፻፷፮ ጋር እንዲነበብ ተደርጓል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፸፪ ድንጋጌ መሠረዝ</u>

ይህ ድንጋጌ ከኢትዮጵያ ፌዴሬራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፴፮ እንዲሁም ኢትዮጵያ ከተቀበለችው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን ጋር የማይጣጣም በመሆኑ እንዲሠረዝ ተደርጓል::

## አንቀጽ ፻፷፯ <u>እሥራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፸፫ ድንጋጌ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፯ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው ፍሬ ነገር ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተሻሽሎአል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ለአካለ መጠን ያልደረሰው ጥፋተኛ ታስሮ የሚቆይበት ጊዜ ከሶስት ዓመት እንደማያንስ የተገለጸው ለአንዳንድ ለአካለመጠን ያልደረሱ ወጣት ጥፋተኞች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ቀድመው የመታረም አዝማሚያ የሚያሳዩ ቢሆን ጊዜውን ለማሳጠር ፍርድ ቤቱን የሚገድበው በመሆኑ መነሻው ተሻሽሎ "ጊዜውም" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ከአንድ ዓመት ሳያንስ" በሚል ሀረግ ተሻሽሎ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ሆኖ ተዘጋጅቷል:: ከዚህም በተረፈ ንዑስ ቁጥሩ የአንዳንድ ሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር ሶስት የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና የአጠቃሽ አንቀጾች አቀማመጥ ማስተካከያ ተደርጎበታል::

<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>
<u>የወል ድንጋጌዎች</u>

## አንቀጽ ፻፷፰ <u>ቀላል ሁኔታዎች፤ በበቂ ምክንያት ቅጣትን ማስቀረት</u>

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፷፰ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተስተካክሎአል::

በቁጥር ፻፸፬ ድንጋጌ ሲያሜ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ይዘቱም በሁለተኛው ፓራግራፍ "ይልቁንም" በማለት የተመለከተው "በተለይ" ለማለት በመሆኑ በዚሁ አኳኋን ተስተካክሎአል:: እንዲሁም "አስፈላጊዎቹ ቅጣቶች በአባት" የሚለው ሀረግ ለአካለመጠን ያልደረሰውን ወጣት አስፈላጊ በሆነው መልክ የማረሙ ኃላፊነት የአባት ብቻ አስመስሎ የሚያሳይ በመሆኑ እናቶችም ቢሆኑ ይህን ኃላፊነታቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲወጡ ለማድረግ እንዲያስችል ልዩነት ሳይደረግ

www.abyssinialaw.com

"የጥንቃቄ እርምጃዎች ወይም ቅጣቶች በወሳጅ..." በሚል እንዲሻሻል ሆኖአል:: ከዚህም በተረፈ በድንጋጌው መጨረሻ ላይ "የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ቅጣቱን ሊያስቀርለት ይችላል::" የሚል ሀረግ ይነበባል:: ዳሩ ግን ፍርድ ቤቱ ለአካለመጠን ላልደረሰው ወጣት ጥፋተኛ ሊያስቀርለት የሚችለው ቅጣቱን ብቻ ሳይሆን የጥንቃቄ እርምጃውንም ነው:: በሕጉ የእንግሊዝኛውና የፈረንሳይኛው ቅጂዎችም ውስጥ ፍርድ ቤቱ የጥንቃቄ እርምጃውን ወይም ቅጣቱን ሊያስቀርለት ይችላል::" ከሚለው ሀረግ በፊት "የጥንቃቄ እርምጃውን ወይም" የሚል ሀረግ ተጨምሮአል:: በተጨማሪም ድንጋጌው ግልጽ ይሆን ዘንድ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፹ <u>ልዩ የይርጋ ደንብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፮ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) "ደንበኛው የይርጋ ዘመን" ይል የነበረው በአንቀጽ ፩፻፲፮ የተመለከተውን የይርጋ ዘመን ለማመልከት በመሆኑ ተስተካክሎ "መደበኛ የይርጋ ዘመን" በሚል ተተክቶአል:: እንዲሁም ለአካለመጠን ያልደረሰው ጥፋተኛ ላይ ክስ መቅረት ያለበት የመደበኛው የይርጋ ዘመን አጋማሽ በማለፉ ብቻ ሳይሆን በልዩ ይርጋም አጋማሽ ማለፍ ተመሳሳይ ሁኔታ መፈጸም ስላለበት ከላይ ከተተካው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም ልዩ የይርጋ ዘመን" የሚል ሀረግ ተጨምሮበት ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ተደርጎ ተዘጋጅቷል:: ከላይ በተደረገው ለውጥ መሠረትም አጣቃሽ ከሆነው አንቀጽ ፩፻፲፮ በተጨማሪ አንቀጽ ፩፻፲፯ በአጣቃሽ አንቀጽነት ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ፍሬ ነገር ግልጽነት እንዲኖረው የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፹፩ <u>ውሳኔውን በገደብ ማገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፯ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ውሳኔውን አግዶ ስለማቆየትና ተቀጪውን በሙከራ ስለማቆየት" ይል ነበር:: ሆኖም በአጭር አገላለጽ ተስተካክሎ "ውሳኔውን በገደብ ማገድ" እንዲል ተደርጓል:

የዚህ አንቀጽ ስያሜ "ውሳኔውን በገደብ ማገድ" የሚል ሲሆን ይዘቱም የፍርድ ቤትን ውሳኔ ስለማገድ እንጂ አቃቤ ሕግ የሚያቀርበውን ክስ የሚመለከት አይደለም:: ስለ ክስ አቀራረብ አንቀጽ ፻፹ ላይ ተመልክቷል:: በመሆኑም "ክስ በቀረበ ጊዜ" የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: በተጨማሪም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፹፪ <u>የጥንቃቄ እርምጃው ወይም ቅጣቱ በሕዝባዊ መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፰ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተስተካክሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፪ ሆኖ ገብቷል:: ---

www.abyssinialaw.com

የድንጋጌው ስያሜ "በሕዝባዊ መብት ላይ ቅጣቱ የሚያስከትለው ውጤት::" የሚል ነው:: ነገር ግን ቀደም ሲል ከላይ የተደነገጉት የሚያመለክቱት ቅጣትን ብቻ ሳይሆን የጥንቃቄ እርምጃንም ሆነ ቅጣትን እንዲያመለክት "የጥንቃቄ እርምጃው ወይም ቅጣቱ በሕዝባዊ መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት::" በሚል እንዲሻሻል ተደርጎአል::

ይዘቱም ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፻፭፫ <u>ጠቅላላ የሆኑ የመከላከልና የመጠበቅ እርምጃዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፭፰ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፭፫ ሆኖ ገብቷል::

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ የተደነገገው የአጣቃሽ አንቀጾች አቀማመጥና የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በሁለተኛው ፓራግራፍ "ለማህበራዊ ኑሮ" በማለት የተገለጸው ግልጽ ባለመሆኑና ለማመልከት የተፈለገውን ለሕብረተሰቡ የሚለውን በመሆኑ ከላይ በትዕምርተ ጥቅስ የተቀመጠው ተሰርዞ "ለሕብረተሰቡ" በሚል ተሻሽሎአል:: እንዲሁም ፓራግራፉ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በሶስተኛው ፓራግራፍ ለአካለመጠን ባልደረሰ ወንጀለኛ ላይ የተወሰነው ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ የማስፈጸም ጉዳይ" ለክፍሉ የሞግዚትነት ባለሥልጣኖች መገለጽ አለበት::" በሚል ተደንግጎአል:: ነገር ግን "ለክፍሉ የሞግዚትነት ባለሥልጣኖች" የሚለው ሀረግ ግልጽ ባለመሆኑ ተብራርቶ" የሞግዚት ስልጣን ለተሰጣቸው ሰዎች ወይም ተቋሞች" በሚል ተሻሽሎአል:: እንዲሁም የሞግዚትነት ስልጣን ካላቸው ሰዎች ወይም ተቋሞች ሌላ ለወጣቱ መታረም የሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች ለአካለመጠን ባልደረሰው ጥፋተኛ ላይ የተወሰደውን የጥንቃቄ እርምጃ ወይም ቅጣት እንዲያውቁት ቢደረግ የተሻለ እንደሆነ በማመን "የሞግዚትነት ሥልጣን ለተሰጣቸው ሰዎች ወይም ተቋሞች" ከሚለው ሀረግ አስቀድሞ "ለሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል::

አንቀጽ ፻፭፬ <u>የፍርድ ውሳኔን መግለጽና በፍርድ መዝገብ ላይ መመዝገብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፭፱ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፭፬ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "በፍርድ ሰሌዳ" በማለት የተገለጸው ቀደም ሲል ከላይ በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት ተስተካክሎ "በፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ምንጊዜም በግልጽ በማስታወቂያ አይወጣም::" በማለት የተደነገገው ግልጽ ካለመሆኑም በቀር በጋዜጣና መጽሄት መሰል ነገሮች ፍርዱ እንዳይገለጽ የሚከለከል መስሎ ስለሚታይ ሌሎች የህዝብ መገናኛ ዘዴዎችን በሚጨምር መልክ ተሻሽሎ "ምንጊዜም በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አይገለጽም::" በሚል እንዲነበብ ተደርጓል:: እንዲሁም የሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

ሁለተኛውም ፓራግራፍ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቅጽ ፻፸፩ ፍርዱን መሠረዝና መሰየም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፩ ሆኖ ገብቷል።

ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ወይም ባለመብቶቹ ሲጠየቁ ከእስራት ቅጣቱ በቀር ለአካለመጠን ባልደረሰው ወጣት ላይ የተወሰኑት የጥንቃቄ እርምጃዎችና ሌሎች ቅጣቶች በተፈጸሙ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተገቢው ባለሥልጣን ከፍርዱ መዝገብ ውስጥ እንዲሰረዙ ለማዘዝ የሚችል መሆኑ ተደንግጓል። ለአካለ መጠን ባልደረሰው ወጣት ላይ የተወሰኑት የጥንቃቄ እርምጃዎችና ቅጣቶች ከፍርዱ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ እንዲሰረዙ ለማዘዝ እንዲቻል ከተፈጸሙ በኋላ የሁለት አመት ጊዜ ብቻ በቂ ሳይሆን ለመሰየም የሚያስፈልጉ ሌሎችም ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል። ስለዚህ "በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ለመሰየም የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች የተሟሉ ከሆነ "የሚል ሀረግ ተጨምሮአል። ከዚህም በቀር በዚሁ ቁጥር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደረጎበታል።

በአማርኛው ቅጂ ላይ "የሁለት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "በተፈጸመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ" በሚል የተሻሻለው በእንግሊዘኛው ቅጂ መሰረት ነው።

## ክፍል ሁለት
## ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ያለ ወጣት ወንጀል አድራጊ

ቅጽ ፻፸፪ መደበኛ ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፪ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "መጠነኛ ሁኔታ" የሚል ነበር። ነገር ግን ይዘቱ የሚያመለክተው ስለመጠነኛ ሁኔታ ሳይሆን ስለመደበኛ ሁኔታ በመሆኑ ስያሜው ተሻሽሎ "መደበኛ ሁኔታ" በሚል ተስተካክሎአል።

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "በ፲፭ እና በ፲፰ ዓመት መካከል" በማለት የተገለጸው ለማመልከት የተፈለገውን የእድሜ ዘመን በግልጽ የማያመለክት በመሆኑ ሊፈጠር የሚችለውን አሻሚ ትርጉም ለማስቀረት ሲባል "ከአስራ አምስት ዓመት በላይ፣ ከአስራ ስምንት ዓመት በታች "በሚል እንዲተካ ተደርጎአል።

ሁለተኛና ሦስተኛ ፓራግራፎችም በይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ የቃላት ማስተካከያና የአሳብ መቃናት ተደርጎባቸዋል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፻፸፯ <u>ልዩ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፯ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) "በአለንጋ እንዲገረፍ" በማለት የተገለጸው ከላይ ስለ ቀድሞው ሕግ ስለ ቁጥር ፻፸፬ መሰረዝ በተሰጠው ምክንያት እዚህም ላይ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ንዑስ ቁጥሩ ከዚህ በተጨማሪ የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቃንቶ ተዘጋጅቷል::

<u>ርዕስ ሁለት</u>
<u>ቅጣትን መወሰንና ማገድ፣ ክስንና ቅጣትን ማቋረጥና ማስቀረት</u>
<u>ምዕራፍ አንድ</u>
<u>ቅጣትን መወሰንና ማገድ</u>
<u>ክፍል አንድ</u>
<u>ቅጣትን መወሰን</u>

አንቀጽ ፻፸፰ <u>ቅጣትን የማቅለልና የማክበድ አወሳሰን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፫ ድንጋጌ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፰ ሆኖ ገብቷል::

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
<u>ቅጣትን የማቅለልና ከቅጣት ነጻ የማድረግ ደንብ</u>

አንቀጽ ፻፸፱ <u>መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፸፱ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ቅጣትን ስለማቀለል" የሚል ነበር:: ነገር ግን አጻጻፉ በደፈናው በመሆኑ ስያሜው ቀጥሎ ከሚመጣው አንቀጽ የተለየና ውሱን ጉዳይን ለማመልከት በሚያስችል መልክ ተሻሽሎ "መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ::" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

በይዘቱም ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

አንቀጽ ፻፹ <u>በመሰለው ቅጣትን ማቅለል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፮ ድንጋጌ በፊደል (ሀ) እና (ለ) ተከፍለው የነበሩት ሁለት ፓራግራፎች እንዲሆኑ ተደርጎ ከተዋሃዱና አንዳንድ ቃላት እንዲስተካከሉ ከተደረገ በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹ ድንጋጌ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፻፹፩ <u>የወል ድንጋጌዎች።</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፫ ድንጋጌ ግልጽነት እንዲኖረው አነጋገሩ ከተሻሻለ በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፩ ሆኖ ገብቷል።

ቀጽ ፻፹፪ <u>ከቅጣት ነፃ ማድረግና ቅጣትን መተው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፬ ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች ያሉት ሲሆን የሁለቱም ሀሳቦች የተያያዘ በመሆኑ አንዳንድ የቃላት ለውጥ በማድረግ በአንድ ፓራግራፍ ተጠቃልሎ ከተቀረጸ በኋላ አንቀጽ ፻፹፪ ሆኖ ገብቷል።

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>የቅጣት ማክበጃ ደንብ</u>

በወንጀል ሕጉ ላይ ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች በሶስት ደረጃ ተመድበው ይገኛሉ፣ እነርሱም፣ ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች፣ ተደራራቢ ወንጀሎችና ደጋጋሚነት ናቸው። በአንድ ወንጀል አፈፃፀም ላይ ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ሲገኙ በተወሰነ ደረጃ ቅጣት የሚያከብዱ ሲሆን፣ ከነዚህ ምክንያቶች ይልቅ ተደራራቢ ወንጀሎች፣ ከተደራራቢ ወንጀሎች ይበልጥ ደጋጋሚነት ቅጣት እንዲያከብድ ተደርጎ ተደንግጐአል። ሆኖም በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ፍርድ ቤቶች ቅጣት አክብዶ የመወሰን ስልጣናቸው ገደብ የለሽ በመሆኑ የተቻለውን ያህል ቅጣት የሚያከብዱበት ስልት እንዲኖር ተደርጎ ተረቅቋል።

ጽ ፻፹፫ <u>መደበኛ የቅጣት ማክበጃ ደንብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፫ የተደረገ ሲሆን ስያሜው "ደንበኛ የቅጣት ማክበድ" ይል የነበረው፣ "መደበኛ የቅጣት ማክበጃ ደንብ" በሚል ሐረግ ተተክቷል።

ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ሲያጋጥሙ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በአንቀጽ ፹፬ እና በዚህ አንቀጽ መሠረት በልዩ ክፍሉ ውስጥ በሚገኙ መቅጫ አንቀጾች ላይ ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ሳያልፍ እስከጣራው ድረስ ቅጣት ለማክበድ እንደሚቻል አንቀጹ የሚደነግግ ሲሆን ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ጽ ፻፹፬ <u>ግዙፍ ወንጀሎች በተደራረቡ ጊዜ ቅጣትን ማክበድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፬ ሆኖ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሎአል።

የድንጋጌው ስያሜ "የወንጀል ተግባር በተደራረበ ጊዜ እርግጠኛ የሆነ የቅጣት ማክበድ ጉዳይ" ይል ነበር። ሆኖም አጠር ባለና ግልጽ በሆነ አነጋገር ማስቀመጡ ስለሚመረጥ ስያሜው "ግዙፍ ወንጀሎች በተደራረቡ ጊዜ ቅጣትን ማክበድ" እንዲል ተደርጓል።

የንዑስ ቁጥር አንድ መግቢያ ግልጽነት እንዲኖረው የቃላት መስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሀ) ላይ "ተደራራቢ ከሆኑት ነፃነትን ከሚያሳጡት ጥፋቶች" የሚል አነጋገር ይነበብበታል:: ነገር ግን በሕጉ ልዩ ክፍል የሚገኙ ከባድ ወንጀሎች ነጻነትን ብቻ ሳይሆን ህይወትንም ሊያሳጡ የሚችሉ ወንጀሎች ስላሉ "ነፃነትን ወይም ህይወትን በማሳጣት ከሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: በተጨማሪም ከተደራራቢ ወንጀሎቹ ውስጥ በአንዱ የሞት ቅጣት የተወሰነ እንደሆነ ይህ ቅጣት በሌሎቹ ወንጀሎች ሊወሰን የሚችለውን ቅጣት አጠቃልሎ እንደሚይዝ ተደንግጎ ነበር:: ይሁን እንጂ የሌሎቹን ወንጀሎች ቅጣት አጠቃልሎ የሚይዘው የሞት ቅጣት ብቻ ስላልሆነ "የሞት" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሳሳይ አይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ ፺፯ እና ፺፰/ ሲወሰን" ተብሎ ተረቅቋል:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣ ከተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ በአንዱ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ወይም ሶስት ዓመት ቀላል እስራት ከተወሰነ፣ በሌሎቹ ተመሳሳይ ቅጣት በሚያስፈርዱ ወንጀሎች ምክንያት ከተገለጸው ቅጣት በላይ መወሰን አይቻልም::

ይህም ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት፣ የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ለእሥራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገውን ከፍተኛ የቅጣት ዘመን መወሰኑ ቀርቶ ከተባለው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ዝቅ በማድረግ ለከባዱ ወንጀል ቅጣት ከወሰነ፣ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከ ተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ድረስ አክብዶ መወሰን እንዲችል ተደርጎ ተረቅቋል::

ይህ ንዑስ አንቀጽ በዚህ መልክ የተቀረፀበት ምክንያት ግልጽ ነው:: ጥፋተኛው በከባድ ወንጀል ምክንያት የሞት ቅጣት፣ የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ለቀላል ወይም ለጽኑ እሥራት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ከተፈረደበት በሌሎቹ ወንጀሎች ምክንያት ከዚህ በላይ ቅጣት አይወሰንበትም:: ይህም የሆነበት ምክንያት ከተገለፁት ቅጣቶች በላይ መወሰን ስለማይቻል እንጂ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት ቅጣቱ ሊከብድበት አይገባም በማለት አይደለም:: ስለዚህ ለከባዱ ወንጀል የተወሰነበት ቅጣት ከተቃለለለት እና ይህንን ቅጣት ለማክበድ ከተቻለ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ምክንያት እስከ አጠቃላዩ የእሥራት ጣሪያ ቅጣት ድረስ ሊደርስ ይገባል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ለ) መሠረት በእሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ በአንቀጽ ፻፹፱(፩) (ለ) የተደነገጉት ሁለት ገደቦች ሳይታለፉ በሕጉ ልዩ ክፍል በሚገኝ መቅጫ አንቀጽ ከተደነገገው ጣሪያ ቅጣት ማለፍ በሚቻልበት ሁኔታ ቅጣቱ ሊከብድ እንደሚችል ተደንግጎአል:: ሁለቱም ገደቦች የሚከተሉት ናቸው::

በአንድ በኩል ለተደራራቢ ወንጀሎቹ የሚወሰነው ቅጣት ከሁሉም ከባድ ለሆነው ወንጀል መቅጫ አንቀፁ በሚደነግገው ጣራ ቅጣት ላይ የዚሁ ቅጣት አጋማሽ ታክሎ ከሚገኘው ቅጣት መብለጥ የለበትም:: በሌላ በኩል ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ባለማለፍ ፍርድ ቤቱ ለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት መወሰን ይኖርበታል::

ሆኖም በሁለቱ ገደቦች ላይ ተመስርቶ ቅጣቱን መወሰን የቅጣት አወሳሰንን ውስብስብ ስለሚያደርገው የመጀመሪያው ገደብ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: አዲስ በተቀረጸው ንዑስ

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ተገቢ የሆነውን ቅጣት ፍርድ ቤቱ እየወሰነ ቅጣቱን በመደመር አንድ አጠቃላይ የቅጣት ውሳኔ ይሰጣል:: ይህም የሚሆነው ሁለተኛው ገደብ እስካልተጣሰ፣ ማለት ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ጣራ ቅጣት እስካልታለፈ ድረስ ነው::

ከዚህም በላይ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) አዲስ ፓራግራፍ የገባለት ሲሆን የእስራት ቅጣቶችን ለመደመር እንዲያመች ሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት ይቆጠራል የሚል ነው::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል (ሐ) መሠረት እሥራትና መቀጮ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በተገኙ ጊዜ ቅጣታቸው ተጣምሮ የሚወሰን ሲሆን እሥራትን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩(ለ)፣ መቀጮን በሚመለከት ደግሞ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩(መ) መሠረት ቅጣቱ እንዲሰላ ተደርጐ ተረቅቋል:: በዚህ መልክ የተቀረጸበት ምክንያት የእሥራቱ ቅጣት በፊደል (ለ)፣የመቀጮ መጠን በፊደለ (መ) ከተመለከተው ሊበልጥ የሚችል መስሎ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ላይ መደንገጉ ባለመደገፉ ነው::

በተጨማሪም በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ላይ የአሳብና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ በቀድሞው ህግ ላይ ያልነበረ ሲሆን፤ "በዚህ ህግ በአንቀጽ ፹ (ሐ) በተደነገገው መሠረት የወንጀሎች መደራረብ ባጋጠመ ጊዜ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር ቅጣቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይወሰናል::" የሚል ነው::

ይህ አዲስ ድንጋጌ እንዲገባ ያስፈለገበት ምክንያት፣ አንድ ድርጊት የሚጥሰው አንድን የህግ ድንጋጌ ብቻ ቢሆንም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፹(ሐ) እንደ ተደራራቢ ወንጀሎች የተቆጠረ በመሆኑ፣ የቅጣት አወሳሰኑም ስለ ግዙፍ ተደራራቢ ወንጀሎች በተደነገገው መሠረት መሆን እንዳለበት ለማሳየት ነው::

ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ላይ፣ "በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር" የሚል ሀረግ ተመልክቷል:: ይህ ሀረግ ሊገባ የቻለው፣ አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ አንድ ድርጊት በብዙ ሰዎች ተመሳሳይ መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደተፈጸሙ የማይቆጠርበት ሁኔታ ሊያጋጥም መቻሉን ለማመልከት ነው:: ለምሳሌ አንድ ሾፌር መኪናውን በቸልተኝነት ሲያሽከረክር አንድን ታክሲ ገጭቶ በውስጡ የነበሩትን የብዙ ሰዎች ሕይወት ቢያጠፋ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ተደራራቢ ወንጀሎችን እንደፈጸመ ተቆጥሮ አይቀጣም:: በዚህ ህግ በአንቀጽ ፭፻፵፫(፫) ላይ የተመለከተውን አንድ ነጠላ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ይቀጣል፤ ቅጣቱ ግን እጅግ እንዲከብድ ተደርጎ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ ይችላል::

የቀድሞው የቁጥር ፻፹፱ (፪) ድንጋጌ ተሸጋሽጎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፻፹፭ <u>ልዩ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፭ ሆኖ ገብቷል::

የተዛመዱ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎችን በሚመለከት /አንቀጽ ፻፹፬/ በንዑስ ቁጥር አንድ እና ሁለት ላይ የቃል ማስተካከያ ተደርጐ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆኖ ገብቷል::

አንቀጽ ፻፹፮ <u>ባለፈ ጊዜ የተፈፀመ ተደራራቢ ወንጀል ከፍርድ በኋላ መታወቁ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፮ የተደረገ ሲሆን በንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ላይ የማያስፈልጉ ሀረጎች ተሰርዘውና ቃላት ተስተካክለው በይበልጥ ግልጽ በሆነ አነጋገር አንቀጹ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) በአንቀጹ ላይ ተጨምሯል::

በአንድ ወቅት የተፈጸሙ ወንጀሎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም በአንድ ፍርድ ቤትም ቢሆን በተለያዩ ችሎቶች ታይተው ውሳኔ ያገኙ ከሆነ ምን ማድረግ እንዳለበት ባለመደንገጉ ይህን የሕጉን ክፍተት ለመሙላት "በአንድ ላይ ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ድርጊቶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል::" የሚል አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ገብቷል::

አንቀጽ ፻፹፯ <u>በአንድ ድርጊት ጣምራ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፪ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፹፯ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "የሕጋዊ ድንጋጌዎች መደራረብ" የሚል ሲሆን በዚህ ምትክ "በአንድ ድርጊት ጣምራ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ" ተብሎ እንዲረቀቅ ተደርጐአል:: ይህ የሆነበት ምክንያት "notional concurrence" ለሚለው ሀረግ ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው አገላለጽ በይበልጥ ተስማሚ መሆኑ ስለታመነበት ነው::

የአንቀፁን ቅርጽ በሚመለከት በቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን ይህ ቀርቶ ሁለት ንዑስ አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጐ ተረቅቋል:: በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ሁለቱ ዓይነት ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች በግልጽ ተለይተው አለመቀመጣቸው ያተረጓጐም ችግር ይፈጥራል:: የሚወሰንባቸው ቅጣት መለያየት የሚገባው እንደመሆኑ መጠን፣ ጥፋተኛው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የሕግ ድንጋጌዎችን ሲጥስ ስለሚወሰነው ቅጣት በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር እንዲገባ፣ ልዩ ልዩ ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ስለሚወሰነው ቅጣት በንዑስ አንቀጽ (፪) ስር በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጐ ተረቅቋል:: በዚህ መሠረት:-

፩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የአንደኛው ፓራግራፍ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ንዑስ አንቀጽ አንድ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆኖአል::

www.abyssinialaw.com

፪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎችን የሚመለከት በመሆኑ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ሆኖ ገብቷል::

፫ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሻሽሎ የንዑስ አንቀጽ አንድ ሁለተኛ ፓራግራፍ እንዲሆን ተደርጎአል::

፬ ንዑስ አንቀጽ ሁለት መግቢያ እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተከፈሉ ሁለት ተጨማሪ ፓራግራፎች ገብተውለታል:: ንዑስ አንቀጽ ሁለት በሶስት ፊደላት ተከፍሎ የተረቀቀበት ምክንያት በአንቀጽ ፹፬ ላይ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚያስከትሉትን ልዩ ልዩ ቅጣት ለማመልከት ነው፤ ይኸውም:-

- ጥፋተኛው ወንጀሎቹን ሁሉ የፈፀማቸው አስቦ ከሆነ በአንቀጽ ፩፻፹፬ መሠረት ቅጣት እንዲወሰንበት፣

- ሁለተኛውን ወንጀል ወይም ሁሉንም ወንጀሎች የፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነ መቅጫ አንቀፁ ለከባድ ወንጀል ከደነገገው ጣራ ቅጣት ሳያልፍ ቅጣት እንዲወስንበት፣

ወንጀሎቹን የፈፀመው በአንቀጽ ፹፬(፪) በተዘረዘሩት ከባድ ሁኔታዎች ከሆነ በአንቀጽ ፩፻፹፬ መሠረት ቅጣቱ እንዲከብድበት፣ ለማድረግ ነው::

ቀጽ. ፩፻፹፭ <u>በተደጋገመ ጥፋት ቅጣትን ማክበድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፺፫ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፭ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌውን አቀራረጽ በሚመለከት የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፩፻፹፭ በሁለት ንዑሳን ቁጥሮች የተከፈለ ሲሆን የዚህ ሕግ አንቀጽ ግን በሚከተሉት ምክንያቶች መሰረት ሦስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎአል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ የመጀመሪያው ዓ0ረፍተ-ነገር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደረገ ሲሆን፣ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፤ የማያስፈልጉና ግራ የሚያጋቡ ዝርዝር ሁኔታዎችን የያዘ አገላለጽም እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ይኸውም የንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር አጋማሽ፣ "የቅጣት ፍርድ ተወስኖ ፍርዱ ተፈጻሚነት ካገኘ በኋላና ተቀጪውም የተወሰነበትን የቅጣት ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ከፈጸመ በኋላ እንደገና በሕግ የተመለከተ የተደጋገመ የወንጀል ተግባር ሰርቶ በተገኘ ጊዜ" በማለት ያስቀመጠው፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፹፯ ላይ የተገለጹትን የደጋጋሚነት መለኪያ ነጥቦችን ባልተሟላ ሁኔታ ከመጥቀሱም በላይ ደጋጋሚነትን በአንቀጽ ፹፯ ላይ ከተመለከተው በሚቃረን መልክ ያስቀመጠ በመሆኑ አገላለጹ ተሰርዞ "በአንቀጽ ፹፯ በተገለጹት ሁኔታዎች አንድ አዲስ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ" በሚል ተስተካክሏል:: የንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር የመጨረሻው አገላለጽም "ፍርድ ቤቱ በሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ የተመለከተውን ከፍተኛ የቅጣት መደብ ሳይከተል ቅጣቱን ሊያከብድበት ይችላል" የሚል ሲሆን፤ በዚህ ምትክ "ፍርድ ቤት ቅጣቱን ማክበድ ያለበት ሲሆን ለአዲስ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ መወሰን ይችላል" የሚል እንዲገባ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

ንዑስ አንቀጽ (፩) አዲስ ሁለተኛ ዓረፍተ ነገር እንዲገባለት ተደርጓል፤ ይኸውም፣ "ቅጣቱም በሕጉ ልዩ ክፍል ለአዲሱ ወንጀል የተደነገገውን ጣራ ቅጣት እጥፍ እስኪሆን ሊከብድ ይችላል" የሚል ነው:: ይህ አዲስ ገደብ የያዘ ዓረፍተ-ነገር ሊገባ የቻለው በሚከተለው ምክንያት ነው::

ለደጋጋሚነት ሊወሰን የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት የሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት ከሚደነግገው ጣራ ለመብለጥ ስለአለመቻሉ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ገደብ ታክሎበታል:: ጥፋተኛው ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው መቅጫ አንቀፁ ለአዲሱ ወንጀል፣ ከሚደነግገው ጣራ ቅጣት አጠፌታ ባለማለፍ እንዲሆን ተደርጐ ተጨማሪ ገደብ ተካትቶአል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከሚደነግገው ጣራ ቅጣት አትለፍ የሚለው ብቸኛ ገደብ ፍርድ ቤቶች በጥፋተኛው ላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ከባድ ቅጣት እንዲወስኑ ሰፊ ስልጣን ስለሚሰጣቸው ነው:: የተጨመረው አዲስ ገደብ በመጠኑም ቢሆን የፍርድ ቤቶችን ሰፊ ስልጣን የሚያጠበው ሲሆን ጥፋተኛውም ለፈፀመው አዲስ ወንጀል ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲወሰንበት ያደርጋል::

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፺፫ (፩) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር "ይህም ሲሆን በጥፋት መደጋገም ሁኔታ በወንጀለኛው ጥፋተኛነትና በስራው አደገኛነት መጠን ከፍተኛውን የቅጣት መደብ ለማለፍ ስለሚችል የሚገደደው በጥፋቱ ዓይነት ከሚወሰነው ከጠቅላላው የከባድ ቅጣት ባለማለፍ ብቻ ነው::" የሚል ሲሆን መሰረታዊ ለውጥ ተደርጎበት ሁለት ፓራግራፎች ያሉት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ፣ "በተደጋገሙት ወንጀሎች ዓይነትና ብዛት እንዲሁም በወንጀለኛው ጥፋተኛነትና በድርጊቱ አደገኛነት መጠን ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመከለተውን ከፍተኛ ቅጣት ሳይከተል ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሊያሳድግ ይችላል::" የሚል ሲሆን በዚህ መልክ የተደነገገበት ምክንያት፣ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ፍርድ ቤት ለመጨረሻው አዲስ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት እጥፍ ለማለፍና ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ጣራ ቅጣት ለመድረስ በሚችልበት ሁኔታ ቅጣት እንደሚወሰን ለማሳየት ነው::

ይሁንና ጥፋተኛው ልማደኛ ደጋጋሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለምሳሌ አንድ ሌባ ሰርቆ ከተቀጣ በኋላ በሚለቀቅበት ጊዜ እንደገና በዚሁ ዓይነት እየሰረቀ እየተቀጣ ድርጊቱና ቅጣቱ በዛ ሳለ ጊዜ የሚደጋገም ሲሆን፣ ለመጨረሻው አዲስ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት ፍርድ ቤቱ አልፎ መወሰን እንዳለበት የሚያመለክት ሁለተኛ ፓራግራፍ በንዑስ አንቀጽ (፪) ስር እንዲገባ ተደርጓል::

ከዚህም በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት ሊወሰን የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት ገደብ እንዳለው ለማሳየት፣ "በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚወሰነው ቅጣት ምንጊዜም ቢሆን ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት መብለጥ አይችልም::" በማለት የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተቀርጿል::

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፺፫ (፪) ድንጋጌ፣ ወንጀለኛው ደጋጋሚና ቅጣት የማይመልሰው በሚሆንበት ጊዜ የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ እንደሚወሰንበት የሚያመለክት ሲሆን የተጠቀሰው የጥንቃቄ እርምጃ ዓይነት ከዚህ የወንጀል ሕግ ስለተሰረዘና የዚህ አንቀጽ

www.abyssinialaw.com

ንዑስ አንቀጽ (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ለልማደኛ ደጋጋሚ ተገቢውን ቅጣት እንዲደነግግ ስለተደረገ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ተሰርዟል::

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች መደራረብ

ይህ ንዑስ ክፍል በቀድሞው ሕግ ውስጥ ያልነበረ ሲሆን በየአንቀጹ ስር የተመለከተውን ልዩ ልዩ የቅጣት ስሌት አዋህዶ እንዲይዝ ታቅዶ የገባ ነው::

### ቁጽ ፻፹፱ የልዩ ልዩ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች መደራረብ

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፹፬ ድንጋጌ ጋር ተዛማጅነት አለው::

የአንቀጹ ስያሜ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ከቁጥር ፹፬ የእንግሊዝኛው ቅጂ ስያሜ ጋር የሚጣጣም ሲሆን ይዘቱ ግን ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶችን ሁሉ አጠቃሎ በመያዝ በሶስት ንዑስ አንቀጾች እንዲረቀቅ ተደርጐአል፤ ይኸውም:

ንዑስ አንቀጽ (፩) በአንድ ወንጀል ላይ ጠቅላላ ማክበጃና ጠቅላላ ማቅለያ ምክንያቶች ሲገኙ ቅጣቱ እንዴት እንደሚሰላ ይደነግጋል:: ይህም የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን የቁጥር ፹፬ን ድንጋጌ ከሞላ ጐደል የያዘ ነው::

ንዑስ አንቀጽ (፪) የወንጀሎች መደራረብና ደጋጋሚነት ባንድነት ሲያጋጥሙ ቅጣቱ በምን ቅደም ተከተል እንደሚሰላ ይደነግጋል:: ይህም የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን የቁጥር ፹፪ (፪) ድንጋጌን የሚመለከት ነው::

ንዑስ አንቀጽ ሶስት ደግሞ ከወንጀሎች መደራረብና ከደጋጋሚነት ጋር ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ሲገኙ ቅጣቱ እንዴት እንደሚወሰን ይደነግጋል:: ይህ አሳብ ከዚህ ቀደም በየትኛውም አንቀጽ ላይ በግልጽ አልተደነገገም ነበር::

በዚህ መልክ ተበታትነው የነበሩትን ድንጋጌዎች በማዋሀድ እና ተጨማሪ አሳብ በማስገባት ይህ አንቀጽ እንዲረቀቅ ተደርጐአል::

## ክፍል ሁለት
## ቅጣትን መገደብ

የክፍል ሁለት ስያሜ "ቅጣትን ስለማቆም" ይል የነበረ ሲሆን ይበልጥ የተሟላ ለማድረግ "ቅጣትን መገደብ" በሚል ተተክቷል::

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ቅጣትን በገደብ ማቆም

የንዑስ ክፍል አንድ ስያሜ "ቅጣትን በገደብ ስለማቆም" የሚል ሲሆን አንቀጾቹ የሚደነግጉት ቅጣትን ስለማገድ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፻፺ <u>መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ መሠረቱ የሚል ነው። ሆኖም ይህ ቃል ቀደም ሲል ለተደረጉት ማሻሻያዎች በተሰጠው ምክንያት ተሰርዞ "መ`ርህ" በሚል ተተክቶአል።

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ያሰራር ዓይነቶችና በሚከተሉት ሁኔታዎች ያንደኛውን ሥርዓት ለመከተል ይችላል።" የሚለው ሀረግ የፍርድ ቤቱ ተግባር ከአማራጭ ሥርዓቶች አንደኛውን መከተል ሳይሆን በሕጉ ውስጥ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ለቀረበው ጉዳይ አግባብ ያለውን መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ስለሆነ ሀረጉ ተሰርዞ "ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ሊወስን ይችላል።" በሚል ተተክቶአል።

በሁለተኛው ፓራግራፍ "እነዚህም ድንጋጌዎች ከወንጀለኛው የመታረምን መልካም ፈቃድና እርዳታውን የሚፈልጉ ስለሆነ" የሚል ሀረግ ተመልክቶአል። ከወንጀለኛው የመታረምን መልካም ፈቃድና እርዳታውን የሚፈልጉት ድንጋጌዎች ሳይሆኑ በድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ስለሆኑ "እነዚህም ድንጋጌዎች" የሚለው ንዑስ ሀረግ ተሰርዞ "በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት" በሚል ሀረግ ተተክቶአል።

አንቀጽ ፻፺፩ <u>ለቅጣት ውሳኔ ጊዜ መስጠት፤ የጥፋተኛነት ውሳኔውን መሰረዝ*</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፭ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፩ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ ውስጥ "ውሳኔውን ስለማገድ" የሚል ይነበባል። ሆኖም በሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገው ውሳኔውን ስለማገድ ሳይሆን ጥፋተኛው የፈተና ጊዜውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፈ ከፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ የጥፋተኛነት ውሳኔው የሚሰረዝበትን ሁኔታ የሚያመለክት በመሆኑ ይህን ይዘቱን ማንፀባረቅ እንዲችል"...፣ ውሳኔውን መሰረዝ" በሚል ተተክቶአል።

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛውን ጥፋተኛነት ካረጋገጠ በኋላ ወንጀለኛው ለወደፊቱ ጠባዩን ለማረም እንዲችል እምነት ሊጣልበት የሚገባው መሆኑንና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከመጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተወሰነበትን ፍርድ ለጊዜው አግዶ የተወሰነ የፈተና ጊዜ ሊሰጠው እንደሚችል ተደንግጎአል። ፍርድ ቤቱ ለወንጀለኛው የፈተና ጊዜ ለመስጠት ለጊዜው የሚያግደው የቅጣቱን መወሰን ሲሆን ይህንንም እገዳ የሚያደርገው የጥፋተኛነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ እንዲሆን ያስፈልጋል። ስለዚህ "እስከመጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን የገመተ እንደሆነ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ የተመለከተው" የተወሰነበትን ፍርድ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የጥፋተኛነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የቅጣቱን መወሰን" የሚል ሀረግ ተተክቶ ከተከታዩ ጋር እንዲነበብ ተደርጓል።

---

* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 191 "<u>በሚያስቀጣ</u>" የሚለው ቃል "<u>የሚያስቀጣ</u>" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

በሁለተኛው ፓራግራፍ "በእርግጥም እንደዚህ ሆኖ በተገኘ ጊዜ" የሚለው ሀረግ ፈተናው መልካም ፍሬ ያስገኘ እንደሆነ ለማለት ነው ተብሎ ሊተረጎም ቢችልም አሻሚ ትርጉም ሊሰጥ ስለሚችል ተሰርዞ "ፈተናው መልካም ፍሬ ያስገኘ እንደሆነ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱም ፓራግራፎች ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

ቶጽ ፻፺፪ <u>ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፮ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፪ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጹ ስያሜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "ቅጣት እንዳይፈጸም ጊዜ ስለመስጠት" የሚል ሲሆን አሳቡን በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ "የቅጣት አፈጻጸምን ማገድ" እንዲል ተደርጎ ተረቅቋል::

የጥንቃቄ እርምጃዎች ስላለመታገዳቸው የሚገልጸው ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፻፺፰ ላይ ንዑስ ቁጥር (፫) ሆኖ ከሚገባ ይልቅ የዚህ አንቀጽ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሁለተኛ ዓረፍተ-ነገር ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ቅጣት የሚታገድበት ጊዜ ቢኖርም የጥንቃቄ እርምጃዎች ውሳኔ ግን አይታገድም የሚለው አሳብ በአንድነት መቀመጡ ነገሩን በይበልጥ ግልጽ ስለሚያደርገው ነው::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁለተኛው ፓራግራፍ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቶጽ ፻፺፫ <u>የተደራረቡ የቅጣት ውሳኔዎች ሲኖሩ ለአፈጻጸማቸው ጊዜ መስጠትን መከፋፈል</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፻፺፯ ድንጋጌ በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፫ ሆኖ ገብቷል::

ቶጽ ፻፺፬ <u>የቅጣት ገደብ የሚከለከልበትና የሚሻርበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፬ ሆኖ የገባ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የድንጋጌው ስያሜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "ጊዜ ለመስጠት የማይቻልበት ሁኔታ" የሚል ሲሆን፣ በዚህ ምትክ "የቅጣት ገደብ የሚከለከልበትና የሚሻርበት ሁኔታ" እንዲል ተደርጐአል:: ይህ የሆነበት ምክንያት አንቀፁ የሚደነግገው ገደብ ስለሚከለከልበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ተሰጥቶ የነበረ ገደብ ስለሚሻርበት ሁኔታ ጭምር በመሆኑ ነው::

ከአንቀጽ ፻፺፪ ጋር በማያያዝ እንደተገለፀው ከዚህ ቀደም የተፈረደበት ጥፋተኛ አሁን በሚፈረድበት ወንጀል ሊገደብለት አይገባም የሚለውን አሳብ ባለመቀበል አስቀድሞ የተፈረደበትም ጥፋተኛ ቢሆን እንደገና በተፈረደበት ወንጀል ቅጣቱ ሊገደብለት እንዲችል ተደርጐአል:: ሆኖም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የአማርኛ ቅጂ እና በሁለቱ የውጪ አገር ቋንቋዎች ቅጂ መካከል፣ ገደብ ማድረግ በሚቻልበት የቅጣት ዓይነትና መጠን ላይ ሁለት ልዩነቶች አሉ፤ ይኸውም:-

www.abyssinialaw.com

፩ ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም የተፈረደበትም ሆነ በአሁኑ ወንጀል ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ከተፈረደበት ቅጣቱ እንደማይገደብለት የፈረንሳይኛውና የእንግሊዝኛው ቅጂዎች የሚደነግጉ ሲሆን በአማርኛው ቅጂ ላይ ግን ስለቀላል እሥራት አልተጠቀሰም::

፪ በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂዎች መሠረት ከዚህ ቀደም በፈፀመውም ሆነ በአሁኑ ወንጀል ጽኑ እሥራት ከተፈረደበት ቅጣቱ የማይገደብለት ሲሆን በአማርኛው ቅጂ መሠረት ግን ገደብ የሚከለከለው ከዚህ ቀደም በፈፀመው ወንጀል ሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት ከነበረና እንደገና በፈፀመው ወንጀል ጽኑ እሥራት /አንድ ዓመት ቢሆን እንኳ/ ሲፈረድበት ነው:: በሌላ አነጋገር በሁለቱም ወንጀሎች ሶስት ሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት ጥፋተኛው ቢፈረድበት ቅጣቱ ሊገደብለት ይችላል ማለት ነው::

ከዚህ ቀደምም ሆነ እንደገና በተፈረደበት ወንጀል ሶስት ሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት የተቀጣ ሰው ሊገደብለት ይችላል ማለቱ ተገቢ ያልሆነ ችሮታ ነው ሊያሰኝ ይችላል:: በመሆኑም የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በአማርኛ ቅጂ ላይ የተቀመጠው የቅጣት አይነትና መጠን ቀርቶ የእንግሊዝኛውና የፈረንሳይኛው ቅጂ አሳብ ተቀባይነት አግኝቶአል:: ሆኖም የአዲሱ ወንጀል አፈፃፀም ደጋጋሚነትን የማይመለከት መሆን አለበት:: የሚገደበውን የቅጣት ዓይነትና መጠን በተመለከተ መሠረት ተደርጎ የሚያዘው በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ የሚደነግገው ወይም ፍርድ ቤት የሚወስነው ቅጣት መሆን እንዳለበት ክርክር አስነስቶ የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤት የሚወስነው ቅጣት መሠረት ተደርጎ ሊያዝ እንደሚገባ ታምኖበታል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፻፹፰ መሠረት ሌላው ቅጣት የማይገደብበት ሁኔታ ከዚህ ቀደም በደጋጋሚነት ጽኑ ግዞት ከተወሰነበትና አሁንም ይኸው እርምጃ ከተወሰደበት ነው:: ይህን አሳብ የያዘው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አነጋገር ተሰርዞአል:: ምክንያቱም የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ አስፈላጊ ባለመሆኑ ይህንን እርምጃ የሚመለከቱ የቀድሞ ሕግ ድንጋጌዎች (፻፹፰-፻፺፪) እንዲሰረዙ በመደረጉ ነው::

ከላይ በፊደል (ለ) እና (ሐ) በተሰጠው አስተያየት መሠረት ድንጋጌው ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) ሆኖ ተረቅቋል::

ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ የሆነ ሰው ከምን በላይ ቢፈረድበት ነው ቅጣቱ የማይገደብለት የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የለም:: ስለዚህ ጉዳይ ሳይደነገግ በመቅረቱ ፍርድ ቤቶች ከፈለጉ እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ሊገድቡ ቢችሉ የሚያግዳቸው ነገር የለም:: በመሆኑም ይህንን ገደብ የለሽ ሥልጣን ለማስቀረት ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት የሚበልጥ ቅጣት የሚፈረድበት ጥፋተኛ እንዳይገደብለት በማድረግ ተረቅቆ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ሆኖ ገብቷል:: በአሰራርም ፍርድ ቤቶች እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ድረስ ሲገድቡ ይታያል::

አንቀጽ ፻፺፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰጥቶ የነበረ ገደብ ስለሚሻርበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን አንዱ መሻሪያ ሁኔታ ቅጣቱ ከተገደበለት በኋላ ሌላ ወንጀል ፈጽሞ እንደነበር ሲደረስበት ነው:: የአዲሱና የቀድሞ ወንጀል ዓይነትና መጠን በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ላይ ከተመለከቱት ወንጀሎች አይነትና መጠን ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ በዚህ መልክ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

አዲስ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፪) በፊደል (ለ) ስር የገባ ሲሆን፣ በአንቀጽ ፪፻ (፪) በሁለተኛው ፓራግራፍ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ የቅጣት አፈጻጸሙ የታገደለት ጥፋተኛ በፈተና ጊዜ ውስጥ አስቦ አንድ ወንጀል ከፈጸመ፣ የቅጣት አፈጻጸሙ ታግዶለት የነበረው ውሳኔ እንደሚሻር የሚደነግግ ነው::

የቁጥር ፻፺፭ (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ሆኖ ገብቷል::

ስለጥንቃቄ እርምጃዎች አለመታገድ የሚደነግገው የአንቀጽ ፻፺፭ (፫) ድንጋጌ ትክክለኛ ቦታው እዚህ አይደለም ተብሎ ይታመናል:: ይህ አንቀጽ የሚደነግገው የቅጣት ገደብ ስለሚከለከልበትና ተገድቦ የነበረ ቅጣት ስለሚሻርበት ሁኔታ ሲሆን ከዚህ ጋር አያይዞ የጥንቃቄ እርምጃዎች አይታገዱም ማለቱ አግባብ ሆኖ አይታይም:: በይበልጥ ተስማሚ የሚሆነው፣ ቅጣት ሲገደብ እንደሚቻል ከሚገልፀው አንቀጽ ጋር በማያያዝ የጥንቃቄ እርምጃዎች ግን የሚገደቡበት ጊዜ አለመኖሩ ቢደነገግ ነው:: የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፭/፫/ ድንጋጌ የአንቀጽ ፻፺፪ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሁለተኛ ዓረፍተ-ነገር ሆኖ እንዲገባ የተደረገው በዚህ ምክንያት ነው::

ጽ ፻፺፮ <u>ማጣራት (ምርመራ)</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፮ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው የመጀመሪያው ፓራግራፍ፣ ፍርድ ቤት ተከሳሹ የሚያቀርበውን የፍርድ መታገድ ጥያቄ ለመወሰን እንዲያስችለው የተዘረዘሩት መስፈርቶች ፍርድ ቤቱ ቢፈልግ የሚያጣራቸው ባይፈልግ የሚተዋቸው ሳይሆኑ በግዴታ መደረግ ያለባቸው በመሆኑ "ለማዘዝ ይችላል" የሚለው የዓረፍተ-ነገሩ ማሰሪያ ተሰርዞ "ማዘዝ አለበት" በሚል ተተክቶአል:: በተጨማሪም ፓራግራፉ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገው፣ የምርመራውን ተግባር እነማን ሊያከናውኑት እንደሚችሉ ነው:: ሆኖም የፈረንሳይኛውና የእንግሊዝኛው ቅጂዎች የሚያመለክቱት ከላይ በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ መጣራት ያለባቸው ነገሮች (መረጃዎች) ከየት መገኘት እንደሚችሉ በመሆኑ የፓራግራፉ አቀራረብ ተሻሽሎና ተለውጦ "ይህም መረጃ ከአንድ የጥበቃ ባልደረባ ወይም እምነት ከሚጣልበት የማህበራዊ ሠራተኛ ወይም አግባብ ካለው ማናቸውም ሌላ አካል ወይም ተቋም ሊቀርብ ይችላል::" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

ጽ ፻፺፯ <u>የወል ድንጋጌዎች፣ ለፈተና የሚሰጥ ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፯ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያ ፓራግራፍ የተደነገገው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በሁለተኛው ፓራግራፍ "ፍርድ ቤቱ ፍርድ ሳይወሰን ወይም ሳይፈጸም እንዲቆይ ጊዜ የመስጠት ትዕዛዝ ለመወሰን..." በማለት የተመለከተው አሳስፈሳጊ በመሆኑ ተሰርዞ ግልጽ በሆነና አጠር ባለ መልክ "ፍርድ ቤት የማገጃ ትዕዛዝ ለመስጠት..." በሚል ተሻሽሎአል::

www.abyssinialaw.com

ንዑስ ቁጥር (፪) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፻፺፯ <u>ፈተና የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፩ ድንጋጌ የዚሁ ሕግ አንቀጽ ፻፺፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር አንድም ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገጉት ፍሬ ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ተሻሽለዋል፡፡

አንቀጽ ፻፺፰ <u>በጥፋተኛው ላይ የሚወሰን የጠባይ አመራር ደንብ</u>

የቀደሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው ላይ "Rule of Conduct" ለሚለው ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የአኗኗር ወይም "ያመራር ደንብ" የሚል ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ይህ አገላለጽ የተፈለገውን አሳብ በትክክል ስለማያንፀባርቅ "የጠባይ አመራር፤ ደንብ" በሚል ተተክቷል፡፡

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ ከተዘረዘሩት የጥንቃቄ እርምጃዎች በተጨማሪ ጥፋተኛው "ከአንድንድ ሰዎች ጋር እንዳይገናኝ መከልከል" ለጠባይ መሻሻል ዕገዛ እንደሚያደርግ በመታመኑ በዝርዝሩ መካከል ላይ ሀረጉ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ቁጥርም ሆነ በሌሎቹ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

አንቀጽ ፻፺፱ <u>በጥፋተኛው ላይ ቁጥጥር ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "ጥፋተኛውን ስለመቆጣጠርና ስለመጠባበቅ" የሚል ሲሆን አጠር ባለ ግልጽ አነጋገር "በጥፋተኛው ላይ ቁጥጥር ማድረግ" እንዲል ተደርጓል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ይህ የፍርድ መታገድ ጉዳይ በሚገባ በተገለፀ በቂ ምክንያት የተሻረ ካልሆነ በቀር" የሚለው ሀረግ አደናጋሪ ከሚሆን በቀር አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሠርዞአል፡፡ እንዲሁም በሶስተኛው ፓራግራፍ ላይ "ፍርዱ በታገደለት ተቀጪ ላይም ስውር የሆነ ደንበኛ መቆጣጠር ይፈፀምበታል፡፡" የሚለው ዓረፍተ-ነገር ፍርዱ በታገደለት ጥፋተኛ ላይ የሚፈጽመውን ስውር ቁጥጥር ገደብ የሌለው ያደርገዋል፡፡ ዳሩ ግን ስውር ቁጥጥር በጥፋተኛው ላይ የሚፈጽመው በየጊዜውም ቢሆን አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ይኸው ዓረፍተ-ነገር ተሠርዞ "አሣዳሪው ወይም የጥበቃ ባልዳረባው ፍርዱ በታገደለት ጥፋተኛ ላይ እንዳአስፈላጊነቱ በየጊዜው ስውር የሆነ ቁጥጥር ይፈጽምበታል፡፡" በሚል ዓረፍተ-ነገር ተተክቶአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሶስቱም ፓራግራፎች ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) "ስለ ቅጣት አፈጻጸም ሕግና ስለዚህ ጉዳይ በሚወጣው ደንብ ላይ ይወሰናል፡፡" በሚል የተመለከተው ሰፋ ባለ ሁኔታ ተሻሽሎ "በሚወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡"

www.abyssinialaw.com

በማለት እንዲነበብ ሆኖአል:: የሕጉ ዓይነት ሳይጠቀስ መቅረቱ እንደ አስፈላጊነቱ በአዋጅም ይሁን በደንብ ለመሥራት ያስችላል::

ቀጽ ፪፻ <u>የፈተናው ፍሬ አለማስገኘት የሚያስከትለው ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሎአል::

የድንጋጌው ስያሜ "ፈተናው ፍሬ ያልሰጠ ስለ መሆኑ፤ ለፈተናው የተሰጠውን ትዕዛዝ ስለማስቀረት "የሚል ነበር:: ነገር ግን ከይዘቱ ለማየት እንደሚቻለው ፈተናው ፍሬ ባላስገኘ ጊዜ ውሳኔው ቀሪ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን የሚደረገው የፈተናውን ጊዜ እንደሚራዘም፣ አዲስ የጠባይ አመራር ደንብ መስጠትና ሌሎች መሰል ሁኔታዎችንም የሚጨምር በመሆኑ እነዚህንና ሌሎች መሰል ሁኔታዎችን ለማመልከት ስያሜው ተሻሽሎ "የፈተናው ፍሬ አለማስገኘት የሚያስከትለው ውጤት ::" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ በፍርድ ቤት ማስጠንቀቂያ ከሚያስጡት ምክንያቶች አንዱ በቸልተኛነት ወንጀል መፈጸም እንደሆነ ተመልክቷል፤ ጥፋተኛው ለዚህ ወንጀሉ የሚከሰስ መሆን አለመሆኑ አልተገለጸም:: ሆኖም በወንጀል ተጠያቂ መሆን ስለሚገባውና ሁኔታውን በግልጽ ማስቀመጡ ተገቢ በመሆኑ፣ "ሳደረገው ወንጀል መከሰሱ እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚል ጥገኛ ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል::

የንዑስ ቁጥር ሦስት "የቅጣቱን ማገድ የሚያሽር አዲስ ወንጀል የተሠራ እንደሆን ስለወንጀል መደጋገም የተመሠረተውን ደንብ በመከተል ያዲሱ ወንጀል ቅጣት ከቀድሞ ወንጀል ቅጣት ጋር ተጨማሪ ይሆናል" ይላል:: ሆኖም በደጋጋሚነት ጊዜ የቅጣት ድምር ስለሌለ ከደጋጋሚነት ቅጣት አወሳሰን ጽንሰ ሐሳብ ጋር በሚጣጣም መልክ ተረቅቋል::

ከዚህም በቀር በሶስቱም ንዑሳን አንቀጾች የተደነገገው ፍሬ-ነገር ግልጽ እንዲሆን የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎ ተሻሽሏል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፭ ድንጋጌ መሠረዝ</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ቁጥር ፪፺፭ እና ፪፺፮ መሠረት በገደብ የተለቀቀ ጥፋተኛ የፈተና ጊዜውን በሰላም ከጨረሰ ፍርዱ ይሰረዛል ተብሎ በቁጥር ፪፻፭ ላይ ተመልክቷል:: ሆኖም የዚህ ድንጋጌ አገላለጽ ስህተት ነው:: ጥፋተኛው በአንቀጽ ፩፻፺፩ መሠረት ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ ሳይወሰንበት በገደብ ሲለቀቅ የፈተናውን ጊዜ በሰላም ከጨረሰ ፍርዱ እንደሚሰረዝለት በአንቀጽ ፪፻፩ ላይ ስለተደነገገ በድጋሚ እዚህ ላይ ማስፈሩ አስፈላጊ አይደለም:: በሌላ በኩል ጥፋተኛው በአንቀጽ ፪፺፪ መሠረት ቅጣት ተወስኖበት በገደብ የተለቀቀ ሲሆን የፈተናውን ጊዜ በሰላም ቢጨርስም ፍርዱ ተመዝግቦ እንደሚቆይ በተጠቀሰው አንቀጽ ላይ ስለተደነገገ ፍርዱ ይሰረዝለታል ተብሎ በቁጥር ፪፻፭ ላይ መደንገጉ ስህተት ነው:: በመሆኑም ድንጋጌው እንዲሰረዝ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com


## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በተወሰነ ገደብ በአመክሮ መፈታት

### አንቀጽ ፩፻፮ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፺፯ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፮ ሆኖአል።

በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "በዚህ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ የተደነገገው ቅጣት ወይም ነፃነትን የሚያሳጣ ውሳኔ።" በሚለው ሀረግ ውስጥ "ነፃነትን የሚያሳጣ ውሳኔ" የሚለው "የጥንቃቄ እርምጃ" ለማለት ተፈልጎ የተደረገ ስህተት በመሆኑ በዚህ መሠረት ተስተካክሏል።

በአንቀጽ ፩፻፯ የተደነገገው አግባብነት ስላለው የአንቀጹ ቁጥር በመጀመሪያ ፓራግራፍ መጨረሻ ላይ በቅንፍ ውስጥ ተጠቅሶአል። በተጨማሪም በመጀመሪያውም ሆነ በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎአል።

### አንቀጽ ፩፻፯ ለመለቀቅ የሚያበቁ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፺፰ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፯ ሆኖ ገብቷል።

በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፩፻፺፰ ስያሜ የመለቀቁ ሁኔታዎች የሚል ነበር። ሆኖም አባባሉ ግልጽ ባለመሆኑ ይዘቱን ማንፀባረቅ በሚችል መልክ ተሻሽሎ "ለመለቀቅ የሚያበቁ ሁኔታዎች" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል።

ይዘቱም ቀድሞ ያለ ንዑስ ቁጥር ተዘጋጅቶ የነበረው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተጨምሮ በሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲከፈል ተደርጓል። በዚህ መሠረት የቁጥር ፩፻፺፰ ድንጋጌ የንዑስ አንቀጽ (፩) ይዘት እንዲሆን ተደርጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ላይ "ተቀጪው ከተወሰነበት የእስራት ጊዜ ከሶስት እጅ ሁለቱን እጅ ወይም ፍርዱ የዕድሜ ልክ እስራት ሲሆን ሃያ ዓመት በፈጸመ ጊዜ" የሚል አዲስ ጥገኛ ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል። ይሄም አሳብ የተወሰደው ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፻፲፱ መግቢያ ሲሆን ከቀድሞ ቦታው ለቅቆ እዚህ እንዲገባ የተደረገው፣ በአመክሮ ለመለቀቅ የሚያበቁ ምክንያቶችን ሁሉ በዚህ አንቀጽ ውስጥ በአንድነት ማስቀመጡ የተሻለ በመሆኑ ነው።

በተጨማሪም በቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፺፰ ድንጋጌ መግቢያ ላይ "በእስር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሳሳቢነት" በማለት የተገለጸው ለአመክሮ የሚያበቁ ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ከእስር ቤቱ ስራ አስኪያጅ ሌላ ሕግ በሚደነግገው መሰረት ለአመክሮ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ስልጣን የሚሰጣቸውን ሌሎች አካላት የሚገድብ በመሆኑ ተሰርዞ "አግባብ ባለው ባለሥልጣን" እንዲል ሆኖአል። ጥፋተኛውም የማሳሰብ መብት ሊኖረው ይገባል። በዚህ መሠረት የንዑስ አንቀጹ መንደርደሪያ "አግባብ ባለው አካል ወይም በጥፋተኛው አሳሳቢነት ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለአመክሮ እንዲፈታ ለመወሰን የሚችለው ጥፋተኛው፣" በሚል እንዲነበብ ሆኗል።

www.abyssinialaw.com

በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተደነገጉት ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

እንዲሁም በፊደል "ሐ" የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በላይ "እንዲሁም ነፃ /በአመክሮ/ በተለቀቀ ጊዜ የሚተዳደርበት /የሚጠብቀው/ የኑሮ ሁኔታ" የሚለው ሀረግ ከፊደል "ሐ" ላይ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ጥፋተኛው በአመክሮ ሲፈታ የሚተዳደርበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ወይም ሌላ ድጋፍ መኖር አለመኖሩ ከግምት ከገባ፣ የሚጎዳው ምንም የሌለውን ደሀ ሰው ነው:: ዞሮ ዞሮ የእስራቱንም ቅጣት ሲፈጽም ድሀ እስረኛ መለቀቁ አይቀርም:: ስለዚህም የዚህ ዓይነቱ መመዘኛ ነጥብ መቀመጡ አግባብ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ችሏል::

ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) የተገለጹት ሁኔታዎች ለአመክሮ ለመለቀቅ የሚያበቁ ሶስቱም በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ በመሆኑ ይህንኑ ለማመልከት "እና" የሚለው መስተፃምር በፊደል (ለ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ እንዲገባ ተደርጎአል::

ምንም እንኳን ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ቢሟሉም ለልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኞች በአመክሮ የመፈታት እድል መስጠቱ የወንጀለኛነት ድርጊታቸውን እንዲገፉበት የሚያበረታታ በመሆኑ ይህንን ለመግታት እንዲያስችል "ከዚህ በላይ የተገለጹት ድንጋጌዎች ቢኖሩም በአመክሮ መፈታት ለልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ተፈጻሚ አይሆንም::" በማለት የሚነበብ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል::

ቀጽ ፩፻፫ <u>በአመክሮ የመፈታትን ጉዳይ ማሳወቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፰ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፫ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፩፻፰ ስያሜ "ለጉዳዩ ተስማሚ የሆነ አሳብ ለመስጠት::" የሚል ነው:: ሆኖም ስያሜው ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ከይዘቱም ጋር የሚጣጣም አይደለም:: ይዘቱ የሚገልጸው አንድ ጥፋተኛ ሲፈረድበትና ማረሚያ ቤት ሲገባ ለአመክሮ የመለቀቅ ዕድል እንዳለው እንዲገለጽለት በመሆኑ ስያሜው ይህንን ይዘቱን እንዲያንፀባርቅ "ለአመክሮ የመፈታትን ጉዳይ ማሳወቅ::" በሚል እንዲነበብ ሆኖ ተሻሽሏል::

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) ተቀጪዎቹ በሚፈረድባቸው ጊዜና እንዲሁም ወደሚላኩበት የእስር ቤት" ብሎ በመጀመር እስከመጨረሻው ባለቤቱና ድንጋጌው በብዙ ቁጥር የተጻፈው፣ ወንጀለኛው አንድ ብቻ ቢሆንስ የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ በብዙ መሆኑ ቀርቶ በነጠላ ቁጥር እንዲጻፍ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፪) "የእስር ቤቱ ሹም" በማለት የተገለጸው ቀደም ሲል ለአንቀጽ ፩፻፩ ማሻሻያ በተሰጠው ምክንያት ተሰርዞ "አግባብ ያለው አካል" በሚል እንዲተካ ሆኗል:: እንዲሁም ለክፍሉ ፍርድ ቤት በሚለው ሀረግ ውስጥ "ለክፍሉ" የሚለው ቃል ግልጽ ካለመሆኑም በላይ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ በንዑስ ቁጥር አንድም ሆነ በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ የሌሎች አንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነዋል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፻፺፩ <u>የፈተናው ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፺፱ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፻፺፱ ስያሜ "የአመክሮ ጊዜ ልክ" የሚል ሲሆን "የፈተናው ጊዜ" በሚል ተተክቷል፡፡

ይዘቱም በሁለተኛው ፓራግራፍ ውስጥ "በጽኑ ግዞት ሥፍራ ተወስኖ እንዲኖር የተወሰነበት ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲሆን የአመክሮ ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊያንስ አይችልም..." በማለት የተደነገገው እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ደጋጋሚ ወንጀለኛ በአንቀጽ ፻፺፪/፪/ የአመክሮ ዕድል ተጠቃሚ እንዳይሆን በመደንገጉ ነው፡፡

ከዚህም በላይ የድንጋጌው የመጨረሻ ዓረፍተ-ነገር "የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተወሰነበት ወንጀለኛ ሲሆን የአመክሮው ጊዜ ከአምስት ዓመት አይወርድም፡፡" የሚል ሲሆን የመጨረሻው ሐረግ ተለውጦ "ከአምስት ዓመት ሊያንስ ከሰባት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡ ለውጡ ያስፈለገበት ምክንያት የሙከራውን ጊዜ ጣራ መወሰኑ ፍርድ ቤቶች ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት በተፈረደበት ጥፋተኛ ላይ ተገቢ ያልሆነ ረዥም የፈተና ጊዜ የመስጠት ስልጣናቸውን ለመገደብ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

አንቀጽ ፻፺፫ <u>የጠባይ አመራርና የቁጥጥር ደንብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፻፺፫ ሆኖ ገብቷል፡፡

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፪፻ ስያሜ "የጠባይ አመራርና የአጠባበቅ ደንብ" ይል ነበር፡፡ ሆኖም ድንጋጌው በአመክሮ የተለቀቀው ጥፋተኛ ለአመክሮ በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ በምን አኳኋን መኖር እንደሚገባው የሚደነግግ ስለሆነ ስያሜው ለድንጋጌው ይዘት ተስማሚ እንዲሆን "የጠባይ አመራርና የቁጥጥር ደንብ" በሚል ተተክቶአል፡፡

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያውና በሁለተኛው ፓራግራፎች "የጠባይ አመራር ሥርዓት" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የጠባይ አመራር ደንብ" በሚል ተተክቷል፡፡

በሶስተኛው ፓራግራፍ "በእሥር ቤቱ ሥራ መምሪያ ክፍልና ያስተዳዳሪነት ሥልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ማህበር አባሎች፣ ባልደረቦች፤ ሞግዚቶች ወይም በበጎ አድራጎት ማህበሮች" በማለት የተገለጸው ለተለቃቂው መተዳደሪያ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የማመቻቸቱ ኃላፊነት የተጣለባቸውን አካላት የሚያመለክት ነው፡፡ ሆኖም ዝርዝሩ አሁን ባለው ሁኔታ ጠበብ ያለ በመሆኑ ሰፋ እንዲል ለማድረግ ሀረጉ ተሰርዞ በሚመለከተው ተቋም ወይም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ባልደረቦች ወይም አግባብ ባለው መንግሥታዊ አካል በሚል ተተክቶአል፡፡ ንዑስ ቁጥሩ በሶስቱም ፓራግራፎች ውስጥ የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፪፻፩ <u>የፈተናው ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፱ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፩ ሆኖ ገብቷል።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፪፻፱ ስያሜ "የአመክሮ ጊዜ ልክ" የሚል ሲሆን "የፈተናው ጊዜ" በሚል ተተክቷል።

ይዘቱም በሁለተኛው ፓራግራፍ ውስጥ "በጽኑ ግዞት ሥፍራ ተወስኖ እንዲኖር የተወሰነበት ደጋጋሚ ወንጀለኛ ሲሆን የአመክሮ ጊዜ ከሁለት ዓመት ሊያንስ አይችልም..." በማለት የተደነገገው እንዲሰረዝ ተደርጓአል። ምክንያቱም ደጋጋሚ ወንጀለኛ በአንቀጽ ፪፻፪/፪/ የአመክሮ ዕድል ተጠቃሚ እንዳይሆን በመደንገጉ ነው።

ከዚህም በላይ የድንጋጌው የመጨረሻ ዓረፍተ-ነገር "የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተወሰነበት ወንጀለኛ ሲሆን የአመክሮው ጊዜ ከአምስት ዓመት አይወርድም።" የሚል ሲሆን የመጨረሻው ሐረግ ተለውጦ "ከአምስት ዓመት ሊያንስ ከሰባት ዓመት ሊበልጥ አይችልም።" በሚል ሐረግ ተተክቷል። ለውጡ ያስፈለገበት ምክንያት የሙከራውን ጊዜ ጣራ መወሰኑ ፍርድ ቤቶች ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት በተፈረደበት ጥፋተኛ ላይ ተገቢ ያልሆነ ረዥም የፈተና ጊዜ የመስጠት ስልጣናቸውን ለመገደብ የሚያስችል በመሆኑ ነው።

አንቀጽ ፪፻፪ <u>የጠባይ አመራርና የቁጥጥር ደንብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፪ ሆኖ ገብቷል።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፪፻፲ ስያሜ "የጠባይ አመራርና የአጠባበቅ ደንብ" ይል ነበር። ሆኖም ድንጋጌው በአመክሮ የተለቀቀው ጥፋተኛ ለአመክሮ በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ በምን አኳኋን መኖር እንደሚገባው የሚደነግግ ስለሆነ ስያሜው ለድንጋጌው ይዘት ተስማሚ እንዲሆን "የጠባይ አመራርና የቁጥጥር ደንብ" በሚል ተተክቶአል።

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያውና በሁለተኛው ፓራግራፎች "የጠባይ አመራር ሥርዓት" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የጠባይ አመራር ደንብ" በሚል ተተክቷል።

በሶስተኛው ፓራግራፍ "በእሥር ቤቱ ሥራ መምሪያ ክፍልና ያስተዳዳሪነት ሥልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ማህበር አባሎች፣ ባልደረቦች፤ ሞግዚቶች ወይም በበጎ አድራጎት ማህበሮች" በማለት የተገለጸው ለተለቃቂው መተዳደሪያ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የማመቻቸቱ ኃላፊነት የተጣለባቸውን አካላት የሚያመለክት ነው። ሆኖም ዝርዝሩ አሁን ባለው ሁኔታ ጠበብ ያለ በመሆኑ ሰፋ እንዲል ለማድረግ ሀረጉ ተሰርዞ በሚመለከተው ተቋም ወይም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን በተሰጣቸው የጥበቃ ባልደረቦች ወይም አግባብ ባለው መንግሥታዊ አካል በሚል ተተክቶአል። ንዑስ ቁጥሩ በሶስቱም ፓራግራፎች ውስጥ የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፪) የአጣቃሽ አንቀጽ አቀማመጥና የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

በዚህ መልክ የተሻሻሉት ንዑስ ቁጥሮች የዚህ አንቀጽ ንዑሳን አንቀጾች ሆነዋል።

ቀጽ ፪፻፮ <u>የፈተናው ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፩ ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፮ ሆኖ ገብቷል።

የቁጥር ፪፻፲፩ መግቢያ በሆነው በመጀመሪያው ፓራግራፍ የተገለጸው ፍሬ-ነገር በንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ከተመለከቱት የተለየና ዐብይ ነገር ስለሆነ ራሱን ችሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል። ንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገው ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆነዋል።

በድንጋጌው በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፩) /በአሁኑ ንዑስ አንቀጽ (፪)/ በሶስተኛው ፓራግራፍ ላይ "በመካከሉ አዲስ የጥፋት ተግባር ተፈጽሞ እንደሆነ የቅጣቱ ወይም የጥንቃቄ ተግባር ውሳኔ የሚፈጸመው በደንበኛው ድንጋጌ ላይ በተመለከተው መሠረት ነው" ይላል። ሆኖም "በደንበኛው ድንጋጌ ላይ በተመለከተው መሠረት" የሚለው ሀረግ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ ወደ ስህተት ሊያመራ ይችላል። በመሆኑም ፓራግራፉ ተስተካክሎ "አዲስ ወንጀል በመካከሉ ተደርጎ እንደሆነ ስለደጋጋሚነት የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆኖ ለአዲሱ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት ከቀሪው ቅጣት ጋር ተዳምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።" እንዲል ተደርጓል። በዚህ መሠረት የደጋጋሚነት ሁኔታዎች ከተሟሉ ጥፋተኛው በደጋጋሚነት እንዲቀጣ ካልተሟሉ ግን የአዲሱ ወንጀል ቅጣት ከቀሪው ቅጣት ጋር ተዳምሮ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።

ከዚህም በላይ በአንቀጹ ላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፪፻፯ <u>የክልከላዎችና የሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች ውሳኔ ውጤት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፯ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የድንጋጌው ስያሜ "ካንዳንድ ሥፍራ ከመድረስ መከልከል፣ በአንድ በተወሰነ ሥፍራ የመኖርና ካገር የመውጣት ውሳኔ የሚያስከትለው ውጤት።" የሚል ነበር። ነገር ግን በስያሜው ውስጥ የተዘረዘሩት በሙሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች በተጨማሪ ከሙያ ሥራ መከልከልንም የሚጨምር በመሆኑ ስያሜው ሙሉ ይዘቱን እንዲያንፀባርቅ ለማድረግ ተሻሽሎ "የክልከላዎችና የሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች ውሳኔ ውጤት" በሚል እንዲነበብ ሆኗል።

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ "ወደ ማኅበራዊ ኑሮ መደቡ መመለስ" በሚለው ሀረግ ውስጥ "ማህበራዊ ኑሮ" የሚለው ንዑስ ሀረግ፤ በተለቃቂው ላይ የተወሰነው የተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ አፈጻጸም ለጊዜው ሲታገድ ተለቃቂው ይመለሳል ተብሎ የሚታመንበትን ደንበኛውን ማህበራዊ ኑሮ ለማመልከት ስለሆነ "ደንበኛው" የሚል ቃል "ማህበራዊ ኑሮ" ከሚለው ሀረግ በፊት እንዲገባ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com



"መደቡ" የሚለው ቃልም አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዟል። እንዲሁም በንዑስ ቁጥሩ ውስጥ በሚገኙት በሁለቱም ፓራግራፎች ላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) እና (፫) የተደነገጉት ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የጥበቃ ባልደረብነት

### አንቀጽ ፪፻፫ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፫ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የድንጋጌው ስያሜ "መሠረቱ" የሚለው፣ "መርህ" በሚል ተተክቷል።

ይዘቱም በመጀመሪያው ፓራግራፍ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ላይ "የሚረዳ ዋነኛ የሆነ አስፈላጊ ድርጅት..." በሚለው ሀረግ ውስጥ ከእንግሊዝኛውና ከፈረንሳይኛው ቅጂዎች ለመመልከት እንደተቻለው "ድርጅት" የሚለው ቃል "ሥርዓት" በሚለው ቃል ምትክ በስህተት የገባ በመሆኑ እንዲስረዝ ተደርጓል። ስለዚህም ከላይ በመጀመሪያ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ የተመለከተው ሀረግ ሳገላለጽ እንዲያመች ተሰርዞ "ፍሬ እንዲያስገኝ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "የሚደረግበት ሥርዓት ነው።" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል።

በሁለተኛውና በሶስተኛው ፓራግራፎች የተመለከቱት ፍሬ-ነገሮች የተቀራረቡና የተያያዙ በመሆናቸው በሶስተኛው ፓራግራፍ የተመለከተው በሁለተኛው ፓራግራፍ ከተመለከተው ጋር ከተዋሀደ በኋላ የዚህ አንቀጽ ሁለተኛ አዲስ ፓራግራፍ እንዲሆን ተደርጓል። ከላይ ከተገለጹት ማሻሻያዎች በቀር የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎአል።

### አንቀጽ ፪፻፬ የጥበቃ ባልደረባነት ዓላማና ተግባር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፬ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፬ ሆኖ ገብቷል።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፪፻፲፬ ስያሜ "የባልደረባነት ዓላማና ስልጣን።" የሚል ነው። ሆኖም "የባልደረባነት" የሚለው ቃል የምን ባልደረባነት እንደሆነ የሚገልጽ ባለመሆኑ ይህን ለማመልከት በማሰብ ከዚህ ቃል በፊት "የጥበቃ" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጎአል። እንዲሁም ሥልጣን የሚለው ቃል ውሱን መስሎ ስለሚታይ ይዘቱን በሚገባ እንዲያንጸባርቅ ቃሉ ተሰርዞ "ተግባር" በሚል ተተክቶአል።

ይዘቱም በንዑስ ቁጥር (፩) የጥበቃ ባልደረብነት ሥልጣን የተሰጠው ድርጅት (አካል) በተቻለ መጠን ተጠባቂዎቹን በሥራ ላይ ሊያውላቸው፣ ሥራ ሊሰጣቸው፣ ሥራ ወይም መኖሪያ ወይም እርዳታ እንዲያገኙ ሊያግዛቸው ወይም በሥራቸው የሚገኙትን ደመወዝና ጥቅም ለተገቢ ጉዳያቸው እንዲያውሉት የማድረጉ ጉዳይ በእርሱ ምርጫ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን መደረግ ስላለበት "ለመስጠት ይችላል" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ያደርግላቸዋል"

www.abyssinialaw.com

በሚል የሁለተኛው ፓራግራፍ ዓረፍተ-ነገር ማሰሪያ ተሻሽሏል:: ከዚህ በተጨማሪ ንዑስ ቁጥሩ ሌሎች አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ፍሬ ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተሻሽሏል::

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የተሻሻሉት ንዑስ ቁጥሮች የዚህ አንቀጽ ንዑሳን አንቀጾች ሆነው ገብተዋል::

አንቀጽ ፪፻፲ አደረጃጀት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፰ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የሥራው ድርጅት" የሚል ነው:: ነገር ግን ይህ ስያሜ ይዘቱን የማይገልጽ በመሆኑ ተሰርዞ "አደረጃጀት" በሚል እንዲተካ ሆኗል::

ይዘቱንም በንዑስ ቁጥር (፩) ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገጉት ፍሬ-ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያዎች ተደርጎባቸው ከተሻሻሉ በኋላ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነው እንዲገቡ ተደርጓል::

ምዕራፍ ሁለት
ክስንና ቅጣትን ማቋረጥና ማስቀረት
ክፍል አንድ
የክሳሽ ወይም የተከሳሽ አለመኖር
ንዑስ ክፍል አንድ
የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ አለመኖር

አንቀጽ ፪፻፲፩ የግል አቤቱታ ወይም የወንጀል ክስ የማቅረብ መብት በጠቅላላው

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፯ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፩ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "በጠቅላላ አቤቱታ የማቅረብ ወይም ..." በማለት የተመለከተው በይዘቱ ውስጥ የተካተተው በበስተቀርታ በመሆኑና በዋነኛነት ደረጃ ክስ የማቅረብ መብት የዐቃቤ ሕግ በመሆኑ ስያሜው ይህንን ይዘቱን እንዲያንፀባርቅ ሀረጉ ተሰርዞ የቀረው ከተቃና በኋላ "ክስ የማቅረብ መብት በጠቅላላው" በሚል እንዲነበብ ሆኖ ስያሜው ተሻሽሎአል::

የንዑሳን ቁጥሮች በፓራግራፎች ተከፍሎ የቀረበው እያንዳንዱ ፓራግራፍ ዐቢይ አሳብ የያዘ በመሆኑ ፓራግራፎቹ በንዑሳን አንቀጾች ተከፋፍለው ቢቀመጡ እንደሚሻል በማመን በዚሁ አኳኋን ተሻሽለዋል:: የቃላት ማስተካከያም ተደርጎባቸዋል:: ነገር ግን በሦስተኛው ፓራግራፍ ላይ የተመለከተው ፍሬ-ነገር ከወንጀል ሕጉ ይልቅ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ውስጥ ቢካተት የተሻለ በመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፪፻፲፪ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፪ የተደረገ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "በግል ከሣሽ አቤቱታ ስለሚቀርብ የወንጀል ክስ" የሚል ነው፡፡ አንድ ወንጀል የተበዳዩን ብቻ ሳይሆን የጠቅላላውን ሕብረተሰብ ጥቅምና ደህንነት የሚመለከት በመሆኑ የወንጀል ክስ የማቅረብ መብት ያለው በመንግሥት ስም ዐቃቤ ሕግ ስለሆነ በግል ከሣሽነት የወንጀል ክስ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ዳሩ ግን አንዳንድ ቀለል ያሉ ወንጀሎች ከሕብረተሰቡ ጥቅምና ደህንነት ይልቅ የተበዳዩን ግለሰብ ጥቅምና ደህንነት የሚመለከቱ በመሆናቸው የሕጉ ልዩ ክፍል በተለይ በሚደነግገው መሠረት እንደዚህ ያለውን ክስ የግል ተበዳዩ ወይም ስለእርሱ ሆኖ የመክሰስ መብት ያለው ሰው የክስ አቤቱታውን ካላቀረበ በቀር በዐቃቤ ሕግም ቢሆን ክስ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ዐቃቤ ሕግ በግል አቤቱታው መሠረት ጉዳዩን አጣርቶ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያቀርባል፡፡ ስለዚህ ከግለሰቦች የግል አቤቱታ ሊቀርብ ከሚችል በቀር የወንጀል ክስ ሊቀርብ አይችልም፡፡ የግል አቤቱታ የሚያስፈልጋቸው ወንጀሎችም የግል አቤቱታ ካልቀረበባቸው በቀር ለማቅረብ አይቻልም፡፡

ስለዚህ በግል ከሳሽ አቤቱታ በቀጥታ የወንጀል ክስ ለማቅረብ ስለማይቻል ስያሜው ተሰርዞ "በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች" በሚል ተተክቶአል፡፡

በድንጋጌው የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ መሆኑ በዚህ ሕግ ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ማሟያ የወንጀል ሕግ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ በግል ተበዳይ ወይም በህጋዊ ወኪሉ የግል አቤቱታ ካልቀረበ በቀር የወንጀል ክስ ማቅረብ አይቻልም፡፡" በሚል ድንጋጌ ተተክቶአል፡፡

ሁለተኛው ፓራግራፍ ግን ቀጥሎ ወዳሉት ድንጋጌዎች የሚያመላክት ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች የወንጀል ሕጉ ወጥተው በወንጀል ሥነ-ሥርዐት ሕጉ እንዲካተቱ ስለተደረገ የሁለተኛው ፓራግራፍ መኖር አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል፡፡

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፲፰ ድንጋጌ መሰረዝ

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ "የክስ አቤቱታ የማቅረብ ተገቢ መብት" የሚል ሲሆን፣ የግል ጠባይ ባላቸው ወንጀሎች የግል አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት፣ በሕጉ መሰረት ችሎታ ያላቸው ሰዎች መሆናቸውንና ተበዳዮቹ ችሎታ የሌላቸው ሲሆን ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሆኑ የሚደነግግ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ድንጋጌ ግን በይበልጥ ትክክለኛ ቦታው ከወንጀል ሕጉ ይልቅ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለሆነ ከዚህ ተሰርዞ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፲፱ ድንጋጌ መሰረዝ

ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰው ድንጋጌ፣ የግል ጠባይ ያለው ወንጀል፣ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች ላይ በሚፈጸምበት ጊዜ እያንዳንዳቸው በግል ወይም ሁሉም በህብረት አቤቱታ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ድንጋጌው በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መካተቱ የተሻለ በመሆኑ ከዚህ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

 www.abyssinialaw.com 

ንቀጽ ፪፻፲፫ <u>የግል አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፳፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፫ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው በመጠኑ ተሻሽሎአል::

የድንጋጌው ስያሜ ".... ያቀራረቡ ፎርም" በማለት የተመለከተው ከወንጀል ሕጉ ይልቅ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ የሚካተት መሠረታዊ አሳብ በመሆኑ ከይዘቱ እንዲወጣ በመደረጉ ከስያሜውም ውስጥ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: የቀረውም የስያሜው ክፍል ተሻሽሎ "የግል አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱም በሁለት ንዑሳን ቁጥሮች የተከፈለው ከላይ ለስያሜው በተሰጠው ምክንያት ውስጥ እንደተገለጸው የግል አቤቱታ አቀራረብ ፎርም ከወንጀል ሕግ ይልቅ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ የሚታይ በመሆኑ በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው እንዳለ እንዲሰረዝ ተደርጎአል::

በመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር ላይ የተመለከተው ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ግልጽ እንዲሆን ተዘጋጅቷል::

<u>የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፳፮ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ይህ ድንጋጌ የግል አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ተበዳዩ ክሱ እንዳይቀጥል ማድረግ እንደሚችል የሚገልጽ ነው:: በሌላ አነጋገር በወንጀል አድራጊው ላይ የተጀመረው ምርመራ እንዲያቋርጥና ፍርድ ቤት እንዳይፈርድበት የሚያደርግ ማመልከቻ ጽፎ ማቅረብ ይችላል ማለት ነው:: ይህ ድንጋጌ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ውስጥ ቢካተት የተሻለ በመሆኑ ከዚህ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

<u>የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፳፯ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ይህ ድንጋጌ ክስ የማይከፋፈል ስለመሆኑ የተጻፈ ሲሆን የግል ጠባይ ባለው ወንጀል ተካፋዮቹ ከአንድ በላይ ሲሆኑ ከእነርሱ መካከል በአንዱ ላይ ብቻ የግል አቤቱታ ማቅረብ ሁሉንም እንደመክሰስ፣ የአንዱን ክስ መተው ደግሞ የሁሉንም ወንጀል አድራጊዎች ክስ እንደመተው የሚቆጥር ድንጋጌ ነው:: ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕግን የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>የተከሳሽ ወይም የተፈረደበት ሰው መሞት</u>

ንቀጽ ፪፻፲፬ <u>የተከሳሽ መሞት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፳፰ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፬ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ስለ መሞቱ" የሚል ነበር:: ይህ ስያሜ ክሱ በፍርድ ቤት ተጀምሮ በተከሳሹ ላይ ከመፈረዱ በፊት ተከሳሽ የሞተ እንደሆነ ብቻ

www.abyssinialaw.com



ያስመስላል:: ነገር ግን ተከሳሹ ገና ፍርድ ቤት እንኳን ሳይቀርብ የሚሞትበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል ስያሜው ይህንን ሁኔታ መግለጽ እንዲችል ተሻሽሎ "የተከሳሽ መሞት" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱም ከላይ በስያሜው እንደተገለጸው ተከሳሹ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከመከሰሱ በፊት ወይም ፍርድ ቤት ቀርቦ ተከሶ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት የሚሞትበት ሁኔታ ስላለ ይህንኑ ለማመልከት "ፍርዱ ከመወሰኑ በፊት ወንጀለኛው የሞተ እንደሆነ" በማለት የተገለጸው ተሻሽሎ "ተከሳሽ በፍርድ ቤት ከመከሰሱ በፊት ወይም ተከሶ ፍርድ ከመወሰኑ በፊት በማናቸውም ጊዜ የሞተ እንደሆነ" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

በተጨማሪም "የተከሳሽ መሞት ክሱን አስቀርቶ ዋጋ የሌለው ያደርገዋል" የሚለው ተሰርዟል:: ምክንያቱም ከዚህ በፊት ያለው ዓረፍተ-ነገር ይህንኑ ሁሉ አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ነው::

አንቀጽ ፩፻፲፮ <u>የተፈረደበት ሰው መሞት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፮ የተደረገ ሲሆን ማሻሻያ ተደርጎበታል::

የድንጋጌው ስያሜ "ከቅጣት ፍርድ ውሳኔ በኋላ ስለ መሞት" የሚል ነው:: ነገር ግን የድንጋጌው ስያሜ "ከቅጣት ፍርድ ውሳኔ በኋላ ስለ መሞት" የሚል ነው:: ነገር ግን የሚፈረደው ፍርድ የቅጣት ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የጥንቃቄ እርምጃ ጭምር በመሆኑ ይህንን አካቶ በሚይዝ መልክ ተሻሽሎ "የተፈረደበት ሰው መሞት::" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱም በአንደኛው ፓራግራፍ ላይ "የገንዘብ መቀጮውንም ውሳኔ" በማለት የተመለከተው "ቅጣት" በሚለው ውስጥ የሚካተት በመሆኑ አላስፈላጊ ስለሆነ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ በአንደኛውም ሆነ በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ የሌሎች የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>የክስና የቅጣት ይርጋ</u>

የክፍሉ ስያሜ በቀድሞው ሕግ መሰረት "ስለ ይርጋ" ይል ነበር:: ሆኖም ይርጋ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች በግልጽ እንዲያመለክት "የክስና የቅጣት ይርጋ" እንዲል ተደርጓል::

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>
<u>የክስ ይርጋ</u>

አንቀጽ ፩፻፲፯ <u>መርህ እና ውጤቱ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፮ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፯ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፩) በማናቸውም ወንጀል የግል አቤቱታና ክስ ለመቀበልም ሆነ ክሱንም በጥፋተኝነት ለማየት እንደማይቻል መደንገጉ በአንድ ወንጀል ምክንያት በጣም በመዘግየት የሚቀርበውን ክስ ስለሚያስቀረው ለቀለጠፈ የዳኝነት አሰራር ጠቃሚ ነው:: ምንም እንኳን ለወንጀል ክስ ይርጋ ድንጋጌ መኖሩ አስፈላጊ ቢሆንም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፰ እና ኢትዮጵያ ባፀደቀችው የሰው ልጆችን ዘር ማጥፋት ወንጀል (Genocide Convention) አለም አቀፍ ሕግ በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በይርጋ እንደማይታገዱ በግልጽ በመደንገጉ ይህንኑ ለማመልከት በመነሻው ላይ "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጎአል::

ከላይ ከተገለጸው ማሻሻያ በተጨማሪ በንዑስ ቁጥር (፩)ም ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገጉት ፍሬ-ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆነው ገብተዋል::

ቁጽ ፪፻፲፯ <u>መደበኛ የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፳፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፯ እንዲሆን ተደርጓል:: የቀድሞው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥሮች አልነበሩትም በዚህ ህግ ግን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) የገባ ሲሆን የቀድሞው ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሆን ተደርጓል::

የንዑስ አንቀጽ (፩) ይዘት እያንዳንዱ ነጣላ ወንጀል እንደከባድነቱና እንደቀላልነቱ የማያስከስሰው ወይም በይርጋ የሚታገደው ምን ያህል ጊዜ ሲያልፍ ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል:: የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ደግሞ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚፈጸሙበት ጊዜ የክስ ማቅረቢያው የይርጋ ዘመን ምን ያህል እንደሆነ ይደነግጋል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት፣ የተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ጣራ ቅጣት ተመሳሳይ ከሆነ የአንዱ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን ለሌሎቹ ወንጀሎች ተገቢነት ይኖረዋል፤ የተደራራቢዎቹ ወንጀሎች ቅጣት በተለያየ ጊዜም የከባዱ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን በሌሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል:: በሌላ አነጋገር የአንዱ ተመሳሳይ ወንጀል ወይም ከሁሉ ከባድ የሆነው ወንጀል የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ብዛት ምክንያት የይርጋ ጊዜው እንዲራዘም አይደረግም ማለት ነው::

ቁጽ ፪፻፲፰ <u>ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፳፯ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፰ ሆኖ ገብቷል::

ከድንጋጌው ይዘት ጋር ተስማሚ እንዲሆን ስያሜው ተሻሽሎ "ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን" ተብሏል::

ይዘቱን በተመለከተ በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፲፫ ጋር እንዲገናዘብ ተደርጓል:: ምክንያቱም አቤት ባይ የወንጀሉን ድርጊትና የጥፋተኛውን ማንነት ካወቀበት ቀን ጀምሮ ወይም ለመክሰስ የማያስችል መሰናክል አጋጥሞት እንደሆነ መሰናክሉ ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ማመልከት እንደሚችል አንቀጽ ~~፪፻፲፰~~ ላይ የተደነገገ ሲሆን የሶስት ወሩ ጊዜ ሊሸጋሸግ የሚችለው እስከምን ጊዜ ድረስ እንደሆነ በአንቀጹ ላይ

www.abyssinialaw.com

አልተገለጸም:: ይህ አንቀጽ (፩፻፲፰) ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጣል፣ ይኸውም የሶስት ወሩ ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ሁለት ዓመት ብቻ እስኪሞላ ድረስ መሆኑን ይደነግጋል:: ከዚህም በላይ የአንቀጽ ፩፻፲፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚል ሀረግ ተጨምሮበታል::

ከዚህም በላይ የዚህ ሕግ የአንቀጽ ፩፻፲፰ ይዘት የግል ጠባይ ያላቸውን ወንጀሎች ምንነት በግልጽ ስለሚያሳይ እና በቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፩፻፳፯ ላይ በምሳሌነት የተሰጠው ዝርዝር አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዞ ይህ አንቀጽ ተሻሽሎአል::

አንቀጽ ፩፻፲፱ <u>የይርጋ ዘመን አቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፰ ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፱ ሆኖ ገብቷል::

በሁለቱም ንዑሳን አንቀጾች የተደነገገው ፍሬ-ነገር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎበት ከተሻሻለ በኋላ የንዑሳን አንቀጾች (፩) እና (፪) ይዘት ሆኖ እንዲገባ ተደርጎአል::

አንቀጽ ፩፻፳ <u>የይርጋ ዘመን መታገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፳ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

በቀድሞው ሕግ በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "ክሱ እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ጥፋተኛው በራሱ ፈቃድ በሚያደርገው ተግባር ካልሆነ በቀር"... የሚለው ሀረግ የፓራግራፉን ይዘት አደናጋሪ ከማድረጉም በቀር ተስማሚ ቦታው በንዑስ አንቀጽ (፪) ስር በመሆኑ ተሰርዟል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ "እንዲሁም በጥፋተኛው ላይ ክስ ቀርቦ ነገሩ በዳኝነት በመታየት ላይ እንደሆነ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም በሌላው ችሎት የቀረበው ክስ ሳይፈጸም በዚህ የወንጀል ክስ ውሳኔ ሊሰጥ የማይገባ እንደሆነ...." የሚለው ሀረግ ተጨምሯል:: ይህ አሳብ የተወሰደው ከ፲፱፻፶፬ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር ፪፻፵ (፪)(ረ) ሲሆን በዚህ በተጨማሪው ሀረግ በተገለጸው ምክንያት ክሱ ታግዶ ሊቆይ ስለሚገባ በዚህ መሠረት ተጨምሯል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ የሚገኘው ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር "መሰናከሉም እንደተወገደ ወዲያውኑ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር ይቀጥላል::" የሚል ሲሆን እራሱን የቻለ የንዑስ አንቀጽ (፩) ሶስተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል:: ይህ የሆነበት ምክንያት "መሰናከሉ እንደተወገደ" የሚለው ሀረግ በፓራግራፍ ሁለት ላይ ላለው ብቻ ሳይሆን በፓራግራፍ አንድ ላይ ላለው መሰናክልም አግባብነት ስላለው ነው::

በዚህ አንቀጽ ስር መጀመሪያ ላይ በተሰጠው አስተያየት መሠረት "እንዲሁም ክሱ እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ጥፋተኛው በራሱ ፍላጎት የሚፈጽመው ተግባር የይርጋ ጊዜውን መቆጠር አያግደውም::" የሚል አረፍተ-ነገር፣ በንዑስ አንቀጽ (፪) ስር አዲስ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

ከዚህ ሌላ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በአንቀጹ ላይ ተደርጓል፡፡

ቁጥ ፪፻፳፮ <u>የይርጋ ዘመን መቋረጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

የመጀመሪያው ፓራግራፍ ድንጋጌ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የእንግሊዝኛና የፈረንሳይኛ ቅጂ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የድንጋጌው አሳብ በትክክል የተንፀባረቀው በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂዎች ላይ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ትክክለኛውን አሳብ እንዲያንፀባርቅ ተደርጎ ተረቅቋል፡፡

ሦስተኛው ፓራግራፍ ግልጽነት ስለሌለው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ቁጥ ፪፻፳፯ <u>ፍፁም የሆነ የይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፩ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው ላይ አጣቃሽ ቁጥሮች በዓረፍተ-ነገሩ መጨረሻ ላይ መሆናቸው ቀርቶ በየቦታቸው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ "ልዩ የይርጋ ዘመን ሲሆን የዚህ ግማሽ አልፎ እንደሆነ..." የሚለው ሀረግ ትክክል ባለመሆኑ" ልዩ የግል አቤቱታ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን ሲሆን /አንቀጽ ፪፻፲፰/ ከዚሁ ዘመን በግማሽ የሚበልጥ ጊዜ አልፎ እንደሆነ ..." በሚል ተሻሽሏል፡፡

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፪ ድንጋጌ መሠረዝ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪፻፵፪ ተሰርዟል፣ ምክንያቱም የፍትሐብሔርን ይርጋ በተመለከተ መደንገጉ የፍትሐብሔር ሕጉ እንጂ የወንጀል ሕጉ ድርሻ ስላልሆነ ነው፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች ይርጋ</u>

ቁጥ ፪፻፳፰ <u>መርህና ውጤቱ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፰ የተደረገ ሲሆን

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ (፩) መግቢያ ላይ "በሕግ በሌላ አኳኋን በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ተጨማሪ ቅጣቶች ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎች ከዋነኛው ቅጣት ጋር ተጣምረው እንዲፈጸሙ ተወስኖ ከሆነ የዋናው ቅጣት የይርጋ ዘመን ማለፍ ለተጨማሪ ቅጣቶችም ሆነ ለጥንቃቄ እርምጃዎቹ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጓል:: የጥንቃቄ እርምጃዎች ያለዋና ቅጣት ብቻቸውን በሚወሰኑበት ጊዜ ግን የይርጋ ዘመኑ ምን ያህል እንደሆነ አልተደነገገም:: ይህን ክፍተት ለመሸፈን በሁለተኛው ፓራግራፍ መጨረሻ ላይ "ሆኖም የጥንቃቄ እርምጃዎች ያለዋነኛ ቅጣት በሚወሰኑበት ጊዜ የአንቀጽ ፻፲፰ (፩) (መ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::" የሚል አዲስ ዓረፍተ-ነገር እንዲገባ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ለሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ የተወሰነ ስለሆነ" የሚለው ሀረግ ማብራሪያ እንጂ የድንጋጌው አካል መሆን ስለማይገባው ተሰርዟል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ "ተመዝግቦ መኖር አለበት" የሚለው አነጋገር ሊስተካከል ይገባል:: ምዝገባው ቅጣት በተወሰነ ጊዜ የሚፈጸም ጉዳይ ነው:: ቅጣቱ በይርጋ ቀሪ ሲሆን የነበረው ምዝገባ ነዋሪ ይሆናል እንጂ እንደ አዲስ ተመዝግቦ መኖር አለበት የሚባል አይደለም:: በመሆኑም በዚሁ መሠረት ፓራግራፉ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኗል:: የተለየ ንዑስ አንቀጽ የሆነው ራሱን የቻለ አሳብ ስላካተተ ነው::

በንዑስ ቁጥር (፫) የሰፈረው ድንጋጌ የፍትሐብሔር ይርጋን የሚመለከት በመሆኑ እና ይህንን መደንገግ የፍትሐብሔሩ ሕግ ተግባር በመሆኑ ከዚህ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፻፲፰ <u>መደበኛ የቅጣት ይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፻፵፬ ድንጋጌ የዚህ ህግ አንቀጽ ፻፲፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የጊዜው ውሳኔ" የሚል ነበር:: ሆኖም ስያሜው በይዘቱ ውስጥ የተደነገገውን በግልጽ ያመለክት ዘንድ "መደበኛ የቅጣት የይርጋ ዘመን" እንዲል ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ጠቅላላ ውርስ" የሚለው ቃል ተሰርዟል:: ምክንያቱም ዋና ቅጣት ባለመሆኑ እና የዋናው ቅጣት የይርጋ ዘመን ከቅጣቱ ጋር ለተያያዘ የንብረት ውርስ ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ነው:: ይህ አሳብ የአንቀጽ ፻፲፫ ሁለተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ሆኖ የገባውም በዚሁ ምክንያት ነው::

በንዑስ ቁጥር (፩) (መ) ላይ "ለማንኛዎቹም ለሌሎቹ ቅጣቶች" ከሚል በቀር የጥንቃቄ እርምጃዎችን የማይጨምር በመሆኑ እንዲካተት ተደርጓል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፻፵፮ (፪) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር በይበልጥ ተስማሚ ቦታው እዚህ በመሆኑ ተሻሽሎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል፤ ምክንያቱም የዚህ ዓረፍተ-ነገር አነጋገር ስለ ይርጋ ዘመን መጠን እንጂ የይርጋው ጊዜ ስለሚቆጠርበት ሁኔታ አይደለምና:: የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ግን ስለ

 www.abyssinialaw.com

ይርጋ ዘመን መጠን እንጂ ስለ ይርጋ አቆጣጠር የተደነገገ ባለመሆኑ ከነበረበት ቦታ ተሰርዞ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል።

ቀጽ ፪፻፳፭ <u>የቅጣት ይርጋ ዘመን አቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፭ ሆኖ ገብቷል።

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፮ (፪) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ተሻሽሎ የአንቀጽ ፪፻፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል። የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ግን በዛው ባለበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል። በተጨማሪም አንቀፁን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አስፈላጊ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርገውበታል።

ቀጽ ፪፻፳፮ <u>የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ የይርጋ ዘመን መታገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፮ ሆኖ ገብቷል።

የቁጥር ፪፻፴፯ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር እንዳለ ተቀባይነትን አግኝቷል።

ቀጽ ፪፻፳፯ <u>የቅጣት የይርጋ ዘመን መቋረጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፯ ሆኖ ገብቷል።

የቁጥር ፪፻፴፰ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር እንዳለ ተቀባይነት አግኝቷል።

ቀጽ ፪፻፳፰ <u>ፍጹም የሆነ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ፣ ይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፰ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜው ላይ "የቅጣት" የሚል ቃል ይገኝበታል። ሆኖም ይዘቱ ከቅጣት በተጨማሪ የጥንቃቄ እርምጃንም የያዘ በመሆኑ ስያሜው ቅጣትንም ሆነ የጥንቃቄ እርምጃን እንዲያመለክት በትዕምርተ-ጥቅስ ውስጥ ያለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጓል።

ይዘቱም ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ይቅርታና ምህረት</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የክፍል ሶስት ስያሜ "በተለይ የሚሰጥ ምህረትና የአዋጅ ምህረት" የሚል ነበር። ሆኖም አንቀጽ ፻፲፯/፪ "ምህረት" እና "የአዋጅ ምህረት" እንደአቀማመጣቸው ቅደም ተከተል "ይቅርታ" እና "ምህረት" በሚል የተተኩ በመሆኑና የአጠቃቀሙንም ወጥነት ለመጠበቅ የክፍል ሶስት ስያሜ ተሰርዞ "ይቅርታና ምህረት" በሚል እንዲነበብ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፪፻፳፱ ይቅርታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፳፱ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሎአል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ " ምህረት" ይላል ሆኖም የአንቀጹ ስያሜ በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ "Pardon" ስለሚል እና የዚህ ቃል ትርጉም "ይቅርታ" ስለሆነ ስያሜው "ይቅርታ" እንዲል ተደርጓል፡፡

ከዚህም ሌላ በአንቀጹ ላይ የፓራግራፍ እና የዓረፍተ-ነገር የቦታ አቀማመጥ ለውጥ ተደርጓል፡፡

የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ቅጣት በጠቅላላው በይቅርታ ሊሻር ወይም ሊለወጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፪) ፓራግራፍ አንድ በመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ላይ ደግሞ ይቅርታ ዋናው ቅጣቶችን እና ተጨማሪ ቅጣቶችን እንደሚያጠቃልል ተመልክቷል፡፡ ሁለቱም ዝምድና ያላቸው በመሆኑ በንዑስ ቁጥር (፪) ፓራግራፍ አንድ ላይ የሚገኘው የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር የንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቶአል፡፡

የንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ እና በንዑስ ቁጥር (፪) በአንደኛው ፓራግራፍ የሚገኘው ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ይቅርታ ስለሚሰጥበት ሥርዓት ወይም ሕግ አወጣጥ የሚደነግጉ በመሆናቸው የንዑስ አንቀጽ (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሆነው ገብተዋል፡፡ የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ላይ "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር" የሚል ሀረግ ገብቷል፡፡ ይህም የሆነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፰ መሠረት በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ይቅርታ እንደማይደረግላቸው የተደነገገውን ለማመልከት ነው፡፡ በንዑስ ቁጥር (፩) "ንጉሠ-ነገሥቱ" የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጎአል፡፡ ይቅርታ ቀደም ሲል ለማናቸውም ወንጀሎች ይሰጥ የነበረው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፰ በሰብዕና ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ሊሰጥ እንደማይችል በግልጽ በመደንገጉ ይህን የሁሉም ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕግ ድንጋጌ ለማመልከት እና እንደአግባቡ ሥልጣን ሊኖረው የሚችለውን አካል እንዲያካትት ታስቦ "ስልጣን በተሰጠው አካል" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፪) "ምህረት" በማለት የተገለጸው ከላይ በተሰጠው ምክንያት ተሰርዞ "ይቅርታ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዚህ ንዑስ ቁጥር (፪) "በወንጀል ፍርድ ስሌዳ" በማለት የተገለጸው ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች ውስጥ በተሰጠው ምክንያት ተሰርዞ "በፍርድ መመዝገቢያ መዝገብ" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል፡፡

በተጨማሪም በአንቀጹ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

ቁጽ ፪፻፴ ምህረት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የዐዋጅ ምህረት" የሚል ነው:: በዚህ ስያሜ ውስጥ "የዐዋጅ" የሚለው ቃል የገባው ከላይ በአንቀጽ ፪፻፳፱ "ምህረት" በማለት ከተገለጸው ለመለየት ነው:: ሆኖም በአንቀጽ ፪፻፳፱ "ምህረት" "ይቅርታ" በሚል የተሻሻለ በመሆኑ የሚፈጥረው ችግር ባለመኖሩ "የዐዋጅ" የሚለው ተሰርዞ ስያሜው "ምህረት" በሚል ብቻ እንዲነበብ ሆኖአል::

ይዘቱንም በንዑስ ቁጥር (፩) ቀደም ሲል ለማናቸውም ዓይነት ወንጀሎች ወይም ወንጀለኞች ምህረት ሊሰጥ የሚችል መስሎ የተቀረፀው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፳፰ በስብዕና ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ምህረት እንደማይሰጥ በግልጽ ከተደነገገው ጋር እንዳይቃረን ንዑስ አንቀጹ "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር" በሚል እንዲጀምር ተደርጎአል:: እንዲሁም በዚሁ ንዑስ ቁጥር በመጀመሪያ ፓራግራፍ ላይ ".... ፍጹም በሆነ አይነት ወይም ባንዳንድ ውል..." በማለት የተገለጸው ግልጽነት የሚጎድለው በመሆኑ ተሻሽሎ"... ያለምንም ገደብ ወይም በአንዳንድ ገደቦች...." በሚል እንዲነበብ ሆኖአል:: ከዚህም በተጨማሪ ንዑስ ቁጥሩ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ቅጣት የሚለው ቃል ተሰርዟል:: ምክንያቱም ፍርድ እና ቅጣት በሁለተኛው ፓራግራፍ የተካተተ በመሆኑ እና የመጀመሪያው ፓራግራፍ ክስን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ነው::

ቁጽ ፪፻፴፩ በፍትሐብሔር በኩል የሚከፈል ካሣና ወጪ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፩ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

ይዘቱ በንዑስ ቁጥር (፩)ም ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌዎች ላይ "ምህረት" ወይም "የአዋጅ ምህረት" በማለት የተገለጹት ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች ውስጥ በተገለጸው ምክንያት ተሰርዘው "ይቅርታ" ወይም "ምህረት" በሚሉ ቃላት እንደአግባብነቱ ተተክተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱም ንኡሳን ቁጥሮች ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

## ክፍል አራት
## መሰየም

ቁጽ ፪፻፴፪ መርህ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፪ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፪ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com



የንዑስ ቁጥር (፩) ዝርዝር በቂ ስላልሆነ "ፍርዱ ወይም የቅጣት አፈጻጸሙ የታገደለት ወይም በአመክሮ የተለቀቀ....." የሚል እንዲጨመር የተደረገ ሲሆን፤ ምክንያቱ ስለ አንቀጽ ፪፻፴፫ በተሰጠው ማብራሪያ ላይ ተገልጿል።

በንዑስ ቁጥር (፩) "ቅጣቱ .... በምህረት በአዋጅ ምህረት ...." በማለት በተገለጸው ዐረፍተ-ነገር ውስጥ "ምህረት" የሚለው ቃል ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች ውስጥ በተገለጸው ምክንያት ተሰርዞ "ይቅርታ" በሚል ቃል ተተክቶአል። ከላይ በትእምርተ ጥቅስ በተቀመጠው ዓረፍተ-ነገር ውስጥ የዐዋጅ ምህረት በማለት የተገለጸው ከላይ ከተመለከቱት ማሻሻያዎች ውስጥ ምህረት በማለት የተገለጸውን ለማመልከት በመሆኑና ምህረት ደግሞ በአንቀጽ ፪፻፴/፪/ ሁለተኛው ፓራግራፍ እንደተመለከተው በመሰየም ሊገኙ የሚችሉ ሕጋዊ ውጤቶችን ሁሉ የሚያስገኝ በመሆኑ ምህረት ያገኘ ሰው እንደገና እንዲሰየም ማድረጉ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፪፻፴፫ <u>ለመሰየም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፫ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

በቀድሞው ድንጋጌ መንደርደሪያ ላይ "መሰየምን ፍርድ ቤቱ የሚፈቅደው" ካለ በኋላ በፊደል /ሀ/ ላይ "ቅጣቱ የሚመለከተው ጽኑ እስራትንና ስለ ወንጀል ልማደኛነት በተደጋገመ ጥፋት ቅጣቱ ባንድ ጽኑ ግዞት ቦታ ተወስኖ በመኖር የተለወጠ ቅጣትን፣ እስከ መጨረሻው ከአገር የመውጣትን ወይም የጠቅላላ መወረስን የሆነ እንደሆነ <u>ተቀጪው የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ወይም ከተፈታበት ቀን ጀምሮ</u> በጥቂቱ የአስር ዓመት ጊዜ ያለፈ እንደሆነ በሌላው ሁኔታ ሲሆን ግን ያለፈው ጊዜ በጥቂቱ አምስት ዓመት የሆነ እንደሆነ" ተብሎ ተደንግጓል። በፊደል (ሀ) ላይ፣ "ቅጣቱ የሚመለከተው ጽኑ እስራትንና" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ፣ በልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ላይ ስለሚወሰነው ጽኑ ግዞት የተቀመጠው አገላለጽ እንዲሰረዝ ተደርጓል። ይህም የሆነው፣ ጽኑ ግዞትን የሚመለከቱት ከቁጥር ፻፳፰-፻፴፪ የተመለከቱት የቀድሞው ህግ ድንጋጌዎች የተሰረዙና የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ እንዲቀር የተደረገ በመሆኑ ነው።

በፊደል (ሀ) ላይ፣ "ተቀጪው የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ወይም ከተፈታበት ቀን ጀምሮ" የሚለው የተሰመረበት ሀረግ በቂ ዝርዝር አላካተተም፤ "ከተፈታበት ቀን ጀምሮ" የሚለውም ግልጽ አይደለም። በመሆኑም ስለቅጣቱ መፈፀም ከሚገልፀው ሐረግ ቀጥሎ ቅጣቱ "በይርጋ ከታገደበት ቀን አንስቶ፣ ወይም ቅጣቱ በይቅርታ በመሻሩ ምክንያት ተቀጪው ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ወይም ተቀጪው ቅጣቱ ታግዶለት ወይም በአመክሮ ተፈትቶ የፈተናውን ጊዜ በሰላም ጨርሶ እንደሆነ ቅጣቱ ከታገደለት ወይም በአመክሮ ከተፈታበት ቀን አንስቶ" በማለት ተጨማሪ ሁኔታዎች እንዲካተቱ ተደርጓል።

ተቀጪው የሚሰየመው ቅጣቱን ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ የተወሰነ ጊዜ ሲያልፍ ብቻ መሆን የለበትም፤ በተዘረዘሩት ሌሎች ምክንያቶችም የተወሰነ ጊዜ ካለፈ የመሰየም መብት ሊኖረው ይገባል።

www.abyssinialaw.com

ቅጣቱ በይርጋ የታገደለት ሰው፣ የመሰየሚያው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ቅጣቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ሲሆን እንደሚገባ አከራካሪ ባለመሆኑ ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ አይደለም።

ይቅርታ የተደረገለት ሰው የመሰየሚያው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ይቅርታ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ወይም ይቅርታ ባያገኝ ኖሮ ቅጣቱን ይፈጽምበት ከነበረው ቀን ጀምሮ እንደሆነ ክርክር ሊያስከትል ይችላል።

ሆኖም መንግሥት ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን በማመዛዘን ይቅርታ ይገባዋል ብሎ ይቅርታ ያደረገለትን ሰው የመሰየሚያ ጊዜ ማራዘሙ ጠቃሚ ሆኖ አይታይም። የተወሰነበት ቅጣት ተፈጻሚ ቢሆን ኖሮ ፍጻሜ ያገኝ ከነበረበት ቀን ጀምሮ የመሰየሚያውን ጊዜ ማስላቱ፣ ይቅርታ የተደረገለትን ሰው የመሰየሚያ ጊዜ ያለአግባብ ያስረዝምበታል። በይቅርታ ከተለቀቀበት ቀን አንስቶ ቅጣቱን ይጨርስ እስከነበረበት ቀን ድረስ የመሰየሚያውን ጊዜ መቆጠር አይጀምርም ማለቱ ሰውየውን በተዘዋዋሪ እንደመቅጣት የሚያስቆጥር ነው። በመሆኑም የመሰየሚያው ጊዜ በይቅርታ ከተለቀቀበት ቀን አንስቶ መቆጠር እንዲጀምር ተደርጎ ተደንግጓል።

ከዚህም ሌላ ስለአመክሮ የሚደነግገው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፬ (፪) ድንጋጌ ከላይ እንደተመለከተው በፊደል (ሀ) ስር እንዲገባ ተደርጓል።

በገደብ የተለቀቀን ሰው የሚመለከት ድንጋጌ ያልነበረ ሲሆን በዚህ አንቀጽ በፊደል (ሀ) ስር ሁኔታው እንዲካተት ተደርጓል። በዚህም ረገድ የመሰየሚያ ጊዜ የሚታሰበው የቅጣቱ ውሳኔ ወይም አፈጻጸሙ ከታገደለት ቀን ጀምሮ እንዲሆን ተደርጎአል። ይህም የሚሆነው ለአመክሮ እንደተደነገገው ሁሉ የፈተናውን ጊዜ በመልካም ሁኔታ ሲጨርስ ብቻ ይሆናል።

በተጨማሪም በተራ ፊደል (ሀ) ተቀጭው የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ወይም ከተፈታበት ቀን ጀምሮ እንደተወሰነበት ቅጣት ክብደት ቢያንስ የአስር አመት ጊዜ ወይም የአምስት አመት ጊዜ እንዲጠብቅ የተወሰነው አላግባብ ረጅም ጊዜ ነው። ወንጀለኞች መደበኛ ቅጣታቸውን ሲፈጽሙ ወይም ቅጣታቸው በይርጋ ወይም በይቅርታ ከቀረላቸው ወይም በገደብ ከታገደላቸው ወይም በአመክሮ ከተለቀቁ በኋላ ለመሰየም በጣም ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ማድረጉ እነርሱን ብቻ ሳይሆን የአገርንም የኢኮኖሚ እድገት ሊጎዳ ስለሚችል "የአስር አመት" የሚለው "አምስት አመት"፣ "አምስት አመት" የሚለው "ሁለት አመት" በሚል ሀረግ ተተክቷል።

የፊደል (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎችን አቀማመጥ በሚመለከት በይበልጥ ተስማሚ ነው ተብሎ በሚታመንበት ሁኔታ፣ የፊደል (ለ) ድንጋጌ በፊደል (መ) ስር፣ የፊደል (ሐ) ደግሞ በፊደል (ለ) ስር እንዲሁም የፊደል (መ) ድንጋጌ በፊደል (ሐ) ስር እንዲገባ ተደርጓል።

በተራ ፊደል (ለ) (በዚህ አንቀጽ ፊደል (መ) በሆነው) በማናቸውም ጥፋት ሳይከሰስና አቤቱታም ሳይቀርብበት ቆይቶ እንደሆነ የሚለው ሀረግም የተብራራ ካለመሆኑም በላይ አቤቱታ ቀረበበት ተብሎ የመሰየምን መብት መንፈጉ አግባብ ስለማይሆን ሀረጉ ተሰርዞ በእስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ሳይሆን ቆይቶ እንደሆነ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል።

www.abyssinialaw.com

በተራ ፊደል (ሐ) እና (መ) /በዚህ አንቀጽ በፊደል (ለ) እና (ሐ)/ የተደነገጉት መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎባቸው ተሻሽለዋል::

ከፊደል (መ) ድንጋጌ በታች አዲስ ፓራግራፍ እንዲገባ ተደርጐአል፤ ይኸውም፣ "ከላይ በፊደል (ሀ) የተገለፀው "ለመሰየም የሚያበቃው አነስተኛ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፯ ስለደጋጋሚነት የተደነገገውን የጊዜ ገደብ እስካልነካ ድረስ ነው::" የሚል ነው::

ይህ ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በፊደል (ሀ) ላይ በተደነገገው መሠረት የሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ የተሰጠው ሰው ይህንን ጊዜ በሰላም ቢጨርስም፣ የመሰየሚያ ጊዜው መቆጠር የሌለበት ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችል በመሆኑ ነው:: የሁለቱን ዓመት የፈተና ጊዜ በመልካም ሁኔታ ከፈፀመ በኋላ አንድ ወይም ሁለት ዓመት ቆይቶ አንድን ወንጀል አስቦ ያደረገ እንደሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፯ መሠረት ደጋጋሚ ተብሎ የባሰ ቅጣት ይወሰንበታል እንጂ፣ የመሰየሚያው ጊዜ መቆጠር ተጀምሯልና በደጋጋሚነት ሊጠየቅ አይገባም የሚል ክርክር ማቅረብ አይቻልም:: ይህ ፓራግራፍ በድንጋጌው እንዲገባ የተደረገው የዚህ ዓይነቱን አሻሚ ሁኔታ ለማስቀረት ነው::

## አንቀጽ ፪፻፴፩ ልዩ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፩ የተደረገ ሲሆን የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ተሰርዞ ንዑስ ቁጥር ሶስት የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል:: የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ የተሰረዘው የአንቀጽ ፪፻፴፫ (ሀ) አካል ሆኖ በመግባቱ ነው::

በተጨማሪም በጠቅላላው አንቀጽ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## አንቀጽ ፪፻፴፪ የመሰየም ውጤቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፪ ድንጋጌ በመጠኑ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፪ ሆኖ ገብቷል:: በቀድሞው ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተከፍለው የነበሩት ድንጋጌዎች እያንዳንዳቸው እራሳቸውን የቻሉ ዓረፍተ ነገሮች ስለሆኑ በንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ስር እንዲመጡ ተደርጓል::

በመንደርደሪያው ማስሪያ ላይ ይችላል በማለት የተገለጸው የአስገዳጅነት ባህርይ የሌለው በመሆኑ የማይችልም መስሎ ስለሚያሳይ ተሰርዞ "ያስከትላል" በሚል ተተክቷል::

በተራ ፊደል (ለ) ከፍርድ የግል ሰሌዳ በማለት የተገለጸው ከላይ በተደረጉት ማሻሻያዎች ውስጥ በተገለጸው ምክንያት ተሰርዞ "ከወንጀለኞች መዝገብ" በሚል እንዲተካ ተደርጓአል::

በተራ ፊደል (ሐ) "ለሕዝባዊ ጥቅም ወይም እውነት ነገር መሆኑን ለመርታት ሳይፈቀድለት" በሚለው ሀረግ ውስጥ "ለመርታት ሳይፈቀድለት" የሚለው ንዑስ ሀረግ ግልጽ አይደለም:: በዚህ ፊደል (ሐ) ዓላማ የተመለከተው አንድ ሰው ከተሰየመ በኋላ

www.abyssinialaw.com

በማናቸውም ምክንያት ያለፈውን ቅጣት አንስቶ መውቀስ ለሕዝባዊ ጥቅም ወይም እውነት ነገር መሆኑን ለማስረዳት ቢቻል እንኳን ወቃሹን በስም ማጥፋት ወንጀለኛነት የሚያስቀጣው መሆኑን ለመደንገግ ነው። ስለዚህ "ለመርታት ሳይፈቀድለት" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ለሕዝብ ጥቅም የተደረገ ነው ብሎ መከላከልም አይቻልም።" በሚል ዓረፍተ-ነገር ተተክቶአል።

ከዚህም በላይ በጠቅላላው ድንጋጌ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቁጥር ፮፻፴፮ ለመሰየም የሚቀርበውን ጥያቄ አለመቀበልና ጥያቄውን እንደገና ማቅረብ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፮ ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፮ ሆኖ ገብቷል።

ቁጥር ፮፻፴፯ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፯ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ይዘቱን በተመለከተ አንድ ጥፋተኛ በተሰየመ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነፃነትን የሚያሳጣ ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት እንደሆነ ሁለተኛ እንደማይሰየም ተደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ ውስጥ "ነፃነትን የሚያሳጣ" የሚለው አገላለጽ ቀላል እስራትንም ሆነ ጽኑ እሥራትን የሚያጠቃልል በመሆኑ ቀላል እስራት የተፈረደባቸው ጥፋተኞች እንኳን ሳይቀር እንደገና ከመሰየም የሚከለክል ነው። ይህ ደግሞ በግለሰቦቹ ላይ ብቻ ሳይሆን በአገር ኢኮኖሚ ላይም የማይናቅ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እሙን ነው። ስለዚህም ሁኔታውን ጠበቅ ለማድረግ በማሰብ አገላለጹ ተሰርዞ "በጽኑ እስራት" በሚል እንዲተካ ተደርጓል። እንዲሁም ዳግመኛ ለመሰየም እንደማይችል የተደነገገው ቀድሞ ስለተሰየመው የሚገልጸው ነገር ባለመኖሩ"..... ተወስኖበት" እንደሆነ ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "የተፈቀደለት መሰየም ይሰረዛል፣" የሚል አዲስ ዓረፍተ-ነገር እንዲገባ ተደርጓል። ዳግመኛ መሰየም እንደማይችልም ለማመመልከት ከላይ ከተጨመረው ዓረፍተ-ነገር ቀጥሎ "እንዲሁም ዳግመኛ እንዲሰየም ሊፈቀድለት አይቻልም።" በማለት ተደንግጎአል።

## ሁለተኛ ታላቅ ክፍል
## ልዩ ክፍል
## ሦስተኛ መጽሐፍ
## በመንግሥት፣ በአገርና በአለም አቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

በዚህ በሶስተኛው መጽሐፍ ስያሜ ውስጥ በስራ ላይ ባለው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ "በመንግሥት ላይ በአገርና በኢንተርናስዮናል ጥቅሞች ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች" ተብሎ የነበረው ሀረግ አገላለጽ ግልጽነት የሚጎድለውና የተንዛዛ ስለነበረ ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን ተስተካክሎ እንዲጻፍ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

## ርዕስ አንድ
## በመንግት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### ምዕራፍ አንድ
### በአገር ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

በቀድሞው ህግ በምዕራፍ አንድ ስያሜ ውስጥ "በመንግሥት ግዛት አገር ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች" ተብሎ የነበረው አገላለጽ ግልጽነት የጎደለው ስለነበረ በስያሜው ላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሎና አጠር ተደርጎ ተቀርጿል።

### ክፍል አንድ
### በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና በአገር ውስጥ ደህንነት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

በዚህ የክፍል አንድ ስያሜ በቀድሞ ሕግ ውስጥ "በንጉሠ ነገሥቱ፣ በሕገ መንግስቱ ደንብና በመንግሥቱ ያገር ውስጥ ፀጥታ ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች" ተብሎ የነበረው አገላለጽ ዛሬ ባለንበት የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ዘውዳዊ ሥርዓት ስለሌለ "በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና በአገር የውስጥ ደህንነት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች" በሚል እንዲተካ እና ግልጽነት ባለው አኳኋን እንዲስተካከል ተደርጓል።

### ንዑስ ክፍል አንድ
### በሕገ መንግሥቱና በመንሥት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

#### የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፵፰ ድንጋጌ መሰረዝ

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፪፻፵፰ ድንጋጌ በንጉሠ ነገሥቱና በንጉሣውያን ቤተሰብ ላይ አደጋ በመጣል የሚደረጉ ወንጀሎችን ይመለከት ነበር። ሆኖም የንጉሠ ነገሥት አገዛዝ በአሁኑ ጊዜ የሌለ በመሆኑና ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲሁም ለንጉሣውያን ቤተሰቦች ጥበቃ የሚያደርግ ድንጋጌ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል።

በምትኩ ለርዕሰ ብሔሩና ለቤተሰቡ ጥበቃ የሚያደርግ የተለየ ድንጋጌ እንደገባ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ የማንኛውም ሰው የሕይወት ወይም የአካል ደህንነት በሕጉ መሠረት ጥበቃ የሚደረግለት ከመሆኑም በላይ በሥራው ሁኔታ ልዩ ጥበቃ በሚያሻው ሰው ላይ በተለይም "...... በሕግ በተቋቋመ ባለሥልጣን ወይም የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የሕዝብ አገልጋይ በሆነ ሠራተኛ ላይ "አንድ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ እንደሚከብድ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፹፬(፩)(ሠ) ላይ የተደነገገው፣ ለርዕሰ ብሔሩም ሆነ ለሌሎች ባለሥልጣኖች በቂ ጥበቃ የሚሰጥ በመሆኑ ነው።

#### የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፵፱ ድንጋጌ መሰረዝ

የድንጋጌው ስያሜም ሆነ ይዘት በዙፋን አወራረስ ላይ የሚፈጸም ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አስተዳደር የዘውድ አገዛዝን የማይከተል በመሆኑ ድንጋጌው ተሽሯል።

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፪፻፴፰ <u>በሕገ መንግሥትና በሕገ መንግሥት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፴፰ ሆኖ ገብቷል።

ይህ ድንጋጌ ከአንቀጽ ፪፻፴፪ ጋር በተጣጣመ ' መልኩ የፌዴራልና የክልል ሕገ መንግሥታዊ አካላትን ሥራ በሚጠብቅ ሁኔታ ተስተካክሎ ተቀርጿል። በተለይም በፊደል ተራ (ሰ) ላይ "የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈጻሚ ወይም የፍርድን ሥልጣን" የሚለው ዝርዝር አገላለጽ ተቀይሮ" በፌዴራል ወይም በክልል ሕገ መንግሥት የተቋቋመውን ሥርዓት ያፈረሰ ወይም የለወጠ እንደሆነ" በሚል ጠቅላላ አነጋገር እንዲተካ ተደርጓል።

ቀጽ ፪፻፴፱ <u>የሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል</u>

ይህ አንቀጽ ከአንቀጽ ፪፻፵ ጋር በተጣጣመ መልኩ የፌዴራልና የክልል ሕገ-መንግሥታዊ አካላትን ስራ በሚጠብቅ ሁኔታ ተስተካክሎ ተቀርጿል። በተለይም "የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈጻሚ ወይም የፍርድን ባለሥልጣን" የሚለው ዝርዝር አገላለጽ ተቀይሮ "በፌዴራል ወይም በክልል ሕገ-መንግሥት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ወይም ባለሥልጣኖች" በሚል ጠቅላላ አነጋገር እንዲተካ ተደርጓል። አካላት ሲባል ሕግ አውጭውን፣ ሕግ አስፈጻሚውን እና የዳኝነት አካላትን የሚመለከት ሲሆን ባለሥልጣኖች ሲባልም የነዚህኑ አካላት ባለሥልጣኖች የሚመለከት ይሆናል።

ቀጽ ፪፻፵ <u>የጦር መሣሪያ ይዞ በማመጽ፤ ወይም የእርስ በርስ ጦርነት በማስነሣት በመንግሥት ላይ የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሎአል።

የአንቀጹ ስያሜ ከይዘቱ ጋር እንዲስማማ ተደርጓል። የድንጋጌው ይዘት የእርስ በእርስ ጦርነት ማስነሣትን የሚመለከት በመሆኑ ስያሜው በዚሁ መሠረት እንዲስተካከል ተደርጓል። አንቀጹ አራት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪፻፶፪ (፩) መግቢያ ላይ ማንም ሰው" በሚል እንዲጀምር የተደረገው ወንጀሉን ለመፈፀም የተነሣበት የአሳብ ሁኔታ የማያመለክት ስለነበረ አዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፩) "ማንም ሰው አስቦ " በሚል ሐረግ እንዲጀምር ተደርጓል። በቀድሞው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ፩(ሀ) ላይ "ለማንሳት የፈለገ እንደሆነ" የሚለው ሐረግ ሃሳብን ብቻ የሚያመለክት ስለሆነና በድርጊት ያልተገለጠ አሳብ በወንጀል የማያስቀጣ በመሆኑ ተሰርዞ "…. እንዲያነሱ ያደራጀ ወይም የመራ እንደሆነ" በሚል ተተክቷል። በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ውስጥ "ያገር ተወላጆችን" የሚለው ሐረግ "ዜጎችን" በሚል ቃል ተተክቷል።

ቅጣትን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) መሠረት ወንጀሉ የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ድረስ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በሞት እንዲያስቀጣ ተደርጐ ነበር። ሆኖም በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል "ሀ" እና "ለ" በግልጽ የተመለከቱት ድርጊቶች ከአስር እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ብቻ እንዲያስቀጡ ማድረግ በቂ

www.abyssinialaw.com



ሆኖ ተገኝቷል። ወንጀሉ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ማስቀጣት የሚገባውም በሕዝብ ደህንነት ወይም ኑሮ ላይ ከፍተኛ ቀውስ ሲያስከትል ብቻ መሆኑ ታምኖበታል። በዚህም መሠረት ንዑስ ቁጥር አንድ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና በንዑስ አንቀጽ (፪) ተከፍሎ ተረቅቋል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሶስት የተደረገ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ አራት እንዲገባ ተደርጓል። ንዑስ አንቀጽ አራት የሚመለከተው በንዑስ አንቀጽ (፩) ፣ (፪) እና (፫) የተጠቀሱትን ወንጀሎች ያደራጀ ወይም በእነዚህ ወንጀሎች ተካፋይ የሆነ ጥፋተኛ ሌላ ወንጀል መፈጸሙ ከተረጋገጠ ለዚሁ ለሌላው ወንጀል በተደራቢነት ተጠያቂ መሆኑን ነው።

በተጨማሪም ድንጋጌው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተረቅቋል።

አንቀጽ ፪፻፵፩ <u>የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፩ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሎአል።

በቀድሞ ስያሜው ውስጥ "የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት" የሚለው ሀረግ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው "የአገሪቱን" በሚል ቃል የተተካ ሲሆን ይዘቱም የተንዛዛና ግልጽነት የሚጎድለው ስለነበረ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተስተካክሎአል። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት መሰረት በኃይል፣ በማስገደድ ወይም ሕገ መንግስቱን በሚጻረር ሁኔታ የሚፈፀም የመገንጠል ጥያቄ ተቀባይነት እንዳይኖረው በመደረጉ በዚህም ድንጋጌ ውስጥ አስፈላጊ ማስተካከያ ተደርጎበት ተቀርጿል።

ቅጣቱንም በሚመለከት ማሻሻያ ተደርጓል። ይኸውም "ከአስር ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ የሆነ እንደሆነ በሞት ይቀጣል" ይል የነበረ ሲሆን የዚህ አንቀጽ መደበኛው ወንጀል ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ግን በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ ይገባል ተብሎ በመታመኑ በዚሁ መልኩ ተረቅቋል።

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፵፱ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪፻፵፱ ከዚህ ተሰርዞ አንቀጽ ፪፻፶፯ ሆኖ ገብቷል። የዚህ ሕግ ስያሜ "የተንኮል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት" የሚል ሲሆን በይበልጥ ተስማሚ ቦታው ስለመገፋፋትና ግዙፍ ስላልሆነ የማሰናዳት ተግባር ከተደነገጉት አንቀጽ ፪፻፶፰ በፊት ስለሆነ ከዚህ ተሰርዞ እዚያ እንዲካተት ተደርጓል።

አንቀጽ ፪፻፵፪ <u>የአገሪቱን የግዛት ወይም የፖለቲካ ሉአላዊነት በመጣስ የሚደረግ ወንጀል</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፪፻፶፩ ድንጋጌ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሲሆን እንደሚከተለው ማሻሻያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

የዚህ አንቀጽ ስያሜ በሥራ ላይ በነበረው ሕግ ውስጥ ግልጽነት የጎደላቸው ቃላት የነበሩበት ስለሆነ ይኸው ታርሞ ከዚህ በላይ ባለው ሁኔታ ተስተካክሏል:: ይዘቱን በተመለከተም አሁን ካለው የፌዴራል መንግሥት ሥርዓት ጋር የማይጣጣሙ ቀጥተኛ ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶች እንዲወጡና በሌሎች እንዲተኩ ከተደረገ በኋላ ተስተካክሎና ታርሞ እንዲቀረጽ ተደርጓል::

ቅጣቱም ቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ተብሎ በቀድሞው ድንጋጌ የተመለከተው በቂ በመሆኑ ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል::

ቁጽ ፪፻፵፫ <u>በሕገወጥ መንገድ ከአገር መውጣት፣ ወደአገር መግባት ወይም በአገሪቱ ውስጥ መኖር</u>

ይህ አንቀጽ አዲስ ሲሆን የተጨመረበትም ምክንያት ድርጊቶቹ ወንጀል ሆነው በነጋሪት ጋዜጣ በወጣ አዋጅ የተካተቱ ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁኔታውን የሚሸፍን አንቀጽ ባለመኖሩና አንድ አጠቃላይ አንቀጽ በወንጀል ሕጉ ውስጥ ሊካተት እንደሚገባ በመታመኑ ነው::

አንቀጹ አምስት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን የያዙት ፍሬ ሃሳብ እንደሚከተለው ነው::

ንዑስ አንቀጽ (፩) በሁለት ፊደላት የተከፈለ ሲሆን፣ የፊደል (ሀ) ድንጋጌ በአንቀጹ ስያሜ ላይ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች የፈጸመን ሰው የሚያስቀጣ ነው፤ የዚህ ዓይነቱ ሰው ድርጊቶቹን እንዲፈጽም ያደረገ ወይም የረዳው ሰው ደግሞ በፊደል (ለ) በተመለከተው ድንጋጌ ስር ይፈረድበታል::

የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ፣ የማይገባ ጥቅም በማግኘት ወይም በሀሰተኛ ሰነድ አማካይነት ወይም በሌላ ህገ ወጥ መንገድ አንድን ግለሰብ ወደ ኢትዮጵያም ይሁን ወደ ሌላ አገር የሚያስገባ ማንኛውንም ሰው ያስቀጣል::

በህገ ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ወይም ወደ ሌላ አገር እንዲገባ የተፈለገው ሰደተኛ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ድርጊት ሲፈጸም ልዩ ልዩ ወንጀል ወይም በደል የደረሰበት እንደሆነ፣ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ጥፋተኛ ከባድ ቅጣት እንዲወሰንበት የሚያደርግ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጊ የህግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት በወንጀል የሚያስቀጣ ሲሆን፣ የሚቀጣው በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) የተዘረዘረው ድርጊት እንዲፈጸም የረዳ እንደሆነ ነው:: በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተመለከቱት ድርጊቶች ሲፈጸሙ የሚረዳ ድርጅትም ሊቀጣ ይገባው ነበር:: ሆኖም የንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች የወንጀል ህጉ ለህትመት ሲቃረብ እንዲገቡ የተደረገ በመሆኑ የንዑስ አንቀጽ (፬)ን ይዘት አስተካክሎ መቅረጽ ሳይቻል ቀርቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ፣ የተፈጸመው ጥፋት ቀላል በሚሆንበት ጊዜ በደንብ መተላለፍ የሚያስቀጣ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## አገርን መድፈር

በቀድሞው ሕግ ላይ የንዑስ ክፍል ሁለት ስያሜ "ንጉሠ ነገሥቱንና መንግሥቱን ስለ መድፈር" ይል ነበር። ከዚህ ቀደም በተሰጠው ምክንያት፣ ንጉሠ ነገሥት የሚለው ሀረግ የተሰረዘ ሲሆን ርዕሰ ብሔርን ስለመድፈር የተለየ ድንጋጌ ማስቀመጡም አስፈላጊ ባለመሆኑ "ርዕሰ ብሔር" የሚለው ሀረግ በ "ንጉሠ ነገሥት" ምትክ እንዲገባ አልተደረገም። በዚህ ምክንያት የማያስፈልጉ ቃላት ተሰርዘው የንዑስ ክፍሉ ስያሜ ከላይ በተጻፈው ሁኔታ ተስተካክሏል።

### የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፮ ድንጋጌ መሰረዝ

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፶፮ ድንጋጌ ንጉሠ ነገሥቱን ወይም የሕገ መንግሥቱን ባሥልጣኖች በመድፈር ስለሚሰራ ወንጀል የሚደነግግ ነበር። መድፈር ሲባልም ስም ማጥፋትን፣ ስድብንና ማዋረድን የሚመለከት ነው። ሆኖም በዚህ የወንጀል ሕግ ግን የዚህ ድንጋጌ መኖር አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፤ ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው።

"ንጉሠ ነገሥት" የሚለው ሀረግ ከጊዜው የፖለቲካ አስተዳደር ጋር ስለማይጣጣም ተሰርዟል፤ በምትኩም ርዕሰ ብሔርን የሚመለከት ድንጋጌ ማካተቱ አላስፈለገም። በማንኛውም ባለሥልጣን ላይ ወንጀል ሲፈጸም በዚሁ ምክንያት አድራጊው ከፍ ያለ ቅጣት እንደሚወሰንበት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፹፬ (፩) (ሠ) ተመልክቷል። አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከስልጣኑ ወይም ከስራው ጋር ተያይዞ ስሙ እንዲጠፋ ሲደረግ፣ ሲሰደብ ወይም ሲዋረድ፣ አድራጊው የሌላውን ሰው ስም ከሚያጠፋበት ወይም ከሚያዋርድበት ጊዜ ይልቅ ከባድ ቅጣት እንደሚቀጣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፮፻፲፫ ላይ ተደንግጓል። ስለዚህም ከሥልጣኑ ጋር በተያያዘ መንገድ ርዕሰ ብሔሩን መስደብ፣ ማዋረድ ወይም ስሙን ማጥፋት በዚሁ አንቀጽ መሠረት እንዲያስቀጣ ማድረጉ በቂ ሊሆን እንደሚችል ታምኖበታል።

ከዚህም ሌላ በቀድሞ ጊዜ አንድ ሰው ጠላቱን ለማጥቃት ሲፈልግ "እገሌ ንጉሠ ነገሥቱን ደፍሯል፤ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፕሬዘዳንቱን ክብር ነክቷል!" እያለ፣ በሀሰት በመወንጀልና በሀሰት በማስመስከር አላስፈላጊ የሆነ የሥራ ጫና በፖሊስ፣ በዓቃቤ ሕግ እና በፍርድ ቤት ላይ ይፈጥር ነበር። በመሆኑም ርዕሰ ብሔርን መድፈር በማንኛውም ሰው አመልካችነት ማስቀጣቱ ቀርቶ ርዕሰ ብሔሩ ወይም የርዕሰ ብሔሩ ወኪል ብቻ ክስ ሲመሰርት፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ማድረጉ በቂ ሆኖ ተገኝቷል።

ከላይ በተገለጸው መሠረት ለሁሉም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ጥበቃ ከሚያደርገው ከአንቀጽ ፮፻፲፫ በተጨማሪ ለርዕሰ ብሔሩ የተለየ ጥበቃ የሚያደርግና በማንም አመልካችነት የሚያስቀጣ ድንጋጌ መቅረጹ አስፈላጊ ስላልሆነና በሀሰት ከሶ ለማስቀጣት በር የሚከፍት ስለሆነ የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፶፮ (፩) ድንጋጌ ተሰርዟል።

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፮ (፪) ድንጋጌም እንዲሰረዝ ተደርጓል። ይህ ንዑስ ቁጥር (፪) በሕገ-መንግሥት ስለተቋቋሙት ባለሥልጣኖች መደፈር የሚደነግግ ሲሆን ጉዳዩ ስም ማጥፋትን፣ ስድብን ወይም ማዋረድን የሚመለከት ስለሆነና በዚህ ሁኔታ መብታችን ተነካ የሚሉ ባለሥልጣኖች ወይም አካላት ደግሞ እንደማንኛውም ሰው በዚህ የወንጀል

www.abyssinialaw.com

ሕግ አንቀጽ ፮፻፲፫ በተመለከተው አኳኋን አቤቱታቸውን ለፍርድ ቤት በማቅረብ መክሰስ ስለሚችሉ ይህ ካልሆነ ግን የመንግሥት አካላት አሰራር ግልጽ ሆኖ ሕዝብ የመተቸት መብት እንዳለው እየታመነ ይህ መብት በሥራ ላይ እንዳይውል የሚገድብ ድንጋጌ ስለሚያስመስለው ለነዚህ አካላት የተለየ ጥበቃ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም:: ስለዚህ የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፶፪ (፪) ድንጋጌ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

ቀጽ ፪፻፵፬ <u>የአገሪቱን መንግሥት እንዲሁም የአገሪቱን ምልክቶችንና በመንግሥት የታወቁ ሌሎች ምልክቶችን መድፈር::</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፪፻፶፪ ድንጋጌ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሲሆን እንደሚከተለው ማሻሻያ ተደርጎበታል::

የቀድሞ ድንጋጌ ስያሜ "ያገር ምልክቶች የሆኑ ዓላማዎችን በመድፈር ስለሚሰራ ወንጀል" ይል ነበር ሆኖም አገሪቱን መድፈር ወንጀል የሚያደርግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) በመግባቱና "ዓላማዎች" የሚለው ቃል ግልጽ ባለመሆኑ፣ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ስያሜው ተስተካክሏል::

አገሪቱን መድፈር የሚመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲገባ ያስፈለገበት ምክንያት፣ ሁኔታውን የሚሸፍን ድንጋጌ በቀድሞ ሕግ ውስጥ ባለመኖሩ ነው:: የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፪(፪) ድንጋጌም የኢትዮጵያን መንግሥት (Government ) እንጂ አገሪቱን (the state of Ethiopia) አይመለከትም ነበር ሆኖም አገሪቱን መሳደብ፣ ማዋረድ፣ በሀሰት መወንጀል (calumny) ወይም ስሟን ማጥፋት እንደቀላል ነገር ሊታይ ስለማይገባ እንደወንጀል ተቆጥሮ እንደሚያስቀጣ በንዑስ አንቀጽ (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ተደንግጓል:: የተዘረዘሩት ድርጊቶች ትርጓሜም በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፮፻፲፫ እና ፮፻፲፮ በተመለከተው መሠረት እንደሆነ የሚገልጽ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፪፻፶፪ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደረገ ሲሆን ወቅታዊ ያልሆኑ አንዳንድ ሀረጎች እንዲሰረዙ ተደርጎ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የታወቁ ምልክቶችን በሚያንጸባርቅ መልኩ እንዲስተካከል ሆኗል::

ቀጽ ፪፻፵፭ <u>በታወቁ ምልክቶች ያለአግባብ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ውስጥ "ግልጽ በሆኑ ምልክቶች" የሚለው ሀረግ ግልጽነት ስለሚጎድለው "በታወቁ ምልክቶች" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጎ የተስተካከለ ሲሆን ይዘቱን በተመለከተ የታወቁ ምልክቶች የሚባሉት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ምልክቶች በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ አጭርና ግልጽ ተደርጎ ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሁለት
## በመንግሥት የውጭ ደህንነት እና በመከላከያ ኃይል ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

በዚህ ክፍል ስያሜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ ውስጥ "በመንግሥቱ የውጭ ኃይል" የሚለው ሀረግ ግልጽ ስላልነበረ ተለውጦ "በመንግሥት የውጭ ደህንነት" ተብሎ ተስተካክሏል።

አንቀጽ ፪፻፵፮ <u>በአገር ነፃነት ላይ የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፮ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ሕግ ውስጥ የዚህ አንቀጽ ስያሜ "የመንግሥትን ነፃነት በመንካት ስለሚሰራ ወንጀል" ተብሎ ተቀርጾ ነበር። ነገር ግን ይህ አገላለጽ የጽንሰ አሳብ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ከዚህ በላይ በስያሜው ውስጥ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሎ ተቀርጿል።

በአንቀጹ ስያሜና ይዘት ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ቅጣቱን በሚመለከትም መሻሻል ተደርጓል፤ ይኸውም "ከአስር ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም በጣም ከባድ የሆነ እንደሆነ በሞት ይቀጣል" ይል የነበረ ሲሆን ለአወሳሰን ግልጽ እንዲሆን መደበኛው ወንጀል ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ ይገባል ተብሎ በመታመኑ በዚሁ መልኩ ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፪፻፵፯ <u>የአገር መከላከያ ኃይል ለመንካት የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፯ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ አንቀጽ ስያሜ በቀድሞው ሕግ የተጻፈው ግልጽነት የሌለው ስለነበረ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ እንዲስተካከል ተደርጓል። ይዘቱን በተመለከተም ከእንግሊዝኛውና ከፈረንሳይኛው ቅጂ ጋር በሚገባ ተነጻጽሮ ግልጽና ቀላል በሆነ አነጋገር የተስተካከለ ሲሆን በተለይ በንዑስ ፊደል (ሐ) ውስጥ "ሽብር" የሚለው ቃል የትኛውን ዓይነት ሽብር እንደሚያመለክት ግልጽ ስላልሆነ "ወታደራዊ ዓመጽ" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል።

አንቀጽ ፪፻፵፰ <u>ከፍ ያለ ክዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፰ ሆኖ ገብቷል።

ይህ አንቀጽ በይዘቱ ውስጥ ከተደረጉበት የቃላት ማቃናት በስተቀረ በቀድሞ ሕግ ውስጥ የሚገኘው ድንጋጌ ተቀባይነት አግኝቷል።

ቅጣቱን በሚመለከት ማሻሻያ ተደርጓል። ይኸውም "ከአሥር አመት እስከ ዕድሜ ልክ ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በሞት ይቀጣል" ይል የነበረ ሲሆን በአወሳሰን ላይ አሻሚነት እንዳይኖረው መደበኛ ወንጀል ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ ይገባል ተብሎ በመታመኑ በዚሁ መልክ ተረቅቋል።

www.abyssinialaw.com

## ጽ ፪፻፵፱ ክዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

የዚህ አንቀጽ ስያሜ በቀድሞው ሕግ ውስጥ "የዲፕሎማቲክ ክዳት" ተብሏል፡፡ ነገር ግን ከይዘቱ ጋር ሲነፃፀር በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ከተመለከተው በስተቀር በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) እና (ሐ) ውስጥ የተመለከቱት ወንጀሎች ዲፕሎማት ባልሆነ በማናቸውም ሰው ሊፈጸሙ የሚችሉ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ማናቸውንም ሰው በሚያቅፍ መልኩ ክዳት ተብሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ "ማናቸውንም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የኢትዮጵያን ጥቅም እንዲያስከብር በግልጽ አደራ የተጣለበት" ተብሎ ተስተካክሎ እንዲፃፍ ተደርጓል፡፡

በንዑስ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ወንጀል በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ወንጀል ያህል ከባድ ባለመሆኑና የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ አንድ ቅጣትም ከአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የማይበልጥ በመሆኑ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሁለት ቅጣት ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት መሆኑ ቀርቶ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## ጽ ፪፻፶ የኢኮኖሚ ክዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶ ሆኖ ገብቷል፡፡

የዚህ አንቀጽ ስያሜ በቀድሞው ሕግ ውስጥ "የኢኮኖሚ የሀብት ክዳት" ይል የነበረው አሳስፈላጊ ድግግሞሽ ሆኖ ስለተገኘ "የኢኮኖሚ ክዳት" ተብሎ ተስተካክሏል፡፡ ይዘቱን በተመለከተም በጠቅላላው የቃላት ማቃናት የተደረገበት ሲሆን በተለይ በንዑስ አንቀጽ (፩)/ሀ/ ውስጥ "ስለንጉሠ ነገሥት መንግሥቱ ግዛት---" የሚለው ተሰርዞ "ስለኢትዮጵያ" በሚል ተተክቷል፤ ንዑስ አንቀጽ (፩)/ለ/ ደግሞ ከእንግሊዝኛው ጋር በተጣጣመ መልኩ "እንዲጠብቃቸው በኃላፊነት የተሰጡትን ዕቃዎች ወይም መሣሪያዎች---" ተብሎ ተስተካክሏል፤ ንዑስ አንቀጽ (፩)/ሐ/ በተለይ

አሳስፈላጊ ቃላት ተሰርዘው ከእንግሊዝኛው ጋር በሚገባ የሚጣጣም ሆኖ ተስተካክሏል፡፡

## ጽ ፪፻፶፩ ከጠላት ጋር መተባበር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

የዚህ አንቀጽ ስያሜ በቀድሞው ሕግ ውስጥ "ከጠላት ጋራ አብሮ ስለመስራት /ጠላትን ስለመርዳት/" ተብሎ በተንዛዛና ግልጽነት በሌለው ሁኔታ ተጽፎ የነበረው ተሻሽሎ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተረቅቋል፡፡ ይዘቱም በስያሜው ላይ በተገለጸው አኳኋን እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በተለይ የፊደል (ሀ) ድንጋጌ ግልጽነት ስለሌለው ተስተካክሎ እንዲጻፍ ከመደረጉ በተጨማሪ በፊደል (ለ) ውስጥ "ከጠላት ግዴታ ለማምለጥ" የሚለው ቀርቶ "ከጠላት ቁጥጥር ለማምለጥ" በሚል ተተክቷል፡፡ የፊደል (ሐ) ክፍል ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ተስተካክሏል፡፡ በቅጣቱ ላይ ለውጥ አልተደረገም፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፶፪ ስለሳ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ውስጥ "ንጉሠ ነገሥት" የሚለው ሀረግ ተሰርዟል፣ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የቃላት ማቃናት እና እርማት ተደርጎበትና ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል:: በቅጣቱ ላይ ለውጥ አልተደረገም::

አንቀጽ ፩፻፶፫ <u>የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ለጦር ጓደኞች መንግሥታት ተፈፃሚ መሆናቸው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ "ይህ የጥበቃው ውሳኔ ለጦር ጓደኞቹ መንግሥታትም ተፈጻሚ ስለመሆኑ" ይል ነበር:: ሆኖም አገላለጹ ተሻሽሎ "የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ለጦር ጓደኞች መንግሥታት ተፈጻሚ መሆናቸው" በሚል ተተክቷል::

ይዘቱን በተመለከተ "ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጋራ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: ከዚህ ውጭ አነስተኛ የቃላት መቃናት ብቻ ተደርጎበት የአንቀጹ ይዘት በቀድሞው ሕግ ውስጥ ያለው ተቀባይነት አግኝቷል::

<u>ክፍል ሶስት</u>
<u>የወል ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ ፩፻፶፬ <u>በተዘዋዋሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፬ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ በሚመለከት "በዘወርዋራ እንደተደረገ ስለሚቆጠር ማገዝና መርዳት" ይል የነበረ ሲሆን ከይዘቱ ጋር በሚጣጣም መልኩ "በተዘዋወሪ መንገድ መርዳትና ማበረታታት "እንዲል ተደርግዋል::

በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ የነበሩት አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው አገላለጹ እንዲስተካከል ተደርጓል::

ንዑስ ቁጥር (፫) ንዑስ አንቀጽ (፪)፤ ንዑስ ቁጥር (፬) ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል:: ይህ የሆነበት ምክንያት በንዑስ ቁጥር (፬) የተጻፈው ድንጋጌ ተፈጻሚነቱ በንዑስ ቁጥር (፩) ለተመለከተው ወንጀል ብቻ ሳይሆን በንዑስ ቁጥር (፫) ለተደነገገው ጭምር በመሆኑ ነው::

ንዑስ ቁጥር (፪) ግን በነበረበት ቦታ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ እንዲቀጥል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com


ቀጽ ፪፻፶፭ ለወንጀል ሥራ ማነሣሣትና አባሪነት፣ የማነሳሳትና የአባሪነት ሙከራ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "በወንጀል ስያሜው ተካፋይነት ጊዜ ስለሚደረግ ሙከራ" ይል የነበረው ከይዘቱ ጋር በሚጣጣም መልክ ስያሜው እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ ድንጋጌውን የሚመለከቱ አንቀጾች በአንቀጹ ይዘት መግቢያ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ አንቀጹ የማነሣሣትና የአባሪነት ሙከራን ብቻ ሳይሆን አባሪነትንና አነሣሽነትንም እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ የማነሳሳት ወይም የአባሪነት ሙከራ ያስቀጣል ከተባለ፣ ከሙከራ ያለፈ የማነሳሳት ወይም የአባሪነት ተግባር ሊያስቀጣ እንደሚገባ ግልጽ በመሆኑና እነዚህ ድርጊቶች እንደሚያስቀጡ የሚደነግግ ሌላ አንቀጽ በዚህ ምዕራፍ ባለመኖሩ ነው፡፡

የቅጣቱም መጠን ከወንጀሉ ክብደት አንጻር ተለውጦ ከአንድ ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚቻል ቀላል እሥራት ወይም ድርጊቱ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ከነበረ ቅጣቱ እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት እንደሚሆን ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

ቀጽ ፪፻፶፮ የተንኰል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ አይነት ማሰናዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

"የተንኰል ድርጊቶችን ግዙፍ በሆነ ዓይነት ማሰናዳት" ወንጀል የቀድሞ ቦታውን ለቅቆ የአንቀጹ ይዘት የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት እና በንዑስ ፊደል (ሀ) እና (ለ) ተከፍሎ ገብቷል፡፡ የፊደል (ሀ) ድንጋጌ "ወታደሮችን፣ የሽምቅ ተዋጊዎችን፣ ሽፍቶችን ወይም ቅጥረኞችን"፤ የፊደል (ለ) ድንጋጌ ደግሞ "የጦር መሣሪያዎችን፣ ጥይቶችን፣ ስንቅን፣ ገንዘብን ወይም እነዚህን የመሳሰሉትን ግዙፍ የሆኑ ነገሮችን"፤ የሚመለከት ሲሆን ድንጋጌው በዚህ መልክ የተቀረጸው ግልጽ እንዲሆን ስለሚረዳ ነው፡፡

ቀጽ ፪፻፶፯ መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜውን በሚመለከት "ስለመነሳሳትና ስለማሰናዳት" ይል የነበረ ሲሆን "መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር" እንዲል ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም በእንግሊዝኛው ትርጉም ላይ "provocation" ለሚለው ቃል ከማነሳሳት ይልቅ "መገፋፋት" የሚለው ቃል በይበልጥ ተስማሚ መሆኑ ስለታመነበትና የመሰናዳቱ አይነት በአንቀጽ ፪፻፷፫ ከተመለከተው ግዙፍ መሰናዳት ለይቶ ማመልከቱ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

የአንቀፁም ይዘት የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ተረቅቋል፡፡

ቀጽ ፪፻፶፰ ከባድ ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፶፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

www.abyssinialaw.com



በቀድሞ ድንጋጌ ይዘት ውስጥ "በንጉሠ ነገሥቱ፣ በዙፋን አወራረስ---" የሚሉት ሀረጎች ተሰርዘዋል:: የአንቀጹ መግቢያም በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን "ሽብር" የሚለው ቃልም ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ስላልተገኘ ተሰርዟል:: በአጠቃላይ አንቀጹ ታርሞና ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል::

አንቀጽ ፩፻፶፱ <u>ተጨማሪ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፱ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ ድንጋጌ ስያሜ ውስጥ "ተደራራቢ ቅጣቶች" የሚለው ሐረግ "additional penalties" የሚለውን የእንግሊዝኛ ሐረግ ስለማይተካ "ተጨማሪ ቅጣቶች" በሚል እንዲተካ ሆኗል:: በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ "በዚህ አንቀጽ" የሚለው ቃል በጣም ሰፊና "title" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካ ስላልሆነና ሕጉ ሊሸፍነው ካሰበው በላይ የሚሄድ ስለሆነ "የተሾመ ወይም ተለውጦ ምዕራፍ" እንዲሆን ተደርጓል:: እንዲሁም በዚህ ቁጥር ውስጥ "የተሾመ ወይም የመሪነት ሥልጣን የተሰጠው ሆኖ ወንጀሉን የፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ---" የሚለው ሀረግ "ሹመት" ሹመትንና የአፍቅሮ ንዋይ ስሜትን አጣምሮ የሚያይ ስለሆነ ይህ መሆኑ ቀርቶ "ሹመት" እራሱን ችሎ የሚከብድ ሲሆን "የግል ጥቅም ማግኘት" ራሱን ችሎ የሚያከብድ ሆኖ በተናጠል እንዲቀረጽ ተደርጓል::

ንዑስ ቁጥር (፪) ተሰርዟል:: ምክንያቱም አንቀጽ ፪፻፫(፪) በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች የሲቪል መብቶችን መሻር ግዴታ ያደረገው በመሆኑ በድጋሚ መደንገጉ አስፈላጊ ባለመሆኑና የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ የአንቀጽ ፪፻፫ (፪)ን ድንጋጌ በሚቃረን መልክ የሲቪል መብቶችን መሻር ለፍርድ ቤቱ የተወው በመሆኑ ነው::

ንዑስ ቁጥር (፫) ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል፣ ንዑስ ቁጥር (፬) ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

አንቀጽ ፩፻፷ <u>ንብረትን መውረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፷ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜውና በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ከመደረጉም በላይ በፊደል (ሀ)፣ (ለ) እና በፊደል (ሐ) ተከፍሎ የነበረው ድንጋጌ በንዑሳን ፊደላት መከፈሉ ቀርቶ በአንድ ፓራግራፍ ተቀርጾአል:: ከዚህም ሌላ በቀድሞው ህግ መሠረት ንብረት ያስወርሳሉ በማለት ከተጠቀሱት አንቀጾች በተጨማሪ አንቀጽ ፩፻፴፰ (የቀድሞው ህግ ቁጥር ፩፻፶)፣ አንቀጽ ፩፻፵፩ (የቀድሞው ህግ ቁጥር ፩፻፶፫) እና አንቀጽ ፩፻፶፪ (የቀድሞው ህግ ቁጥር ፩፻፷፩) በዝርዝሩ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል:: ይህም የሆነው፣ በተጨማሪነት በተጠቀሱት አንቀጾች ላይ የተደነገጉት ወንጀሎች አገርን የሚጎዱና ከፍተኛ ቅጣት የሚያስፈርዱ በመሆናቸው ነው::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሁለት
## በውጭ አገር መንግሥት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

### ቀጽ ፪፻፷፩ በውጭ አገር መንግሥት ላይ የሚደረግ የተቃዋሚነት ድርጊት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜውና በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

በድንጋጌው ውስጥ "የሞከረ" የሚለው ቃል በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ውስጥ የተሸፈነ ስለሆነ ተሰርዟል፣ "በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት" "የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት" የሚሉት ሐረጎች ተሰርዘው "በኢትዮጵያ መንግሥት" "የኢትዮጵያ መንግሥት" በሚሉ ሐረጎች ተተክተዋል፤ "አፍራሽ በሆነ ንቅናቄ" የሚለውም ሀረግ "subversive acts" የሚለውን ሐረግ ስለማይተካ "በተንኮል ሥራ" ተብሎ ተተክቷል፤ በንዑስ ፊደል /ሐ/ "ውስጥ የሁከት ሥራ" የሚለውም "Hostile act" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ስለማይተካ "የጠላትነት ድርጊት" በሚል ተስተካክሏል።

### ቀጽ ፪፻፷፪ በውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች፣ መልእክተኞች እና በሌሎች በዓለም አቀፍ ህግ ጥበቃ ባገኙ ሰዎች ላይ የሚፈፀም ወንጀል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ ውስጥ የነበረ "አደጋ በመጣል" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል። ምክንያቱም የወንጀሉ ዓይነት በይዘቱ ውስጥ ስለሚገለጽ ነው። ከዚህም ሌላ ስያሜው የውጭ አገር መንግሥት መሪዎችን ብቻ ሳይሆን መልዕክተኞችንና በዓለም ዓቀፍ ህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውንም ሰዎች እንዲያካትት ተደርጓል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ የውጭ አገር ገዥዎችን፣ መሪዎችንና መልዕክተኞችን ብቻ ይመለከት ነበር። የዚህ ህግ የንዑስ አንቀጽ (፩) ግን የውጭ አገር መንግሥት ርዕሰ ብሔርን፣ መሪን፣ የውጭ አገር ሚኒስትርን፣ መልዕክተኛ ወይም ቤተሰቡን ወይም ተከታዩን ወይም በዓለም ዓቀፍ ድርጅት ተወካይ ወይም በዓለም ዓቀፍ ጥበቃ ያገኘ ሌላ ሰውን ያጠቃልላል። ዝርዝሩ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የተዘረዘሩት ሰዎች የሚሰሩባቸው ተቋሞች፣ የግል ቤቶች ወይም ተሽከርካሪዎች በዝርዝሩ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል። ይህ ንዑስ አንቀጽ በተጠቀሱት ሰዎች አካል፣ ነጻነት ወይም ደህንነት ጉዳት ያደረሰ ብቻ ሳይሆን በሚሰሩባቸው ተቋሞች ወይም በሚገለገሉባቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት ሲደርስ ጥፋተኛው በወንጀል እንዲቀጣ ያደርጋል። ከተጠቀሱት ድርጊቶች በተጫማሪ በሰዎቹ ላይ መዛት እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል። በቀድሞው የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ወንጀሉ ሲሞከር ያስቀጣል ተብሎ የነበረው ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ማናቸውም የወንጀል ሙከራ በአንቀጽ (፳፯) መሠረት የሚያስቀጣ በመሆኑና በህጉ ልዩ ክፍል ውስጥ በየአንቀጹ ላይ ስለወንጀል ሙከራ መደንገጉ አስፈላጊ ባለመሆኑ ነው።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ የራሱን ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን የዚህ ህግ ንዑስ አንቀጽ (፪) ግን "ወንጀሉ ሲፈጸም ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሰዎች የአንዱ ሕይወት አልፎ እንደሆነ ስለሰው መግደል የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።" በማለት ይደነግጋል። በቀድሞው ድንጋጌ መሠረት ከሃያ ዓመት ጽኑ

www.abyssinialaw.com

እስራት በላይ አይቀጣም ነበር፤ በዚህ ህግ ግን አድራጊው የሚቀጣው እንደአገዳደሉ ሁኔታ ነው፤ ቢያስፈልግም እስከ ዕድሜ ልክ እስራት ወይም ሞት ሊፈረድበት ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፷፫ <u>የውጭ አገር መንግሥትን ግዛት መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፫ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "የውጭ አገር መንግሥትን ግዛት ሙሉ ስልጣን ስለመጣስ።" የሚለው ከዚህ በላይ በተመለከተው አይነት ከይዘቱ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ተሻሽሏል።

በፊደል (ሀ) "የሰው ልጆችን ሕግ ወይም ያሉትን የስምምነት ውሎች ወይም ድንጋጌዎች ተቃራኒ በሆነ ልዩነት የውጭ አገር መንግሥት ግዛት በሆነ ውስጥ ወይም ሁከት የማነሣሣት ወይም አደገኛ የሆነ ተግባር ለመፈፀም ሲል "የሚለው ግልጽ ያልሆነና የተምታታ አገላለጽ በቀላሉ መረዳት እንዲቻል "የዓለም አቀፍ ሕግን፤ ወይም ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን ወይም ድንጋጌዎችን በመጣስ ሕገወጥ ድርጊት ለመፈፀም" በሚል አገላለጽ በፊደል (ሀ) እና (ለ) ለተገለጹት ሁኔታዎች በጋራ እንዲያገለግል የአንቀጹ መግቢያ ሆኖ ገብቷል። የነበረው የቅጣት ሁኔታ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፪፻፷፬ <u>የውጭ አገር መንግሥታትን ማዋረድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፬ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ንዑሳን አንቀጾች ሲኖሩ በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ "የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ግዛት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን" በሚል ሀረግ ተተክቷል፤ ይዘቱን በተመለከተ ሕጉ የሚሰጠው ጥበቃ በየት ቦታ እስካሉ ድረስ ነው የሚለው አሳብ ካከራከረ በኋላ መሪዎች በየትም ቦታ እስካሉ ድረስ ጥበቃ እንዲሰጣቸው፣ መልዕክተኞች ከሆኑ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉበት ጊዜ ብቻ እንዲሆን ተወስኖ በዚሁ መሰረት ድንጋጌው ግልጽና አጠር ያለ ተደርጎ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፪፻፷፭ <u>የታወቁ የውጭ አገር ምልክቶችን ማዋረድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፭ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ ድንጋጌ ስያሜ ውስጥ "ግልጽ የሆኑ ምልክቶች" ይል የነበረው ሐረግ ግልጽነት እንዲኖረው፣ "የታወቁ የሉአሳዊነት ምልክቶች" በሚል እንዲተካ ተደርጓል፣ ይዘቱን በተመለከተም እነዚህ ምልክቶች የሉዓሳዊነት መግለጫዎች ስለሆኑ ሕጉ ይህንን ቃል እንዲይዝ ተደርጓል። አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ በሚያደርግ ሁኔታ ተሻሽሎ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፪፻፷፮ <u>በመንግሥታት መካከል የተቋቋሙ ድርጅቶችን ማዋረድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፮ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ "የተቋቋሙትን ሥራዎች (ኢንስቲቱሽኖች)" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የተቋቋሙ ድርጅቶችን" በሚል ሀረግ ተተክቷል። ይዘቱን በተመለከተም

www.abyssinialaw.com


"ተካፋይ" የሚለው ቃል "አባል" በሚል ተተክቷል፤ እንዲሁም "ድርጅቶች" ብቻ ይል የነበረው "ተቋም ወይም ድርጅት" በሚል ተስተካክሏል። ምክንያቱም የእንግሊዝኛው ቅጅ ሁለቱንም ስለሚያመለክት ነው።

ቀጽ ፲፯ <u>የውለታ መመለስ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፯ ሆኖ ገብቷል።

የአንቀጹ አነጋገር ይበልጥ ግልጽ በሚያደርገው ሁኔታ ተረቅቋል።

ቀጽ ፲፰ <u>የክስ አቀራረብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፰ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞ ድንጋጌ ይዘት ውስጥ "በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አሳሳቢነት መንግሥት ሲወስን ክስ ይቀርባል" የሚለው አባባል ተሰርዞ በምትኩ "የፌዴራሉ የፍትህ ሚኒስትር ወይም ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ከመንግሥት ጋር ተመካክሮ ሲፈቀድ ብቻ ነው" በሚል ተተክቷል። ይህ የሆነበት ምክንያት አፈፃፀሙን አጭር ለማድረግና የክስ አቀራረቡም በመንግሥት ደረጃ መሆኑ ቀርቶ በፍትህ ሚኒስቴር ዳረጃ እንዲወሰን ለማድረግ ነው።

## <u>ርዕስ ሁለት</u>
## <u>ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

ቀደም ሲል "በሰው ልጆች መብት ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች" በሚል በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚመለከት የነበረ ሲሆን ስያሜው መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ይህው አገላለጽ ከእንግሊዘኛው ጋር እንዲጣጣም ተደርጓል።

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>
### <u>መሠረታዊያን ወንጀሎች፤ በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>.

በዚህ ምዕራፍ ሥር የሚገኙ ድንጋጌዎችን ለማሻሻልና አንቀጾቹን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ እንዲያስችል ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች፤ የጄኒቫ ኮንቬንሽኖችና የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ሰነዶች በንጽጽር ታይተው አዳዲስ ሃሣቦች በወንጀል ሕጉ እንዲካተቱ ተደርጓል።

ቀጽ ፪፻፷፱ <u>ዘርን ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፱ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜውን በሚመለከት ቀደምሲል "ዘርን ስለማጥፋት፣ በሰብአዊነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች" (crimes against humanity) ይል የነበረ ሲሆን "በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ

www.abyssinialaw.com

ወንጀሎች" የሚለው ሐረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምክንያቱም "ዘር ማጥፋት" በሰብአዊነት ላይ ከሚፈፀሙት ወንጀሎች አንዱ በመሆኑና ከአንቀጽ ፪፻፭ ጀምሮ ያሉት ተከታታይ አንቀጾች በሰብአዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ስለሆነ ነው::

በአንቀፁ መግቢያ ላይ በዘር ማጥፋት ወንጀል ዙሪያ ከተካተቱት መሠረታውያን ሀሳቦች በተጨማሪ ዜግነትና ቀለም በስዕብና ላይ የሚያተኩሩ ጉዳዮች ሆነው በመገኘታቸው በሕጉ ውስጥ እንዲዋሃዱ ተደርገው ተረቅቋል::

በንዑስ ፊደል (ሀ) ላይ በሰላምም ይሁን በጦርነት ጊዜ፣ ሰዎች ይሙቱ ይኑሩ ሳይታወቅ ጠፍተው የሚቀሩበት ሁኔታ በመኖሩ እንዲጠፉ ያደረጓቸው ባለሥልጣኖች ወይም ሌሎች ሰዎች ሰውን በማጥፋት ወንጀል ሊጠየቁ ስለሚገባ ይህን አሳብ እንዲያካትት ተደርጓል::

በፊደል (ሐ) ላይ "የማህበረሰቡ አባላት" የሚለው ሐረግ ህፃናትንም ስለሚጨምር "ህፃናት" የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጓል::

ቅጣቱን በሚመለከት በድንጋጌው ላይ "ከአስር ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በሞት ይቀጣል" የሚል ሲሆን "የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት" መወሰን የሚኖርበት ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ነው ተብሎ በመታመኑ በዚህ መልኩ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፪፻፮ <u>በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የሚፈፀም የጦርነት ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ቀ) ባሉት ድንጋጌዎች ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ተረቅቋል::

ከዚህም በተጨማሪ ከፊደል (በ) እስከ (ከ) ድረስ አዲስ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን እነዚህም ከዓለምአቀፍ ሕግ የተወሰዱ ናቸው:: በተጨማሪም እንዲካተቱ የተደረጉት ድንጋጌዎች፤

1ኛ/ የጄኔቫ ኮንቬንሽንን (ፕሮቶኮል አንድ) Protocols Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and relating to the protection of victims of International Armed Conflicts of 8 June 1977. Article 53-56; 69; 73; 75 and 77.

2ኛ/ የጄኔቫ ኮንቬንሽንን (ፕሮቶኮል ሁለት) Protocols Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949 and relating to the protection of victims Non-International Armed Conflicts of 8 June 1977. Article 283 ይገኙባቸዋል::

በዚህ መሠረት በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ በውጭው ዓለምም ሆነ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር አስፈላጊና ሊከሰቱ የሚችሉ ሕገወጥ ድርጊቶች በመኖራቸው እንደ ምግብ፣ እርሻ ቦታ፣ የጤና ተቋማት ወይም ትምህርት ቤቶች ላይ ጉዳት ማድረስ፣ ለወታደራዊ ጥቅም ከሚያስፈልገው በላይ በዘፈቀደ /አላግባብ የግብር ክፍያ እንዲከፈል ማድረግ፣ አንደኛው ወገን በተቆጣጠረው ሥፍራ ላይ ለሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አለማቅረብ፣ እንደስደተኛ

www.abyssinialaw.com

ወይም ዜግነት እንደሌላቸው የሚታወቁ ሰዎችን ማጥፋት ወይም ማፈናቀል፣ ዕድሜያቸው ከአሥራ አምስት ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን በጦርነት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ በተፈጥሮ አካባቢ ሊስፋፋ የሚችልና ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ከባድ ጉዳትም ሊያደርስ የሚችል መሣሪያ /የውጊያ ስልት መጠቀም፣ ለፍርድ ሂደት ዋስትና ከሚሰጡ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጪ ቅጣት መወሰን ወይም በሰላማዊ ነዋሪ ላይ አደጋ ሊያደርስ በሚችል ሁኔታ ግድቦችን ሆነ' ኒውክሊየርና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችን ማጥቃት እንደ ከባድ ወንጀሎች ተቆጥረው በአንቀፁ ሥር ተካተተዋል::

ቀጽ ፪፻፹፮ <u>በቁስለኞች፣ በበሽተኞች፣ በስጥመት አደጋ ላይ ባሉ ሰዎች ወይም በጤና አገልግሎት ላይ የሚፈጽም የጦርነት ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፸፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፮ ሆኖ ገብቷል::

ይዘቱን በሚመለከት በሁለት ፊደሎች ተከፍሎ የነበረው ድንጋጌ አዲስ አሳብ ተጨምሮበት በሦስት ፊደሎች ተከፍሎ በንዑስ አንቀጽ አንድ ስር እንዲመጣ ሲደረግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ታክሎበታል በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ላይ "የስጥመት አደጋ የደረሰባቸውን" የሚለው ተሰርዞ "በባህር ወይም በአየር አደጋ ላይ ባሉ" በሚለው ሀረግ ተተክቷል:: በፊደል (ሐ) ስር የጤና አገልግሎት ሠራተኞች፣ የሃይማኖት አገልግሎት ሰጪዎችና ጋዜጠኞች የሙያ ስነምግባር ከሚያዘው ውጭ እንዲሰሩ ወይም ቁስለኞችን አሊያም ሰላማዊ ሰዎችን ለመጠበቅ የወጡ መመሪያና ደንቦችን ተላልፈው እንዲሰሩ ማስገደድ ተጠያቂ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ በወንጀል ሕጉ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ "ቁስለኛ እና ሕመምተኛ" እንዲሁም "በባህር ወይም በአየር አደጋ ላይ ያለ" ለሚሉት ቃላትና ሀረጎች ትርጉም ተሰጥቷቸዋል::

ቀጽ ፪፻፹፯ <u>በታሰሩ የጦር ምርኩኞች እና በተጋዙ ሰዎች ላይ የሚፈፀሙ የጦርነት ወንጀሎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፯ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "በታሠሩና በተጋዙ የጦር ምርኮኞች" የሚለው ሐረግ ተሻሽሎ ይዘቱን ሊያንፀባርቅ በሚችል ሁኔታ ተለውጧል:: በተራ ፊደል (ሀ) ይዘት "ከሰብአዊ ፍጥረት ውጭ የሆነ የሥቃይ ሥራ እንዲፈፀምባቸው ወይም ከባድ የሆነ ሥቃይና ጉዳት እንዲደርስባቸው" በሚለው ሐረግ ምትክ "ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ የሆነ የማጉላላት በደል እንዲፈፀምባቸው" በሚል አጭር ሐረግ ተተከተዋል::

ቀጽ ፪፻፹፰ <u>በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ገፈፋ፣ ዘረፋና የባህር ውንብድና</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፸፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፰ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ስያሜ ላይ "የዘረፋ የየብስና የባህር ወንበዴነት" በሚለው ሐረግ ምትክ "ገፈፋ፣ ዘረፋና የባህር ውንብድና" በሚለው ተተክቶአል:: በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ "የየብስና የባህር ወንበዴነትን" የሚለው ሐረግ ወንጀሉ የየብስና የባህር ወንበዴነትን በአንድነት በማጣመር የሚፈጸም ስለሚያስመስለው "ና" የሚለው መስተጻምር ተሰርዞ "ወይም" የሚለው ቃል ተጨምሮ የተወሰነ ለውጥ በማድረግ "የባህር ወንበዴነትን፣ የዘረፋን፣ የገፋፊነትን ወይም ሕገወጥ የሆነ የንብረት ማፍረስን ወይም የመውሰድን"

www.abyssinialaw.com

በሚሉ ሀረጎች ተተክተዋል፡፡ ከዚህ በቀር ድንጋጌው ግልፅ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፪፻፸፬ <u>መገፋፋትና ማሰናዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፪፻፹፮ መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ "ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ከተመለከቱት ተግባሮች" በሚለው ምትክ "ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች ከተመለከቱት ወንጀሎች" በሚል አገላለጽ ተተክቶአል፡፡ በፊደል "ሀ" "ያነሳሳ" ከሚለው ቃል በኋላ "ያደፋፈረ" የሚለው ቃል በአማራጭ ወይም በአንድነት የሚቆሙ መሆናቸው ስለሚያሳይ ወይም የሚለው ቃል በአማራጭነት እንዲያገለግሉ ስለሚያደርግ ተጨምሮአል፡፡ በፊደል ተራ (ለ)ም "የወንበዴ ክፍል ወይም አንድ ጓድ እንዲቋቋም ያነሳሳ ወይም ከነዚህ ጋር የተስማማ ያደመ በማኅበሩ ውስጥ የገባ ወይም የሥራ ተካፋይ የሆነ ወይም በሥራው አመራር ተደራቢ የሆነ" የሚለው አገላለጽ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ በተራ ፊደል (ለ) ውስጥ "የወንበዴ ማህበር ወይም ቡድን እንዲቋቋም ከሌሎች ጋር ያደመ፣ ዕቅድ ያወጣ፣ ወይም እንዲቋቋም የገፋፋ ወይም ራሱ ያቋቋመ፣ በዚህ ማህበር ወይም ቡድን ውስጥ የገባ፣ ዓላማውን የተከተለ ወይም ትዕዛዙን የፈጸመ" በሚለው አገላለጽ ተተክቶአል፡፡ በንዑስ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትም የወንጀል ድርጊቶች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ ስለሆነ ከንዑስ ፊደል (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም የሚል ቃል ገብቶአል፡፡ ከዚህም በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፪፻፸፭ <u>ሊወሰድ የሚገባውን ተግባር መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ውስጥ "ደንብ" የሚለው ቃል ብቻውን ምን ዓይነት ደንብ መሆኑን ስለማይገልጽ "ዓለማቀፍ ሕጎችን እና የሰብዕና አጠባበቅ ስምምነቶችን" የሚሉ ቅጽል ሀረጎች ከፊቱ ገብቶአል፡፡ ከንዑስ ፊደል (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱት ወንጀሎች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በንዑስ ፊደል (ሐ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል፡፡ በፊደል ተራ (ሐ) ውስጥ ብርበራ ወይም የሃይል ተግባር የመፈጸም ድርጊትም ሊያስቀጣ እንዲችል ተደርጎ ተካቷል፡፡ በፊደል ተራ (መ) የተመለከተው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ቅጣቱን በሚመለከት "የጽኑ እስራት ቅጣት ይደርስበታል፤ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ከፍ ያለ እንደሆነ በሞት ፍርድ ይቀጣል" ይል የነበረው ተሻሽሎ፣ "በጽኑ እስራት ወይም ወንጀሉ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል" እንዲል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፪፻፸፮ <u>ሕገወጥ በሆኑ የጦር መሣሪያዎች መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

በቀድሞ ሲያሜ ውስጥ በመታገዝ የሚለው ቃል ግልጽ ስላልሆነ ተሰርዞ "መገልገል" በሚል ቃል ተተክቶአል፡፡ ይዘቱን በሚመለከት "በታወቁት በኢንተርናሲዮናል

www.abyssinialaw.com



ስምምነቶች" የሚለው ሐረግ ኢትዮጵያ እንድታስከብር የምትገደደው ማናቸውንም ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ሳይሆን ፈቅዳ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ብቻ ስለሆነ ይህንኑ ለማመልከት "በታወቁት በኢንተርናሲዮናል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፋዊ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ከዚህ ማሻሻያ በቀር አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፪፻፸፯ <u>የጦር ማቆም ውልን ወይም የሰላም ስምምነትን ማፍረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፯ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፪፻፸፰ <u>ፋኖ በመሆን በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፰ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ፋኖ አለቃ በመሆን" የሚለው ሀረግ "ፋኖ" በሚለው ቃል ተተክቶአል። የፋኖ አለቃ በመሆን የሚለው ለአለቆች ብቻ የተደነገገ መሆኑን ማመልከቱ ከይዘቱ ጋር የሚሄድ አይደለም። "ንጉሠ ነገሥቱ" የሚለው ሐረግም ተሰርዞ "በኢትዮጵያ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። "የጦር ሠራዊትነቱ ወይም /የተጨማሪ/ የተደራራቢ ጦር ባልደረባነቱ ሳይታወቅለት" በሚለው ሀረግ ምትክ "የታወቀ የመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም የድጋፍ ሰጪ ኃይል አባል ሳይሆን" በሚሉ ሀረጎች እንዲተኩ በማድረግ የበለጠ ግልጽ አቀራረብ እንዲኖረው ተደርጓል። ከዚህም በላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ነንቀጽ ፪፻፸፱ <u>በቁስለኞች፣ በበሽተኞችና በእሥረኞች ላይ መጨከን ወይም የሚገባቸውን ማጓደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፱ ሆኖ ገብቷል።

ብቀድሞ ድንጋጌ ይዘት ላይ "የሰው ልጆችን መብት ሥርዓት" በሚለው ሐረግ ምትክ "ዓለም አቀፍ ሕግጋትን" በሚለው ተተክቶአል። በተጨማሪም ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፪፻፹ <u>ፍትህን መከልከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ላይ "የጦር ምርኮኛ የሆነ ግዞተኛ ትክክል የሆነ የዳኝነት ሥርዓትንና ሚዛናዊ ፍርድን እንዲያገኝ የሚያስችለውንና በሰብአዊ አስተዳደር እንዲኖር የሚያደርገውን የራሱን የመከላከያ መብት የሚያሳጣውን ተግባር በመፈጸም ፍርድ እንዲያጣ" የሚለው አገላለጽ ተሻሽሎ "የጦር ግዞተኛ ስብዕናውን የሚያረጋግጥለትን በሕግ መሰረት የመዳኘት መብቱን እንዲሁም በነፃነት ራሱን የመከላከል መብቱን እንዲያጣ" በሚለው አገላለጽ ተተክቶአል። ቀላል እሥራት በዚህ የወንጀል ሕግ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቀላል እሥራቱ የሚደርሰው

www.abyssinialaw.com

እስከ ሦስት ዓመት ብቻ ነው:: ሆኖም በዚህ የወንጀል ሕግ ከሦስት ዓመት ቀላል እሥራት በላይ ጥፋተኛውን የመቅጣት አስፈላጊነት ስለሚታይ "በእሥራት ይቀጣል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ቀላል እሥራት ይቀጣል::" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በሰብአዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች</u>

በምዕራፉ ስያሜ ውስጥ "በበጐ አድራጎት ማህበር" በሚለው ሐረግ ምትክ "በሰብአዊ ድርጅቶች" የሚለው ሐረግ የበለጠ ተስማሚ በመሆኑ እንዲተካ ተደርጓል::

አንቀጽ ፪፻፹፩ <u>በአለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈፀም የጠላትነት ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

በቁጥር ፪፻፺፫ ስያሜ ላይ "በኢንተርናሲዮናል የበጎ አድራጎት ሰብአዊ ማህበሮች" የሚለው ተለውጦ "በዓለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅች" በሚል ተተክቷል:: "ተቃዋሚ ሥራ" በሚለው ምትክ "የጠላትነት ድርጊት" በሚለው ተተክቷል:: የድንጋጌውን አቀራረጽ በሚመለከት የቀድሞው ህግ የቁጥር ፪፻፺፫ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥሮች ሳያኖሩት በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተከፈለ ሲሆን፣ ይህ አንቀጽ ግን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲኖረው ተደርጓል:: በቀድሞው ድንጋጌ በፊደል (ለ) ላይ የተመለከተው ድርጊት በጦርነት ጊዜ የተፈጸመ መሆኑን ሲገልጽ፣ በፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ወንጀል ግን በሰላም ጊዜ የተደረገ መሆን አለመሆኑ በግልጽ አልተቀመጠም:: ሆኖም በሰላምና በጦርነት ጊዜ የተፈጸሙ ድርጊቶች ተመሳሳይ ቅጣት እንዲወሰንባቸው መደንገጉ ትክክል አይደለም::

ስለዚህ በቀድሞው ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት ድርጊቶች በሰላም ጊዜ ሲደረጉ በቀላል እስራት ብቻ ማስቀጣታቸው ቀርቶ፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር በቀላል እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እ ንዲያስቀጡ ተደርጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ድርጊቶች በጦርነት ጊዜ ሲፈጸሙ፣ በአዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጡ ተደርጓል::

አንቀጽ ፪፻፹፪ በዓለም <u>ዓቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች አርማዎችና መለያ ምልክቶች ያለአግባብ</u>
<u>መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፪ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "በኢንተርናሲዮናል" በሚለው ሀረግ ምትክ "በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶች" የሚለው የበለጠ ገላጭነት ስለሚኖረው እንዲገባ ተደርጎአል:: ይዘቱም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ቅጣቱም በቀላል እሥራት ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ እንዲሆን ተደርጎ ተሻሽሏል::

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፪፻፹፫ በዕርቅ መልዕክተኛ ላይ የጠላትነት ድርጊት መፈጸም[*]

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ተቃዋሚ ድርጊት" በሚለው ሐረግ ምትክ "የጠላትነት ድርጊት" በሚል ተተክቶአል:: ይዘቱን በተመለከተ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቶ አንቀጹ ተረቅቋል:: ቅጣቱም ቀላል እስራት እንደሚሆን በግልጽ ተቀምጧል::

## ርዕስ ሦስት
## ወታደራዊ ወንጀሎች እና በመከላከያ ሠራዊት እንዲሁም በፖሊስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

ወታደራዊ ወንጀሎችና በመከላከያ ሠራዊት እንዲሁም በፖሊስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚመለከት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት፣ የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር ፳፯/፹፰፣ የፖሊስ አደረጃጀት አዋጅ ቁጥር ፪፻፯/፺፪ እና የውጭ አገር የወንጀል ሕጎች ተገናዝበዋል::

## ምዕራፍ አንድ
## ወታደራዊ ወንጀሎች
## ክፍል አንድ
## የአገልግሎት ግዴታን በመጣስ የሚደረጉ ወንጀሎች

ቀጽ ፪፻፹፬ ወታደራዊ አገልግሎትን እንቢ ማለት

ያቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፬ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ስያሜ ከይዘቱ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተቀርጿል:: ይዘቱም አንዳንድ የቃላት ማሻሻያ ተደርጎበታል:: በተለይም ለውትድርና እንዲመለመል የሚጠራበት የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች "በግል ወይም በአደባባይ በተለጠፈ ማስታወቂያ ወይም በመገናኛ ብዙሃን በተነገረ ማስታወቂያ----" በሚል በተሻሻለ ሁኔታ አቀራረቡ ተቃንቶ እንዲገባ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻ ላይ "---በአዋጅ የተገለፀውን---" የሚለው ሐረግ ጥሪን ማስተላለፊያ መንገድ ነው ብሎ ለማለት ስለማይቻል በሳይኖቹ አባባሎች ተለውጧል:: ቅጣትን በሚመለከት ቀደም ሲል በነበረው ዓይነት ቢሆንም ለንዑስ አንቀጽ (፩) የሚጣለው ቅጣት ቀላል እስራት እንደሚሆን በግልጽ ተቀምጠዋል::

ቀጽ ፪፻፹፭ የጥሪ ትዕዛዝን አለማክበር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፭ ሆኖ ገብቷል::

ለዚህ አንቀጽ የተሰጠው ስያሜ ከይዘቱ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተስተካክሎ ተጽፏል::

---

[*]ወንጀል ሕጉ አንቀጽ 283 በስያሜው ላይ "ዕርቅ" የሚለው ቃል "በዕርቅ" ተብሎ ይነበብ::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ መጠነኛ የቃላት ማሻሻያ ተደርጐበታል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የጥሪ ትዕዛዝ አለማክበር ጉዳይ በጦርነት ጊዜ ብቻ ባለመሆኑና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅም አስፈላጊነት ስለሚኖረው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፺፫ (፩) (ሀ) ላይ ያለው አነጋገር እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በድንጋጌው ላይ በጠቅላላ የቃላት ለውጥ ተደርጐበት ተረቅቋል::

የአገር አንድነትንና ነፃነትን ለመጠበቅና ለማጠናከር ጥሪ ተደርጎላቸው ባልተገኙት በእንቢተኞች ላይ እርምጃ መውሰዱ አስፈላጊ በመሆኑ የንዑስ ቁጥር (፩) ቅጣቱ አነስተኛ መሆኑ ስለታመነበት ".... እስከ ስድስት ወር ....." የሚለው ቅጣት ቀርቶ "..... እስከ አንድ ዓመት ቀላል እስራት..." እንዲሆን ቅጣቱ ተሻሽሎ እንዲገባ ተደርጓል::

አንቀጽ ፪፻፹፮ ከአገልግሎት ግዴታ ለማምለጥ ታስቦ የሚደረግ የችሎታ ማጣት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፮ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀፁ ስያሜ ከይዘቱ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተስተካክሏል:: ይዘቱን በተመለከተ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያዎች ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ ይኸው ተደርጓል::

አንቀጽ ፪፻፹፯ ከወታደራዊ አገልግሎት ለማምለጥ የሚፈፀም ማጭበርበር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፯ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ይዘት ቀደም ሲል ከነበረው መንፈስ ጋር እንዲሄድ እንዲሁም አንዳንድ መጠነኛ የቃላት መልዕክቱን ግልጽ ለማድረግ ሲባል ብቻ እንዲስተካከሉና እንዲለወጡ ተደርጓል:: የንዑስ ቁጥር (፩) ቅጣት ወንጀለኛው ካደረገው የማጭበርበርና ማታለል ድርጊቶች ጋር የተመጣጠነ ሆኖ ባለመገኘቱ ቅጣቱ ከሦስት ዓመት ባላነሰ ቀላል እሥራት በሚል ከፍ እንዲል ተደርጎ ተሻሽሏል:: ሆኖም አገላለጹ ስህተት ነው:: ለተወካዮች ምክር ቤት በቀረቡት ሁለት የወንጀል ህግ ረቂቆች መሠረት ቀላል እስራት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቢሆንም፣ በመጨረሻ የተወሰነው የቀላል እስራት ጣራ ሶስት ዓመት እንዲሆን ነው:: የንዑስ አንቀጽ (፩) ቅጣት ከሶስት ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እንዲሆን ነው:: የንዑስ አንቀጽ (፩) ቅጣት ከሶስት ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እንደ በዚህ ህግ ትርጉም የሚኖረው በቀድሞዎቹ ሁለት የህግ ረቂቆች መሠረት እንጂ በዚህ ህግ መሠረት ትርጉም የለሽ ነው:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥፋተኛ የሆነው ሰው ምንግዜም የሚቀጣው ሶስት ዓመት ቀላል እስራት ብቻ ነው፤ ከሶስት ዓመት በላይ ፈጽሞ ሊቀጣ አይቻልም:: የድንጋጌው ቀጣት "ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት ይቀጣል::" በማለት ሊቀረጽ ይገባው ነበር::

አንቀጽ ፪፻፹፰ ኩብለሳ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፰ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጹ ስያሜ "ስለ መክዳት" የሚለው ከይዘቱ ጋር በሚስማማ መልኩ "ኩብለሳ" ተብሏል::

www.abyssinialaw.com

በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ለውጦች ከመደረጋቸውም በላይ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ወደ አገልግሎት ተግባሩ ያልተመለሰም" ወደ ክፍሉ እንዳልተመለሰ የሠራዊት አባል ተመሣሣይ ቅጣት የሚጣልበት ሁኔታም ተጨምሮበታል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) ይዘት ላይ መጠነኛ ማሻሻል ከመደረጉ ውጭ መሠረታዊ ለውጥ አልተደረገበትም::

ቅጣትን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) "እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት" የሚለው የጸና ሲሆን፣ የንዑስ ቁጥር (፪) ቅጣት "መነሻ አምስት ዓመት ሆኖ እስኪ ዕድሜ ልክ ለመድረስ ይችላል ወይም ከባድ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ በሞት ፍርድ ይቀጣል::" የሚለው ተሻሽሎ ፣ "ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ያስቀጣል::" እንዲል ተደርጓል::

ቀጽ ፪፻፹፱ <u>ያለአግባብ መቅረት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፹፱ ሆኖ ገብቷል::

የዚህን አንቀጽ ይዘት በተመለከተ መልዕክቱን ግልጽ ለማድረግ ሲባል የቃላትና የአባባል ማስተካከያዎች ተደርገውበታል:: ቅጣትን በተመለከተ ወታደራዊ ዲስፒሊን ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) እና (ለ) ላይ ለተጠቀሱት ወንጀሎች ቅጣታቸው በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ እስከ ስድስት ወር... የሚለው ቅጣት "እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት..."እንዲሆን ሲደረግ፤ ንዑስ ቁጥር (፪) ደግሞ እስከ ሁለት ዓመት ያስቀጣ የነበረው ተሻሽሎ "እስከ ሶስት አመት ቀላል እስራት" እንዲያስቀጣ ተደርጓል::

ቀጽ ፪፻፺ <u>አስበ ወደ ጦር ክፍሉ ተመልሶ አለመምጣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺ ሆኖ ገብቷል::

ቀደም ሲል የነበረው ስያሜ " ሆን ብሎ ወደ ጦር ክፍሉ ተመልሶ ስላለመምጣት" የሚለው ተቃንቶ "አስበ ወደ ጦር ክፍሉ ተመልሶ አለመምጣት" እንዲል ሆኗል:: በይዘቱ ላይ መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጓል::

የእሥራት ቅጣቱ ቀላል እሥራት እንደሚሆን በግልጽ ከመቀመጡ በቀር የተደረገ ሌላ ለውጥ የለም::

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>በወታደራዊ ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል</u>

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የክፍል ሁለት ስያሜ "የአገልግሎት ሥልጣን ከመጠን ስለማሳለፍ"የሚል ነበር:: ዳሩ ግን በዚህ ክፍል ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና ከሕጉም የፈረንሣይኛ ቅጂ ለመረዳት እንደሚቻለው ስያሜው መሆን የሚገባው "በወታደራዊ ሥልጣን ያለአግባብ መገልገል" ነው:: ስለዚህ የቀድሞው የክፍል ሁለት ስያሜ ተሰርዞ ከላይ ባለው ሁኔታ ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፪፻፺፩ <u>ከአገልግሎት ግዴታ ያለአግባብ ነፃ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፩ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ አንቀጽ ስያሜ የነበረው "በማይገባ ከሥራ እንዲቀር ስለመፍቀድ" የሚል ነበር። ዳሩ ግን ከሥራ መቅረት ሲባል ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀር ለማድረግ ስለሚመስልና በሌላም በኩል ከድንጋጌው ይዘትና ከሕጉ የፈረንሣይኛ ቅጂ ለመረዳት እንደሚቻለው በዚህ ቁጥር የተደነገገው ከአገልግሎት ግዴታ በማይገባ ነፃ በማድርግ ስለሚሠራ ወንጀል ስለሆነ ስያሜው ተሠርዞ "ከአገልግሎት ግዴታ ያለአግባብ ነፃ ማድረግ" በሚል በአዲስ ስያሜ ተተክቷል። በንዑስ ቁጥር (፩) "የሥራ አገልግሎት ወይም የተሰጠውን መብት" የሚለው ሐረግ ግልጽ ስላልሆነ ተሠርዞ "የተሰጠውን የሥራ ወይም ወታደራዊ ሥልጣኑ" በሚል ሐረግ ተተክቷል። ወታደራዊ አገልግሎት እንዲፈጽም ግዴታ ያለበትን ሰው ከግዴታው ነፃ ለማድረግ የሚቻለው ወታደራዊ ሥልጣኑን ከመጠን በላይ በማሳለፍ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ወታደራዊ ሥልጣን አላግባብ በመገልገልም ሊሆን ስለሚችል " ከመጠን በላይ በማሳለፍ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ወይም በዚሁ ሥልጣኑ ያለአግባብ በመገልገል" የሚል ሐረግ ተተክቷል። "በሕግ አግባብ ያገልግሎቱን" በሚለው ሐረግም "በሕግ አግባብ" የሚለው ሐረግ አገልግሎት በሕግ አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ አስፈላጊ ስላልሆነ ተሠርዟል። በተጨማሪም ቅጣትን በተመለከተ በቂና ተመጣጣኝ ስላልነበረ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስድስት ወር እንዳለ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ አምስት ዓመት የነበረው እስከ አሥር ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ሲደረግ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በማድረግ አንቀጹ እንዲሻሻል ተደርጓል።

<u>የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፫፻፬ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰው ድንጋጌ ወደ ደንብ መተላለፍ ሕግ የሚያመለክት በመሆኑና የአንቀጽ ፫፻፵፩ ድንጋጌም ተመሳሳይ አሳብ የያዘ በመሆኑ የቁጥር ፫፻፬ ድንጋጌ ተሰርዟል።

አንቀጽ ፪፻፺፪ <u>በበታች ላይ የሚፈጸም ዛቻና የኃይል ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፪ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ በተመለከተ "የእጅ እልፊት" የሚለው አባባል ተሻሽሎ ግልፅ በሆነ ሁኔታ እንዲገባ ለማድረግ "የኃይል ድርጊት" በሚለው ተስተካክሎ ሌላው እንዳለ እንዲቀመጥ ተደርጓል። በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "ማሰቃየት የሚለው ቃል በጣም ከባድ ሁኔታን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ከድንጋጌው ይዘት ጋር የማይመጣጠን ስለሆነ ወጥቷል። ሆኖም "ማሰቃየት" የሚለው ቃል ወደ ጭካኔ ስለሚቃረብና "የሀይል ድርጊት" በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለጹት ድርጊቶች ከበድ ስለሚል "በጭካኔ ወይም በሀይል ተግባር" የሚል ሀረግ በንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲገባ ተደርጓል። የተመደበው አነስተኛ ቅጣት የስድስት ወር ቀላል እሥራት ስለሆነና እንደአስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ቅጣትም ለመቅጣት እንዲቻል የታችኛውን ቅጣት ለቀቅ አድርጎ የላይኛውን ቅጣት መገደቡ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ "እጅግ ቢያንስ በስድስት ወር" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ አንድ ዓመት ሊመድረስ በሚችል" በሚለው ሐረግ ተተክቷል። በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ "ወንጀሉ የተፈጸመው" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "በጭካኔ ወይም በኃይል ተግባር" የሚል እንዲገባ ተደርጓል። በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድርጊት "በጦር መሣሪያ ወይም በሌላ

www.abyssinialaw.com

መሣሪያ" አማካይነት የኃይል ድርጊት ወይም ... እንዲካተቱ ተደርጓል:: የንዑስ አንቀጽ ሁለት ቅጣት ግን ... ሐረጎች እንዲካተቱ ተደርጓል:: ... አልተለወጠም::

## ክፍል ሦስት
## ወታደራዊ የአገልግሎት ተግባሮችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

የዚህ ክፍል ስያሜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ "ባገልግሎት ተግባሮች ላይ ስለሚሠራ ወንጀል" በሚለው ምትክ የገባ ነው::

## ንዑስ ክፍል አንድ
## መልካም ሥርዓቶችንና ዲስፕሊንን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

የንዑስ ክፍሉ ስያሜ ቀጥሎ ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ሲባል "ደንብንና ሥነ-ሥርዓትን በመጣስ ስለሚሠሩ ወንጀሎች" በሚለው ምትክ እንዲገባ ተደርጓል::

### ፬፻፺፫ ጠቅላላ የአገልግሎት ደንቦችን መጣስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፫ ሆኖ ገብቷል:: ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ለውጥና የአሳብ መቃናት ተደርጎበት አንቀጹ ተረቅቋል::

### ፬፻፺፬ የልተሟላ ወይም ትክክል ያልሆነ መረጃን መስጠት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፬ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ስያሜ "ሊሠራ አገልግሎት ጉዳይ በሚሰጥ መረጃ ላይ አውቆ በማስቀረትና ያልተሟላ መረጃ ስለ መስጠት" የሚለው ተሰርዞ በምትኩ ግልጽና አጠር ያለ እንዲሆን ከላይ ባለው ሁኔታ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ሦስት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩት ሲሆን ይህ አንቀጽ ግን አራት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል:: ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲፈጸም የሚያስቀጣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ሲቀረጽ የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፪) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) ደግሞ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ ንዑሳን ክፍሎች ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል:: ቅጣትን በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፬) (ሀ) ላይ አዲስ ቅጣት ለብቻው የገባ ሲሆን ይህም "ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት" እንዲሆን ተደርጓል:: መነሻ ቅጣቱ ከፍ ያለበት ምክንያት በፊደል (ለ) ከተመለከተው ድርጊት ይልቅ በፊደል (ሀ) ላይ ያለው የወንጀል አፈጻጸም ከበድ ያለ በመሆኑ ነው::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፪፻፺፮ ሰክሮ መገኘት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፮ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም " የሚል ቃል እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ ላይ የነበረው "ወይም" ተሰርዟል። የሌሎች ቃላት ማስተካከያም በአንቀጹ ላይ ተደርጓል።

አንቀጽ ፪፻፺፯ ከሥነ-ሥርዓት /ዲስፕሊን/ ውጭ መሆን

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ላይ የቃላት ለውጥ ተደርጓል።

ቅጣትን በተመለከተ እንደዚህ ያለውን ሥርዓት የለሽነት ከመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ለማስወገድና በመከላከያ ሠራዊት መካከል መተሳሰብንና ዲስፕሊን ለማስፈን ሲባል ቅጣቱን ማክበዱ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ "እስከ አንድ ዓመት..." የሚለው የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቅጣት " እስከ ሦስት ዓመት... ቀላል እሥራት" ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፪፻፺፰ በበላይ አለቃ ወይም በማዕረግ እኩያ በሆነ አባል ላይ የሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻና የእጅ እልፊት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፰ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "በበላይ አለቃ ላይ ስለሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻና የእጅ እልፊት" የሚል ነበር። ይህ አባባል ተሻሽሎ "በበላይ አለቃ ወይም በማዕረግ እኩያ በሆነ አባል ላይ የሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻና የእጅ እልፊት" በሚል ተስተካክሏል።

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ስድብ ወይም ዛቻው ወይም የእጅ እልፊቱ በአንድ የበላይ አለቃው ላይ ብቻ ሳይሆን በማዕረግ እኩያው በሆነውም አባል ላይ ሊደረግ ስለሚችል በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት "የሀይል ተግባር" የሚል ሀረግ ተጨምሯል። ምክንያቱም ንዑስ አንቀጽ አንድ ያካተተው የእጅ እልፊትን ብቻ ስለሆነ ነው።

ድንጋጌው ይበልጥ ዲስፕሊን ለማስከበር ስለሚያስፈልግ በዚሁ መልኩ የተረቀቀ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፪፻፺፱ ለበላይ አለመታዘዝ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ለውጥና ማስተካከያ ተደርጎበታል። ቀደም ሲል በሁለት ፓራግራፎች ተከፍሎ የነበረው የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ የራሱን ቅጣት ስለሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

የወንጀሉም አፈጻጸም ከባድ በመሆኑ የንዑስ አንቀጽ (፩) ቅጣት እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ የንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ የንዑስ አንቀጽ (፫) ቅጣት ደግሞ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም ሞት እንዲሆን ተደርጓል::

ቀጽ ፪፻፺፱ ወታደራዊ አመጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "አድማ" ይል ነበር:: ሆኖም ድርጊቱ የኃይል ተግባር የተቀላቀለበትና አለመታዘዝ የሚታይበት ሁኔታ ስላለ በእንግሊዘኛው ቅጂ መሠረት "ወታደራዊ አመጽ" በሚል ስያሜ እንዲሻሻል ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "በመሰብሰብ" የሚለው ሐረግ ስብሰባው ሕጋዊ መሆንና አለመሆኑን ስለማያመለክት ይህ ሐረግ ተሻሽሎ "ሕጋዊ ባልሆነ ስብሰባ በመካፈል..." በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፪) ሥር ቅጣቱ እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ፣ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ሞት ይሆናል የሚል ሲሆን ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም የሞት ቅጣት ይሆናል በሚል ተስተካክሏል::

በንዑስ ቁጥር (፫) የአመጹ መሪዎች ወይም አደራጆች በተለይ ጽኑ የሆነ ቅጣት እንደሚፈፀምባቸው ሲደነግግ የቅጣቱ መጠን ምን እንደሆነ ለምንስ በተለይ በጽኑ እንደሚቀጡ አይደነግግም:: የሚቀጡት ከቅጣቱ ክልል ሳይታለፍ መሆኑን ለማመልከት "አደራጆች" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የቅጣት ወሰኖች ሳይታለፍ ለመቀጣጫ" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: በዚሁ ንዑስ አንቀጽ መጨረሻ ላይ "ቁጥር ፹(፩) (መ)" የሚለው ጥቅስ ቀርቶ "አንቀጽ ፹፬ (፩) (መ)" የሚለው እንዲካተት ተደርጓል::

ከዚህም በላይ አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፫፻ ወታደራዊ አመጽ ለማነሳሳት የሚደረግ አድማ ወይም መተባበር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ስያሜ ከይዘቱ ጋርና ከአንቀጽ ፪፻፺፱ ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ፣ "ወታደራዊ አመጽ ለማነሳሳት የሚደረግ አድማ ወይም መተባበር" ተብሎ ተቀርጿል:: ይዘቱን በተመለከተ የድንጋጌው ሁለት ፓራግራፎች የየራሳቸውን ቅጣት ስለሚደነግጉ በሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲከፈሉ ተደርጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የእስራት ቅጣት ከወንጀሉ ጠባይና ከአንቀጽ ፫፻፲ ቅጣት ጋር ሲነፃፀር በጣም የቀለለ ሆኖ በመገኘቱ በቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጓል::

በዚሁ መልክ የንዑስ አንቀጽ (፪) የአስር ዓመት ጣሪያ ቅጣት ከፍ ተደርጎ ከሶስት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል::

ከዚህም በላይ አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፭ ወታደራዊ አመጽ እንዲደረግ ማነሳሳትና የማነሣሣት ሙከራ፣ አባሪነትና የአባሪነት ሙከራ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፭ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ "በተካፋይነት ስለሚደረግ ሙከራ" ከሚል ይልቅ "ወታደራዊ አመጽ እንዲደረግ ማነሳሳትና የማነሳሳት ሙከራ፣ አባሪነትና የአባሪነት ሙከራ" እንዲል ተደርጎ ተረቅቋል::

በዚህ አንቀጽ ሥር የሚያስቀጣው የማነሳሳትና የአባሪነት ሙከራ ብቻ ሳይሆን /አንቀጽ ፰፯(፪)/ "ወታደራዊ አመጽ እንዲደረግ ማነሳሳትና (አንቀጽ ፴፮ (፩) እና አባሪነት (አንቀጽ ፴፯(፫) ጭምር እንዲሆን፣ ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት የማነሳሳት ወይም የአባሪነት ሙከራ ወንጀል ከሆነ ማነሳሳት ወይም አባሪነትም እንደ ወንጀል መቆጠር እንዳለበት ግልጽ በመሆኑና ወታደራዊ አመጽ እንዲደረግ ማነሳሳት ወይም አባሪነት እንዲያስቀጣ የሚያደርግ ሌላ አንቀጽ ባለመኖሩ ነው::

የቀድሞ ድንገጌው ድርጊቱ የሚያስቀጣ መሆኑን ከመግለጽ በቀር የቅጣቱን ዓይነት የማይደነግግ በመሆኑ "በቀላል እስራት ያስቀጣል" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: ከዚህም ሌላ አንቀጹ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፮ በዘብ፣ በዘብ ጠባቂና በቃኚ ዘብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፮ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ንዑስ ክፍል ሁለት
የጦበቃ ግዴታን ወይም ትዕዛዞችን በመጣስ
የሚፈፀሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፫፻፫ የጥበቃ ግዴታን መጣስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፫ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ ድንጋጌ ስያሜ ላይ "የዘብ ወንጀል" ይል የነበረው " የጥበቃ ግዴታን መጣስ" በሚል እንዲተካና ግልጽ እንዲሆን ሲደረግ፤ በአንቀጹ ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር ሁለት የሚገኙት ሁለት ፓራግራፎች በየበኩላቸው ቅጣት ስለሚደነግጉ ሁለተኛው ፓራግራፍ እራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል:: ቅጣቱንም በሚመለከት በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ቅጣቱ "ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ፣ የዕድሜ ልክ እስራት ወይም የሞት ቅጣት ይሆናል" በሚል ተረቅቋል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፬ <u>ወታደራዊ ትዕዛዝን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

በዚህ አንቀጽ ሥር በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት የጥፋት ዓይነቶች እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከተው መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቷል፡፡ መሣሪያ የተከማቸበትን ግምጃ ቤት ወይም መሣሪያ የተከማቸበትን ሌላ ቦታ መጠበቅን የሚመለከት ልዩ ትዕዛዝን መጣስ የወታደርን ልዩ ትዕዛዝ በመጣስ የሚፈፀም ከበድ ያለ ወንጀል ሆኖ በዝርዝር ውስጥ ያልተመለከተ ስለሆነ በፊደል ተራ (ለ) "መርከቦች መልሕቆችን ጥለው የሚቆሙበት ቦታ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "መሣሪያዎች የተከማቹበትን ግምጃ ቤት ወይም ሌላ ቦታ" የሚል ሐረግ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ " ወንጀሉ የተፈጸመው" ተብሎ ከተፃፈ በኋላ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎች የጦር መሣሪያዎች ወይም እነዚሁ የሚገኙበትን ቦታዎች ከመጥቀስ በቀር ወንጀሉ እንዴት እንደተፈጸመ የሚገልጽ ሐረግ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ በንዑስ አንቀጽ (፩) መጨረሻ በፊደል (ሀ) (ለ) እና (ሐ) የተዘረዘሩትን በሙሉ በሚያቅፍ አኳኋን ሆኖ "መጠበቅን በሚመለከት ልዩ ትዕዛዝን በመቃወም እንደሆነ" የሚል ሐረግ ገብቶአል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፫) ወንጀሉ በምን አኳኋን እንደሚከብድ ስላልተብራራ ተሰርዞ "ወንጀሉ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ " በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም በንዑስ ቁጥር ሁለት "እስከ ሦስት ወር እሥራት" የነበረው " ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ..." ፤ በንዑስ ቁጥር ሦስት ደግሞ "እስከ አምስት ዓመት ... " የነበረው "እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት..." ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአንቀጹ ስያሜና ይዘት መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፫፻፭ <u>ትዕዛዝን ያለአግባብ መግለጽ ወይም መለዋወጥ ወይም በአግባቡ አለማስተላለፍ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "ለዘብ የተሰጠውን ምሥጢራዊ ትዕዛዝ ስለመግለጽና ስለመለዋወጥ" የሚል ነበር፡፡

ዳሩ ግን ለአንድ ወታደር የሚሰጠው ልዩ ትዕዛዝ ዘብን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለዚህ ማናቸውም ሌላ ትዕዛዝን እንዲሸፍን ለማድረግ የነበረው ስያሜ ተሠርዞ "ትዕዛዝን ያለአግባብ መግለጽ ወይም መለዋወጥ ወይም በአግባቡ አለማስተላለፍ" በሚል አዲስ ስያሜ ተተክቷል፡፡ በተራ ፊደል (ሐ) ላይ አዲስ ድንጋጌ የገባ ሲሆን አንድ የመከላከያ ሠራዊት ባልደረባ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ እንዲያስተላልፍ የታዘዘውን መልዕክት ሳያስተላልፍ የቀረ እንደሆነ የሚቀጣበትን ሁኔታ እንዲያካትት ተደርጎ ተቀርጿል፡፡

www.abyssinialaw.com

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ፣ "አድራጊው ይህን ተግባር የፈጸመው በቸልተኛነት እንደሆነ የሚቀጣው በሥነ ሥርዓት አግባብ ነው::" የሚል ሲሆን የድንጋጌው መኖር የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ ተሰርዟል::

የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲሆን ተደርጓል::

ንዑስ ክፍል ሦስት

ታማኝነትን በማጓደል የሚፈጸሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፬፻፮ በዕቃዎች ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፮ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ፊደል (ሀ) እና ፊደል (ለ) ላይ የተዘረዘሩት ጥፋቶች ደረጃ የተለያየ በመሆኑ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) እንዲሆኑ ተደርገዋል:: ቅጣታቸውም የተለያየ እንዲሆን ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት ድርጊቶች ቀለል ያሉ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱት ግን ከባድ በመሆናቸው ነው:: በተጨማሪም በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "የሸጠ" የሚለው ቃል ተሰርዞ በንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል:: ንዑስ ቁጥር (፪)፣ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ የገባ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተረቅቆ ገብቷል:: ይኸውም "ወንጀል የተፈፀመባቸው ወታደራዊ መሣሪያዎች ወይም ዕቃዎች ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት" ሊያስቀጣ እንደሚችል ሆኖ ተደንግጓል::

ንዑስ ቁጥር (፪) የነበረው ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ የገባ ሲሆን ቅጣቱም ተሻሽሎ "ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ፣ ነገሩ ከባድ እንደሆነ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ይሆናል" እንዲል ተደርጎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፬፻፯ የማይገባ ጥቅምን ማግኘት ወይም ያለአግባብ ማጥፋት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፯ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘቱ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ እና ለውጥ ተደርጎበታል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ላይ "ነዳጅን" የሚል ቃል ገብቷል:: ይህም የሆነው በንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ... ጉዳዩን በግልጽ መሸፈን አስፈላጊነት እንዳለው ስለታመነበት ነው:: ቅጣቱን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር አንድ "እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል::" የሚለው "እስከ አሥር ዓመት ..." እንዲሆን፤ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ቅጣቱ "እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት" የሚለው ቀርቶ እስከ ሃያ ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እንዲሆን ተሻሽሏል::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል አራት
## በመከላከያ ሠራዊት ደህንነት፣ ሞራል ወይም ኃይል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### ቀጽ ፫፻፳ አደጋን አለማስታወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "በአደጋ ጊዜ የማስጠንቀቅን ተግባር ስላለመፈጸም ይል የነበረው አጠር ባለና ግልጽ በሆነ አነጋገር "አደጋን አለማስታወቅ" እንዲል፤ሆኗል::

አቀራረጹን በተመለከተ ድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩት ሲሆን፣ ማሻሻያ ተደርጎበት ሶስት ንዑስ አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል:: አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንድ የገባ ሲሆን የቀድሞው ንዑስ ቁጥር አንድ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የቀድሞው ንዑስ ቁጥር ሁለት ንዑስ አንቀጽ ሶስት እንዲሆን ተደርጓል::

ድርጊቱ ማስቀጣት ያለበት የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ሁኔታዎች በሌሉበት ጊዜ ቢሆንም እንኳ አደጋ ሊደርስ መቃረቡን እያወቀ አደጋን አለማሳወቅ ወንጀል መሆን ስለሚገባው በቀላል እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጐ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ተረቅቋል:: ወንጀሉ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ (፪) ተደንግጓል::

የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጐበት ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል::

### ቀጽ ፫፻፳፩ አስፈላጊ የሆነውን የደህንነት ጥንቃቄ አለማድረግ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፩ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ላይ "አንድ አዛዥ መኮንን" የሚለው ሀረግ ከሠራዊቱ አደረጃጀት አኳያ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ በተጨማሪ "በመከላከያ ሠራዊት አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ሌላ ማንም ሰው" የሚል ሐረግ ተጨምሮበታል:: ቅጣትን በተመለከተ ከተዘረዘሩት የወንጀል አሠራር ዓይነቶች አንፃር የማይመጣጠንና አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "እስከ አንድ ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል" የሚለው "በቀላል እስራት ወይም እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት" በሚል እንዲሻሻል፤ በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ደግሞ "እስከ ሦስት ወር..." የሚለው "እስከ አንድ ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እስራት" በሚል ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ) ላይ ወንጀሉ ታስቦ ሲፈጸም ቅጣቱ እስከ ሰባት ዓመት፣ ነገሩ ከባድ ሲሆን እስከ አስር ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት በሚል እንዲስተካከልና እንዲሻሻል ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፫) (ለ) ላይ ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈጸመ ከሆነ እስከ ሶስት ዓመት፣ ነገሩ ከባድ ሲሆን እስከ አስር ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እስራት እንደሚሆን ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፫፻፲ ሐሰተኛ የአደጋ ምልክት መስጠት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲ ሆኖ ገብቷል፡፡

በዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፪) የእሥራት ቅጣቱ "እስከ አምስት ዓመት..."የነበረው እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት..." እንዲሆንና ከወንጀሉ ከባድነት ጋር እንዲመዛዘን ተደርጓል፡፡ በዚሁ ዓይነት በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ የተጠቀሱት ቅጣቶችም " ሦስት ወር..." የነበረው ወደ "ስድስት ወር...."፤ "አንድ ዓመት" የነበረው ወደ "ሁለት ዓመት" ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ከላይ በተገለፀው መሠረት ቅጣቱ አነስተኛ ስላልሆነና ከወንጀሉ ጋር ስላልተመጣጠነ ነው፡፡

## አንቀጽ ፫፻፲፩ የመከላከያ ሠራዊቱን ተስፋ ማስቆረጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

የዚህ ድንጋጌ ስያሜም ሆነ ይዘቱ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ይኸውም በስያሜው ላይ "የጦር ወታደሩን " የሚለው "የመከላከያ ሠራዊቱን" በሚል ተተክቷል፡፡ በንዑስ ቁጥር አንድ መግቢያ ላይም "የወታደር አለቃ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "የጦር አዛዥ" የሚለው እንዲገባ ተደርጓል፡፡ "የጦር አዛዥ ከሚለው በፊትም "የመከላከያ ሠራዊት አባል" የሚል ሀረግ ገብቷል፡፡

የቀድሞው ድንጋጌ ተሻሽሎ ንዑሰ ቁጥር (፩) እና ንዑስ አንቀጽ ሁለት፣ የተደረገ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ገብቷል፡፡ ይህም አዲስ ንዑስ አንቀጽ የመከላከያ ሠራዊቱን ተስፋ ማስቆረጥ በውጊያ ጊዜ ወይም ከውጊያ በፊት ሳይሆን በማናቸውም ጊዜ ቢፈጸም በጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጎ የተደነገገ ነው፡፡ ተስፋ ማስቆረጡ የተደረገው በውጊያ ጊዜ ወይም ከውጊያ በፊት ጥቂት ቀደም ብሎ ወይም ውጊያው እንዳበቃ ወዲያውኑ ከሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማያንስ ጽኑ እስራት ሆኖ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ተረቅቋል፡፡ የቀድሞው ንዑሰ ቁጥር (፪) የቃላት ለውጥ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖአል፡፡

## አንቀጽ ፫፻፲፪ ፊሪነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፪ ሆኖ ገብቷል፡፡

በይዘቱ ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው እራሳቸውን ችለው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በ(ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በቀሪው የአንቀጹ ይዘት ላይም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com



ቀጽ ፫፻፲፫ <u>ለጠላት እጅን መስጠት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፫ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ መንደርደሪያ ላይ "የጦር አዛዥ" ከሚለው በተጨማሪ "ወይም የመከላከያ ሠራዊት አባል" የሚል ሐረግ ተጨምሮበት ተረቅቋል::

የፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለው ለየብቻ ለማስቀጣት እንዲችሉ "ወይም" የሚል ቃል በተራ ፊደሎቹ መካከል እንዲገባ ተደርጓል:: የእሥራት ቅጣቱንም በሚመለከት መነሻው የአንድ ዓመት ጽኑ እሥራት ከወንጀሉ ክብደት አንጻር የሚያንስ ስለሆነ "እስከ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት" ከሚለው ሀረግ ላይ "እስከ" የሚለው ተሰርዞ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ወይም ሞት እንዲሆን ተደርጎ ተሻሽሏል::

ቀጽ ፫፻፲፬ <u>የጦር መሣሪያዎችን እንደተማረኩ መተው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፬ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ይዘት መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት እንደሚከተለው ተሻሽሏል:: በንዑስ ቁጥር (፩) መንደርደሪያ ላይ "ማንም ወታደር ወይም የወታደር ሹም" የሚለው ተሰርዞ "ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ወይም የጦር አዛዥ መኮንን" በሚል ተተክቷል:: ቅጣትን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የተደነገገው ከወንጀሉ ከባድነት አንፃር የተመጣጠነ ስላልሆነ በንዑስ አንቀጽ (፩) "ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም ፋቱ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት..." እንዲሆን ተደርጓል:: ወንጀሉ በቸልተኛነት የተፈጸመ እንደሆነ ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጎ የነበረው የቀድሞው ህግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ጸንቷል:::

ቀጽ ፫፻፲፭ <u>በጠላት የደንብ ልብስ ወይም የጦር መሣሪያ ያለአግባብ መገልገል</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ውስጥ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ነው:: የዚህ ድንጋጌ አስፈላጊነት የመነጨው፣ በሙያ በታ ላይ ከልምድ እንደታየው ከፍተኛ ችግር ስለሚያስከትል በሕግ ተደንግጎ ቅጣት ሊጣልበት ስለሚገባ ነው::

ቀጽ ፫፻፲፮ <u>የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ትቶ መሄድ</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ውስጥ ያልነበረ እና አዲስ ነው:: አስፈላጊነቱም የመነጨው ከልምድ እንደታየው ድርጊቱ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ሳለ በሕግ ላይ ወንጀልነቱ ስላልተደነገገ ነው:: ስለዚህም ማንኛውም ሰው በጦር ሜዳ የተሰዉ ጓዶችን እና ቁስለኞችን ጥሎ ቢሄድ ወይም የወታደር ሀኪም ቁስለኞችን መርዳት ሲገባው ይህንን ሳያደርግ ቢቀር፣ በቁስለኛው ላይ ሞት ወይም ከባድ ጉዳት ሊደርስ ስለሚችል ድርጊቱ የሚያስቀጣ መሆኑ በዚህ አንቀጽ ላይ ተደንግጓል::

ቀጽ ፫፻፲፯ <u>የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባል በያዘው ንብረት ላይ የሚፈፀም ወንጀል</u>

ይህ አንቀጽ የቆሰለ ወይም የተሰዋ ጓድ በያዘው ንብረት ላይ የሚፈፀም ወንጀልን አስመልክቶ የተደነገገ አዲስ አንቀጽ ሲሆን ይህ የሆነበት ምክንያት ችግሩ

www.abyssinialaw.com


እንደሚያጋጥም መረጃ የተገኘ በመሆኑና ወደፊትም ተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ በመታመኑ ነው።

## ክፍል አምስት
## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫፻፲፰ ሲቪሎች ወይም ሚሊሺያዎች የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች

ይህ አንቀጽ ከመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር ፳፯/፲፱፹፰ አንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተወሰደ ሲሆን በጦር ግዳጅ ላይ የሚገኙ ሲቪሎች ወይም ሚሊሺያዎች ለሚፈጽሟቸው ወንጀሎች እንደወታደር ተቆጥረው ተጠያቂ መሆን ያለባቸው በመሆኑ ከአንቀጽ ፪፻፹፬ ፫፻፳፩ ያሉት ድንጋጌዎች በእነርሱም ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ተደርጎ ተረቅቋል።

### አንቀጽ ፫፻፲፱ የጦር ምርኮኞችና የወታደር ግዞተኞች የሚፈጽሙአቸው ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፱ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላትና የአባባል ማስተካከያዎች ተደርጎበታል።

### አንቀጽ ፫፻፳ ወታደራዊ ግዴታን በመጣስ መኰንኖችና አዛዥ መኰንኖች የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳ ሆኖ ገብቷል።
የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘቱ ግልጽ እንዲሆን አቀራረቡ ተሻሽሎአል።

### አንቀጽ ፫፻፳፩ ለከባድ ሁኔታዎች ተጨማሪ የሚሆኑ ቅጣቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፩ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ይዘት መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ቅጣትን በተመለከተ "ወንጀሉን የፈፀመው በአፍቅሮ ነዋይ የሆነ እንደሆነ፣ የጦር አዛዥ መኮንን ከሆነ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ፣ አዛዥ መኮንን ካልሆነ እስከ ሃያ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ እንዲቀጣ" በሚል የቀድሞውን "የሃያ ሺህ ብርና የአምስት ሺህ ብር መቀጮ" በማሻሻል ቅጣቱ እንዲከብድ ተደርጓል።

### አንቀጽ ፫፻፳፪ የሥነ-ሥርዓት ቅጣቶች የተጠበቁ መሆናቸው

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፪ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፫፻፵፩ መግቢያ ላይ "ያገለግሎትን ትእዛዝና ድንጋጌዎችን በመጣስ በድንገተኛ ስካር፣ ባለመታዘዝ ወይም ደንቡን ባለመከተል ወይም ያለመጠን በመገልገል ቀላል የሆኑ የደንብ መተላለፍ ሥራዎች በተሠሩ ጊዜ" የሚለው አገላለጽ ተሰርዞ "ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በወታደራዊ ሕጐች ደንቦች

 www.abyssinialaw.com

ወይም መመሪያዎችና ቋሚ ትእዛዞች ውስጥ የተመለከቱትን የተላለፈ እንደሆነና ጥፋቱ አነስተኛ በመሆኑ በወንጀል የማያስጠይቀው በሚሆንበት ጊዜ፣" በሚል ግልጽ የሆነ ሐረግ ተተክተዋል::

ዕራፍ ሁለት

በመከላከያ ሠራዊትና በአባሎቻቸው ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

ክፍል አንድ

ሥራቸውን በማከናወን ላይ በሚገኙ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፫፻፳፫ የሥራ ግዴታ በማይገባ ሁኔታ እንዲፈፀም ወይም እንዲጣስ ማስገደድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፫ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፳፬ ሥራውን በማከናወን ላይ ባለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ የሚፈፀም ጥቃት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፬ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ ድንጋጌ ስያሜና ይዘት ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላትና የአባባል ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ቅጣትን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተደነገገው ከወንጀሉ ክብደት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ስላልተገኘ በንዑስ አንቀጽ (፩) "እስከ አንድ ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል" የሚለው "እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት..." እንዲሆን ተደርጓል:: የንዑስ አንቀጽ (፪) ቅጣት መነሻው ደግሞ እንደቀድሞው "አንድ ወር" መሆኑ ቀርቶ "ስድስት ወር" እንዲሆን ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፳፭ ከባድ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፭ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ ድንጋጌ ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: በፊደል ተራ የተቀመጡት ንዑሳን አንቀጾች መካከል " ወይም" የሚል አያያዥ መስተፃምር በማስገባት እያንዳንዳቸው ለብቻቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት ሲባል ተጨምሯል:: ቅጣትን በተመለከተ በቀድሞ ድንጋጌ በስተመጨረሻ" ... ለጤና ማናቸውንም ጉዳት ያላደረሰ እንደሆነ ቅጣቱ ቢያንስ የአንድ ወር እሥራት ይሆናል:: " የሚለውን በማሻሻል "የአንድ ወር" የሚለው ተሰርዞ "ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::" በሚል ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል:: ድርጊቱ በኃይልና በጦር መሣሪያ የተፈፀመ ከሆነ "ቅጣቱ ቢያንስ የሦስት ወር እሥራት ይሆናል::" የሚለው ቀርቶ "ጥፋተኛው ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::" ተብሎ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እንዲሻሻል ተደርጓል:: ምክንያቱም የወንጀሉ ጠባይ ሲታይ የሠራዊቱን ክብር በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሆኖ በመገኘቱ ነው::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## በመከላከያ ሠራዊትና በድጋፍ ሰጪ የአገልግሎት ክፍሎቻቸው ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች::

አንቀጽ ፫፻፷፮ የሕግ ወይም የውል ግዴታዎችን መጣስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፮ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ባሉ የፊደል ተራዎች ለየብቻቸው የሚያስቀጡ ወንጀሎች መሆናቸውን ለማመልከት በ(ሀ) እና (ለ) በተራ ፊደሎቹ ድንጋጌ መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል:: በተጨማሪም በአንቀጹ ይዘት ላይ ግልፅና የተብራራ ለማድረግ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: የእስራት ቅጣቱ አይነት በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፫፻፷፯ የተንኮል ሥራ /አሻጥር/

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፯ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ቀደም ሲል የነበረው "ስለ ማሰናከል" የሚለው ተለውጦ "የተንኰል ሥራ /አሻጥር/" ተብሎ ተሻሽሏል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በ (ሀ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቷል:: ከዚህም ሌላ በአንቀጹ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቅጣቱን በሚመለከት ከወንጀሉ ክብደት ጋር እንዲጣጣም በንዑስ ቁጥር (፩) "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል:: ወይም ነገሩ ከባድ እንደሆነ እስከ አሥር ዓመት ሲደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት" የሚለው አገላለጽ ተለውጦ "እስከ አሥር ዓመት ሲደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል" በሚል ዓረፍተ ነገር ተተክቷል:: በቸልተኝነት ለሚፈጸም ድርጊት አማራጭ ቅጣት "እሥራት ይሆናል" የሚለው ሀረግ ተስተካክሎ "ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ" እንደሚሆን ተደርጐ በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፷፰ በወታደራዊ ዕቃዎች መነገድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፰ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ያለ ንዑስ አንቀጽ ተቀርጾ የነበረ ቢሆንም ይህ አንቀጽ ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎአል ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው::

በቀድሞው ድንጋጌ ከተካተቱት ድርጊቶች ውስጥ ከፊሎቹ ቀለል ያሉ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ከበድ ያሉ በመሆናቸው ቅጣት መወሰን ያለበት እንደየጥፋቱ ደረጃ ነው:: በመሆኑም ወታደራዊ ዕቃዎችን ከሕግ ውጭ ማዋስን በእዳ ማስያዝን ወይም በተውሶ ወይም በመያዣነት መቀበልን የመሳሰሉት ድርጊቶች በዕቃዎቹ ላይ ግልጽ ጉዳት የማያስከትሉ በመሆናቸው በንዑስ አንቀጽ አንድ ስር እንዲካተቱና በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ እንዲያስቀጡ ተደርጓአል:: ወታደራዊ ዕቃዎችን መሸጥ፣መግዛት ወይም ሙሉ በሙሉ

www.abyssinialaw.com

ለራሱ ጥቅም ማዋል፣ ማጥፋት፣ ማፈረስ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ማድረግ ከባድ ድርጊቶች በመሆናቸው መነሻ ቅጣታቸው ስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲሆን የተደረገበት ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል:: ነገሩ ከባድ በሚሆንበት ጊዜም እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ንዑስ አንቀጽ ሶስት እንዲገባ ተደርጓል::

ቀጽ ፫፻፳፱ <u>የመከላከያ ሠራዊት ወታደራዊ የደንብ ልብስን፣ ምልክትንና ሽልማትን ያለአግባብ ማምረትና ለንግድ ማዘዋወር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፳፱ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል:: ቅጣቱን በተመለከተ "እስከ አንድ ዓመት ለመድረስ በሚችል እሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::" የሚለው ቅጣት ስላነሰና ትንሽ ከፍ ማድረግ በማስፈለጉ፣ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል::

ቀጽ ፫፻፴ <u>የመከላከያ ሠራዊት የደንብ ልብስን፣ ምልክትንና ሽልማትን በማይገባ መልበስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ይዘትም ሆነ በስያሜው ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

ቀጽ ፫፻፴፩ <u>ወታደራዊ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ቅጣትን በተመለከተ በተለይም የንዑስ አንቀጽ አንድን የገንዘብ መቀጫ "እስከ አምስት መቶ ብር..." በሚል እንዲሻሻል የተደረገ ሲሆን ምክንያቱም የገንዘቡን መቀጫ ለመገደብ ነው::

ቀጽ ፫፻፴፪ <u>ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ ለማድረግ ሌላውን ሰው ማነሳሳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፪ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ይዘት መጠነኛ የቃላትና የአባባል ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ቀጽ ፫፻፴፫ <u>የተወሰኑ ወታደራዊ ሥፍራዎችን እና ዕቃዎችን ለመጠበቅ የወጡ ክልከላዎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፫ የተደረገ ሲሆን በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በዚህ አንቀጽ ሥር በፊደል ተራ የተቀመጡትን ንዑሳን አንቀጾች በቁጥሮች እንዲቀመጡ ተደርጓል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተከፈሉት ድርጊቶች የጥፋት

www.abyssinialaw.com


ደረጃ የተለያየ በመሆኑ እንደየደረጃቸው የተለያየ ቅጣት ለመደንገግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው::

አንቀጽ ፪፻፵፬ <u>ጠቅላላ ትዕዛዞችን ወይም መመሪያዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፬ ሆኖ ገብቷል::

ይህ ድንጋጌ የአንቀጽ ፪፻፹ን እና የአንቀጽ ፪፻፹፪ን ይዘት በማይቃረን ሁኔታ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባው ለማመልከት የአንቀጽ ፪፻፹ እና ፪፻፹፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚል ሐረግ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በአንቀፁ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከተው እያንዳንዱ ድንጋጌ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በፊደል (ሀ) ከተመለከተው ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቷል:: ጠቅላላ ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም ማጥፋት ከባድ ወንጀል ስለሆነ ቅጣቱ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ብቻ ቢሆን ቅጣቱ ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠንና አነስተኛ ስለሚሆን እስከ ሰባት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንዲሆን ተደርጎ ተሻሽሏል:: ከዚህም በላይ በቀድሞው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድና ሁለት ላይ የአገላለጽና የቃላት ለውጥ ተደርጎባቸው አንቀጹ ግልጽ ሆኖ እንዲረቀቅ ተደርጓል::

አንቀጽ ፪፻፵፭ <u>በመከላከያ ሠራዊት ላይ እና ወታደራዊ ግዴታዎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አለማስታወቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፴፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ማንም ሰው የመክዳት ወይም የስለላ፣ የማሸበር ወይም የመኮብለል ወንጀል ዕቅድ ወይም ተግባር መዘጋጀቱን አውቆ በማናቸውም ምክንያት አለመግለጽ ወይም እንዳይፈፀም ለማገድ አለመፈለግ ወይም አድራጊዎቹን ሳያስታውቅ መቅረት በቀላል እሥራት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ በተመለከተው ውስጥ መክዳትና ስለላ በወታደራዊም ሆነ በሌሎች አገር ነክ ጉዳዮች ረገድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፪፻፶፭ የተሸፈኑና ይህም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለጸ ስለሆነ በድጋሚ መደንገጉ አስፈላጊ ስላልሆነ ከዚህ አንቀጽ ተሰርዟል:: የአመጽ ወንጀል መዘጋጀቱን ሣያስታውቅ መቅረት ብቻ ሣይሆን መፈፀሙንም አለማስታወቅ አገርንና ኅብረተሰብን የሚጎዳ ድርጊት ስለሆነ ይህም እንደሚያስቀጣ ለማመልከት "የአመጽ ወንጀል መዘጋጀቱን" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ወይም መፈፀሙን" የሚል ሐረግ ተጨምሯል:: በማናቸውም ምክንያት አውቆ አለመግለጽ ሣይሆን አውቆ በማናቸውም ምክንያት አለመግለጽ ስለሆነ የቃላቱ አገባብ ተስተካክሎ ትክክለኛ ትርጉሙን እንዲይዝ ተደርጎ አቀራረቡ ተቃንቷል:: "እንዳይፈፀም ለማገድ ያልፈለገ" የሚለው ሐረግ መፈለግና አለመፈለግ ውስጣዊ የሆነ የሰውን አስተሳሰብ ስሜት የሚገልጽ እንጂ በድርጊት የሚገለጽ ተጨባጭ ሁኔታ ስላልሆነ ያልፈለገ የሚለው ቃል ተሠርዞ "የሚቻለውን ያላደረገ" በሚል ሐረግ ተተክቷል:: የኩብለላ ወይም የአመጽ ወንጀልን ያዘጋጀ ወይም የፈፀም ወንጀለኛ ተይዞ ፍርዱን እንዲያገኝ ቢደረግ እንደዚህ ያለውን ወንጀል ለመከላከል ይረዳል:: ስለዚህም የኩብለላ ወይም የአመጽ ወንጀል እንዳይፈፀም ለማገድ የሚቻለውን አለማድረግ ብቻ ሣይሆን ወንጀለኛው እንዲያዝ የሚቻለውን አለማድረግም እንደሚያስቀጣ ተደርጎ ተዘጋጅቷል:: በዚህ ምክንያት "እንዳይፈፀም ለማገድ ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ወይም ወንጀለኛው እንዲያዝ" የሚል ሐረግ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

የኩብለሳ ወይም የአመጽ ወንጀል መዘጋጀቱን ወይም መፈፀሙን እያወቀ ሣያስታውቅ የቀረ፣ ወይም እንዳይፈጽም ለማገድ ወይም ወንጀለኛው እንዲያዝ የሚቻለውን ያላደረገ ሰው ሁሉ እንዲቀጣ ማድረጉ ትክክለኛ ፍትሕን የተከተለ አይሆንም። ስለዚህ በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው አዲስ መስመር ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሣይኖር የሚል ሐረግ ገብቷል። ከዚህም በላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ታክሎበት አንቀጹ ተረቅቋል።

ቀጽ ፫፻፴፮ ወታደራዊ ምሥጢርን መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፮ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማሻሻያ ተደርጎበታል።

ቅጣቱን በሚመለከት በንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ወንጀል ካለው ክብደት አኳያ እንደቀድሞው "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ" መባሉ ተመጣጣኝ ስላልሆነ "ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት" እንዲያስቀጣ ተደርጓል። በንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው ቅጣት የአጻጻፍ ለውጥ ከመደረጉ በስተቀር ሌላ ማሻሻያ አልተደረገበትም። ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ በንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት የተገለጹት ድርጊቶች በቸልተኛነት ሲፈጸሙ ስለሚያስቀጣው ቅጣት የሚደነግግ ሲሆን፣ ለንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ "ስድስት ወር እሥራት" የሚለው ተለውጦ "ከአንድ አመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት" እንዲሆን ሲደረግ ለንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ "እስከ ሁለት አመት ቀላል እሥራት" ይል የነበረው "እስከ ሶስት ዓመት የሚደረስ ቀላል እሥራት" እንደሚሆን ተደርጐ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

ቀጽ ፫፻፴፯ የሐሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፯ ሆኖ ገብቷል።

ከላይ የተመለከተው ስያሜ "የሐሰት ወይም የማደናገር ወሬ ስለመስጠት" በሚለው የቀድሞ ስያሜ ምትክ እንዲገባ ተደርጓል።

በዚህ ድንጋጌ ለተመለከተው ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ የሆነ እንደሆነ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ነበር። ዳሩ ግን ወታደሮች በጦርነት ላይ ግዳጃቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት የሐሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ ቢሰጥ የመከላከያ ሠራዊቱን ወኔ እንዲከዳውና እንዲፍረከረክ ሊያደርገው ይችላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ አገርንና ብሔራዊ ጥቅምን የሚጎዳ ከባድ ወንጀል ስለሆነ ጥፋተኛውን በመቀጮም ለመቅጣት እንዲቻል ሆኖ በአማራጭ መቅረቡ ተገቢ አይሆንም። ስለዚህ "ወይም በገንዘብ መቀጮ" የሚለው ሐረግ ተሠርዟል።

የወንጀሉ አፈፃፀም ከባድ ሆኖ ሲገኝ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ብቻ እንደሚያስቀጣ የተደነገገው ቅጣት ከወንጀሉ ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ሆኖ ስለሚገኝ አገላለጹ ተሰርዞ "እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ወይም ወንጀሉ ከባድ ሲሆን እስከ ዕድሜ ልክ ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል።" በሚል ሐረግ ተተክቷል። ከዚህም በላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቋል።

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሦስት
## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫፻፴፰ በአደጋ ወይም በጦርነት ጊዜ ቅጣት የማከብድበት ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፰ ሆኖ ገብቷል::

በመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ ወይም በመከላከያ ኃይሉ ወይም በአጋዥ ኃይሉ ላይ ወይም በወታደራዊ ጥቅም ላይ በምዕራፍ ሁለት ሥር በተመለከቱት ድንጋጌዎች ከተዘረዘሩት ወንጀሎች አንዱ የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ እንደሆነ ወንጀሉ ከባድ ስለሆነ ቅጣቱም በዚያው ልክ መክበድ ይኖርበታል:: ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (፩)(ሀ) ቅጣቱን የሚያከብድ ሌላ ልዩ ድንጋጌ ከሌለ ፍርድ ቤቱ በቀላል እሥራት ፈንታ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ የተደነገገው ቅጣት ከወንጀሉ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ ስለታመነ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እንዲያስቀጣ ሆኖ ተዘጋጅቷል:: እንዲሁም በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) መጀመሪያ ላይ "ቅጣቱ ጽኑ እስራት የሆነ እንደሆነ የተደነገገውን ከፍተኛ የቅጣት ጊዜ እስከ አጠፌታ ድረስ ለመፍረድ ይቻላል" የሚለው ተሰርዞ፣ ".... በጽኑ እስራት ምትክ የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት አጠፌታ ድረስ ከፍ በማድረግ ለመወሰን ይቻላል" ተብሎ ንዑስ አንቀጽ አንድ (ለ) ተረቅቋል:: በንዑስ አንቀጽ አንድ (ለ) መጨረሻ ላይ የተቀመጠው ቅጣት ግን ከቀድሞው ሕግ ቅጣት የተለየ አይደለም:: በንዑስ ቁጥር ሁለት በ(ሀ)ም ሆነ በ(ለ) የተመደቡት ቅጣቶች ከወንጀሉ ጋር ሲነፃፀሩ አነስተኛ ስለሆኑ በ(ሀ) የተመለከተው ተሰርዞ "ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ምትክ እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ቅጣት" በሚል ሐረግ ተተክቷል:: በ(ለ) የተመለከተውም ሐረግ ተሠርዞ "ከአምስት ዓመት ሲያንስ በሚችል ቀላል እሥራት ምትክ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ቅጣት" በሚል ተተክቶ "ለመወሰን ይችላል" የሚለው ሐረግ በ(ሀ) እና በ(ለ) የተመለከቱትን ሁለቱንም ሐረጎች እንዲያስር በሚያደርገው አቀማመጥ ሆኖ ተጽፏል::

በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ ደግሞ መቀጮ ሲወሰን ተፈጻሚ በሆነው ድንጋጌ መሠረት ሕጉ የደነገገውን የመቀጮ መጠን አጠፌታ ድረስ ለማድረስ እንደሚችል ሆኖ ተረቅቋል:: በተጨማሪም በአንቀጹ ላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

### አንቀጽ ፫፻፴፱ በአፍቅሮ ንዋይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፱ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ ድንጋጌ ስያሜና ይዘት ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርገዋል:: ቅጣትን በተመለከተ ወንጀሉ የተፈፀመው በአፍቅሮ ንዋይ ከሆነ ድርጊቱን ለማውገዝና ወንጀለኛው ያገኛል ተብሎ የታሰበውን ጥቅም በቅጣት ለማስቀረት ሲባል ጭምር የገንዘብ መቀጫው መክበድ አለበት ተብሎ ስለታመነበት እንደአለው ሀብት መጠን ፍርድ ቤቱ "..ከእሥራቱ ቅጣት ጋር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ አጣምሮ ሊወስን ይችላል" በሚል ተሻሽሏል:: በመሆኑም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የቀድሞ ድንጋጌ "እስከ አሥር ሺህ ብር..." የሚለው እንዲቀር ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>
<u>ከአንቀጽ ፪፻፹፬-፫፻፴፯ የተደነገጉት ሁኔታዎች</u>
<u>በፖሊስ ሠራዊት ላይም ተፈፃሚ መሆናቸው</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ "ደንቡ በፖሊስ ሠራዊት ላይ የሚፀና ስለመሆኑ" የሚለው የምዕራፍ ሦስት ስያሜ የትኛው ደንብ እንደሆነ ግልጽ ስላልሆነ ዳሩ ግን በቁጥር ፫፻፵፩ በፖሊስ ሠራዊት አባሎች ላይ ተፈፃሚዎች የሚሆኑት ከቁጥር ፪፻፺፮ እስከ ፫፻፵ የተመለከቱት ድንጋጌዎች መሆናቸው ቁጥሮቹን በመጥቀስ የተገለፀ ስለሆነ የምዕራፍ ሦስት ስያሜ የተብራራ እንዲሆን ለማድረግ የነበረው ስያሜ ተሠርዞ "ከአንቀጽ ፪፻፹፬ እስከ ፫፻፴፯ የተደነገጉት ሁኔታዎች በፖሊስ ሠራዊት ላይም ተፈፃሚ መሆናቸው::" ተብሎ ተሻሽሎ ስያሜው እንዲቀረጽ ተደርጓል::

በምዕራፉ ስያሜ ላይ "ከአንቀጽ ፪፻፹፬ እስከ አንቀጽ ፫፻፴፯" የተባለው በስህተት ነው:: "፫፻፴፯" የሚለው "፫፻፴፮" እንዲል ሆኖ ሊነበብ ይገባል:: በአንቀጽ ፫፻፵ "ከዚህ በላይ ባሉ ምዕራፎች ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::" የሚለው ከፊል ዓ/ነገር የሚያሳየው፣ በሁለቱም ምዕራፎች ያሉት ድንጋጌዎች ሁሉ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ነው:: ሁለተኛው ምዕራፍም አንቀጽ ፫፻፴፭ን እና አንቀጽ ፫፻፴፮ን ያጠቃልላል:: እነዚህ ሁለት አንቀጾች በፖሊስ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆኑም ሕግ አውጭው ያስቀመጠው ምክንያት የለም፤ ሁለቱን አንቀጾች የመሰረዝ ዓላማም የለውም:: የቀድሞው ህግ የቁጥር ፫፻፶ ድንጋጌም የተሰረዘው አጣቃሾቹ ቁጥሮች የአንቀጽ ፫፻፴፮ ድንጋጌን እንደከተቱ በመታመኑ ነው::

ስለዚህ በምዕራፉ ስያሜም ሆነ በአንቀጽ ፫፻፵ መጨረሻ ላይ ተጠቃሹ ቁጥር አንቀጽ ፫፻፴፯ መሆኑ ቀርቶ ፫፻፴፮ ተብሎ ሊስተካከል ይገባል::

አንቀጽ ፫፻፵ <u>የአፈፃፀም መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፵፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፻፵ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ይዘት መጠነኛ የቃላትና የአቀራረብ ማስተካከያዎች ከተደረጉበት በኋላ እንዳለ እንዲቀጥል ተደርጓል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶ ድንጋጌ መሠረዝ</u>

በተጠቀሰው ድንጋጌ ውስጥ የተመለከቱት ቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎችና አንቀጾች በአንቀጽ ፫፻፴፮ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑ ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል ድንጋጌው ተሰርዟል::

አንቀጽ ፫፻፵፩ <u>ልዩ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፩ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ አንቀጽ ይዘት ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ አንዳንድ የቃላትና የአባባል ማስተካከያዎች ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፵፪ <u>የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በፖሊስ ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፪ እና የቁጥር ፫፻፶፫ ድንጋጌዎች የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፪ ሆነው ገብተዋል፤ ምክንያቱም የሁለቱም ድንጋጌዎች ይዘት በጣም ተቀራራቢ በመሆኑ ነው። የመጀመሪያው ድንጋጌ አንደኛ ፓራግራፍ ሲሆን ሁለተኛው ድንጋጌ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ አንቀጽ ይዘት በተቻለ መጠን ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ሀለተኛው ፓራግራፍ በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ግንኙነት ያላቸውን አንቀጾች እንዲያመላክት ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት የሚዛመዱ አንቀጾች መጥቀሱ ጉዳዩን በይበልጥ ግልጽ ስለሚያደርገው ነው።

<u>ርዕስ አራት</u>
<u>በመንግሥት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች</u>
<u>ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>
<u>ምዕራፍ አንድ</u>
<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

በዚህ ርዕስ አራት ሥር የነበረው ስያሜ አጻጻፍ "በመንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞቹ ላይ" የሚለው ሀረግ ጠበብ የሚልና ግልጽነት የሚጎድለው ስለነበር ቀረጥና ግብር የሚሉት ቃላት ኢኮኖሚ በሚል ቃል ተተክተው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፵፫ <u>ልዩ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፫ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "..በልዩ ደንብ ወንጀለኛ ስለ መባል.." ይል ነበረ። ይህ አገላለጽ በይዘቱ ላይ የተገለጹትን ሕጎች በሚሸፍን ሁኔታ ስላልተቀመጠ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከዚህ ወንጀል ሕግ ውጭ ያሉ ማናቸውንም ሕጎች /ደንብም ይሁን አዋጅ/ በሚሸፍን ሁኔታ እንዲስተካከል ተደርጓል። ይዘቱም "..ትዕዛዝ፣ ደንብ... "ድንጋጌ" ማለቱ ቀርቶ "ሕጎችን" በሚል ሰፋ ያለ ሁኔታ በሚይዝ ቃል እንዲተካ ተደርጓል። እንዲሁም ሕጎቹ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የወጡ ሊሆኑ እንደሚችሉ በሚያመለክት ሁኔታ ተስተካክሏል። በተጨማሪም ጥበቃ የተደረገላቸው ሀብቶች ዝርዝር አላስፈላጊና ጠባብ ስለሆነ ተሰርዞ "..የአገርን ገንዘብና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም.." በሚል አጠቃላይ አነጋገር እንዲተካ ተደርጓል።

በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ወንጀሉ ያስከተለው የጉዳት መጠን በገንዘብ ሲተመን አምስት ሺህ ብር ያልሞላ እንደሆነ በደንብ ተላላፊነት ብር አምስት ሺህ ከሞላ ግን በወንጀል እንዲያስቀጣ ተደርጐ በቀድሞው ሕግ የተደነገገ ሲሆን ብር አምስት ሺህ መሆኑ ቀርቶ ብር አስር ሺህ እንዲሆን ተደርጐ ተረቅቋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የብር

www.abyssinialaw.com

የመግዛት ኃይሉ እጅግ በቀነሰበት በአሁኑ ጊዜ የገንዘቡ መጠን ከብር አምስት ሺህ ከፍ ሊል እንጂ ዝቅ ሊል የማይገባው በመሆኑ ነው::

አንቀጽ ፫፻፷፬ <u>የወንጀል ቅጣቶች ዓይነታቸውና መጠናቸው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፬ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፩) ሦስተኛ መስመር ላይ "..ባመኑ ጊዜ" የሚለው ሐረግ ስህተት ስለሆነ "በግልጽ የማይመኑ ሆነው በተገኙ ጊዜ" ተብሎ ተስተካክሏል:: እንዲሁም "..ደንቦች፣ ትዕዛዞችና ድንጋጌዎች.." የሚሉት ቃላት ተሰርዘው "..ሕጎች.." ተብሎ ተስተካክሏል፤ በንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ የነበረው የሃያ ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣትም ወደ አንድ መቶ ሺህ ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፷፭ <u>ተደራቢ የቀረጥና የግብር ቅጣቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፭ ሆኖ ገብቷል::

የዚህ ድንጋጌ ይዘት የተንዛዛና ግልጽነት የሚጎለው ስለነበረ አጭርና ግልጽ ሆኖ እንዲስተካከል ተደርጓል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>ልዩ ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ ፫፻፷፮ <u>በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብና በውጭ አገር ገንዘብ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መነገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፮ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞ ድንገጌ ይዘት ውስጥ "..ከዚህ በታች ባለው በአምስተኛው አንቀጽ.." መባሉ ቀርቶ "..በአምስተኛው ርዕስ.". ተብሎ ተስተካክሏል:: ምክንያቱም አንቀጽ "Article" የሚለውን፣ ርዕስ ደግሞ "Title" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል እንዲተካ በመደረጉ ነው:: በእስራት ወይም እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይል የነበረው ቅጣት ተሰርዞ እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና እስከ ብር ሃምሣ ሺህ ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሆኖ ከፍ እንዲል ተደርጓል::

ይህም የሆነው፣ በድንጋጌው ለተመለከተው ወንጀል የቅጣቶቹ ዓይነትም ሆነ መጠን አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ቀላል እስራትና መቀጮ በአማራጭነት መቀመጡ የወንጀሉን ከባድነት ያላገናዘበ መሆኑ ስለታመነበት ነው::

አንቀጽ ፫፻፷፯ <u>በከበሩ ማዕድናት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መነገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፯ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "ባለዋጋ ማዕድኖችንና ዕንቁችን" ተብሎ የነበረው ተለውጦ "በከበሩ ማዕድናት" በሚል ሐረግ ተተክቷል:: ምክንያቱም የተጠቀሱት ማዕድናት በሙሉ "የከበሩ ማዕድናት" ስለሆኑ ነው:: ይዘቱን በተመለከተም አንዳንድ የቃላት መቃናት

www.abyssinialaw.com



ተደርጎበት ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በሚገባ እንዲጣጣም ተደርጓል። ይህ አንቀጽ የከበሩ ማዕድናትን በሚመለከት ሕገወጥ ንግድ በተደረገ ጊዜ ቅጣትን የሚጥል ቢሆንም ለሕጉ አፈጻጸም የተከለከሉና የተፈቀዱ ማዕድኖችን የሚደነግግ ሌላ ራሱን የቻለ ሕግ እንደሚወጣ ግንዛቤ በመውሰድ ባለበት ሁኔታ እንዲሆን ተደርጓል። አሁን ባለበት ሁኔታ ግን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳለ ግንዛቤ ተወስዷል።

አንቀጽ ፫፻፵፰ <u>በመንግሥት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፰ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ ቀደም ሲል በነበረው ሁኔታ ግለጽነት የሌለው ስለነበረ ከዚህ በላይ ባለው ሁኔታ ተስተካክሏል፤ ይዘቱም ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ግልጽነት የሌለው ሆኖ ስለተገኘ የእንግሊዝኛውን ቅጂ ተከትሎ እንዲስተካከል ተደርጓል፤ እንዲሁም ቅጣቱ ከአስር ዓመት ያልበለጠ ጽኑ እሥራት እና እስከ ሃምሣ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ ውጤት ያስከተለ እንደሆነ እስከ ሃያ ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ሆኖ ከፍ ተደርጓል።

በቀድሞው ድንጋጌ ላይ የተቀመጠው ቅጣት ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ሲሆን ከወንጀሉ ከባድነት ጋር የማይጣጣም እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ከፍ ብሎ በተመለከተው ሁኔታ ቅጣቱ እንዲጨምር ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፵፱ <u>ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥትን ቀረጥና ግብር የመክፈል እንቢተኛነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፵፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ይዘት ግልጽነት ባለው ሁኔታ የተስተካከለ ሲሆን የሚከፈለው ግብር ወይም ቀረጥ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በዓይነትም ሊሆን ስለሚችል ይኸው እንዲገባ ተደርጎ ተስተካክሏል። እንዲሁም በንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ "የሽፍትነት ሥራ አስከትሎ እንደሆነ" የሚለው ሐረግ ተቀይሮ "አመጽን አስከትሎ እንደሆነ" ተብሎ ተስተካክሏል፤ ቅጣቱም በአገር ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት አንፃር ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፶ <u>ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ሽብር" የሚለው ቃል "አመጽ" በሚል ተተክቷል እንዲሁም ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ስለሆነ ቅጣቱ በአጠቃላይ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፶፩ <u>በመንግሥት የገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፩ ሆኖ ገብቷል።

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ የተንዛዛ ሆኖ ስለተገኘ አጭርና ገላጭ በሆነ ሁኔታ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው እንዲስተካከል ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

ይዘቱን በተመለከተም አላስፈላጊ ድግግሞሽ ስለሚታይበት ይኸው እንዲቀር ሆኖ የተስተካከለ ሲሆን ቅጣቱ እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እና እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ ሆኖ ከፍ እንዲል ተደርጓል::

እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲገባ ተደርጓል:: ይህ ንዑስ አንቀጽ ከግብር፣ ከቀረጥና ከሌሎችም ተመሳሳይ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የመገመትና የመወሰን ሥልጣን ያለው ሰው መከፈል ከሚገባው በታች እንዲከፈል ወይም እንዲቀነስ ካዘዘ "በስልጣን ያለአግባብ በመገልገል (አንቀጽ ፬፻፯) ተጠያቂ ይሆናል::" በማለት ይደነግጋል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የገባ ስለሆነ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ ሶስት ሆኖአል::

## አንቀጽ ፫፻፶፪ ኬላ መስበር /ኮንትሮባንድ/

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ የንዑስ ቁጥር (፩) ይዘት ግልጽ ስላልነበረና ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን በመጨመር በሶስት ተራ ፊደላት እንዲከፈል ተደርጓል:: ይኸውም የቀድሞ ድንጋጌ ፊደል (ሀ) ሆኖ ሲገባ ቀረጥ ያልተከፈለበት ዕቃ በአገር ውስጥ ማዘዋወር እንዲሁም የአገር ውስጥ ምርትንም ቀረጥ ሳይከፍሉ ማዘዋወር ለየብቻቸው ግልጽ ሆነው በፊደል (ለ) እና (ሐ) ስር ገብተው እንዲያስቀጡ ተደርጓል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲገባ ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ወንጀሉ በኃይል፣ በዛቻ፣ በማጭበርበር፣ ወይም በቡድን የተፈፀመ እንደሆነ ቅጣቱን ማክበዱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዚሁ መልክ ተረቅቋል::

የቀድሞው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (፪)፣ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ የገባ ሲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## አንቀጽ ፫፻፶፫ በአገር ኢኮኖሚና በመንግሥት ሞኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ ማስተካከያ ተደርጎበታል:: አቀራረጹን በሚመለከት ድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩት ሲሆን፣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንዲገባ በማድረግ የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፪) ተሸጋሽጎ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖአል:: የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደረገ ሲሆን አዲስ ንዑስ ፊደል (ሐ) እና (መ) በማስገባት የቀድሞው የፊደል (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች በፊደል (ሠ) እና (ረ) ስር እንዲገቡ ተደርጓአል::

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያና ከፊደል ተራ (ሀ-መ) ባሉት ድንጋጌዎች ላይ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት በይበልጥ ግልጽ በሆነ አነጋገር ተቀርጾ በፊደል (ሐ) እና (መ) ስር የነበረው የፊደል (ሠ) እና (ረ) ድንጋጌ እንዲሆን ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል (ሐ) የገባው አዲስ ድንጋጌ "በዱር እንስሳት ወይም በፍሬያቸው መጠቀምን ወይም እነዚህኑ እንስሳት ማደንን ወይም መግደልን፣" የሚል ሲሆን በፊደል (መ) የተቀመጠው ደግሞ "በተከለሉ ደኖች፣ ፓርኮች ወይም በ[illegible] ቦታዎች መስፈርን ወይም ሌሎች ተግባራት ማከናወንን፣" ይመለከታል።

አዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፪) በጄኔቲክ ሃብት ላይ የሚፈጸመውን ወንጀል የሚመለከት ሲሆን "የጄኔቲክ ሃብት መሰብሰብን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን፣ ከሀገር ማስወጣትን ወይም ወደ አገር ማስገባትን ወይም መጠቀምን አስመልክቶ የወጣን ህግ" የጣሰ ሰው ከባድ ቅጣት እንደሚወሰንበት ይደነግጋል።

አዲሱ የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ደግሞ፣ "ማንም ሰው ሕግን በሚቃረን መንገድ ብርቅዬ እንስሳትን ያደነ ወይም የገደለ እንደሆነ፤ ወይም ብርቅዬ እንስሳትን ወይም ዕጽዋትን ወይም ውጤታቸውን ይዞ የተገኘ፣የሰበሰበ፣ ያጓጓዘ፣ ያስተላለፈ ወይም ከአገር ያስወጣ እንደሆነ፤" ከባድ የእስራት ቅጣትና ከፍተኛ መቀጮ ሊጣልበት እንደሚችል ይደነግጋል።

ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደረገው የቀድሞ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ተሻሽሎ ከላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱ በቸልተኝነት ሲፈጸም የሚያስቀጣ መሆኑን ይደነግጋል።

አንቀጽ ፫፻፶፬ <u>ወንጀሉን የሚያከብድ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፬ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ቀደም ሲል "..ቅጣቱን የሚያከብዱ ምክንያቶች.." ይል የነበረው "aggravations to the offence" የሚለውን የእንግሊዝኛ ሐረግ ስለማይተካ "ወንጀሉን የሚያከብድ ሁኔታ" ተብሎ ተስተካክሏል። ቅጣቱንም በተመለከተ ወንጀሉ ከባድ እንደመሆኑ መጠን እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት እና እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ ሆኖ ከፍ እንዲል ተደርጓል።

ቅጣትን ሊያከብዱ የሚችሉ የባንክ ሕጎች በተለይም የባንክ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር (፭)፻፺፪ አንቀጽ ፶፱ በንጽጽር የታየ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በማድረግ ቅጣቱ "... ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚል ሐረግ ተካትቷል። ምክንያቱም ወንጀለኛው የተከለከለ ዕቃን የማስተላለፍ ድርጊት የዘወትር የሙያ ሥራው ያደረገ ሆኖ ሲገኝ ከመቀጮው እና ከእሥራቱ በተጨማሪ ንብረቱ ሊወረስ እንደሚገባ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ድርጊቶች የፈጸመው የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፺ መሠረት እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

ከአገር ኢኮኖሚ ወይም የመንግስት የፋይናንስ ጥቅሞች ጋር በተያያዘ ጉዳይ በንዑስ አንቀጽ አንድ የተገለጸው ወንጀል የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት በሚፈጸምበተ ጊዜ ድርጅቱ መቀጣት ስለሚገባው፣ ይህንን የሚመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሁለት (፪) እንዲገባ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

## ርዕስ አምስት
## በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ ቴምብሮች ወይም መሣሪያዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፫፻፶፭ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ

ይህ አንቀጽ አዲስ ሲሆን በዚህ ርዕስ ስር በተመለከቱት ወንጀሎች አፈጻጸም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ተካፋይ ሲሆን የወንጀል ተጠያቂነቱን የሚደነግግ ነው::

አንድ ድርጅት በአንድ ወንጀል ተካፋይ ነው የሚባለውም፣ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፴፬(፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ከተዘረዘሩት ፍሬ ሃሳቦች አንዱ ሲሟላ ነው::

## ምዕራፍ አንድ
## የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች

አንቀጽ ፫፻፶፮ መሥራት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌውን ይዘት በሚመለከት "በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" የሚለው ሐረግ በአሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተቀባይነት ስለሌለው ተሰርዞ "በኢትዮጵያ" በሚል ሐረግ ብቻ ተተክቷል:: በሕዝብ እጅ ገብተው ለመገበያያነትና ለንግድ ሥራ የሚውሉ ገንዘቦች ብቻ ሳይሆኑ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ጭምር እንደሚሆኑ በምዕራፉ ስያሜ ላይ የተገለፀ ስለሆነ "ገንዘቦች የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች" በሚል ተሻሽሏል:: በሕዝብ እጅ ገብተው መገበያያ እንዲሆኑ ለማድረግ በማቀድ ሐሰተኛ ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን መሥራት ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖር እንደነዚህ ያሉትን ሐሰተኛ ነገሮች የመሥራት ድርጊት ጎጂና አደገኛ በመሆኑ ወንጀሉን ለማቋቋም በቂ ስለሚሆን "መብት ሳይኖረው አስመስሎ የሠራና በሕዝብ እጅ እንዲገቡ /መገበያያ እንዲሆኑ/ ያደረገ እንደሆነ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ያለ ፈቃድ የሠራ ወይም አስመስሎ የሠራ እንደሆነ" በሚል ሐረግ ተተክቷል:: ይህም የሆነው በሕዝብ እጅ ያልገባ ቢሆንም ተሠርቶ መገኘቱ ሊያስቀጣ እንደሚገባ የታመነበት በመሆኑ ነው:: ቅጣቱንም በሚመለከት በዚህ በከባድ ወንጀል ቢያስፈልግ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ድረስ ለመቅጣት ፍርድ ቤቱ እንዲችል፣ እጅግ ቢያንስ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

አንቀጽ ፫፻፶፯ ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፯ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ውስጥ በኢትዮጵያ "ንጉሠ ነገሥት" የሚለው ሐረግ አሁን ባለው የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ተስማሚ ስላልሆነ ተሰርዞ "በኢትዮጵያ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: ገንዘብም ሆነ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ የአገሪቱን

www.abyssinialaw.com

የፋይናንስ አቋም ሊያናጋ ኢኮኖሚውን ሊጎዳ የሚችል ከባድ ወንጀል ስለሆነ የተመደበለት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል የጽኑ እሥራት ቅጣት ያንሳል። ስለዚህ "አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል "የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከአሥራ አምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል።" በሚል ሀረግ ተተክቶአል።

አንቀጽ ፫፻፶፰ <u>ዋጋውን ዝቅ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፰ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ እንዳለ ሆኖ በድንጋጌው ይዘት ላይ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ "ማንም ሰው" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ሙሉ ባለዋጋነታቸውን እንደያዙ አስመስሎ እንዲዘዋወሩና በሕዝብ እጅ እንዲገቡ በማቀድ" የሚለው ሀረግ እንዲጨመርበት ተደርጓል። ይህ ወንጀል ከባድ በመሆኑ በድንጋጌው የተመደበው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ከወንጀሉ ክብደት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ስለሆነ "እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል" እንዲል ሆኖ ተሻሽሎአል። ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በቀር ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

<u>የቀድሞው ድንጋጌዎች የቦታ አቀማመጥ ለውጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸ (፩) ድንጋጌ አንቀጽ ፫፻፶፱፣ የቁጥር ፫፻፷፱ ድንጋጌ ደግሞ አንቀጽ ፫፷፩ ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል።

ይህ የሆነበት ምክንያት በቁጥር ፫፻፸ ድንጋጌ ላይ "የሀሰት ገንዘብን ባገር ስለማስገባት፣ ስለ መግዛት፣ በአደራ አስቀማጭነት ስለመያዝና ለስጦታ ስለማቅረብ" ተብሎ የተገለጸው ወንጀል በቁጥር ፫፷፱ ድንጋጌ ላይ ከተገለጸው የማዘዋወር ድርጊት በፊት መግባቱ በይበልጥ ተስማሚ በመሆኑና ከፊተኞቹ አንቀጾች ጋር የበለጠ ዝምድና ስላለው ነው። የቀድሞው ድንጋጌ ቁጥር ፫፻፸ (፪) ግን የአንቀጽ ፫፻፷፪ አካል ሆኖ ተረቅቋል።

አንቀጽ ፫፻፶፱ <u>ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት፣መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፶፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ የሀሰት ገንዘብን ብቻ ማመልከቱ ቀርቶ ከይዘቱ ጋር ተስማሚ እንዲሆን ከዚህ በላይ በተቀመጠው ዓይነት ተሻሽሏል።

ድንጋጌው የሀሰት ገንዘብን ብቻ ሳይሆን የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን እንዲያካትት ተደርጓል። በተጨማሪም "... እንዲገበያይባቸው ወይም እንዲዘዋወሩ ለማድረግ በማሰብ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ" የሚል ሐረግ ብቻ በአንቀጹ ውስጥ ተካትቶ የነበረ ሲሆን "ከአገሩ ያስወጣ" የሚል ሐረግ እንዲጨመር ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፷ <u>የማዘዋወር አሳብ ግምት</u>

ይህ አዲስ አንቀጽ ሲሆን እንዲገባ ያስፈለገበት ምክንያት ከአንቀጽ ፫፻፶፰ እስከ አንቀጽ ፫፻፶፱ የተገለፁትን ወንጀሎች በተመለከተ ድርጊቶቹ የተፈፀሙት በማዛወር አቅድ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ እንዲያስረዳ ከማድረግ ይልቅ በተገለጸው ዕቅድ እንዳልሆነ ማስረዳቱ ለአድራጊው ቀላል በመሆኑ ይህን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

አንቀጽ ፫፻፷፩ <u>ማዘዋወር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

ቀደም ሲል የቁጥር ፫፻፸ ድንጋጌ የነበረው ቦታውን ለቅቆ እዚህ የገባ ሲሆን ስያሜው ተስተካክሎ ተረቅቋል። በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን በተለይ ንዑስ አንቀጽ (፪) በንዑስ ፊደላት ተከፍሎ ተረቅቋል።

አንቀጽ ፫፻፷፪ <u>ቀላል ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸ (፪) ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ ድንጋጌ የሰፈረው አሳብ በቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸(፪) ድንጋጌ የነበረው ሲሆን በአዲስ መልክ ራሱን ችሎ ተረቅቋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የዚህ ዓይነቱን ቀላል ሁኔታ ሊሸፍን የሚገባው የቀድሞው የቁጥር ፫፻፸ (፩) ድንጋጌ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፪ የተመለከተውን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከአንቀጽ ፫፻፶፯-፫፻፷፫ ባሉት አንቀጾች ስር የገንዘቡ መጠን አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወንጀሉ አነስተኛ ሲሆን ቅጣቱም በቀላል እስራት ሊያስቀጣ እንደሚገባ በመታመኑና ድግግሞሽን ለማስወገድ በማታሰቡ ነው።

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>የታወቁ ማህተሞች፣ ቴምብሮችን፣</u>
<u>ምልክቶችን፣ ሚዛኖችንና መለኪያዎችን ወደሐሰተኛነት መለወጥ</u>

የምዕራፉ ስያሜ "ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ምልክቶችን፣ በህግ <u>የታወቁትን</u> ሚዛኖችንና መለኪያዎችን ወደ ሀሰተኛነት ስለ መለወጥ" ይል የነበረ ሲሆን "የታወቁትን" የሚለው ቃል ገላጭነቱ ለተዘረዘሩት ሁሉ መሆን ስለሚገባው በሐረጉ መግቢያ ላይ እንዲገባ ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፷፫ <u>የመንግስት ማህተሞችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ ወይም በማህተሞች ያለአግባብ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፫ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜና በንዑስ ቁጥር (፩) "የንጉሠ ነገሥቱን" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የመንግስት" የሚለው ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት የወንጀሉ ድርጊቶች የአፈፃፀም ዓይነቶች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል

www.abyssinialaw.com

እንዲገባ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ)"መብት ሳይኖረው" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ተሰርዞአል፤ ምክንያቱም ማንም ሰው መብት ይኑረውም አይኑረውም ያለአግባብ የሰራበት እስከሆነ ድረስ ተጠያቂ መሆን እንደሚገባው ግልጽ በመሆኑ ነው:: በተጨማሪም በዚህ ሕግ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) እና (፪) ለተመለከቱት የወንጀል አፈፃፀም ዓይነቶች የተመደቡት ቅጣቶች አነስተኛ ሆነው ስለተገመቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በንዑስ ቁጥር (፩) አነስተኛው ቅጣት የሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ከፍተኛ በመሆኑ ዝቅ እንዲል ማድረግ ስለሚያስፈልግ፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) "ከሶስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት" የሚለው ሐረግ ተተክቶአል:: በንዑስ ቁጥር (፪) "እንደሚያደርስ ታውቆ ይኸውም" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዞአል:: በዚሁ ንዑስ ቁጥር "ከፍ ያለ ግምት ያለው ጉዳት" ከሚለው ሐረግ ውስጥ አስፈላጊ ያልሆኑና ለውጥ የሚያስከትሉ ቃሎችን በማውጣት "ከፍተኛ ጉዳት" የሚል ሐረግ እንዲተካ ተደርጓል:: ቅጣቱንም በሚመለከት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ቢባል ወንጀሉ በአገር ጥቅም ወይም መብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ በአንድ ዓመት ጽኑ እሥራት ብቻም ለመቅጣት ስለሚቻልና ይኸውም ከወንጀሉ ክብደት ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ቅጣት ስለሆነ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አስፈላጊ ከሆነ እንደወንጀሉ ክብደት የጽኑ እሥራት ቅጣት ለመወሰን እንዲቻል "ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል::" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: በዚህ መሠረት መነሻና መድረሻ ቅጣቱ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል::

## አንቀጽ ፫፻፷፬ <u>የሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅቶችን ማህተም ወደ ሐሰት መለወጥና በማህተሞቹ ያለአግባብ መሥራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፬ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "የሕዝብ አገልግሎት ያላቸውን" የሚለው ሐረግ ከመንግስታዊ ድርጅቶች ውጭ የሚገኙትን ለመለየት የገባ ቢመስልም ጠቃሚነት ያለው ባለመሆኑ እንዲወጣ ተደርጓል:: ቀደም ሲል ያልገባው "ወደ ሐሰት" የሚለው ሐረግ ስለመለወጥ ከሚለው ቃል በፊት በመግባቱ የተለወጠው ማህተም ምንነት ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል:: የቁጥር ፫፻፹፪ ይዘት ከመንግስት ማህተሞች ውጭ የሌሎች ድርጅቶችን ማህተሞችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ ወይም አስመስሎ መሥራት ህብረተሰቡን የሚጎዳ ድርጊት በመሆኑና ይህም ወንጀል መሆኑ ተገልጾ እንዲደነገግ አስፈላጊ ስለሆነ በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) በተመለከተው ውስጥ "የሕዝብ ጉዳይ ማከናወኛ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የሆነውን" በሚለው ምትክ "የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅትን" የሚለው ሀረግ እንዲተካ ተደርግዋል:: "ማህተሙን የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራበት" የሚለው ሐረግ ማህተሙ እንዴት እንደሚለወጥ ወይም እንዴት እንደሚሠራበት ባለመነገሩ ግልጽ ስላልሆነ "ማህተም" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ወደ ሐሰተኛነት" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: እንዲሁም "ወይም" ከሚለው ቃል በኋላ "የሠራበት እንደሆነ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ወደ ሀሰተኛነት በተለወጠው ማኅተም" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል:: ማህተሞችን አስመስሎ መሥራት ብቻ ሳይሆን ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠው ወይም በተሠራው ማህተም መገልገልም መንግስትንና ሕዝብን የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም ስለሆነ በዚህ አኳያ የሚፈፀም ወንጀል የሚያስቀጣ መሆን ይገባዋል:: ስለዚህ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ከዚህ በላይ በተሻሻለው ዓይነት "የሕዝብ አገልግሎት ወይም የግል ድርጅትን ማሕተም ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም ወደ ሀሰተኛነት በተለወጠው ማሕተም የተገለገለ" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል:: "ወይም" የሚለው ቃል በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ ላይ ያለቦታው የገባ ስለሆነ ከዚያ ተሰርዞ

www.abyssinialaw.com

በፊደል ተራ (ሀ) ላይ ከተመለከተው አገላለጽ መጨረሻ እንዲጻፍ ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት ቅጣት "እስከ አምስት ዓመት" በሚለው ተሻሽሎአል:: በንዑስ ቁጥር (፪) "ቅጣቱ እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ ይችላል" የሚለው ሐረግ ምን ዓይነት ቅጣት መሆኑን ስለማይገልጽ "ወንጀሉ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

አንቀጽ ፫፻፷፭ <u>የታወቁ ምልክቶችን ወደ ሐሰት መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፭ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ እንዲሁም በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ባሉት ድንጋጌዎች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል:: ቅጣቱን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እንደተመለከተው የመደበኛው ወንጀል ቅጣት ከሦስት ወር እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት የተደገፈ ሲሆን፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ የተደነገገው አማራጭ የገንዘብ ቅጣት እንዲሰረዝ ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፷፮ <u>ዋጋ ያላቸውን የታወቁ ቴምብሮች ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፮ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "ግልጽ የሆኑ" በሚለው ሐረግ ምትክ "የታወቁ" የሚለው ቃል ግልጽ የሚያደርገው ሆኖ ስለተገኘ በተሻሻለው አንቀጽ ስያሜ ውስጥ እንዲገባ ተደርጎአል:: በድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) "ከዚህ በላይ የተመለከተውን አቅድ አግቡ ለማድረስ ሲል" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "እንደእውነተኛ ወይም እንዳልተሠራባቸው በማድረግ ሊሠራባቸው ወይም ሌሎች እንዲሠሩባቸው በማሰብ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: የዚሁ ንዑስ ቁጥር ማሰሪያ ከሆነው ዓረፍተ ነገር ውስጥ "በሶስት ወር እስራት" የሚለው ሀረግ የእሥራት ቅጣቱ አስፈላጊ ሲሆን ከሶስት ወር አስበልጦ ለመወሰን ስለሚያስችልና ከሶስት ወር የማያልፍ ቀላል አስራትም ከወንጀሉ ጋራ የማይመዛዘን አነስተኛ ቅጣት ሰለሚሆን ተሰርዞ "ቢያንስ በሶስት ወር ቀላል እስራት" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: እንዲሁም ከዚሁ ዓረፍተ ነገር "ወይም ጥፋቱ ከፍ ያለ ሆኖ ሲገመት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል እሥራትና በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል":: በሚለው ውስጥ "እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል" በሚል ተስተካክሎአል:: "በገንዘብ" የሚለው ቃል መቀጮ ምንግዜም በገንዘብ በመሆኑ ድጋሚ ቃል ስለሆነ ተሰርዞአል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ጥፋቱ ቀላል በሆነ ጊዜ መቀጮ ብቻ ሊወሰን እንደሚቻል ተደርጎ ተረቅቋል::

በተጨማሪም 'በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተሻሽሏል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፫፻፷፯ <u>የመመዘኛ ክብደቶችንና መለኪያዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ አቀራረቡ ተቃንቷል። በተለይም በድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት ልዩ ልዩ ድርጊቶች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከተው ድንጋጌ ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። ጥፋቱ ቀላል ሲሆን በወንጀለኛው ላይ የቀላል እሥራትና የመቀጮ ቅጣት መወሰን ከወንጀሉ ጋር የማይመዛዘን ያለአግባብ የከበደ ቅጣት ስለሚሆን በንዑስ አንቀጽ (፪) ፍርድ ቤቱ ከሚለው ንዑስ ሐረግ ቀጥሎ "እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ለመወሰን ይችላል።" የሚለው ሐረግ ገብቷል።

አንቀጽ ፫፻፷፰ <u>ከአገር ማስወጣት ወደ አገር ማስገባት፣ መግዛት፣ በአደራ ማስቀመጥና ማቅረብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፰ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜውና በይዘቱ ላይ "ከአገር ማስወጣትን" እንዲያካትት ተደርጓል።

ሐሰተኛ መሆናቸውን ወይም ወደ ሐሰተኛነት መለወጣቸውን በማወቅ ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ቴምብርነት ያላቸው ወረቀቶችን፣ ምልክቶችን በግልጽ የታወቁ መመዘኛ ክብደቶችን ወይም መለኪያዎችን ወደአገር ውስጥ ማስገባት፣ መግዛት፣ በአደራ ማስቀመጥ ወይም ለሽያጭ ወይም ለስጦታ ማቅረብ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑ ከተደነገገ በኋላ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ "እስከ ሁለት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ነው" የሚለው ሀረግ መጠነኛ ማስተካከያዎች ከተደረጉበት በኋላ ስለቅጣቱ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል።" በሚል ተስተካክሎአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት አነስተኛ ማሻሻያዎች በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተቃንቷል።

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>
<u>የወል ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ ፫፻፷፱ <u>የሚታለል አሳብ ሳይኖር አስመስሎ መሥራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፱ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜው ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሎ ተረቅቋል። በንዑስ አንቀጽ (፪) በፊደል ተራ (ለ) ላይ "ወደውጭ አገር ማስወጣትን" በማካተት ተረቅቋል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፷ <u>በገንዘብ፣ በግዴታ ወይም በዋስትና ሰነዶች ወይም በታወቁ ምልክቶች፣ ቴምብሮች ወይም ማህተሞች ላይ አደጋ ማድረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ገንዘብ" ከሚለው ቃል በኋላ ያለው "ግልጽ በሆነ" የሚለው ገላጭ ሐረግ ጠቃሚ አገልግሎት የሌለው በመሆኑ ተሰርዞአል። ገንዘብ ከሚለው ቃል በመቀጠል የማይገባው "በባለ ዋጋ ነገሮች ወይም ሰነዶች" በሚለው ሀረግ ምትክ "በግዴታ ወይም በዋስትና ሰነዶች" የሚለው ሐረግ እንዲተካ ተደርጎአል። ድንጋጌው "በታወቁ ምልክቶች" እንዲሁም "ቴምብሮች" ላይ አደጋ የማድረስ ወንጀልም የሚያስቀጣ መሆኑን ለማሳየት በስያሜው ላይ እንዲጨመሩ ተደርጎአል። ድንጋጌው "ለገንዘብ፣ ለግዴታ ወይም ለዋስትና ሰነዶች ለታወቁ መለያ ምልክቶች፣ ለቴምብሮች፣ ለባለሥልጣን ማህተሞች (ቲተሮች) ወይም ለማህተም ማተሚያ መሥሪያ የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች፣ ፎርሞች፣ ከውሮች፣ ወረቀቶች፣ ሞዴሎች፣ ወይም ማንኛቸውንም ሌሎች ዓይነት እቃዎችን ወይም መሣሪያዎችን" የሚመለከት መሆኑን ለማሳየት በግልጽ እንዲቀመጡ ተደርጎአል።

በንዑስ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተደነገጉት ለየብቻቸው እንደሚያስቀጡ ለማሳየት በንዑስ ፊደል (ሀ) መጨረሻ ወይም የሚል ቃል ገብቶአል። ቅጣቱን በሚመለከት "እስከ ስድስት ወር ለመድረስ በሚችል እሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" የሚለው ሐረግ ተሻሽሎ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል" በሚለው ሐረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ማሻሻያዎች በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፷፩ <u>ሐሰተኛ ነገሮችን ለመሥራት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መሥሪያዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "የሐሰት ነገር" በሚለው ሐረግ ምትክ "ሐሰተኛ ነገሮችን ለመሥራት የሚያገለግሉ" በሚለው ሐረግ ቢተካ የበለጠ ግልጽ እንደሚያደርገው ታምኖበታል። በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ "ያለመብቱና ያለአግባብ ሲሠራበት በማሰብ ሐሰተኛ የገንዘብ ወረቀቶችን" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በሕገወጥ መንገድ ሊሰራበት በማሰብ" የሚለው ሐረግ ብቻ እንዲገባ ተደርጎአል። በመቀጠልም በድንጋጌው ላይ "የባንክ ወረቀቶችን" በሚለው ሀረግ ምትክ "የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶችን" የሚለው ሀረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ የቅጣት ሁኔታ አገላለጽ "እጅግ ቢያንስ በስድስት ወር እስራት ይቀጣል" የሚለው አነጋገር "ከስድስት ወር ባላነሰ ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል በሚል ተሻሽሎአል። የመቀጮ ቅጣትም በተጨማሪነት እንዲኖረው ተደርጎአል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተመለከተው የመሥሪያ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን ብሔራዊ ገንዘቦችን፣ የመንግስት ወይም የመንግስት ባለሥልጣን ማህተሞችን /ቲተሮችን/ ሐሰተኛ አድርጎ ወይም አስመስሎ ለመሥራት የሚያገለግሉ የሆኑ እንደሆነ በአገርና በሕዝብ ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ እንደነዚህ ያሉትን የመሥሪያ ዘዴዎችና መሣሪያዎች በመሥራት ወንጀለኛ ለሆነው ሰው የተመደበው የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት በቂና ተመጣጣኝ ቅጣት ሊሆን አይችልም። ከዚህም በቀር "ለመፍረድ ይችላል" የሚለው ሐረግ ፍርድ ቤቱ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንኳን እንዲፈረድ

www.abyssinialaw.com

የሚያስገድድ ድንጋጌ ባለመሆኑ ለወንጀሉ ተመጣጣኝ ቅጣት አልተመደበለትም፡፡ ( ... "ፍርድ ቤቱ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ የተመለከተው "እስከ አምስት ዓመት" የ... ንዑስ ሐረግ ተሰርዞ "እስከ ሰባት ዓመት" በሚል ንዑስ ሀረግ ተተክቶአል፡፡ "ለመ... ይችላል" የሚለው ማሠሪያ ግስ የሆነው ድንጋጌው የመጨረሻ ሐረግም ተሰርዞ "ይ... በሚል ቃል ተተክቶአል፡፡

ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ማሻሻያዎች በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተ... ተደርጎበት አቀራረቡ ከተቃና በኋላ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ሆኖ ገብቶአል፡፡

አንቀጽ ፫፻፷፮ <u>የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "ልዩ አስተያየት ስለሚደረግለት ጉዳይ" ከማለት ይልቅ "የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች" ቢባል ከድንጋጌው ይዘት ጋር አብሮ ይሄዳል በሚል ተሻሽሎአል፡፡ በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ "በዚህ አንቀጽ" በሚለው ሐረግ ምትክ "በዚህ ርዕስ " የሚል ሐረግ ገብቶአል፡፡ በመቀጠልም "አንደኛውን በመሥራት ወይም በማዘጋጀት ጉዳይ ተካፋይ በሆነው ሰው" በሚለው ንዑስ ሐረግ ምትክ "አንደኛውን በፈጸመ ሰው" የሚለው ሐረግ በተለያየ ደረጃ ለወንጀሉ ተግባር ተካፋይ የሆኑ ሰዎችን ስለሚያካትት ሌሎች አሳስፈላጊ ሀረጎች እንዲወጡ ተደርገዋል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፫፻፹ (፩) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንዱ ብቻ እንኳን ቢያጋጥም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በማቃለል ለመወሰን የሚችል መሆኑን ለማመለከት በፊደል ተራ (ለ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል፡፡ ከዚህም በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ አቀራረቡ ተቃንቶአል፡፡

አንቀጽ ፫፻፷፯ <u>ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "ቅጣትን የሚያከብዱ ጉዳዮችና ተጨማሪ ቅጣቶች" የሚለው ተሻሽሎ "ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች" በሚል ተተክቶአል፡፡ የድንጋጌውን ይዘት በተመለከተ ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል በዚህ ሕግ ጠቅላላ ክፍል የተመለከቱትን የቅጣት ማክበድ ደንቦች እና የመውረስ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆኖ ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ ስሜት በተፈፀመ ጊዜ መቀጮው እስከ ብር ሁለት መቶ ሺህ ለመድረስ ይችላል፡፡ ሐሰተኛ ገንዘብ የመሥራት ወንጀል ተፈጽሞ እንደሆነ መቀጮው እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር ለመድረስ ይችላል በሚል የድንጋጌው ይዘት እንዲሻሻል ተደርጎአል፡፡

አንቀጽ ፫፻፷፰ <u>የውጭ አገር መንግሥታትን ጥቅሞች መጠበቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አራተኛ መጽሐፍ
## በሕዝብ ጥቅሞችና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ርእስ አንድ
## በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## ሐሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፣ ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ማጥፋት

### አንቀጽ ፫፻፸፭ በግዙፍ የሚፈፀም ሐሰት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፸፭ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ከላይ በተመለከተው ዓይነት ተሻሽሏል። መግቢያው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በፊደል ተራ (ሀ) " ለሕጋዊ ውሳኔ አሰጣጥ የሚረዳ ማስረጃ" የሚለው ሐረግ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር ቀረቤታ ባለው" ሕጋዊ ክርክሮች ሲካሄዱ በማስረጃነት የሚቀርቡ " በሚል ተተክቷል።

### አንቀጽ ፫፻፸፮ ረቂቅ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ሐሰት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፸፮ ሆኖ ገብቷል።

በይዘቱ ውስጥ "ሀሰተኛ የሆኑ ቃላትን ጣልቃ በማግባት" የሚለው ሐረግ ተለውጦ "ሐሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ" በሚል ሐረግ ቢተካ ብዙ ሁኔታዎች በስፋት ሊሸፍን እንደሚችል ታምኖበታል። ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

### አንቀጽ ፫፻፸፯ ልዩ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፸፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ስለ ልዩ ልዩ" በሚለው ሐረግ ምትክ "ልዩ" በሚል ቃል ተስተካክሏል። በድንጋጌው መግቢያ ላይ "ከዚህ በላይ የተመለከቱትን የወንጀል ተግባሮች ለመፈፀም በማቀድ" የሚለው ሐረግ" ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፸፮ በተመለከተው የወንጀል አሳብ በመነሳት" በሚል ተቃንቶ ገብቶአል። ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በተጨማሪም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

### አንቀጽ ፫፻፸፰ በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፸፰ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ይዘት ላይ "..... የሀሰት ነገርን በመፍጠር ወንጀል ውስጥ ተካፋይ ሳይሆን ሌላው ሰው በፈጠረው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞአል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሀሰተኛ ሰነድ የፈጠረው ወይም ወደሀሰት የለወጠው ሰው በአንቀጽ ፫፸፭/፮ መሠረት ሳይቀጣ ቢችልም በአንቀጽ ፫፸፰ መሠረት በፈጠረው ሀሰተኛ ሰነድ የሚቀጣበት ጊዜ ሊኖር በመቻሉ ነው።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፫፻፹፱ <u>መንግሥታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ "ሰነዶች ወደሐሰት ስለመለወጥ" ከሚለው ሐረግ በተጨማሪ ስፋት እንዲኖረው ለማድረግ የተሻሻለው ስያሜ "ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደሐሰት መለወጥ" የሚል ሐረግ ተጨምሮበት እንዲጻፍ ተደርጓል፡ በስያሜው መጨረሻ "ስለሚሠራ ወንጀል" የሚለው ሐረግ ጠቃሚነቱ የጎላ ባለመሆኑ እንዲሠረዝ ተደርጎአል። በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ "ሰነዶችን ወደሐሰተኛ የመለወጡ ወንጀል በልዩ ልዩ አድራጎት ረገድ የተፈፀመው ወይም የተገለገለበት" የሚለው ሐረግ ተሻሽሎ" በዚህ ምዕራፍ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ የተፈፀመው" በሚል ሐረግ እንዲተካ ተደርጎአል። "የመንግሥት መዝገብ" የሚለው ሐረግ "የሕዝብ ወይም የመንግሥት መዝገብ" በሚል ሐረግ እንዲለወጥ ተደርጓል።

በቁጥር ፫፻፸፮ (፪) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት የወንጀል ድርጊት ዓይነቶች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ለ) ከተመለከተው መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። "ቅጣቱ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል" የሚለው ሀረግ በንዑስ ቁጥር (፫) የተደነገገው ቅጣትም የወንጀሉ አፈፃፀም በጣም ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቅጣት ስለሚሆን ለእንደዚህ ያለው ሁኔታ አግባብነት አይኖረውም። በመንግስት ሰነዶችና በሕዝብ ሰነዶች ላይ የሐሰት ሥራ በመሠራት በሕብረተሰቡ ላይ ከባድ በደል ሊደርስ ስለሚችልና እንደዚህ ያለው ወንጀል አፈፃፀም ከባድ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜም ጥፋተኛው ከአሥራ አምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እሥራት ብቻ ቢቀጣ በቂ ቅጣት አግኝቷል ሊባል ስለማይችል "ቅጣቱ ከአምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ሊደረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል። የወንጀሉ አፈፃፀም በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።" በሚል ተሻሽሎ አዲስ ዓረፍተ-ነገር እንዲጨመርበት ተደርጎአል።

አንቀጽ ፫፻፺ <u>ሰነዶችን ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር (፩) "የሰረዘ" የሚለው "ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረገ" በሚለው ተተክቷል። ይህም ከእንግሊዝኛው suppress ከሚለው ቃል ጋር ቀረቤታ ያለው ነው። በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "በዘመዱ ላይ የቅርብ ዝምድና ባለው ሰው ላይ" በሚለው ሀረግ ውስጥ "በዘመዱ" የሚለው "በቤተሰቡ አባል" በሚለው ተተክቷል። እንዲሁም "ከወንጀለኛው ጋራ በጥቅም ወይም በፍቅር በተሳሰረ ወይም አብሮት በሚኖር ሰው ላይ" እንዲሆን ተደርጓል። "በጥቅምና" ከሚለው ቃል ላይ "ና" ተሰርዞ "ወይም" የሚለው ቃል እንዲገባ የተደረገበት ምክንያት የዝርዝር ሁኔታዎች ድምር መሆኑ ቀርቶ እያንዳንዱ ሁኔታ እንደሚሟያ ነጥብ መወሰዱ አግባብ በመሆኑ ነው። ሰዎችም የሚተሳሰሩት በጥቅም ወይም አብሮ በመኖር ብቻ ሳይሆን በፍቅር ጭምር ሊሆን ስለሚችል፣ "በጥቅም" ከሚለው ቀጥሎ "ወይም በፍቅር" የሚለው ሀረግ ሊገባ ችሏል።

www.abyssinialaw.com

ቅጣትን በሚመለከት በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው አዲስ መስመር እስከ ሁለት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ደግሞ እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት በመመደብ የተደነገጉት ቅጣቶች በመጠኑ ከፍ ማለት እንደሚገባቸው ተገቢ ሆኖ ተገኝቶአል። ስለዚህ በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ቅጣት ተሰርዞ "ነገሩ ቀላል ሲሆን እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፤ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል።" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በቀር ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፹፭ <u>መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሠነዶችን ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፭ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፩) "እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ሊሆን ይችላል። " በሚል ሐረግ የተገለፀው ቅጣት በመንግስት ጥቅም ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመንግስትን ወይም የወታደራዊ ሠነድ ማጥፋት ከባድ ወንጀል በመሆኑ ቅጣቱ ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠንና አነስተኛ ነው። ስለዚህ "ቅጣቱ እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ሊሆን ይችላል።" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ ቅጣቱ "እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ነው።" በሚል ሐረግ ተተክቷል። ወንጀሉን የፈፀመው እነዚህን የመሳሰሉትን ሰነዶች እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ፣ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት የተሰጠው ሠራተኛ ከሆነ ወንጀሉ ከባድ ስለሚሆን ቅጣቱ በዚያው መጠን መክበድ ስለሚገባው በንዑስ አንቀጽ (፪) ቅጣቱ "እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ነው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ቅጣቱ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ነው።" በሚል ሀረግ ተተክቷል። ወንጀሉ በቸልተኛነት የተፈፀመ ሲሆን ያስቀጣል ተብሎ የተደነገገው "እስከ አንድ ዓመት ለመድረስ የሚችል የቀላል እሥራት ቅጣት" ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ በመሆኑ ሐረጉ ተሰርዞ "ቅጣቱ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ነው" በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

አንቀጽ ፫፻፹፮ <u>የንግድ ወይም ተላላፊ የዋስትና ሰነዶችን ወደሐሰት መለወጥና ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር ቀረቤታ ያለው "ተላላፊ የዋስትና ሰነዶች" የሚለው ሐረግ ተጨምሮበታል። በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) ላይ "የማዘዣ ሰነድ" የሚለው "የተስፋ ሰነድ" በሚለው ተለውጧል። "የመግቢያ ካርድ" ዘመናዊ ሰነድ በመሆኑ እንዲካተት ተደርጓል። በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩት ነገሮች ተመሳሳይ በመሆናቸው በንዑስ ፊደላት መከፋፈላቸው ቀርቶ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር ዝርዝራቸው በፊደል ተራ ሳይከፋፈል ተጽፏል።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ "የተደረገው ወንጀል የዚህን ዓይነት ሰነድ ወይም ማስረጃ የማጥፋት እንደሆነ ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስራት ነው።" የሚለው ግልጽነት እንዲኖረውና ቅጣቱ እንዲከብድ ተደርጓል። ይኸውም "በአንቀጽ ፫፻፹፭ የተመለከተው ድርጊት በእነዚህ ሰነዶች ወይም

www.abyssinialaw.com



ማስረጃዎች ላይ የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት ይሆናል::" ተብሎ ከተረቀቀ በኋላ እራሱን የቻለ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ቸልተኛነትን የሚመለከት ሲሆን እራሱን ችሎ ቅጣት ስለሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲሆን ተደርጓል::

አንቀጽ ፫፻፹፫ <u>እንደዋና የሚቆጠር ጽሑፍ ወይም ትክክለኛ ግልባጭ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ላይ "ትክክለኛነታቸው በባለሥልጣን የተረጋገጠላቸው ወይም የዋናው ትክክለኛ ግልባጮች መሆናቸው የተመሰከረላቸው ሰነዶች ሁሉ በሕጉ አግባብና ሥርዓት በዋናው ሰነድ ምትክ የሚሆኑ ወይም እንደዋና ማስረጃ የሚቆጠሩ ናቸው::" በሚል የተደነገገው እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰነዶች ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ ወይም እነዚህን አስመስሎ መፍጠር ወይም ማጥፋት እንደሚያስቀጣ በግልጽ የሚያመለክት ሐረግ ስለሌለ ግልጽ ለማድረግ ስለቅጣት ወይም ከቅጣት ጋር የተዛመደ ሐረግ ተጨምሮ የተሟላ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ የድንጋጌው ማሠሪያ አንቀጽ የሆነውን "ናቸው" የሚለውን የመጨረሻ ቃል በመሰረዝ "ግልባጮች ላይ የሚፈጸም ወደ ሐሰተኛነት የመለወጥ ወይም የማጥፋት ድርጊት አግባብ ባላቸው በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ያስቀጣል::" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጎአል::

አንቀጽ ፫፻፹፬ <u>የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ወረቀቶችንና የማጓጓዣ ወረቀቶችን ወደ ሐሰት መለወጥና በነዚሁ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፬ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ከሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ወረቀቶች በተጨማሪ "የማጓጓዣ ወረቀቶችን" ጭምር እንዲያካትት ተደርጎ ተቃንቶአል:: በድንጋጌው መግቢያ ላይ "ሕገወጥ የሆነ ጥቅም" የሚለው ሐረግ "ተገቢ ያልሆነ ጥቅም" እንዲባል ሲደረግ "በማቀድ" የሚለው ቃል "በማሰብ" በሚለው ተተክቶአል:: በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) ላይ "መብት ሣይሰጠው" የሚለው ሀረግ "ሕጋዊ ሥልጣን ሳይኖረው" በሚል ሐረግ እንዲተካ ተደርጎአል:: በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) ውስጥ "ቲኬት" ከሚለው ቃል በኋላ "ደረሰኝ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ መሳክ" የሚለው ሐረግ እንዲጨመር ተደርጎአል:: ለንዑስ ቁጥር (፩) የተወሰነው ቅጣት "እጅግ ቢያንስ በአንድ ወር እስራትና በመቀጮ ይቀጣል:: ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል እሥራትና በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" የሚለው ሐረግ በጣም የተንዛዛ በመሆኑ አጠር ባለ ሁኔታ "በቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል" በሚለው ሐረግ እንዲተካ ተደርጎአል:: የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ "ያገለገሉትን ወረቀቶች" በሚለው ሐረግ ምትክ ድንጋጌው የሚመለከተውን ጉዳይ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ "ያገለገሉትን ቲኬቶች፣ ደረሰኞች ወይም የመጓጓዣ ሰነዶች" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሁለት
## በምስክር ወረቀቶች ላይ የሚደረግ ሐሰት

### አንቀጽ ፫፻፹፭ ሐሰተኛ ምስክር ወረቀቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፭ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያው ላይ መጠነኛ ለውጥ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) ላይ "ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ" ከሚለው ቀጥሎ "አስመስሎ የሠራ" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል:: ሐሰተኝነቱን እያወቀ ይህን የመሳሰለውን ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ ውን ወይም በሐሰት የተሰራውን ሰነድ ለሌላ ሰው የሰጠ ወይም እንዲገለገልበት ያደረገ" የሚለው "... እያወቀ ይህን የመሳሰለውን ሰነድ እንዲገለገልበት ለሌላ ሰው የሰጠ ..." በሚለው ተለውጧል:: "... በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ውስጥም ለእርሱ አገልግሎት ያልታሰበውን ..." የሚለው ሐረግ ተጨምሯል:: ከንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ስር ባለው ፓራግራፍም "የመለያ ምስክር ወረቀት" በሚል ሐረግ ምትክ መታወቂያ ወረቀት"፣ በሚል ሐረግ ተተክቷል:: "ሰነዱ የህዝብ ጉዳይም የሚመለከት ሲሆን መነሻ ቅጣቱ ወደ ሶስት ወር ከፍ ተደርጓል:: በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል::

ወንጀሉ የተሠራው እነዚህን የመሳሰሉትን ሰነዶች እንዲያዘጋጅ፣ እንዲያስቀምጥ፣ እንዲጠብቅ ወይም እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ሠራተኛ እንደሆነ እና ይህንንም ወንጀል የሠራው በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ ሳያቅድ ቢሆንም ከባድ ኃላፊነት እያለበት እንዲህ ያለውን ወንጀል ከሠራ ቢያንስ በስድስት ወር ቀላለ እሥራት መቀጣት ይገባዋል:: እንደወንጀሉም ክብደት ቅጣቱ በቀላል እሥራትና በመቀጮ እንዲሆን የሚያስፈለግበትም ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል:: ስለዚህ በንዑስ ቁጥር (፪) በመጀመሪያው አዲስ መስመር "ቅጣቱ እጅግ ቢያንስ የሶስት ወር እስራት ሆኖ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ወይም የገንዘብ መቀጮ ነው የሚለው" ሐረግ ተሰርዞ ቅጣቱ" ከስድስት ወር እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ወይም ሁለቱም ነው" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

ከላይ እንደተመለከተው የንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ እራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሲሆን የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲፈጸም እራሱን ችሎ የሚያስቀጣ በመሆኑ ነው:: እስከ አምስት መቶ ብር መቀጮ ያስቀጣ የነበረውም ተለውጦ እስከ አንድ ሺህ ብር እንዲያስቀጣ ሆኖ ተደንግጓል::

### አንቀጽ ፫፻፹፮ ሐሰተኛ የሆነ አፊሴላዊ ምስክርነት በማጭበርበር ማግኘት

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፫፻፺፬ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ከተቃና በኋላ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፮ ሆኖ ገብቶአል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፹፮ <u>ሐሰተኛ የሕክምና ምስክር ወረቀት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "... የህኪም ምስክርነት ለመስጠት መብት ያላቸው ማንኛዎቹም የዚሁ ዓይነት ሰዎች" የሚለው ሀረግና የዓረፍተ-ነገሩ ማሰሪያ በብዙ ቁጥር መጻፉ ቀርቶ በነጠላ ቁጥር እንዲጻፍ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት የወንጀል ሕጉ የአጻጻፍ ስልት በዚህ መልክ ከመሆኑም በላይ በብዙ ቁጥር መጻፉ ጥፋተኛው አንድ ሰው ከሆነ በወንጀል አይጠየቅም የሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ነው። በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው ፓራግራፍ "እስከ አንድ አመት ለመድረስ በሚችል እሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" በማለት የተደነገገው ቅጣት ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቅጣት ስለሆነ ተሰርዞ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል። ወንጀሉ በተደጋገመ ጊዜ የሞያውን ሥራ በሚመለከት የሚወሰነው ተጨማሪ ቅጣት የፀና ይሆናል/አንቀጽ ፮፻፹፫ (ሐ)/።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) እና (፫) የተመለከቱት ቅጣቶችም ከወንጀሉ ጋር ሲነጻጸሩ አነስተኛ ናቸው። ስለዚህም በንዑስ ቁጥር (፪) "የእሥራት ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ሆኖ ከገንዘብ መቀጮ ጋር ይጣመራል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቅጣቱ እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ ይሆናል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፫) ደግሞ፣ በንዑስ ቁጥር (፩) ለተመለከተው ጥፋት የሚወሰንበት ቅጣት እጅግ ቢያንስ የአንድ ወር እሥራት ነው።" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው ወንጀል ከሶስት ዓመት ባላነሰ ቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። በዚህ ንዑስ ቁጥር መጨረሻ " በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተመለከተው ወንጀል እስከ አሥራ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራትና እስከ ብር መቶ ሺህ ሊደርስ የሚችል የገንዘብ መቀጮ ይሆናል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በቀር ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፹፯ <u>ተደራራቢ ወንጀሎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፯ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ይዘቱን በትክክል ስለማያመለክት ተሰርዞ "ተደራራቢ ወንጀሎች" በሚል ተተክቶአል። የድንጋጌውን ይዘት በሚመለከት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ እንዲቃና ተደርጓል።

አንቀጽ ፫፻፹፰ <u>ሐሰተኛ የቃል አሰጣጥና ምዝገባ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፰ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ወንጀሉን በትክክል ስለማያመለክት ተሰርዞ "ሐሰተኛ የቃል አሰጣጥና ምዝገባ" በሚል ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) በተለከተው ድንጋጌ መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በዚሁ በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻ "እስከ ሶስት ወር ሊደርስ በሚችል እሥራት ወይም እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ ይቀጣሉ" በማለት የተደነገገው ቅጣት በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ

www.abyssinialaw.com

(ሀ) እና (ለ) ከተገለጸው ወንጀል ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ስለሆነ ተሰርዞ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፪) "አድራጊው ወንጀሉን የሠራው በጥቅም ፍላጎት የሆነ እንደሆነ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "እጅግ ቢያንስ እሥራቱ ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት፣ የገንዘብ መቀጮ እስከ ደንበኛ ከፍተኛው መቀጮ ለመድረስ ይችላል" የሚለው ሐረግ የእሥራት ቅጣቱንና መቀጮውን በማጣመር በጥፋተኛው ላይ መወሰን ይቻል እንደሆነ ግልጽ ካለመሆኑም በላይ የቅጣቱ መነሻ የሆነው የአንድ ወር ቀላል እሥራት ከወንጀሉ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ስለሆነ ሐረጉ ተሰርዞ "ቅጣቱ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ቀላል እሥራትና መቀጮ ይሆናል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል፡፡

አንቀጽ ፫፻፺ <u>የሐሰት ሥራ ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና መሥሪያዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜና ይዘት ግልጽ እንዲሆን የቃላት ለውጦችና ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ለንዑስ ቁጥር (፩) የተወሰነው ቅጣት አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ "እጅግ ቢያንስ በሶስት ወር እሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል" በሚለው ሀረግ ተተክቶአል፡፡

የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል፡፡

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>ዕቃዎችን ወደ ሐሰት መለወጥ</u>

አንቀጽ ፫፻፺፩ <u>ዕቃዎችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ጥራታቸውን ማርከስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

ሌላውን ሰው ለማታለል በማቀዱ የንግድ ዕቃዎች ወደሐሰተኛነት በመለወጥ፣ አስመስሎ በመሥራት፣ ወይም ጥራታቸውን በማርከስ ወይም በማበላሸት ለሚፈጸም ወንጀል፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፫፻፺፱ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ እንደሚያስቀጣ የተደነገገው ቅጣት ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ቅጣት ስለሆነ "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከሶስት እስከ ሰባት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል፡፡ ከዚህም ሌላ ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፫፻፺፪ <u>ማዘዋወር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፪ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ ተለውጦና ተሻሽሎ "ማዘዋወር" ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ወደ ሐሰተኛነት የተለወጡትን፣ አስመስሎ የተሰሩትን ወይም ጥራታቸው የረከሰውን ወይም የተበላሹትን የንግድ ዕቃዎች እንደእውነተኛ፣ እንዳልተበላሹ፤ ወይም ምንም ጉድለት እንደሌለባቸው በማስመሰልና ሌላውን ሰው ለማታለል በማቀድ በልዩ ልዩ መንገድ በሕዝብ እጅ

www.abyssinialaw.com

እንዲዘዋወሩ ማድረግ በነጋዴዎችና በሸማቾች መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር የሸማቾቹን ሕዝብ ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት ስለሆነ ቀላል ወንጀል አይደለም:: ስለዚህ ለዚህ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻ በንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) የተመለከቱት ቅጣቶች ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠኑ አነስተኛ ቅጣቶች በመሆናቸው በንዑስ ቁጥር (፩) "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል.." በማለት በአማራጭ ቅጣት ለመወሰን የሚያስችለው ሐረግ ተሰርዞ "በአንቀጽ ፫፻፺፪ በተደነገገው ቅጣት ይቀጣል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: በዚህ መሠረት የወንጀሉ ድርጊት እስከ ሰባት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በመቀጮ የሚያስቀጣ ይሆናል ማለት ነው:: በንዑስ ቁጥር (፪) ደግሞ "የሚደርስበት ቅጣት እስከ አምስት መቶ ብር የሚደርስ መቀጮ ሊሆን ይችላል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ " እስከ አሥር ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ የሚያስቀጣው::" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ማሻሻያዎች በቀር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፺፫ <u>ዕቃዎችን ከውጭ ወደአገር ማስገባት፣ ወደውጭ መላክ፣ በእጅ ማድረግና ማከማቸት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፫ ሆኖ ገብቷል::

ወደሐሰተኛ የተለወጡትን ወይም አስመስሎ የተሰሩትን ወይም ጥራታቸው የረከሰውን ወይም የተበላሹትን የንግድ ዕቃዎች ሌላውን ሰው ለማታለል በማቀድ ወይም ለማታለያ የታሰቡ መሆኑን እያወቀ ከውጭ አገር ማስመጣት፣ መግዛት፣ በእጅ ማስገባት ወይም ማከማቸት የሕዝብን ጥቅምና የማኅበራዊ ኑሮን የሚጎዳ ወንጀል ስለሆነ ለዚህ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተመደበው የመቀጮ ቅጣት በቂ አይደለም:: "በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በቀላል እስራትና በመቀጮ" እንደሚያስቀጣ ተደርጎ ተለውጦአል:: ከዚህም በላይ ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፺፬ <u>ቅጣትን ማከበድና ተጨማሪ ቅጣቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፬ ሆኖ ገብቷል::

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን የወንጀል ተግባሮች ሙያው አድርጎ ለያዘ የኅብረተሰቡን ጥቅም ለሚጎዳ እንደዚህ ላለው አደገኛ ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፪/፩/ "ቅጣቱ እጅግ ቢያንስ የሶስት ወር እሥራትና እንደነገሩም ከባድነት መጠን እስከ አሥር ሺህ ብር ድረስ ሊደርስ የሚችል መቀጮ ነው" በሚል ሐረግ የተመለከተው ቅጣት በቂ አይደለም:: ስለዚህ ይኸው ስለቅጣቱ የሚገልጸው ሐረግ ተሰርዞ "ከአምስት እስከ አስር ዓመት ጽኑ እሥራትና እንደነገሩ ከባድነት ከብር አምስት ሺህ ባላነሰ መቀጮ ይቀጣል.." በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: ከዚህም ሌላ ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ በስያሜውና በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፺፭ <u>ጤናን በሚጎዳ አኳኋን የንግድ ዕቃን ወደ ሐሰት መለወጥና ጥራቱን ማርከስ</u>

ጤናን በሚጎዳ አኳኋን ዕቃን ወደሐሰት ስለመለወጥና ጥራቱን ስለማርከስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፫ የተደነገገው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፭ ሆኖ ገብቶአል::

www.abyssinialaw.com

## ርዕስ ሁለት
## የሕዝብ ጥቅምን የሚመለከት ምስጢርን መግለጽ

### አንቀጽ ፫፻፺፮ ወታደራዊ ምስጢርን መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፮ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲ ንዑስ ቁጥር (፩) ማንኛውም ወታደር ወይም በመከላከያ ኃይል አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ሰው ከዳትንና ስለላን በሚመለከት ከሚያስቀጡት ሁኔታዎች /አንቀጽ ፪፻፵፱-፪፻፶፫/ ውጭ በሥራው ወይም በወታደራዊ ግዳጅ ምክንያት ሊያውቃቸው የቻለውን በጠባያቸው ወይም ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት ሚስጥር ሆኖ እንዲጠበቁ የተደረጉትን ወይም ለሕዝብ እንዳይገለጹ የተከለከሉትን መረጃዎች፤ ሰነዶች ወይም ፍሬ ነገሮች ሥራው ወይም ግዳጁ ከተፈጸመ በኋላ ቢሆንም እንኳ የተባሉት ምስጢሮች ለሕዝብ የሚገለጹበት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሳይገለጹ ምስጢሩን መጠበቅ ስለሚገባው በዚሁ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎ ተቃንቶአል። በዚሁ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስለቅጣት የተመለከተው "እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ ሰባት አመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል" በሚል ሐረግ ተተክቶ ቅጣቱ በመጠኑ እንዲከብድ ተደርጎአል። በንዑስ አንቀጽ (፪) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በቀር ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቷል።

### አንቀጽ ፫፻፺፯ የሥራ ምስጢርን መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፯ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲፩(፩) "..የጦር መኮንኖች፣ የጸጥታ ጥበቃ ዘበኞች፣ የሕዝብ ጉዳይ ማከናወኛ መስሪያ ቤት ሠራተኞችና በጠቅላላውም እንደመንግስት ሹማምንትና ሠራተኞች ሆነው የሚቆጠሩ ማንኛዎቹም ሰዎች" በሚል ሀረግ የተዘረዘሩት በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፬፻፪ የመንግሥት ሠራተኛ ለሚለው ሐረግ በተሰጠው መግለጫ ውስጥ ተጠቃልለው የገቡ ስለሆነ ተሰርዘው "ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ በብዙ ተጽፎ የነበረው በነጠላ እንዲሆን ተደርጎአል። በንዑስ ቁጥር (፪)ም የተጻፈው ከንዑስ ቁጥር (፩) ጋራ የተያያዘ ስለሆነ በብዙ የተጻፈው በነጠላ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቶአል። ወንጀሉን በንዑስ ቁጥር (፪) በተመለከተው አኳኋን ለፈጸመ ወንጀለኛ በዚሁ ንዑስ ቁጥር የተመለከተው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል የጽኑ እሥራት ቅጣት ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ስለሆነ እንዲመጣጠን ለማድረግ "ቅጣቱ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል.." የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቅጣቱ እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እሥራት ይሆናል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ወንጀሉ የተፈጸመው በቸልተኝነት ቢሆንም በንዑስ ቁጥር (፫) የተመደበው እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ ወይም ጥፋቱ ከባድ ሲሆን እስከ አንድ አመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እሥራት የሥራን ምስጢር በመግለጽ ለሚፈጸም ወንጀል በጣም ስለሚያንስ "እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ

www.abyssinialaw.com

"እስከ ብር አንድ ሺህ ለመድረስ የሚችል መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። "እስከ ስድስት ወር ሊደርስ የሚችል እሥራት ለመሆን ይችላል" የሚለው ሐረግም ተሰርዞ "ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ቀላል እሥራት ይሆናል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በቀር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃኝቷል።

አንቀጽ ፫፻፺፰ <u>እንዲገለጽ የተፈቀደ ምስጢር</u>

የምስጢር መገለጽ የሚፈቀደውና ተገቢ የሚሆነው ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጥ የሆነ እንደሆነ ነው። ስለዚህ በቁጥር ፬፻፮ የተመለከተው ድንጋጌ "ለሕዝብ ጥቅም ሲባል" በሚል ሐረግ እንዲጀምር ተደርጓል። የቁጥር ፬፻፮ ድንጋጌ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከተሻሻለ በኋላ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ከተቃና በኋላ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፰ ሆኖ ገብቶአል።

አንቀጽ ፫፻፺፱ <u>በሞያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢርን መግለጽ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌውን ስያሜ ከይዘቱ ጋር ለማጣጣም ሲባል "የግል ሞያን የሥራ ሚስጥር ስለመግለጽ" የሚለው ተሰርዞ "በሞያ ወይም በሥራ ምክንያት የታወቀ ምስጢርን መግለጽ" በሚል ተተክቶአል። በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) በመግቢያነት የሰፈረው "የክስ አቤቱታ በቀረበባቸው ጊዜ በእሥራት ወይም በገንዘብ የሚቀጡት" የሚለው ሐረግ ከንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ መጨረሻ እንዲገባ ሆኖ አገላለጹም "የግል አቤቱታ ሲቀርብበት በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል" የሚል ሐረግ ሆኖአል። የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ በፊደላት እንዲከፋፈል ተደርጎ የነበረው በፊደል መከፋፈሉ ቀርቶ በንዑስ ቁጥር (፩) ሥር ብቻ እንዲዘረዘር ተደርጎአል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ አጠር ባለና ግልጽ በሆነ አነጋገር እንዲቀረጽ ተደርጓል። በብዙ ቁጥር ተመልክቶ የነበረውም በነጠላ ቁጥር እንዲጻፍ ተደርጓል።

ለንዑስ ቁጥር (፫) የተወሰነው ቅጣት ከፍ እንዲል መደረግ ያለበት መሆኑ ስለታመነበት "እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ የሚችል መቀጮ ወይም እስከ ስድስት ወር ለመድረስ የሚችል እሥራት ይሆናል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ ብር አንድ ሺህ ለመድረስ የሚችል መቀጮ ወይም እስከ አንድ አመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት ይሆናል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ማሻሻያዎች በቀር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቷል።

አንቀጽ ፬፻ <u>እንዲገለጽ የተፈቀደ ምስጢር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) መንደርደሪያ ላይ "በተለይ በፍርድ ችሎት ወይም በኢንሹራንስና በኪሳራ አከፋፈል ጉዳይ ስላለው ክርክር" የሚለው ሐረግ የኢንሹራንስ ድርጅት ከደንበኞቹ ጋር በሚያደርገው የመድን ዋስትና ውል መሠረት በሕይወታቸው፣በጤንነታቸው ወይም በንብረታቸው ላይ ጉዳት ቢደርስ የሚከፈላቸው ካሣ እንጂ ኪሣራ ስላልሆነ ሐረጉ በአጠቃላይ ተሰርዞ "ሚስጢር መገለጽ የሚያስቀጣው"

www.abyssinialaw.com

በሚለው ሐረግ ተተክቶአል። በፊደል ተራ (ለ) "አሳብ አቅራቢነት" በሚለው ሐረግና "ጠያቂነት" የሚለው ቃል ተመሣሣይ በመሆናቸው ምስጢር እንዲገለጽ ለማድረግ የበላይ የሆነው የክፍሉ ባለስልጣን ፈቃድ ሃሣብ ካቀረበ መጠየቅ፤ ከጠየቀ ደግሞ ሐሳብ ማቅረብ የሚያስፈልገው ስላልሆነ "አሳብ አቅራቢነት" በሚለው ሐረግ ምትክ "አሳሳቢነት" በሚል ቃል ተተክቶ "ጠያቂነት" ከሚለው ቃል ጋር በ"ወይም" እንዲገናኝ ተደርጎአል። በፊደል ተራ (ሀ) (ለ) (ሐ)እና (መ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሐ) በተመለከተው መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በ(ለ)፣ በ(ሐ) እና (መ) መጀመሪያ ላይ "ወይም" የሚለው ይኸው ቃል ያለቦታው ስለተጻፈ ተሰርዞአል። በቁጥር ፬፻፰ ድንጋጌ ላይ ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## አንቀጽ ፬፻፮ የሳይንስን፣ የኢንዱስትሪን ወይም የንግድ ሚስጥርን መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፮ ሆኖ ገብቷል።

ማንኛውም ሰው በሕግ ወይም በውል ያለበትን ግዴታ በመጣስ በምስጢር መጠበቅ የሚገባውን ማናቸውንም የኢኮኖሚ፣ የሳይንስ ወይም የቴክኖሎጂ ግንባታ ዘዴ ወይም መረጃ፣ የማናቸውንም ሳይንሳዊ ምርምር ውጤት ወይም መረጃ፣ ወይም የማናቸውንም ሳይንሳዊ ምርምር አሠራር ሥርዓት ወይም መረጃ ሊገለጽለት ለማይገባው ሰው ሲገልጽ በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻ ላይ "በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሶስት ወር ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል"ተብሎ የተደነገገው ለድርጊቱ የማይመጥን አነስተኛ ቅጣት በመሆኑ ሐረጉ ተሰርዞ "ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል" በሚለው ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ "..በዚህ ምክንያት የክስ አቤቱታ ሲቀርብበት ይህ ጥፋቱ የግል ሞያን ወይም የሠራተኛነትን ምስጢር መግለጽ ተብሎ በሚጠራው ወንጀል ላይ ሊወሰን በሚገባው ከፍ ባለው ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ተሰርዞአል።

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት እንዲሰረዙ ተደርጓል። ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በተጨማሪ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

# ርዕስ ሶስት
# በመንግሥት ሥራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

ርዕስ ሶስት በቀድሞው ሕግ ላይ እንደነበረው በሁለት ምዕራፎች ሳይሆን በሶስት ምዕራፎች እንዲከፈል ተደርጓል። የቀድሞው ሕግ ሁለት ምዕራፎች ምዕራፍ ሁለትና ሶስት ሆነው እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን "ጠቅላላ ድንጋጌዎች" በሚል ስያሜ አዲስ ምዕራፍ አንድ ገብቷል። በምዕራፍ አንድ ውስጥ የተቀረጹት ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ በርዕስ ሶስት ለሚገኙት በመንግሥት ስራ ላይ ለሚደረጉ ወንጀሎች ተፈጻሚነት አላቸው። በምዕራፍ አንድ ውስጥ ትርጓሜ ስለሚያስፈልጋቸው ቃላት፣ ስለ ጥቅም ማግኘት ወይም ስለጉዳት

www.abyssinialaw.com

አሳብ ግምት፣ ስለመርህና፣ የአስተዳደር ቅጣትና የፍትሐብሔር ኃላፊነት በተደራራቢነት ተፈጻሚ ስለሚሆኑበት እንዲሁም ከክስ ነጻ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ አንቀጾች ይገኛሉ።

አንቀጽ ፬፻፪ <u>ትርጓሜ</u>

ይህ አንቀጽ የመንግሥት ሠራተኛን ከሚተረጉመው የቀድሞ ቁጥር ፬፻፲ (፩) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም የስያሜና የይዘት ለውጥ ተደርጎበታል። ስያሜው "መሠረቱ" ከማለት ይልቅ ትርጓሜ ቢባል የሚሻል ሆኖ ተገኝቷል። አንቀጹ አሻሚ ትርጉም ሲሰጣቸው እና ያለአግባብ ክርክር ሲያስነሱ የነበሩ ቃላትና ሐረጎች ትርጉም ይዟል። በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) "የመንግሥት ሠራተኛ"፣ "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" "የመንግሥት የልማት ድርጅት"፣ ለሚሉት ሐረጎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ትርጉም ተሰጥቶአቸዋል። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ንዑስ አንቀጾች የተካተቱት ትርጉሞች የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፭/፺፫ በአንቀጽ ፪ የተሰጡትን ትርጉሞች መሠረት ያደረጉ ናቸው።

ንዑስ አንቀጽ (፬) "ጥቅም" ማለት ምን እንደሆነ በምን ዓይነት መልክና ሁኔታ ጥቅም ሊገኝ እና ሊሰጥ እንደሚችል የሚተረጉም ነው።

ንዑስ አንቀጽ (፭) ደግሞ "የማይገባ ጥቅም" ምን እንደሆነ ይተረጉማል።

አንቀጽ ፬፻፫ <u>ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት አሳብ ግምት</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ላይ አልነበረም። በአንድ ድንጋጌ ውስጥ የተፈጸመው የሙስና ወንጀል ያለአግባብ ሰውን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት መሆኑ ከተገለጸ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የወንጀሉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር (ድርጊቱ) እንደተፈጸመ ከተረጋገጠ የተፈጸመው ድርጊት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ተደርጎ ግምት ሊወሰድ መቻሉን የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፬፻፬ <u>መርህ</u>

የአንቀጹ ስያሜ ከቀድሞው ሕግ ቁጥር ፬፻፲ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይዘቱም በተወሰነ ደረጃ ከቀድሞው ቁጥር ፬፻፲ (፪) እና በከፊልም ከንዑስ ቁጥር (፩) ጋር ይቀራረባል። አንቀጹ በአምስት ንዑሳን አንቀጾች ተከፍሏል።

ንዑስ አንቀጽ (፩) ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተደነገጉት ወንጀሎች አንዱን ባደረገ ጊዜ ከዚህ በታች የተጻፉት የቅጣት ድንጋጌዎች እንደሚፈጸሙበት ይገልጻል።

ንዑስ አንቀጽ (፪) ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ የተከሰሰበት፣ በወንጀለኛነት የፈጸመው ወይም ሳይፈጸም በግድፈት የተወው ተግባር የተሰጠውን ስራ በሚሰራበት ጊዜ የተፈጸመ እንደሆነና ተግባሩም መደበኛ ሕግ የሚፈጸምበት ሆኖ ነገር ግን በመንግስት ስራ ላይ በመሆኑና በእርሱ ላይ ከተጣለው እምነት የተነሳ፤ ያለበትን ግዴታ ለመወጣት ቅጣቱ

www.abyssinialaw.com

የሚከብድ ሲሆን በዚህ የወንጀል ሕግ በሌሎች ርዕሶች የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑበት ይገልጻል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የገባ ሲሆን አጠር ባለ መልክ የሙስናን ምንነት የሚገልጽ ድንጋጌ ነው::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የሙስና ወንጀሎችን ዝርዝር የሚያሳይ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ክፍል ፩ እና በምዕራፍ ፫ ክፍል ፩ ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች በተጨማሪ በወንጀል ሕጉ ውስጥ በተለያየ ቦታ የሚገኙትን የሙስና ወንጀሎች እንዲያመላክት ተደርጓል:: በዚህ መልክ የተጠቀሱት ብቻ እንዳልሆኑ እንዲታወቅ ተደርጓል::

ንዑስ አንቀጽ (፭) በተከሳሹ ላይ ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ በሕገወጥ መንገድ ያገኘው ጥቅም፣ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲወረስ ወይም ጥቅሙም ሆነ ንብረቱ ካልተገኘ ተመጣጣኝ ዋጋውን የሚከፍል መሆኑን እንዲያመለክት ተደርጎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፬፻፴፫ <u>የአስተዳደር ቅጣትና የፍትሐብሔር ኃላፊነት በተደራራቢነት ተፈጻሚ መሆናቸው</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜ ከቀድሞው ሕግ ቁጥር ፬፻፲፩ ስያሜ ጋር ተቀራራቢት አለው:: ይዘቱ በፊት ከነበረው አገላለጽ ለየት ባለ ሁኔታ የወንጀልና የፍትሐብሔር ክስ በጣምራ ወይም በተናጠል ሊቀርብ የሚቻል መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፬፻፴፬ <u>ከክስ ነጻ ማድረግ</u>

ይህ አንቀጽ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን ስያሜው እንደጉቦ መቀበልና ጉቦ መስጠት በመሳሰሉ ወንጀሎች ተካፋይ የነበረ ሰው ክሱ ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ለሚመለከተው አካል በመጠቆም ድርጊቱ ተጋልጦ ለሕግ እንዲቀርብ ካደረገ ከመከሰስ ነፃ የሚሆንበት ሁኔታ ይደነግጋል:: ይህም በስውር የሚፈጸመውን ወንጀል ለማጋለጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል:: ጠቋሚው ከክስ ነጻ የሚደረገው ጠቃሚ ማስረጃ በሚሰጥበት ጊዜ ሲሆን፣ "ስለማስረጃው ጠቃሚነት አወሳሰንና ድርጊቱን ያጋለጠ ሰው እንዳይከሰስ ስለሚደረግበት ሁኔታ ዝርዝር አፈጻጸሙን በሚመለከት አግባብ ባለው የስነስርዓት ሕግ ይደነገጋል::" ተብሎ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ተመልክቷል:: ህጋዊ በሆነ መልኩ ሳገኘው ወይም ሊያገኘው የሚገባ አገልግሎት የሰጠው ማንኛውም ጥቅም እንዲሰጥ የተገደደ ሰው ወይም ተጽዕኖ የደረሰበትና የወንጀሉን ድርጊት በራሱ ፈቃድ ሳጋለጠ የሰጠው ጉቦ ወይም ስጦታ ወይም ዋጋ ያለው ነገር በጉቦ ምክንያት ከተወረሰ ንብረት እንደሚመለስለት በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ተደንግጓል::

## ምዕራፍ ሁለት
## የመንግሥትና የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች በመንሥት ሥራ ላይ የሚፈጽሙአቸው ወንጀሎች

ይህ ምዕራፍ የቀድሞ ሕግ ምዕራፍ አንድ የነበረው ሲሆን በውስጡ የነበሩት ሁለት ክፍሎች አቀማመጥ እንዲቀያየር ተደርጓል።

## ክፍል አንድ
## ቅንነትና ታማኝነትን በማጓደል የመንግሥትና የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች የሚፈጽሙአቸው የሙስና ወንጀሎች

ይህ ክፍል የቀድሞ የምዕራፍ አንድ ሁለተኛው ክፍል (ቁጥር ፬፻፳-፬፻፳፮) ሲሆን "በሞያ ሥራ ቅንንትና ታማኝነት ተግባር ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች" የሚል ስያሜ ነበረው። ይህ ስያሜ ተሻሽሎ "ቅንነትና ታማኝነትን በማጓደል የመንግሥትና የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች የሚፈጽሙአቸው የሙስና ወንጀሎች" እንዲል ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት የመንግሥትና የሕዝብ አገልግሎት ሠራተኞች በስራቸው ላይ ሆነው የሚያደርጓቸው ወንጀሎች ሁሉ የሙስና ወንጀሎች እንዳልሆኑ ለማመልከትና፣ የሙስና ወንጀሎችን በአንድ ክፍል በማስቀመጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በቀላል እንዲከታተሉት ምቹ ለማድረግ ነው።

አንቀጽ ፬፻፯ <u>በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል</u>*

ይህ አንቀጽ ከቀድሞ ሕግ ከቁጥር ፬፻፲፬ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የቃላት ማስተካከያ እንደሚከተለው ተደርጎበታል።

ስያሜውን በተመለከተ "በሥልጣን ያለአግባብ ስለ መስራት" ይል የነበረው፣ "በሥልጣን ያለአግበብመገልገል" በሚለው ሀረግ ተተክቷል።

በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ "ከዚህ በላይ የተመለከቱት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች" የሚለው ሀረግ "ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ" እንዲል ተደርጓል። "በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ" በማለት ፈንታ "በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ" እንዲል ተደርጓል። የተንዛዛው የንዑስ ቁጥር (፩) የፊደል ተራ (ሀ) አገላለጽ አጠር ተደርጎ የተረቀቀ ሲሆን በተለይ "ቅጣትን በሚያስከትል ግድፈት" የሚለው ተሰርዞ "በግድፈት" የሚለው ቃል ብቻ እንደገባ ተደርጓል። ግድፈቱ ያለአግባብ ለመጠቀም ወይም ለመጉዳት ታስቦ እስከተፈጸመ ድረስ መለኪያው መሆን ያለበት ያለአግባብ የተገኘው ጥቅምና የደረሰው ጉዳት መጠን እንዲሁም ታስቦ መደረጉ እንጂ ግድፈቱ ቅጣት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ ግልጽ መመዘኛ ነጥብ ሲሆን አይችልም። የንዑስ ቁጥር (፩) የፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) አገላለጽም አንድአንድ ለውጥ ተደርጎበታል።

ከንዑስ ቁጥር (፩) (ሐ) በታች ባለው ፓራግራፍ ላይ "በሕጉ ላይ ስለዚህ ጉዳይ የሚወሰን በተለይ ከፍተኛ የሆነው የቅጣት ድንጋጌ ደንብ እንደጸና ሆኖ" የሚለው ተሻሽሎ "በሕጉ ላይ ጉዳዩን በግልጽ የሚመለከት ድንጋጌ ከሌለ በቀር" እንዲል ተደርጓል። ይህ እንዲሆን

---

* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ <u>407</u> ንዑስ አንቀጽ <u>(፪)</u> "የተገኘው ጥቅሙ" የሚለው ቃል "የተገኘው ጥቅም" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

የተደረገበት ምክንያት ከዚህ አንቀጽ ይልቅ አንድን ጉዳይ የሚሸፍን ግልጽ ድንጋጌ በሕግ ላይ ካለ፣ የሚደነግገው ቅጣት ከፍተኛ ቢሆንም ባይሆንም፣ አግበብነት የሚኖረው ድንጋጌ ይህ አንቀጽ ፬፻፯ ሳይሆን ጉዳዩን በግልጽ የሚሸፍነው ሌላው ድንጋጌ መሆን እንዳለበት ለማመልከት ነው።

በቀድሞው ሕግ በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ እንደተገለጸው ወንጀሉ ጉዳት ያደረሰው ወይም የሚያደርሰው "በሕዝብ ወይም በግል ጥቅም" ላይ ብቻ መሆኑ ቀርቶ መንግሥትም እንዲያካትት ተደርጓል።

ቅጣቱን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻ ላይ "በእስራት ቅጣት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣሉ" በሚለው ምትክ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ፣ አድራጎቱ በግል ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን ብቻ ይጠቅሳል። ሆኖም አድራጎቱ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሰው በመንግሥት ላይ ጭምር መሆኑ ከመገለጹም በላይ፣ "ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፣ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው ኃላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ......" የወንጀሉ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ሆነው በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ከገቡ በኋላ በዚህ መልክ የተቀረጸው ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል። የንዑስ ቁጥር (፪) ቅጣትም እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራትና መቀጮ መሆኑ ቀርቶ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ የሚደርስ መቀጮ እንዲሆን ተደርጎአል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የገባ ሲሆን "በንዑስ አንቀጽ (፪) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥመቀጮ ይሆናል።" በማለት ይደነግጋል።

ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የአንቀጹ ይዘት የተቀረጸውና ቅጣቱ በሶስት ደረጃ የተከፈለው፣የሙስና ወንጀሎችን የሚፈጽሙ ሰዎች እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲቀበሉ ለማድረግ ነው።

አንቀጽ ፬፻፰ <u>ጉቦ መቀበል</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፬፻፳፩ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይ ነው።

ንዑስ አንቀጽ (፩) ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባውን ሳለማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲሰጠው ቢጠይቅ፣ የተስፋ ቃል ቢቀበል በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የሚያከብዱ ምክንያቶች ከሌሉ እና የተፈጸመው ወንጀል ቀለል ያለ መስሎ ሲታይ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እና እስከ ብር ሃያ ሺህ ለመድረስ የሚችል የመቀጮ ቅጣት ለመወሰን እንደሚቻል ይደነግጋል።

www.abyssinialaw.com

ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫)፣ የወንጀሉን አፈጻጸም ከባድ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ... በተከሳሾች ላይ የሚወሰነው ቅጣት ሊከብድና ከፍ ሊል እንደሚችል የሚያ... ድንጋጌዎች ስለሆኑ ከላይ በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) እና (፫) በተደነገገው ዓይነት ተቀር... ይህም የሆነበት ምክንያት የወንጀሉን አፈጻጸም እንደከባድነቱ ደረጃ ተመጣጣኝ ... ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

በቀድሞው ቁጥር ፬፻፳፭ (፫) ላይ የተደነገገው አስታራቂ ሽማግሌዎች የመሳሰሉ የ... ስልጣን ያላቸው ሰዎች በስልጣናቸው ምክንያት መደለያ ሲቀበሉ ከመንግስትና ... አገልግሎት ሠራተኛ በተለየ ሁኔታ መታየት ስለሚገባቸው ተለይቶ በአንቀጽ ፬፻፲ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በአዲስ መልክ የገባ ሲሆን የመንግሥት ሠራተኞች ከዓለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈጽሙትን የጉቦ መቀበል ወንጀል የሚመለከት ድንጋጌ ነው።

## አንቀጽ ፬፻፰ የማይገባ ጥቅም መቀበል

ይህ አንቀጽ ከቀድሞ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፫ ጋር ግንኙነት አለው። የንዑስ አንቀጽ (፩) ቅጣት ከቀድሞ ይልቅ ከፍ ያለ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ሰባት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እና እስከ ብር አስር ሺህ ለመድረስ የሚችል መቀጮ እንደሚሆን ተደንግጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፪) አዲስ የገባ ሲሆን የወንጀሉ አፈጻጸም በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) ዓይነት ሲሆን ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና መቀጮው እስከ ብር ሰላሳ ሺህ የሚደርስ መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ ተቀርጿል።

የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌም አዲስ ሲሆን ወንጀሉ ከዓለም ዓቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የስራ ኃላፊነት ወይም ግዴታ መነሻ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ስለሚጣለው ቅጣት የሚያሳይ ድንጋጌ እንዲሆን ተደርጓል።

## አንቀጽ ፬፻፲ አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈጽሙአቸው የጉቦ መቀበል ወንጀል

የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (፩) ይዘት ከቀድሞ ሕግ ከቁጥር ፬፻፳፭ (፫)፣ የንዑስ አንቀጽ (፪) ይዘት ደግሞ ከቁጥር ፬፻፳፫(፪) ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ራሱን የቻለ አንቀጽ እንዲሆን ተደርጓል። ድንጋጌው አስታራቂ ሽማግሌን፣ የግልግል ዳኛን፣ የፍርድ ቤት ነባሪን፣ ንብረት ጠባቂ ወይም አጣሪን፣ ስራውን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚን ወይም አስተርጓሚን ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክነት በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያው ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛውም ልዩ አዋቂን (ኤክስፐርት) የሚመለከት ሲሆን ከቀድሞ ድንጋጌ ይልቅ ሰፋ እንዲል ተደርጎ ተቀርጿል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፲፩ <u>የመንግስት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት</u>

የአንቀጹ ስያሜና ይዘት በተወሰነ ሁኔታ ከቀድሞው ቁጥር ፬፻፳ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: ንዑስ አንቀጽ (፩) ከቀድሞው ድንጋጌ ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያለው ቢሆንም ቅጣቱ ግን ከቀድሞው ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ሲነጻጸር እንዲከብድ ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈጸመ ወንጀል ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና እስከ ሀምሳ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ እንደሚሆን ይደነግጋል::

የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች ይዘትና ቅጣት በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) እና (፫) ዓይነት የተቀረጸ ነው::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የገባ ሲሆን ድርጊቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተመለከተው ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት አሳብ ሳይኖር ማንኛውም ሰው እራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን በሆነበት ድርጅት ወይም መስራች ወይም አባል በሆነበት የበጎ አድራጎት ድርጅትና በእርሱ መሥሪያ ቤት መካከል በንግድ ወይም በሌላ ስራ፣ በግዥ ወይም በሽያጭ፣ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር የተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ውል እንዲፈጸም ቢያደርግ ወይም የተወሰኑ ንብረቶች እንዳይገዛ ወይም እንዳይጫረት በሕግ ወይም በደንብ ተከልክሎ እያለ በስሙ ወይም በሌላ ሰው ስም ወይም ከሌላ ሰው ጋር በመመሳጠር ንብረት ቢገዛ፣ ወይም ቢጫረት ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል:: በንዑስ አንቀጽ (፫) መጨረሻ ላይ "ዘመድ" የሚለው ቃል ማን ማንን እንደሚጨምር የሚተረጉም ፓራግራፍ ገብቷል::

አንቀጽ ፬፻፲፪ <u>አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፩ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: የንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ግልጽነት የሚጎድለው ስለነበረ "ማንኛውም የመንግሥት ሥራን የሚያከናውን ሰው" ብሎ እንዲጀምር ሆኖአል:: ይዘቱም ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የተስተካከለ ሲሆን ቅጣቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) የቅጣቱ ጣራ አምስት መቶ ብር መቀጮ እና አንድ ዓመት ቀላል እሥራት መሆኑ ቀርቶ ሰባት ሺህ ብር መቀጮና አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት እንዲሆን ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር "የአመጽ ትርፍ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ጥቅም" በሚለው ቃል ተተክቷል:: ቅጣቱ ሰስት ዓመት እሥራት መሆኑ ቀርቶ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን፤ መቀጮውን በተመለከተ ግን አገላለጹ ተመሳሳይ ነው:: በንዑስ አንቀጽ (፫) ሥር ደግሞ ቅጣቱ ሰስት መቶ ብር መሆኑ ቀርቶ አንድ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ እንዲሆን ተደርጎ ተስተካክሏል::

አንቀጽ ፬፻፲፫ <u>በሥራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፪ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: በዚህ ስያሜ ይዘት ውስጥ "የመስረቅ" የሚለው ቃል በሕጉ ውስጥ በሌላ ቦታ ከተቀመጠው የመስረቅ ወንጀል ጋር የሚያምታታ ሆኖ ስለተገኘ ተገቢውን መልእክት ለማስተላለፍ እንዲችል "የመሰወር" ተብሎ ተስተካክሏል:: አቀራረጹን በተመለከተ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ተከፍሎ የነበረው የቀድሞው ሕግ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደረገ ሲሆን በቅጣት ረገድ መነሻው አንድ ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑ ቀርቶ አንድ ዓመት ቀላል እስራት ከመደረጉ በቀር ሌላ ለውጥ አልተደረገበትም::

www.abyssinialaw.com


የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ቅጣቱም እንደሚከብድ የሚደነግጉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የገቡ ሲሆን በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) እና (፫) መልክ የተረቀቁ ናቸው::

አንቀጽ ፬፻፲፩ <u>በሥልጣን መነገድ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፬ ጋር ተወራራሽ ነው:: የዚህ አንቀጽ ስያሜ ይዘቱ ግልጽነት የጎደለው ስለነበረ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አጠር ተደርጎ ተስተካክሏል:: ምክንያቱም "በግልጽ በተሰጠ ሥልጣን" የሚለው ሀረግ ሁልጊዜም ወንጀሉ ሥልጣን ባለው ሰው ብቻ የሚፈጸም ስለሚያስመስለውና ነገር ግን በግልጽ ሥልጣን ባልተሰጠውም ሰው ወንጀሉ ሊፈጸም ስለሚችል ነው::

አቀራረጹን በተመለከተ የቀድሞ ሕግ ድንጋጌ በሶስት ፊደላት ብቻ የተከፈለ ነበር:: አሁን ግን የቀድሞ ድንጋጌ በነበረበት ሁኔታ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫)እንዲገባ ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል አፈጻጸም ከባድ በሚሆንበት ጊዜ ተመጣጣኝ ቅጣት የያዘ ድንጋጌ በማስፈለጉ ነው::

ይዘቱን በተመለከተ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን ለንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተለያዩ የቅጣት ድንጋጌዎች እንዲሆን ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ ካልሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና ከሰላሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ተደንግጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ በሆነ ጊዜም ቅጣቱ በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) እና (፫) በተመለከተው ዓይነት እንዲከብድ ተደርጓል::

አንቀጽ ፬፻፲፪ <u>በሕገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፮ ጋር ተወራራሽነት ያለው ቢሆንም አዳዲስ ጉዳዮች ታክለውበታል:: በአንቀጹ ስያሜም ላይ የተወሰነ ለውጥ ተደርጓል:: የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መንደርደሪያ ወጥነት ለመጠበቅ እና ግልጽ እንዲሆን "ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ" ብሎ እንዲጀምር ሆኗል፤ ቅጣቱን በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተፈጸመ ወንጀል እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራትና እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል::

በቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ምትክ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የገቡ ሲሆን ይዘታቸውና የሚያስወስኑት ቀጣት በአንቀጽ ፬፻፯ (፪) እና (፫) በተገለጸው አኳኋን ተቀርጿል:: አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የገባ ሲሆን፣ ወንጀሉ የተደረገው በቸልተኝነት እንደሆነ በቀላል እስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ የሚያመለክት ድንጋጌ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፲፮ <u>ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት በቀድሞው ድንጋጌ ውስጥ አልነበረም:: ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራው ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከሕግ ወይም ከስራ ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ከተለመደው አሰራር ውጭ ያለ በቂ ምክንያት የቀረበለት ጉዳይ ሳይወሰን ቢቀር ወይም ቢያዘገይ ወይም ባለጉዳዩን ቢያጉላላ ድርጊቱ በደንብ መተላለፍ ከሚያስቀጡ ሁኔታዎች ውጭ መሆኑ ሲረጋገጥ በመቀጮ፣ በቀላል እስራት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት መቅጣት እንደሚቻል የሚደነግግ አንቀጽ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጓል::

አንቀጽ ፬፻፲፯ <u>ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት በቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ አልነበረም:: የአንቀጹ ይዘት ከስያሜው ጋር በሚስማማ ሁኔታ ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል:: ይህ እ.ኤ.አ በ፲፱፻፺፩ ከወጣው የሱዳን የወንጀልና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የተገኘ ነው:: የዚህ ድንጋጌ መካተት የመንግሥት ሠራተኛ ከመንግሥት ከሚከፈለው ደሞዝና ሌላ ጥቅም ውጭ በሥራው አጋጣሚ ከሚያገኘው ተገልጋይ ላይ ዋጋ ያለው ነገር በነጻ ወይም አነስተኛ የሆነ ክፍያ ከፍሎ እንዳያገኝ በመከልከል ሥራውን በአግባቡ እንዲያከናውን ለማገዝ ነው:: ንዑስ አንቀጽ (፩) ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለበቂ ክፍያ ወይም ያለክፍያ ከማንም ሰው ላይ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር ቢቀበል እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል:: ንዑስ አንቀጽ (፪) ስጦታ መቀበልን ማሳወቅ ወይም ማስመዝገብ እንደሚገባ የሚገልጽ ሕግ ወይም ደንብ ተላልፎ ቢገኝ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ዓይነት እንደሚቀጣ ይደነግጋል::ንዑስ አንቀጽ (፫) ስጦታዎች የማያስቀጡበት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ የሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ እንዲሆን ተደርጎ ተረቋል::

አንቀጽ ፬፻፲፰ <u>ያለአግባብ ፈቃድ መስጠት እና ማጽደቅ</u>

ይህ አንቀጽ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ አልነበረም:: ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ አስቦ ብቁ ሳልሆነ ወይም ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ቢሰጥ ወይም ቢያፀድቅ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበት ቦታ ያለአግባብ ቢፈቅድ ወይም ቢሰጥ በወንጀል ተግባር ተጠያቂ እንዲሆን ተደንግጓል:: ቅጣቱም እንደነገሩ ሁኔታ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እንደሚሆን ተደርጎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፬፻፲፱ <u>ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያልነበረ ነው:: የዚህ ተመሳሳይ ድንጋጌ እነ ሆንግ ኮንግ እና ህንድ በሕጋቸው አካተዋል:: አንዳንድ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዛቸው ትንሽ ሆኖ ነገር ግን ከገቢያቸው በላይ ሀብት ሲያካብቱ ይታያል:: የሀብታቸው ምንጭ እንዲህ ሊሆን የሚችለው ያላቸውን ሥልጣን

www.abyssinialaw.com

በመጠቀም ጥቅም የሚያገኙ በመሆኑ እንደሆነ ይገመታል። የዚህ ዓይነቱን ድርጊት በወንጀል እንዲቀጣ ማድረጉ የሚታመንበት ነው።

በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው የወንጀል ድርጊት ተከሳሹ በማስረጃ ማስተባበል ካልቻለ በእጁ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት መወረስ ወይም ለባለቤት መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ከተከሳሹ ጋር ቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው ከተከሳሹ እጅ በስጦታም ሆነ በሌላ መንገድ የተቀበለው ንብረት ቢኖር ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ንብረቱ በተከሳሹ እጅ እንዳለ የሚቆጠር መሆኑ ተደንግጓል። ይህም ተከሳሽ የተንኮል ዘዴ በመፍጠር በሕገወጥ ዘዴ ያገኘውን ንብረት እንዳያሸሽ ለማድረግ ነው።

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>የሥራ ግዴታን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፬፻፳ <u>የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲፬ ጋር ተቀራራቢነት አለው። የቁጥር ፬፻፲፬ ስያሜ "የሥራ ግዴታን ተግባር ስለመጣስ" ይል የነበረው ገላጭነት ስለሌለው "የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል" ተብሎ ተስተካክሏል።

ይዘቱም በዚሁ ሃሣብ መሠረት የተስተካከለ ሲሆን የንዑስ ቁጥር (፩) ቅጣት እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ቀላል እስራት መሆኑ ቀርቶ እስከ ስድስት ወር ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት እንዲሆን ተደርጓል። በአማራጭ የሚወሰነው መቀጮውም ከአምስት መቶ ብር ወደ አንድ ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል እንደሚሆን ተደርጓል።

በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ በሕዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም" የሚለው ተሰርዟል። ምክንያቱም በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ ስለተጠቀሰ አላስፈላጊ ድግግሞሽን ለማስቀረት ነው። በተጨማሪም "መንግሥት" የሚለው ቃል በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ገብቷል። የንዑስ አንቀጽ (፪) ቅጣት "ቀላል እስራትና መቀጮው በሕግ እስከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት ሊደርስ ይችላል"

አንቀጽ ፬፻፳፩ <u>ሕገወጥ የስራ ማቆም አድማ</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜ ከቀድሞ ሕግ ከቁጥር ፬፻፲፭ ጋር ተቀራራቢነት አለው። የዚህ አንቀጽ ይዘት በሕገ መንግሥታችን መርህ መሠረት የሥራ ማቆም አድማ ሊያደርጉ የሚቻላቸውን ሠራተኞች መብት ላለመገደብ ታስቦ በዚሁ መሠረት ሃሣብ ቅጣት የሚያስከትለው አድማ "ሕግን ወይም ሙያውን በሚቃረን ሁኔታ" ከተሰራ ብቻ መሆን ስላለበት በዚሁ መሠረት ተስተካክሎ ቀርቧል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፳፪ <u>የሰውን ንብረት የመበርበር ወይም የመያዝ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው ሕግ ቁጥር ፬፻፲፭ ጋር ተቀራራቢነት አለው:: የቀድሞው ስያሜ የተንዛዛ ስለነበር አጠር ባለ ሁኔታ ተስተካክሎ እንዲጻፍ ተደርጓል:: ይዘቱን በተመለከተም በፊት የነበረው ድንጋጌ ንዑሳን አንቀጾች ያልነበሩት ሲሆን ይህ መሆኑ ቀርቶ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል:: በመጀመሪያው ንዑስ አንቀጽ ውስጥ ምንም ስልጣን ሳይኖረው የሰውን ንብረት ያለአግባብ የበረበረ ወይም የያዘ ወይም የወሰደ እንደሆነ እስከ ሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ደግሞ ሥልጣን ቢኖረውም ሕግንና ሥርዓትን ተቃራኒ በሆነ መንገድ የሰውን ንብረት የያዘ የበረበረ ወይም የወሰደ እንደሆነ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተደርጎ ተስተካክሎ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፬፻፳፫ <u>በሕገወጥ መንገድ ሰውን መያዝ ወይም ማሰር</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው ሕግ ቁጥር ፬፻፲፮ ድንጋጌ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን የዚህ አንቀጽ ይዘት አልተለወጠም:: ቅጣቱን በተመለከተ እሥራቱ ከአምስት ዓመት ወደ አሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ከፍ እንዲል ተደርጓል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ከፍተኛ ሕገ መንግታዊ ጥበቃ የተሰጠውን የሰውን የነፃነት መብት ስለሚነካ ነው::

አንቀጽ ፬፻፳፬ <u>በማይገባ የአሠራር ዘዴ መጠቀም</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፬፻፲፯ ድንጋጌ ጋር ተወራራሽነት አለው:: የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ ግልጽነት የጎደለው ስለነበር በዚሁ መሠረት ተስተካክሎ እንዲታይ ተደርጓል:: አቀራረጹን በተመለከተ ከዚህ በፊት የነበረው አቀማመጥ ተለውጦ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል::

ይዘቱን በተመለከተ በሁለቱም ንዑሳን አንቀጾች ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ሃሳቦች እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን በተለይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተመለከተውን ባካተተ መልክ የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ወይም በምስክርነት የቀረበን ሰው በመደለል ወይም ተስፋ በመስጠት ኢሰባአዊ ድርጊት ቢፈጽም እንደሚያስቀጣ በግልጽ ተደንግጓል::

የመጀመሪያው ንዑስ አንቀጽ ማናቸውም የመንግሥት ሠራተኛ የተመለከቱትን ኢሰብአዊ ድርጊቶች ቢፈጸም ቅጣቱ እስከ አስር ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና መቀጮ እንዲሆን በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ደግሞ ኢሰብአዊ ድርጊቱ የተፈጸመው በባለሥልጣን ትዕዛዝ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አስራ አምስት ዓመት ሲደርስ የሚችል ጽኑ እሥራትና መቀጮ እንዲሆን፣ ተደርጓል:: ይህ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀደም ሲል ያልነበረና ሕግንና ሥርዓትን ማክበር የሚገባው ባለሥልጣን ሕግና ሥርዓት እንዲጣስ ያደረገ እንደሆነ ጠበቅ ያለ ቅጣት ሊጣልበት የሚገባ ሆኖ ስለተገኘ ነው::

አንቀጽ ፬፻፳፭ <u>እስረኛን ሕገወጥ በሆነ መንገድ መፍታትና እንዲያመልጥ መርዳት</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲፰ ጋር የሚወራረስ ነው:: በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ውስጥ ቅጣቱን በተመለከተ እሥራቱ ከሶስት ወር ወደ ሶስት ዓመት መቀጮው ከአንድ መቶ ብር ወደ ሶስት ሺ ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ የተደረገ ለውጥ የለም። በንዑስ አንቀጽ (፫) ሥር ያለው ቅጣት ግን መቀጮው ከአምስት መቶ ብር ወደ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፬፻፹፮ <u>የጠር ምርኮኞችንና የወታደር ግዞተኞችን መፍታት እንዲያመልጡ መርዳት</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲፱ ጋር ተቀራራቢነት አለው። ይህ አንቀጽ አጀማመሩ ያልተሟላና የዓረፍተ-ነገሩን ባለቤት ለይቶ የማያመለክት ስለነበር ይኸው ታርሞና ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ተደርጓል። ቅጣቱንም በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ ከአስር ዓመት ወደ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ከፍ እንዲል፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ደግሞ ከአንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወደ ሁለት ዓመት ቀላል እሥራት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>

<u>ሌሎች ሰዎች በመንግስት ስራ ላይ የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች</u>

ይህ ምዕራፍ የቀድሞው ሕግ የምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎችን (ቁጥር ፬፻፹፯-፬፻፺፯) እና አዲስ አንቀጾችን ከማካተቱም በላይ ምዕራፉ በሁለት ክፍል እንዲከፈል ተደርጓል። የክፍል አንድ ስያሜ "ሌሎች ሰዎች ከመንግሥት ስራ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚፈጽሟቸው የሙስና ወንጀሎች" እንዲል የተደረገ ሲሆን፣ የክፍል ሁለት ደግሞ "ሌሎች ሰዎች በመንግሥት ስራ አፈጻጸም ላይ የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች" የሚል ሆኗል። ምዕራፉ በዚህ መልክ የተከፈለበት ምክንያት፣ የመንግሥት ስራ የማይሰሩ ሰዎች የሚፈጽሟቸውን የሙስና ወንጀሎች ከሌሎች ወንጀሎች ለይቶ ለማመልከትና ለክትትል አመቺ እንዲሆን ለማድረግ ነው።

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ሌሎች ሰዎች ከመንግስት ስራ ጋር</u>

<u>በተያያዘ መንገድ የሚፈጽሟቸው የሙስና ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፬፻፹፯ <u>ጉቦ መስጠት</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፺፯ ተወራራሽነት አለው። አንቀጹ እንደቀድሞው ድንጋጌ በአንድ ላይ በተጠቃለለ መልኩ ሳይሆን ለአፈጻጸም አመቺና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በድስት ንዑስ አንቀጾች እንዲይዝ ተደርጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፩) "ማንም" ሰው አንድን የመንግሥት ሠራተኛን በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታው ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ ቢሰጥ፣ ቢያቀርብ በቀላል እስራት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራትና እስከ ብር አስራ አምስት ሺህ ለመድረስ በሚችል መቀጮ እንዲቀጣ የሚያደርግ ሆኖ ተደንግጓል።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ከዓለም ዓቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ለማንኛውም የሌላ አገር መንግስት ወይም ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ጉቦ መስጠት በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ቅጣት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል።

በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ስጦታው ከፍተኛ ሲሆን ወይም ድርጊቱ በመንግስት፣ በሕዝብ ወይም በግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ካስከተለ ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሀምሳ ሺህ ለመድረስ የሚችል መቀጮ እንደሚሆን ተደርጎ ተደንግጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ አድራጊው ጥቅሙን ወይም ስጦታውን ያቀረበው የመንግሥት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት ወይም ተግባር መሠረት እንዲፈጸምለት በማሰብ ወይም ከፈጸመለት በኋላ መሆኑ ሲታወቅ ቅጣቱ እንደነገሩ ሁኔታ መቀጮ፣ ቀላል እስራት ወይም እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ለመወሰን የሚያስችል ድንጋጌ እንዲሆን ተደርጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፭)፣ ወንጀሉ የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት በተፈጸመ ጊዜ ቅጣቱ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጸም የሚደነግግ ሆኖ ተቀርጿል።

ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨማሪ ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን ጥፋተኛው ከመንግስት ጋር ማናቸውንም ዓይነት ውል ወይም ግብይት በዘላቂነት ወይም ለተወሰነ ጊዜ እንዳይፈጽም የሚከለክል ትዕዛዝ ፍርድ ቤት ሊሰጥ እንደሚችል የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፬፻፳፰ <u>ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ አልነበረም። አንቀጹ የመንግስት ስራ ለሚያከናውን ሰው ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሌላ ሰው ያለ ክፍያ ወይም ያለ በቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር ማቅረብ፣ መስጠት፣ ለመስጠት መስማማት እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጎ ተደንግጓል።

አንቀጽ ፬፻፳፱ <u>ማቀባበል</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜም ሆነ ይዘት በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ነው። ይህ ድንጋጌ ከእስራኤል ሕግ የተወሰደ ነው። አቀባባዮች በጉቦ ሰንሰለት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። እገሌን አውቀዋለሁ እኔ ጉዳይህን አጨርሳለሁ በማለት ትክክለኛውን አሠራር የሚያዛቡ በመሆኑ በጉቦ ሰጪና ተቀባይ መካከል እንደድልድይ ሆነው የሚያገለግሉትን ሰዎች ለመቅጣት ያገለግላል። አንዳንዶች እንደ ገቢ ማስገኛ የሚያከናውኑት የድለላ ስራ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ግን ገንዘብ ለራሱ ሳይቀበል ይህን ተግባር የሚፈጽም ሰው ጭምር ለመቅጣት ያስችላል። በዚህ የወንጀል ተግባር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራትና በመቀጮ ሊቀጣ እንደሚችል ተደርጎ ተደንግጓል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፴ <u>በሌለው ሥልጣን መጠቀም</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን በሶስት ፊደላት የተከፈሉ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን ይዞ ተደንግጓል።

በፊደል ተራ (ሀ) ላይ አድራጊው ወንጀሉን የሚፈጽመው "ከመንግሥት ወይም ከሕዝብ አገልግሎት ስራው ከለቀቀ፣ ከስራው ከታገደ፣ ከተዛወረ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ" ሲሆን አገላለጹ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፬፻፲፬ (፩) (ሐ) (ከዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፬፻፯ (፩) (ሐ)/ጋር አንድ ዓይነት ይመስል ይሆናል። ሆኖም በዚህ በአዲሱ ድንጋጌ መሠረት አድራጊው ቀደም ሲል የመንግሥት ሠራተኛ የነበረ ቢሆንም፣ ወንጀሉን በሚያደርግበት ጊዜ በየትኛውም በኩል ቢሆን በመንግሥት ወይም በሕዝብ አገልግሎት ስራ ላይ የማይገኝ ሰው ነው። በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፬፻፯ (፩) (ሐ) መሠረት ግን አድራጊው ወንጀሉን የሚፈጽመው "በተለይም ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ከስራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ" ቢሆንም ወንጀሉን በሚፈጽምበት ጊዜ ከመንግሥት ስራ ላይ ገና ያልለቀቀ ሰው ነው። ለሶስተኛ ወገን በነባር ሥልጣኑ ወይም ተግባሩ ላይ የተሰማራ መስሎ በመታየቱ ወንጀሉን ለማድረግ የበለጠ ምቹ አጋጣሚ ይፈጥርለታል።

በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) ላይ አድራጊው ወንጀሉን የሚፈጽመው "ለወደፊቱ የመንግሥት ሠራተኛ እንደሚሆን አምኖ ይህንኑ ተስፋ ያደረገውን ስራ ምክንያት በማድረግ" ሲሆን ይህ ድንጋጌ ሊገባ የቻለው ድርጊቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ገና የመንግሥት ሠራተኛ አለመሆኑ ከወንጀል ተጠያቂነት ሊያድነው አይገባም ተብሎ በመታመኑ ነው።

በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሐ) ላይ አድራጊው በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው "የመንግሥት ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ" በሌለው ሥልጣን ሲጠቀም ነው። ይህ ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት የዚህ ዓይነቱን ድርጊት መደበኛው የአታላይነት አንቀጽ የማይሸፍነው በመሆኑ ነው።

በሶስቱም ፊደላት የተገለጹት ድርጊቶች እያንዳንዳቸው እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጡ ተደርጎ ተደንግጓል።

አንቀጽ ፬፻፴፩ <u>በግል ተሰማኒት መነገድ</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜና ይዘት ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፮ ጋር ተዛማጅነት አለው። ስያሜው "በግል ወዳጅነት ስለመነገድ" መባሉ ቀርቶ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን "በግል ተሰሚነት መነገድ" በሚል ሐረግ ቃል ተተክቷል። ይህ የሆነበት ምክንያት ወንጀሉ የሚፈጸመው በወዳጅነት መነሻ ሳይሆን በተሰሚነት ምክንያት በመሆኑ ነው። ቅጣቱን በሚመለከት ከአንድ ዓመት ባላነሰ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## ሌሎች ሰዎች በመንግሥት ሥራ አፈጻጸም ላይ የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች

**አንቀጽ ፬፻፴፪ መንግሥታዊ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና ሕጎችን መድፈር**

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፯ ጋር ተወራራሽነት አለው:: የዚህ ድንጋጌ ስያሜ ግልጽ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና ዐዋጆችን ስለመናቅ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "መንግሥታዊ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና ሕጎችን መድፈር" ተሰኝቷል:: ይዘቱን በተመለከተም "ማናቸውም መብት ሳይኖረው" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ በምትኩ "ሥልጣን ወይም መብት ሣይኖረው" በሚል ሀረግ ተተክቷል:: የቅጣቱን ጣራ በተመለከተም የሶስት ወር ቀላል እሥራት ወይም የአምስት መቶ ብር መቀጮ መሆኑ ቀርቶ የስድስት ወር ቀላል እሥራትና የአንድ ሺህ ብር መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል::

**አንቀጽ ፬፻፴፫ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፍቃድ ውጭ መስራት**

ይህ አንቀጽ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አልነበረም:: አንድ ሰው በሕግ ወይም በደንብ መሠረት ፈቃድ ሊሰጥበት የሚገባው ማናቸውንም ስራ ያለፈቃድ ቢሰራ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ ቢሰራ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ የሚቀጣ መሆኑን ይደነግጋል::

**አንቀጽ ፬፻፴፬ የማስመዝገብ ግዴታን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መጣስ**

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፰ ጋር ተወራራሽነት አለው:: በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "..ትዕዛዝ.." የሚለው አላስፈላጊ ቃል ስለሆነ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ተጨማሪ ማስተካከያዎች የተደረጉ ሲሆን አለማስመዝገብ ብቻ ሣይሆን በሐሰት ማስመዝገብም ወንጀል መሆኑ ተገልጾ ተስተካክሏል:: ቅጣቱን በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር በገንዘብ መቀጮ ብቻ መሆኑ ቀርቶ እስከ ሶስት ወር ለመድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ወይም እስከ አንድ ሺ ብር መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር ደግሞ ሶስት ወር እሥራት ብቻ መሆኑ ቀርቶ ከስድስት ወር ያልበለጠ እሥራት ወይም ከሁለት ሺ ብር ያልበለጠ መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል::

**አንቀጽ ፬፻፴፭ እንዳይገለጹ የተከለከሉ መንግሥታዊ ውይይቶችን ወይም ሰነዶችን መግለጽ**

ይህ አንቀጽ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፳፱ ድንጋጌ ጋር ተወራራሽነት አለው::

የድንጋጌው ስያሜ "ክርክሮች ወይም የመንግሥት ጉዳዮች እንዳይገለጹ የሚከለክለውን ደንብ ስለመጣስ" ይል የነበረ ሲሆን ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን እንዲስተካከል ተደርጓል:: ይዘቱን በተመለከተም "በሕዝብ ጉዳይ ማከናወኛ መሥሪያ ቤት ውስጥ የተደረገውን" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል፤ እንዲሁም "ሰነድ" የሚል ቃል የተጨመረበት ሲሆን ቅጣቱም እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት እንዲሆን ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፴፮ <u>ሕገወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር</u>

ይህ አንቀጽ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴ ጋር ተመሳሳይነት አለው የዚህ አንቀጽ ስያሜ "በራስ ሥልጣን ፍርድን የመፈጸም ተግባር" መባሉ ቀርቶ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሏል። ይህ የሆነበት ምክንያት ጥፋተኛው በሕገወጥ መንገድ የፈጸመው ፍርድን ብቻ ሣይሆን ሳይፈረድለት መብቴ ነው ብሎ የሚፈጽመውን ተግባር ስለሚጨምር "ፍርድን የመፈጸም ተግባር" የሚለው ሊሰረዝ ስለሚገባው ነው። ይዘቱም በዚሁ አኳኋን ተስተካክሏል። ቅጣቱንም በተመለከተ እሥራቱ ከስድስት ወር ወደ አንድ ዓመት ቀላል እስራት፣ መቀጮው ከአምስት መቶ ብር ወደ አምስት ሺህ ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፬፻፴፯ <u>ሥልጣንን በማይገባ መያዝ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፩ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የዚህ አንቀጽ ይዘት የቃላት መቃናት የተደረገበት ከመሆኑ በስተቀር የተለወጠ ነገር የለም። ቅጣቱን በተመለከተ ግን በንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር እሥራቱ ከ፮ ወር ወደ አንድ ዓመት መቀጮው ከአምስት መቶ ብር ወደ አንድ ሺህ ብር ከፍ እንዲል ሆኗል።

አንቀጽ ፬፻፴፰ <u>የመንግሥት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ አልነበረም። ማንም ሰው ከመንግሥት ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ወይም ከፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት በመንግሥት ሠራተኛ ሲጠየቅ ቀርቦ ለማስረዳት ተገቢውን መልስ ለመስጠት፣ ሰነዶችን ለማቅረብ ወይም ለማስመርመር ወይም ልዩ ልዩ ቤቶችን፣ ቦታዎችንና ወይም ነገሮችን ለማስፈተሽ እምቢተኛ ከሆነ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ እንዲቀጣ ለማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ ሆኖ ተረቅቋል።

አንቀጽ ፬፻፴፱ <u>እሽጎችን መቅደድ መስበርና ዕቃዎችን መውሰድ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፪ ጋር የተዛመደ ነው። ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፪ ጋር የተዛመደ ነው። በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "በጥበቃ ላይ ያለውን ዕቃ" የሚለው ሀረግ አሳስፈላጊ ስለሆነ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሎ ተጽፏል። በድንጋጌው መግቢያ ላይ ተሰርዞ "ህጋዊ ምክንያት መብት ሳይኖረው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ"... ሕጋዊ ስልጣን "ባንድ ትዕዛዝ ምክንያት መብት ሳይኖረው" ተብሎ ተተክቷል፤ "አውቆ" የሚለው ቃል "አስቦ" በሚል ተተክቷል ቅጣቱን በተመለከተ እሥራቱ በቀላል እሥራት ምትክ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት መቀጮው የገንዘብ መቀጮ መባሉ ቀርቶ እስከ አስር ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፬፻፵ <u>መቃወምና አለመታዘዝ</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፫ ላይ የተወረሰ ሲሆን የቀድሞው ድንጋጌ የንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) የተንዛዛና ግልጽነት የሚጎድለው ስለሆነ ብሔራዊ ሆነ አጭርና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተስተካክሏል። በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) ውስጥ "ብሔራዊ ሆነ ወታደራዊ ባለሥልጣን" የሚለው ሀረግ "የመንግሥት ሠራተኛ" በሚለው ሀረግ የሚሸፈን ስለሆነ ተሰርዞ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል፤ ዓረፍተ-ነገሩ ሌላ ማስተካከያም

www.abyssinialaw.com

ተደርጎበታል። የቅጣቱን ጣራ በተመለከተም እሥራቱ ከአንድ ወር ወደ አንድ ዓመት፣ መቀጮዉ ከአንድ መቶ ብር ወደ አንድ ሺህ ብር ከፍ ብሏል። የንዑስ ቁጥር (፪) ዓረፍተ-ነገርም ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፬፻፴፩ <u>የኃይልና የማስገደድ ድርጊት</u>

ይህ አንቀጽ ከቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፷፩ ላይ የተወረሰ ሲሆን የኃይልና የማስገደድ ስራ" የሚለው ስያሜ "የኃይልና የማስገደድ ድርጊት" በሚል ተተክቷል። ይዘቱን በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) መንደርደሪያ ላይ "አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን፣ ወይም ሰራተኛ ወይም አንድ የሕዝብ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ሹም ወይም የዚሁ መሥሪያ ቤት አባል. . " የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "አንድ የመንግሥት ሠራተኛ. " በሚል ተተክቷል። ምክንያቱም የተጠቀሱት ሁሉ በአንቀጽ ፬፻፪ ለመንግሥት ሠራተኛ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ ይካተታሉና ነው። በፊደል ተራ (ሀ) ላይ "…. የሥራው ስልጣን የሚፈቅድለትን ያገልግሎት ጉዳይ … ያሰናከለ ወይም እንዲሰራ ያስገደደ…." የሚሉት ሁለት አማራጮች በቂ ስላልሆኑ "<u>ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ</u>" ያስገደደ እንደሆነ የሚል ሀረግ እንዲጨመር ተደርጓል። የቅጣቱን ጣራ በተመለከተም በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) እና (ለ) ሥር እሥራቱ ከስድስት ወር ወደ ሦስት ዓመት መቀጮው ከሶስት መቶ ብር ወደ አምስት ሺህ ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፪) ሥር የተደነገገው ቅጣት ለወንጀሉ አነስተኛ ስለሆነ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራትና እስከ ብር አስር ሺህ የሚደርስ መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ፣ "በዚህም ምክንያት የአካል መቁሰል ወይም ጉዳት በተበዳይ ላይ ደርሶ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ለማክበድ ይችላል" የሚለው አነጋገር ግልጽ ስላልሆነ "የእጅ እልፊቱ ወይም የኃይል ተግባሩ በተበዳይ ላይ የአካል ጉዳት ወይም የጤንነት ጉድለት ያስከተለ እንደሆነ ስለወንጀሎች መደራረብ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል" በሚል ተተክቷል።

አንቀጽ ፬፻፴፪ <u>በሕብረት የሚፈጸም ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፴፪ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ "ሸብር" የሚለው ቃል "ረብሻ" በሚለው ቃል የተተካ ሲሆን ግልጽ በሆነና አጠር ባለ አነጋገር ተሻሽሎ ተረቅቋል።

www.abyssinialaw.com

## ርዕስ አራት
## በፍትሕ አስተዳደር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
### ምዕራፍ አንድ
### በዳኝነት ሥራ አካሄድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፬፻፵፫ ወንጀልን አለማስታወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፫ ሆኖ ገብቷል::

በቀድሞ ድንጋጌ ላይ "ለፍርድ ባለሥልጣን ስላለመግለጽ" የሚለው ስያሜ በድንጋጌው ውስጥ ተለይተው የተዘረዘሩትን ወንጀሎች ለነዚሁ ባለሥልጣኖች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሕጋዊ ባለሥልጣኖች መግለጽ ግዴታ መሆን ስለሚገባው የድንጋጌው ስያሜ ተሰርዞ "ወንጀልን አለማስታወቅ" በሚል ተተክቶአል:: በንዑስ ቀጥር (፩) መንደርደሪያ ዓብይ ሐረግ ውስጥ የሚያከራክር "ሕጋዊ" የሚለው ሐረግ ግልጽ ስላልሆነ ተሰርዞ "በቂ" በሚል ቃል ተተክቶአል:: በዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በ(ሀ) ከተመለከተው መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል:: በዚህ በንዑስ ቁጥር ፩ (ሀ) ውስጥ የሚገኘው "የሚያስከትል የወንጀል ሥራ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የሚያስቀጣ ወንጀል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ በመሆኑ ተሰርዞአል:: በዚሁ በፊደል ተራ (ለ) ውስጥ "ለሕዝብ ፀጥታ ወይም ሰላም ወይም ጥቅም" በሚለው ሐረግ ምትክ "ለሕዝብ ደህንነት ወይም ሰላምና ሥርዓት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: ቅጣትን በተመለከተ የቀድሞው ድንጋጌ ቅጣት አነስተኛ ስለሆነ ቅጣቱን ከፍ በማድረግ "እስከ አንድ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ወይም እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::" በሚለው ሀረግ ተተክቶአል:: የቁጥር ፬፻፴፰(፪) ድንጋጌ አገላለጽ ተለውጦ ፍሬ ነጥቡን ብቻ ሊገልጽ በሚችል ሁኔታ "..በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፵፮ እና ፫፻፴፯ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ናቸው" በሚል ዓረፍተ-ነገር ብቻ እንዲገለጽ ተደርጎአል:: ከዚህ በቀር በቁጥር ፬፻፴፰ በተመለከተው ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጽ ፬፻፵፫ ሆኖአል::

አንቀጽ ፬፻፵፬ በጠቋሚዎች እና በምስክሮች ላይ የሚፈጸም ወንጀል*

ይህ አዲስ አንቀጽ እንዲካተት የተደረገው በወንጀል ጉዳዮች ላይ ጥቆማና ማስረጃ በሚያቀርቡ ሀቀኛ ዜጎች ላይ እና በወንጀል ጉዳይ ላይ ምስክር ሆነው በሚቀርቡ ሰዎች ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመከላከልና ለመቅጣት የሚያስችል ድንጋጌ እንዲኖር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ እየወጡ ያሉ፣ ወንጀል መከላከልን የሚመለከቱ ኮንቬንሽኖች ሲታዩ ተመሳሳይ ጥበቃ እንዲሰጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስገነዝቡ በመሆናቸው ይኸው በድንጋጌው ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል:: ስለዚህም ተራ ጥቃት በሆነ ጊዜ በእስራትና በመቀጫ እንደሚያስቀጣ፣ ከዚህ ያለፈ ጥቃት ሆኖ በተበዳዩ ላይ ጉዳትን የሚያደርስ ከሆነ የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት የተደነገጉ ሌሎች ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ተገልጾ ተረቅቋል::

---

* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 444 ንዑስ አንቀጽ (1) "መረጃ የሰጠ ሰው" የሚለው ቃል "መረጃ በሰጠ ሰው" ተብሎ ይነበብ::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፵፭ መሸሸግና መርዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፴፱ "..አንድ ተከሣሽ ወደ ፍርድ እንዳይቀርብ ስለመደበቅ" የሚለው የድንጋጌው ስያሜ በድንጋጌው ውስጥ ተለይተው የተዘረዘሩት ድርጊቶችን በሚገባ ስለማያመለክት "መሸሸግና መርዳት" በሚል ተተክቶአል:: በድንጋጌው መጨረሻ "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ያስቀጣል" የሚለው ሐረግ የእሥራቱን ዓይነት በግልጽ ስለማያመለክት "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል" በሚለው ሐረግ እንዲተካ ተደርጎአል::

አንቀጽ ፬፻፵፮ የፍትሕን ሥራ ማሳሳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፮ ሆኖ ገብቷል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵ ስያሜ የፍርድን ሥራ ብቻ የሚመለከት ሳይሆን አጠቃላይ "የፍትሕን አሠራር የሚመለከት" መሆኑን ለማሳየት "የፍርድን ሥራ እንዲሣሣት ስለማድረግ" የሚለው ሐረግ ተለውጦ "የፍትሕን ሥራ ማሳሳት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: ሁለቱም ንዑሳን ክፍሎች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል:: በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ የተመለከተው "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ ስለሆነ ተሰርዞአል:: የቁጥር ፬፻፵ ድንጋጌ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በቀር አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጽ ፬፻፵ ሆኖአል::

አንቀጽ ፬፻፵፯ በሐሰት መወንጀል ወይም መክሰስ፣

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፯ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵፩ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል:: በፊደል ተራ (ለ) የተመለከተው "ወይም" የሚለው ቃልም ያለቦታው የገባ በመሆኑ ተሰርዞአል:: ንጹሕ በሆነ ሰው ላይ በሐሰት ላይ የተመሠረተ ክስ ማቅረብ የሰዎችን ደህንነት የሚጎዳ አደገኛ ድርጊት ስለሆነ ከባድ ወንጀል በመጥቀስ ከወንጀሉ ንጹሕ የሆኑ ሰዎችን በሐሰት የሚወነጅሉ በቂ ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ "እስከ ስድስት ወር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እና መቀጮ ይቀጣል:: ሆኖም በሐሰት የቀረበው ውንጀላ በተወንጃዩ ላይ ከዚህ በላይ ከተመለከተው ቅጣት የበለጠ ቅጣትን አስከትሎ እንደሆነ በንጹሁ ሰው ላይ በተወሰነው ቅጣት ልክ ይቀጣል" በሚል ሐረግ እንዲተካና እንዲስተካከል ተደርጎ ተሻሽሎአል:: ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በቀር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፬፻፵፰ ለፍትሕ እርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፰ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) መንደርደሪያ ውስጥ "በሥርዓት የተጠራ" በሚለው ሐረግ ውስጥ "በሥርዓት" የሚለው ንዑስ ሀረግ ተሰርዞ "በሕጉ መሠረት" በሚል ሀረግ ከተተካና "ወይም በሕጉ መሠረት የተጠራ ወይም ተከሣሽን ወይም ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘው" የሚል ሀረግ ገብቶ ከተከታዩ "ማንኛውም ሰው" ከሚለው ሀረግ ጋር አብሮ እንዲነበብ በማድረግ ተሻሽሎ ገብቶአል።

የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ተከፍሎ ነበር። ሆኖም አዲስ ድንጋጌ በንዑስ ፊደል ተራ (ለ) ስር እንዲካተት በመደረጉ የቀድሞው የፊደል (ለ) ድንጋጌ ፊደል ተራ (ሐ) ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል። አዲስ የፊደል (ለ) ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት ማስረጃን ወይም ተከሳሽን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ ታዝዞ ትዕዛዙን ያልፈጸመን ሰው የሚመለከት አነጋገር በቀድሞው ድንጋጌ ውስጥ ባለመኖሩ ነው።

በዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) በ(ሀ) በ(ለ) እና በ(ሐ) ፊደል ተራዎች የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በ(ሀ) እና በ(ለ) መጨረሻ ላይ ወይም የሚል ቃል ገብቶአል። በፊደል ተራ (ለ) የተመለከተው "ወይም" የሚለው ቃልም ያለቦታው የገባ በመሆኑ ተሰርዞአል። ለንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ ቅጣት "እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ወይም ተደጋጋሚ እልከኛ ሲሆን እስከ አንድ ወር ለመድረስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።" የሚለው ሀረግ ተሻሽሎ "ከሁለት ወር ባልበለጠ ቀላል እሥራት ወይም እስከ አንድ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጫ ይቀጣል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) "አጥፊው ሰው" በሚለው ሀረግ ምትክ "ጥፋተኛው" የሚለውን እንዲተካ ተደርጎአል። የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ ይኸው ሰው ሀሰተኛ ምክንያት በማቅረብ ከግዴታው የዳነ እንደሆነ በፈጸመው ያጭበርባሪነት ወንጀል ሊደርስበት የሚገባው ከባድ ቅጣት አወሳሰን ደንብ የተጠበቀ መሆኑን በመግለጽ የቀላል እሥራቱ ቅጣት እስከ መደበኛው ቅጣት ጣራ ለመድረስ እንደሚችል ተደርጎአል። በሌላ በኩል ግን በፍትሕ አሰጣጥ እርዳታ መስጠትን እንቢ የማለት ወንጀል የተፈጸመው በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ፊት ከሆነ ቀጠሮ ሳያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ለመወሰን እንዲችል ለማድረግ "ወንጀሉ የተፈጸመው በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ፊት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው ሌላው አካል ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ ከዚህ በላይ የተደነገገውን ቅጣት ለመወሰን ይችላል።" የሚል አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ገብቶአል።

በዚህ ድንጋጌ ላይ የሚገኘው "የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለው አካል" የሚለው ሐረግ ሲያከራክር ቆይቷል። በአንድ በኩል "እንደ ፖሊስ የመሳሰሉትን የምርመራ አካላት ሊያካትት ይገባል፤ በእነዚህ አካላት ቀርቦ በሐሰት የመሰከረ ሰው በሐሰት በመመስከሩ በወንጀል ሊቀጣ ይገባል።" የሚል አስተያየት ይቀርባል። በሌላ በኩል እንደ ፖሊስ ያሉ የምርመራ አካላት የዳኝነት ነክ ሥልጣን እንዳላቸው ሊቆጠሩ እንደማይገባ አስተያየት የሚሰጡ የሕግ ባለሙያዎች አሉ።

ሊደገፍ የሚገባው የኋለኛው አስተያየት ነው። በፖሊስ መስሪያ ቤትና በሌሎች የምርመራ አካላት የሚከናወነው የማስረጃ አሰባሰብ፣ በመነሻነት በፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ ወይም አንዳንድ እርምጃ ለመውሰድ የሚረዳ እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት አያገለግልም። ምስክሮችም ከእነዚህ የምርመራ አካላት ዘንድ ቀርበው ቃል የሚሰጡት ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው በሚችል ሁኔታ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ በእውነት ባይመሰክሩ በሐሰተኛ ምስክርነት ይቀጡ የሚል አቋም መውሰዱ ሚዛናዊ ሆኖ አይታይም።

www.abyssinialaw.com

ስለዚህ "የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለው አካል" የሚለው ሐረግ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሳይሆኑ፣ የዳኝነት ውሳኔ ለመስጠት በሕግ የተቋቋሙ ወይም የተፈቀደላቸው አካላትን እንጂ ጉዳዮችን የማጣራት ወይም ምርመራ የማካሄድ ሥልጣን ያላቸውን አካላት ሊያካትት እንደማይገባ ተደርጎ ተወስዷል።

አንቀጽ ፬፻፵፱ ፍርድ ቤትን መድፈር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፱ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵፫/፩/ ድንጋጌ ላይ "በሚከናወንበት ወይም በችሎት ላይ ፍርድ ቤቱንና ዳኛውን የደፈረ የሰደበ በፍርድ ቤቱና በዳኛው ወይም ከአባሎቹ በአንደኛው ላይ ያፌዘ የዛተ ወይም በማናቸውም ዓይነት አድራጎት የሥራውን መልካም አካሄድ በማሰናከል ሁከት ያደረገ" የሚለው ሀረግ፣ አነጋገሩን በይበልጥ ግልጽ በሚያደርግ ሁኔታ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተከፈለ ሲሆን፦

« ሀ. ፍርድ ቤቱን ወይም የዳኝነት ሥራ በማከናወን ላይ ያለውን ዳኛ በማናቸውም መንገድ የሰደበ፣ ያወከ ወይም በነዚሁ ላይ ያፌዘ ወይም የዛተ እንደሆነ፤ ወይም

ለ. የፍርድ ቤቱን ሥራ በማናቸውም ሌላ መንገድ ያወከ እንደሆነ፤" እንዲል ተደርጓል። ይህም የፍርድ ቤቶችን ሥራ በሚያውክ መንገድ በማንም ሰው ላይ የሚፈፀመውን ሕገ-ወጥ ድርጊት ያጠቃልላል።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ይህ ድፍረት የተፈጸመው በግልጽ ያልሆነ ወይም ከችሎቱ ውጭ የሆነ እንደሆነ...." የሚለው አገላለጽ ድርጊቱ በማናቸውም ሌላ ቦታ ምንጊዜም በዳኛ ላይ ቢፈጸም እንደሚያስቀጣ የሚደነግግ መስሎ በመታየቱና ይህ ግን የማይደገፍ በመሆኑ አገላለጹ ተሻሽሎ "ወንጀሉ የተፈጸመው ከችሎት ውጭ ሆኖ ዳኛው ሥራውን እያከናወነ ባለበት ጊዜ ከሆነ..." በሚል ተተክቷል።

የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ ግልጽነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በድንጋጌው መጨረሻ ላይ የተካተተው አጣቃሽ ቁጥር ስህተት በመሆኑ አገላለጹ ተሻሽሎና አጠር ተደርጎ "ወንጀሉ የተፈጸመው በችሎት ወይም በማናቸውም የዳኝነት ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ሆኖ በኃይል ወይም በማስገደድ የሆነ እንደሆነ አግባብ ያለው ድንጋጌ /አንቀጽ ፬፻፵፩/ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ" እንዲል ተደርጎ ተረቋል።

አንቀጽ ፬፻፶ የፍርድ ሂደትን ምስጢር መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵፬ ስያሜ ላይ "የፍርድ ሥነ-ሥርዓት" የሚለው ሀረግ ወጥቶ "የፍርድ ሂደት" የሚለው ሀረግ ገብቶአል።በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ"…. ያስፈቃድና መብታዊ የሆነ ከፍ ያለ ምክንያት ሳይኖረው..." የሚለው ሐረግ ተሰርዞ ሕጋዊ ፈቃድ ወይም ይቅርታ የሚያሰጥ ምክንያት ሳይኖረው" በሚለው ሀረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) በተመለከተው አኳኋን ወንጀሉ የተፈጸመ እንደሆነ "እስከ ሶስት መቶ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ወይም እስከ ስድስት ወር ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።" ተብሎ ተደንግጓል። የእሥራቱ ቅጣት እስከ ስድስት ወር ብቻ

www.abyssinialaw.com



ሊደርስ መቻሉ በቂ ነው መቀጮውን በተመለከተ ግን አነስተኛ በመሆኑ "አምስት መቶ ብር በሚደርስ መቀጮ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተመለከቱት አጣቃሽ ቁጥሮች በአግባቡ እንዲጠቀሱ ተደርጓል፤ ድንጋጌውም ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፩፻፶፩ <u>የፍርድ ሂደትን በተመለከተ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተከለከለ ዘገባ ማግለጽ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፩ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፩፻፵፰ ስያሜ ላይ "ትክክለኛ ያልሆኑትን ወይም የተከለከሉትን ሥራ ማስታወቫዎች በአደባባይ ስለመግለጽ" የሚለው ሀረግ ከድንጋጌው ጋር እንዲስማማ ለማድረግ "የፍርድ ሂደትን በተመለከተ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተከለከለ ዘገባ መግለጽ" በሚል ሀረግ እንዲስተካከል ተደርጎአል:: በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ የሚገኘው "ሆነ ብሎ ያልተረጋገጡትን /ያልተስተካከሉትን/ ያልታረሙትን ወይም የተዘባረቁትን የወሬ ምንጮች ማስታወቫዎች በምርመራ የተጣሩ ጉዳዮች ወይም የሥራ መግለጫዎች" በሚለው ሀረግ ምትክ "በቀጠሮ ወይም በመስማት ላይ ስላሉ ወይም ውሳኔ ስላላገኙ የዳኝነት ጉዳዮች ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተዛባ መረጃን፣ ማስታወቫን ፍሬ አሳብን ወይም ዘገባን" የሚለው ሀረግ ተተክቶና ተሻሽሎ እንዲገባ ተደርጎአል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተደነገገው ጥፋት የሚጣለው ቅጣት "እስከ አምስት መቶ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በተለይም የሕብረተሰቡ አስተሳሰብ እንዲታወክ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ የሚችል በሆነ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል::" በሚል ሀረግ ተተክቶአል:: በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውም ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ከመሆኑም በቀር በውስጡ የተመለከቱት አጣቃሽ አንቀጾች ድንጋጌዎች በአግባቡ እንዲጠቀሱ ሆኗል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በፍትሕ ሥራ ላይ ሊደረግ በሚገባው በእውነተኛነትና</u>
<u>በታማኝነት ተግባር ላይ የሚፈጸም ወንጀል</u>

መፍረድ መወሰን ነው:: የሚወሰነው ሁሉ ሕግን የተከተለ፣ ቀጥተኛና ፍትሐዊ ላይሆን ይችላል:: ሕግን በመከተል፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ እና ፍትሐዊ ውሳኔ ሲሰጥ ፍትሕ ተሰጠ ሊባል ይቻላል:: በምዕራፍ ሁለት ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለምሳሌም እንደ ሐሰተኛ ምስክርነት (አንቀጽ ፩፻፶፫)፣ በሙግት ጊዜ ማጭበርበር (አንቀጽ ፩፻፶፮)፣ ለፍትሕ ተግባራት አስፈላጊ በሆነው ዕውነተኛነትና የታማኝነት ግዴታ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው:: ስለዚህ "በፍርድ ሥራ ላይ በሚል..." ሐረግ የሚጀምረው የምዕራፍ ሁለት ስያሜም በዚህ አኳያ ሊታረምና ሊሻሻል ስለሚገባው "በፍርድ ላይ ሊደረግ በሚገባው በእውነተኛነትና በታማኝነት ተግባር ላይ ስለሚሠራ ወንጀል" የሚለው ስያሜ ተሰርዞ "በፍትሕ ሥራ ላይ ሊደረግ በሚገባው በእውነተኛነት በታማኝነት ተግባር ላይ የሚፈጸም ወንጀል::" በሚል ስያሜ ተተክቶአል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፶፪ <u>አንድ ተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ወንጀሉን በግልጽ ስለማያብራራ የቃላት ማስተካከያና የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ሆኖ ገብቶአል::

አንቀጽ ፬፻፶፫ <u>ሐሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ከይዘቱ ጋር የሚጣጣም ስለማይመስል "ሐሰተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል:: የቁጥር ፬፻፵፪/፩/ መግቢያ "ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው የአስተዳደር፣ የፍትሐብሔር፣ የወንጀል ወይም የሽምግልና የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ" የሚለው ሀረግ የተንዛዛ በመሆኑ አጠር ባለ ሁኔታ "የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ" በሚል አጠቃላይ ሀረግ እንዲተካ ተደርጎ ተሻሽሎአል::

በንዑስ ቁጥር (፫) "ተርጓሚ" የሚለው ሐረግ መተርጎምና ማስተርጎም የተለያየ ሥራ ስለሆነ ተርጓሚ ከሚለው ቃል በኋላ ያለው "ና" ጠፍቶ "ወይም" በሚል ቃል ተተክቶአል:: ሐሰተኛ ምስክርነት በፍርድ ቤት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቢሰጥ የፍትሕ አሠራርን ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ስለሆነ በንዑስ ቁጥር (፩) "ፍርድ ቤቱን" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ "ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያለው አካል" የሚል ሀረግ ታክሏል::

ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በላይ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያና የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፬፻፶፬ <u>ቃልን ማቃናትና መለወጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፬ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵፫ መግቢያ ላይ "አጥፊው ሐሰተኛ ምስክርነቱ ማስታወቂያው የምርመራ አስተያየቱ ወይም ሐሰተኛ ትርጉሙ" የሚለው ሐረግ አጠር ባለና ሁሉን በሚያካትት ሁኔታ "ሐሰተኛ ምስክርነቱን፣ አስተያየቱ፣ በሀሰት መተርጎሙ ወይም ማስተርጎሙ፣ "በሚለው ሀረግ በመተካት እንዲሻሻል ተደርጎአል:: አላስፈላጊ ነገሮች ተሰርዘው ድንጋጌው በአጭሩና በግልጽ እንዲቀረጽ ተደርጎአል::

በተጨማሪም ድንጋጌው የቃላት ማስተካከያና የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፶፫ <u>መገፋፋትና ማግባባት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፫ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ላይ የተወሰነው ቅጣት ከወንጀሉ ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ ቅጣቱ እስከ አንድ ዓመት መሆኑ ቀርቶ እስከ ሦስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት እንዲሆን ተደርጎ ተሻሽሎአል። ከዚህም በቀር ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያና የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል።

የቀድሞው ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደረገ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ገብቷል። በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው "የኃይል ሥራ በመስራት፣ የዛቻ ወይም የማስፈራራት ተግባር በመፈፀም ወይም የማይገባ ጥቅም በመስጠት ወይም በማቅረብ ከሁለት ዓመት በላይ በጽኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ" እንደሆነ "ወይም በምስክር አሰጣጡ ወይም ማስረጃ አሰባሰቡ ላይ ጣልቃ በመግባት ያደናቀፈ እንደሆነ፣ ወይም በሕግ ማስከበር ሥራ በተሰማራ ወይም በመንግሥት ሠራተኛ መደበኛ ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ያወከ እንደሆነ፣" እስከ ሰባት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ የሚያደርግ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል።

አንቀጽ ፬፻፶፬ <u>በሙግት ጊዜ ማጭበርበር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፬ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፶ በተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በንዑስ በፊደል ተራ (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚለው ቃል ገብቶአል። በንዑስ በፊደል ተራ (ለ) መጨረሻ "ወይም" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ..." እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለው ከወንጀሉ ክብደት ጋር ሲመዛዘን አንሶ ስለሚገኝ ይህ ሀረግ ተሰርዞ "እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል።

በተጨማሪም ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የአቀራረጽ ለውጥና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፬፻፶፭ <u>የፍትሕን ሂደት ለማዛባት በተንኮል የሚፈጸም የወሬ መግለጽ ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፶፭ ሆኖ ገብቷል።

የፍርድን ውሣኔ ለማሳሳት ትክክለኛ ያልሆኑ ወሬዎችን በልዩ ልዩ መንገድ ለሕዝብ በመንዛት ለሚፈጸም ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፶፩ የተመለከተው እስከ አምስት መቶ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ ወይም እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት ቅጣት የሚያንስ ነው። ስለዚህ "እስከ አምስት መቶ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ወይም እስከ ሶስት ወር ሊደርስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "እስከ አንድ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ፣ ወይም እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

 www.abyssinialaw.com

ከዚህም በቀር ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የአቀራረብ ለውጥና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፬፻፵፰ <u>በአንድ ወገን የተከራካሪ ጥቅም ላይ ያከህደት ተግባር መፈጸም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፵፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፵፯/፩/ "ባለሥልጣን ፍርድ ቤት" የሚለው ሐረግ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጭ ያሉትን የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያላቸውን አካላት ስለማይጨምር ተሰርዞ "በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ፊት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያ አዲስ መስመር "ተከሣሹ ይህን ሥራ የፈጸመው ከተቃዋሚው ወገን ጋር በመስማማት እንደሆነ..." ከሶስት ወር የማያንስ የቀላል እሥራት፣ እንዲሁም "በአፍቅሮ ንዋይ ሰሜት እንደሆነ" እስከ አሥር ሺህ ብር ለመድረስ የሚችል መቀጮ" ተብለው የተመደቡት ቅጣቶች ከወንጀሉ ጋር ሲመዛዘኑ ስለሚያንሱ የእስራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ መቀጮው ደግሞ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ እንዲሆን ከፍ ተደርጐ ተቀርጿል፡፡

በዚህ ንዑስ ቁጥር በመጨረሻው አዲስ መስመር፡፡" የግል ነጻነትን የማሳጣቱ ቅጣት ጽኑ ሆኖ ከፍ ያለ ጥፋት በሆነ ጊዜ እሥራቱ፡፡" በሚለው ሐረግ ለመግለጽ የተፈለገው ስለቅጣቱ ስለሆነ ተሰርዞ "ቅጣቱ" በሚል ቃል ተተክቶአል፡፡

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲገባ የተደረገ ሲሆን ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲፈጸምም እንዲያስቀጣ የሚደነግግ ነው፡፡ በተጨማሪም ድንጋጌው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>

<u>በወንጀል ፍርድ አፈጻጸም ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፬፻፶፱ <u>ተጨማሪ ቅጣቶችን የመከላከልና የመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አለማክበር</u>

ይህ አንቀጽ የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፰ ድንጋጌ ሲሆን የድንጋጌው ስያሜና ይዘት ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቷል፤ በውስጡ የተጠቀሱት የድንጋጌ ቁጥሮችም በዚህ የወንጀል ሕግ መጠቀስ እንደሚገባቸው ሆነው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፬፻፷ <u>የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማስናከል</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፶፱ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን ስያሜው ከተቃናና የይዘቱም አቀራረብ ከተሻሻለ በኋላ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፬፻፷ ሆኖ ገብቶአል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፷፩ <u>የእሥረኛ ማምለጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

የቀድሞው ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን በዚህ ሕግ ግን ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል። ይኸውም አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንድ የገባ ሲሆን የቀድሞው ድንጋጌ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ ሁለት፣ የቀድሞው ድንጋጌ ሁለተኛው ፓራግራፍ ደግሞ ተስተካክሎ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ሆኖ ገብቷል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ የገባው ድንጋጌ ጥፋተኛው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ምንም የኃይል ተግባር ሳይፈጽም ከተያዘበት ቦታ የሚያመልጥበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እንዲቀጣ የሚያደርግ ነው።

ሆኖም ጥፋተኛው የተፈረደበትም ይሁን ገና ያልተፈረደበት ወይም እንዲቆይ የተደረገበት ሁኔታ በመደበኛ እስራትም ይሁን በማረፊያ ቤት እስራት ሁሉንም አይነት ሁኔታ እንዲያካትት ለማድረግ "በፍርድ ባለስልጣን ተፈርዶበት በሕግ አግባብ ተይዞ በማናቸውም ዓይነት እስር ቤት እንዲቆይ የተደረገ ሰው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ማንም ሰው በሕግ አግባብ ተይዞ፣ ታስሮ ወይም ተግዞ..." በሚል ተተክቷል።

ንዑስ አንቀጽ ሁለት የሚመለከተው በሰዎች ላይ የኃይል ተግባር በመፈጸም ወይም በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ጥፋተኛ ሲሆን ቅጣቱም እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት እንዲሆን ተደርጓል።

ንዑስ አንቀጽ ሶስት ደግሞ በቀድሞው ድንጋጌ በሁለተኛው ፓራግራፍ የነበረውን ቅጣቶችን የመደመር ስሌት በመተው እንደ ሁኔታው ስለተደራራቢ ወንጀሎች ወይም ስለ ደጋጋሚነት በተጻፉት ድንጋጌዎች መሠረት በጥፋተኛው ላይ ቅጣት እንደሚወሰን የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፬፻፷፪ <u>እሥረኛ እንዲያመልጥ ማመቻቸትና መርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፶፪(፩) "የመንግሥቱን ሥራ ግዴታ ስለመጣስ በተመለከተው አወሳሰን ድንጋጌ ውጭ በሆነ አድራጎቱ..." የሚለው ሐረግ ግልጽ ባለመሆኑ ተሰርዞ "የመንግሥት ሠራተኛ ሳይሆን" በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) "እጅግ ቢያንስ" የሚለው ሐረግ "እስከ ሶስት ወር የሚደርስ" ከሚለው ሐረግ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ግልጽ ለማድረግ "እጅግ ቢያንስ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ እሥራት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በዚህ ንዑስ ቁጥር (፪) በተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ለ) በተገለጹት አኳኋን ወንጀሉ ከተፈጸመ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ቅጣት ለወንጀሉ የሚያንስ ስለሆነ "እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት" በሚለው ሐረግ ውስጥ "አምስት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ሰባት" በሚል ቃል ተተክቶአል። በፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) በተመለከተው አኳኋን ወንጀሉ ከተፈጸመ

www.abyssinialaw.com

ቅጣቱ ግዴታ ስለሆነ " ለመሆን የሚቻለው "የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የሚሆነው" በሚል ቃል ተተክቶአል:: ወንጀሉ የተፈጸመው በፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) በተመለከተው አኳኋን ቢሆንም እያንዳንዱ ሊያስቀጣ የሚችል መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ(ሀ) ከተመለከተው ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል:: በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ ላይ የተመለከተው "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ በመሆኑ ተሰርዞአል:: እንዲሁም "ብሔራዊ ወይም ወታደራዊ ቢሆንም" የሚለው ሀረግ አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዟል:: በተጨማሪም "የሃያ ዓመት ጽኑ እሥራት" በሚል ሀረግ የተገለጸው ቅጣት ዝቅተኛውን /መነሻውን/ የሚያመለክት ስለሚመስል "ቢያንስ" የሚል ቃል ከፊቱ ገብቶ "ቢያንስ የሃያ ዓመት ጽኑ እሥራት" በሚል እንዲነበብ ሆኖ ተሻሽሎአል:: ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በላይ ማስተካከያም ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፬፻፷፫ <u>የጦር ምርኮኞችና የወታደራዊ ግዞተኞች ማምለጥና እንዲያመልጡ መርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፫ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ስለምርኮኞችና የወታደር ግዞትኛ ማምለጥ ብቻ ሳይሆን እንዲያመልጡ ስለመርዳትም የሚደነግግ ስለሆነ ስያሜው ይህንኑ ሁኔታ እንዲገልጽ ለማድረግ የቃላት ማሻሻያ ተደርጎበት "የጦር ምርኮኞችና ወታደራዊ ግዞተኞች ማምለጥና እንዲያመልጡ መርዳት" በሚል ተተክቶአል:: ድንጋጌው ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በቀር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቷል፣ በውስጡም የተመለከቱት ቁጥሮች በዚህ የወንጀል ሕግ መጠቀስ በሚገባቸው ሁኔታ ተስተካክለዋል::

አንቀጽ ፬፻፷፬ <u>የእሥረኞች አመጽ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፬ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ "ግርግር" የሚለው ቃል በድንጋጌው ውስጥ የተገለጸውን አሳብ የሚገልጽ ቃል ባለመሆኑ ተሰርዞ ወንጀሉን በሚገልጸው "አመጽ" በሚል ቃል ተተክቶአል:: በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በ(ለ) ከተመለከተው መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል:: በ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) በተመለከቱት አኳኋን ወንጀሉን የሰራው ሰው ከሶስት ወር ባነሰ ቀላል እስራት እንዲቀጣ ማድረጉ በቂ አይደለም:: ከሶስት ወር ባላነሰ የሚለው ሀረግ በ(ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) በተመለከተው አኳኋን ለሚፈጸም ወንጀል የመጨረሻ አነስተኛ ቅጣት የሶስት ወር ቀላል እስራት መሆኑን ያረጋግጣል:: ስለዚህ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ወር በላይ ለመወሰን እንዲችል "ከሶስት ወር እስከ አምስት ዓመት" የሚለው ሀረግ ተተክቶአል:: በንዑስ ቁጥር (፪) የማስገደድ ወይም የኃይል ሥራ ሳይፈጸም አመጽን ማዘጋጀት ወይም መምራት ያስቀጣል ተብሎ የተመደበው እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ለወንጀሉ የሚያንስ ስለሆነ እንደወንጀሉ ክብደት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ለመቅጣት እንዲቻል "እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል" በሚለው ሐረግ ውስጥ "ሶስት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "አሥር" በሚል ቃል ተተክቶአል:: የድንጋጌው ሶስቱም ንዑስ ቁጥሮች ግልጽ እንዲሆኑ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ ሦስት ንዑሳን አንቀጾች ሆነዋል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፬፻፷፮ <u>አካባቢያዊ ክልከላን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፮ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ከይዘቱ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ "አካባቢያዊ ክልከላን መጣስ" በሚል ተሻሽሎአል። አንቀጹ የሚመለከተው የጥንቃቄ እርምጃ የተወሰነበት ወንጀለኛ ነው። በወንጀለኛነት ቅጣት የተወሰነበት ግለሰብ ቅጣቱን ሳይፈጽም ሌላ ወንጀል ለመፈጸም እንደሚችል ግልጽ ነው። ቅጣቱን ሳይጨርስ ለፈጸመው ወንጀል የተወሰነው ቅጣት እንደማንኛውም ወንጀለኛ መቀጣት የሚገባው መሆኑ ግልጽ እንዲሆን ተደርጎአል።

<u>ርዕስ አምስት</u>
<u>በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምጽ አሰጣጥ</u>
<u>ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

ቀደም ሲል በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ከዚህ በላይ በመግቢያው ላይ የተገለጸው "አንቀጽ አምስት" መባሉ ቀርቶ "ርዕስ አምስት" ተብሎ "Title" ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር እንዲስማማ ተደርጓል። የርዕሱ ስያሜ በተመለከተም ግልጽነት ስለሌለው ተሰርዞ "በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምጽ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች" ተብሎ ተተክቷል።

አንቀጽ ፬፻፷፯ <u>ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል</u>

ይህ አንቀጽ የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷ ድንጋጌ የነበረ ነው። ስያሜውን በተመለከተ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የተቀረጸ ሲሆን በተለይ የእንግሊዝኛውን ቅጂ እንዲከተል ተደርጎ ተስተካክሏል። ይዘቱን በተመለከተ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርገዋል። ቅጣቱን በተመለከተም በአንቀጽ ፬፻፸፫ መሠረት ይወሰናል መባሉ ቀርቶ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራትና እስከ አንድ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፬፻፷፰ <u>የምርጫ ድምጽ የመስጠትን ወይም የመመረጥ መብትን መንካት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፰ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ስያሜም ሆነ ይዘት የቃላት መቃናት የተደረገበት ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተ እሥራቱ ከስድስት ወር ወደ ቀላል እሥራት፣ የገንዘብ ቅጣቱም "በገንዘብ መቀጮ" መባሉ ቀርቶ በመቀጮ እንዲል ተደርጎ ከወንጀሉ ክብደት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም የእስራቱን ቅጣት ወደ ሦስት ዓመት፣ መቀጮውን ከአምስት ሺህ ብር ወደ አስር ሺህ ብር ከፍ ያደርገዋል።

አንቀጽ ፬፻፷፱ <u>በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፱ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ ረዘም ያለና ግልጽነት የሌለው ስለነበር አጠር ተደርጎ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሏል። ይዘቱን በተመለከተ የወንጀሉ ባሕርይ ከጉቦ ጋር የተያያዘና ይህ ወንጀል ደግሞ በአሁኑ ጊዜ እንደከባድ ከሚቆጠሩት ወንጀሎች አንዱ

www.abyssinialaw.com

ስለሆነ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር "በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" መባሉ ቀርቶ "እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል" ተብሎ ተስተካክሏል፡፡ የንዑስ አንቀጽ (፪) ቅጣትም በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፬፻፷፱ <u>የማይገባ አሠራር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፷፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

ቀደም ሲል የነበረው ድንጋጌ በምርጫ ወቅት የማይገቡ አሠራሮች ተብለው በሌሎች አገር ሕጎች ውስጥ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር ሲነጻጸር ጠባብ ሆኖ ስለተገኘ ከፈረንሳይ፣ ከፖኪስታንና ከሕንድ ሕጎች ለአገራችን አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው የታመነባቸው ተለቅመው በሁለት አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች ውስጥ ተጠቃለው እንዲቀረጹ ሲደረግ ቀደም ሲል የነበረው ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የንዑስ አንቀጽ (፫) ተራ ፊደሎች ሆነው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ ማንኛውም ተመራጭ ለምርጫ ወጪ የሚሆነውን ገንዘብ ሕግ ወይም መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ከማንም ሰው፣ ቡድን፣ ወይም ድርጅት ቢቀበል፣ የምርጫ ወጪን ጣራ በመተላለፍ ወጪ ቢያደርግ፣ የምርጫ ሕግ የሂሣብ ደንቦችን ቢጥስ ወይም ወጪውን ሆን ብሎ አሳንሶ ቢያስታውቅ፤ በንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ ማናቸውም ሌላ ሰው ተመራጩ ሳይፈቅድለት ለምርጫ ወጪ የሚሆን ገንዘብ ቢሰበስብ፣ ቢከፍል ወይም በማናቸውም መንገድ አስተዋጽኦ ቢያደርግ፣ ሁለቱም እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራትና በገንዘብ እንደሚቀጡ ተመልክቷል፡፡ "ሕግ ወይም መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ" ተብሎ ለነዚህ ድንጋጌዎች የገባው አሁን ሊሰራበት የማይችል እንኳን ቢሆንም ለወደፊቱ አስፈላጊ ሆኖ ዝርዝር ሕግ ሊኖር እንደሚችል በመገመቱ ነው፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የአንቀጽ ፬፻፷፫ ይዘት በሙሉ የአዲሱ አንቀጽ ፬፻፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ይዘቱም ግልጽነት የሌለው ስለነበረ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር እንዲጣጣም ከተደረገ በኋላ ቅጣቱ ከ፮ ወር እሥራት ወደ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ከፍ እንዲል ሲደረግ መቀጮው በነበረበት ፀንቷል፡፡

አንቀጽ ፬፻፸ <u>በአመዘጋገብ ላይ የሚፈጸም ማጭበርበር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፸ ሆኖ ገብቷል፡፡

የዚህ ድንጋጌ ስያሜ ግልጽነት የሌለው ስለነበረ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አጠር ብሎ ተስተካክሎ እንዲጻፍ ተደርጓል፡፡ ይዘቱን በተመለከተም ቀደም ሲል የነበረው ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተብሎ የተስተካከለ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ እሥራቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት፣ መቀጮው ከአንድ ሺህ ብር ያልበለጠ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጨመረ ሲሆን ይህ ንዑስ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል በተለይ በእጩ ተመራጭ የሚፈጸም ከሆነ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጽኑ እሥራትና ከአሥር ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከአንድ ተመራጭ የሚጠበቀው የታማኝነት ሁኔታ ከፍ ያለ ሲሆን ስለሚገባ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፸፩ <u>በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸም የማጭበርበር ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፸፩ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ ድንጋጌ ሲያሜ ውስጥ "ሥራ" የሚለው "ድርጊት" በሚል ተተክቷል። ይዘቱን በተመለከተ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፸፪ <u>የወንጀሎች መደራረብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፸፪ ሆኖ ገብቷል።

የዚህ ድንጋጌ ሲያሜ ቀደም ሲል "የተለዩ ወንጀሎች" ይል የነበረው ሐረግ ከይዘቱ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ስለተገኘ ተሰርዞ "የወንጀሎች መደራረብ" በሚል ሀረግ ተተክቷል። በይዘቱ መጨረሻ "በተጨማሪነት" የሚለው ቃል ተሰርዞ "በተደራቢነት" በሚለው ቃል ተተክቷል፣ የቃላት ቅደም ተከተል ለውጥም ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፸፫ <u>የድምጽ አሰጣጥ ምስጢር አጠባበቅን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፸፫ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ሲያሜ ግልጽ ስላልነበረ ተሰርዞ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሏል።

አንቀጽ ፩፻፸፬ <u>የድምጽ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሳጥኖችን መውሰድና ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፸፬ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ሲያሜ ግልጽነት ስለሌለው ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ተስተካክሏል። ይዘቱን በተመለከተም ግልጽ ያለመሆኑ የጎላ ሆኖ ስለተገኘ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በሚገባ በተጣጣመ ሁኔታ እንዲስተካከልና ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፩፻፸፭ <u>ተጨማሪ ቅጣቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፸፭ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ይዘት የዓረፍተ-ነገርና የጽንሰ ሐሳብ ማስተካከያ ተደርጎበታል። በዚህም መሠረት የዐረፍተ-ነገሩ የአቀማመጥ ለውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሕዝባዊ መብት የመሻር ተጨማሪ ቅጣት የሚወሰነው የምርጫ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ ፌፎ ሳይሆን የተፈጸመው ወንጀል የእሥራት ቅጣት ያስወሰነ በሆነ ጊዜ ብቻ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ ተስተካክሏል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፸፮ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፸፮ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው የመጀመሪያ ፓራግራፍ ይዘት የቃላት መቃናት ተደርጎበታል። በመጨረሻው ፓራግራፍ ውስጥም "ነገሩ ከባድ በሆነና ተደጋግሞ በተሠራ ጊዜ" የሚለው ቀርቶ "ወንጀሉ ከባድ የሆነ እንደሆነ ወይም ተደጋግሞ የተፈጸመ እንደሆነ" በሚል በአማራጭ መልክ እንዲሆን ተደርጎ ተስተካክሏል።

ርዕስ ስድስት
በሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ
የሚፈጸሙ ወንጀሎች

ምዕራፍ አንድ
በሕዝብ ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
ክፍል አንድ
ሌሎች ወንጀሎች እንዲፈጸሙ የሚያነሳሱ
ወይም ሊያነሳሱ የሚችሉ ወንጀሎች

አንቀጽ ፬፻፸፯ አደገኛ የሆነ ሥራ ፈትነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፸፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ "የለማኝነትን ኑሮ" የሚለው ሐረግ በነበረበት ሁኔታ እንዲቀጥል ማድረጉ፣ አንዳንድ ችግረኞች የተሰማሩበትን የልመና ተግባር እንደወንጀል የቆጠረው ስለሚያስመስልና በዚህ አንቀጽ ላይ የተመለከተውን የልመና ዓይነት ከችግረኞች የልመና ተግባር ለይቶ ማወቁ ስለሚያዳግት ከድንጋጌው ላይ ሐረጉ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በንዑስ ቁጥር /፩/ ሁለተኛ አዲስ መስመር "የነጻነት መወሰን ባለበት የግዴታ ሥራ" የሚለው ሐረግ ግልጽ ትርጉም የሌለውና ግራ የሚያጋባ በመሆኑ ተሰርዞ "የግል ነፃነትን ከመቀነስ ጋር በሚወሰን የግዴታ ስራ" በሚል ሐረግ ስለተተካ ስለዚሁ የግዴታ ሥራ አንቀጽ ፻፫ ተጠቅሶአል።

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (፫) መጨረሻ ላይ የተመለከቱት አጣቃሽ ቁጥሮች ከ፬፻፺፰-፭፻፫ ያሉት ድንጋጌዎች ሲሆኑ፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) ግን /አንቀጽ ፬፻፺፬፣ ፬፻፺፭/ ተብሎ ተመልክቷል። በቀድሞው የቁጥሮች አጠቃቀስ መሠረት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ብዛት ስድስት ሲሆን የአዲሱ ንዑስ አንቀጽ አጠቃቀስ ግን አንቀጽ ፬፻፺፬ እና ፬፻፺፭ን፣ ማለት ሁለት ድንጋጌዎች ብቻ ተፈፃሚ መሆናቸውን ይገልፃል። አጠቃቀሱ ስህተት ቢሆንም በፍርድ ቤት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ከአንቀጽ ፬፻፺፬ እስከ ፬፻፺፱ ያሉት ድንጋጌዎች የሚገኙት ከአንቀጽ ፬፻፹፬ በሚጀምረው ክፍል ስር ሲሆን፣ አጠቃላይ መርህ ባስቀመጠው በአንቀጽ ፬፻፹፬ መሠረት በሕጉ ልዩ ክፍል ባይደነገግም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በዚህ ክፍል ስር የተዘረዘሩት የጥንቃቄ እርምጃዎችን ፍርድ ቤት መወሰን ይችላል። ስለዚህም በአንቀጽ ፬፻፺፬ እና ፬፻፺፭ የተመለከቱትን ብቻ ሳይሆን ከአንቀጽ ፬፻፺፩ እስከ ፬፻፺፫

www.abyssinialaw.com

ባሉት አራት ድንጋጌዎች መሠረትም ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ ከመወሰን የሚያግደው ነገር የለም።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፬) ድንጋጌ ጽኑ ግዞትን የሚመለከት ሲሆን የጽኑ ግዞት የጥንቃቄ እርምጃ ከወንጀል ሕጉ ላይ እንዲወጣ በመደረጉ የንዑስ ቁጥር (፬) ድንጋጌ ተሰርዟል።

አንቀጽ ፬፻፸፰ <u>የከፉ አድራጊዎች ማህበርተኛነት</u>*

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፸፰ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አቀራረቡ ተለውጧል። ወንጀሉም የሚያስቀጣው ከባድ ወንጀል ለመፈጸም በማሰብ ድርጊቱ በሚፈጸምበት ጊዜ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል። በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ አዲስ ሁለተኛ ፓራግራፍ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ የከባድ ወንጀል ምንነት ማመልከት ለሕጉ አፈጻጸም አስፈላጊ ስለሆነ "ከባድ ወንጀል" ማለት ቢያንስ በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ማስቀጣት የሚችል ወንጀል እንደሆነ የሚተረጉም ነው። ይህም ከእንግሊዘኛውና ከፈረንሳይኛው የአንቀጹ ቅጂ ላይ የተወሰደ ነው።

በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን አቀራረቡ ተለውጧል። በንዑስ ቁጥር (፪) "በዚሁ አድማ ብዙ ሰዎች የተባበሩ እንደሆነና የጦር መሣሪያ የያዙ" የሚለው ሀረግ በከፉ አድራጊዎች ማህበርተኛነት ወንጀል ብዙ ሰዎች መተባበራቸው ብቻውን ወንጀል አይደለም የሚል ትርጉም ያስከትላል። ዳሩ ግን በአንድ ማህበር ውስጥ ብዙ ሰዎች የተባበሩ እንደሆነ ወይም የጦር መሣሪያ የያዙ እንደሆን በሁለቱም ረገድ ወንጀል ስለሆነ እላይ በተጠቀሰው ሐረግ ምትክ "ወንጀለኞቹ ብዙ የሆኑ እንደሆነ ወይም የጦር መሣሪያዎችን ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም የሚያገለግሉ ሌሎች መሣሪያዎችን ታጥቀው ወይም ይዘው የተገኙ እንደሆነ" በሚል ሐረግ ተሻሽሎ እንዲገባ ተደርጓል። የከፉ አድራጊዎች ማህበርተኛነት ለሕዝብ ደህንነት አደገኛ የሆነ ወንጀል ስለሆነ "ቅጣቱ እጅግ ቢያንስ የስድስት ወር እሥራት ወይም የሺህ ብር መቀጮ ይሆናል።" በሚል ሐረግ የተደነገገው ቅጣት ስለሚያንስ ይኸው ሐረግ ተሰርዞ" ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ ይሆናል። " በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

አንቀጽ ፬፻፸፱ <u>የከፉ አድራጊዎች መጠጊያና ረዳት መሆን</u>*

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፸፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር ፩ (ሀ) ላይ የተገለጸው የወንጀል አፈጻጸም በንዑስ ቁጥር ፩ (ለ) ከተገለጸው የወንጀል አፈጻጸም አኳያ ሲታይ ከበድ ያለ በመሆኑ የየራሳቸውን የቅጣት መጠን ማመልከት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) ላይ ለተመለከተው የወንጀል ድርጊት "ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እስራትና በመቀጮ ይቀጣል" የሚል

---

* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 478 ንዑስ አንቀጽ (3) "በሕግ የተደነገገውን ከፍተኛ" የሚለው ቃል "በሕግ የተደነገገውን ከፍተኛ" ተብሎ ይነበብ።
* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 479 ንዑስ አንቀጽ (4) "ስለአባሪነት የተደነገገውን መሠረት" የሚለው ቃል "ስለአባሪነት የተደነገገውን መሠረት" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

የቅጣት ሐረግ እንዲጨመርበት የተደረገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ (፭) (ለ) ላይ ለተመለከተው የወንጀል ድርጊት "በቀላል እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል" በሚል እንዲቀመጥ ተደርጓል:: በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ የተመለከተው ቅጣት " ከሶስት ወር እስራት የማያንስ ይሆናል:: " የሚለው ሐረግ ተሠርዞ " ከአንድ አመት የማያንስ ቀላል እስራት ይሆናል" በሚል ተሻሽሏል:: የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ ወደ ቁጥር ፴ (በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፫) የሚያመሳክት ሲሆን የዚህ ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ባይኖርም በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፫ የተመለከተው ተፈፃሚ ሲሆን ስለሚችል የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፬፻፸፱ በንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ስር አዲስ ድንጋጌዎች እንዲገቡለት ተደርጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ እንደተደነገገው፣ ማንም ሰው በአባሪነት ከሚያስቀጣው ሁኔታ ውጭ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ለልዩ ልዩ ወንጀል አፈፃፀም "በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚውል እያወቀ በማናቸውም መንገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ገንዘብን ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ንብረት የሰበሰበ፣ ለድርጊቱ ፈፃሚዎች የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፣" ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::

በንዑስ አንቀጽ (፬) ደግሞ አንድ ቡድን ልዩ ልዩ ወንጀል እንዲፈፀም ወይም የቡድኑ ሕገወጥ አላማ ሥራ ላይ እንዲውል ማናቸውንም አስተዋጽኦ ያደረገ፣ ወይም በተጠቀሰው ወንጀል ላይ ለማሠማራት ሰውን የመለመለ፣ ወይም ልዩ ልዩ ድጋፍ ወይም አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፣ በንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ ፬፻፹ <u>ወንጀል እንዲፈጸም በአደባባይ መገፋፋት ወይም ወንጀልን በጅቷል ማለት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፸፬ የመንደርደሪያው ዓረፍተ-ነገር ባለቤት እንዲታወቅ "ማንም ሰው" በሚል ሐረግ እንዲጀመር ተደርጓል:: የድንጋጌው የፊደል ተራ (ሀ) ፣(ለ) እና (ሐ) ድርጊቶች የሚያስቀጡት በአደባባይ ሲፈጸሙ በመሆኑ በመንደርደሪያው ዓረፍተ ነገር መጨረሻ "በአደባባይ" የሚል ገብቷል:: በንዑስ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተመለከተቱት ድንጋጌዎች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቷል:: በድንጋጌው መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር መጀመሪያ ላይ "ማንም ሰው" የሚል ሐረግ በማስገባት የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት ግልጽ እንዲሆን በመደረጉ በፊደል ተራ (ሐ) መጨረሻ ላይ የተመለከተው "የሚሳተፍ ሰው" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ስላልሆነ ተሰርዞ "የሰበሰበ እንደሆነ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

ከዚህም ሌላ አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::

አንቀጽ ፬፻፹፩ <u>በጠር መሣሪያ መነገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፷፭ ስያሜ የድንጋጌውን ይዘት በሚገባ ስለማያመለክት "በጦር መሣሪያ መነገድ" በሚል ስያሜ ተስተካክሎአል:: በንዑስ ቁጥር (፭) በፊደል ተራ

www.abyssinialaw.com

(ሀ) ና (ለ) ለተመለከቱት የወንጀሉ አፈጻጸም ዓይነቶች "የሚደርስበትን የገንዘብ መቀጮና የተባሉትም ዕቃዎች መወረሱ ሳይቀር በእሥራት ይቀጣል" በሚል ሐረግ የተገለጸው ቅጣት በቂ ስላልሆነ በመቀጮና እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ሁኔታው ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ይቀጣል::" እንዲል ሆኖ ተረቋል::

የቀድሞው የቁጥር ፬፻፸፮ (፩) ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ሲደረግ በንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፬) ስር አዲስ ድንጋጌዎች ተቀርፀዋል::

አዲስ የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደሚደነግገው፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ወንጀል የተፈፀመው ኒውክለር ንጥረ ነገርን በመያዝ፣ በመቀበል፣ በመጠቀም ወይም ልዩ ልዩ ተመሳሳይ ድርጊቶችን በመፈፀም እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ያስቀጣል::

የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ የሚያስቀጣው፣ ድርጊቱ የተፈፀመው ስርዓትንና ደንብን በመጣስ አድራጊው "በሕገ ወጥ የመሣሪያ ንግድ በተገኙ መለዋወጫና ለዩ ልዩ አካላት ተጠቅሞ የጦር መሣሪያን በሰራ ወይም በገጣጠመ ጊዜ" ነው:: ቅጣቱም ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት ጽኑ አስራት እንዲሆን ተደርጓል::

አዲሶቹ የንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንዲገቡ ያስፈለገበት ምክንያት ከጦር መሳሪያ ንግድ ጋር ተያይዞ እነዚህ ድርጊቶች ሊፈፀሙ ስለሚችሉና እንደወንጀል ተቆጥረው ሊያስቀጡ ስለሚገባ ነው:: አሸባሪዎች በዚህ መልክ የሚያከናውኗቸውን ሕገወጥ ድርጊቶች ለመከላከል ድንጋጌዎቹ ያስችላሉ ተብሎ ይታመናል::

ወንጀሉ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ ወይም የሙያ ሥራ በማድረግ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንደሚሆን የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ገብቷል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፸፰ ንዑስ ቁጥር (፩) የቃላት ማስተካከያ እና ለውጥ ተደርጎበት ንዑሰ አንቀጽ (፭) ሆኖ ገብቷል::

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>የሕዝብ ሁከት የሚያነሳሱ ወይም</u>
<u>ሊያነሳሱ የሚችሉ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፬፻፹፩ <u>የተከለከሉ ማህበሮችና ስብሰባዎች::</u>

የቀድሞው ሕግ ፬፻፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ በሶስት የፊደላት ተራ ተከፍሎ ነበር:: ነገር ግን የፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ መሪውን ወይም አዘጋጁን የሚመለከት በመሆኑና ለዚህ ዓይነቱ ጥፋተኛ የሚወሰነው ቅጣት በተከለከለው ማህበር ወይም ስብሳባ ተካፋይ ከሆነው ሰው ይልቅ ሊከብድ ስለሚገባ እራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ ሁለት እንዲሆን ተደርጓል:: ከዚህም የተነሳ የፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ተሸጋሽገው የንዑስ አንቀጽ አንድ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ሆነዋል:: ቅጣቱም እስከ ብር አንድ ሺህ ለመድረስ የሚችል መቀጮ ሆኖ ተደንግጓል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ አንቀጽ አንድ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት ድርጊቶች እያንዳንዳቸው እራሳቸውን ችለው እንደሚያስቀጡ ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቷል:: በቀድሞው የፊደል ተራ (ሐ) የአሁኑ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መግቢያ ላይ የነበረው "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ በመሆኑ ተሰርዟል::

የተከለከለ ማህበር ወይም ስብሰባ መሪዎችን ወይም አዘጋጆችን የሚመለከተው የቀድሞው ድንጋጌ የመጨረሻው ዓረፍተ-ነገር ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደረገ ሲሆን ቅጣቱ እስከ ስድስት ወር ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር አምስት መቶ ለመድረስ የሚችል መቀጮ መሆኑ ቀርቶ እስከ አንድ ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል:: "መሪዎች" ወይም "አደራጆች" የሚሉት ቃላትም በተለመደው የወንጀል ሕግ አጻጻፍ መሠረት በብዙ ቁጥር መሆናቸው ቀርቶ በነጠላ ቁጥር እንዲጻፉ ተደርጓል::

አንቀጽ ፬፻፹፫ <u>ሕቡዕ የሆኑ ማህበሮች ወይም መሣሪያ የታጠቁ ቡድኖች::</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ መጠነኛ የቃላት ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን በአንቀጹ ላይ "በወንጀሉ ተካፋይ ሆነው የተገኙ እንደሆነ" የሚለው ሐረግ የትኛውን ወንጀል እንደሚያመለክት ግልጽ ባለመሆኑ "...አንቀጽ ፬፻፹ የተመለከተውን ወንጀል ሲፈጽም ተካፋይ የሆነው ሰው...." በሚል ተተክቷል:: በማህበሮች ወይም ቡድኖች፣ መሪዎች፣ አደራጆች ወይም ዋነኛ አባላት ላይ ቅጣት የሚጥለው ድንጋጌ ራሱን በቻለ ንዑስ አንቀጽ ቢደረግ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል:: የሚወሰነውም ቅጣት ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና ከብር አንድ ሺህ የማያንስ መቀጮ እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፬፻፹፬ <u>የተከለከሉ ስብሰባዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፬ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩት ንዑስ ቁጥር አንድ ሁለት ፓራግራፍ፣ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ሁለት ተከታታይ ዓረፍተ-ነገሮች የነበሩት ሲሆን እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው ቅጣት የሚደነግጉ ናቸው:: የወንጀሉ መሪዎች ወይም አዘጋጂዎች ከወንጀሉ ተካፋዮች ይልቅ ከባድ ቅጣት ሊወሰንባቸው ስለሚገባና የጦር መሣሪያ ከያዙ ተራ ተካፋዮች ይልቅም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኝ የወንጀሉ መሪ ወይም አዘጋጅ በይበልጥ መቀጣት ስላለበት ለአራቱም ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተለያየ ቅጣት መቀመጡ የሚደገፍ ነው:: በዚህ መሠረት የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለት ፓራግራፎች ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪)፣ የንዑስ ቁጥር ሁለት ሁለቱ ዓረፍተ-ነገሮች ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንዲሆኑ ተደርጓል:: በብዙ ቁጥር የተጻፉ ቃላትም በነጠላ ቁጥር የተጻፉ ሲሆን የሌሎች ቃላት ማስተካከያ እና የሐሳብ መቃናት በድንጋጌው ላይ ተደርጓል::

የተከለከሉ ስብሰባዎች ወይም ሕገወጥ ሰልፎች የሚደራጁት ወይም የሚመሩት የሕግ ሰውነት በተሰጣቸው ድርጅቶች ሊሆን ይችላል:: ይህን በመሳሰለም ጉዳይ ድርጅቶቹ

www.abyssinialaw.com

ሳይቀጡ ሊታለፉ ስለማይገባ እንደሚቀጡ የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲገባ ተደርጓል።

<u>በወሬ ሕዝብን ማሸበር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፭ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፸፱ በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆናቸውን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) ለተመለከተው እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት ከወንጀሉ ክብደት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ አነስተኛ ቅጣት ስለሆነ "የሚፈረደው ቅጣት እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ነጻነትን የሚያሳጣ እሥራት ነው። "የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ሌላ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፬፻፹፮ <u>ሐሰት ወሬዎችና ሕዝብን ማነሳሳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፹ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እያንዳንዳቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማመልከት በተራ ፊደል (ሀ) ከተመለከተው ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚለው ቃል ገብቷል። ለድንጋጌው የተወሰነው ቅጣት ወንጀሉ ከበድ በሚልበት ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል። "በሚል ሐረግ ተተክቶአል። ድንጋጌው ሌላ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፬፻፹፯ <u>የማነሳሳት ጠባይ ያላቸው የሐሳብ መግለጫዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፯ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፹፩ ድንጋጌ ላይ ቅጣትን በሚመለከት "እስከ አምስት መቶ ብር ለመድረስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ ወይም "እስከ ስድስት ወር ለመድረስ በሚችል እሥራት ይቀጣል።" የሚለው ሐረግ የእስራቱን ቅጣት በማስቀደምና የመቀጮውን ቅጣት በማስከተል የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበት "እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እሥራት ወይም እስከ አምስት መቶ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል" በሚል ሐረግ ተስተካክሎአል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፹፰ ረብሻ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፰ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፩፻፹፯ (፪) የተመለከተው የእሥራት ቅጣት ብቻ በቂ ስለማይሆን ወንጀሉን የፈጸመው ሰው በሁለቱም ሁኔታዎች በመቀጮም ጭምር እንዲቀጣ ተደርጐ ተዘጋጅቷል። ድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፹፱ ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው ጉዳዮች፤ መታዘዝ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ውስጥ የተጠቀሰው ቁጥር በዚህ የወንጀል ሕግ መጠቀስ በሚገባው ቦታ ተቀምጦ ተስተካክሏል። ግልጽ እንዲሆን ለማድረግም የቃላት ማሻሻያ ተደርጐበት አቀራረቡ ተቃንቷል።

## ምዕራፍ ሁለት
## በሕዝብ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፩፻፺ ስብሰባን ወይም ጉባኤን ማወክ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፺ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ አንድ (፩) ድንጋጌ ላይ ባለቤቱ ግልጽ እንዲሆን "ማንም ሰው" በሚል ሐረግ እንዲጀመር ተደርጓል። በንዑስ አንቀጽ (፪) ለተደነገገው ወንጀል መቀጮ አነስተኛ በመሆኑና መነሻውን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና ከአምስት መቶ ብር የማያንስ መቀጮ እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል። በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ "ነጻነትን የመከልከሉ ቅጣት በጽኑ እስራት ለመሆኑና ከዚህ በላይ የተባለውም ጥፋት የተፈጸመው በሕዝብ ጉባኤ ላይ ሲሆን ይህን ጽኑ እስራት ለአምስት አመት ለማስረዘም ይቻላል።" የሚለው ሐረግ ግልጽ ሆኖ ያልተጻፈ ከመሆኑም በላይ በንዑስ ቁጥሩ በተመለከተው ፍርዱ ወንጀሉን ለፈጸመ ሰው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት ስለሚያንስ ተሠርዞ "ቅጣቱ እስከ ሰባት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት" በሚል ሐረግ ተተክቷል። ድንጋጌው ሌላ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፺፩ በራስ ጥፋት ከሃላፊነት ውጪ በመሆን የሚፈጸም የሁከት ተግባር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፺፩ ሆኖ ገብቷል።

ሲያሜው ከድንጋጌው ይዘት ጋር የተስማማ እንዲሆን "በራስ ጥፋት ከሃላፊነት ውጪ በመሆን የሚፈጸም የሁከት ተግባር" በሚል ተስተካክሏል። ይዘቱም ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፺፪ <u>የሃይማኖትን ሰላምና ስሜት መንካት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፪ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተከፈለ ሲሆን "ማንኛውም ሰው" የሚለው ሀረግ በፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ የተቀመጠው ያለቦታው በመሆኑ ከፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) በፊት በድንጋጌው መንደርደሪያ ላይ እንዲገባ ተደርጓል። በመንደርደሪያው ላይ የሚገኘው "ግልጽ በሆነ አድራጎት" የሚለው ሀረግም ተሰርዞ በምትኩ "በአደባባይ" የሚለው ቃል "ማንም ሰው" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ እንዲጻፍ ተደርጓል።

አንቀጽ ፬፻፺፫ <u>የሙታንን ሰላምና ክብር መንካት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፫ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ አስፈላጊ የቃላት ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን አዲስ ድንጋጌ የፊደል ተራ (መ) ሆኖ ተረቅቋል፤ ይኸውም ሬሳ መውሰድን፣ ማጥፋትን ወይም የሬሳ የአካል ክፍሎች መበታተንን የሚመለከት ነው።

የቅጣቱ ድንጋጌ አገላለጽ ለሁሉም ንዑሳን ክፍሎች ማጠቃለያ ሐረግ ሆኖ በአዲስ መስመር ላይ እንዲጻፍ ተደርጓል። እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል ለየብቻው የሚያስቀጣ መሆኑን ለማሳየት በፊደል ተራ (ሐ) መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል።

<u>ርዕስ ሰባት</u>
<u>በሕዝብ፣ በመገናኛዎችና በማጓጓዣዎች ደህንነት</u>
<u>ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>
<u>ምዕራፍ አንድ</u>
<u>በሕዝብ ፀጥታና ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

የርዕስ ሰባት ስያሜ ግልጽ እንዲሆንና በስሩም ያሉትን ድንጋጌዎች በሚሸፍን አኳኋን ተነባቢ እንዲሆን ቀደም ሲል በነበረው "በጋራ ጸጥታ /ሴኩሪቲ/ ኮሌክቲቭና" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ" በሕዝብ፣ በመገናኛዎችና በመጓጓዣዎች ደህንነት" በሚል ሐረግ ተተክቶ ከተከታዩ ጋር እንዲናበብ ተደርጎ ተሻሽሏል። በዚህም መሰረት የርዕስ ሰባት ስያሜ "በሕዝብ፣ በመገናኛዎችና በመጓጓዣዎች ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች። "የሚል እንዲሆን የምዕራፉ ስያሜ ደግሞ "በሕዝብ ፀጥታና ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች" የሚል አገላለጽ እንዲኖረው ተደርጎ ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፬፻፺፬ <u>የእሳት ቃጠሎ ማድረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፬ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፹፰ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የቃላት ማስተካከያና የአቀራረብ ለውጥ ተደርጎበታል። ወንጀሉ በንዑስ ቁጥር (፪) በተመለከተው አኳኋን የተፈጸመ ከሆነ ቅጣቱ በንዑስ ቁጥር (፩) ከተመለከተው

www.abyssinialaw.com

ይበልጥ በወንጀሉ ልክ እንዲከብድ ስለሚያስፈልግ በንዑስ ቁጥር (፪) መጨረሻ ላይ "ከዚህ በላይ በተወሰነው መጠን በተለይ ከፍ ባለ አኳኋን ይፈጸማል የሚለው ሐረግ ተሠርዞ "እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡ በዚህ በንዑስ ቁጥር (፫)ም እንደዚሁ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል፡፡

አንቀጽ ፬፻፺፮ <u>የተፈጥሮ አደጋዎችን ማድረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ ከይዘቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ "ፍጥረታውያን መቅሰፍቶችን ስለመቀስቀስ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "የተፈጥሮ አደጋዎችን ማድረስ" በሚል ስያሜ እንዲተካ ተደርጓል፡፡ በድንጋጌው መግቢያ ላይ "ይህንኑ ፈቅዶና ሆነ ብሎ" የሚለው ሐረግ ማንን ለማለት ግልጽ ስላልሆነ ተሰርዞ ግልጽ እንዲሆን "ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ ለማድረስ አስቦ" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡ በውስጡ የተጠቀሰው የቁጥር ፬፻፹፰ ድንጋጌም ምትክ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፭ ተስተካክሎ ተጠቅሷል፤ ድንጋጌውም መቃናት ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፬፻፺፯ <u>ግዙፍ ሥራዎችን ወይም የመጠበቂያ ስራዎችን መጉዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፺ "ይህንኑ አቅዶና አስቦ" የሚለው ሐረግ ማንን ለማለት እንደሆን ግልጽ ስላልሆነ ተሠርዞ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ "ማንም ሰው በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ ለማድረስ አስቦ" የሚለው ሐረግ በትምቢታዊ አንቀጽ ስለተጻፈ የሚቀጣው ደግሞ ወንጀል የፈፀመ እንጂ ገና ወደፊት የሚፈጽም ሰው ባለመሆኑ ሐረጉ ተሰርዞ "ያበላሸ ወይም ያፈረሰ እንደሆነ" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡ እንደ ቧንቧዎችን ቦዮችን የመሳሰሉትን ማፍረስ ወይም ማበላሸት በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ በሰዎች ላይ ጉዳት ቢደርስም ባይደርስም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ስለሆነ "ከዚህም የተነሣ በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋን የሚያደርስ ሰው፡፡" የሚለው ሐረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል፡፡

አንቀጽ ፬፻፺፰ <u>ማፈንዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፺፩ የተመለከተው ድንጋጌ ባለቤት ግልጽ እንዲሆን "እንዲሁም" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ማንም ሰው" በሚል ሐረግ ተተክቷል፡፡ ድንጋጌው ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን ከመሻሻሉም በቀር ግልጽ እንዲሆን በስያሜውና በድንጋጌው ይዘት የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ ፩፻፺፰ በቸልተኛነት የሚፈጸሙ ወንጀሎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፺፰ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው የመጀመሪያው አዲስ መስመር "አጥፊነትን በሚያስከትል ቸልተኛነት የእሳት ቃጠሎን፣ የተፈጥሮ መቅሰፍትን ያነሣሣ ወይም በተቋቋሙ የሥራ ሕንፃዎችና ቤቶች ላይ አደጋ ያደረሰ" በሚል ከተዘረዘረ በኋላ "ወይም" በሚል አማራጭ ስለ እሳት ቃጠሎ፣ የተፈጥሮ መቅሰፍቶችን ስለመቀስቀስ፣ የሥራ ቦታዎችንና የመጠባበቂያ ሥራዎችን ስለመጉዳት እና ስለማፈንዳት የተደነገጉት "ከቁጥር ፩፻፹፰ (አንቀጽ ፩፻፺፩) እስከ ፩፻፺፯ በተመለከተ ዓይነት" በሚል ሐረግ እንደገና መጠቀሱ እነዚያን ሁኔታዎች መድገም ስለሆነ ግልጽ እንዲሆን በአዲስ አቀራረብ ተስተካክሏል:: አጥፊው በሰዎች ወይም በንብረቶች ላይ ከባድ የሆነ አደጋ በማድረሱ ብቻ በቀላል እስራት መቅጣቱ ተገቢ ስለሆነ አደጋው እንደደረሰ ለማወቅ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ሐረግ ማስገባቱ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል::

## አንቀጽ ፩፻፺፱ በሚፈነዱ፣ በሚቀጣጠሉ ወይም በሚመርዙ ነገሮች አደጋ ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፺፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፩፻፺፫ ስያሜ ላይ ስለሚቀጣጠሉ ነገሮች ያልተገለፀ በመሆኑ ይዘቱን አይሸፍንም:: ስለዚህ በስያሜው ውስጥ "በሚፈነዱ" ከሚለው ንዑስ ሐረግ ቀጥሎ "በሚቀጣጠሉ" የሚል ንዑስ ሐረግ ገብቶ ከተከታዩ ጋር አብሮ እንዲነበብ በማድረግ ተሻሽሎአል:: በንዑስ ቁጥር (፩) በሁለተኛው አዲስ መስመር ወንጀለኛው በአደጋ ላይ የጣለው ንብረት ብቻ ሲሆንና ያደረሰውም ጉዳት ቀላል ሲሆን "ፍርድ ቤቱ ከአንድ ወር የማያንስ እስራት ሊፈርድበት ይችላል" የሚል ሲሆን የተጠቀሰው መነሻ ቅጣት ከወንጀሉ ክብደት አንጻር ስለሚያንስ "ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራት ይሆናል" በሚል ሀረግ ተተክቷል::

አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ በአንቀጹ ስያሜ ላይ የተገለፀው ድርጊት "በሰው ሕይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም በኢኮኖሚ ላይ ከባድ ጉዳት በሚያደርስ ወይም ሊያደርስ በሚችል ድርጊት በአደባባይ፣ በሕዝብ መገልገያ ቦታ፣ በመንግስት ተቋም፣ በአገልግሎት መስጫ ተቋም ወይም ሥርዓት ላይ ጉዳት ለማድረስ ታስቦ በተጠቀሱት ተቋማት፣ አገልግሎቶች ወይም ሥርዓቶች ላይ የባዮሎጂካል ኤጀንቶችን፣ መርዝነት ያላቸው ነገሮችን በማፍሰስ፣ በመልቀቅ፣ በማሰራጨት ወይም በሰው ሕይወት ወይም አካል ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ ሃይል ያላቸው ወይም ለዚሁ ተግባር የተሰሩ ተቀጣጣይና ፈንጂዎችን በማስቀመጥ፣ በመወርወር፣ በማፈንዳት የተፈፀመ በሆነ ጊዜ" ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እንዲሆን ተደርጐ ተቀርጿል:: በዚህ ሁኔታ የሚፈፀመውን የአሸባሪነት ተግባር ለመግታት ወይም ለመከላከል ድንጋጌው እንደሚያስችል ይታመናል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያው ፓራግራፍ ራሱን የቻለ ወንጀልና ቅጣት የሚደነግግ በመሆኑ የቃላትና የአሳብ ማሻሻያ ተደርጐበት ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኗል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተገለፀው ወንጀል በአብዛኛው ጊዜ በቸልተኛነት ሊፈፀም

www.abyssinialaw.com

ስለሚቻልና ይህም ወንጀል ሆኖ ማስቀጣት እንዳለበት በመታመኑ ወንጀሉ በቸልተኛነት ሲፈፀም እንደሚያስቀጣ የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተረቋል።

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፫)ን እና (፬)ን እንዲያመለክት የተደረገ ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖ ተረቅቋል።

አንቀጽ ፭፻ <u>ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም የሚመርዙ ነገሮችን መሥራት፣ መያዝ፣ መደበቅ፣ ወይም ማጓጓዝ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻ ሆኖ ገብቷል።

የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም የሚመረዙ ነገሮችን የሚሠራ ሰው እነዚህ ነገሮች አጥፊ መሆናቸውን ሊያውቅ አይችልም ብሎ ለመገመት አዳጋች ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፲፬ የንዑስ ቁጥር (፩) መጀመሪያ የሆነው "ለአጥፊነት መሠራታቸውን" የሚለው ሐረግ ተሰርዞአል። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ነገሮች የሚሠራው ሰው የሚቀጣው ሕገወጥ ለሆነ ዓላማ እንደሚውሉ እያወቀ የሠራ እንደሆነ ብቻ ስለሆነ "ማንም ሰው ሕገወጥ ለሆነ ዓላማ ለማዋል መታቀዳቸውን" የሚለው ሐረግ "እያወቀ" ከሚለው ቃል በፊት ገብቶአል።

በዚሁ የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ላይ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበታል። በሕግ የተከለከሉ እቃዎችን ሠርቶ ለማውጣት የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ብቻ ሣይሆን መመሪያዎችንም መስጠት ዕቃዎቹን ለመሥራት ስለሚረዳና ይኸውም የኅብረተሰቡ ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ በዚህም ረገድ ጥፋተኛው እንዲቀጣ እነዚህን ነገሮች ሠርቶ ለማውጣት የሚያገለግሉትን መሣሪያዎች ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ወይም መመሪያዎችን የሰጠ እንደሆነ" የሚል ሐረግ ገብቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) ለተገለጸው የወንጀል ድርጊት የተመደበው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ወይም ከሶስት ወር የማያንስ የቀላል እስራት ቅጣት ከወንጀሉ ክብደት ጋር ሲነጻጸር የሚያንስ ሆኖ በመገመቱ "እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት፤ ወይም ከሶስት ወር በማያንስ እስራት ይቀጣል።" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል። " በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፫) "የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ነገሮችን ወይም የሚመርዙ ጋዞችን የሚሠሩባቸውን ቅመሞችንም ማስመጣት፣ መግዛት፣ ፈልጎ ማግኘት ወይም እጁ እንዲገባ ማድረግ ወዘተ ለሕዝቡ ደህንነት አደገኛ ድርጊት ስለሆነ ሐረጉ" የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም የሚመርዙ ነገሮችን" በሚል ተስተካክሎ ከዚህ ቀጥሎ "እነዚህኑ ለመሥራት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን" የሚል ሐረግ ገብቶአል። በወንጀል የሚቀጣው ወንጀል የሠራ እንጂ የሚሠራ ስላልሆነ የሚያስመጣ፣ የሚገዛ ወዘተ በሚል በትንቢታዊ ግሶች የተጻፈው ሁሉ በኃላፊ ግሶች ተጽፎአል። ቅጣትን በተመለከተ "ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት" የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊት እንደሚሆን ተገልጿል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፭ <u>የሕንፃ ሥራ ደንቦችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፭ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፬፻፺፭(፩) የተመለከተው ድንጋጌ ባለቤቱ ግልጽ እንዲሆን "ማንም ሰው" በሚል ሀረግ እንዲጀምር ተደርጎአል። በዚሁ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ የሞያ ሥራ የልምድና የጥንቃቄ ደንቦችን የሚለው ሐረግ "ሙያ ወይም ልምድ የሚሰራባቸውን የጥንቃቄ ደንቦችን" በሚል አማራጭ አጻጻፍ ተሻሽሏል። ድርጊቱም የሚያስቀጣው ታስቦ ሲፈጸም ስለሆነ "አስቦ" የሚል ቃል ገብቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) "ፍርድ ቤቱ በተለይ ከዚህ በላይ ከተወሰነው ዝቅተኛ የሆነ እሥራት ወይም መቀጮ ነው" የሚለው ሐረግ ግልጽ ስላልሆነ ተሰርዞ "ቅጣቱ ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም መቀጮ ይሆናል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

ወንጀሉ ታስቦ ሲፈፀም በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጣራ ቅጣቱ ያልተለወጠ ሲሆን፣ ድርጊቱ በቸልተኛነት በሚፈፀምበት ጊዜ ጣራ ቅጣቱ ዝቅ ሊል ስለሚገባው ሦስት ዓመት መሆኑ ቀርቶ ወደ አንድ ዓመት እንዲወርድ ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፮ <u>የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን ወይም ዕቃዎችን ማንሳት ወይም አለማደራጀት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፮ ሆኖ ገብቷል። በድንጋጌው ስያሜ ላይ "መጠባበቂያ የሚሆኑትን መሣሪያዎች" የሚለው ሀረግ አደጋ እንዳይደርስ መከላከያ የሚሆኑ መሣሪያዎችን እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም። በዚህ መሰረት የድንጋጌው ስያሜ "መጠባበቂያ የሚሆኑትን መሣሪያዎች ወይም የሚያገለግሉትን ዕቃዎች ማጥፋት ወይም አለማደራጀት" ከሚለው ይልቅ "የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን ወይም ዕቃዎችን ማንሳት ወይም አለማደራጀት" የሚለው ቢሆን እንደሚሻል ተደርጎ ተወስዷል። የድንጋጌውን ይዘት በሚመለከት በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት መንደርደሪያ የሆነው "አስቦ" የሚለው ቃል ብቻውን ባለቤቱን በሚገልጽ አኳኋን የተብራራ ስላልሆነ "ማንም ሰው አስቦ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በፊደል ተራ (ሀ) የሚነበቡት "የሚያጠፉ"፣ "የሚያስቀር"፣ "የሚያበላሽ" በሚል የተመለከቱት ትንቢታዊ ግሶች በፊደል ተራ (ለ) እንደተመለከቱት ግሶች ተተክቶአል። በፊደል (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውስጥ እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመላከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተ ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በድንጋጌው መጀመሪያ ላይ "ማንም ሰው አስቦ" የሚል ሀረግ የገባ በመሆኑ በፊደል ተራ (ለ) መጨረሻ ላይ የተጻፈው "ማንኛውም ሰው" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል። በንዑስ ቁጥር (፪) "አጥፊው በቸልተኛነት ያደረገው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከነዚህ ቅጣቶች አንዱን ይፈርዳል" በሚለው ዓረፍተ ነገር "ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱን ይፈርዳል" የሚለው ሐረግ በንዑስ ቁጥር (፩) መጨረሻ የተመለከተውን የእስራት ቅጣት ወይም መቀጮ ለማለት ነው። በዚህ ሕግ መሠረት በተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ ቢቀመጥ ቅጣቱን በጣም ከፍ እንደሚያደርግ ግንዛቤ በመወሰዱ "ፍርድ ቤቱ ከነዚህ ቅጣቶች አንዱን ይፈርዳል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከአንድ ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። የእስራቱ ቅጣት ጣራ ዝቅ የተደረገው፣ በቸልተኛነት የተፈፀመ ድርጊት ታስቦ ከተፈፀመ ወንጀል እኩል ሊያስቀጣ ስለማይገባ ነው።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፫ <u>በሕዝብ ላይ የሚደርስ ከባድ አደጋን አለማስታወቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፫ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "በሕዝብ ላይ ከባድ አደጋ ሲደርስ ባለማስታወቅ የሚደረግ ጥፋት" የሚለው ሐረግ ተሻሽሎ "በሕዝብ ላይ የሚደርስ ከባድ አደጋን አለማስታወቅ" በሚል ሐረግ ተተክቶአል፡፡ የድንጋጌው ይዘት ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ተቃንቷል፡፡

አንቀጽ ፭፻፬ <u>የተጠበቁ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "የማይነኩ ሁኔታዎች" የሚለው ሐረግ በተሻለ ሁኔታ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ "የተጠበቁ ሁኔታዎች" በሚል ሐረግ ተተክቶአል፡፡ ድንጋጌ ውስጥ ያልተሸፈኑ ሆነው የሌሎች ድንጋጌዎች አንቀጾች በተገቢ ቦታቸው እንዲጠቀሱ ተደርጓአል፡፡ በድንጋጌው ውስጥ "ለአገር መከላከያና ለወታደራዊ አገልግሎት የቆሙ የሥራ ቦታዎችንና ሥራዎችን በጉዳት ላይ በማዋል ወይም በማበላሸት በተለይም በማፍረስ ወይም በማሰናከል በጉዳት ላይ የማዋል ነገሮች የፈጸሙ ሰዎች" የሚለው ረዥምና የተንዛዛ ሐረግ እንዲሠረዝ ተደርጎ "የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች" በሚል ሐረግ ብቻ እንዲጠቃለልና እንዲሻሻል ተደርጓአል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በማጓጓዣዎችና በመገናኛዎች ነፃነትና ፀጥታ</u>
<u>ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፭፻፭ <u>ለሕዝብ ጥቅም በተቋቋሙ ግዙፍ ሥራዎችና አገልግሎቶች ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውስጥ እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) እና (ለ) ለተደነገጉት የወንጀል ድርጊቶች ተወስኖ የነበረው ቅጣት ለከባድ ሁኔታዎች አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ ከንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) በኋላ በነበረው አዲስ መስመር "የከለከለ ያወከ ወይም ያበላሸ እንደሆነ በእሥራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል" የሚለው የቅጣት ዓረፍተ-ነገር ተሰርዞ "መደበኛ አሠራር የከለከለ፣ ያወከ፣ ወይም ያሰናከለ፣ በቀላል እሥራትና በመቀጮ፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" በሚል ዓረፍተ-ነገሩ ተሻሽሎ እንዲቀረጽ ተደርጓአል፡፡ በንዑስ ቁጥር (፪) እንደወንጀሉ ከብደትና አነስተኛነት ፍርድ ቤቱ ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ደግሞ እስከ ሰባት አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ለመወሰን እንዲችል "ቅጣቱ" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "እጅግ ቢያንስ አንድ ወር እሥራትና የገንዘብ መቀጮ ነው፡፡"

www.abyssinialaw.com

የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራትና መቀጮ፤ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ደግሞ እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት ይሆናል።" በሚል ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ በቸልተኝነት ለተፈጸመው ድርጊት የተቀመጠው ቅጣት "መቀጮው እስከ አምስት መቶ ብር ይሆናል ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ከሶስት ወር በማያልፍ እሥራት ይቀጣል።" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቅጣቱ እስከ አንድ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ፤ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ቀላል እሥራት ይሆናል" በሚለው ሐረግ ተተክቶአል።

## አንቀጽ ፭፻፯ መገናኛዎችንና ማጓጓዣዎችን በከባድ አደጋ ላይ መጣልና ማበላሸት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፯ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ)፣ (ለ)፣(ሐ)፣ እና (መ) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እያንዳንቸው የሚያስቀጡ መሆኑን ለማሳየት በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሐ) መጨረሻ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በንዑስ ቁጥር (፩) ሥር ለተመለከቱት ንዑሳን ድንጋጌዎች ስለሚመለከተው ቅጣት በመጠኑ መከበድ እንደሚገባው የታመነበት በመሆኑ "እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል። "የሚለው ሐረግ ተሰርዞ እስከ "አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል" በሚለው ሐረግ ተተክቶአል። በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ቅጣቱ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችለው" የሚለው በንዑስ ቁጥሩ መጀመሪያ ላይ የነበረው ሐረግ እንዳለ እንዲገባ ሆኖ ቅጣቱም "እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችለው" የሚል ሐረግ እንዲገባበት ተደርጎአል። ንዑስ ቁጥር (፫) ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ፓራግራፍ ራሱን ችሎ ቅጣት የሚደነግግ በመሆኑ የጀመሪያው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ ሁለተኛው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ገብቷል። ቅጣቱን በተመለከተ የንዑስ አንቀጽ (፫) ቅጣት በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የንዑስ አንቀጽ (፬) ቅጣት ግን በእስራት የሚለው ተሰርዞ ከአንድ ወር የማያንስ ቀላል እስራት እንዲል ተደርጓል።

አዲስ ድንጋጌዎች በሚከተለው መልክ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ሆነው ገብተዋል።

በአንቀጽ ፭፻፯ ስያሜ ላይ ከተገለፁት ድርጊቶች አንዱ፣ "ለበረራ ወይም ለባህር ላይ ጉዞ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችን ወይም መሣሪያዎችን በማውደም፣ በማበላሸት ወይም አሰራራቸውን ለማሰናከል ጣልቃ በመግባት የተፈፀመ ሆኖ በበረራ ላይ የሚገኝ አይሮፕላንን ወይም በጉዞ ላይ የሚገኝ መርከብን ለአደጋ የሚያጋልጥ የሆነ እንደሆነ፣ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጓል።

የንዑስ አንቀጽ (፮) ድንጋጌ ደግሞ፣ "በንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።" በማለት ይደነግጋል።

የንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ድንጋጌዎች በአሸባሪዎች የሚፈፀሙትን ድርጊቶች ለመከላከል ያስችላሉ ተብለው የገቡ ናቸው።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፯ <u>በኮንትኔንታል ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ አይሮፕላንን ወይም መርከብን ያለአግባብ መያዝ</u>

ይህ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ድንጋጌ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ያልነበረ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በኮንትኔንታል ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ወይም በማረፊያ የሚገኝ አይሮፕላንን፣ ወይም በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ወይም በወደብ ውስጥ የቆመ መርከብን መያዝ ወይም በቁጥጥር ስር ማድረግ ወንጀል እንደሆነ የሚደነግግ አዲስ አንቀጽ ነው። ድርጊቱም በሰው ሕይወት፣ አካል ወይም ንብረት ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጓል።

በበረራ እና በአገልግሎት ላይ ያለ አይሮፕላን ምን ማለት እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ተተርጉሟል።

አንቀጽ ፭፻፰ <u>በኮንትኔንታል ሸልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ አይሮፕላንን ወይም መርከብን አስጊ ሁኔታ ላይ መጣል</u>

ይህ በቀድሞው ህግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ሲሆን ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ይገኙበታል።

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በኮንትኔንታል ሸልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ስፍራ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ባለ ወይም በማረፊያ በቆመ አይሮፕላን፣ ወይም በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ባለ ወይም በወደብ በቆመ መርከብ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ አስቦ በህገ-ወጥ መንገድ የኃይል ድርጊት የፈጸመ እንደሆና ድርጊቱም የስፍራውን፣ የአይሮፕላኑን ወይም የመርከቡን ድህንነት አደጋ ላይ ለመጣል የሚችል እንደሆነ ቅጣቱ ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጎአል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በቸልተኛነት በሰው ላይ የኃይል ድርጊት ሲፈጸምና የስፍራውን፣ የአይሮፕላኑን ወይም የመርከቡን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል የሚችል ሲሆን ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፱ <u>በኮንትኔንታል ሸልፍ በሚገኝ ቋሚና በተተከለ ስፍራ፣ አይሮፕላን ወይም መርከብ ላይ አደጋ ማድረስ</u>

ይህ በቀድሞው ህግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ሲሆን ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ይገኙበታል።

ይህ ድንጋጌ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ያልነበረ ሲሆን በኮንትኔንታል ሸልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለ ስፍራን፣ በአገልግሎት ወይም በበረራ ላይ ወይም በማረፊያ የሚገኝ አይሮፕላንን፣ ወይም በአገልግሎት ወይም በጉዞ ላይ ወይም በወደብ ውስጥ የቆመ መርከብን አስቦ በሕገ ወጥ መንገድ ያወደመ እንደሆነ፣ ከነዚህ ነገሮች በአንዱ ላይ በአደረሰው ጉዳት ለአገልግሎት ለበረራ ወይም ለጉዞ ብቁ እንዳይሆን ያደረገ እንደሆነ ወይም ያገልግሎት፣ ወይም የበረራ ወይም የጉዞ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ

 www.abyssinialaw.com

ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንደሚሆን ተደንግጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ድርጊቱ በቸልተኛነት ሲፈጸም ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፲ <u>ምልክቶችንና የእርዳታ ጥሪዎችን ያለአግባብ ማድረግ</u>*

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፻፩ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አቀራረቡ ከተቃና በኋላ በዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፭፻፲(፩) ሆኖ ገብቶአል።

ቅጣቱን በተመለከተ በቀድሞው ሕግ ድንጋጌ ላይ "በገንዘብ ወይም እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እስራት ይቀጣል" የሚለው ለወንጀሉ አነስተኛ ስለሆነ እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት መቅጣት እና መቀጮውን ማጣመር እንዲቻል፣ "በቀላል እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል።" ተብሎ ተደንግጓል። ከዚህም ሌላ ሁለት አዲስ ንዑሳን አንቀጾች በድንጋጌው ላይ እንዲገቡ ተደርጓል። አዲሱ የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ "ወንጀሉ በበረራ ላይ ያለ አውሮፕላንን ወይም በጉዞ ላይ ያለ መርከብን ለአደጋ ለማጋለጥ ሀሰተኛ ማስረጃን በማስተላለፍ የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።" የሚል ሲሆን ድርጊቱ በቸልተኛነት በሚፈፀምበት ጊዜ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጐ በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ተመልክቷል።

አንቀጽ ፭፻፲፩ <u>አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ወይም መሣሪያዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መጫን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፩ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፻፪ ድንጋጌ ላይ ያለው ስያሜ ከድንጋጌው ጋር እንዲቀራረብ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ "ለሕዝብ ማመላለሻ ለሆኑት አደገኛ የሆኑትን ነገሮች ከደንብ ውጭ ስለመስጠት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ወይም መሣሪያዎችን በሕገወጥ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መጫን" በሚል ስያሜ ተተክቶአል።

የቀድሞው ድንጋጌ ንዑሳን ቁጥሮች ያልነበሩት ሲሆን ይህ አንቀጽ ግን (፫) ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎ ተቀርጿል። ንዑስ አንቀጽ (፩) አዲስ ሲሆን፣ ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ አደጋ ለማድረስ በማሰብ፣ በአየር ወይም በውሀ የሕዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የሚቀጣጠሉ፣ በመብነን ወይም በመበተንና በመቅነን የሚበላሹ ወይም የሚጎዱ ነገሮችን ወይም መሣሪያዎችን ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጥ ያደረገ፣ የጫነ ወይም ያስጫነ፣ ወይም ይዞ የተሣፈረ እንደሆነ ከአምስት አመት እስከ አሥር ዓመት ጽኑ እሥራት እንደሚቀጣ ተደነግጓል።

---

* በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 510 ንዑስ አንቀጽ (2) "ሀሰተኛ ማስረጃን በማስተላለፍ" የሚለው ቃል "ሀሰተኛ መረጃን በማስተላለፍ" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ አዲስ ሲሆን በኮንቲኔንታል ሸልፍ ቋሚ በሆነና በተተከለ ስፍራ፣ በአውሮፕላን ወይም በመርከብ ወይም በጭነቱ ላይ ከባድም ይሁን ቀላል ጉዳት ማድረስ "የሚችል ማናቸውንም መሣሪያ ወይም እቃ በማናቸውም እቃ በማናቸውም ዘዴ በአውሮፕላኑ ወይም በመርከቡ ወይም በኮንቲኔንታል ሸልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ ላይ ያስቀመጠ ወይም እንዲቀመጥ ያደረገ" ማንም ሰው ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

ንዑስ አንቀጽ (፫) የቀድሞው ድንጋጌ ሲሆን፣ ማንኛውም አደጋ ለመጣል ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ሳይሆን ሰለትራፊክ ደህንነት አጠባበቅ የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመጣስ ተነሳስቶ የሆነ ድርጊት ፈጽሞ ቢገኝ እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጓል። ይህም የቀድሞውን የመቀጮና የቀላል እስራት ቅጣት በመሰረዝ ነው።

ንዑስ አንቀጽ (፬) አዲስ ሲሆን ማንኛውም በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ የሕዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የሥራ ግዴታውን በአግባቡ ሣይወጣ ቀርቶ በነዚሁ ማጓጓዣዎች ወይም በተቋሞቻቸው ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ወይም መሣሪያዎች ተቀምጠው ወይም ተጭነው የተገኙ እንደሆነ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ይገልጻል።

የአዲሱ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ደግሞ፣ "በንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ድርጊት በቸልተኝነት ተፈጽሞ ከሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል።" በማለት ይደነግጋል።

አንቀጽ ፭፻፲፱ <u>ከባድ ሁኔታ</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን ሁለት ንዑሳን አንቀጾች አሉት።

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ "ከአንቀጽ ፭፻፰ -፭፻፲፩ ከተመለከቱት ወንጀሎች አንዱ ታስቦ ሲፈጸም በሰው ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ" ቅጣቱ ከአስር እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆንና ነገሩ ከባድ ሲሆን ዕድሜ ልክ እስራት ወይም ሞት እንደሆን ተዳርጓል። በንዑስ አንቀጽ ሁለት ላይ ወንጀሉ በቸልተኝነት ሲፈጸም ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ እንደሚችል ተደንግጓል።

አንቀጽ ፭፻፳ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

ይህ ድንጋጌ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ከአንቀጽ ፭፻፮-፭፻፳ የተዘረዘሩት ወንጀሎች የሚያስቀጡት በግለሰብ ብቻ ሲደረጉ መሆን የለበትም፤ የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው የመጓጓዣና የመገናኛ ድርጅቶችም በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። እነዚህ ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑት፣ ከመገናኛና ከመጓጓዣ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተጣለባቸውን ግዴታ በመጣስ

www.abyssinialaw.com

ሠራተኞቻቸው በመጓጓዣና በመገናኛዎች ነጻነትና ደህንነት ላይ ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊቶችን በሚፈጽሙበት ጊዜ ነው። ለምሳሌ፣ የመርከብ ካፒቴንም ሆነ ነጂ በባህር ላይ ጉዞ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በኋላ ለመርከቡም ሆነ ለተሳፋሪው ደህንነት መከናወን ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች አስመልክቶ የወጣ ደንብ በመጣስ በመርከቦች፣ በተሳፋሪዎች ወይም በባህር እንስሳት ላይ ጉዳት የሚያስከትል አደጋ ቢያደርስ ካፒቴኑና ነጂው ብቻ ሳይሆኑ ቀጣሪያቸው የባህር ማጓጓዣ ድርጅትም ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብነት ባለው አንዱ አንቀጽ መሠረት ይቀጣሉ። ይህም ሊደነገግ የቻለው በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፬ የተቀመጠውን መርህ በመከተል ነው።

## ርዕስ ስምንት
## በጤና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ "አንቀጽ ስምንት" በማለት የተመለከተው ቀደም ሲል በተደረገው ማሻሻያ መሠረት ወጥነቱን ለመጠበቅ እንዲያስችል "አንቀጽ" የሚለው ተሠርዞ "ርዕስ" በሚል እንዲተካ ተደርጓል። ስያሜውም "በሕዝብ ጤና ላይ ስለሚደረጉ ወንጀሎች" በማለት የሚነበበው የውስጥ ይዘቱ በሕዝብ ላይ ብቻ ሣይሆን በእንስሳትና ዕጽዋት ላይም የሚፈጸሙትን ጤናን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የተካተቱበት በመሆኑ በሕዝብ የሚለው ተሠርዞ ሁሉንም ሊያመለክት በሚችል አኳኋን" በጤና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች።" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

## ምዕራፍ አንድ
## የጥበቃ ጠቅላላ ድንጋጌዎች መጣስ

በምዕራፍ አንድ ሥር "ለጥበቃ በተደረጉት ጠቅላላ ድንጋጌዎች ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች" በማለት የሚነበበው ግልጽነት የሚጎድለው በመሆኑና በድንጋጌዎች ላይ ሣይሆን ወንጀሉ የሚፈፀመው ድንጋጌዎቹን በመጣስ በመሆኑ የምዕራፍ ስያሜ ተሻሽሎ "የጥበቃ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን መጣስ" በሚል እንዲነበብ ሆኗል።

## ክፍል አንድ
## በሽታን በማሰራጨትና አካባቢን በመበከል የሚደረጉ ወንጀሎች

ምዕራፍ አንድ በቀድሞው ሕግ መሠረት በስሩ ክፍሎች አልነበሩትም። በዚህ ሕግ ግን በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ የክፍል አንድ ስያሜ "በሽታን በማሰራጨትና አከባቢን በመበከል የሚደረጉ ወንጀሎች"፣ የክፍል ሁለት (አንቀጽ ፭፻፳፰ - ፭፻፵፬) ደግሞ "ሰውና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን በማምረትና በማሰራጨት የሚደረጉ ወንጀሎች" እንዲል ተደርጓል። ተዛማጅ አንቀጾችን በዚህ መልክ ከፋፍሎ ማስቀመጡ ለግልጽነት ይረዳል ተብሎ በመታመኑ ምዕራፉ በሁለት ክፍሎች ሊከፈል ችሏል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፲፬ <u>የሰውን በሽታ ማሰራጨት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፬ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "የሰውን በሽታ ማባዛት" የሚል ነው። ሆኖም ስያሜው ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር በይበልጥ በሚጣጣምበት መልኩ "የሰውን በሽታ ማሰራጨት" በሚል ሀረግ ተተክቷል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ ያስቀመጠው ቅጣት ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ነበር። ሆኖም ,ታስቦ ለተፈፀመ ወንጀል ቅጣቱ ስለሚያንስ ወደ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፪) "አስፈላጊም ሲሆን ከገንዘብ መቀጮ ጋራ ፍርድ ቤቱ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ለመፍረድ የሚችለው" በማለት የተደነገገው ተሰርዞ ቅጣቱን የሚያከብደው ሀረግ ከፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) መጨረሻ ላይ እንዲገባ ተደርጓል። በፊደል ተራ (ሀ) "ከባድ በሽታ" በማለት ብቻ የተመለከተው በቂ መስፈርት መሆኑ ስላልታመነበት ተሻሽሎ "ከባድ ጉዳትን ወይም ሞትን የሚያስከትል በሽታ" በሚል እንዲነበብ ተደርጎአል።

በንዑስ አንቀጽ (፪) በፊደል ተራ (ለ) ስር አዲስ ድንጋጌ የገባ ሲሆን ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው ድርጊት የተፈፀመው በጥላቻ፣ በቂመኝነት፣ በክፋት ወይም በወራዳነት መንፈስ ባይሆንም ከባድ ቅጣት እንዲያስቀጣ ተደርጓል።

የየቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፪) በፊደል ተራ (ሐ) ስር እንዲመጣ ተደርጓል።

ቅጣቱን በተመለከተ የቀድሞው አነስተኛ ቅጣት ተሰርዞ በንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሐ) ስር ባለው ፓራግራፍ ላይ "ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፣ ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።" የሚል አዲስ ሐረግ ተጨምሯል። ይህም በሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ የመሳሰሉ በሽታዎችን በማሰራጨት ወይም በማስተላለፍ የሚደረጉትን ወንጀሎች ለመቅጣት የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌ ይሆናል።

በንዑስ ቁጥር (፫) የተደነገገው ከአንድ ዓመት የማይበልጥ እስራትና መቀጮ አነስተኛ በመሆኑ ዳኛው እንደአስፈላጊነቱ እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት መወሰን ይችል ዘንድ በቀላል እሥራት ተብሎ የተሻሻለ ሲሆን አነስተኛ ለሆኑ ጉዳዮች እንዲያገለግል መቀጮ በአማራጭ እንዲገባ ተደርጎአል።

በተጨማሪም በሶስቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ ሶስቱም ንዑሳን አንቀጾች ተቃንተው ተረቅቀዋል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፲፭ <u>የእንስሳትን በሽታ ማሠራጨት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፭ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "የከብት በሽታን ስለማባዛት" በማለት የተገለፀው በአንቀጽ ፭፻፲፭ በድንጋጌው ስያሜ ላይ በተደረጉት ለውጦች መሠረት "የእንስሳት በሽታን ማስራጨት" በሚል ተተክቷል።

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ "በዶሮ ቤት" የሚለው ሐረግ፣ የእንስሣት በሽታን በማሠራጨት ጥፋተኛ የሚያደርገው በሽታውን በዶሮ ቤት በመንዛት ብቻ ሣይሆን በዶሮዎች መካከል እንዲሰራጭ በማድረግ ስለሆነ "በዶሮ ቤት" የሚለው ንዑስ ሀረግ ተሰርዞ "በዶሮዎች" በሚል ተተክቶአል። ዶሮን የመሳሰሉ እንደ ዳክዬ፣ የግሪክ ዶሮ ባሉት በሚበሉና ለማዳ በሆኑ አእዋፍ መካከልም የእንስሳት በሽታን ማሰራጨት ወንጀል መሆን ስላለበት "በዶሮ ቤት" በሚለው ሐረግ ምትክ ከገባው ንዑስ ሐረግ ቀጥሎ ወይም "ዶሮን በመሣሰሉ ለማዳ አእዋፍ" የሚል ሀረግ ገብቶአል። እንዲሁም "በሚበሳ የዱር እንስሳ" ከሚለው ይልቅ "በሚታደኑ የዱር እንስሳት" የሚለው ንዑስ ሐረግ ሰፋ ያለ በመሆኑ በዚህ አኳኋን እንዲሻሻል ተደርጓል። በተጨማሪም በንቦች መካካል የንብ በሽታ ማሰራጨትም በጤናና በአገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ በወንጀል ሊያስቀጣ ይገባል። ስለዚህ "በአሣ" ከሚለው ንዑስ ሐረግ ቀጥሎ "በንቦች" የሚል ቃል ገብቶ ከተከታዩ ጋራ እንዲነበብ በማድረግ ተሻሽሎአል። ቅጣቱንም በተመለከተ "እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት" የሚለው ሀረግ ቅጣቱ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ዳኛው እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እሥራት ለመወሰን በሚያስችለው መልክ ተሻሽሎ "በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ" በሚል እንዲሻሻል ተደርጎአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) "ነፃነት የማሳጣት ቅጣት እጅግ ቢያንስ ሶስት ወርና እስከ ሶስት ዓመት እሥራት ለመሆን የሚችለው" የሚለው መንደርደርያ ሃሣብ ከተከታዮች ጋር ሆኖ ሲነበብ ውስብስብ ሆኖ ስለሚታይ ሐረጉ ተሠርዞ የንዑስ አንቀጹ መንደርደሪያ "ጥፋተኛው" በማለት እንዲጀምር ተደርጎአል።

በዚህ ንዑስ ቁጥር ፊደል ተራ (ሀ) የተገለፀው ግልፅነት የሚጎድለው በመሆኑ ተሠርዞ "በከፋት እንደሆነ" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል። በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውስጥ እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በፊደል ተራ (ለ) መጀመሪያ "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ ስለነበር ተሠርዞአል።

የቅጣቱ ሀረግ አቀማመጥም ቅጣቱ በንዑስ ቁጥር ሁለት መግቢያ መሆኑ ቀርቶ በንዑስ ቁጥር ሁለት ከፊደል ተራ (ለ) መጨረሻ "ቅጣቱ ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል።" በማለት እንዲገለጽ ተደርጎአል።

በንዑስ አንቀጽ ሶስት እና በሌሎች ሁለት ንዑስ አንቀጾች ላይ ተጨማሪ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ሶስቱም ንዑሳን አንቀጾች ተረቅቀዋል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፲፯ <u>የሰብልን ወይም የደንን ተባይ ማራባት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፯ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ትል" በማለት የተገለፀው ጠበብ ያለ መስሎ ስለሚታይ እንዲሰፋ ለማድረግ ቃሉ ተሠርዞ "ተባይ" በሚል ቃል ተተክቶአል። እንዲሁም በዚህ ስያሜ ውስጥ "ስለመንዛት" የሚለው ከመንዛት በፊትም እንኳን ቢሆን ማራባቱ ወንጀል መሆን ስላለበት ከትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለው ንዑስ ሀረግ ተሠርዞ "ማራባት" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል።

ይዘቱንም በተመለከተ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያዎች ተደርገውበት ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፭፻፲፰ <u>ውሃን መበከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፰ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ውሀን ስለማበላሸት።" የሚል ሲሆን "ውሃን መበከል" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል።

ይዘቱንም በተመለከተ ለንዑስ ቁጥር (፩) የተደነገገው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል የጽኑ እሥራት ቅጣት ከወንጀሉ ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ስለሆነ "እስከ አምስት ዓመት" በሚለው ሀረግ ውስጥ "አምስት" የሚለው ቃል ተሠርዞ "ሰባት" በሚል ቃል ተተክቶአል። በተጨማሪ ንዑስ ቁጥሩ ላይ "ለሰው ወይም ለእንስሳት" ከሚለው ቀጥሎ "ለእጽዋት" የሚል ገብቷል።

በድንጋጌው በሶስቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ ተጨማሪ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ሶስት ንዑስ አንቀጾች ተረቅቀዋል።

አንቀጽ ፭፻፲፱ <u>ግጦሽን መበከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፲፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ላይ "ማበላሸት" የሚለው ቃል በመርዝ የመበከልን ውጤት የማያስረዳ አጠቃላይ ቃል ተሠርዞ "መበከል" በሚል ቃል ተተክቶአል።

የንዑስ ቁጥር አንድን ይዘት በተመለከተ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት "ማንኛውም ሰው" የሚለው ሀረግ በድንጋጌው መጨረሻ ላይ ከሚገባ ይልቅ በመግቢያው ላይ መቀመጡ ስለሚመረጥ ካለበት ቦታ ተሰርዞ በዓረፍተ-ነገሩ መግቢያ ላይ "ማንም ሰው" ተብሎ እንዲገባ ተደርጓል።

እንዲሁም ግጦሽን ለመበከል ማንም ሰው መብት ይኖረዋል ተብሎ ስለማይገመት አስቦና መብት ሳይኖረው" የሚለው ሀረግ ከንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ ተሰርዟል። "በመጣል አኳኋን" የሚለው ሀረግም ግልጽ ስላልሆነ ተሠርዞ "ለመጣል አስቦ" በሚል ሀረግ ተተክቶአል። በዚህ ንዑስ ቁጥር "ያበላሸ" በማለት የተገለፀው አጠቃላይ በመሆኑና በመርዝ መበከልን በሚገባ የማያንፀባርቅ በመሆኑ በስያሜው ላይ በተሻሻለው አኳኋን ትስውጠ "የበከለ" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል።

www.abyssinialaw.com

በዚህ ንዑስ ቁጥር የተመደበው እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እሥራት ስለሚያንስ "እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ" የሚለው ሀረግ ተሠርዞ "እስከ ሰባት ዓመት ለመድረስ በሚችል" በሚል ሀረግ ተተክቶአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) "እሥራት" በማለት የተገለፀው የእሥራቱን ዓይነት እንዲያመለክት ቀደም ሲል በተደረጉት ማሻሻያዎች መሠረት "ቀላል እሥራት" በሚል እንዲስተካከል ተደርጎአል።

ድንጋጌው ከላይ በተገለፀው አኳኋን ተሻሽሎና ሌላ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቋል።

አንቀጽ ፭፻፲፱ <u>የአካባቢ መበከል</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ አልነበረም።

ንዑስ አንቀጽ (፩) ሕግ በመተላለፍ በካይ ነገሮችን ወደ አካባቢ መልቀቅን ወንጀል የሚያደርግ ሆኖ የተረቀቀ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ ድርጊቱ በሰው ሕይወት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ሲያስከትል ቅጣቱ ከፍ የሚል መሆኑን የሚደነግግ ነው። ንዑስ አንቀጽ (፫) ደግሞ አድራጊው ከፍተኛ ቅጣት የሚደነግግ ሕግ የጣሰ ሲሆን ለዚሁ ወንጀል በተደራቢነት የሚጠየቅ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

አንቀጽ ፭፻፳ <u>አደገኛ የሆነ ቆሻሻና ሌላ ቁስን በአግባቡ አለመያዝ</u>

አንቀጹ አዲስ ሲሆን አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ያልያዘ፣ እነዚህን ነገሮች በተመለከተ መለጠፍ ያለበትን ዝርዝር ያልለጠፈ ወይም አደገኛ ነገሮችን ወይም ቆሻሻዎችን ዝውውር ያካሄደ ሰው ወንጀል የፈፀመ መሆኑን የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፭፻፳፩ <u>የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶችን መፈጸም</u>

አንቀጹ በቀድሞው ህግ ያልነበረ ሲሆን ማንኛውም የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ እንዲደረግበት በሕግ የታዘዘውን ፕሮጀክት ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ ወይም ይህንን በሚመለከት ሐሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ በወንጀል የሚቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፭፻፳፪ <u>ጤናን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፪ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ ከእንግሊዝኛውና ከፈረንሣይኛው ቅጂዎች ጋር ተመሳክሮ "ጤናን ለመጠበቅና ለመንከባከብ በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች መጣስ" በሚል እንዲስተካከል ተደርጎአል።

www.abyssinialaw.com

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩትና እያንዳንዱ ንዑስ ቁጥር በሁለት ፓራግራፎች የተከፈለ ሲሆን፣ አራቱም ፓራግራፎች በየበኩላቸው ቅጣት ስለሚደነግጉ አራት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎ ተረቋል::

ይዘቱንም በተመለከተ የንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ በባለቤት እንዲጀመር ለማድረግ "ማንኛውም ሰው" የሚለው ሀረግ ከፓራግራፉ መጨረሻ ላይ ተሰርዞ ከዓረፍተ-ነገሩ መጀመሪያ ላይ ገብቶአል:: ተላላፊ በሽታዎችን በይበልጥ ማስወገድ የሚቻለው በመከላከል እንደመሆኑ "ለማስወገድ" የሚለው "መከላከል" በሚል ቃል ተተክቶአል:: ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማቆም ብቻ ሣይሆን ለመግታትም በሕግ መደንገግ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ሊያጋጥም ስለሚችል "ለመከላከል" ከሚለው ቃል በኋላ "ለመግታት" የሚል ቃል ገብቶአል:: እንዲሁም "በሕግ በደንብ በባለሥልጣን የተሰጡትን ድንጋጌዎች" የሚለው አገላለጽ ግለጽነት የሚጎድለው በመሆኑ ተሰርዞ የእንግሊዝኛውና የፈረንሣይኛውን ቅጂዎች ተከትሎ "በሕግ የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች" በሚል ሀረግ ተተክቶአል::

የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደረገ ሲሆን የተደነገገው መቀጮ አነስተኛ በመሆኑ "እስከ ሺህ ብር" ይል የነበረው ተሠርዞ "እስከ ሶስት ሽህ ብር" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል::

ንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደረገ ሲሆን፣ "የከብት በሽታ ወይም የትል ርቢ ወይም የሰብል ወይም የደን ትልን ማብዛት ለማስወገድ" የሚለው ሀረግ ግልጽ ስላልሆነ ተሠርዞ "የእንስሳት በሽታን ወይም የሰብል ወይም የደን ተባይ ወይም የረቂቅ ህዋሣት መሰራጨትን ለመከላከል "በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

"ለመከላከል" ከሚለው ቃል በፊትም "የአከባቢ ብክለት" የሚል ሐረግ የገባ ሲሆን ከዚህ በላይ የተካተቱትን፣ ስለአካባቢ ብክለት የተደነገጉትን የሦስት አዲስ አንቀጾች ይዘት ለማመልከት ነው:: በንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ እንደተገለፀው በሽታን ለማስወገድ ወይም ለማቆም ብቻ ሳይሆን ድንጋጌው የሚያስፈልገው ለመግታት ጭምር በመሆኑ "ለመከላከል" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ለመግታት" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጎአል:: በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ቁጥር "ውሣኔዎች ወይም ደንቦች" በማለት የሚነበበው ግልጽ ባለመሆኑ ተሠርዞ ከላይ በንዑስ ቁጥር (፩) በተሻሻለው መሠረት "የተደነገጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች" በሚል ሀረግ እንዲተካ ተደርጎአል:: የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኗል::

አንቀጽ ፭፻፳፫ <u>ችግር ወይም ረሀብ እንዲደርስ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፫ ሆኖ ገብቷል::

ከንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ማንኛውም ሰው" የሚለው ተሰርዞ በዐረፍተነገሩ መጀመሪያ ላይ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ "ሆን ብሎ የማይገባውን በመሥራት ወይም የሚገባውን ባለመሥራት" የሚለው ሀረግ አስፈላጊ ስላልሆነ ተሠርዞአል:: እንዲሁም በመነሻነት የተቀመጠው ዝቅተኛው ቅጣት እንዳለ ሲቀመጥ በመድረሻነት የተቀመጠው ከፍተኛው የቅጣት ጣሪያ ያነሰ መስሎ ስለሚታይ "እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ

www.abyssinialaw.com

እሥራት" የሚለው ተሠርዞ እስከ "አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት" በሚል እንዲነበብ ሆኖ ተሻሽሎአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ፍሬ ሀሣብ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ብቻ ተደርጎበታል።

በንዑስ ቁጥር (፫) ወንጀሉ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማቀድ ሲሆን የእሥራት ቅጣቱን በሚመለከት ከሰስት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል እንደሚሆን የተደነገገው ለወንጀሉ የሚያንስ ስለሆነ መነሻው የእሥራት ቅጣት ቀርቶ "እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት" በሚል እንዲሻሻል ተደርጎአል። የሃያ ሺህ ብር መቀጮውም አሁን ካለው ሁኔታ ጋር የማይጣጣምና እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ተሠርዞ "እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል።

ድንጋጌው ሌሎችም አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፭፻፳፬ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

ይህ ድንጋጌ አዲስ የገባ አንቀጽ ሲሆን ያንድ ድርጅት ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች የሰውና የእንስሳትን በሽታ በማሰራጨት፣ የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢን መበከል፣ እንዲሁም ለከባድ ረሀብና ችግር በማድረስ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት በወንጀል ተጠያቂ በሚሆኑበት ጊዜ፣ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፴፬ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ኃላፊዎቹና ሠራተኞቹ ብቻ ሳይሆኑ የሚሰሩበት/ ቀጣሪያቸው ድርጅትም በወንጀል እንደሚቀጣ የሚደነግግ ነው።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>በሰውና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን</u>
<u>በማምረትና በማሰራራጨት የሚደረጉ ወንጀሎች</u>

የዚህ ክፍል ስያሜ በቀድሞው ሕግ ላይ ያልነበረ ሲሆን፣ ይህ ክፍል በሚገኝበት ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ምዕራፉ በሁለት የተከፈለው፣ ተቀራራቢ አንቀጾችን በየክፍሉ መመደቡ ለግልጽነት አስዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ ነው።

አንቀጽ ፭፻፳፭ <u>መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም እፆችን ማምረት ወይም መስራት፣ እንዲዘዋወሩ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲ ድንጋጌ ከፍተኛ ለውጥ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፭ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ ላይ፣ መርዛማ ወይም የሚያፈዙ ነገሮች ብቻ ተጠቅሰው ነበር። በዚህ አንቀጽ ግን "የሚያፈዙ" የሚለው ቃል ተሰርዞ "ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች እና ዕጾች" እንዲጨመሩ ተደርጓል። ድርጊቱንም በተመለከተ "ማውጣት ወይም መስራት እንዲዘዋወሩ ማድረግ" ብቻ በማለት ፈንታ ማብቃል፣ ማምረት፣ መስራት፣መለዋወጥ፣ መፈብረክ፣ ማዘዋወር እና መጠቀም የሚሉት ቃላት ተካትተዋል።

www.abyssinialaw.com

የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ተከፍሎ አዲስ አሳቦችም ታክለውበት እንዲቀረጽ ተደርጓል። የፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ በስያሜው ላይ የተመለከቱትን ነገሮች ማብቀልን፣ ማምረትን፣ መስራትን፣ መለዋወጥን እና መፈብረክን ብቻ የሚመለከት ሲሆን፣ የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ደግሞ ነገሮቹን ይዞ መገኘትን፣ ወደ አገር ማስገባትን፣ ወደ ውጭ አገር መላክን፣ ለሽያጭ ማቅረብን፣ ማሰራጨትን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ መደለልን፣ መግዛትን፣ ማዘዋወርን፣ አሳልፎ መስጠትን እና ለሌላ ሰው ማስገኘትን እንዲሸፍን ተደርጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል ተራ (ሐ) ስር አዲስ አሳብ የያዘ ድንጋጌ እንዲጨመር ተደርጓል፤ ይኸውም፣ በድንጋጌው ስያሜ ላይ ከተዘረዘሩት ነገሮች አንዱን ለማምረት፣ ለማቀነባበር ወይም ለመፈብረክ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን መስራትን፣ይዞ መገኘትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን ወይም ወደ ውጭ አገር መላክን እንደወንጀል የሚቆጥር ድንጋጌ ሆኗል። በንዑስ አንቀጽ (፩) በፊደል ተራ (መ) ላይ በፊደል ተራ (ሀ) ለተገለጹት ነገሮች መስሪያነት፣ ማቀነባበሪያነት፣ ማምረቻነት፣ መሸጫነት ወይም ማከፋፈያነት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሆነበትን ቤቱን፣ ግቢውን ወይም ቦታውን የሚሰጥ፣ የሚያከራይ ወይም የሚፈቅድ ሰው የሚቀጣበት ድንጋጌ ሆኗል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) ስር የገባ ሲሆን የአሳብ መቃናትና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

በቀድሞው ሕግ በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ የተቀመጠው የእስራት ቅጣት ከሶስት ወር እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ሲሆን የዚህ ሕግ ንዑስ አንቀጽ (፩) ግን በአሁኑ ጊዜ የወንጀሉን ክብደት ከግንዛቤ በማስገባት ቅጣቱ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት እንዲሆን ደንግጓል። የመቀጮውም ጣራ ከብር ሃያ ሺህ ወደ ብር አንድ መቶ ሺህ አድጓል።

የቀድሞ ሕግ ንዑስ ቁጥር (፫) በንዑስ ቁጥር (፩) የተመለከቱት ድርጊቶች ሲፈጸሙ የሚችሉበትን ከባድ ሁኔታዎች በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከፍሎ የሚዘረዝር ሲሆን፣ አገላለጹ ተሻሽሎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እና (ለ) ሆኖ ገብቷል።

ከዚህም በላይ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ በዓለም-አቀፍ ኮንቬንሽን የተመለከቱ ቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች ያካተተ ሲሆን ወንጀሉ የተፈጸመው ህፃናትን ወይም የአእምሮ በሽታ ያደረበትን ሰው ለወንጀል ድርጊቱ አፈጻጸም መጠቀሚያ በማድረግ ወይም እንደ ትምህርት ቤቶች በመሳሰሉት ወይም በደጋጋሚነት እንደሆነ፣ የቅጣቱ ጣራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና ብር ሰላሳ ሺህ መሆኑ ቀርቶ፣ የጽኑ እስራቱ ቅጣት መነሻ አስር ዓመት እንዲሆንና የመቀጮውም ጣራ ብር ሁለት መቶ ሺህ እንዲደርስ አድርጎ ይደነግጋል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የገባ ሲሆን ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተመለከቱት ድርጊቶች በቀጥታ ተሳታፊ ባይሆንም ሁኔታውን እያወቀ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ነገሮች ይዞ የተገኘ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ ወይም አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ሊቀጣ መቻሉን የሚደነግግ ነው።

አንቀጹ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) የገባለት ሲሆን ማንም ሰው ከዚህ በፊት ባሉት ንዑሳን አንቀጾች በተገለጸው ዓላማ ሳይሆን ራሱ ወይም ሌላ ሰው በግሉ እንዲጠቀምበት በማሰብ

 www.abyssinialaw.com

የተከለከሉትን ነገሮች ያበቀለ፣ የገዛ፣ የተቀበለ ወዘተ...... ወይም በነዚህ ነገሮች ያለ ሀኪም ፈቃድ የተጠቀመ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ያደረገ እንደሆነ እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል።

አንቀጹ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ያለው ሲሆን በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ነገሮች በተመለከተ "ለሕገወጥ ዓላማ ሲል የሕክምና ባለሙያን በማጭበርበር የመድኃኒት ማዘዣው እንዲጻፍለት ያደረገ ወይም በሕጋዊም ሆነ በሕገወጥ መንገድ ያገኘውን ማዘዣ ለተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ ሰው ወይም አስቦ ሕገወጥ የመድኃኒት ማዘዣ የሰጠ የሕክምና ባለሙያ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል" የሚል ነው።

ንዑስ አንቀጽ (፮) ወደ ሌሎች አንቀጾች የሚመራ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን "በዚህ ሕግ ለመውረስ ገቢ ሲሆን ስለሚገባው ሀብት (አንቀጽ ፻፵) እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ስለማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ ፮፻፹) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።" በማለት ይደነግጋል።

የዚህ አንቀጽ በዚህ መልክ መቀረጽ በዓለም ዓቀፍም ሆነ በአገር ደረጃ ከአደንዛዥ እጾች ጋር ተያይዞ እየተስፋፋ የመጣውን ልዩ ልዩ አስከፊ ሕገ ወጥ ድርጊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

አንቀጽ ፭፻፳፮ <u>ዶፒንግ</u>

ይህ አንቀጽ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ያልነበረ ሲሆን ከስፖርት ውድድር ጋር በተያያዘ ሁኔታ መድኃኒቶችን ያለአግባብ ማምረትን፣ ወደ አገር ማስገባትን፣ ማዘዋወርና መሸጥን ወይም መጠቀምን ለመከላከል የገባ ነው።

ድንጋጌው ሦስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል። በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ፣ ኃይል የሚጨምሩ ጎጂ የሆኑ ሰው ሠራሽ ነገሮችን ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማዘዋወር፣ መሸጥ ወይም መጠቀም እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል። ንዑስ አንቀጽ (፪) በንዑስ አንቀጽ (፩) ለተገለፀው ዓላማ ለማዋል በመሳብ፣ በሕግ የተፈቀደ መድሃኒትን ያለአግባብ ወይም ከተሰራበት ዓላማ ውጭ ማዘዝን፣ መስጠትን ወይም መጠቀምን እንደወንጀል ቆጥሮ እንዲያስቀጣ የሚያደርግ ሲሆን፤ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ድርጊት በቸልተኛነት ሲፈፀም የሚያስቀጣ መሆኑን የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ይገልፃል።

አንቀጽ ፭፻፳፯ <u>የሚጎዱ ወይም የተበላሹ ዕቃዎችንና ምግቦችን መሥራትና መሸጥ እንዲሁም ጥራታቸውን ማርከስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፯ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "የሚጎዱ ወይም የተበላሹ ምግቦችንና ዕቃዎችን መስራትና መሸጥ" የሚለው ይዘቱን በሚገባ የማያንፀባርቅ በመሆኑ የተባሉትን ነገሮች ከመስራትና ከመሸጥ በተጨማሪ በይዘቱ ውስጥ ጥራታቸውንም ማርከስ የተገለፀ በመሆኑ ይህንኑ የሚያመለክት ሀረግ በስያሜው ላይ ገብቷል።

www.abyssinialaw.com

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተጻፈው "ማንኛውም ሰው" የሚለው ሀረግ ካለበት ቦታ ተሰርዞ በንዑስ አንቀጹ መግቢያ ላይ "አስቦ" ከሚለው ቃል በፊት "ማንም ሰው" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጎአል።

በፊደል ተራ (ሀ) "ምግቦችን፣ ቀለቦችን" ብቻ ሣይሆን ለሰው ምግብነት ተስማሚ ያልሆኑና በምግብነት የሚያገለግሉ ሌሎች ነገሮችንም የሕዝብ ጤና አደጋ ላይ ለመጣል በማሰብ መስራት በዚህ ድንጋጌ ሊያስቀጣ የሚገባ ድርጊት ስለሆነ በፊደል ተራ (ሀ) "ምግቦችን፣ ቀለቦችን" ከሚሉት ቃላት በኋላ "በምግብነት የሚያገለግሉ ሌሎች ነገሮችን ለሰው ፍጆታ እንደማይመቹ በማድረግ" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጎአል።

በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውስጥ እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) መጨረሻ ላይ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። በፊል ተራ (ለ) በመጀመሪያው አዲስ ፖራግራፍ መጀመሪያ ላይ የተመለከተው "ወይም" የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ ስለሆነ ተሰርዞአል።

ቅጣቱም "የሶስት ወር ቀላል እስራትም ሆነ በከባድ ሁኔታዎች እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት" በማለት የተደነገገው ከወንጀሉ ድርጊት አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ "ሶስት ወር" በሚለው ምትክ "ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት" እንዲሁም "ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት" የሚለው "ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት" በሚል እንዲሻሻል ሆኖአል።

በንዑስ ቁጥር (፪) "ቅጣቱ በተለይ ከፍ ያለ የሚሆነው" የሚለው አገላለጽ ቢያንስ ዝቅተኛውን የቅጣት ጊዜ የማያመለክት በመሆኑ አገላለፁ ተሻሽሎ "ቅጣቱ ከሰባት ዓመት የማያንስ ጽኑ እሥራት የሚሆነው" በማለት እንዲነበብ ሆኖአል።

በንዑስ ቁጥር (፫) የተደነገገውም ሆነ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል።

አንቀጽ ፭፻፳፰ <u>የከብት ድርቆሽና ሌላም መኖ ጉዳት እንዲደርስ አድርጎ መሥራት፣ ጥራትን ማርከስና መሸጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፰ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር ፩ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውስጥ እያንዳንዱ የሚያስቀጣ መሆኑን ለማመልከት በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ቀጥሎ "ወይም" የሚል ቃል ገብቶአል። ጉዳት የሚያደርስ ድርቆሽ ወይም ሌላ አይነት መኖ ለሽያጭ ማቅረብ፣ ተገዝቶ ለቤት እንስሳት እንዲቀርብ መጋበዝ ስለሚሆን ድርጊቱ እንደሚያስቀጣ መደንገጉ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ለ) "ያስቀመጠ" የሚል ቃል "ያከማቸ" በሚል ቃል ተተክቶ "ያከማቸ" የሸጠ" ከሚሉት ቃላት ቀጥሎ" "ለሽያጭ ያቀረበ" የሚል ሐረግ ገብቶአል።

በፊደል ተራ (ለ) "እሥራት" በማለት የተመለከተው የእሥራቱን ዓይነት ለይቶ ለማመልከት እንዲያስችል "በቀላል እሥራት" በሚል ተሻሽሎአል።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ቅጣት ከወንጀሉ ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ተሻሽሎ "እስከ ሶስት ወር" በማለት የሚነበበው "እስከ ሶስት ዓመት" በሚል እንዲተካ ተደርጓል::

ድንጋጌው የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፭፻፹፱ <u>ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፱ ሆኖ ገብቷል::

ወንጀሉ የተፈፀመው ወንጀሉን ሙያ አድርጎ በመያዝ ወይም ከፍተኛ ብዛት ባላቸው ዕቃዎች ላይ ከሆነ በዚሁ ድንጋጌ ውስጥ የመቀጮውን ቅጣት በሚመለከት እስከ ሃያ ሽህ ብር ብቻ ሊሆን ስለማይገባ "መቀጮውም እስከ ሃያ ሺህ ብር ለመድረስ ይችላል" በሚለው ዓረፍተ-ነገር ውስጥ "ሃያ" የሚለው ቃል ተሠርዞ "ሁለት መቶ ሽህ ብር" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

ድንጋጌው የሌሎች የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፭፻፺ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

የዚህ ዓይነት አንቀጽ የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ ሲሆን በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፶፱ በተደነገገው መርህ መሠረት እንዲቀረጽ የተደረገ ነው:: ተቀጣሪ ግለሰቦች መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ዕጾችን፣ ኃይል የሚጨምሩ ጎጂ የሆኑ ሰው ሰራሽ ነገሮችን፣ የሚጎዱ ወይም የተበላሹ ዕቃዎችንና ምግቦችን ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የከብት ድርቆሽን ወይም ሌላ መኖን ሲያመርቱ፣ ሲሰሩ፣ ሲያዘዋውሩ..... ወዘተ በወንጀል በሚቀጡበት ጊዜ፣ የቀጠራቸው ድርጅትም የአንቀጽ ፶፱ ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል የሚደነግግ አንቀጽ ሆኖ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፭፻፺፩ <u>በአልኮል ወይም በእስፒርቶ መጠጦች የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ማጋለጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፩ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ ቀደም ሲል "በማይገባ ስለማስጠት" በሚለው ሀረግ ምትክ "የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ማጋለጥ" በሚል አዲስ ሀረግ እንዲተካ ተደርጓል:: ቀደም ሲል በአንድ ፓራግራፍ ውስጥ የነበረው "ባለማሰብ አውቆ አልኮል እስፒርቶ ለአካለ መጠን ሳልደረሱ የሰጠ" የሚለው አነጋገር በአንድነት የሚካተት ሳይሆን በተናጠል አስበ ይህን ድርጊት መፈጸም በንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሆንና በቸልተኝነት ለሚፈጸም ድርጊት ደግሞ በንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲካተት ተደርጎ ተረቅቋል:: ደጋጋሚነትን በተመለከተ ራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

ለተመለከተው ወንጀል የተመደበው ቅጣት "እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ቀላል እሥራት" ለወንጀሉ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ "እስከ ሶስት ወር" የሚለው ተሰርዞ "እስከ አንድ ዓመት" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል:: እንዲሁም እሥራቱ ከመቀጮው ጋር በአማራጭነት ተደንግጎ የነበረው ቢጣመር የተሻለ መሆኑ ስለታመነበት "ወይም" የሚለው

www.abyssinialaw.com

ተሠርዞ "ና" በሚል መስተጻምር እንዲያያዝ ተደርጎአል:: በተጨማሪም "በገንዘብ መቀጮ" በማለት የሚነበበው መቀጮ ብቻ ተደርጎአል:: ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ይዘቱ የአንዳንድ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፴፪ ለሰምሮን በማነኩ ድርጊቶች ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፭ ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያ ከተደረገበት እና አቀራረቡ ተሻሽሎ ግልጽ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፪ ሆኖ እንዲገባ ተደርጎአል::

አንቀጽ ፭፻፴፫ በድግምት፣ በጥንቆላ ወይም ይህን በመሳሰሉ ነገሮች በሰው ላይ አደጋ ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፫ ሆኖ ገብቷል::

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፭፻፲፮ ድንጋጌ ከአንዳንድ የቃላት ማስተካከያ በቀር እንዳለ ተቀባይነትን አግኝቶ የዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፫ ሆኖ እንዲገባ ተደርጎአል::

አንቀጽ ፭፻፴፬ ከባድ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፬ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) ወንጀለኛው ከዚህ በላይ በተመለከቱት አንቀጾች ከተጠቀሰው ወንጀል እንደኛውን እንደ ሞያ አድርጎ የያዘ እንደሆነ እስከ ስድስት ወር ሊደርስ እንደሚችል የተደነገገው የእሥራት ቅጣት ለወንጀሉ ስለሚያንስ ተመጣጣኝ ቅጣት ለመመደብ "ስድስት ወር" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራትና በመቀጮ ይቀጣል" በሚል ሐረግ ተተክቶአል::

በንዑስ ቁጥር (፪) የተደነገገው ፍሬ ሃሣብ የአንዳንድ ቃላት ማስተካከያና የአጣቃሽ አንቀጽ አቀማመጥ ማሻሻያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፴፭ <u>በሕክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ መስራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፭ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ የሕክምናንና የጤና አጠባበቅን ሥራ አስፈላጊው ሳይፈጽም መሥራትን የሚያመለክት ብቻ መስሎ ይታያል። ነገር ግን ይዘቱ አንድ ግለሰብ ሙያ እንኳን ኖሮት በሙያው ያለአግባብ መሥራትንም እንደ ወንጀል ድርጊት የሚቆጥረው በመሆኑ ይህንኑ በተሻለ ሁኔታ ለማመልከት ስያሜው ተሻሽሎ "በሕክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ መስራት" በሚል እንዲነበብ ሆኖአል።

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲገባ ሲደረግ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ሆነዋል።

ይዘቱንም በተመለከተ በንዑስ ቁጥር (፩) ባለቤቱን ለማመልከት "ማንኛውም ሰው" በሚል እንዲጀምር ሲደረግ ከነበረበት የቀድሞ ቦታ እንዲሰረዝ ተደርጓል። በዚሁ ንዑስ ቁጥር ለተደነገገው የወንጀል ድርጊት የተመደበው ቅጣት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በእስራት በማለት የተመለከተውን ዝቅተኛውን የቅጣት ጊዜ መገደቡ አስፈላጊ በመሆኑ ተሻሽሎ "ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት" በሚል እንዲነበብ ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር (፪) ለተመለከተው ወንጀል በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መቅጣቱ ቅጣቱን የሚያከብድ በመሆኑ "ይኸው ድንጋጌ ይጸናል።" በማለት የሚነበበው ተሰርዞ" በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።" በሚል ተተክቷል። በንዑስ ቁጥሩ "ለከብት" በማለት የተመለከተው ጠባብ በመሆኑና ከከብቶች ሌላም ሌሎች እንስሳትን ሊያካትት በሚችል መልክ ለመቅረጽ ከላይ በትእምርተ ጥቅስ የተቀመጠው ቃል ተሰርዞ "እንስሳትን" በሚል ተተክቷል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ የገባው ድንጋጌ በአራት ፊደላት የተከፈለ ሲሆን በልዩ ልዩ ሕገ ወጥ መንገድ የተዘጋጀን ጥራት የጐደለውን፣ የተበላሸውን፣ ጊዜ ያለፈበትን ወዘተ ... መድኃኒት ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ የህክምና መሣሪያ ያመረተ፣ የሸጠ ወዘተ ... ሰው ከባድ ቅጣት እንዲወሰንበት ይደነግጋል።

በቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) እና (፬) /በዚህ ሕግ በንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭)/ የተመለከቱትም ግልጽ ስላልሆኑ በአዲስ አቀራረብ ተዘጋጅተዋል።

በተጨማሪም ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት መቃናት ተደርጎበት አንቀጹ ተረቋል።

አንቀጽ ፭፻፴፮ <u>መርዛማና አደገኛ የሆኑ ነገሮችን አለአግባብ ማቅረብ፡</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፮ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው መግቢያ ላይ "መድኃኒት ቀማሚ" የሚለው ሐረግ አሻሚ ትርጉም እንዳያመጣ እና ፋርማሲስት" ማለት እንደሆነ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ ከሐረጉ ቀጥሎ "ፋርማሲስት የሚል ቃል ገብቶአል። ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፴፭ እንደተገለፀው "የከብት" የሚለው ንዑስ ሐረግ ተሰርዞ "የእንስሳት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል።

 www.abyssinialaw.com

እንዲሁም" የሚያፈዙ በሆኑ" በማለት የተመለከተ ግልጽነት የሚጎድለው በመሆኑና ናርኮቲክንና ሣይኮትሮፒክ ነገሮችን ለማመልከት በመሆኑ" "የሚያፈዙ በሆኑ" በማለት የሚነበበው ተሰርዞ "መርዛምና" በሚለው ውስጥ "ና" የሚለው መስተፃምር በ "ወይም" ከተተካ በኋላ እንዲሁም "ወይም" በማለት ከተመለከተው በፊት "በሆነ" የሚል ቃል እንዲገባ "ወይም" በማለት ከገባው ቃል ቀጥሎ ደግሞ "በናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ ነገሮች" በማለት የሚነበብ አዲስ ሐረግ ገብቶአል:: "የሰጠ" ከሚለውም ቃል ቀጥሎ "ወይም የሸጠ" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል::

ቅጣቱንም በተመለከተ ለወንጀል ድርጊቱ የተመደበው ቅጣት ከወንጀሉ ድርጊት ጋር ሲታይ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ "በእሥራት ይቀጣል" በማለት የተመለከተው ዝቅተኛውን ቅጣት በማስቀረት "ከሶስት ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት" በሚል እንዲተካ ተደርጎአል:: በተጨማሪም ነፃነት ከማሳጣቱ ጋር ተጣምሮ የሚወሰን መቀጮ በአዲስ ሁኔታ እንዲገባ ተደርጓል::

ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜም የተደነገገው የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ተሻሽሎ ወደ ሰባት ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል:: በአፍቅሮ ንዋይ ፍላጎት ለሚደረገው የወንጀል ድርጊት የተመደበው የሃያ ሺህ ብር መቀጮም እንዲሁ ተሻሽሏል:: "ሃያ ሺህ" የሚለው ተለውጦ "አንድ መቶ ሺህ" በሚል ተተክቶአል:: ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፴፯ <u>የሕክምና እርዳታን ያለምክንያት መከልከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፯ ሆኖ ገብቷል::

በፊደል ተራ (ለ) ላይ "መድኃኒት ቀማሚ" የሚለው ሐረግ አሻሚ ትርጉም እንዳያመጣ እና "ፋርማሲስት" ማለት እንደሆነ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ ከሐረጉ ቀጥሎ "ፋርማሲስት" የሚል ቃል ገብቶአል:: ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፭፻፴፭ እንደተገለፀው "የከብት" የሚለው ንዑስ ሐረግ ተሰርዞ "የእንስሳት" በሚል ንዑስ ሐረግ ተተክቶአል:: እንዲሁም "ተግባሩ የሆነ በደንብ የታወቀ ሰው" በሚለው ሀረግ ምትክ "ተግባሩ መሆኑ በሕግ የታወቀለት ማንኛውም ሌላ ሰው" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: "በተግባሩ ተቃራኒ በመሆንና ባልተገባ ምክንያት በእውነት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሳያደረግም በማለት" በሚለው ሐረግ ምትክ "ተግባሩን በሚቃረን መንገድና በቂ ባልሆነ ምክንያት" በሚል ሐረግ ተተክቶአል:: "አስፈላጊ የሆነውን በሙያ ተግባሩ ሊያደርግ የሚገባውን አገልግሎት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ" የሚል አዲስ ሐረግ ድንጋጌውን ይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችል እንዲገባ ተደርጓል::

ቅጣቱን በሚመለከት "በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ነገሩም በተደጋገመ ጊዜ እስከ አንድ ወር ለመድረስ በሚችል እስራት ይቀጣል" የሚለው ተሰርዞ "በመቀጮ ወይም ወንጀሉ የተደጋገመ እንደሆነ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት" የሚያስቀጣ ተደርጎ ተረቅቋል::

የንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

## አምስተኛ መጽሐፍ
## በሌሎች ሰዎችና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ርዕስ አንድ
## በሰው ሕይወት፣አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## ምዕራፍ አንድ
## በሰው ሕይወት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

## ክፍል አንድ
## የመግደል አደራረግና ዓይነቶች

### አንቀጽ ፭፻፴፰ መርህ

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፭፻፳፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፰ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የድንጋጌው ስያሜ "መሠረቱ" ይል የነበረ ሲሆን "መርህ" በሚል ተተክቷል፡፡ የቀድሞው ድንጋጌ ሶስት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን በዚህ ሕግ ግን በሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

አንቀጹ በንዑስ አንቀጾች የተከፋፈለው በአንቀጹ ላይ ያሉት ሃሳቦች ጎላ ብለውና ተለይተው እንዲወጡ ስለተፈለገ ነው፡፡ በአንቀጹ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ ፭፻፴፱ ከባድ የሰው ግድያ

የ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የቁጥር ፭፻፳፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፱ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ፣ "ከባድ (የግፍ) አገዳደል" ይል ነበር በእንግሊዘኛው ቅጅ ላይም፣ "Aggravated Homicide - Homicide in the First Degree" የሚል ስያሜ አለው፡፡ የቀድሞው ድንጋጌ የአማርኛ ስያሜ፣ የሚገደለው ሰው መሆኑን በግልጽ ካለማሳየቱም በላይ ትኩረት የሚያደርገው በአገዳደሉ፣ ማለት በግድያው አፈፃፀም ላይ እንጂ በግድያው ማለት በውጤቱ ላይ አይደለም፡፡ የድንጋጌው የእንግሊዘኛው ትርጉምም፣ ~~የሚገልጸው~~ ሰው መሆኑን በግልጽ ማመልከቱ የሚደገፍ ሲሆን በሁለት በተለያዩ ተመሣሣይ ሐረጎች ስሚው መገለፁ ግን አስፈላጊ አይደለም፡፡

ስለዚህ ስያሜው ተሻሽሎ የወንጀሉን ከባድነት፣ የሚገደለውን ማንነት እና የወንጀሉን ውጤት በሚያሳይ አጭር አገላለጽ "ከባድ የሰው ግድያ" እንዲል ተደርጓል፡፡

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ "ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ያደረገው አገዳደል"፡፡ ከሚለው ሀረግ ውስጥ "ማንም ሰው" የሚሉት ቃላት ባሉበት እንዲሆኑ ሲደረግ ሌላው አነጋገር ግን ተሰርዞ በንዑስ ቁጥር (፩) ከፊደል ተራ (ሐ) በታች በሚገኘው ፓራግራፍ ላይ "አስቦ የገደለ እንደሆነ" በሚል ተተክቷል፡፡ የቃላቱና የአቀማመጡ ለውጥ አንቀጹን በይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) የነበረው አገላለጽ ተቃንቷል፤ አጣቃሽ ቁጥሮችም በየቦታቸው እንዲገቡ ተደርጓል::

ንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) ላይ ስብሰባ የሚለው (የእንግሊዝኛው ቅጂ እንደሚያሳየው) የወንበዴ ቡድን ለማለት ተፈልጎ ስለሆነ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን በሚል ተተክቷል::

በተጨማሪም በንዑስ ቁጥር አንድ በፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ላይ የቃላት አቀማመጥ ለውጥና ማስተካከያ ተደርጐበት፣ በይበልጥ ግልጽ ነው ተብሎ በሚታመንበት አነጋገር ተቀርጿል::

የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በእንግሊዝኛው ~~የፈረንሳይኛና የእንግሊዝኛ~~ ቅጅ መሰረት ግድያ የፈፀመ ሰው የሞት ቅጣት የሚፈረድበት አስቀድሞ ለፈፀመው ወንጀል የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደበት ወንጀለኛ ሁሉ ሳይሆን የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈፀም ላይ እያለ ከባድ ግድያ የፈፀመ ወንጀለኛ ብቻ መሆኑን ያሣያል:: የዚህ ዓይነቱ ወንጀለኛ በሞት እንዳይቀጣ የሚያደርግ ምንም ማቅለያ ምክንያት የሌለው በመሆኑ ምንጊዜም ቢሆን የሞት ቅጣት ሊፈረድበት ይገባል:: የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ቢፈረድበትም ቅጣቱን በመፈፀም ላይ ያልሆነ ወንጀለኛ ግን ሰው በሚገድልበት ጊዜ ፣ የዕድሜ ልክ እስራት በመፈጸም ላይ የሚገኘውን ወንጀለኛ ያህል አደገኛ ነው የማይባልበት ጊዜ ሊኖር ይችላል:: ሁኔታው እየታየ የሞት ቅጣት ወይም የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊፈረድበት ይችላል::

ለምሳሌ ጥፋተኛው በመጀመሪያ ከተፈረደበት የዕድሜ ልክ እስራት ውስጥ ምንም ሳይቀጣ ይቅርታ ወይም ምህረት ተደርጎለት ይሆናል፤ ወይም የዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደበት በሌለበት ሊሆን ይችላል:: የዚህ ዓይነቱ ጥፋተኛ ከባድ ግድያ ቢፈፅም፣ የዕድሜ ልክ እስራት እየፈጸመ ባለበት ጊዜ ከባድ ግድያ የሚፈጽመውን ጥፋተኛ ያህል ቅጣቱ ሳይከብድበት ይችላል፤ ምክንያቱም ቅጣት ስላልደረሰበትና ከቅጣት ያገኘው ትምህርት ስለሌለ ነው::

በቀድሞው ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በአማርኛው ትርጉም መሰረት ~~ጭን~~ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ከተፈረደበት በኋላ ማናቸውንም ዓይነት የሰው ግድያ የፈጸመ ሰው ሞት እንደሚፈረድበት ተደርጐ ተደንግጓል:: ይህ ግን ስህተት ነው፤ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው የሞት ቅጣት የሚፈረድበት ሰው የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈፀም ላይ እያለ በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የተመለከተውን ከባድ ግድያ ብቻ ሲፈጽም እንጂ ከዚህ ውጭ አስቦም ይሁን በቸልተኝነት ወይም በሕጋዊ መከላከል በሚገድልበት ጊዜ መሆን የለበትም:: ስለዚህም ንዑስ ቁጥር ሁለት በዚህ መልክ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

## አንቀጽ ፭፻፵ ተራ የሆነ የሰው ግድያ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ተራ የሆነ አገዳደል፤ ግድያ" ይል ነበር ሆኖም የአንቀጽ ፭፻፴፱ ስያሜን በሚመለከት በተሰጠው አስተያየት መሰረት "ተራ የሆነ የሰው ግድያ" ተብሎ ተስተካክሏል:: "ተራ" የሚለው ቃል የግድያውን ቀላልነት የሚያሳይ ሳይሆን በከባድ ግድያና በቀላል ግድያ መካከል የሚገኘውን የግድያ አይነት የሚያሳይ ነው::

www.abyssinialaw.com

ይዘቱን በሚመለከት፣ በቀድሞው ድንጋጌ ላይ፣ አድራጊው ግድያውን የሚፈጽመው "አስቦ" ወይም "በቸልተኝነት" መሆኑ አልተገለፀም ነበር:: ሆኖም በቸልተኝነት ሰውን ስለመግደል በአንቀጽ ፭፻፴፱ ላይ ስለተደነገገና በዚህ አንቀጽ ላይ ግድያው የሚፈፀመው ታስቦ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ "አስቦ" የሚል ቃል እንዲገባ ተደርጓል::

ከዚህም ሌላ ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ በሚያደርግ መልኩ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፭፻፵፩ <u>ቀላል የሆነ የሰው ግድያ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፩ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የድንጋጌው ስያሜ "የመግደልን ቅጣት ስለማቅለል" ይል ነበር:: ነገር ግን የድንጋጌው ስያሜ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት "Extenuated Homicide" የሚለውን ሀረግ በመከተል "ቀላል የሆነ የሰው ግድያ" ተብሏል::

የድንጋጌው የፊደል ተራ (ሀ) አነጋገር "ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ሳይሆን ወይም ያስፈላጊነት ግዴታ በመኖሪያ ቤቱ ወይም ባጥሩ ግቢ ባሉ ቤቶች በኃይል ወይም በተንኮል የገባውን ሰው ለማስወገድ ሲል የገደለ እንደሆነ" የሚል ሲሆን አነጋገሩ ግልጽ እንዳልሆነና መሻሻል እንደሚያስፈልገው፣ ዶ/ር ፊሊፕ ግራቨን ከቀድሞ ሕግ ከቁጥር ፸፰ እና ፸፬ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ በታወቀው መጽሐፋቸው ላይ የሰጡት አስተያየት የሚደገፍ ነው::

በፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የአማርኛው ቅጂ ላይ "ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ሳይሆን ወይም ያስፈላጊነት ግዴታ ሳይኖረው" ለሚለው ሀረግ የእንግሊዘኛው ቅጂ " there being no true state of necessity or legitimate self-defence" በሚል አገላለጽ የተቀመጠ ሲሆን፣ አባባሉ በአማርኛ ሲተረጎም "እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም አልሞት ባይ ተጋዳይነት" ማለቱ ነው:: "እውነተኛ /true/ የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው ላይ ገብቶ በአማርኛው ቅጂ ላይ ሳይገባ መቅረቱ በመጠኑም ቢሆን የትርጉም ችግር ማስከተሉ አይቀርም::

በተጨማሪም ከላይ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ከተመለከተው ሀረግ ጋር የቁጥር ፸፭ እና የቁጥር ፸፰ ድንጋጌዎች መጠቀሳቸው በአተረጓጎም ላይ ሌላ ችግር የሚያስከትል ነው:: እነዚህ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ሁኔታም ሆነ ህጋዊ መከላከል በወንጀል የማያስቀጣባቸውን መስፈርት የሚያስቀምጡ ሲሆን ሰውን መግደል በቀላሉ የሚያስቀጣባቸው ሁኔታዎች በተዘረዘሩበት ድንጋጌ ውስጥ መካተታቸው፣ ድንጋጌው ግልጽነት እንዳይኖረው ያደርጋል:: ያም ሆነ ይህ በአማርኛውና በእንግሊዝኛው ትርጉም ላይ መጠነኛ ልዩነት ያለውና የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያለቦታቸው የገቡ ቢሆንም፣ ከአንድ ትክክለኛ (Logical) ትርጉም ላይ መድረስ ይቻላል:: የድንጋጌው የፊደል ተራ (ሀ) አነጋገር ሰውን መግደል በቀላሉ የሚያስቀጣበትን ሁኔታ የሚዘረዝር ከሆነና፣ በውስጡ የቁጥራቸው የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አስገዳጅ ሁኔታና የሕግ መከላከል ፈጽሞ የሚያስቀጡበትን መስፈርት የሚደነግጉ ከሆነ፣ ግድያው የተፈጸመው የአስገዳጅ ሁኔታ ወሰንን በማለፍ ወይም ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ግድያው በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት ቢፈጸም ኖሮ እንደማያስቀጣ የታወቀ ነው::

www.abyssinialaw.com

ከዚህም በላይ በድንጋጌው የፊደል ተራ (ሀ) አገላለጽ መሠረት አስገዳጅ ሁኔታን ወይም ህጋዊ መከላከልን ከመጠን አሳልፏል ተብሎ ተከሳሽ የሚጠየቀው ወደ መኖሪያ ቤቱ ወይም በአጥር ግቢ ውስጥ ወደሚገኙ ቤቶች በኃይል ወይም በተንኮል የገባውን ሰው ለማስወገድ በሚጣጣርበት ጊዜ ብቻ ነው:: ይህ ሁኔታ ግን ሁለት ችግሮች ይታዩበታል:: በአንድ በኩል በተጠቀሰው ሁኔታ ሰውን መግደል በይበልጥ ከህጋዊ መከላከል ጋር እንጂ ከአስገዳጅ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ያስቸግራል:: በመሆኑም ህጋዊ መከላከልን የሚመለከተው ድንጋጌ ብቻ መጥቀሱ በቂ ነበር:: በሌላ በኩል ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የግድያው ቅጣት መቅለል የሚገባው፣ ወደመኖሪያ ቤቱ ወይም ወደ አጥር ግቢው በኃይል ወይም በተንኮል የገባውን ሰው በሚያስወግድበት ጊዜ ብቻ መሆኑ ትክክል መስሎ አይታይም:: ከተባለው ሁኔታ ውጭ በራሱ ወይም በሌላ ሰው ህይወት ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት ሲመልስ ወይም በሌላ ሁኔታ መብቱን ሲያስከብር ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ ሰውን ሲገልም ድንጋጌው ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል::

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስቀረት፣ ግድያው የተፈጸመው ያስገዳጅ ሁኔታን ወይም የአልሞት ባይ ተጋዳይነትን መስፈርት በመጣስ ወይም በማለፍ እስከ ሆነ ድረስ ግድያው የተፈጸመው በማናቸውም ቦታ፣ ጊዜ ወይም ሁኔታ ቢሆንም አንቀጹ አጠቃላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረጉ ትክክል መሆኑ ስለታመነበት የማያስፈልጉ ሀረጎች ተሰርዘውና አሳቡ ተቃንቶ የፊደል (ሀ) ድንጋጌ ተረቋል::

የቀድሞው የቁጥር ፭፻፳፬ የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ግልጽነት በሌለው ሁኔታ የተጻፈ ሲሆን በእንግሊዘኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ መሠረት አገላለጹ ተቃንቶና ተስተካክሎ በፊደል ተራ (ለ) ስር ገብቷል:: "የገደለ እንደሆነ" የሚለው ሀረግ በቀድሞ ህግ መሠረት የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ አካል ሆኖ የገባ ሲሆን፣ ሀረጉ ተሰርዞ በአዲስ ፓራግራፍ "አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ" ተብሎ ተቀርጿል::

በዚህ መልክ መቀመጡ ሀረጉ አግባብነት ያለው ለፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን በፊደል ተራ (ሀ) ለተመለከተው ጭምር መሆኑን በግልጽ ያሳያል::

አንቀጽ ፭፻፵፪ <u>ሌላ ሰው ራሱን እንዲገድል ማነሳሳትና መርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፪ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ "ራሱን እንዲገድል ስለማነሳሳትና ስለ ማገዝ" የሚል ሲሆን "ሌላ ሰው ራሱን እንዲገድል ማነሳሳትና መርዳት" በሚል ተተክቷል::

በቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ ወንጀል አድራጊው የሚቀጣው ወንጀሉን የፈፀመው "ራስን ብቻ በመውደድ ወይም በወራዳነት መንፈስ" ሲሆን ብቻ መሆኑ ተደንግጓል:: ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን አንድ ሰው ራሱን እንዲገድል ማንኛውም ሰው እንዲያነሳሳ ወይም እንዲረዳ ሊፈቀድለት ስለማይገባ በጥቅስ ምልክት ያለው ሐረግ እንዲሠረዝ ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ አነሳሹ ወይም ረጂው የሚቀጣው የተነሳሳው ሰው ራሱን ሲገድል ብቻ ነው:: ሆኖም በንዑስ ቁጥር አንድ በተደነገገው ዓይነት ራስን የመግደል ሙከራው ሲፈፀምም አነሳሹ ወይም ረዳቱ እንዲቀጣ ተደርጎ ተረቅቋል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፭፻፵፫ <u>በቸልተኝነት ሰውን መግደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፫ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የድንጋጌው ስያሜ "በቸልተኝነት ስለመግደል" ይል የነበረው "በቸልተኝነት ሰውን መግደል" በሚል ተተክቷል::

ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው የመኪና አሽከርካሪዎች በቸልተኛነት ሰውን በሚገድሉበት ጊዜ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይቀጣሉ:: የመኪና አሽከርካሪ ለሰው ሕይወት ከባድ የሆነ ጥንቃቄ ወስዶ ለማሽከርከር አለበት:: ስለዚህ እንደዚህ ያለው ወንጀል በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር እንዳይወድቅ ለማድረግ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚያገለግለው የወንጀሉ አፈጻጸም በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ በማይወድቅበት ጊዜ መሆኑን በመግለጽ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ውስጥ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ" የሚል ሀረግ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ተጨምሮአል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ አስፈላጊ ያልሆነ ሐረግን በመሰረዝ፣ እንዲሁም የቀላል እስራቱንና የመቀጮውን መነሻ ከፍ በማድረግ ተረቅቋል:: በመጀመሪያ ጊዜ ለተፈጸመ ተራ የቸልተኛነት ግድያ የቀላል እስራቱን መነሻ ወደ ስድስት ወር የመቀጮውንም ወለል ወደ ሁለት ሺህ ብር ከፍ አድርጎ መደንገጉ፣ ለወንጀሉ ተመጣጣኝ ነው ተብሎ በመታመኑ በዚህ መልክ ተቀርጿል:: የሰው ህይወት መጥፋቱ እየታወቀ የቀላል እስራቱ መነሻ አስር ቀን፣ የመቀጮው ደግሞ አንድ ብር ተብሎ በቀድሞው ህግ የተደነገገው ፈጽሞ ሲደገፍ አይገባም::

አንቀጽ ፭፻፳፮ (፪) የሚያስቀጣው ሙያው ሆኖ ጥንቃቄ መውሰድ ሲገባው በከባድ ቸልተኛነት ሰውን የገደለ እንደሆነ ነው:: ለዚህ ዓይነቱ ወንጀል የቅጣት መነሻው ከፍ ቢል ሰውን ተጠንቅቆ የሙያ ግዴታውን ይወጣዋል ተብሎ ስለሚገመት ቅጣቱ "ከአንድ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ቀላል እስራት እና ከሰስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ የሚደርስ መቀጮ ይሆናል" በሚል ሀረግ ተቀይሯል::

ንዑስ አንቀጽ (፫) አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሲሆን የገባውም ብዙ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ጉዳት ስለሚደርስባቸው ነው:: ለምሳሌ፤ የመኪና አደጋ ብዙ ሰዎችን ያለአግባብ በመጫንና በፍጥነት በማሽከርከር የሚመጣ ስለሆነ የዚህ ዓይነቱን አደጋ ለመቀነስ የወንጀል ድርጊቱን ዘርዘር አድርጎ መደንገግና ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በተጨማሪም የሚያሰክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰድ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል እንዲቻል፣ይኸው ተዘርዝሮ ለማስተማር በሚረዳ መልኩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፶፱ (፩) እና (፪) መንፈስ ድንጋጌው የተረቀቀ ነው:: ቅጣቱም ከንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከፍ ያለ ሆኖ" ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና ከአስር ሺህ እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ሆኖ ተደንግጓል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፵፬ <u>ህፃንን መግደል*</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

በንዑስ ቁጥር (፩) ሁለተኛ ፓራግራፍ ውስጥ ቅጣቱ "ከስድስት ወር በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ትቀጣለች" የሚለው ህረግ የወንጀሉ ፈጻሚ እናት ሆና በትግርና በትክክል ማሰብ በማትችልበት ሁኔታ ላይ ስትሆን ወንጀሉን የምትፈጽም ስለሆነ መነሻው ከስድስት ወር ማነስ አለበት፡፡ ስለዚህ መነሻ ቅጣቱ ተሰርዞ በቀላል እስራት ትቀጣለች በሚለው ተለውጧል፡፡

በንዑስ ቁጥር ሶስት ላይ "ህፃኑን ለገደሉት ወይም ለመገደሉ አስተባባሪዎች ወይም ግብረ አበሮች ለሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ..." የሚለው ሀረግ ተሻሽሎ "በዚህ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር (፩) በተመለከተው ወንጀል በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ተካፋይ የሆነ ሌላ ሰው ..." እንዲል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በላይ በሶስቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ አስፈላጊ የቃላት ማስተካከያና ለውጦች ተደርገውባቸው አንቀፁ ተረቅቋል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>በጽንስ ላይ የሚደረግ ወንጀል፤ ጽንስ ማስወረድ</u>

የቀድሞው ስያሜ "በጽንስ ሕይወት ላይ ስለሚደረግ ወንጀል" ይል የነበረ ሲሆን ጽንስ ህይወት የሚለውን ያጠቃለለ ስለሆነ ሕይወት የሚለው ቃል ተሰርዞአል፡፡

አንቀጽ ፭፻፵፭ <u>መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

መሠረቱ የሚለው መርህ በሚል ተቀይሯል፡፡ ቁጥር ፭፻፳፱ (፩) አስገዳጅ በሆኑ ምክንያቶች ይህን ድንጋጌ የሚያፈርስ ሌላ ሕግ ከሌለ በቀር የሚለው ሀረግ ከአንቀጽ ፭፻፵፮-፭፻፶፫ ውጪ ያሉ ሌሎች ህጎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚገልጽ ስለሚያስመስለው ተሰርዞ በምትኩ "በአንቀጽ ፭፻፶፩ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ" በሚለው ተቀይሯል፡፡

ንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ ግልጽ ሆኖ ለብቻው ንዑስ አንቀጽ ሆኖ መቀመጥ ያለበት ስለሆነ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል፡፡ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለትም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፭፻፳፱ (፩) ሶስተኛው ፓራግራፍ ባይኖርም በቸልተኛነት የተፈጸመ ተግባር ሕጉ ያስቀጣል ብሎ ካልደነገገ በቀር የሚያስቀጣ ስላልሆነ ተሰርዞአል፡፡

* በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 544 ንዑስ አንቀጽ 1 "ለመውለድ ምጥ በተያዘች" የሚለው ቃል "ለመውለድ በምጥ የተያዘች" ተብሎ ይነበብ፡፡

www.abyssinialaw.com


የቀድሞው የቁጥር ፭፻፳፰ (፪) ድንጋጌ ወደ ደንብ መተላለፍ ድንጋጌ የሚመራ ሲሆን ከዚህ አንቀጽ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፭፻፵፭ <u>አንዲት ሴት በራሷ ላይ የምትፈጽመው የማስወረድ ድርጊት</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፭፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ወንጀሉ የሚያስቀጣው ሆን ብላ (with intention) የፈጸመችውን ድርጊት መሆን ስላለበት "አስባ" የሚል ቃል ተጨምሯል:: የቅጣቱ መነሻና ጣራም ዝቅ ተደርጓል::

ንዑስ ቁጥር (፪) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል:: ቅጣቱንም በተመለከተ መነሻውና ጣራው ዝቅ እንዲል ተደርጓል::

አንቀጽ ፭፻፵፮ <u>በሌላ ሰው የሚፈጸም የማስወረድ ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፮ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው ላይ "ሶስተኛ ሰው" የሚለው ወንጀሉን ፈጻሚው ከእናትየው የተለየ ሰው መሆኑን ለመግለጽ ተፈልጎ ስለሆነ በሌላ ሰው ቢባል ስያሜው ይበልጥ ግልጽ ስለሚሆን ሶስተኛው ሰው የሚለው ተሰርዞ በሌላ ሰው በሚል ተቀይሯል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ግልጽ እንዲሆኑ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሆነው ገብተዋል:: የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቅጣትም ዝቅ ተደርጎ ተቀርጿል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በሕግ ከተፈቀደው ውጪ ጽንሷ እንዲወርድ ፈቃድ የሰጠች ሴት የምትቀጣበት ድንጋጌ ነው::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፵፯ <u>ከባድ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፯ ሆኖ ገብቷል::

የማስወረድ ድርጊት የተደረገው ለገንዘብ ወይም የሞያ ስራ በማድረግ ከሆነ ቅጣቱ ከፍ እንደሚል የሚደነግግ አንቀጽ ስለሆነ ስያሜው ይህንን በሚገልጽ መልኩ ከባድ ሁኔታዎች በሚል ተቀይሯል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች የቃላት ማስተካከያና የሃሳብ መቃናት ከተደረገባቸው በኋላ የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፩)፣ የንዑስ ቁጥር (፪) ደግሞ በንዑስ አንቀጽ (፫) ስር እንዲገባ ተደርጓል:: አዲስ የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ የገባ ሲሆን በቂ የህክምና ሞያ ሳይኖረው ጽንስ የሚያስወርደውን ሰው የሚያስቀጣ ነው::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፵፱ <u>እርግዝና በሌላት ሴት ላይ የማስወረድ ድርጊት ለመፈጸም መሞከር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፶ <u>ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ መግቢያ ላይ ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን የሚደነግገውን አንቀጽ ፸፱ን መጥቀሱ ባለማስፈለጉ ሐረጉ የተሰረዘ ሲሆን ጥልቅ የሆና የሚቆይ የኑሮ ችግር ሲያጋጥም በአንቀጽ ፻፹ መሠረት ፍርድ ቤት ቅጣት ማቅለል ይችላል ከማለት ይልቅ ማቅለል እንዳለበት ስለታመነ በዚሁ መልክ ተረቋል::

ነገር ግን በመደፈር ወይም ከቅርብ ዘመድ በተደረገ የግብረ ስጋ ግንኙነት የተረገዘን ጽንስ ማስወረድ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሳይሆን በሕግ ከተፈቀዱት ሁኔታዎች መካተት ስለአለበት ከዚህ ድንገጋጌ ተሰርዟል፤ ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው::

በመደፈር የተጸነሰ ጽንስ ከእናትየዋ ፍላጎት ውጪ የመጣ ስለሆነ ጽንሱን በግድ ያዝ ማለት ከተፈጸመባት ወንጀል (መደፈር) ባሻገር ሌላ ችግር ውስጥ ማስገባት ስለሆነ አንዲት ሴት በመደፈር ከጸነሰች ጽንሱን ማቋረጥ መቻል ይኖርባታል::

በዘመድ መካከል በተደረገ የግብረስጋ ግንኙነት ምክንያት የተገኘ ጽንስም ሳይፈለግ የመጣ ጽንስ ሲሆን ልጁም ቢያድግ የህሊና መረበሽ ሊመጣባት ይችላል ስለዚህ እነዚህ ምክንያቶች ከዚህ ተሰርዘው በአንቀጽ ፭፻፶፩ እንዲገቡ ተደርጓል::

አንቀጽ ፭፻፶፩ <u>ጽንስን ማቋረጥ በሕግ የተፈቀደባቸው ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፬ (፩) ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል:: ሆኖም የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ፪፣፫ እና ፬ የጽንስ ማስወረዱ ተግባር ስለሚካሄድበት ውስብስብ ሥነ-ሥርዓት የሚገልጹ ሲሆን አስፈላጊ ባለመሆናቸው እንዲሰረዙ ተደርጓል:: የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፮ ድንጋጌ ጽንስ ማስወረድ የሚቻልበትን ሁኔታ የሚደነግግ እንደመሆኑ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ጽንስ ማስወረድ የተፈቀደባቸውን አራት ሁኔታዎች የሚያስቀምጥ ሲሆን፤ ይኸውም:-

ሀ/ "በመደፈር ወይም በዘመድ መካከል በተደረገ የግብረስጋ ግንኙነት ምክንያት ጽንሱ የተገኘ ሲሆን፤

ለ/ "የእርግዝናው መቀጠል በእናቲቱም ሆነ በጽንሱ ህይወት ወይም በእናቲቱ ጤንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ሲሆን ወይም የልጁ መወለድ በእናቲቱ ጤንነት ወይም ሕይወት ላይ አደጋ የሚያመጣ ሲሆን፤

www.abyssinialaw.com

ሐ/ "ጽንሱ ሊድን የማይችል ከባድ የአካል ጉድለት ያለው (ዲፎርምድ) ሲሆን፤

መ/ አንዲት እርጉዝ ሴት የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለባት በመሆኗ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰች በመሆኗ የሚወለደውን ህጻን ለማሳደግ የህሊናም ሆነ የአካል ዝግጅት የሌላት ሲሆን ነው"::

ጽንስን ማቋረጥ የሚቻለው በህክምና ብቻ ሳይሆን በመደፈር ወይም በዘመድ መካከል በተደረገ የግብረስጋ ግንኙነት ምክንያት የተገኘ ጽንስ ከሆነ ጭምር እንዲሆን በማለት አንቀጹ ተሻሽሏል::

እንዲሁም ብቃት በሌላቸው የመንደር አስወራጆች ውርጃ እንዳይፈጸም በታወቀ ህክምና በሚል ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፭፻፶፪ <u>ጽንስ የሚቋረጥበት ስነ-ስርዓትና ስነ-ስርዓቱን መጣስ የሚያስከትለው ቅጣት</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜ አዲስ ሲሆን በአንቀጽ ፭፻፶፩ መሠረት ጽንስ ከመቋረጡ በፊት ምን ዓይነት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸውና ስለነዚህ ጉዳዮች የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ የሚጥስ ሰው እንደሚቀጣ የሚደነግግ ነው:: ይኸም፣ በቀድሞው ድንጋጌ በቁጥር ፭፻፴፬ (፪) ፣ (፫) እና (፬) እንዲሁም በቁጥር ፭፻፴፭ የተደነገገውን ውስብስብና ከባድ ስነ-ስርዓት የሚተካ ሲሆን በመደፈር ወይም ከቅርብ ዘመድ ጋር በተደረገ የግብረስጋ ግንኙነት የተገኘን ጽንስ የምታስወርድ ሴት ስለደረሰባት ሁኔታ ከመግለጽ በቀር ፍርድ ቤት እንድትቀርብ እና ማስረጃ እንድታሰማ የማትደረግ መሆኑን ይገልጻል::

<u>የቀድሞው ህግ የቁጥር ፭፻፴፮ መሰረዝ</u>

ድንጋጌው አንቀጽ ፭፻፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ስለገባ ከዚህ ተሰርዟል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በሰው አካልና በሰው ጤና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፭፻፶፫ <u>መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "መሠረት" ይል የነበረው፣ "መርህ" በሚል ቃል ተተክቷል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) ውስጥ "ነገር" የሚለው ቃል የእንግሊዝኛውን ቃል 'means' የሚለውን በትክክል ስለማይገልጸው ነገር ከሚለው ቀጥሎ ወይም ዘዴ የሚል ሀረግ ተጨምሮበታል::

የንዑስ ቁጥር (፬) የሁለተኛ ፓራግራፍ ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር "ይኸውም የጥፋቶቹ ምክንያቶች ውጤትና አጥፊው ያደረገው የጉዳት ሥራ ግንኙነት የተረጋገጠ እንደሆነ ነው:: (ቁጥር ፳፬)" ይላል:: ሆኖም ሁለተኛ ፓራግራፍ የሚተነትነው የጉዳቶቹን አይነት

www.abyssinialaw.com


ስለሆነ እና ወንጀሉ የተገለፀው በንዑስ ቁጥር (፭) ስለሆነ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ተሰርዞ በንዑስ ቁጥር (፩) በመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ ተጠቃሎ ተስተካክሏል::

የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌም በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::

አንቀጽ ፭፻፶፫ <u>አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚደረግ የልዩ አዋቂ ወይም ባለሙያ ምርመራ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፩ ድንጋጌ ስያሜውም ሆነ ይዘቱ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፬ ሆኖ ገብቷል::

በምዕራፉ መጀመሪያ ከሚገኘው "መርህ" በሚል ስያሜ ከተመለከተው አንቀጽ ቀጥሎ ድንጋጌው እንዲገባ የተደረገበት ምክንያት፣ በምዕራፉ ስር ላሉት የጉዳት ዓይነቶች ሁሉ አግባብነት ያለው ጠቅላላ ድንጋጌ በመሆኑ ነው:: የቀድሞ አቀማመጡ ታስቦ ለተደረገ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት፣ እንዲሁም መጠነኛ ጉዳት ለማድረስ ታስቦ በቸልተኛነት ለደረሰ ከባድ ጉዳት (የቀድሞው ቁጥር ፭፻፴፰-፭፻፴፱) ብቻ ተፈጻሚነት ያለው መስሎ ይታያል:: ነገር ግን በቀድሞ ሕግ በቁጥር ፭፻፵፪-፭፻፵፩ ድረስ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኛነት ወንጀሎች ሲፈጸሙ የደረሰው ጉዳት ከባድ ወይም ቀላል መሆናቸው ጥርጥር ሊያስከትል ይችላል:: በዚህ ጊዜ የሐኪም ምርመራ እንዲደረግ ፍርድ ቤቱ ማዘዙ ግድ ይሆናል:: ስለዚህ ሁሉንም አንቀጾች በሚያመለክት መልኩ የቦታ የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፶፭ <u>ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፭ ሆኖ ገብቷል::

በተለይ እጅግ ከባድ ጉዳት በማድረስ ወንጀሉ የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከፍ ያለ መሆን ስላለበት ቅጣቱም ከአሥር ዓመት ወደ አስራ አምስት ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል:: ከዚህም ሌላ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::

አንቀጽ ፭፻፶፮ <u>ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፮ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን ቅጣቱን በሚመለከት የቀላል እስራቱ ጣራ ከሶስት ዓመት ወደ አንድ ዓመት ዝቅ እንዲል ተደርጐ ተረቅቋል፤ ምክንያቱም ለዚህ ዓይነቱ ወንጀል ከአንድ ዓመት ቀላል እስራት በላይ መቅጣቱ ተመጣጣኝ አይደለም ተብሎ ስለታመነበትና በአንቀጽ ፭፻፶፭ ታስቦ ለተደረገ ከባድ የአካል ጉዳት ከተደነገገው የአንድ ዓመት ቀላል እስራት መነሻ ቅጣት ፈጽሞ መብለጥ ስለማይገባው ነው::

የንዑስ ቁጥር (፪) መግቢያ ማሻሻያ ተደርጐበታል:: "ውጤቱ ከባድ ባይሆንም እንኳ" የሚለው ሀረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል:: "ክሱም በደንበኛ ባለሥልጣን የሚቀርበው" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ በምትኩ ከተጠቀሰው የስድስት ወር ቀላል እሥራት መነሻ ቅጣት በተጨማሪ የቅጣቱ ጣራ ሶስት አመት መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል::

www.abyssinialaw.com

በፊደል ተራ (ሐ) ላይ "ድውይ" የሚለው ቃል የሰውን ስሜት የሚጎዳ በመሆኑና የሚጨምረው ነገር ባለመኖሩ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በላይ በድንጋጌው ላይ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቅቋል፡፡

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፪ ድንጋጌ ከቁጥር ፭፻፴፱ ቀጥሎ እንዲገባ መደረጉ</u>

ቀላል ግድያ /አንቀጽ ፭፻፵፪/ ከተራ ግድያ /አንቀጽ ፭፻፵፩/ ቀጥሎ እንደገባው ሁሉ የአካል ጉዳትንም በሚመለከት "የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች" የቀድሞ ሕግ ቁጥር ፭፻፵፪ (አንቀጽ ፭፻፶፯) ባለበት ቦታ መሆኑ ቀርቶ ከተራ የአካል ጉዳት የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፭፻፴፱ (አንቀጽ ፭፻፶፮) ቀጥሎ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፭፻፶፯ <u>የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

ማንም ሰው አስቦ ይል የነበረውን አስቦ የሰራው ምን እንደሆነ በግልጽ እንዲቀመጥ በማለት "ማንም ሰው በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰው" በሚል ተሻሽሏል፡፡

የድንጋጌው የፊደል ተራ (ሀ) አነጋገር የአንቀጽ ፭፻፵፩ (ሀ) አገላለጽ በተስተካከለበት ዓይነት ተስተካክሏል፡፡ ጥፋተኛው የአካል ጉዳት የሚያደርሰው ወደ አጥር ግቢው ወይም ወደ መኖሪያ ቤቱ በኃይል ወይም በተንኮል የገባውን ሰው ለማስወገድ ሲል ብቻ ሳይሆን፣ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በማለፍ ወይም ህጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ በማናቸውም መንገድ ወይም ሁኔታ ድርጊቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ሁሉ ሊሆን ይገባል፡፡

የድንጋጌው የፊደል ተራ (ለ) አነጋገር ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የመቀጮውን ጣራ አለመጥቀሱ የፍርድ ቤቱን ቅጣት ገደብ የለሽ ሊያደርግ ስለሚችል ይህንን ለማስቀረት ጣራው ወደ ብር አራት ሺህ ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፭፻፶፰ <u>ከጥፋተኛው አሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎ አሳቡ የተቃና ሲሆን የሶስት ዓመት ጣራ ቅጣት ቢደነገግም መነሻ ቅጣቱ አስር ቀን መሆኑ ቀርቶ በስድስት ወር ቀላል እሥራት ተተክቷል፡፡ ይህም የሆነው፣ የአድራጊው ጥፋት ሁለት አይነት በመሆኑ ነው፡፡ በአንድ በኩል ቀላል የአካል ጉዳት የማድረስ አሳብ ያለው ሲሆን በሌላ በኩል ድርጊቱ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል መገንዘብ ወይም መገመት እየቻለ በተበዳይ ላይ ከባድ ጉዳት በማስከተሉ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ጉዳት መነሻ ቅጣቱን የአሥር ቀን ቀላል እስራት ማድረጉ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

አንቀጹ ከላይ በተገለጸው መልኩ ተስተካክሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፶፱ <u>በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶፱ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ የተመለከተው ቅጣት የጸና ሲሆን የጉዳቱን መጠን በሚመለከት ግን ንዑስ ቁጥር አንድ ቀላል ጉዳትን ብቻ እንዲያካትት ተደርጎ ተረቅቋል::

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር (፪) ማሟያ ነጥቦች (Elements) ሆነ በቅጣቱ ላይ ለውጥ ተደርጓል:: በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር መቀመጥ ያለበት የጉዳት መጠን ከባድ መሆን እንዳለበት ማለት በአንቀጽ ፭፻፶፭ የተደነገገው ጉዳት ዓይነት እንዲሆን በግልጽ ተመለክቷል:: ጉዳት አድራሹም የተለየ ኃላፊነት ያለው ሰው መሆኑን በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ሐኪም እና አሽከርካሪ በምሳሌነት እንዲጠቀሱ ተደርጓል:: ቅጣቱንም በሚመለከት መነሻው ከአስር ቀን ወደ ስድስት ወር ቀላል እሥራት፣ ጣራው ከአንድ ዓመት ወደ ሶስት ዓመት ቀላል እሥራት እንዲያድግ የተደረገ ሲሆን መቀጮውን በተመለከተ መነሻው ከብር ሶስት መቶ ወደ ብር አንድ ሺህ ከፍ ብሏል::

የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) በይበልጥ ግለጽ እንዲሆን እና አሳቡ እንዲቃና ተደርጓል:: "ክሱ የሚቀርበው" የሚለው ሐረግ "ድርጊቱ የሚያስቀጣው" በሚል ተተክቷል፤ ምክንያቱም ጉዳዩ ክስ በማቅረብ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን እስከ ማስቀጣትም የሚያደርስ በመሆኑ ነው:: "ጉዳቱ ቀላል ወይም ከባድ ከሆነ" ማለቱ ብቻ ስለማይበቃ የጉዳቱ ከባድነት በአንቀጽ ፭፻፶፭፣ የጉዳቱ ቀላልነት ደግሞ በአንቀጽ ፭፻፶፮ በተገለፀው ዓይነት መሆን እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል:: እንዲሁም "በተጐጂው በኩል" የሚለው ሐረግ "በግል አቤቱታ አቅራቢነት" በሚል ተለውጧል:: "ክሱ የሚቀርበው... በዓቃቤ ሕግ በኩል ነው" የሚለውም አነጋገር ስህተት በመሆኑ "ድርጊቱ የሚያስቀጣው..በወንጀል ክስ አቅራቢነት ነው" በሚል ተተክቷል:: ጉዳቱ ቀላል ይሁንም ከባድ ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርበው ዓቃቤ ሕግ ነው:: ጉዳቱ ከባድ ከሆነ ግን ተጐጂው አቤቱታ ቢያቀርብም ባያቀርብም ማንኛውም ሰው ለፖሊስ ባቀረበው ማመልከቻ ወይም ክስ መሰረት ጥፋተኛው በፍርድ ቤት ተከስሶ ሊቀጣ ይችላል:: በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚለው ሀረግ የገባውም በዚሁ ምክንያት ነው:: ከዚህም ሌላ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቋል::

አንቀጽ ፭፻፷ <u>የእጅ እልፊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፷ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የመቀጮው መጠን ያልተጠቀሰ ሲሆን ጣራው ከብር ሦስት መቶ እንዳይበልጥ አድርጎ በግልጽ መደንገጉ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት በዚህ መልክ ንዑስ ቁጥር (፩) ተረቅቋል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት እንደሰንበር እና እንደደም መቋጠር የመሳሰሉት ጉዳቶች እንደአካል ጉዳት ወይም እንደጤና ጉድለት አይቆጠሩም የሚል ሲሆን ትርጉሙ ወይም ማብራሪያው በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የተመለከተውን የአካል ጉዳት ወይም የጤንነት ጉድለት በመሆኑ ዓረፍተ-ነገሩ ከንዑስ ቁጥር (፪) ወጥቶ የንዑስ ቁጥር (፩) የመጨረሻው ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ተረቅቋል::

ከዚህም በላይ በንዑስ ቁጥር (፫) እና በመጀመሪያዎቹ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው አንቀጹ ተሻሽሏል::

## ምዕራፍ ሶስት
## በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሕይወት፣ በአካል እና በጤና ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

በቀድሞው ሕግ ትኩረት ያልተደረገባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተዘዋዋሪ ሁኔታ ለማስወገድ የሚያስችሉ ተበታትነው የሚገኙ የተወሰኑ ድንጋጌዎች የነበሩ ቢሁንም በሕብረተሰቡ ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ ሊያስጨብጡ ባለመቻላቸው የተፈለገውን ውጤት አላስገኙም:: ይህ ሁኔታ ባለበት እንዲቀጥል ማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ በተለያየ ሁኔታ ከሌሎች የወንጀል ድርጊቶች ጋር ተቀላቅለው እንዲቀመጡ ከማድረግ ተለይተው በግልጽ እንዲቀመጡና ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ በአንድ አካባቢ እንዲሰባሰቡ ቢደረግ ለአፈጻጸም አመቺ ሁኔታን ይፈጥራሉ የተባሉትን የተወሰኑ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተሰባስበው በአንድ ምዕራፍ ሥር እንዲሆኑ ተደርጓል:: ይህ አካሄድ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለይቶ ለማወቅና ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል ተብሎ በመታመኑ ሲሆን የምዕራፉ ስያሜ "በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሕይወት፣ በአካልና በጤና ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች" እንዲል ተደርጓል::

### አንቀጽ ፭፻፷፩ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴት እና ሕጻናት ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ግልጽ በሆነ መልክ አልተደነገገም ነበር::

ይህ አንቀጽ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን፣ የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ፣ የእርጉዝ ሴትን ሆድ በማሸት፣ በመውለድ ላይ ያለችን ሴት አካል በማርገፍገፍ፣ የተወለደ ሕጻንን እትብት የተለያዩ ነገሮችን በመቀባት፣ ሕጻንን ፀሐይ እንዳይሞቅ በመከልከል ቅቤ እንዲውጥ በማድረግ፣ የሕጻንን እንጥል በመቁረጥ፣ ግግ በማውጣት የተጎጂው (የተጎጂዋ) ሕይወት ቢያልፍ ድርጊቱ እንደ ሌሎች በዝርዝር ያልተገለጹት ተመሳሳይነት ያላቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ቢኖሩ ጎጂነታቸው በሕክምና ሙያ የተረጋገጠ መሆኑ ከታወቀና ለሕይወት ሕልፈት የሚያበቁ ከሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት እንዲያስቀጡ ተደርጎ ተረቅቋል::

የእርጉዚቱ ሴት ወይም የህፃኑ ሕይወት ያለፈው በቸልተኛነት ከሆነ፣ በቸልተኛነት ሰው ስለመግደል የተመለከተው አንቀጽ ተፈጻሚ እንደሚሆን የሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ (፪) ገብቷል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፷፱ <u>በኀጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴት ወይም በሕፃን አካል ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ላይ በግልጽ አልተቀመጠም ነበር::

በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የእርጉዝ ሴትን ሆድ በማሸት፤ በመወለድ ላይ ያለችን ሴት አካል በማርገፍገፍ፤ አዲስ የሚወለድ ሕፃንን እትብት የተለያዩ ነገሮችን በመቀባት፤ ህፃን ልጅ ፀሐይ እንዳይሞቅ በመከልከል፤ ቅቤ እንዲውጥ በማድረግ፤ እንጥል በመቁረጥ ወይም ግግ በማውጣት በሴት ወይም በህፃን ላይ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት የሚያደርስ ማንም ሰው ቅጣት የሚጣልበት መሆኑን ያመለክታል:: ከተዘረዘሩት ጎጂ ባህሎች ሌላ ተመሳሳይነት ያላቸውና ጎጂነታቸው በሕክምና ሙያ የተረጋገጠ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ፈጻሚዎች ቢያጋጥሙ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተደንግጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ፣ "በአካል ወይም በአእምሮ ጤና ላይ ጉዳት የደረሰው በቸልተኛነት እንደሆነ ስለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለው የዚህ ህግ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል (አንቀጽ ፭፻፶፱)::" ተብሎ ተደንግጓል::

የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቸልተኛነት በማይኖርበት ጊዜ የሚያስቀጣ ሲሆን፣ ድርጊቱ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል መረዳት ወይም መገመት የሚገባው ሆኖ ድርጊቱን ፈጽሞ ጉዳት ያስከተለ ሰው በመደበኛው የቸልተኛነት አንቀጽ እንደሚቀጣ ንዑስ አንቀጽ (፪) ያመለክታል::

አንቀጽ ፭፻፷፫ <u>የፍርድ ቤት ልዩ አስተያየት</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ላይ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ነው::

የአንቀጹ ስያሜ "የፍርድ ቤት ልዩ አስተያየት" እንዲል የተደረገው ፍርድ ቤት መቀጮ ወይም ቀላል እስራት በመወሰን ፈንታ ሊከተለው የሚገባ አማራጭ የቅጣት ዓይነት ምን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት አንቀጽ በመሆኑ ነው:: ፍርድ ቤት በአንቀጽ ፭፻፷፩ ሆነ በአንቀጽ ፭፻፷፪ መሠረት በሚቀርቡለት ጉዳዮች ላይ ቅጣት በሚወስንበት ጊዜ የወንጀል አድራጊውን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኑሮ ልምድ ወይም የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ማገናዘብ እንዳለበት አንቀጹ ይደነግጋል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ልማዳዊ ድርጊቶችን የመፈጸም ጉዳይ ካለማወቅ፣ በትምህርት ካለመብሰል ወይም ከትውልድ ተያይዞ በመጣ ባህላዊ ልማድን በመከተል ብቻ የሚከናወን እንጂ ጉዳት የሚያመጣ መሆኑን በማገናዘብና በመረዳት ካለመሆኑ ባሻገር ጎጂው ባህል ይጠቅማል የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ በመያዝ እንደሚደረግ ስለሚገመት ነው:: የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ በትምህርት ወይም በኑሮ ሁኔታ መሻሻል ሊወገድ እንደሚችል በተግባር እየታየ በመሆኑ ጎጂ ባህሎችን የሚከተሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ንቃተ ህሊናቸው የሚዳብርበት ሁኔታ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጣና በልዩ ልዩ ጽሁፎች ማስተማሩ በቅድሚያ መመቻቸቱ ባይቀርም የዚህ ዓይነቱ ዕድል ያላጋጠመው ሰው ሊኖር ይችላል:: የዚህ ዓይነቱ ሰው በነዚህ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ድርጊቶች በሚፈጽምበት ጊዜ አድራጊው በመቀጮ ወይም በእስራት ከመቅጣት ይልቅ በማስጠንቀቂያ ቢታለፍ ትምህርት ይሆነዋል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ይህንኑ አማራጭ ፍርድ ቤት እንዲከተል ለማድረግ የሚያስችለው ድንጋጌ እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፭፻፷፬ <u>በትዳር ጓደኛ ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረስጋ ግንኙነት በሚኖር ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ</u>

ይህ ድንጋጌ በቀድሞው ሕግ ላይ በግልጽ ያልበነረ አዲስ ድንጋጌ ነው።

የአንቀጹ ስያሜ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችል ከእንግሊዝኛው "Domestic Violence" ከሚለው ጽንሰ አሳብ ጋር ይያያዛል። የድንጋጌው ይዘት በትዳር ጓደኝነት ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚኖሩ ሴቶች ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎችን ለመቅጣት ያስችላል። ይህ ድንጋጌ ባል ሚስቱን የመቅጣት መብት አለው የሚለውን የተሳሳተና ኋላ ቀር አስተሳሰብ ለማስወገድ ያስችላል። ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች ባሎቻቸውን በሕግ ለመጠየቅ የሚችሉ መሆኑን በግልጽ ስለሚያሳይ ምርመራ እንዲጣራ ለማድረግ የነበረውን ችግር እንደሚቀርፍ ይገመታል። "ሚስት ባሏን በወንጀል እንድትከስ ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ ሕግ የለም፤ የባልና ሚስት የወንጀል ጉዳይ ማጣራት አይቻልም፤ ሚስት ባሏን በወንጀል መክሰስ ያስነውራል፤ በባልና ሚስት መካከል በሚነሳ ጸብ ላይ መመስከር አይቻልም" ወዘተ የሚሉ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን ለማስወገድ በማሰብ የተቀረጸ ድንጋጌ ነው። ሆኖም ድንጋጌው አግባብነት ወዳላቸው አንቀጾች ከሚመራ በቀር እራሱ ቅጣት አይደነግግም። ቅጣቱ እዚህ ላይ ያልተደነገገው ከአንቀጽ ፭፻፶፭ እስከ ፭፻፷ ያሉት ዝርዝር ሁኔታዎች ጉዳዩን ስለሚሸፍኑና ቅጣቱንም በአንቀጽ ፶፭ ወይም ፶፮ መሠረት ማክበድ ስለሚቻል ነው። ነገር ግን ድንጋጌው በወንዶች ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ሴቶች ቢኖሩ እነርሱንም እንዲያካትት ተደርጎአል።

አንቀጽ ፭፻፷፭ <u>ሴትን መግረዝ</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ላይ አልነበረም።

የሴትን ብልት መግረዝ ከጎጂ ባህሎች አንዱ ስለሆነ ሕብረተሰቡ ይህንን ተገንዝቦ ከዚህ ድርጊት እንዲቆጠብ ለማድረግ ሲባል ወንጀል ሆኖ እንዲያስቀጣ ተደርጓል። ድርጊቱ ከሕጻናት ሴቶች በተጨማሪ በትላልቅ ሴቶችም ላይ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ በድንጋጌው ይዘት ላይ "በየትኛውም የዕድሜ ክልል የምትገኘውን ሴት" የሚል ሀረግ ገብቷል። በገረዘ ሰው ላይ የሚወሰነው ቅጣት እንደነገሩ ሁኔታና ክብደት ከሶስት ወር የማያንስ ቀላል እስራት ከአምስት መቶ ብር የማያንስ መቀጮ እንዲሆን ተደርጎ ተደንግጓል።

አንቀጽ ፭፻፷፮ <u>የሴትን ብልት መስፋት</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ውስጥ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ነው።

የሴትን ብልት መስፋት በጣም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ጎጂ ባህል እንደሆነ ህብረተሰቡ ተገንዝቦ ከዚህ ዓይነት ድርጊት እንዲታቀብ ለማድረግ እንደወንጀል ተግባር ተቆጥሮ የሚያስቀጣ እንዲሆን ተደርጓል።

ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግሥቱ ለሴቶች ከተሰጡት መብቶች ጋር አብሮ እንደሚሄድ ይገመታል። ድርጊቱ የሰብዓዊ መብቶችን የሚጻረርና ሴቶችን ለከፍተኛ ስቃይና ችግር የሚያጋልጥ በመሆኑ በድርጊቱ ፈጻሚዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ጠንከር ቢል ውጤት

www.abyssinialaw.com

ያስገኛል የሚል ግምት በመወሰዱ ከአምስት እስከ አስር ዓመት ሊደርስ የሚችል የጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስከትል እንደሚሆን ተደርጎ ተደንግጓል::

አንቀጽ ፭፻፳፯ <u>በሌሎች ልማዳዊ ጎጂ ድርጊቶች አማካይነት የሚፈጸም የአካል ጉዳት</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ላይ አልተካተተም ነበር::

ይህ ድንጋጌ ከላይ ባሉት አንቀጾች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ ጎጂነቱ በሕክምና ሙያ የተረጋገጠና ኢሰብአዊነቱ የታወቀ ልማዳዊ ድርጊት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ሲያስከትል የሚያስቀጣ ነው::

ድርጊቱ በህክምና የማይደገፍ ከመሆኑም በላይ በሰውነት ላይ ጉዳት የሚያስከትልና ሲፈጸም የስቃይ ስሜት የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል::

ድርጊቱ በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ላይ ጥበቃ የሚደረግላቸውን ሰብዓዊ መብቶች የሚጋፋና የሚጥስ ኢሰብአዊ ተግባር መሆኑ ከታወቀ እንደወንጀል ተቆጥሮ በፈጻሚው ላይ ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ድንጋጌ ነው::

በወንጀል አድራጊው ላይ የሚጣለው ቅጣት እንደጉዳቱ ክብደት በሕጉ ላይ ስለቀላልና ስለከባድ የአካል ጉዳት በሚወሰነው ቅጣት መሰረት እንደሚሆን ተደርጎ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፭፻፳፰ <u>በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፍ</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ውስጥ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ነው::

ከዚህ በላይ በተደነገጉት አንቀጾች ውስጥ በተመለከቱት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት ተበዳይዋ (ተበዳዩ) በተላላፊ በሽታ ብትያዝ (ቢያዝ) በዚህ ሕግ ተላላፊ በሽታዎችን ስለማባዛት በተደነገገው መሠረት ወንጀል አድራጊው በተደራቢነት እንደሚቀጣ የሚደነግግ አንቀጽ ነው::

አንቀጽ ፭፻፳፱ <u>በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ መሆን</u>

አንቀጹ በቀድሞው ሕግ ውስጥ ያልነበረ አዲስ ነው::

እንደ ወንጀል በተቆጠሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ የሆነን ወላጅ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሰው የሚያስቀጣ ድንጋጌ ሲሆን በወንጀሉ ተካፋይ በሚሆኑ ሰዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት በዋና ወንጀል አድራጊዎች ላይ ከሚጣለው ቅጣት ያነሰ እንዲሆን ለማድረግ ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት መቶ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንዲሆን ተደርጎ ተደንግጓል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፸ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈጸሙ ማነሳሳት

የዚህ ዓይነት ድንጋጌ በቀድሞው ሕግ ላይ አልተካተተም ነበር።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በወንጀል ሕግ በመከልከል ለማስቆም ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ በተለያየ ሁኔታ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ለሕጉ ታማኝ የሆኑ ሰዎች ድርጊቶቹ በሕግ በመከልከላቸው ቢፈጸሙ ለባለሥልጣን በማመልከትና ማስረጃ በማቅረብ ወንጀል አድራጊዎችን ሊያስቀጡ ይችላሉ።

ሌሎች ደግሞ ድርጊቶቹን ቢፈጽሙ ሊከተል የሚችለውን ቅጣት በመፍራት ከአድራጎታቸው ሊታቀቡ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ግን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንደመልካም ነገር በመቁጠር ህብረተሰቡ የወጣውን ሕግ ተቀብሎ ተግባራዊ እንዳያደርግ ቅስቀሳ ለማድረግ የሚፈልጉ ሊኖሩ ይችላሉ። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈጸሙ በይፋም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያነሳሳ ወይም የሚቀሰቅስ ይህን ዓይነት ዓላማ ለማስፈጸም ሕዝብ የሚያደራጅ፣ ለዚህ ዓላማ ድጋፍ የሚሰጥ ማንኛውም ሰው እንዲቀጣ የሚያደርግ ድንጋጌ ቢኖር ጎጂ ባህሎችን ለማስወገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያግዛል በሚል ይህ አንቀጽ እንዲቀረጽ ተደርጓል።

ለድርጊቱ መወሰን ያለበት ቅጣት እንደሁኔታው ቀላል እስራት ወይም መቀጮ ወይም በሁለቱም ዓይነት ለመቅጣት የሚያስችል ድንጋጌ ሆኖ ተደንግጓል።

## ምዕራፍ አራት
## የሰውን ሕይወት፣ አካል ወይም ጤንነት ለአደጋ በማጋለጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

አንቀጽ ፭፻፸፩ የሰውን ሕይወት ለአደጋ ማጋለጥ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፩ ሆኖ ገብቷል።

"ያለ ይሉኝታ" የሚለው አስፈላጊ ሐረግ ስላልሆነ ተሰርዟል። የአቀማመጥ ለውጥም ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፸፪ የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሰውን ህይወት፣ አካል ወይም ንብረት ለአደጋ ማጋለጥ

ይህ በቀድሞ ሕግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ሲሆን እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ እየጣሱ በሕይወት፣ በአካል ወይም በንብረት ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ ለመግታት ይጠቅማል ተብሎ እንዲገባ የተደረገ ነው።

ብዙውን ጊዜ ተሽከርካሪ በሚንቀሳቀስባቸው መንገዶች ላይ እግረኞች ግራ ቀኙን ሣያዩ ሲያቋርጡ ወይም ትክክለኛ መስመራቸውን ትተው ሲጓዙ የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ከመግታትም በላይ ተሽከርካሪዎች እርስ በርስ ሲጋጩ ወይም በእግረኞች ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉበት ሁኔታ ይከሰታል። በሌላ በኩል ተሽከርካሪዎች በትራፊክ ደንቦች ላይ የተሰጠውን ልዩ ልዩ ምልክት በመጣስ እና ትክክለኛ መስመራቸውን ባለመያዝ፣

www.abyssinialaw.com

አንዳንድ ጊዜም በአግረኛ መንገድ ላይ በመውጣት በሰው ሕይወት፣ አካል፣ ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ለማስከተል የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ይታያል።

ይህ አንቀጽ የተቀረጸው የዚህ ዓይነቱን ድርጊት ለመከላከል ነው ድርጊቱ አስጊ ወይም አደገኛ ሁኔታ ከመፍጠሩም አልፎ በሰው ሕይወት፣ አካል፣ ጤና ወይም ንብረት ላይ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ አድራጊው አግባብ ባለው አንቀጽ መሠረት በተደራራቢነት እንደሚቀጣ ተደርጎ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፭፻፸፫ <u>ሰብዓዊ አካል ለአደጋ ማጋለጥ</u>

የሰው አካል ወይም የአካሉ ብልት ወይም ክፍል ሊሸጥ እንደማይቻል የሚደነግግ አዲስ አንቀጽ ሆኖ ገብቷል። ከዚህም ሌላ አንድን ሰው በማስገደድ ወይም ሳይፈቅድ በአካሉ ላይ የሕክምና ወይም የሳይንስ ምርመራም ሆነ ምርምር ማድረግ እንዲያስቀጣ የተደረገ ሲሆን የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅትም በወንጀሉ ተካፋይ ሲሆን ተጠያቂ እንደሚሆን አንቀጹ ይገልጻል።

አንቀጽ ፭፻፸፬ <u>ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፬ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የቃል ማስተካከያ እና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጓል። ስለቅጣቱ የሚደነግገው ሐረግ ከፊደል ተራ (ለ) አካል በታች በአዲስ ፓራግራፍ የተፃፈ ሲሆን መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፭፻፸፭ <u>በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፭ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው ግልጽና አጭር ሆኖ ተሻሽሏል። የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ የቃላትና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት ተረቅቋል።

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፩) መጀመሪያ ቅጣቱን ከገለጸ በኋላ ወንጀሉ የሚከብድበትን ሁኔታ የሚተነትን ሲሆን አንቀጹ ከሌሎች አንቀጾች ጋር አንድ ዐይነት አቀራረጽ እንዲኖረው ቅጣቱ በስተመጨረሻ ሆኖ ተሻሽሏል።

ቅጣቱ ከፍ ቢል ሰዎች የተሻለ ጥንቃቄ ይወስዳሉ ተብሎ ስለታመነ ጣራ ቅጣቱ አንድ አመት መሆኑ ቀርቶ ከሁለት አመት በማይበልጥ እስራት እና በመቀጮ ይቀጣል በሚል ተደንግጓል።

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ለ) ላይ "ሕጋዊ" እና "የሕክምና" ግዴታ የሚሉት ቃላት "ሌላ ሕጋዊ ግዴታ" በሚል ሐረግ ተተክተዋል፤ ምክንያቱም በንዑስ አንቀጹ ላይ የተመለከቱት ሌሎች ግዴታዎችም ከሕግ የመነጩ በመሆኑ ነው። አነጋገሩም ግልጽ እንዲሆን የቃላት እና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፸፮ <u>ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን መጉዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፮ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው የቁጥር ፭፻፵፰ ድንጋጌ "አሥራ አምስት አመት ያልሞላው ልጅ" የሚል ሐረግ ይገኝበታል:: ሆኖም፣ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ለአካለመጠን ያልደረሱት ልጆች እድሜ እስከ አስራ ስምንት ዓመት ከፍ ስላለ ለአካለመጠን ያልደረሱ በሚል ሐረግ ተተክቷል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደረገ ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንድ ገብቷል:: ይኸውም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትንና የሕፃናት ኮንቬንሽንን መሠረት በማድረግ ለአካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ መበደል፣ ችላ ማለት፣ ከአቅም በላይ ማሠራት ወይም መምታት ብቻ፣ ምንም ጉዳት በማያስከትልበት ጊዜ እንደወንጀል እንዲቆጠር የተደረገበት ድንጋጌ ነው::

ንዑስ ቁጥር አንድ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኗል::

አንቀጽ ፭፻፸፯ <u>አምባጓሮ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፵፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፯ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጐበታል:: አምባጓሮም ማስቀጣት ያለበት በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በንብረት ላይ ጭምር ጉዳት ሲያደርስ ሊሆን ስለሚገባ በዚሁ መሠረት ንብረትንም እንዲያካትት ተደርጐ ተረቅቋል:: ከዚህም ሌላ አምባጓሮው ማስቀጣት ያለበት በጠብ ተካፋዮቹ ላይ ብቻ ጉዳት ሲያደርስ ሳይሆን በሌላ ሰው ላይም ጉዳት ሲያስከትል ሊሆን ስለሚገባ በዚሁ መልክ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን "ጉዳት ያልደረሰ እንደሆነ" የሚል ሐረግ ታክሎበታል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ይህ ሐረግ በንዑስ ቁጥር ሁለት ካልተካተተ ከንዑስ ቁጥር ሦስት ጋር ልዩነት ስለማይኖረው ነው::

በንዑስ ቁጥር ሦስት ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት ተረቅቋል::

በንዑስ ቁጥር አራት ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::

አንቀጽ ፭፻፸፰ <u>የይዋጣልን ፍልሚያ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፰ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበታል::
በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ አስፈላጊ ያልሆነ ሐረግ ተሰርዟል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር ሦስት ላይ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጐበታል።

አንቀጽ ፭፻፸፱ <u>የይዋጣልን ፍልሚያ እንዲደረግ መጠየቅ፣ ማነሳሳትና መርዳት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፸፱ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ ከሚገኙት ሦስት ፓራግራፎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፓራግራፎች መርዳት፣ ማነሳሳት ራሳቸውን ችለው ቅጣት የሚደነግጉ በመሆናቸው እና ሶስተኛው ፓራግራፍ የተለየ አሳብ የያዘ በመሆኑ በሦስት ንዑስ አንቀጾች እንዲከፈሉ ማለት እንደ ቀደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) እንዲሆኑ ተደርጐ ተረቅቋል። በዚሁ መሠረት ንዑስ ቁጥር (፪) ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ ንዑስ ቁጥር (፫) ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖ ገብቷል። በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን፣ በተለይም በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ "ወይም ፍልሚያው ተካሔዳ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል።" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል። ይህም የሆነበት ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (፬) ስር በተመለከተው ድንጋጌ ላይ ወንጀሉን ያነሳሳው ሦስተኛውን ወገን በቀላል እስራት እንዲቀጣ ሲደረግ፣ የይዋጣልን ፍክክሩን ያነሳሳው ዋና ወንጀል አድራጊው በመቀጮ ብቻ እንዲቀጣ ማድረጉ ትክክል ባለመሆኑ ነው።

<u>ርዕስ ሁለት</u>

<u>በሰው ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>በሰው የግል ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

"ስለሚሰሩ" የሚለው "ስለሚፈጽሙ" በሚል ተሻሽሏል።

አንቀጽ ፭፻፹ <u>ዛቻ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹ ሆኖ ገብቷል።

"ድንጋጤና ሽብር" በሚለው ሐረግ ውስጥ ለወንጀሉ መፈፀም ሁለቱም ሁኔታዎች በአንድነት መሟላት እንዳለባቸው የሚያሳይ ይመስላል ሆኖም "ና" የሚለው ማያያዣ ፊደል (መስተፃምር) የሚለው በዛቻ ማስደንገጡ ወይም ማሸበሩ ብቻ ለወንጀሉ በቂ ስለሆነ "ና" የሚለው በ "ወይም" ተተክቷል።

ቅጣቱ ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ ስላልሆነ ቅጣቱ ተሰርዞ እስከ አንድ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት ለመድረስ በሚችል ቀላል እስራት ይቀጣል በሚል ተለውጧል። አንቀጹ በዚህ መልክ ተሻሽሏል።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፭፻፹፭ <u>የመክሰስ ወይም የማዋረድ ዛቻ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

ከድንጋጌው ስያሜ ላይ "ሕገወጥ" የሚለው ቃል ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ዛቻ ምን ጊዜም ቢሆን ህጋዊ ነው የሚባልበት ሁኔታ ሊኖር ስለማይገባ ነው፡፡ በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ እና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ ፭፻፹፮ <u>ማስገደድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፮ የተደረገ ሲሆን በመጠኑ ተሻሽሏል፤ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥም ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፭፻፹፯ <u>የመወሰን ችሎታን ማሳጣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው "የማሰብን ችሎታ ስለማሳጣት" የሚለው ሰውየው የሚያሳጣው የማሰቡን ችሎታ ሳይሆን የመወሰን ችሎታውን ስለሆነ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል፡፡ ድንጋጌው አግባብ ያላቸውን አንቀጾች እንዲያስቀጣ የተደረገበት ሲሆን አግባብነት ያላቸው አጠቃሽ አንቀጾች በንዑስ አንቀጽ (፪) መጨረሻ ላይ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

በቀድሞው ድንጋጌ ላይ የተጠቀሰው ቁጥር ፭፻፲፯ (በዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፬) ብቻ ነበር፡፡ ሆኖም የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፲፮ እና ፭፻፲፯ (አንቀጽ ፭፻፴፪ እና ፭፻፴፫) ድንጋጌዎች ጭምር ከአንቀጽ ፭፻፹፯ ጋር ግንኙነት ስላላቸው አንቀጽ ፭፻፴፬ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ከአንቀጽ ፭፻፴፪ እስከ ፭፻፴፬ ያሉት ድንጋጌዎች ተጠቃሽ አንቀጾች ሆነው ገብተዋል፡፡

አንቀጽ ፭፻፹፰ <u>የወንጀሎች አንድ መሆን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

ድንጋጌው ግልጽነት እንዲኖረው የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጐበት አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

አንቀጽ ፭፻፹፱ <u>ከሕግ ውጭ ይዞ ማስቀመጥ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው "በግድ ይዞ" የሚለው ሕገወጥ ድርጊት ለመግለጽ ሲባል ስለሆነ የእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ ያለውን (Illegal restraint) የሚለው ትርጉም ከሕግ ውጭ ይዞ ስለማስቀመጥ በሚል ተሻሽሏል፡፡

ንዑስ አንቀጽ (፩) ተንትኖ ዘርዘር ባለ መልኩ ማስቀመጡ ለግልጽነት ስለሚጠቅም ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) እና (ለ) ሆኖ ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን፣ "ድርጊቱ የተፈጸመው መንግሥት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅት፣ ግለሰብ፣ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት አንድን ተግባር ካልፈጸመ ወይም ከመፈጸም ካልተቆጠበ በቀር በታጋቹ ሰው ሕይወት፣ አካል ወይም ነጻነት ላይ ከባድ ጉዳት እንደሚደርስ ወይም እስራቱ እንደሚቀጥል በመዛት የሆነ እንደሆነ" ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚያስቀጣ ድንጋጌ ነው:: ይህም የአሸባሪዎች ድርጊት ለመከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል::

አንቀጽ ፭፻፹፮ <u>ሰውን መጥለፍ</u>

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቁጥር ፭፻፶፰ ስለመጥለፍ የሚያካትተው የሴትን መጥለፍ ብቻ ሲሆን ወንዶችም ሊጠለፉ ስለሚችሉ ሁለቱንም ጾታዎች የሚያጠቃልል አንቀጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ መልኩ ተቀርጿል:: ለማግባት አስቦ ሴትን መጥለፍ በአንቀጽ ፭፻፹፯ የሚያስቀጣ ሲሆን የጠለፋው ዓላማ ለጋብቻ ካልሆነ ግን በዚህ አንቀጽ መሠረት ያስቀጣል ማለት ነው::

አንቀጽ ፭፻፹፯ <u>ሴትን መጥለፍ</u>

ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፭፻፶፰ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሲሆን፣ በዚህ ሕግ "ሴትን መጥለፍ" የሚል ግልጽ ስያሜ ተሰጥቶት አንቀጽ ፭፻፹፯ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው በአገራችን በአንዳንድ አካባቢዎች ሴትን መጥለፍ እንደ ባህል ተደርጎ የሚታይበትን ሁኔታ የሚያስወግድ፣ እንዲሁም ያለሴቷ ፍላጎትና ስምምነት በጋብቻ ስም የሚከናወነው የጠለፋ ድርጊት እንደወንጀል የሚቆጠር ነው::

ይህ አንቀጽ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፴፭ ላይ እንደተደነገገው ሴቶች ከጎጂ ባህልና ልማድ ተጽዕኖ የመላቀቅ መብት እንዳላቸውና ከወንዶች ጋር እኩል የጋብቻ መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያረጋግጥ መሆኑ ይታመናል::

አንዲት ሴትን አገባታለሁ በሚል አሳብ በኃይል የሚጠልፍ፤ ወይም ይህንኑ ድርጊት በኃይል፣ በዛቻ፣ በተንኮል ወይም በማታለል የሚፈጽም ሰው የሚወሰንበት ቅጣት ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚሆን በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ተደንግጓል::

ንዑስ አንቀጽ (፪) አዲስ የገባ ድንጋጌ ሲሆን፣ የተጠለፈችዋ ሴት ተገዳ ተደፍራ ከሆነ ጠላፊው ስለአስገድዶ መድፈር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት በተጨማሪ እንዲቀጣ የሚያደርግ ንዑስ አንቀጽ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የጠለፋውን ድርጊት ተከትሎ በጠላፊውና በተጠላፊዋ መሀከል ጋብቻ ቢፈጸም የወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስቀር እንደማይችል ተደንግጓል:: ይህም ተበዳይዋ ፈቅዳ ወንጀል አድራጊውን ካገባችው በወንጀል መጠየቁ ይቀራል የሚለውን የቀድሞውን ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ የሚሰርዝ ነው::

ንዑስ አንቀጽ (፬) በቀድሞው ሕግ ያልነበረ ሲሆን ተበዳይዋ በጠላፊው ድርጊት ለደረሰባት የሕሊናና የማቴሪያል ጉዳት አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ የመጠየቅ መብቷ የተጠበቀ መሆኑን ይደነግጋል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፹፭ የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነችን ወይም የመከላከል አቅም የሌላትን ሴት መጥለፍ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፭ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው "ክፉና በጎ ለይታ ለማወቅ የማትችል" የሚለው የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነችን ሴት ለማለት ተፈልጎ ስለሆነ በዚህ መልኩ ተሻሽሏል። አንቀጹ በዚህ ሁኔታ ተስተካክሏል።

ቅጣቱንም በተመለከተ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የነበረው ቅጣት ለወንጀሉ አነስተኛ በመሆኑ፣ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፹፮ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን መጥለፍ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው "ሕጻንን ስለ መዝረፍ /ስለመንጠቅ/" የሚለው በመጀመሪያ ሕጻን የሚለው ቃል ለአካለመጠን ያልደረሰን ልጅ በሙሉ ስለማያጠቃልልና ሕጉ መጠበቅ የሚፈልገው ለአካለመጠን ያልደረሰን ልጅ በሙሉ ስለሆነ ስያሜው ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን በሚል ተለውጧል። መዝረፍ /መንጠቅ/ የሚለው መጥለፍን ለማመልከት ስለሆነ በዚሁ ቃል ተተክቷል።

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች በንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንዲገቡ ሲደረግ፣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ገብተዋል።

የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የሚሸፍነው በኃይል፣ በዛቻ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ድርጊት በአንቀጽ ፭፻፹፯ በተመለከተው ዓይነት የልጅን ጠለፋ ያካሔደን ሰው ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

ጠላፊው የተፈፀመው በአብድ፣ የአእምሮ ጉድለት ወይም በማናቸውም ሌላ በሚሆንበት ጊዜ ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲያስቀጣ ተደርጎ በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ተደንግጓል። የወንጀል አፈፃፀሙ ከላይ በአንቀጽ 588 በተደነገገው ዓይነት ነው።

የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፩) እና (፪) የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች ሆነዋል።

አንቀጽ ፭፻፹፯ ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፹፯ ሆኖ ገብቷል።

ቁጥር ፭፻፷፩ (፩) ላይ መጥለፍ ስላልተጨመረበት መጥለፍ የሚለው ቃል ገብቶ ንዑስ አንቀጹ ተሻሽሏል።

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) እና (ለ)፣ እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ቅጣቱን በሚመለከት በንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) የተመለከቱት ቅጣቶች ከፍ እንዲሉ ተደርጎ ተረቅቋል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ለተዘረዘሩት ወንጀሎች የቀድሞ ሕግ ቅጣት አነስተኛ መሆኑ ስለታመነበት ነው::

### አንቀጽ ፭፻፺፩ ህፃንን ማለዋወጥ እና የራስ ያልሆነን ህፃን መውሰድ

ይህ አንቀጽ አዲስ የገባ ሲሆን አንድን ሕፃን በሌላ ህፃን መለወጥ ወይም የራስ ያልሆነን ህፃን ልጅ እንደ ራስ አድርጎ መውሰድ በሕፃናት ማዋለጃ ሐኪም ቤቶች ወይም በሌላ ቦታ ሊከሰት የሚችል በመሆኑና እንደወንጀል ሊቆጠር የሚገባው ስለሆነ ይህንን ሁኔታ ለማካተት የተቀረፀ ድንጋጌ ነው::

### አንቀጽ ፭፻፺፪ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን አለማቅረብ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፪ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

### አንቀጽ ፭፻፺፫ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን በሚመለከት ልዩ ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፫ (፩) ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፫ የተደረገ ሲሆን፤ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበትና ተገቢነት ያላቸው አንቀጾች ተጠቅሰው እንዲሻሻል ተደርጓል::

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ከዚህ ለቆ በአንቀጽ ፭፻፺፬ ውስጥ ገብቷል::

### አንቀጽ ፭፻፺፬ ከባድ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፫ (፪) ድንጋጌ ተሻሽሎ አዲስ አንቀጽ ፭፻፺፬ ሆኖ ገብቷል:: ምክንያቱም ጉዳዩ የሚመለከተው በአንቀጽ ፭፻፺፪ ስር የተመለከቱትን ሰዎች ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ ፭፻፺፫ ያሉትንም ሰዎች ጭምር በመሆኑ ነው::

### አንቀጽ ፭፻፺፭ በፖለቲካ ምክንያት ሰውን መጥለፍ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፭ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ "በፖለቲካ ምክንያት ሰውን ስለመስረቅ" ይል የነበረ ሲሆን፣ በይበልጥ ተስማሚ መሆኑ በሚታመንበት ሀረግ "በፖለቲካ ምክንያት ሰውን መጥለፍ" በሚል ተተክቷል::

አቀራረፁን በሚመለከት የቀድሞው ድንጋጌ በንዑስ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ብቻ የተከፈለ ሲሆን ይህ አንቀጽ ግን በሁለት ንዑስ አንቀፆች እና ንዑስ ቁጥር አንድ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) እና (ሐ) እንዲከፈል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

የቀድሞው ሕግ ድንጋጌ መግቢያ "ማንም ሰው" ብቻ የሚል ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ግን ሰፋ እንዲል ተደርጓል። ስለ ፖለቲካ የተጠቀሰው በድንጋጌው ስያሜ ላይ ብቻ ነበር። በዚህ አንቀጽ ግን በንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ላይ "በፖለቲካ ምክንያት" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል። እንዲሁም "... በዛቻ፣ በተንኮል፣ በሀይል ድርጊት ወይም በማስገደድ ሌላውን ሰው ጠልፎ በሕይወቱ፣ በአካሉ፣ ወይም በጤንነቱ ወይም በነፃነት አደጋ እንዲደርስበት ለማድረግ" የሚለው አገላለጽ ፊደል ተራ (ሀ) ውስጥ መሆኑ ቀርቶ በንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ ላይ እንዲገባ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት በአገላለፁም ላይ የተመለከቱት የወንጀል መፈፀሚያ ዘዴዎችና አላማዎች ተገቢነት ያላቸው በፊደል ተራ (ሀ) ለተገለፀው ወንጀል ብቻ ባለመሆኑ ነው።

ከቀድሞው ድንጋጌ ከፊደል ተራ (ሀ) ውስጥ ከላይ የተጠቀሰው አገላለጽ ከተሰረዘ በኋላ ቀሪው አነጋገር ተስተካክሎ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ሆኖ ገብቷል። ~~የቀድሞው የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደረገ ሲሆን [illegible]~~ የተከፈሉ አዲስ ድንጋጌዎች ~~ተብተዋል~~ እነሱም:-

(ለ) በአገር ውስጥ ለሚገኝ ለአንድ ቡድን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ" ወይም

(ሐ) በአገር ውስጥ ከሕዝብ ተገልሎ እንዲቀመጥ ያደረገ እንደሆነ፤" የሚሉ ናቸው። በእነዚህ ሀረጎች የተመለከቱት ድርጊቶች በንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ላይ በተገለፁት ሁኔታዎች ሊፈፀሙ ስለሚችሉ እንዲካተቱ ተደርጓል።

የቀድሞው የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ "ይህንን ስርቆት ያዘዘና ያሰናዳ ወይም እያወቀ እርዳታውን የሰጠ እንደሆነ" የሚል ሲሆን አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው "ጠለፋን ያዘዘ ወይም ያደራጀ እንደሆነ" እንዲል ተደርጓል። የዚሁ አይነቱም ወንጀል አድራጊ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ጥፋተኛ ይልቅ ለኅብረተሰቡ አደገኛ ወንጀለኛ መሆኑ ስለታመነበት የሚወሰንበት ቅጣት ከከአስራ አምስት ዓመት እሥራት ወደ ሃያ ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፺፮ <u>ሰውን አገልጋይ ማድረግ*</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፭ ድንጋጌ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የነበሩት ሲሆን ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጎ ተሻሽሎ አንቀጽ ፭፻፺፮ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኗል።

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኗል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የገባ ሲሆን ወንጀል የተፈፀመው በህፃናት፣ በሴቶች፣ በአእምሮ ደካሞች ወይም በሽተኞች ላይ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ እንደሚከብድ ተመልክቷል።

* በወንጀል ህጉ አንቀጽ 596 ንዑስ አንቀጽ 2 "በመድረሻ ቢታው" የሚለው ቃል " በመድረሻ በታው" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

አንቀ ፭፻፺፯ <u>በሴቶችና በልጆች መነገድ</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ላይ በግልጽ አልተቀመጠም ነበር::

ይህ አንቀጽ ሴትን ወይም ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ለግዳጅ ስራ የሚመለምል፤ በእጁ የሚያስገባ፣ የሚደብቅ፣ ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውር፣ ከአገር የሚያስወጣ ወይም ወደ አገር የሚያስገባ፣ ሰው እንዲቀጣ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው::

ለተፈጸመው ድርጊት የሚወሰነው ቅጣት ከሶስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሆነና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ለመጣል እንደሚቻል በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ተገልጿል::

ከዚህም በተጨማሪ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ወንጀል ለማስፈጸም ተበዳዮችን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወይም በውጭ አገር በጉዞ መጨረሻ ሲደርሱ ለማስረከብ በማቀድ በየብስ፣ በባህር ወይም በአየር የሚልክ፣ የሚያጓጉዝ ወይም ማጓጓዙን የሚመራ ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ቅጣት ዓይነት እንደሚቀጣ የሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲገባ ተደርጓል::

አንቀጽ ፭፻፺፰ <u>በሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ</u>

አንቀጹ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ ያልነበረ ሲሆን በዚህ ሕግ ሊካተት የቻለበት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋና እየጨመረ የመጣውን ሴቶችን ስራ ለማስቀጠር በሚል ምክንያት ከኢትዮጵያ ውጭ እንዲወጡ እየተደረገ ዋስትና በሌለው ሁኔታ የሚደርስባቸውን በደል ለመግታት ያስችላል በሚል እምነት ነው::

የአንቀጹን ይዘት በሚመለከት በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ሴቶችን ለሥራ ማሰማራት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ በሕገወጥ መንገድ ለስራ ወደ ውጭ አገር የላከን ሰው ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ለመቅጣት ከማስቻሉ በተጨማሪ እስከ ብር ሃያ አምስት ሺህ የሚደርስ መቀጮ ሊጣልበት እንደሚችል ይደነግጋል::

በስራ ሰበብ ወደ ውጭ አገር እንድትሄድ የተደረገች ሴት በሰብዓዊ መብቷ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ ከታወቀ በጥፋተኛው ላይ የሚወሰነው የጽኑ እስራት ቅጣት ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት፣ መቀጮውም እስከ ሃምሳ ሺህ ብር ከፍ ሊል እንደሚችል የሚደነግግ ንዑስ አንቀጽ (፪) ገብቷል::

በሴቶች ላይ የሚፈጸመው የድርጊት ዓይነት በወንዶች ኢትዮጵያውያንም ላይ ተፈጽሞ ቢገኝ በተመሳሳይ ሁኔታ ለመቅጣት የሚያስችል ንዑስ አንቀጽ (፫) ተቀርጿል::

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፭፻፺፱ <u>በዚህ ርዕስ በተመለከቱት ወንጀሎች የሕገ ወጥ ማህበርና የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

ከላይ በተገለጸው መሰረት የተለወጠው የአንቀጽ ፭፻፷፯ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ዓይነት በሁለት ፓራግራፎች እንዲቀጥል የተደረገ ሲሆን አላስፈላጊ ቃላት ተሰርዘው አስፈላጊ የሆኑ ደግሞ ታክለውበት የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖአል::

አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ የገባ ሲሆን፣ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ እርዕስ በተመለከቱት ወንጀሎች ተካፋይ ሲሆን በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፺ መሠረት እንደሁኔታው የሚቀጣ መሆኑን ይደነግጋል::

አንቀጽ ፮፻ <u>የክትትል ወይም የቁጥጥር ጉድለት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻ ሆኖ ገብቷል::

የክፍለ አገሩ ገገር ወይም የአንድ ከተማ፣ የአንድ መንደር ወይም የአንድ ነገድ አስተዳዳሪ የሆነ ማናቸውም ሹም በሚገዛው አገር ወይም በሚያስተዳድረው ከተማ ወይም መንደር የሚለው ወቅታዊውን ሁኔታ ስለማያንጸባርቅ አሁን ያለውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተስተካኳል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>በሌሎች ሰዎች መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፮፻፩ <u>በሲቪል መብቶች በነፃ መጠቀምን መከልከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፩ ሆኖ ገብቷል::

ብሔራዊ መብት ከሰው መብቶች አንዱ ስለሆነ ሁሉንም የሰውን መብቶች ባጠቃለለ መልኩ አንቀጹ ተሻሽሏል:: በንዑስ አንቀጽ (፩) መጨረሻ ላይ "በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር" የሚለው ሀረግ የገባው፣ የቅጣት መደራረብ እንዳይኖር በማለት ነው::

ንዑስ ቁጥር (፪) "የህዝባዊንና የፖለቲካ ነጻ ተግባር የመንካት ወንጀሎች ይልቁንም ድምጽ የመስጠትንና የመምረጥን መብቶች የመንካት ወንጀሎች" የሚለው ሀረግ በአንድ ቃል ማለትም በፖለቲካ መብቶች በሚለው መጠቃለል ስለሚችል ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፪ <u>የመዘዋወር ነጻነት መብትን መድፈር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፪ የተደረገ ሲሆን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፮፻፫ <u>የሥራ ነፃነት መብትን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፴ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፫ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "የስራ ነፃነትን ሕግ ስለመደፈር" ይል የነበረ ሲሆን "የስራ ነፃነት መብትን መጣስ" በሚል ሀረግ ተተክቷል።

በንዑስ ቁጥር አንድ መግቢያ ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት የተሰረዙ ሲሆን፣ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት "ሌላውን ሰው" የሚል እንዲገባ ተደርጓል። ይህም በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች በማን ላይ እንደሚፈፀም በግልጽ ያሳያል።

የድንጋጌው የንዑስ ቁጥር (፩) "ሀ" አነጋገር የሠራተኛውን መብት እንጂ የአሰሪውን መብት በግልጽ የማይጠብቅ በመሆኑ የሁለቱንም ወገኖች መብት በሚጠብቅ ሁኔታ ተሻሽሎ ተረቅቋል።

የንዑስ ቁጥር አንድ (ለ) አነጋገር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበትና አሳቡ ተቃንቶ ተረቅቋል።

የንዑስ አንቀጽ አንድ መነሻ ቅጣት ወደ ሶስት ወር ቀላል እሥራት ከፍ እንዲል ተደርጓል።

የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል።

አንቀጽ ፮፻፬ <u>የግል ቤቶችን ወይም የተከለሉ ቦታዎችን መድፈር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፬ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "መኖሪያ ቤትን ስለመድፈር" የሚል ሲሆን ከአንቀጹ ይዘት ጋር በይበልጥ በሚጣጣምበት መልክ "የግል ቤቶችን ወይም የተከለሉ ቦታዎችን መድፈር" እንዲል ተደርጓል።

በግልጽ ከተዘረዘሩት ነገሮች በተጨማሪ የሚደፈሩ ሌሎች የግል ንብረቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ በፊደል (ሀ) መጨረሻ ላይ "የግል ይዞታ ወደሆነ ማናቸውም ሌላ ንብረት" የሚል አዲስ ሐረግ እንዲጨመር ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር አንድ በፊደል (ለ) ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው ተስማሚ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል።

በፊደል (ሐ) ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ቃላት ተሰርዘው የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል።

በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፲ <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፲ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ መግቢያም ሆነ በፊደላቱ ተራ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል:: በተጨማሪም የፊደል ተራ "ሐ" ድንጋጌ በፊደል ተራ (መ) ሥር እንዲመጣ የተደረገ ሲሆን አዲስ ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሐ) ሥር ተረቅቋል፤ ይኸውም ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት እስከ ጧቱ አስራ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ የሚል ነው::

ንዑስ አንቀጹ የተጨመረው ከቀን ይልቅ በሌሊት ድርጊቱ መፈጸሙ ሁኔታዎችን ስለሚያከብድ ነው::

አንቀጽ ፮፻፲፩ <u>የመጻጻፍ ወይም የግንኙነት ግላዊነት መብትን መድፈር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፸፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፲፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ረዥምና ውስብስብ በመሆኑ እንዲያጥር ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የቃላት ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን ዘመናዊ መገናኛ ዘዴዎችን ባካተተ መልኩ ከሕገ መንግስቱ ጋር በማነፃፀር የንዑስ ቁጥር (፩) "ለ" ማሻሻያ ተደርጎበታል::

የንዑስ ቁጥር (፪) አገላለጽ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሆኖ ገብቷል:: ቅጣቱም እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ቀላል እስራት ነው::

ንዑስ ቁጥር ሦስት ደግሞ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ ሦስት ሆኗል::

<u>ርዕስ ሶስት</u>

<u>በክብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

አንቀጽ ፮፻፲፪ <u>መርህ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፲፪ ሆኖአል::

የድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮች የዚህ አንቀጽ ሁለት ንዑስ አንቀፆች የተደረጉ ሲሆን የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛና ሰስተኛ ፓራግራፎች የተያያዘ አሳብ ያላቸው በመሆኑ በአንድ ፓራግራፍ ተዋህደው የንዑስ አንቀጽ አንድ ሁለተኛ ፓራግራፍ እንዲሆኑ ተደርጓል:: በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይም የተቀረፁት በዚሁ መልክ ነው::

ድንጋጌው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፰ <u>ወንጀሉ የሚፈፀምባቸው ዘዴዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፸፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፰ ሆኖ ገብቷል::

የመጀመሪያው ፓራግራፍ የክብር መንካት ወይም የስም ማጥፋት ወንጀል የሚፈጸምባቸውን ዘዴዎች ከመጥቀሱም በላይ ድርጊቱ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል:: ሆኖም ክብርን መንካት ወይም ስምን ማጥፋት እንደሚያስቀጣ በአንቀጽ ፩፻፲፫ ላይ ስለተመለከተ በድጋሚ መፃፍ ስላላስፈለገ ተሰርዟል:: የአንቀጹ ስያሜም ከላይ በተመለከተው መሠረት ተስተካክሏል:: ሁለተኛው ፓራግራፍም መጠነኛ የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፩፻፱ <u>ሕጋዊ ሰውነት በተሰጣቸው አካላት ወንጀሉ ሲፈጸም የሚወሰን ቅጣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፸፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፱ ሆኖ የገባ ሲሆን በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ፣ ነፃነት የማሳጣቱ ቅጣትም በእገዳ፣ በክልከላ ወይም በማፍረስ የሚተካ ሆኖ /ይኸውም/ በእያንዳንዱ ጉዳይ በፍርዱ ውሳኔ ውስጥ መገለጽ እንዳለበተ የሚደነግግ ሲሆን እንደስም ማጥፋት ላሉ ቀላል ወንጀል አንድ ድርጅት እንዲታገድ ወይም እንዲዘጋ ማድረጉ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ እንደወንጀሉ ክብደት ፍርድቤት እየመረመረ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንደሚችል በአንቀጽ ፻፵፫ ላይ ስለተደነገገ ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር እንዲሰረዝ ተደርጓል::

አንቀጽ ፩፻፲ <u>የጉዳት ካሣ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፸፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ እና በንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል:: የንዑስ ቁጥር ሁለት ሁለተኛው ፓራግራፍ ግን የስም ማጥፋቱ ወንጀል ስለሚገለጽበት የማስታወቂያ ዓይነት ለፍርድ ቤት መመሪያ የሚሰጥ ሲሆን ስለማስታወቂያ አወጣጥ የተደነገገው አንቀጽ ፻፶፩/፪ በቂ በመሆኑ ፓራግራፉ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፩፻፲፩ <u>የለመከሰስ መብት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፩ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ከመደረጉ በላይ በይዘቱ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፩፻፲፪ <u>የሚያስቀጡ ትችቶችና ንግግሮች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፸፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፪ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## ምዕራፍ ሁለት
## ልዩ ድንጋጌዎች፤ ክብርን መንካት

### አንቀጽ ፮፻፲፫ ስም ማጥፋት እና የሐሰት ሐሜት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፲፫ ሆኖ ገብቷል፡፡

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "በሀሰት ስለመወንጀል" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "የሀሰት ሀሜት" በሚል ተተክቷል፡፡ በሀሰት መወንጀል በአንቀጽ ፬፻፵፯ የሚያስቀጣ እንጂ እዚህ አንቀጽ ውስጥ አይካተትም፡፡ በንዑስ አንቀጽ (፫) ግልጽ ሆኖ የተቀመጠው የሀሰት ሀሜት /ካለምኒ/ በመሆኑ በዚህ መሠረት ተስተካክሎአል፡፡
ከ

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ ጥፋተኛው የተበዳዩን ስም የሚያጠፋው ወይም ክብር የሚነካው በሐሰት ወይም በእውነት መሆኑ ግልፅ አይደለም፡፡ የተገለፀው ነገር ሐሰት ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት መካተቱ ሲታይ ግን የንዑስ ቁጥር አንድ የወንጀል አነጋገር እውነት በሆነ ነገር ላይ ተመስርቶ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ እውነት የተናገረ ሁሉ ግን ክብር ነክቷል ወይም ስም አጥፍቷል እየተባለ በወንጀል እንዲቀጣ ማድረጉ ተገቢ ስላልሆነ የሚፈረድበት የመጉዳት አሳብ ሲኖረው ብቻ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ የመጉዳት አሳብ እንደሌለው ግን የማስረዳት ሸክም የጥፋተኛው እንዲሆን ተደርጎ በአንቀጽ ፮፻፲፬ (፪) ላይ ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም ጥፋተኛው ነገሩን የሚገልፀው "ለአንድ ለሌላ ሰው ወይም ሌሎች ሰዎች" መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በዚህ ሐረግ ምትክ "ለሦስተኛ ወገን" የሚለው እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የንዑስ ቁጥር (፩) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ተረቅቋል፡፡

የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ የስም ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል ስለሚባልበት ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን በአንቀጽ ፮፻፲፮ እና ፮፻፲፯ በተደነገገው ላይ የሚያመጣው ተጨማሪ አሳብ ስለሌለ ተሰርዟል፡፡

የንዑስ ቁጥር አንድ ሦስተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ የገባ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ይዘቱም ያልተሟላ በመሆኑ በፈጸመው ወንጀል የተቀጣውን ሰው ብቻ ሳይሆን ባይቀጣም የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሳላፈበትን፣ እንዲሁም ምህረት (amnesty) እና ይቅርታ (pardon) የተደረገለትንም ሰው ጭምር በግልጽ እንዲያጠቃልል ተደርጎ ተረቅቋል፡፡

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዳቸው ስለተለየ ወንጀል የሚደነግጉና ለወንጀሎቹ ተገቢውን ቅጣት የሰፈሩ ስለሆነ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆነው ገብተዋል፡፡ የሁለቱ ወንጀሎች መነሻ ቅጣትም ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

አዲስ ንዑስ ቁጥር አራት የገባ ሲሆን የተነገረው ወይም የተገለጸው ነገር ሐሰት ሆኖ፣ የተፈጸመው ግን በቸልተኛነት በሚሆንበት ጊዜ እንዲያስቀጣ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም አሳብ ከአንቀጽ ፮፻፲፬ (፩) ጋር የሚጣጣም ነው፤ ምክንያቱም በዚህ በተጠቀሰው ንዑስ ቁጥር "... የተናገርሁት ባላምንበትም እንኳ ሌላ ሰው የተናገረውን ... ነው ወይም በጥርጣሬ ወይም ሳይሆን አይቀርም በማለት ነው ብሎ በጠቅላላው ለመከላከል አይችልም፡፡" የሚል ሲሆን ሐሰተኛ ነገሮችን በቸልተኛነት መናገር ወይም መግለጽ ከቅጣት አያድንም ማለቱ ግልጽ በመሆኑና ሐሰተኛ ነገሮችን በቸልተኛነት መግለጽ ወንጀል መሆኑን የሚደነግግ ሕግ ባለመኖሩ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የቀድሞው ንዑስ ቁጥር ሦስት የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጐበት ንዑስ አንቀጽ አምስት ሆኖ ገብቷል::

አንቀጽ ፫፻፲፬ እውነትንና ከፍ ያሉትን ጥቅሞች ስለመጠበቅ የሚደረገው ልዩነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፬ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፪) (ሀ) መሰረት የተናገረው ወይም የገለጸው እውነት መሆኑን ወይም እውነት መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከቅጣት ይድናል:: ሆኖም መከላከያ መሆን የሚገባው የተነገረው ወይም የተገለጸው ነገር እውነት መሆኑን ማስረዳት ብቻ ሳይሆን ሰውን የመጉዳት ዓላማ እንዳልነበረው በተጨማሪ እንዲያስረዳ የሚገልጽ ድንጋጌ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

የንዑስ ቁጥር ሁለት የመጨረሻው ፓራግራፍ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል:: ከዚህም ሌላ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጐበት አንቀፁ ተረቅቋል::

የቀድሞ የቁጥር ፭፻፹፪ ድንጋጌ መሰረዝ

ይህ ድንጋጌ የአንድን ሰው ግላዊ ወይም ቤተሰባዊ አኗኗር የሚመለከት አነጋገር በሐሰት ወይም በተንኮል መግለጽ እንደማይቻል የሚደነግግ ሲሆን የአንቀጽ ፫፻፲፫ እና የአንቀጽ ፫፻፲፬ ድንጋጌዎች ይህንን አሳብ የሚያካትቱ በመሆናቸው እዚህ ላይ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ስላልሆነ ድንጋጌው ተሰርዟል::

አንቀጽ ፫፻፲፭ ስድብና ማወረድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፭ ሆኖ ገብቷል::

ቁጥር ፭፻፹፫ (፩) የሚለው ንዑስ ቁጥር (፪) የሌሌው ስለሆነ ተሰርዟል::

ቁጥር ፭፻፹፫ ሁለተኛው ፓራግራፍ ወንጀሉ ትንሽ ቢሆንም በደንብ መተላለፍና በወንጀል እንደሚቀጣ ሲገልጽ የእንግሊዝኛው ቅጂ ወንጀሉ ቀላል ሲሆን በደንብ መተላለፍ ከባድ ከሆነ በቁጥር ፭፻፹፫ እንደሚያስቀጣ በግልጽ ስላስቀመጠውና ወንጀሉ ቀላል ሲሆን በደንብ መተላለፍ ብቻ መቅጣቱ በቂ ስለሆነ ቁጥር ፭፻፹፫ በእንግሊዘኛው ቅጂ መሰረት ተስተካክሎ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ሆኗል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፫፻፲፮ መቆስቆስ እና አጸፋ መመለስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለ ጠብ ማንሳትና ስለጠቡ መልስ" ይል የነበረ ሲሆን በእንግሊዝኛው ቅጅ ላይ "Provocation and Retaliation" ከሚለው ሐረግ ጋር በይበልጥ ይጣጣማል ተብሎ በሚታመንበት ሐረግ "መቆስቆስ እና አፀፋ መመለስ" በሚል ተተክቷል::

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፩) የአማርኛው አነጋገር "ለ፫ኛ ወገኖችም ቢሆን አስቀያሚ አናዳጅ በሆኑ....." የሚለው ለሰሚ ሶስተኛ ወገን ሆኖ የተቀረጸ ሲሆን እንግሊዝኛው ቅጂ "ev... toward a third party" የሚለው ለሰሚ ለሶስተኛ ወገን ሳይሆን አስቀያሚ አናዳጅ ... የመሳሰሉት የሆኑ ሥራዎች የተሰነዘሩት ለሌላ ሶስተኛ ወገንም ላይ ቢሆን የሚል ስለሆነ የ... ይሄም ከአንቀጽ ፹፩ ህጋዊ መከላከል የራስንም ወይም የሌላ ሰውን መብት ከሕገወጥ ጥቃት ለማዳን ሲባል የሚደረግ ስለሆነ አንቀጹ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "... ፍርድ ቤቱ ... ሁለቱንም ጥፋተኞች ወይም መሳሹን በነፃ ለማሰናበት ይችላል" በሚለው "ሁለቱንም ጥፋተኞች ወይም ከሁለቱ አንዱን ብቻ ከቅጣት ነፃ ለማድረግ ይችላል" በሚል ተስተካክሏል:: ይህም የሆነው የአፀፋ መሳሹ ድርጊት ከከበደ፣ ጠብ አንሽው ብቻ በነፃ መለቀቅ ያለበት ጊዜ ስለሚኖር ነው::

አንቀጽ ፬፻፲፪ <u>ቃልን ማንሳትና መጸጸት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፲፪ ሆኖ ገብቷል::

ሲያሜው ቃልን ስለመለወጥ ሌላ ትርጉም ሊሰጥ ስለሚችል የድንጋጌው ይዘት አንድ ሰው ለሰራው ጥፋት ጥፋተኛነቱን አውቆ መጸጸቱን መግለጹን የሚገልጽ ስለሆነ ስያሜውም በዚህ መሠረት ተስተካክሏል::

ንዑስ አንቀጽ (፩) አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ንዑስ አንቀጽ (፪) በሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ የሚለው በንዑስ አንቀጽ (፩) ጊዜ አጥፊው አጠፋሁ ሲል ቃሉን ያስተባበለበትን ግልጽ የሆነ ጽሁፍ እንደማይሰጥ ስለሚያስመስለው ተሰርዞ ይህም በሚሆንበት ጊዜ በሚለው ሀረግ ተተክቷል::

በዚሁ ንዑስ ቁጥር (፪) ላይ "ለተከሳሹ ጠቃሚ ስለሚሆኑት" የሚለው ለተከሳሹ ጠቃሚ ስለሚሆኑት /ምክንያቱም የተበደለው ከሳሽ ስለሆነ/ ለማለት ተፈልጎ ስለሆነ ይሄንን በሚገልጽ መልኩ ንዑስአንቀጽ (፪) ተስተካክሏል::

አንቀጽ ፬፻፲፫ <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ልዩ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፲፫ ሆኖ ገብቷል::

ይህ ወንጀል የሚያስቀጣው /በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሠረት/ "የሥራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ የመንግስት ሰራተኛ ላይ" ድርጊቱ ሲፈጸም ነው:: ሆኖም ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባው ስራውን በማከናወን ላይ የሚገኝን የመንግስት ሰራተኛ ብቻ ሳይሆን ስራውን በማከናወን ላይ ባይሆንም ከስራው ጋር በተያያዘ መንገድ ስሙ ከጠፋ ጥፋተኛው ከበድ ያለ ቅጣት ሊወሰንበት ስለሚገባ በዚህ መሰረት የንዑስ ቁጥር (፩) መግቢያ ተሻሽሎ ተረቅቋል::

የዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የአንቀጽ ፬፻፲፩ /ስድብና ማዋረድ/ ቅጣት ማከበጃ ሲሆን፣ የእስራቱ ቅጣት ባለበት ጸንቷል:: የመቀጮው ግን ወደ ብር አንድ ሺህ ከፍ ብሏል:: እስራቱና መቀጮው አማራጭ ቅጣቶች መሆናቸው ቀርቶ በጣምራ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

ኑገሮ—ማት የፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች ቅጣት ግን በቂ ስለሆነ በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው እና የቃላት ለውጥ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

አንቀጹ ከላይ በተዘረዘረው መልኩ ተሻሽሏል::

<u>የቀድሞው የቁጥር ፭፻፹፯ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ስም አጥፊው፣ ሀሜተኛው፣ ተሳዳቢው ወይም አዋራጁ የሚቀጣው የክስ አቤቱታ ሲቀርብ እንደሆነ ድንጋጌው ይደነግጋል:: ሆኖም "የግል አቤቱታ ሲቀርብበት" የሚለው ሀረግ በየአንቀጹ /፮፻፲፫፣ ፮፻፲፮ እና ፮፻፲፰/ ስለገባ ድንጋጌው ተሰርዟል::

አንቀጽ ፮፻፲፱ <u>የጠፉ ወይም የሞቱ ሰዎችን ክብር የመንካት ወንጀል ሲፈጸም ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፲፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

<u>ርዕስ አራት</u>

<u>በመልካም ጠባይ እና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>በመልካም ጠባይ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>በፆታዊ ሥጋ ነፃነትና ንጽህና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፮፻፳ <u>አስገድዶ መድፈር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳ ሆኖ ገብቷል::

ንዑስ አንቀጽ (፩) ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ከቅጣት አንፃርም ወንጀሉ ከዕለት ወደ ዕለት እየበረከተ በመምጣቱና ቅጣቱ የማስፈራራትና የመግታት ኃይል እንዲኖረው ፈጻሚውም በቀላል ቅጣት እንዳይተው ለማድረግ የቅጣቱ ወለል መነሻ ወደ ሦስት ዓመት ከፍ እንዲል ተደርጓል::

በንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) መሰረት ወንጀሉ የሚያስቀጣው ተበዳይዋ አስራ አምስት ዓመት ያልሞላት እንደሆነ ነው:: በአሁኑ የቤተሰብ ሕግ ግን የጋብቻ እድሜ አስራ አምስት ዓመት መሆኑ ቀርቶ አስራ ስምንት ዓመት ስለሆነና ዕድሜያቸው ከአስራ ሦስት ዓመት በታች የሆኑትን ልጆች በሚመለከት አንቀጽ ፮፻፳፮ ስለተቀረጸ ይህንን አሳብ በሚያካትት መልክ "ዕድሜዋ ከአስራ ሦስት ዓመት በላይ ሆና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላት ሴት ልጅ" እንዲል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

የንዑስ ቁጥር (፪) (ለ) ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጐበታል።

ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) ሲሆን አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) በታ ለቅቆ እና ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ገብቷል። ቅጣቱ መክበድ ያለበት በፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ገብቷል። ቅጣቱ መክበድ ያለበት በፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) ላይ በተገለጹት ሁኔታዎች ብቻ ላይ ሳይሆን "በዕድሜ መግፋት፣ በአካል ወይም በአእምሮ ህመም፣ በመንፈስ ድክመት ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የድርጊቱን ምንነት /ባህርይ/ ወይም ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለይታ ለማወቅ ወይም ለመከላከል በማትችል ሴት ላይ" ወንጀሉ በሚፈጸምበት ጊዜ ጭምር መሆን ስለሚገባው በዚህ መሰረት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ተረቅቆ ገብቷል።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ንዑስ ቁጥር (፪) (ሐ) ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) ሆኖ የገባ ሲሆን "በጭካኔ ወይም በማሰቃየት" የሚል ሐረግ ታክሎበታል። ይህ የሆነበት ምክንያት ጥፋተኞቹ ወንዶች ብዛት ሲኖራቸው ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛው አንድ ወንድ ሆኖ ወንጀሉን የፈጸመው በጭካኔ ወይም በማሰቃየት በሚሆንበት ጊዜም ከባድ ቅጣት ሊቀጣ ስለሚገባው ነው።

አዲስ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የገባ ሲሆን "አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ የዕድሜ ልክ እስራት ይሆናል" በማለት ይደነግጋል። ይህም የሆነው ለወንጀሉ አፈጻጸምና ወንጀሉ ለሚያስከትለው ውጤት ተመጣጣኝ ቅጣት ማስቀመጥ በማስፈለጉ ነው።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንዲገባ ተደርጓል። "ከአስገድዶ መድፈሩ ከወንጀል ጋር ተያይዞ ተበዳዩን ከሕግ ውጭ ይዞ የማስቀመጥ ወይም የመጥለፍ ሌላ ወንጀል የተደረገ ወይም ተበዳይዋ በወንጀሉ ምክንያት በሽታ የተላለፈባት ሲሆን አግባብነት ያላቸው የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።" የሚል ዓረፍተ-ነገር ተረቅቆ ገብቷል። በዚህ መልክ ግልጽ አድርጐ ማስቀመጡ ለክስ አቀራረብና ለቅጣት አወሳሰን ይረዳል ተብሎ ይታመናል።

አንቀጽ ፮፻፳፩ <u>አንድን ወንድ አስገድዶ የግብረሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ማድረግ</u>

አዲስ አንቀጽ ፮፻፳፩ የገባ ሲሆን "አንዲት ሴት አንድን ወንድ አስገድዳ ከእርሷ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ያደረገች እንደሆነ፣" እንድትቀጣ የሚያደርግ ነው። ይህ አዲስ ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት ድርጊቱ በአሁኑ ጊዜ እየተዘወተረ በመምጣቱ ነው።

አንቀጽ ፮፻፳፪ <u>በንጽህና ክብር ላይ የሚፈጸም የኃይል ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፪ ሆኖ ገብቷል።

ለጥፋተኛውና ለሌላው ሰው ትምህርት ይሆን ዘንድ የቅጣቱ መነሻ ከ፫ ወር ወደ ፭ ዓመት ቀላል እስራት፣ ጣራውም ከስምንት ዓመት ወደ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ ብሎአል፤ ድንጋጌው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆንም አንዳንድ የቃላት ለውጥ ደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፳፫ <u>አእምሮአቸውን በሳቱ ወይም የአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፫ ሆኖ ገብቷል።

በዚህ የወንጀል ድርጊት ተጠቂ /ሰለባ/ የሚሆኑት ሰዎች ሊጠነቀቁላቸው የሚገባ ስለሆነና እነዚህ ሰዎች ካሉበት ሁኔታ የተነሳ በቀላሉ ለወንጀል ድርጊቱ ሰለባ ሊሆኑ የሚችሉ፣ ይልቁንም በታመኑባቸውና በአደራ ከሚጠብቁአቸው ሰዎች እንክብካቤን የሚሹ ስለሆነ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ወንጀል ቢፈጸምባቸው ጠበቅ ያለ ቅጣት እንዲያስከትል ታስቦ ቀላል እስራቱ ከ፭ ዓመት እንዳያንስ ጽኑ እስራቱ ደግሞ እስከ አስራ አምስት ዓመት ሆኗል። የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል።

የቀድሞው ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) የአማርኛው ትርጉም ግልጽ ባይሆንም የእንግሊዝኛው ቅጂ ድንጋጌ "The same punishments apply to anyone shown to have committed such an act by misrepresentation" ይላል። ጥፋተኛው የራሱን ማንነት በመደበቅ ወይም በማታለል ድርጊቱን ሲፈጽም በንዑስ ቁጥር (፩) አይሸፈንም የሚባልበት ምክንያት ባለመኖሩና የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

አንቀጽ ፮፻፳፬ <u>ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንጽህና ድፍረት በደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፬ ሆኖ ገብቷል። አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ቅጣቱን በተመለከተ፣ መነሻው ከአንድ ወር ወደ አንድ ዓመት ቀላል እስራት፣ ጣራው ከአምስት ዓመት ወደ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት አድጓል።

አንቀጽ ፮፻፳፭ <u>አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸም ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፭ ሆኖ ገብቷል።

በተለይም "ለክብረንጽህና ተቃራኒ የሆነውን ይህን የመሳሰለውን ስራ" የሚለው ሀረግ ግልጽ ባለመሆኑ ተሰርዞ "የግብረሥጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት" ወይም "ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት" በሚሉ ሁለት ሀረጎች እንዲተካ ተደርጓል፤ ሌላ የቃላት ማስተካከያም ታክሎበታል።

አንቀጽ ፮፻፳፮ <u>ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፬ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፮ ሆኖ ገብቷል።

ከሕገ መንግሥቱና አገሪቱ ከፈረመችው የሕጻናት መብቶች ስምምነት /ኮንቬንሽን/ አንጻር ማናቸውም ለአካለመጠን ያልደረሰ ሰው ማለትም ዕድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ሰው ሁሉ ጥበቃ ማግኘት ስላለበት ይህ አንቀጽ የቀድሞውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፭፻፺፬ ፣ ፭፻፺፭ እና ፭፻፺፮ በመቀላቀል ተቀርጿል። አንቀጹ ዕድሜው አስራ ሶስት ዓመት ሆኖት አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላው ሴትም ሆነ ወንድ ልጅ ጋር

www.abyssinialaw.com

በማታለል ወይም ፈቅደውም ይሁን ወይም በሌላ መንገድ የሚደረግ ማናቸውም የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሚያስቀጣ በግልጽ በሚያመለክት መልክ ተዘጋጅቷል:: ቅጣቱም ከወንጀሉ አደገኛነትና ከልጆች ጥበቃ አንጻር ከፍ እንዲል ተደርጓል፤ "አስራ ሶስት ዓመት ላልሞላቸው ልጆች ልዩ ጥበቃ የሚያደርግ አዲስ ድንጋጌ አንቀጽ ፮፻፳፮ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ የሚከተለው ማሻሻያ ተደርጓል፤ ይኸውም:-

ሀ/ በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ላይ የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ልጅ ላይ የሚፈጽመውን የግብረ ስጋ በደል ብቻ የሚመለከት ነው:: ነገር ግን በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የእንግሊዘኛና የፈረንሳይኛ ቅጂዎች ላይ እንደተመለከተው ድንጋጌው የተገለጸውን ድርጊት ብቻ ሳይሆን አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ልጅ ላይ የምትፈጽመውንም የግብረ ስጋ በደል ሊያጠቃልል ስለሚገባ በንዑስ አንቀጽ አንድ መግቢያ ላይ "ማንም ሰው" ከሚለው ቀጥሎ "ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካለው" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል::

ለ/ "አስራ አምስት ዓመት ባልሞላት ልጅ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ዕድሜዋ ከአስራ ሶስት ዓመት በላይ ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር" በሚል ተስተካክሎአል::

ሐ/ የራሱ ያልሆነ ልጅ የሚለው ሐረግ ተሰርዟል:: ምክንያቱም ከራሱ ሴት ልጅ ጋርም ቢሆን በአንቀጽ ፮፻፳ መሠረት በተደራራቢ ወንጀል ከሚጠየቅ በቀር በዚህ አንቀጽ ስር ከመቀጣት የሚድንበት ምክንያት ባለመኖሩ ነው::

መ/ በንዑስ ቁጥር ፩ ላይ "ግብረሥጋን የመሰለ የወንድና የሴት ግንኙነት" የሚለው ከንዑስ ቁጥር (፩) ላይ ተሰርዞ በንዑስ አንቀጽ (፫) ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል:: ምክንያቱም ይህ ድርጊት በይበልጥ ተቀራራቢነት ያለው በቀድሞው በንዑስ ቁጥር (፪)/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)/ላይ ከተመለከተው ድርጊት ጋር በመሆኑ ነው::

አዲስ የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ የገባ ሲሆን፣ ዕድሜው ከአስራ ሶስት ዓመት በላይ ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ወንድ ልጅ ከእርሷ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ያደረገች ሴት የምትቀጣበት ነው::

የቀድሞው ህግ የቁጥር ፭፻፺፬ (፪) ድንጋጌ ተሻሽሎ የንዑስ አንቀጽ (፫) አካል ሆኗል::

የቀድሞው ህግ የቁጥር ፭፻፺፬ (፫) ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሲሆን በቀድሞው በንዑስ ቁጥር (፫) (ለ) ላይ "የሕግ የጉዲፈቻ ልጅ፣ የእንጀራ ልጅ" የሚለው ሐረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምክንያቱም የጉዲፈቻም ሆነ የእንጀራ ልጅ ከጥፋተኛው ጋር ዝምድና ያለው በመሆኑና ድርጊቱ በአንቀጽ ፮፻፳ መሰረት ስለሚያስቀጣ ይህንኑ ምክንያት ቅጣት ማክበጃ አድርጎ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር መደንገጉ አግባብ ስላልሆነ ነው::

 www.abyssinialaw.com

ቅጣቱን በተመለከተ የቀድሞው የቁጥር ፭፻፺፬ (፫) ቅጣት ተሰርዞ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ከተመለከቱት ወንጀሎች አንጻር፣ አድራጊው በልዩ ልዩ ሁኔታ ከእርሱ ጋር ቅርብ ግንኙነት ካላቸው ልጆች ጋር ድርጊቱን በሚፈጽምበት ጊዜ ቅጣቱ ከብዶ በንዑስ አንቀጽ (፬) ስር ተደንግጓል።

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) የገባ ሲሆን የግብረ ስጋ ጥቃቱ ለአካለ መጠን ባልደረሰው (ባልደረሰችው) ልጅ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ወይም ሞት ባስከተለ ጊዜ አግባብነት ያለው የዚህ ህግ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ እንደሚሆን ይደነግጋል።

አንቀጽ ፮፻፳፮ <u>በሕፃናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል</u>

የዚህ አንቀጽ ስያሜ አዲስ ሲሆን በይዘት ረገድ ግን በቀድሞው ህግ በቁጥር ፭፻፺፬ የተመለከቱትን መደበኛ የግብረ ስጋ ግንኙነትን፣ እንዲሁም ከመደበኛ የግብረ ስጋ ግንኙነት ውጭ የሆኑትን እና ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶችን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ነው።

ወንጀሉንም የሚያደርገው ማንም ሰው ሲሆን ወንጀሉ የሚፈጸምባቸው ልጆች ጾታ ከጥፋተኛው ጾታ የተለየ ነው። ቅጣቱን በሚመለከት የአስራ ሶስት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ዕድሜ ባላቸው ልጆች ላይ ከሚፈጸመው ወንጀል ይልቅ ከአስራ ሶስት ዓመት በታች ዕድሜ ባላቸው ልጆች ላይ ወንጀሉ በሚደረግበት ጊዜ እንዲከብድ ተደርጓል።

የተለየ ቅጣት ማስቀመጡ ያስፈለገበት ምክንያት የአካላቸውም ሆነ የአእምሮአቸው ብስለት ወይም ብቃት ዕድሜያቸው በአስራ ሦስትና በአስራ ስምንት ዓመት መካከል ከሚገኝ ሴት ልጆች ጋር ስለማይመጣጠንና የሚፈጸምባቸው ወንጀል የባሰ ጉዳት ስለሚያደርስባቸው ነው።

ቅጣቱ ከመክበዱ ሌላ አንቀጹ በአምስት ንዑሳን አንቀጾች የተቀረጸው፣ አንቀጽ 626 በተረቀቀበት መልክ ነው። በዚህም አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለጸው ድርጊትም የሚያስቀጣው በዕድሜ ልክ እስራት ነው።

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፭ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

የድንጋጌው ይዘት በአንቀጽ ፮፻፳፮ ስለተካተተ ተሰርዟል።

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፮ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

የድንጋጌው ይዘት በአንቀጽ ፮፻፳፮ ስለተካተተ ተሰርዟል።

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፯ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

የዚህ ሕግ የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ አስፈላጊው የቃላት ለውጥ ተደርጎበትና ተሻሽሎ የአንቀጽ ፮፻፳፩ አካል ሆኖ ገብቷል። /ዝርዝር ምክንያቱ ከተጠቀሰው አንቀጽ ጋር ተያይዞ ይሰጣል።/

www.abyssinialaw.com

የዚህ ሕግ የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ግን እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምክንያቱም ለአካለመጠን ያልደረሰች ልጅ ወደ ወንጀሉ ገፋፍታኛለች የሚል ሁኔታ መከላከያ ሊሆን አይገባም ተብሎ ስለታመነበት ነው::

አንቀጽ ፮፻፴፫ <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ሌሎች ምክንያቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፫ ሆኖ ገብቷል::

ከአንቀጽ ፮፻፴ ጀምሮ ካሉት ድንጋጌዎች ጋር በሚጣጣም መልክ ተረቋል:: ይኸውም:-

ከአንቀጹ መግቢያ ላይ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው አጭርና ግልጽ በሆነ አነጋገር ተረቅቋል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተዘረዘሩት ቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች በአንቀጽ ፮፻፴ ላይ የተካተተ በመሆኑ ተሰርዟል::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የፊደል ተራ (ለ) አነጋገር በሁለት ተከፍሎ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ሆኖ ገብቷል፤ የፊደል (ሐ) ድንጋጌ ግን በመጠኑ ተሻሽሎ በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል:: ቅጣቱም እንዲከብድ ተደርጓል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፭፻፺፱ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

አስገድዶ በመድፈር እና ሌሎች የግብረስጋ ግንኙነት በደል በማድረስ ወንጀል የሚፈጽም ሰው ከወንጀሉ በኋላ ብዙውን ጊዜ ከተበዳይዋ ጋር ጋብቻ እንፈጽም ብሎ መስማማቱ ከክስና ከቅጣት ለማምለጥ እንጂ እውነተኛ ጋብቻ ለመመስረት አስቦ ተበዳይዋን ያገባታል ተብሎ ስለማይታመንና ፈቅዳ በማግባትዋ ክሱ ወይም ቅጣቱ ይሰረዝለት ማለቱ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙትን ወንጀሎች ስለሚያስፋፋ ድንጋጌው ተሰርዟል::

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ለተፈጥሮ ባህሪ ተቃራኒ የሆኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች</u>

አንቀጽ ፮፻፴፬ ግብረ ሰዶምና ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፬ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "አመንዝራነት" የሚለው ቃል አንድ ሰው ከሚስቱ /ከባሏ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ሲኖረው የምንጠቀምበት ቃል ስለሆነና አንቀጹ ላይ የተደነገገውን ወንጀል በሚገባ ስለማይገልጸው አመንዝራነት የሚለው ቃል ተሰርዞ ግብረ ሰዶምና ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶች በሚለው ተለውጧል::

በስያሜው ላይ በተገለጸው ዓይነት በይዘቱም ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ድንጋጌው በወንዶች መካከል ብቻ ሳይሆን በሴቶች መካከል የሚፈጸመውንም ድርጊት እንደሚሸፍን መታወቅ ይኖርበታል:: በተጨማሪም ድንጋጌው

www.abyssinialaw.com

ድርጊት ፈጻሚውን ብቻ ሳይሆን፣ ተስማምቶ ድርጊቱ የሚፈጸምበትንም ሰው ~~ድንጋጌው~~ ያስቀጣል።

የድንጋጌው ሁለተኛ ፓራግራፍ ተሰርዞ በአንቀጽ ፮፻፳፮ ውስጥ ተካትቷል፤ ምክንያቱም እዚያው ይገለፃል።

አንቀጽ ፮፻፴ ወንጀሉን የሚያከብዱ ጠቅላላ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴ ሆኖ ገብቷል።

ቁጥር ፮፻፲፩ (፪) (ለ) የአባለዘር ደዌ የሚለውን ሌሎች በግብረሥጋ ግንኙነት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን ባካተተ መልኩ ተሻሽሏል።

የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) (ሐ) ድንጋጌ ጥቃቱ የተፈፀመው ዕድሜው አስራ አምስት ዓመት ባልሞላው ልጅ እንደሆነ ይገልፃል፤ ሆኖም አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸውን ልጆች ሁሉ በእኩልነት የሚያካትት አዲስ አንቀጽ ፮፻፴፩ ስለተካተተ የፊደል (ሐ) ድንጋጌ ከዚህ ተሰርዞ ቀጥሎ ያለው አንቀጽ እንዲገባ ተደርጓል።

የፊደል (መ) ድንጋጌ በተሰረዘው የፊደል (ሐ) ምትክ እንዲገባ ተደርጓል።

ቅጣቱን ከፍ በማድረግ ጥፋተኛው በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) እና (ለ) ወንጀል ከፈጸመ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቀላል እስራትና ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት፣ ጥፋተኛው በንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ከፈጸመ ከሶስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሆኖ ተሻሽሏል። በተጨማሪም በአንቀጹ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጌበታል።

አንቀጽ ፮፻፴፩ ለአካለ መጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ የሚፈጸም የግብረ ሰዶም ጥቃትና [illegible]

በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፮፻፲፩ (፪) (ሐ) ላይ ዕድሜያቸው አስራ አምስት ዓመት ባልሞላቸው ወንዶች ልጆች ላይ ጥቃት ማድረስ በጥቅሉ እንዲያስቀጣ መደረጉ [illegible] ላይ የሚፈጸመው የግብረሰዶም ጥቃት ከፍተኛ በደል የሚያስከትል [illegible] የሚያመለክት ስለሌለ የወንጀሉን ክብደት ለማጉላት የሚያስችል አዲስ አንቀጽ በማስፈለጉ ሀረጉ ከቀድሞው ቁጥር ፮፻፲፩ (፪) (ሐ) ተሰርዞ በአዲስ መልክ እንዲቀረጽ ተደርጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ በሁለቱም [illegible] ልጆች ላይ የሚፈጸመውን [illegible] የሚመለከት [illegible] (የተበዳዩዋ) ዕድሜ አስራ ሶስት ዓመት ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው (ልሞላት) ሲሆን ከሶስት እስከ አስራ አምስት ዓመት ድረስ፤ የተበዳዩ (የተበዳዩዋ) ዕድሜ ከአስራ ሶስት ዓመት በታች በሚሆንበት ጊዜ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት እንዲያስቀጣ ተደንግጓል። አንቀጹ ወንድ በወንድ ልጅ ላይ ሴት በሴት ልጅ ላይ የሚፈጽሙትን የግብረ ሰዶም ጥቃት ይመለከታል።

www.abyssinialaw.com

[illegible] ነው፤ ይኸውም አንዲት ሴት በሴት ልጆች ላይ የምትፈጽመውን የግብረ ሰዶም ጥቃት የመሰለ ድርጊት የሚሸፍን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በሴቶች መካከል የሚፈጸመውን ሌዝቢያንዝም የተሰኘውን ድርጊት የሚመለከት ድንጋጌ ነው፡፡

አዲስ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (፫) ስር የገባ ሲሆን፣ ማንም ሰው፣ ማለትም ወንድ በወንድ ልጆች ላይ፣ ሴት በሴት ልጆች ላይ፣ ግብረ ሰዶም ወይም ሌዝቢያኒዝም ያልሆነ ሌላ የንጽህና ክብርን የሚቃረን (Indecent) ድርጊትን በሚፈጽምበት ጊዜ የሚያስቀጣ ነው፡፡

የንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፮፻፳፯ (፬) እና ፮፻፳፰ (፬) በተመለከተው አኳኋን የተቀረጸ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) የተገለጸው ወንጀል የተፈጸመበት ልጅ ከጥፋተኛው ጋር በልዩ ልዩ ምክንያት ቅርብ ግንኙነት በሚኖረው ጊዜ በአድራጊው ላይ ቅጣቱን አክብዶ የሚደነግግ ነው፡፡

ንዑስ አንቀጽ (፭) ደግሞ በተበዳዩ ላይ የደረሰው ጥቃት ሞትን ወይም ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን አስከትሎ በሆነ ወይም በጥቃቱ ምክንያት ተበዳዩ (ተበዳይዋ) ራሱን (ራሷን) [illegible] ከሆነ ቅጣቱ እስከ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንደሚያድግ ይደነግጋል፡፡

አንቀጽ ፮፻፴፩ [illegible]

[illegible] የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት [illegible] ድርጊት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት ጊዜ መኖሩን ይደነግጋል፡፡

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወንዶችንም ሆነ ሴቶች ልጆችን [illegible] ለማባለጥ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ [illegible] ድርጊት [illegible] ወይም [illegible] ወይም በሌሎች ስፍራ ለማፈጸም የግብረሰዶም ጥቃት ወይም ግብረስጋ ግንኙነት [illegible] ድርጊት [illegible] ወይም [illegible] የተፈጸመው ድርጊት [illegible] በወንጀል ተጠያቂ [illegible] ይህ አንቀጽ ይደነግጋል፡፡ ቅጣቱም ዕድሜያቸው አስራ [illegible] ዓመትና ከዚያ በላይ በሆናቸው ልጆች [illegible] ዕድሜያቸው ከአስራ [illegible] ዓመት በታች በሆናቸው ልጆች ላይ [illegible] ተደርጎ ተቀርጿል፡፡

አንቀጽ ፮፻፴፪ <u>በእንስሳት ላይ የግብረስጋ ግንኙነት መፈፀም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፪ ሆኖ ገብቷል፡፡ አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፫ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ይህ ድንጋጌ ወደ አንቀጽ ፴፱፣ ፻፴ እና ፻፴፩ የሚመራ ሲሆን ድንጋጌው ባይኖርም ፍርድ ቤቱ በተጠቀሱት አንቀጾች መሠረት ውሳኔ መስጠቱ ስለማይቀር አስፈላጊ አይደለም ተብሎ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሶስት
## በሌላው የሥነ-ምግባር ብልሹነት መጠቀም

ስያሜው ላይ "አመንዝራነት" የሚለው ቃል ከፍ ብሎ በተመለከተው ስያሜ ሲለወጥ ችሏል::

ይህ የሆነበት ምክንያት፣ የሕጉ የእንግሊዝኛው ቅጂ "Exploitation of the immorality of others" ስለሚልና ክፍሉ አመንዝራነትን ብቻ ሳይሆን ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ድርጊቶችንም ስለሚሸፍን ነው::

**አንቀጽ ፮፻፴፩** <u>የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት የዘወትር መጠቀሚያ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ማንኛውም ሰው ገንዘብ ለማግኘት የሚለው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ጥቅሞች ለማግኘት ሲባል ወንጀሉ ሲፈጸም ስለሚችል ገንዘብ የሚለው ጥቅም በሚል ተለውጧል::

አንቀጹ ፮፻፩ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

**አንቀጽ ፮፻፴፪** <u>ሴቶችንና ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፪ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜ ላይ በማከራየት ይል የነበረው ሰውን ማከራየት ሰውን እንደ ዕቃ ማየት /ባርነት/ ስለሚያስመስል ተሰርዟል::

፮፻፪ (፩) የሚለው (፪) ቢኖር ኖሮ ስለነበር ተሰርዟል::
፮፻፪ (፩) ውስጥ ለጥቅም ሲል ከማለቱ በፊት ስሙ (subject) ስላልተጠቀሰ ማንም ሰው የሚል ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

**አንቀጽ ፮፻፴፫** <u>ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፫ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

**አንቀጽ ፮፻፴፬** <u>ሴቶችንና ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት ለማቅረብ የሚደረጉ ዝግጅቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፬ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት መቃናት ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፴፰ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት፣ የወንጀል ተጠያቂነት</u>

ይህ አንቀጽ አዲስ ሲሆን በዚህ ክፍል ከአንቀጽ ፮፻፴፫ እስከ ፮፻፴፯ ውስጥ ከተመለከቱት ወንጀሎች በአንዱ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩን የሚደነግግ ነው።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>በመልካም ጠባይ ላይ የሚፈጽሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፮፻፴፱ <u>ለመልካም ሥነ-ምግባርና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ብልግናና አሳፋሪ ሥራን በአደባባይ መፈጸም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፴፱ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው ውስጥ ክብረ ንጽህና ከማለት ይልቅ መልካም ሥነ-ምግባር ቢባል የተሻለ ስለሆነ ክብረንጽህና የሚለው መልካም ሥነ-ምግባር በሚል ከተለወጠ በኋላ ስያሜው ግልጽ እንዲሆን በማለት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ቅጣቱም የመግታት ውጤት (deterrence) እንዲኖረው መነሻው ሶስት ወር እንዲሁም የንዑስ አንቀጹ ሁለት መነሻ ስድስት ወር ሆኗል።

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፮፻፵ <u>ጸያፍ ወይም የብልግና ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለሕዝብ መግለጽ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ አሳትሞ ስለመግለጽ ይል የነበረው ማሳተም በጽሁፍ መልክ ያሉትን የሚገልጽ ቃል ስለሆነና አንቀጹ በፊልም ወይም በሌሎች ነገሮች የሚገለጹ ነገሮችን ስለሚያጠቃልል "ማሳተም" የሚለው ተሰርዞ "ለሕዝብ መግለጽ" በሚል ተለውጧል።

የቀድሞው የንዑስ ሁለት ድንጋጌ በሁለት ንዑሳን ፊደላት የተከፈለ ሲሆን በንዑስ ፊደል (ሐ) ስር አዲስ ድንጋጌ እንዲገባ ተደርጓል። ይኸውም "ለዚሁ ዓላማ ሲባል ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች የግብረስጋ ግንኙነት የፈጸሙ በማስመሰል ያሳየ ወይም ሀፍረተስጋቸው እንዲታይ ያደረገ እንደሆነ" የሚል ነው።

ይህን ወንጀል የሚፈጽመው ነጋዴ ስለሆነና ስርጭቱም በኅብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው አደጋ ከፍ ያለ ስለሆነ በተለይም የሕፃናትን ስብዕና ሊያበላሽና ሊያጠፋ ስለሚችል የንዑስ አንቀጽ (፩) ቅጣት ከስድስት ወር በማያንስ የንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራት ሆኖ ከመቀጮ ጋር ተጣምሮ እንዲሻሻል ተደርጓል።

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ ፮፻፵፬** <u>ፀያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ማሳየት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፬ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

**አንቀጽ ፮፻፵፭** <u>የተፈቀዱ ሥራዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

ቁጥር ፮፻፲፩ ውስጥ ሳይንሳዊ የሆነ ሥራዎች ያልተገለጹ ስለሆነ ሳይንሳዊ ስራ መልካም ጠባይን እንደነካ መቆጠር ስለሌለበት ሳይንሳዊ የሚል ቃል ተጨምሯል:: አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

**አንቀጽ ፮፻፵፮** <u>ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ መግለጫዎችና ማስታወቂያዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፮ ሆኖ ገብቷል::

ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን የማስተዋወቅ ወንጀል ሕብረተሰቡን የሚነካ ስለሆነ የዐቃቤ ሕግ ክስ ሆኖ እነዚህኑ ነገሮች ወደ ግል መኖሪያ ቤት ከተላኩ ግን የወንጀሉ ግለኝነት (privacy) ባህሪ ስላለው የግል አቤቱታ ሲቀርብ የሚያስከስስ ሆኖ ተሻሽሏል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: ቅጣቱም በአማራጭ ወደ ቀላል እስራት ከፍ ተደርጓል::

**አንቀጽ ፮፻፵፯** <u>ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ሥራዎች መጠበቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፯ ሆኖ ገብቷል::

ሲያሜው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

በፊደል ተራ (ሀ) ውስጥ ህፃናትን ፀባያቸውን ሊያበላሽ ይችላል ተብሎ ከሚገመተው አንዱ የብልግና የቪዲዮ ፊልም ስለሆነ እሱን እንዲጨምር ሆኖ ተስተካክሏል::

በህፃናት ላይ የሚደረግ ወንጀል ስለሆነ ቅጣቱ ከፍ ማለት ስለአለበት ቅጣቱ ከስድስት ወር ባላነሰ እና እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና በመቀጮ በሚል ተሻሽሏል::

**አንቀጽ ፮፻፵፰** <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት፣ የወንጀል ተጠያቂነት</u>

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ ሲሆን በዚህ ክፍል ከአንቀጽ ፮፻፴፱ እስከ ፮፻፵፯ በተመለከቱት ወንጀሎች ረገድ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ተጠያቂ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻል::

www.abyssinialaw.com



## ምዕራፍ ሁለት
## በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ክፍል አንድ
## በጋብቻ ሥርዓት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፮፻፵፮ ጋብቻን በተንኮል ወይም በማታለል መፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፮ ሆኖ ገብቷል።

ንዑስ ቁጥር አንድ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላትን በመሰረዝና የቃላት የአቀማመጥ ለውጥ በማድረግ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ አንድ ሆኖዋል።

ንዑስ ቁጥር ሁለት "የጋብቻው ሥርዓት ካልፈረሰ በቀር ክስ ለማቅረብ አይቻልም" የሚል ሲሆን ከዚህ ለቅቆ የአንቀጽ ፮፻፵፱ አካል ሆኖ ገብቷል። በዚህ መሰረት ንዑስ ቁጥር ሦስት ተሻሽሎ ንዑስ ቁጥር ሁለት ሆኖ ገብቷል።

### አንቀጽ ፮፻፵፯ በሕግ የተከለከለ ጋብቻን ማስፈጸም ወይም መፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፯ ሆኖ ገብቷል።

የወንጀለኛው መቅጫ ሕጉ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጾች ያልተከፈለ አንድ ወንጀልን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ሶስት ንዑስ አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል። አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ያስፈለገበት ምክንያት መቀጣት ያለበት በሕገ ወጥ መንገድ ጋብቻን ያስፈፀመ ባለሥልጣን ብቻ ሳይሆን ከሕግ ውጭ የተጋቡ ለጋብቻው ፍቃዳቸውን የሰጡና በምስክርነት የቀረቡ ሰዎች ጭምር በመሆናቸው ነው።

ንዑስ አንቀጽ (፫) ደግሞ፣ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ድርጊት በቸልተኛነት ሲፈጸም እንደወንጀል ተቆጥሮ የሚያስቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ነው።

### አንቀጽ ፮፻፵፰ ያለ ዕድሜ ጋብቻ

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ ሲሆን ያለዕድሜ ጋብቻን ለመግታት የገባ አንቀጽ ነው። የዚህ ዓይነቱ ጋብቻ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ሴት ልጆች ላይ ብዙውን ጊዜ ከባድ የአእምሮና የአካል ጉዳት የሚያስከትልባቸው በመሆኑ የድንጋጌው መቀረጽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### አንቀጽ ፮፻፵፱ ሕገ ወጥ ጋብቻ መፈፀምና ማስፈፀም በወንጀል የሚያስጠይቅበት ሁኔታ

የዚህ አንቀጽ ሲያሜ አዲስ ሲሆን በአንቀጽ ፮፻፵፮ እና ፮፻፵፯ መሠረት ክስ የሚቀርበው ጋብቻው አስቀድሞ ሲፈርስ ብቻ መሆኑን የሚያሣይ ነው። ፍሬ ነገሩ ከቀድሞው ሕግ ከቁጥር ፮፻፲፬ (፪) የተወሰደ ነው።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፶ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶ ሆኖ ገብቷል።

በአማርኛው ቅጂ በንዑስ ቁጥር አንድ እና በንዑስ ቁጥር ሁለት መሰረት የሚቀጣው ወንዱ ብቻ ነው፤ ወንጀል ፈጻሚዋ ሴት አትቀጣም።, በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ መሰረት ግን ወንጀል ፈጻሚዋ ሴቷ ጭምር ትቀጣለች፤ ትክክለኛው ነገርም ይኸው ነው። በዚህ ምክንያት ወንጀል ፈጻሚው ወንድ ወይም ሴት እንዲቀጡ ተደርጐ ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት ተረቅቋል።

አንቀጽ ፮፻፶፩ የተለየ ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፩ ሆኖ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፍትሐብሔር ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ከተፈጸመ እንደማያስቀጣ ይገልጻል። /የፍትሐብሔር ሕጉ ግን አልፈቀደም/ በጋብቻ ላይ ጋብቻን የሚፈቅደው ግን ማናቸውም ህግ ሊሆን ስለሚችል "አግባብ ባለው ሕግ ..." በሚል ሐረግ ተተክቷል።

አንቀጽ ፮፻፶፪ አመንዝራነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፪ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው ሴሰኝነት የሚለው በትክክል የወንጀሉን አይነት የማይገልጽ ስለሆነና በጋብቻ ታስሮ እያለ ከሌላ ሰው ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ያደረገ ሰው አመነዘረ ስለሚባል ስያሜው አመንዝራነት በሚል ተለውጧል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የአማርኛ ቅጂ ንዑስ ቁጥር (፩) መሰረት ትዳር ያለው ሰው ከሌላ ሰው ጋር ሲያመነዝር እንደሚቀጣ በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ላይ ተገልጿል። ከባለ ትዳሩ ጋር የሚያመነዝረውን ሌላውን ሰው ግን ድንጋጌው አይቀጣም ነበር። በእንግሊዝኛው እና በፈረንሳይኛው ቅጂ መሰረት ሌላው ሰው ትዳር ካለው ሰው ጋር እያወቀ ድርጊቱን ከፈጸመ ይቀጣል፤ ተብሎ በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ተመልክቷል። በዚህ መሠረት የዚህ ዓይነቱ ሰው የሚቀጣበት ድንጋጌ ከንዑስ አንቀጽ (፩) የቅጣት ሀረግ በታች በሚገኝ ፓራግራፍ ላይ ለብቻው ተረቅቆ ገብቷል።

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በንዑስ ቁጥር ሁለት መሰረት ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ይሆናሉ ተብለው የተዘረዘሩት:-

፩ አመንዝራነቱ በተፈጸመ ጊዜ ተጋቢዎቹ አብረው መኖራቸው ቀርቶ እንደሆነ፤

፪ የከሳ አቤቱታ አቅራቢው ራሱ አመንዝራነት ፈጽሞ እንደሆነ፤ ወይም

፫ በሕግ ለመፋታት ወይም ተለይቶ ለመኖር የሚያበቃ ምክንያት ተገኝቶበት እንደሆነ፤ ነው።

ሆኖም ድጋፍ ያገኘው በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተው ሁኔታ ብቻ ነው። በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ተቀባይነት አላገኘም፤ ምክንያቱም የከስ አቤቱታ አቅራቢው ራሱ

www.abyssinialaw.com

ቢያመነዝር ተገቢውን ቅጣት ከሚቀበል በቀር ከሌላው ተጋቢ የአመንዝራነት ድርጊት ጋር የሚመዛዘንበት ወይም የሚካካስበት ምክንያት የለም:: በተራ ቁጥር ሦስት የተመለከተውም በተራ ቁጥር አንድ ከተገለፀው ይሄን ያህል ልዩነት የለውም::

ስለዚህም የመጨረሻዎቹ ሁለት ምክንያቶች ተሰርዘው፣ የመጀመሪያው ምክንያት ብቻ እንዲገባ ተደርጎ ተረቅቋል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ንዑስ ቁጥር (፫) ላይ፣ ቅጣቱ የሚከብደው ክርስቲያን በሆነ ወንጀል አድራጊ ላይ ነው:: ሆኖም ሳይፋታ ወይም ሌላው ተጋቢ ጥሎት ሳይሄድ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ውሽማ የሚያስቀምጥ ክርስቲያን ይሁን ማንኛውም ሌላ ሃይማኖት ያለው ወይም የሌለው ሰው ከባድ ቅጣት እንዲቀጣ የሚያደርግ ሆኖ ተረቅቆ ገብቷል::

አንቀጽ ፮፻፶፫ <u>የአቤት ባዩ መሞት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ አንድ ፓራግራፍ ብቻ የነበረው ሲሆን ይህ አንቀጽ ሁለት ፓራግራፎች እንዲኖሩት ተደርጓል::

የመጀመሪያው ፓራግራፍ የቀድሞው ህግ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ሲሆን ግልጽ እንዲሆን፤ "ተበዳዩ የግል አቤቱታ ሳያቀርብ የሞተ እንደሆነ፤ ጥፋተኛው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም::" ተብሎ ተቀርጿል:: ይህ ግን የሟቹን ቅርብ ዘመዶች የግል አቤቱታ የማቅረብ መብት እንደሚያግድ ተደርጎ መወሰድ የለበትም::

የቀድሞው ድንጋጌ ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር የዚህ አንቀጽ ሁለተኛ ፓራግራፍ የተደረገ ሲሆን የቃላት ማስተካከያና የሃሳብ መቃናት ተደርጎበታል:: በተለይም ፋተኛው ቤተሰብ የማስተዳደር ወይም የመደገፍ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ በጥፋቱ ምክንያት የእስራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ይሰርዝለታል:: የሚለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው፣ ተበዳዩ የግል አቤቱታ ካቀረበ በኋላ በሚሞትበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሕይወትም ባለበት ጊዜ ጭምር መሆን ስለአለበት፣ "ተበዳዩ ቢሞትም ባይሞትም" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት መስተካከል ተደርጎበታል::

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ይህ አንቀጽ ሴሰኛው ወንጀል የፈጸመው አስራ አምስት ዓመት ባልሞላት ልጅ ላይ ከሆነ በተደራቢነት የቀድሞው ቁጥር ፭፻፺፱ (የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፳፮ እና ፮፻፳፯) እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል:: ሆኖም ይህንና ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን አጠቃሎ የያዘ አዲስ አንቀጽ ፮፻፳ ስለተቀረጸ አንቀጹ ከዚህ ተሰርዟል::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## በዘመዳሞች መካከል የሚፈጸም የግብረሥጋ ግንኙነት ወንጀል

ስያሜው ውስጥ ዝሙት የሚለው ከአንቀጽ ፮፻፵፯ ጀምሮ ካሉት ወንጀሎች ጋር እንዳይመሳሰል በማለት ዝሙት የሚለው ተሰርዞ የግብረሥጋ ግንኙነት በሚል ተሻሽሏል፡፡

### አንቀጽ ፮፻፶፬ በዘመዳሞች መካከል የሚፈጸም የግብረ ስጋ ግንኙነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፬ ሆኖ የገባ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

ስያሜው ውስጥ ዝሙት የሚለው ከላይ /ክፍል ሁለት ርዕስ/ በተዘረዘረው ምክንያት ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ንዑስ ቁጥር ሁለት ፓራግራፍ ሁለትና ሦስት የሚደነግጉት፣ ወንጀሉ የተፈጸመበት ልጅ በወንጀል ስለማይጠየቅበት ሁኔታና ለጥበቃው ስለሚወሰደው እርምጃ ሲሆን ከዚህ ተሰርዞ አጠቃላይ አሳብ በያዘው በአንቀጽ ፮፻፷፩ ተካቷል፡፡

### አንቀጽ ፮፻፶፭ በዘመዳሞች መካከል የሚፈጸም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ የብልግና ድርጊት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ መሰረት ወንጀሉ የሚያስቀጣው የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መሀከል ድርጊቱ ሲፈጸም ነው፡፡ የጋብቻ ዝምድና ያላቸውንም ሰዎች ድርጊት ማጠቃለል ይገባዋል ተብሎ በዚሁ መሰረት ተሻሽሎ ተረቅቆ ነበር፡፡ ሆኖም ሀሳቡ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ሳይካተት ቀርቷል፡፡

አንቀጹ ለአካለመጠን በደረሰ ወይም በሕፃን ላይ ወንጀሉ ሲፈጸም እንዲያስቀጣ ተደርጐ ነበር፡፡ ሆኖም ለአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ የሚፈጸመው ወንጀል በዚህ አንቀጽ ስር መካተቱ ቀርቶ ተመሳሳይ አጠቃላይ አሳብ በያዘው በአንቀጽ ፮፻፷ ተካትቶ ተረቅቋል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሁለተኛ ፓራግራፍ ላይ ድርጊቱ "በሕዝብ ላይ አስነቃፊ ነገርን" የፈጠረ እንደሆነ የሚል ተጨማሪ ማሟያ ነጥብ ሆኖ እንደሚያስቀጣ ተገልጿል፡፡ ሆኖም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ግብረሥጋን የመሰለ ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት እንደተፈጸመ ከታወቀና ከተረጋገጠ በሕዝብ ዘንድ ማስነቀፉ ግልጽ ስለሆነ የሐረጉ መኖር አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል፡፡

ስለዚህ ከላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት አላስፈላጊ የሆኑ ሐረጐች ተሰርዘው አስፈላጊ የሆኑ ቃላት ታክለው አንቀጹ ተረቅቋል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሶስት
## በክብር መዝገብ ላይ እና የቤተዘመድ ግዴታዎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

**አንቀጽ ፮፻፶፭ የህፃን መወለድን ወይም ተጥሎ መገኘትን አለማስታወቅ**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው ውስጥ አንዳንድ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል፡፡

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

**አንቀጽ ፮፻፶፮ የክብር መዝገብን በሀሰት መለወጥ፣ አስመስሎ ሕፃንን ማቅረብ ወይም መለወጥ**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው ውስጥ ከተባለው መዝገብ ስለ መሰረዝ የሚለው በአንቀጹ ይዘት ውስጥ ስለ መዝገብ መሰረዝ የሚገልጸው ነገር ስለሌለ ተሰርዟል፡፡

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽነት እንዲኖረው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

**አንቀጽ ፮፻፶፰ የቀለብ መስጠት ግዴታን አለመፈጸም**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፰ ሆኖ ገብቷል፡፡
ስያሜው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ንዑስ ቁጥር (፩) የፈታትም ብትሆን ለሚስቱ ሊሰጥ የሚገባውን ቀለብ አልሰጥም ያለ የሚለው ቀለብ መስጠት ፍቺ ላይ ስለሚያቆም ተሰርዞ የፍቺ ጥያቄ ሳቀረበ የትዳር ጓደኛም ቢሆን በሚል ተለውጧል፡፡

ንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብራው ለኖረች ሴት የሚል ተጨምሮበታል፡፡ ምክንያቱም በዚህ አይነት ግንኙነት አብራው ለኖረች ሴት ሰውየው የተወሰኑ ግዴታዎች እንዳሉበት የፍትሐብሔር ሕጉ ስለሚደነግግ ነው፡፡

አንቀጹ በዚህ መልክ ተስተካክሏል፡፡

**አንቀጽ ፮፻፶፱ የልጅ ማሳደግ ግዴታን አለመፈጸም**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፶፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

ንዑስ ቁጥር (፩) ጥቅምን በመፈለግ እና ያለበትን ግዴታ ቸል በማለት የሚለው ጥቅምን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን በተለያየ ምክንያት ግዴታውን ቸል ሊል ስለሚችል "እና" የሚለው ተሰርዞ "ወይም" ሆኖ ተስተካክሏል፡፡
አንቀጹ ከላይ በተገለጸው አኳያ ተስተካክሏል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የወል ድንጋጌዎች

ይህ አዲስ ምዕራፍ የወል ድንጋጌዎችን ይዟል:: እነዚህ አንቀጾች የተረቀቁበት ምክንያት በየቦታው ተበታትነው የነበሩትንና እንዲሰረዙ የተደረጉትን ድንጋጌዎች በአንድነት የሚያካትት አጠቃላይ መመሪያ ማስፈር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፤ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ነው::

አንቀጽ ፮፻፷ <u>የወንጀሎች መደራረብ</u>*

ወንጀሎች የሚደራረቡበት ሁኔታ በሦስት መንገድ ተከፍሏል::

ድርጊቱ አንድ ሆኖ ከአንድ በላይ በሆኑ ጣምራ ወንጀሎች የሚያስከስስበት እና የሚያስቀጣበት ሁኔታ፣ በአንቀጽ ፮፻፳፫-፮፻፳፱ ወይም ፮፻፶፬ ወንጀሎች ላይ ሊከሰት ይችላል:: ለምሳሌ ሴሰኛው የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመው ከስጋ ዘመዱ ጋር ሊሆን ይችላል:: በዚህ ጊዜ አንቀጽ ፮፻፶ እና አንቀጽ ፮፻፶፬ በተደራራቢነት ይጠቀሱበታል ማለት ነው::

በስጋ ዝምድና አንቀጽ ፮፻፶፫ የተሳሰሩ ሰዎች አስገድደው ቢደፍሩ አንቀጽ ፮፻፳ ወይም ልዩ ልዩ የግብረ ስጋ በደሎችን ቢያደርሱ ፮፻፳፫-፮፻፳፰ አንቀጽ ወይም ድርጊቱ የተፈጸመው በአደባባይ ከሆነ አንቀጽ ፮፻፴፱ ጋር ሊጣመር ይችላል ማለት ነው::

የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መሀከል ግብረ-ሥጋን የመሰለ ግንኙነት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ሲፈጸም ከአንቀጽ ፮፻፶፭ በተጨማሪ አንቀጽ ፮፻፳፮-፮፻፴፮ እና ፮፻፴፱ ሊያስቀጡ ይችላሉ::

እነዚህን ሁሉ ሀሳቦች እንዲያካትት ተደርጎ አንቀጽ ፮፻፷ በሦስት ንዑስ አንቀጾች ተከፍሎ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፮፻፷፩ <u>ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች የወንጀል ተጠያቂነት</u>

ወንጀሉ ለአካለመጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ ሲፈጸም እነዚህ ልጆች ስለማይጠየቁበትና ስለሚጠየቁበት ሁኔታ የሚደነግግ አንቀጽ ነው::

ለአካለመጠን ያልደረሰው ተታላይ የማይቀጣ መሆኑን የሚያመለክቱት የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፭፻፶፪/፩ የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ፶፫ (፪) የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር፣ ፮፻፴፮ (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ሕፃናትን የሚመለከቱት ሐረጎች ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ላይ ተሰርዘው በአንድነት ተካትተው በንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የገቡ ሲሆን ተጠያቂ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው::

ለአካለመጠን ያልደረሰው ተታላይ የማይቀጣ ቢሆንም ቁጥር ፭፻፶፪ (፩) ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ቁጥር ፶፫ (፪) ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር እና ፮፻፴፮ (፪) ሦስተኛው ፓራግራፍ ያስቀመጡት አሳብ በአንድነት ተዋህዶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሁለተኛው ፓራግራፍ ሆኖ የገባ ሲሆን ወንጀሉ በተፈጸመበት ለአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ

* በወንጀል ህጉ አንቀጽ 560 በንዑስ አንቀጽ 1 "ተጣምሮ ሲገቱ" የሚለው ቃል "ተጣምሮ ሲገኝ" ተብሎ ይነበብ::

www.abyssinialaw.com

"ተስማሚ የሆኑት የመልካም አስተዳደግና የጥበቃ ውሳኔዎች በእርሱ ላይ ሊፈጸሙ ይችላሉ" የሚል ነው።
አዲስ አሳብ የያዘ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የገባ ሲሆን "በሌሎች ሰዎች ላይ ወንጀሉን የፈጸመው ለአካለመጠን ያልደረሰ ሰው የዚህ ሕግ መደበኛ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል (አንቀጽ ፶፪-፶፮)" የሚል ነው። ይህ ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከእርሱ በእድሜ ባነሱም ሆነ በበለጡ ሰዎች ላይ በኃይል፣ በተንኮል ወይም በተመሳሳይ መንገድ ወንጀል ሲፈጽም ተጠያቂ ሲሆን መቻሉን ለማመልከት ነው።

## ስድስተኛ መጽሐፍ
## በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

በሀብቶች ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች ከሚለው ይልቅ አሁን እየተለመደ የመጣው ንብረት የሚለው ቃል ስለሆነና ንብረት በሰዎችና በዕቃዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ስለሆነ ሀብቶች የሚለው ንብረት በሚል ተለውጧል።

## ርዕስ አንድ
## በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች
### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ ፮፻፷፱ መርህ**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፱ ሆኖ የገባ ሲሆን፣ የድንጋጌው ስያሜ መሰረቱ የሚለው መርህ በሚል ተቀይሯል።

ንዑስ አንቀጽ (፩) "በሌላ ሰው....." በሚል እንዲጀምር የተደረገው የግለሰብንና የመንግሥትን ንብረት እንዲያጠቃልል በማለት ነው።

አንቀጹ በተጨማሪም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

**አንቀጽ ፮፻፸ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ወይም ያለአግባብ የመበልጸግ ግምት**

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜው ውስጥ መክበር የሚለው የተለመደው የሕግ ቃል መበልጸግ ስለሆነ መክበር የሚለው ቃል መበልጸግ በሚል ተለውጧል። የአንቀጹም ይዘት በስያሜው መሰረት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጹ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፮፻፷፬ <u>በቤተዘመድ አባሎች መካከል ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ የሚቀርብ ክስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

በስያሜው ውስጥ "በቤተ ዘመድ አባሎች በኩል" የሚለው በቤተዘመድ አባሎች መካከል የሚደረግን ወንጀል ለመግለጽ ተፈልጎ ስለሆነ እንግሊዝኛው ቅጂም "within" ስለሚል "በኩል" የሚለው "መካከል" በሚል ተቀይሯል፡፡

ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ላይ የእንጀራ ልጅ የሚል ቃል ተጨምሯል ምክንያቱም በሕብረተሰቡ እየተለመደ የመጣ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ሕጋችን በእናት ልጅ ብቻ ወይም በአባት ልጅ ብቻ (half blood) የሚል ልዩነት ስለማይፈጥር በእናት ወይም በአባት ወይም በሁለቱም በሚገናኙ ልጆች በሚል ተስተካክሏል፡፡

ከዚህም በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) እና በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የሃሳብ መቃናትና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>
<u>በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>
<u>በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፮፻፷፭ <u>ስርቆት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

የቀድሞው ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል፡፡

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲገባ የተደረገ ሲሆን ከማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ተንቀሳቃሹን ንብረት የነጠለው ራሱ ሌባው ከሆነና ዕቃውን ሲነጥል በተንቀሳቃሹ ወይም በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ከስርቆት ወንጀል በተጨማሪ ንብረት በማፍረሱ፣ በማበላሸቱ፣ በማውደሙ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ንብረቱ ለባለቤቱ አገልግሎት በማይሰጥበት ሁኔታ ጉዳት በማድረሱ ከአንቀጽ ፮፻፹፱ እስከ ፮፻፺፩ ባሉት ድንጋጌዎች ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህም የሆነው አድራጊው ከማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተነጠለን ተንቀሳቃሽ ዕቃ በመስረቁ ብቻ ሳይሆን ንብረቱን ሲነጥል ጉዳት በማድረሱ ጭምር መከሰስና መቀጣት እንዳለበት ለዓቃቤ ሕጎችና ለዳኞች ግልጽ ለማድረግ ነው፡፡

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፩ ድንጋጌ አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎበት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ራሱን የቻለ አንቀጽ መሆኑ እንዲቀር ያስፈለገበት ምክንያት "ቀላል የሆነ ስርቆት" የሚል ስያሜ ቢኖረውም ወደ ደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች ከማመላከት በቀር ቅጣት የማይደነግግና መርህ የማያስቀምጥ በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ቀላል ስርቆትን ከተራ (Ordinary) ስርቆት በንጽጽር ለይቶ

ማስቀመጡ፣ ድርጊቱ ደንብ መተላለፍ እንጂ ወንጀል አለመሆኑን በቀላሉ ለማሳየት ስለሚረዳ የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፮፻፴ ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሊሆን ችሏል።

አንቀጽ ፮፻፷፮ <u>ኃይልን መስረቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፮ ሆኖ ገብቷል።

በስያሜው ውስጥ የሥራ ኃይል ያለው የተፈጥሮ ሰው ስለሆነ የሥራ የሚለው ተሰርዟል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፮፻፷፯ <u>የጋራ ንብረት የሆኑትን ዕቃዎች መስረቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፯ ሆኖ ገብቷል።

ንዑስ ቁጥር (፩) በህብረት ባለሀብትነት የሚለው Co-ownership ለማለት ተፈልጎ ስለሆነ በጋራ ባለሀብትነት በሚል ተለውጧል።

አንቀጹ ሌላ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፮፻፷፰ <u>በሙታን ላይ የሚፈጸም ስርቆት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፰ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜም ሆነ በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ለውጥ የተደረገ ሲሆን ከተቀበረ አስከሬን ብቻ ላይ ሳይሆን ካልተቀበረውም ቢሆን ንብረት ሲሰረቅ መቻሉን በሚያሳይ መልክ ተቀርጿል።

<u>የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፮፻፴፬ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

የድንጋጌው ስያሜ "ቀላል የሆነ ስርቆት" የሚል ሲሆን ይዘቱ ወደ ደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች የሚያመላክት ከመሆኑ በቀር የተለየ ጥቅም የሌለው በመሆኑ ራሱን የቻለ አንቀጽ መሆኑ ቀርቶ "ስርቆት" ን የሚመለከተው የአንቀጽ ፮፻፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሆኖ ገብቷል።

አንቀጽ ፮፻፷፱ <u>ከባድ ስርቆት</u>*

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፷፱ የተደረገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

በድንጋጌው መግቢያ ላይ መነሻ ቅጣቱ ከስድስት ወር ወደ አንድ ዓመት ቀላል እስራት፣ ጣራ ቅጣቱ ከአስር ዓመት ወደ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ እንዲል ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት የቀድሞው ቅጣት ለከባድ ስርቆት ያንሳል ተብሎ በመታመኑ ነው።

---

* በወንጀል ህጉ አንቀጽ 669 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ "የሚገቋ" የሚለው ቃል "የሚገኙ" ተብሎ ይነበብ።

www.abyssinialaw.com

በንዑስ ቁጥር (፩) (ሀ) ላይ "የተሰረቁት ዕቃዎች በቤተክርስቲያኖች የሚገኙ ንዋየ ቅዱሳት ወይም የቤተክርስቲያን ዕቃዎች" ሲሆኑ እንደከባድ ስርቆት የሚቆጠር መሆኑ ተገልጿል:: ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች በሕገ መንግሥቱ እኩል ስለሆኑ "የሃይማኖት ሥርዓት በሚፈጸምበት ስፍራ ውስጥ የሚገኙ.....ዕቃዎች" በሚል ተሻሽሏል::

የቀድሞ ሕግ የንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) ድንጋጌ ተሻሽሎ፣ "ለቴሌኮሙኒኬሽን፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል፣ ለውሃና ፍሳሽ ወይም ለማናቸውም ሌላ ድርጅት አገልግሎት የሚውሉ ጠባቂ የሌላቸው መሣሪያዎች ወይም ዕቃዎች" የሚል ሐረግ እንዲገባ ተደርጎአል:: በአሁኑ ጊዜ በተዘረዘሩት ዕቃዎች ላይ የስርቆት ወንጀል እየተስፋፋ በመምጣቱ ሁኔታውን የሚሸፍን ግልጽ ድንጋጌ እንዲኖር በማስፈለጉ ንዑስ አንቀጹ ሊሻሻል ችሏል::

ቁጥር ፮፻፴፮ (፪) (ሀ) ወታደር ሆኖ ሌብነቱ ጉዳት ያደረሰው በቤታቸው ባረፈባቸው ወይም በማደሪያቸው በሰፈረባቸው ሰዎች ላይ የሆነ እንደሆነ የሚለው በአሁኑ ጊዜ ወታደሩ የተመደበለት በጀት ያለው ስለሆነ ተሰርዟል::

የንዑስ ቁጥር (፫) (ሀ) ድንጋጌ ስርቆትን ወይም ሌሎች ንብረት ነክ ወንጀሎችን ሙያው አድርጎ የያዘን ልማደኛ ሌባን የሚመለከት ሲሆን እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ልማደኛ ሌባ ምንጊዜም ቢሆን ከአስር ዓመት ፅኑ እስራት በላይ የማይቀጣ ሆኖ ሳለ ከዚህ ቀደም ባንድ ንብረት ነክ ወንጀል ከተቀጣ በኋላ አንድ ነጠላ የስርቆት ወንጀል የፈጸመ ሌባ ስለደጋገሚነት በተደነገገው በቀድሞው ህግ በቁጥር ፻፯፫ በአሁኑ በአንቀጽ ፻፹፰ መሠረት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ማድረግ የሚችል በመሆኑና ይህም ከልማደኛ ሌባ ይልቅ ጥቂት ጊዜ የሰረቀውን ሌባ በይበልጥ የሚቀጣ በመሆኑ ቅራኔውን ለማስቀረት በማሰብ ነው::

በዚህ መልክ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፬) (ሀ) ሲሰረዝ በፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ስር ያሉት ድንጋጌዎች ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ) እና (ለ) ሆነው ገብተዋል:: የቀድሞው የፊደል ተራ (ለ) አነጋገር "የነዚህን አይነት ወንጀሎች ለመስራት በተቋቋመ ማህበር አባልነት ሰርቆ እንደሆነ" የሚለው "በሰዎች ወይም በንብረት ላይ ወንጀል ለመፈጸም የተቋቋመ ቡድን አባል ሲሆን" በሚል ተተክቶ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ) ሆኖአል:: በንብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ላይም ወንጀል ለመፈጸም የተቋቋመ የቡድን አባል ከሰረቀ እንደ ከባድ ስርቆት የማይቆጠርበት ምክንያት ስለሌለ በዚህ መልክ በድንጋጌው ላይ ማሻሻያ ተደርጓል::

ከዚህም በላይ በጠቅላላው ድንጋጌ ላይ እንደአስፈላጊነቱ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት አንቀጹ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፮፻፸ ውንብድና

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸ ሆኖ ገብቷል::

ስለ ወንበዴነት በሚደነግገው በቀድሞው ሕግ በቁጥር ፮፻፴፮ ላይ የኃይል ተግባሩ የሚፈጸመው "የስርቆት ወንጀል ለመስራት አስቦ ወይም በስርቆት ወንጀል ተይዞ ወይም ደግሞ በስርቆት ያገኘውን ነገር ለመሰወር በማሰብ" እንዲሆን ተመልክቷል፣ ይህም የወንበዴነት ወንጀል ተደርጓል የሚባለው ስርቆትና የኃይል ተግባር ተጣምረው ሲገኙ መሆኑን ያሳያል:: ሆኖም አንድ ሌባ የስርቆት ወንጀል የሚፈጽመው ባለ ንብረቱ ወይም

www.abyssinialaw.com



ሌላ ሰው እንደማያየው ወይም እንዳማይዘው በማረጋገጥ ስለሆነ የሰውን ንብረት ከመውሰድ ጋር የኃይል ተግባር ከተጣመረ የንብረት አወሳሰዱ ስርቆት መሆኑ ይቀራል፤ ምክንያቱም ስርቆት ማለት አዩኝ አላዩኝ ብሎ ንብረት መውሰድ ነውና።

ስለዚህ ስርቆት እና የኃይል ተግባር ሊጣመሩ እንደሚችሉ አድርጎ መደንገጉ የሚፈጥረውን ግራ መጋባት ለማስቀረት ሲባል ተደጋግሞ የተጻፈው "ስርቆት" የሚለው ቃል ከድንጋጌው ላይ ተሰርዟል።

በቀድሞው ድንጋጌ መግቢያ ላይ በነበረው ሐረግ ምትክም "ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ፣ የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ ያጋጠመውን ተቃውሞ ውጤታማነት ለማስቀረት ሲል፤.." የሚል ሐረግ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ እና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል።

## አንቀጽ ፮፻፸፩ ከባድ ውንብድና

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፩ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው በእንግሊዝኛ ቅጂ መሠረት የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን የንዑስ ቁጥር አንድ (ለ) ድንጋጌ ተሰርዞ እንደ ቅደም ተከተላቸው ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ሆነው ገብተዋል። ፊደል ተራ (ለ) ሊሰረዝ የቻለው፣ ድንጋጌው ልማደኛ ወንበዴነትን ተሚመለከት ሲሆን ልማደኛ ስርቆትን የሚመለከተው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፮ ንዑስ ቁጥር (፪) (ሀ) በተሰረዘበት ምክንያት ነው።

## አንቀጽ ፮፻፸፪ ዘረፋ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፪ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቀላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## አንቀጽ ፮፻፸፫ የባህር ውንብድና

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፫ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## አንቀጽ ፮፻፸፬ ልዩ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፵ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፬ ሆኖ ገብቷል።

የሰዎችን መብት ተቃራኒ በሆነ አኳኋን የሚለው ምን ጊዜም ቢሆን ውንብድናን፣ ዘረፋ ወይም የባህር ውንብድናን የሚፈጽሙ ሰዎች የሰውን መብት በመጋፋት የሚፈጽሙት ወንጀል ስለሆነ የሰዎችን መብት ተቃራኒ በሆነ አኳኋን የሚለው ተሰርዟል።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፮፻፸፭ <u>እምነት ማጉደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፭ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) ላይ ያሉት ዝርዝር ነገሮች በንዑስ ቁጥር (፩) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከቱት ፍሬ ሃሳቦች ጋር ስለተዋሃዱ የንዑስ ቁጥር (፩) ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መክፈሉ ቀርቷል::

የወንጀሉን አፈጻጸም በሚመለከትም "ለራሱ ያደረገ እንደሆነ" ወይም "ለግል ጥቅሙ የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ያደረገ እንደሆነ" በሚሉት ሀረጎች ብቻ ሳይወሰን "ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ በሚል አገላለጽ ተስፋፍቶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተረቅቋል::

ከዚህም በላይ በድንጋጌው በሶስቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያና የአሳብ መቃናት የተደረገባቸው ሲሆን በተለይ የንዑስ ቁጥር (፫) ድንጋጌ በእንግሊዘኛው ቅጂ መሠረት እንዲሻሻል በማድረግ አንቀጹ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፮፻፸፮ <u>ከባድ የእምነት ማጉደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፮ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ በስሩ በአራት ተራ ፊደሎች የተከፈሉ ድንጋጌዎች የነበሩት ሲሆን በፊደል ተራ (መ) ላይ የሰፈሩት ጉዳዮች አሳብ በዚህ አንቀጽ አዲስ ሆኖ በገባው ንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ የተሸፈኑ በመሆኑ ተሰርዟል::

በቀድሞው በቁጥር ፮፻፴፪ (ለ) ላይ የመንግሥት ስራንና የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ይመለከት የነበረው ሐረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተካተተ በመሆኑ ከፊደል ተራ (ለ) ተሰርዟል:: በመሆኑም አንቀጹ በሁለት ንዑስ አንቀጾች እንዲከፈል ተደርጓል::

ይኸውም የቀድሞው ድንጋጌ የቁጥር ፮፻፴፪ (ሀ) በአሁኑ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ)፣ የቀድሞው ፊደል (ለ) ደግሞ በአሁኑ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) ስር እንዲመጣ የተደረገ ሲሆን፣ የቀድሞው የቁጥር ፮፻፴፪ (ሐ) ድንጋጌ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት (ሐ) ሆኖ ገብቷል::

ቅጣቱን በተመለከተ አዲሱ የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ መነሻ ቅጣቱን ወደ አንድ ዓመት ቀላል እስራት፣ ጣራ ቅጣቱን ወደ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በማሳደግ እንዲያስቀጣ ተደርጎ ተቀርጿል::

ከዚህም በላይ ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የሃሳብ መቃናትና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com



ንቀጽ ፮፻፸፮ <u>በመንግሥት ወይም በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን</u>

ይህ ድንጋጌ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ ያልነበረ ሲሆን በመንግሥት እና በሕዝብ ንብረት ያለአግባብ መገልገልና ማባከንን እንደ ወንጀል መቁጠር አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ሁኔታ የሚሸፍን አዲስ አንቀጽ ፮፻፸፮ ሆኖ ገብቷል:: ድንጋጌው ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን ድርጊቱ የተፈጸመው ታስቦም ሆነ በቸልተኛነት እንዲያስቀጣ የሚያደርግ ነው::

<u>የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፮፻፴፪ እና ፮፻፴፩ የአቀማመጥ ለውጥ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፮፻፴፩ (የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፭) ስያሜ "በሌላ ሰው ሀብት ያለአግባብ መገልገል" የሚል ሲሆን "በመንግስት ወይም በህዝብ ንብረት ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን" የሚል ስያሜ ካለው ከአንቀጽ ፮፻፸፮ ጋር ተቀራራቢነት ስላለው ቀጥሎ እንዲገባ ተደርጐአል:: የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፮፻፴፪ ድንጋጌ ደግሞ አንቀጽ ፮፻፸፯ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጽ ፮፻፸፭ <u>በሌላ ሰው ሃብት ያለአግባብ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፭ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ግልጽ በሆነና አጠር ባለ መልኩ ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፮፻፸፯ <u>አግኝቶ መደበቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፯ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹ በፊደል ተራ (ለ) ውስጥ "በመጠጋቱ ምክንያት በእጁ ስለገባ የራሱ ያደረገ እንደሆነ" የሚለው የእንግሊዝኛው ቅጂ ግልጽ ስለሆነ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት የገባ አዲስ ሀረግ ነው::

በተጨማሪም ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፮፻፸፰ <u>ወድቆ የተገኘን ንብረት ለራስ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፴፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፸፰ ሆኖ ገብቷል::

ቁጥር ፮፻፴፫ (፪) የቦታ ባለቤት የሚለው ቦታ በግል የመያዝ መብት ቀርቶ የመገልገል መብት ብቻ ስላለና በመሬት ላይ የሚገኘው ንብረት የመንግሥት ስለሆነ ተሰርዟል::

ተደብቆ ወይም ተቀብሮ የሚገኘው ንብረት ገንዘብ ብቻ ሳይሆን እንደ ወርቅ እንቁ ያሉም ስለሚሆን ይህንን እንዲያካትት ተደርጓል::

አንቀጹ ከዚህ በተጨማሪም ቅጣቱ ወደ ብር አምስት ሺህ ከፍ እንዲል ሆኖ ተገቢው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፮፻፹፩ <u>ባለቤት የሌለውን ዕቃ ወይም የተፈጥሮ ሀብትን መውሰድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፵፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

በአንቀጹም ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

አንቀጽ ፮፻፹፪ <u>መሸሸግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፵፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፪ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ "..... ዕቃው የተገኘው ባንድ ንብረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ምክንያት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ የሚገባው ሆኖ....." ይህንን ንብረት የሸሸገ ሰው እንደሚቀጣ ተደንግጎ ነበር:: "ማወቅ የሚገባው ሆኖ" የሚለው አነጋገር ማወቅ ወይም መገመት ነበረበት ማለት ነው:: ይህም አድራጊው እያወቀ ወይም አስቦ ሳይሆን በቸልተኝነት ድርጊቱን እንደፈጸመ ያመለክታል::

ድርጊቱን በቸልተኝነት የፈጸመው ሰው እያወቀ ወንጀሉን ካደረገው እኩል መቅጣቱ ተገቢ አይደለም:: ስለዚህም በቸልተኝነት ድርጊቱን የፈጸመ ሰው የሚቀጣበት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሶስት እንዲገባ ተደርጓል:: በመሆኑም የቀድሞው ንዑስ ቁጥር (፫) እና (፬) የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ሆነው ገብተዋል::

በተጨማሪም አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፮፻፹፫ <u>ከባድ የመሸሸግ ወንጀል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ በአራት የፊደሎች ተራ የተከፈለ ነበር ሆኖም የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ስለተሰረዘ የፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች ተሸጋሽገው ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ስር እንዲመጡ ተደርጓል::

የፊደል (ለ) ድንጋጌ የተሰረዘው በቀድሞው ድንጋጌ በቁጥር ፮፻፵፱ ንዑስ ቁጥር (፫) (ሀ) ላይ ልማደኛ ሌብነትን የሚመለከተው ሀረግ እንዲሰረዝ በተደረገበት ምክንያት ነው:: ልማደኛ ሸሻጊ ከቀድሞው ሕግ ይልቅ በደጋጋሚነት በአንቀጽ ፻፹፰ መሠረት የበለጠ ቅጣት እንዲወሰንበት ማድረግ ስለሚቻልና ይህም ተገቢ ስለሆነ በዚህ ምክንያት የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ሊሰረዝ ችሏል::

በቀድሞው ድንጋጌ ላይ "የተሰረቀው ዕቃ" የሚለው ሀረግ በተደጋጋሚ ተጽፎ ይታያል:: ሆኖም ዕቃው የተገኘው በስርቆት ብቻ ሳይሆን በሌሎች በርካታ ንብረት ነክ ወንጀሎች ምክንያት ሊሆን ስለሚችል "የተሰረቀ" የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጓል:: የሌሎች ቃላት ማስተካከያም በአንቀጹ ላይ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ ፫፻፹፬ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ መርዳት**

ይህ አንቀጽ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ላይ አልተካተተም ነበር:: አንቀጹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "Money Laundering" የሚለውን ድርጊት የሚመለከት ሲሆን፣ በአሁኑ ዘመን ድርጊቱ እየተስፋፋ ስለመጣ እንደወንጀል ተቆጥሮ እንዲያስቀጣ መደረጉ አስፈላጊ ስለሆነ የተቀረጸ ድንጋጌ ነው::

ድርጊቱ ከብዙ ከባድ ወንጀሎች ጋር ተያይዞ ሊፈጸም ይችላል፤ ይኸውም ሙስናን፣የአደንዛዥ ዕጽ ወይም መድኃኒት ዝውውርና ሕገወጥ የጦር መሣሪያ ንግድን የመሳሰሉት ወንጀሎችን ይመለከታል:: ከእነዚህም በተጨማሪ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፪፻፵፫ (፪) (፫)፣ ፪፻፷፱ (፩) (፪)፣ ፬፻፺፩ (፪)፣ ፭፻፺፮ ፫) (፬)*፣ ፭፻፺፯ እስከ ፭፻፺፱፣ ፭፻፲ (፪)፣ ፭፻፲፩ (፪) (፫) (፭) ወይም ፭፻፲፪ የተመለከተውን ወይም ማናቸውንም ሌላ ከባድ ወንጀል እንደሚያጠቃልል በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ተገልጿል:: "ከባድ ወንጀል" ሲባልም ቢያንስ በአስር ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወይም በወንጀሉ አማካይነት የተገኘው የገንዘብ መጠን ወይም የንብረቱ ዋጋ ቢያንስ ሃምሳ ሺ ብር ሲሆን ነው፤ ይህም በንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ ተመልክቷል:: በእነዚህ ወንጀሎች አማካይነት የተገኘውን ሕገወጥ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የተዘረዘሩት ወንጀሎች እያንዳንዳቸው በሚገኙበት ምዕራፍና ክፍል ስር ማስቀመጥ ቢቻልም፣ ሁሉንም ወንጀሎች ባካተተ መልኩ መቀረጹ የተሻለ በስለሆነ ይህ አጠቃላይ አንቀጽ ሲቀረጽ ችሏል::

አንቀጹ ሰባት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን ከዋና ወንጀል አድራጊው በተጨማሪ ድርጊቱን እያወቀ በሕገ ወጡ ገንዘብ ወይም ንብረት የለወጠ፣ ያስተላለፈ፣ የተቀበለ፣ ይዞ የተገኘ ወይም በዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት የተጠቀመ ለፖሊስ ያሳስታወቀ ወይም ምርመራውን ያሰናከለ ሰውም እንዲቀጣ የሚያደርግ ነው:: በድርጊቱ ተካፋይ የሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅትም በወንጀሉ ተጠያቂ ይሆናል:: ለሕገወጡ ገንዘብ ወይም ንብረት ማስገኛ የሆነው የመጀመሪያው ከባድ ወንጀል አስር ዓመት ወይም ከዚህ በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆን እንዳለበት ወይም የሕገወጡ ገንዘብ መጠን ወይም የንብረቱ ዋጋ ቢያንስ ሃምሳ ሺህ ብር ሲሆን እንደሚገባ በንዑስ አንቀጽ ሰባት ላይ ተደንግጓል::

---

* በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ንዑሳን አንቀጾች ውስጥ የአንቀጽ ፭፻፺፮ (፫) እና (፬) ይገኙባቸዋል፤ ሆኖም ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ተብሎ መጠቀስ ነበረበት:: አዲስ የገቡትና በጣም ከባድ ቅጣት የሚያስቀጡት አንቀጽ ፭፻፺፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) እንጂ አንቀጽ ፭፻፺፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) አይደሉም:: ስህተቱ ሊፈጠር የቻለው፣ አዲሶቹ ንዑስ አንቀጾች በመጀመሪያ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነው ከተረቀቁ በኋላ በመጨረሻ የቦታ የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) በሚሆኑበት ጊዜ፣ የዚህ አንቀጽ ፫፻፹፬ (፩) አጣቃሽ ቁጥሮች በተደረገው ለውጥ መሠረት ማስተካከያ ስላልተደረገባቸው ነው::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፮፻፹፭ በከብት መንጋ አማካይነት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፵፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፭ ሆኖ ገብቷል::

የመሬት የግል ባለቤትነት ስለቀረ ስያሜው ላይ "በሰው ርስት" ይል የነበረው ሐረግ ተሰርዞ "በሌላ ሰው ንብረ" በሚል ሐረግ ተለውጧል:: የአንቀጹ ይዘትም በዚህ መልኩ ተሻሽሏል::
በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ ሁኔታዎቹ ቀላል በሆኑ ጊዜና ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኝነት እንደሆነ በደንብ መተላለፉ ማስቀጣቱ ተደንግጓል:: ሆኖም እዚህ ላይ ባይደነገግም ድርጊቱ በቸልተኝነተ ሲፈጸም በደንብ መተላለፍ ማስቀጣቱ አይቀርም:: በሌላ በኩል በዚህ ድንጋጌ አገላለጽ መሠረት ሁኔታዎቹ ቀላል ባልሆኑ ጊዜ በከባድ ቸልተኝነት ድርጊቱን የፈጸመ ሰው በወንጀልም ሆነ በደንብ መተላለፉ አያስቀጣም ይህ ግን አግባብ አይደለም ሁኔታዎቹ ቀላልም ይሁኑ ከባድ ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኛነት ከሆነ በደንብ መተላለፍ እንዲያስቀጣ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል:: ይህን ማድረግ እንዲቻል ቸልተኛነትን የሚመለከተው ሀረግ ከንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ ተሰርዟል::

አንቀጹ የሌሎች ቃላት ማስተካከያዎች ተደርጎበታል::

### አንቀጽ ፮፻፹፮ በሰው ንብረት ላይ ሁከት ማድረግ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፮ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (፪) ውስጥ ቅጣቱ መገለጽ ያለበት የወንጀሉ ዓይነት ከተገለጸ በኋላ መሆን ስላለበት አንቀጹ በዚሁ መሠረት ተስተካክሏል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

### አንቀጽ ፮፻፹፯ በሰው ይዞታ ላይ ጉዳት ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፯ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው "በሰው ርስት ላይ ጉዳት ስለማድረስ" የሚለው "በሰው ይዞታ ላይ ጉዳት ማድረስ" በሚል ተተክቶአል:: በተጨማሪም አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

ጽ ፮፻፹፰ <u>የወሰን ምልክቶችን ከስፍራቸው ማዛወርና ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፰ ሆኖ ገብቷል።

ይህ አንቀጽ ለተሻለ ግልጽነት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ</u>

ፐጽ ፮፻፹፱ <u>ወቅሳሳ ድንጋጌዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፹፱ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ለተሻለ ግልጽነት የአቀማመጥና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ወንጀል የሚፈጸምባቸውንም ንብረቶች ዝርዝር የተሟላ ለማድረግ፣ "የግብርና ምርት፣ ደን፣ ቤት፣ የሕንጻ ስራዎች" የሚሉት ቃላት እንደገቡ ተደርጓል።

ቀጽ ፮፻፺ <u>ከባድ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ የቀድሞው ህግ በሶስት ፊደላት የተከፈለ ነበር፤ ይህ አንቀጽ ግን ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል።

ንዑስ አንቀጽ (፩) የቀድሞውን የፊደል (ሀ) እና (ሐ) ድንጋጌ የያዘ ሲሆን ቅጣቱም በመጠኑ ከበድ እንዲል ተደርጓል።

በፊደል (ለ) ላይ የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ንብረቶች እጅግ ከፍተኛ የታሪክ ወይም የኢኮኖሚ ዋጋ ያላቸው በመሆኑና በእነዚህ ላይ የሚፈጸመው ወንጀል ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ ስለሚገባ ራሱን የቻለ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲሆን ተደርጓል።

በተጨማሪም አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) የገባ ሲሆን ወንጀሉ የተፈጸመው ሰውን ለመግደል ወይም ሌሎች ከባድ ወንጀሎችን ለመፈጸም ታስቦ እንደሆነ ከፍተኛ ቅጣት እንዲያስቀጣ ተደርጎ የተደነገገ ነው።

በቀድሞው ህግ በፊደል (ሀ) ድንጋጌ መጨረሻ ላይ "ይህም ጉዳት በዕቃዎች በስራዎች በሕንጻዎች ወይም የግል ሀብት በሆኑ ተክሎች ጉዳትን ያስከተለ እንደሆነ" የሚለው ጥገኛ ሀረግ ተሰርዟል። ምክንያቱም የንብረቶቹን ዝርዝር ዓይነት በተሟላ ሁኔታ በአንቀጽ ፮፻፹፱ ላይ በመገለጹ ነው።

www.abyssinialaw.com

የቀድሞው የቁጥር ፮፻፶፬ ድንጋጌ በሶስት ተራ ፊደላት የተከፈለ ነበር፤ ይህ አንቀጽ ግን ሶስት ንዑሳን አንቀጾች እንዲኖሩት ተደርጓል:: የቀድሞው የፊደል ተራ (ሀ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ንዑስ አንቀጽ (፩) ሲሆኑ የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ የአገሪቱንና የህዝብን ከፍተኛ ጥቅም የሚመለከቱ ሁኔታዎችን ያካተተ ስለሆነ ከባድ ቅጣት እንዲያስቀጣ ተደርጎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖአል::

በቀድሞው ድንጋጌ በተራ ፊደል (ሀ) መጨረሻ፣ "በዕቃዎች፣ በስራዎች፣ በህንጻዎች ወይም የግል ሀብት በሆኑ ተክሎች" የሚሉትን ቃላት የያዘው ሀረግ ከዚህ እንዲሰረዝ ተደርጓል:: ምክንያቱም አጠቃላይ ሁኔታዎችን የሚሸፍነው የአንቀጽ ፮፻፹፱ ድንጋጌ እነዚህን የንብረት ዓይነቶች ባካተተ መልክ በመቀረጹ ነው::

አዲስ የገባው የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ፣ "ወንጀሉ የተፈጸመው ሰውን ለመግደል፣ በአካሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ይዞ ለማቆየት በማስፈራራት፣ ወይም በመንግሥት የህግ ሰውነት የተሰጠው አካልን፣ ቡድንን ወይም ግለሰብን አንድ ነገር እንዲፈጽም ወይም ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማስገደድ ታስቦ በሆነ ጊዜ" ከባድ ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን የአሸባሪዎችን ተግባር ለመከላከል እና ለመግታት ይረዳል ተብሎ የተደነገገ ነው::

አንቀጽ ፮፻፺፩ <u>ከባድ ዘዴዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፩ ሆኖ ገብቷል::

በስያሜው ላይ "አሠራሮች" የሚለው "ከባድ ዘዴዎች" ቢባል የተሻለ ስለሚሆን በዚሁ መልክ እንዲስተካከል ሆኗል፣ በድንጋጌው ላይም አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት አንቀጹ ተሻሽሏል::

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>
<u>በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>
<u>ማታለልን ያካተቱ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፮፻፺፪ <u>አታላይነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፪ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ተከፋፍሎ የነበረው አስፈላጊ ባለመሆኑ በአንድ ፓራግራፍ ተጠቃልሎ የተቀረጸ ሲሆን በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ቃላቶቹ እንዲስተካከሉና አሳቡ እንዲቃና ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

ቀጽ ፮፻፺፫ <u>የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፫ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቀጽ ፮፻፺፬ <u>በተጭበረበረ ሁኔታ የአክሲዮን ገቢያን ንግድ ማካሄድ</u>

ቀደም ሲል በ፲፱፻፵፱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ በወንጀል ሕጉ እንዲገባ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት በአገራችን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ እየተስፋፋ የመጣ በመሆኑ በstock exchange ዙሪያ የተለያዩ ወንጀሎች ወደፊት ሊፈጸሙ ይችላል የሚል እምነት በመኖሩ ነው። ይኸውም:-

ሀ. በአክስዮን ባለቤትነት ላይ ምንም ጠቃሚ ለውጥ የማያመጣ የአክስዮን ንግድ ማካሄድ ወይም

ለ. አክስዮኖቹ በተጠየቁት ተቀራራቢ መጠን፣ በዚያው ሰው ወይም በሌላ ሰው እንደተገዛ ለዚያው ሰው /ለሌላ ሰው የግዥ ጥያቄ እንደቀረበ/ እንደሚቀርብ እያወቀ አክስዮኖቹን ለመግዛት ጥያቄ ማቅረብ ወይም

ሐ. አክሲዮኖቹ በተጠየቁት ተቀራራቢ መጠን በዚያው ሰው ወይም በሌላ ሰው እንደተሸጡ ወይም ለዚያው ሰው /ለሌላ ሰው የሽያጭ ጥያቄ እንደቀረበ ወይም እንደሚቀርብ እያወቀ አክሲዮኖችን ለመሸጥ ጥያቄ ማቅረብ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መልክ ለመፍጠር ማሰብ በወንጀል ሊያስጠይቅ እንደሚችል በሕጉ ተካትቷል።

አንቀጽ ፮፻፺፭ <u>በአክሲዮኖች ወይም በሸቀጦች መቆመር</u>

ቀደም ሲል በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የተመዘገቡ ወይም ያልተመዘገቡ ኩባንያዎች ወይም የሌሎች የንግድ ድርጅቶች አክሲዮኖች ወይም ማናቸውም ዕቃዎች /ሸቀጦች ዋጋቸው ዝቅ ከፍ እንዲል ትርፍ ለማግኘት በማሰብ የሚገዛ/ የሚሸጥ በማስመሰል በቃል ወይም በጽሑፍ ማዘጋጀት ሊያስጠይቅ በሚችል መልኩ በሕጉ ውስጥ ገብቷል።

አንቀጽ ፮፻፺፮ <u>ከባድ አታላይነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፮ ሆኖ ገብቷል።

ከባድ አታላይነት በሕብረተሰቡ ላይ በጣም ከሚዘወተሩና ጉዳት ከሚያደርሱ ወንጀሎች አንዱ ስለሆነ ቅጣቱ ከፍ ተደርጎ እስከ አስራ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተስተካክሏል።

የቀድሞው ድንጋጌ በአራት የፊደሎች ተራ የተከፋፈለ ነበር። ሆኖም የፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የተሰረዘ በመሆኑ በሚቀጥሉት ሶስት ፊደል ተራ ያሉት ድንጋጌዎች ተሸጋሽገው በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ስር እንዲመጡ ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com



የቀድሞው የፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ልማደኛ አታላይነትን የሚመለከት ሲሆን፣ ስለ ልማደኛ ስርቆት ተደርጎ የነበረው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፵፰ ንዑስ ቁጥር (፫) (ሀ) በተገለጸው ምክንያት ሊሰረዝ ችሏል::

በቀድሞው የፊደል ተራ (ሀ) የአሁኑ የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ላይ የአክስዬን ገቢያንና ድርጅትን በግልጽ የሚሸፍን ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል::

በተጨማሪም አንቀጹ የሌሎች ቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፮፻፺፯ <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>

ስለአክሲዮኖች፣ ስለዕቃ ሰነዶች፣ ስለቦንዶች ወይም ስለማናቸውም የዋስትና ሰነዶች የሚወጡ ሌሎች አዋጆች /ደንቦች ቢኖሩ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ ሕግ ሊያስቀጡ እንደሚችሉ ተደርጐ አዲስ አንቀጽ በወንጀል ሕጉ ተረቅቆ ገብቷል::

አንቀጽ ፮፻፺፰ <u>ኢንሹራንስን በሚመለከት የሚፈጸም የአታላይነት ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፰ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ የተደረገበት ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖአል::

በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸውን ወንጀል የፈጸመው የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት እንደሆነ በዚህ ህግ በአንቀጽ ፺ መሠረት እንደሚቀጣ የሚደነግግ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ ገብቶአል:: ይህም የሆነው ድርጊቱ በተፈጥሮ ሰው ብቻ ሳይሆን በድርጅትም በኩል ሊፈጸም ስለሚችል ነው::

አንቀጽ ፮፻፺፱ <u>በሀሰተኛ ሰነድ ማታለል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፯፻ <u>በሕዝብ እምነት በመጠቀም ማታለል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

ንቀጽ ፯፻፬ ሌሎች የሚታለል ድርጊቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፪ ድንጋጌ ስለአታላይነት በተጻፈው በዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፪ (፪) ስር የገባ ሲሆን፣ የቀድሞው ህግ የቁጥር ፯፻፷፪ ስያሜ ሳይለወጥ አዳዲስ ልዩ የወንጀል ድርጊቶችን ያካተቱ አምስት ንዑሳን አንቀጾች ተቀርጸው ገብተዋል።

የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የሚመለከተው፣ ያልደረሱበትን ልዩ ልዩ ችግሮች ደረሱብኝ ብሎ የሀሰት ንግግር በማድረግ ወይም ማናቸውንም ሌላ የአታላይነት ዘዴ በመጠቀም ከግለሰብ ወይም ከህዝብ ገንዘብ ወይም ማናቸውንም ሌላ ማቴሪያላዊ ነገር የሚሰበስብን ሰው ነው።

የንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ በሌላ ሰው ላይ ልዩ ልዩ ጉዳት ወይም ችግር የደረሰ በማስመሰል ሌላውን ሰው መለመኛ ያደረገውን ወንጀል አድራጊ የሚያስቀጣ ነው።

በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ማንኛውም ሰው በሌላ ሰው ላይ አስቦ ጉዳት በማድረስ የዚህ ዓይነቱን ሰው መለመኛ በሚያደርግበት ጊዜ የሚቀጣበት ሁኔታ ተደንግጓል።

በንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ ማንም ሰው በፖለቲካ፣ በሃይማኖታዊ፣ በባሕላዊ፣ በማህበራዊ ወይም በሰብዓዊ ዓላማ ተነሳስቶ ተፈቅዶለትም ሆነ ሳይፈቀድለት ገንዘብ ወይም ሌላ ማቴሪያል ከሰበሰበ በኋላ ከሰበሰበበት ዓላማ ውጭ ገንዘቡን ወይም ሌላውን ንብረት በሚጠቀምበት ጊዜ የሚቀጣ መሆኑ ተመልክቷል።

የንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ደግሞ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ከዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፬) ከተመለከቱት ድርጊቶች በአንዱ ተካፋይ ሲሆን በዚህ ህግ በአንቀጽ ፺ መሠረት የሚቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ነው።

የዚህ አንቀጽ መቀረጽ ያስፈለገበት ምክንያት፣ ድርጊቶቹን እንደወንጀል የሚቆጥር ህግ ስለሌለና የድርጊቶቹ መስፋፋት ያስከተለው ጉዳት በዝምታ ሊታለፍ ስለማይገባ ነው።

አንቀጽ ፯፻፭ በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ የተፈጸመ ጉዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፭ ሆኖ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ ድርጊቱ ታስቦ ወይም በቸልተኝነት ሲፈጸም አንድ ዓይነት ቅጣት እንዲያስቀጣ ተደርጎ ተደንግጎ ነበር። ሆኖም በቸልተኛነት የተፈጸመ ድርጊት የጥፋተኛነቱ ደረጃ አነስተኛ በመሆኑ ታስቦ የሚፈጸመውን ያህል ሊያስቀጣ ስለማይገባ ቸልተኝነትን የሚመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተረቅቆ ገብቷል።

በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ ተደንግጎ የነበረው የእስራት ቅጣት መነሻው ስድስት ወር የሚለው ጥቅም ለማግኘት ተብሎ ለተፈጸመ ወንጀል አነስተኛ በመሆኑ ወደ አንድ ዓመት ከፍ ብሎ ተረቅቋል። የመቀጮውም መጠን ከብር አስር ሺህ ወደ ሰላሳ ሺህ ብር አድጓል።

በንዑስ ቁጥር (፩) ላይ ድንጋጌው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በተለይም "ለሚሰራበት ድርጅት በሚፈጽመው አገልግሎት ላይ" የሚል ሀረግ የተጨመረ ሲሆን፣ አድራጊው በግለሰብ ጥቅም ላይ ብቻ ሳይሆን በሚሰራበት ድርጅት ጥቅም ላይም ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ ተጠያቂ እንዲሆን ታስቦ የገባ አነጋገር ነው።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፫ ከባድ ሁኔታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፫ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ስያሜ"ከባድ የሆነ ተንኮል ያለበት የሥራ አመራር" ይል ነበር:: አንቀጹ ከዚህ በፊት ባለው በአንቀጽ ፫፻፩ የተመለከተውን የወንጀል አፈጻጸም ስለሚያከብዱ ሁኔታዎች የሚደነግግ በመሆኑ የቀድሞው ስያሜ ተሰርዞ በአጭርና በግልጽ አነጋገር "ከባድ ሁኔታ" በሚል ተተክቷል::

የድንጋጌውን አቀራረጽ በተመለከተ የቀድሞው የቁጥር ፫፻፷፬ ድንጋጌ ሁለት ንዑስ ቁጥሮች ነበሩት:: ይህ አንቀጽ ግን አዲስ ንዑስ (፪) እና (፫) የገባለት በመሆኑ የቀድሞው የንዑስ ቁጥር (፪) ድንጋጌ ንዑስ ቀንቀጽ (፬) ሆኗል::

አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ጉቦ ስለመቀበል በአንቀጽ ፬፻፳፣ ንዑስ አንቀጽ (፫) ደግሞ የማይገባ ጥቅምን ስለመቀበል በአንቀጽ ፬፻፱ በተደነገገው ዓይነት የተቀረጹና ከባድ ቅጣት የሚያስቀጡ ናቸው:: እነዚህን ንዑሳን አንቀጾች መቅረጽ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በአንቀጽ ፬፻፪ (፪) እና (፫) ላይ በተገለጸው መሠረት የመንግሥት መስሪያ ቤትንና የመንግሥት ልማት ድርጅትን ትርጉም በማያሟሉ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግል ድርጅቶች የሚሰሩ ኃላፊዎችና ሰራተኞች፣ የሙስና ወንጀሎችን ፈጽመዋል እየተባሉ በመንግሥት ሠራተኞች ላይ የሚወሰደው እንደ ዋስትና ማጣት የመሰለ እርምጃ ተፈጻሚ እንዳይሆንባቸው ቢደረግም፣ ቅጣትን በሚመለከት ግን የመንግሥት ሠራተኞች ከሚወሰንባቸው ጋር የተቀራረበ ከባድ ቅጣት ሊፈረድባቸው ይገባል ተብሎ በመታመኑ ነው::

አንቀጽ ፫፻፬ ጥቅም ታገኛለህ በማለት ሌላውን ሰው በመደለል ማነሳሳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፬ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው መሠረት ማንም ሰው በንግድ ስራ ልምድ የሌለው መሆኑን ምክንያት በማድረግ ተበዳዩ ካለው ንብረት ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑን እያወቀ ብቻ ሳይሆን ማወቅም ሲገባው ድርጊቱን ከፈጸመ እንደሚቀጣ ሕጉ ይደነግጋል:: "ማወቅ ሲገባው" የሚለው አነጋገርም ቸልተኛነትን ያሳያል:: በቸልተኝነት የተፈጸመ ድርጊት ግን ታስቦ የተፈጸመውን ያህል ሊያስቀጣ አይገባም:: በመሆኑም በቸልተኝነት ሰርቼ አተርፋለሁ የሚል እምነት ሌላው ሰው እንዲያደርግበት በማድረግ ወንጀሉን የፈጸመ ሰው የሚቀጣበት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተረቅቆ ገብቷል::

ከዚህም በላይ አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተረቅቋል::

አንቀጽ ፫፻፭ ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ንብረታቸውን የሚጎዳ ስራ እንዲፈጽሙ ማነሳሳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፭ ሆኖ ገብቷል::

ይህ አንቀጽ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## በኮምፒውተር አማካይነት የሚፈጸሙ ወንጀሎች

በኮምፒውተር አማካይነት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚሸፍኑና በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያልነበሩ አዲስ አንቀጾች በዚህ ክፍል ስር እንዲካተቱ ተደርጎ ተረቋል።

**አንቀጽ ፯፻፮ ያለፈቃድ ወደ ኮምፒውተር መግባት፣ የኮምፒውተር አገልግሎትን ያለፈቃድ መውሰድ ወይም መጠቀም፣***

ይህ አንቀጽ በስያሜው የተመለከቱት ድርጊቶች ወንጀል መሆናቸውን የሚደነግግ ነው። በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ያለፈቃድ ወደ ኮምፒውተር፣ ኮምፒውተር ሥርዓት ወይም ኮምፒውተር መረብ የገባ፣ በንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ ያለፈቃድ የኮምፒውተር ዳታን የወሰደ ወይም ለራሱም ሆነ ለሌላ ሰው ጥቅም ያዋለ ሰው እንዲቀጣ የሚያደርግ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲፈጸም የሚያስቀጣ መሆኑን ይደነግጋል።

**አንቀጽ ፯፻፯ በዳታ ላይ ጉዳት ማድረስ**

ይህ አንቀጽ ሶስት ንዑስ አንቀጾች ያሉት ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድርጊቶች ታስበው ሲፈጸሙ፣ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲደረግ ማስቀጣቱን ይደነግጋሉ። በንዑስ አንቀጽ አንድ የተመለከቱት ድርጊቶች የኮምፒውተር ዳታን መቀየር፣ መለወጥ፣መሰረዝ እና ማጥፋት ናቸው። ንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ድርጊቶች የተፈጸሙት ለመስረቅ፣ ለማጭበርበር፣ ለማታለል ወይም ለመንጠቅ ወዘተ በማቀድ እንደሆነ፤ ወይም ይህ ዕቅድ ባይኖርም የደረሰው ጉዳት ከባድ የሆነ እንደሆነ፤ አድራጊው በወንጀል እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

**አንቀጽ ፯፻፰ የተፈቀደለት ተጠቃሚ የኮምፒውተር አገልግሎቶችን እንዳያገኝ ማቋረጥ**

ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚመለከተው ህጋዊ ተጠቃሚ ማግኘት የሚገባውን የኮምፒውተር አገልግሎት እስከ የሚያቋርጥን ሰው ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (፪) ደግሞ ድርጊቱ በቸልተኝነት ሲፈጸም ማስቀጣቱን ይደነግጋል።

**አንቀጽ ፯፻፱ የኮምፒውተር ወንጀሎችን አፈጻጸም ለማመቻቸት የሚከናወኑ ድርጊቶች**

ይህ አንቀጽ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን፣ ከዚህ በላይ በተመለከቱት አንቀጾች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ለመፈጸም እንዲመቸው እስከ መሣሪያዎችን፣ የሚስጢር ኮዶችን (ፓስ ወርዶችን) ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ማምረት መሸጥ ወዘተ...... የመሳሰለው ድርጊት ወንጀል መሆኑን የሚደነግግ ነው።

---

* በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 706 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ "ኮምፒውተር አገልግሎትን" የሚለው ቃል "የኮምፒውተር አገልግሎትን" ተብሎ ይነበብ።

አንቀጽ ፯፻፲ <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>

ይህ አንቀጽ የሚደነግገው ኮምፒውተርን መሣሪያ በማድረግ በዚህ ክፍል ከተመለከቱት ውጭ ሌሎች ወንጀሎች የተፈጸሙ እንደሆነ ለእነዚህ ሌሎች ወንጀሎች አግባብነት ያላቸው የወንጀል ሕጉ አንቀጾች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ለመግለጽ ነው።

አንቀጽ ፯፻፲፩ <u>የወንጀሎች መደራረብ</u>

በዚህ ክፍል ሥር በኮምፒውተር አማካይነት የሚፈጸሙት ወንጀሎች፣ ሌሎች ወንጀሎችን አስከትሎ እንደሆነ ጥፋተኛው ተደራራቢ ወንጀሎችን በመፈጸሙ እንደሚቀጣ የሚደነግግ አንቀጽ ነው።

እነዚህ አዳዲስ አንቀጾችን (በተለይ የመጀመሪያዎቹን ሶስት ድንጋጌዎች) ለማርቀቅ፦

፩ኛ/ የማሳቹሰትስ ሕግ "An act to prevent Computer Crime 1990"፣

፪ኛ/ የቴክሳስ "Computer Crime Law 1994"፣

፫ኛ/ የእንግሊዝ "Computer Misuse Act 1990"፣

፬ኛ/ የዩናይትድ ስቴትስ ሕግ "Fraud and related activity in Connection with Computers"፣

፭ኛ/ Computer Crime: An Emerging Challenge for Law Enforcement 1997" ከሚችጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ የተገኘ ጽሑፍ ለንጽጽር ሥራ የዋሉና ከእነዚህም ሕጎች የተወሰዱ ናቸው።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የህሊናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፯፻፲፪ <u>አራጣ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፪ ሆኖ ገብቷል።

ይህ አንቀጽ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፯፻፲፫ <u>በማስገደድ መጠቀም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፫ ሆኖ ገብቷል።

ይህ አንቀጽ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፲፬ <u>ጥቅም ለማግኘት ማስፈራራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፬ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፲፭ <u>ከባድ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፭ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ፊደል ተራ (ሀ) ላይ "ይህንኑ ስራ እንደሞያ ስራው አድርጎ ይዟል በሚያሰኝ ሁኔታ" የሚለው ሀረግ እንዲሰረዝ ተደርጓል። ሊሰረዝ የቻለው ልማደኛ ስርቆትን የሚመለከተው የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፵፭ ንዑስ ቁጥር (፫) (ሀ) ንጋጌ በተሰረዘበት ምክንያት ሲሆን ደጋጋሚነትን ወይም ተደራራቢ ወንጀሎችን የሚሸፍኑት አንቀጾች ከዚህ ድንጋጌ ይልቅ ለወንጀሉ ተገቢ የሆነና ሰፋ ያለ ቅጣት የሚያስቀጡ በመሆኑ ነው።

ከዚህም በላይ በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያ እና ለውጥ የተደረገ ሲሆን የእንግሊዝኛውን ቅጂ መሠረት በማድረግ በተለይ የፊደል ተራ (ሐ) አሳብ ተቃንቶ ተረቅቋል።

## <u>ርዕስ ሁለት</u>
## <u>በንግድና በኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፩፻፲፮ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት</u>

ፍጹም ፩፻፴፩ ፩፻፲፯

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ~~፩፻፳~~ ድንጋጌ ተሻሽሎ የዚህ ሕግ አንቀጽ ~~፩፻፲፮~~ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው በቀድሞው ህግ መሠረት የምዕራፍ ሁለት አካል ነበር። ነገር ግን አግባብነቱ ለምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ብቻ ሳይሆን ለምዕራፍ አንድ አንቀጾችም ጭምር በመሆኑ፣ ተፈጻሚነቱ ለሁለቱም ምዕራፎች መሆኑን በሚያሳይ መልክ የርዕሱ (Title) የመጀመሪያው አንቀጽ ሆኖ ተቀርጿል።

በድንጋጌው ውስጥ "ላይ" የሚለው ቃል መኖሩ በስያሜውና በይዘቱ ላይ መሠረታዊ ልዩነት ያስከትላል። "ላይ" የሚለው ቃል መኖሩ በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ማህበር ወይም ድርጅት ላይ በደል እንደሚፈጸምበት ያመለክታል። ሆኖም የአንቀጹ አሳብ አንድ ማኅበር ወይም ድርጅት የወንጀል ተግባር መፈጸሚያ መሣሪያ ሲሆን ድርጅቱም ሆነ የእርሱ ኃላፊዎች ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። በዚሁ መሠረት ድርጅቱም ሆነ የድርጅቱ ኃላፊዎች መጠየቅ እንዲችሉ "ላይ" የሚለው ቃል ተሰርዟል።

www.abyssinialaw.com

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ አዲስ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ ፪ የቀድሞውን ሕግ የቁጥር ፮፻፹፱/ ድንጋጌን የሚተካ ነው። ንዑስ አንቀጽ ፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ርዕስ ስር ባሉት ወንጀሎች ተካፋይ የሚሆንበትን ሁኔታ ይመለከታል፤ ንዑስ አንቀጽ ፪ ደግሞ የአንድ ድርጅት ባለሥልጣኖች ወይም ሠራተኞች ከድርጅት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወንጀል ሲፈጽሙ እነርሱም ተጠያቂ እንደሚሆኑ ይደነግጋል።

## ምዕራፍ አንድ
## ግዙፍነት በሌላቸው መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ ፯፻፲፯ በሌላ ሰው መልካም ስም ላይ ጉዳት ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፯ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "በሌላ ሰው ታማኝነት ላይ ጉዳት ስለማድረግ" የሚል ነበር። ሆኖም " Attack on another's credit" ከሚለው የእንግሊዝኛ ሀረግ ጋር በይበልጥ ተስማሚ ነው ተብሎ በሚታመንበትና ግልጽ በሆነ አነጋገር "በሌላ ሰው መልካም ስም ላይ ጉዳት ማድረስ" በሚል ተሻሽሏል።

የንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል።

የንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

### አንቀጽ ፯፻፲፰ ጉዳትን የሚያደርሱ ሀሰተኛ መግለጫዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፰ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

### አንቀጽ ፯፻፲፱ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፲፱ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን በማለት የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል።

ሆኖም የነጻ ገበያንና የንግድ ውድድርን የሚቃረኑ ድርጊቶችን በሚመለከት አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፱/፲፱፻፺፭ የወጣ ሲሆን የአስተዳደር እርምጃ ከመውሰድም አልፎ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ መቀጮ የሚወስን ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። ከተጠቀሰው አዋጅና ከዚህ የወንጀል ህግ አንቀጽ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የትኛው እንደሆነ በፍርድ ቤት ሊወሰን ይገባል።

www.abyssinialaw.com

...ቀጽ ፯፻፳ <u>ምልክቶችን፣ የመገኛ ምንጭ ማስታወቅን ዲዛይኖችን ወይም ሞዴሎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳ ሆኖ ገብቷል::

ሰያሜውና ይዘቱ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ለውጥ ተደርጎበታል::

የወንጀሉ አፈጻጸም እየተስፋፋ በባለመብቶች ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እያስከተለና ጥቅም እያስቀረባቸው በመምጣቱ፣ ወንጀሉ የሚያስቀጣው በግል አቤቱታ ብቻ መሆኑ ቀርቶ በወንጀል ክስ አቅራቢነት እንዲሆን ተደርጓል:: በሌላ አነጋገር የግል ተበዳዩ ወይም ህጋዊ ወኪሉ አቤቱታ ባያቀርብም በማንኛውም ሰው አመልካችነት ወይም በፖሊስ ክትትል ወንጀል አድራጊው ሊቀጣ ይችላል ማለት ነው:: ቅጣቱም እስከ አስር ዓመት ጽኑ እስራት እንዲያድግ ተደርጎ ተቀርጿል:: ድርጊቱ በቸልተኛነት ሲፈጸምም የሚያስቀጣ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ገብቷል::

...ቀጽ ፯፻፳፩ <u>የድርሰት፣ የኪነ ጥበብ ወይም የአእምሮ ስራ ፈጠራ መብቶችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፭ እና የቁጥር ፯፻፷፮ ድንጋጌዎች ተዋህደው የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳፩ ሆነው ገብተዋል::

ሰያሜው የአንቀጹን ይዘት በይበልጥ በሚገልጽ አኳኋን ተሻሽሏል፤ ይዘቱም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ይህ አንቀጽ የቀድሞው ህግ የቁጥር ፯፻፷፭ እና የቁጥር ፯፻፷፮ ድንጋጌዎችን አዋህዶ ከላይ ስለ አንቀጽ ፯፻፳ በተሰጠው ግልጽ በሆነና በአጭር መልክ የተቀረጸ ሲሆን ከላይ ስለ አንቀጽ ፯፻፳ በተሰጠው ማብራሪያ ላይ ከተመለከተው አሳሳቢ ሁኔታ የተነሳ ወንጀሉ ታስቦም ሆነ በቸልተኛነት ሲፈጸም በወንጀል ክስ አቅራቢነት ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣ ነው:: ይህ ሊሆን የቻለው በአሁኑ ጊዜ የወንጀሉ አፈጻጸም እጅግ አሳሳቢ እየሆነ ስለመጣና በመብቱ ተጠቃሚዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስላስከተለ ቅጣቱ እንዲከብድ ተደርጎ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ በሚያደርገው በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ ስለተደነገገ ነው::

...ንቀጽ ፯፻፳፪ <u>የግል አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳፪ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ስያሜና ይዘት ላይ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ በማድረግ ድግግሞሽንም በማስቀረት አንቀጹ እንዲሻሻል ተደርጓል::

አንቀጽ ፯፻፳፫ <u>ከባድ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ሰያሜ "የተለዩ ወንጀሎች" የሚለው ቀርቶ፣ በእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ "Aggravated Cases" ከሚለው ሀረግ ጋር በሚጣጣም መልክ "ከባድ ሁኔታዎች" እንዲል ተደርጓል::

ይዘቱን በሚመለከት ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፹፩ <u>ተጨማሪ እርምጃዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

"ፍርድ ቤቱ ፍርዱ ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል" የሚለው ሐረግ በአግባቡ ተተርጉሞ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ዕዳን ለማስከፈል በሚደረግ ክስ አቀራረብ፣ በፍርድ አፈጻጸም እና በአከሳሰር ጉዳይ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

አንቀጽ ፬፻፹፪ <u>በማጭበርበር ዕዳ ለመክፈል አለመቻል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፪ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜውና ይዘቱ ለግልጽነት በእንግሊዘኛው ቅጂ መሠረት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

አንቀጽ ፬፻፹፫ <u>አላግባብ መክሰር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ መክሰርን ሳይሆን ሆነ ተብሎ አላግባብ ኪሳራ ያደረገን ሰው ለመቅጣት የተደነገገ ስለሆነ በስያሜው ውስጥ "አላግባብ" የሚል ቃል ተጨምሮ ተሻሽሏል::

ንዑስ ቁጥር (፩) ላይ በንግድ ሥራ የተሰማራ ባለዕዳ ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ወይም ሂሳብ ባለመያዝ አስቦም ሆነ በቸልተኝነት ድርጊቱን ፈጽሞ ሲገኝ በአንድ ዓይነት ወንጀል እንደሚጠየቅ ተደንግጎ ነበር:: ሆኖም በቸልተኝነት የተፈጸመ ድርጊት ከላይ በተመለከተው ንዑስ ቁጥር (፩) መሠረት ሊቀጣ ስለማይገባ ቀለል ባለ ቅጣት እንደሚቀጣ ሆኖ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተረቅቋል::

የንዑስ ቁጥር (፪) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ (፫) ሲሆን የንዑስ ቁጥር (፪) ሁለተኛው ፓራግራፍ ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ገብቷል:: በጠቅላላው አንቀጽ ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጓል::

አንቀጽ ፬፻፹፬ <u>በማጭበርበር ኪሳራ እንዲደርስ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፹፬ ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ ቁጥር (፩) የመጨረሻው ፓራግራፍ ራሱን የቻለ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት የያዘ በመሆኑ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደረገ ሲሆን ንዑስ ቁጥር (፪) ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ ንዑስ ቁጥር (፫) ደግሞ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንዲሆን ተደርጓል:: አንቀጹ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

·ጽ ፯፻፳፰ <u>በፍርድ አፈጻጸም ላይ የሚፈጸም የማጭበርበር ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

በአንቀጹ ላይ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጐበታል፡፡

ቀጽ ፯፻፳፱ <u>በመያዣነት ወይም በሕግ አግባብ የተያዘን ንብረት አለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፳፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል፡፡

ይዘቱም ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ንቀጽ ፯፻፴ <u>በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ ወይም ማጥፋት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፴ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜና ይዘቱ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተከካያ ተደርጎባቸዋል፡፡

ንቀጽ ፯፻፴፩ <u>በገንዘብ ጠያቂዎች መካከል ተገቢ ያልሆነ አድልዎ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፴፩ ሆኖ ገብቷል፡፡

ስያሜው የአንቀጹን ይዘት በሚገልጽ መልኩ ተሻሽሏል፡፡

ይዘቱ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፯፻፴፪ <u>የድምጽ ብልጫን ለማግኘት መደለያ መስጠት*</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፴፪ ሆኖ ገብቷል፡፡

ንዑስ ቁጥር (፪) (ሀ) እና (ለ) በአንድ ንዑስ አንቀጽ ተካተው ተሻሽለዋል፡፡

በተጨማሪም አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፯፻፴፫ <u>ስምምነትን በማጭበርበር ማግኘት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፴፫ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

---

* በወንጀል ህጉ አንቀጽ 732 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ "ከሦስት ዓመት" የሚለው ቃል "እስከ ሦስት ዓመት" ተብሎ ይነበብ፡፡

www.abyssinialaw.com

## ሦስተኛ ታላቅ ክፍል
## የደንብ መተላለፍ ሕግ
## ሰባተኛ መጽሐፍ
## ጠቅላላ ክፍል
## ርዕስ አንድ
## ቅጣትን የሚመለከቱ ደንቦች

ርዕሱ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

### ምዕራፍ አንድ
### የሕጉ ተፈጻሚነት ወሰን

አንቀጽ ፲፻፴፩ ወደ ወንጀል ሕግ ጠቅላላ መርሆች መምራት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

ከድንጋጌው ላይ የማያስፈልጉ ሀረጎች ተሰርዘው የቃላት ማስተካከያና የአሳብ መቃናት ተደርጎበት አንቀጹ ተረቋል::

አንቀጽ ፲፻፴፪ ደንብ መተላለፍ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፴፪ ሆኖ ገብቷል::

ይህ ድንጋጌ ስለደንብ መተላለፍ ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በተሻሻለው ሕገ መንግሥት የሕግ፣ የደንብ/ ትዕዛዝ ሕግ ክፍል ማስታወቂያ አወጣጥ ሥርዓት መሠረት የአስፈጻሚው አካል መሥሪያ ቤቶች እነዚህን የሚያውጁበትን ሁኔታ በሸፈነ መልኩ ነበር:: ሆኖም የሕግ ዓይነቶች ሁሉ ሕግ በሚለው ቃል የሚጠቃለሉ በመሆኑ ዝርዝር የሕግ ዓይነቶችን መጥቀሱ ቀርቶ ሕግ የሚለው ቃል ብቻ እንዲተካቸው ተደርጓል:: ከዚህም በላይ አንድ ሰው ደንብ ተላልፏል የሚባለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ያወጣውን ሕግ በሚጥስበትና ከዚህ በታች የተመለከቱት የቅጣት ዓይነቶች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ህጋዊ ገንዘብን እንዳለመቀበል ወይም ወዲያውኑ ለሙብላት እሸትን እንደመስረቅ የመሳሰሉ በወንጀል የማያስቀጡ ቀላል ጥፋቶችን ሲፈጽም ጭምር ነው:: በመሆኑም አንቀጹ በዚህ መልክ ተሻሽሎ ተረቋል::

አንቀጽ ፲፻፴፫ ሕጉ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው ጥፋቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፴፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፲፻፴፬ ሕጉ በእኩልነት ተፈጻሚ መሆኑ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፴፬ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "በሰው ላይ የሚሆን የሕጉ ተፈጻሚነት" የሚል ሲሆን በይበልጥ ግልጽነት እንዲኖረው "ሕጉ በእኩልነት ተፈጻሚ መሆኑ" በሚለው ሀረግ ተስተካክሏል::

www.abyssinialaw.com

በድንጋጌው ይዘት ላይም "አጥፊዎች" የሚለው ቃል "ጥፋተኞች" በሚል የተተካ ሲሆን ሌላ የቃላት ማስተካከያም ተደርጎበታል::

ንቀጽ ፳፻፴፰ ቦታን በማመልከት የሕጉ ተፈጻሚነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፻፴፰ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጹ ስያሜና ይዘት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ንቀጽ ፳፻፴፱ በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፻፴፱ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን በውጭ አገር የተሰጡ ደንብ ተላላፊነትን የሚመለከቱ ፍርዶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚታዩ የወንጀልና የደንብ ተላላፊነት ጉዳዮች ላይ ውጤት እንደማይኖራቸው የሚደነግጉ ናቸው:: በውጭ አገር የተሰጠ ደንብ መተላለፍን የሚመለከት ፍርድ በኢትዮጵያ በሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሊኖረው ስለሚችለው ውጤት በዚህ ርዕስ ስር ሳይሆን በመጀመሪያ ታላቅ ክፍል መካተት ስለሚገባው የወንጀል ጉዳይን የሚመለከተው የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሰርዟል::

የደንብ ተላላፊነትን የሚመለከተው ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሻሽሎ ድንጋጌው አንድ ፓራግራፍ ብቻ እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን፣ በውጭ አገር የተሰጡ የደንብ ተላላፊነት ፍርዶች ብቻ ሳይሆኑ የወንጀልም ፍርዶች ጭምር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰጡ የደንብ ተላላፊነት ፍርዶች ላይ ውጤት እንዳይኖራቸው ተደርጎ ተቀርጿል::

## ምዕራፍ ሁለት
## ለቅጣት ኃላፊ መሆን

አንቀጽ ፳፻፵ የሚያስቀጡ ድርጊቶችና የሚቀጡ ሰዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፳፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፳፻፵ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ "የሚያስቀጣው የተፈጸመው የደንብ መተላለፍ ስራ ብቻ ነው" የሚለው ዓረፍተ-ነገር አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል::

በንዑስ ቁጥር ሁለት መጨረሻ ላይ "እያንዳንዱ የሚቀጣው ከሌላ ሰው ጋራ በመተባበሩ ሳይሆን በገዛ ራሱ ሥራ ብቻ ነው::" የሚለው የሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር አካል የያዘው ፍሬ-ነገር በአንቀጽ ፳፻፵፩ (፪) ላይ የተካተተ በመሆኑ በጥቅስ ምልክት ውስጥ የተቀመጠው አገላለጽ እንዲሰረዝ ተደርጎ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖአል::

www.abyssinialaw.com

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በደንብ መተላለፍ ተጠያቂ እንደሚሆን የሚገልጽ ድንጋጌ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ ሲሆን ይህንን የሚያመለክት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ሶስት እንዲገባ ተደርጓል:: አንድ ድርጅት በደንብ መተላለፍ ረገድ በማሰናዳት እና በሙከራ እንዲሁም በማነሳሳትና በአባሪነት አይቀጣም፤ የሚቀጣው የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከሙከራ ደረጃ አልፎ ደንብን በሚጥስበት ጊዜ እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ ተደንግጓል::

ንዑስ ቁጥር ሶስት ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚመለከት ሲሆን ቁጥር ፶፪ ብቻ መጠቀሱ ቀርቶ ከቁጥር ፶፪ እስከ ፶፭ እንዲል ተደርጓል::

በንዑስ ቁጥር አራት መግቢያ ላይ "በጋዜጣ ወይም በጠቅላላው በጽሁፍ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "በመገናኛ ብዙሃን" በሚለው ሀረግ ከተተካ በኋላ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖአል::

ከዚህም ሌላ በሁሉም ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል::

አንቀጽ ፮፻፵፩ <u>የሚያስቀጡ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፩ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ ፍጹም ኢ-ኃላፊነትን ብቻ አስመልክቶ የተጻፈ ሲሆን ይህ መሆኑ ቀርቶ ሁለቱንም የኢ-ኃላፊነት ዓይነቶች በሚያመለክትና አጣቃሽ አንቀጾችን ባካተተ መልኩ ተረቋል::

በንዑስ ቁጥር ሁለት መግቢያ ላይ "ማንኛውም ሌላ ሰው ደንብን ተላልፎ ከተገኘ በደንብ መተላለፍ የተጻፉት ቅጣቶች ይፈጸሙበታል" የሚለው ዓረፍተ-ነገር አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል::

በንዑስ ቁጥር (፫) ላይ "በህብረት ለመክሰስና ለማስቀጣት አይቻልም::" የሚለው አረፍተ ነገር አላስፈላጊ ስለሆነ ተሰርዟል::

በተጨማሪም በጠቅላላው አንቀጽ ላይ የቃላት ማስተካከያ እና ለውጥ ተደርጓል::

አንቀጽ ፮፻፵፪ <u>ጉዳዩን ለማጣራት የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፪ ሆኖ ገብቷል::

ግልጽ እንዲሆን የቃላት እና የአቀራረጽ ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፮፻፵፫ <u>የሚያስቀጡና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፵፫ ሆኖ ገብቷል::

በንዑስ ቁጥር አንድ በመጀመሪያው ፓራግራፍ መጨረሻ ላይ (ቀጥር.፰፬፣ ፰፭፣ ፰፺፣ ፸፭፣ ፸፫፣ ፰፱::) በማለት የድንጋጌዎቹ ቁጥሮች በተከታታይነት መጻፋቸው ቀርቶ በዚህ

www.abyssinialaw.com

ህግ የአንቀጾች ቁጥር መሠረት ከተስተካከሉ በኋላ እያንዳንዱን ሁኔታ ከሚሸፍነው ሀረግ ቀጥሎ በየቦታው እንዲገቡ ተደርጓል::

በተጨማሪም የተበዳይን ፈቃድ የሚመለከተው ድንጋጌ (ቁጥር.፫) በዚህ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተካተተ ሲሆን ይህንን ሁኔታ የሚመለከተው የቀድሞው የንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ እንዲሰረዝ ተደርጓል::

የንዑስ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፓራግራፎች በአንድ ፓራግራፍ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ሶስተኛው ፓራግራፍ ሁለተኛ ፓራግራፍ ሆኖአል::

በተጨማሪም በጠቅላላው አንቀጽ ላይ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጓል::

አንቀጽ ፲፻፵፩ ስህተት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፵፩ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ድንጋጌ ሁለት ፓራግራፎች የነበሩት ሲሆን በሁለት ንዑስ አንቀጾች እንዲከፋፈል ተደርጓል::

ግልጽ እንዲሆን በማለት የቃላትና የአቀራረጽ ለውጥ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፲፻፵፰ ቅጣትን የሚያቃልሉ እና የሚያከብዱ ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፪፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፵፰ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት እንዲሁም የአቀራረጽ ለውጥ ተደርጎበታል::

ርዕስ ሁለት

ቅጣቶችን የማመለከቱ ደንቦች

ምዕራፍ አንድ

ተፈጻሚነት ያላቸው ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች

ክፍል አንድ

ዋና ቅጣቶች

የዚህ ምዕራፍ የቀድሞው ስያሜ "የሚፈጸሙ ቅጣቶችና የጥንቃቄ ውሳኔዎች" ይል የነበረ ሲሆን ከዚህ በላይ በተመለከተው አገላለጽ ተስተካክሏል::

አንቀጽ ፲፻፵፮ መደበኛ የሆኑ የወንጀል ቅጣቶች ተፈጻሚ አለመሆናቸው

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፲፪፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፻፵፮ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ደንበኛ በሆኑት በወንጀል ቅጣቶች ስላለመስራት" የሚል ሲሆን ሐረጉ ተሰርዞ "መደበኛ የሆኑ የወንጀል ቅጣቶች ተፈጻሚ አለመሆናቸው" በሚል ተተክቷል::

www.abyssinialaw.com


በድንጋጌው በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ "ሰውነትን በሚጎዳ ቅጣት" እና "ነፃነትን ለማሳጣት በሚደረጉ ለፀጥታ አስፈላጊ በሆኑ ጥንቃቄዎች በማዘት" የሚሉት ሀረጎች ተሰርዘዋል፤ ምክንያቱም የተጠቀሱት ቅጣቶች ለወንጀልም እንኳ ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸው የተደረገ በመሆኑ ነው።

ከዚህም በላይ ንዑስ ቁጥር አንድም ሆነ ንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሶስት ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው አንቀጹ ተረቋል።

አንቀጽ ፩፻፵፯ የማረፊያ ቤት እስራት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፵፯ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፵፰ የመደበኛ ማረፊያ ቤት እስራት አፈጻጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፵፰ ሆኖ ገብቷል።

ከስያሜው ላይ "የፖሊስ" የሚለው ቃል እንዲሰረዝ ተደርጓል፤ ምክንያቱም የማረፊያ ቤቱ እስራት የሚፈጸመው በፖሊስ ጣቢያ ብቻ ባለመሆኑ ነው። የድንጋጌው ይዘትም ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፵፱ በመኖሪያ ቤት ወይም በድርጅት ውስጥ የሚፈጸም የማረፊያ ቤት እስራት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፵፱ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፶ ስለወታደሮችና ወጣት ጥፋተኞች የተለየ የቅጣት አፈጻጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶ ሆኖ ገብቷል።

የቃላት ማስተካከያ በስያሜውና በይዘቱ ላይ ተደርጎበት ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጽ ፩፻፶፩ በማረፊያ ቤት እስራት ፈንታ የግዴታ ሥራን መወሰን

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፩ ሆኖ ገብቷል።

የንዑስ ቁጥር አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ፣ "የጊዜውንም ልክ በፍርዱ ውስጥ በትክክል ይወስናል" ይላል። ሆኖም ስለ ጊዜው ልክ ብቻ ሳይሆን በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት "የተቀናሽ ገንዘቡ መጠን" ጭምር በፍርድ ቤት እንዲወሰን ተደርጎ ሁለተኛው ፓራግራፍ ተስተካክሏል።

በተጨማሪም በሁለቱ ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው አንቀጹ ተስተካክሏል።

www.abyssinialaw.com

ንቀጽ ፮፻፺፯ <u>መቀጮ፣ መደበኛ ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፯ ሆኖ ገብቷል::

በዚህ አንቀጽ ስር አዲስ ንዑስ አንቀጽ አራት የገባ ሲሆን፣ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የሚቀጣው በመቀጮ ብቻ እንደሆነ እና መጠኑም ከአስር ብር እስከ ሁለት ሺህ ብር ለመድረስ እንደሚችል የሚደነግግ ነው:: የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች መደራረብ እና ደጋገጋሚነት ሲያጋጥም የመቀጮ መጠን እንደሚጨምር ለማመልከት፣ እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከቱት የአንቀጽ ፮፻፷፮ እና ፮፻፷፱ ድንጋጌዎች የተጠበቁ መሆኑን የሚያመለክት ሐረግ እንዲገባ ተደርጓል::

ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት ተሻሽሏል::

ነንቀጽ ፮፻፺፰ <u>መቀጮ በግዴታ ሥራ የሚለወጥበት ሁኔታ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "መቀጫን ስላለመክፈል በመታገድ ወይም በግዴታ ስራ መቀጫን መለወጥ" ይል የነበረው ግልጽነት እንዲኖረው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተስተካክሎ ተረቅቋል::

ይዘቱን በሚመለከት በሁለቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ ግልጽነት የሌላቸው ሀረጎች ግልጽ እንዲሆኑ በማድረግና አንዳንድ ቃሎችን በማስተካከል አንቀጹ ተረቅቋል::

አንቀጽ ፮፻፺፱ <u>በወታደሮችና በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚጣለውን መቀጮ ማስገባት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፮፻፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፮፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

የንዑስ አንቀጽ (፩) "የደመወዙ መያዝ ነገር ከአንድ ወር ሊበልጥ አይችልም" የሚለው አደናጋሪና በሌላ በኩል በጠቅላላው ድንጋጌ ጊዜ የግዴታ ስራ የሚሰራ ወንጀለኛ እንኳ የዋጋውን የተወሰነ ክፍል ብቻ ስለሚከፍል በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዐትም በኩል ደመወዝ ከሲሶ በላይ ስለማይነካ ይህም የሆነው የፍርድ ባለእዳውን ኑሮ ላለመጉዳት ስለሆነ ከነዚህ ግንዛቤዎች አንጻር እንዲስተካከል ሆኗል::

በንዑስ ቁጥር ሁለትም ወጣት ጥፋተኛው መቀጮ መክፈል ባይችል እንደ ከውል ውጭ ኃላፊነት በቤተሰቦቹ እንዲከፈል ማድረጉ የወንጀል የተናጠል ኃላፊነትን መርህ ጥሶ የጋራ ኃላፊነትን /collective liability/ ስለሚያመጣ በተጨማሪም የወንጀል ሕጉን ጠቅላላ ድንጋጌ /አንቀጽ ፲፰፯/ ጋር የሚቃረን ስለሆነ በዚያ መንፈስ ተስተካክሏል::

ግልጽ እንዲሆንም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፯፻፶፭ <u>የጉዳትና የሞራል ካሣ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፭ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜም ሆነ ይዘቱ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ተጨማሪ ቅጣቶች</u>

አንቀጽ ፯፻፶፮ <u>ማስጠንቀቂያና ወቀሳ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፮ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌውም ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፯፻፶፯ <u>ከመብት የመሻር ቅጣት ተፈጻሚ አለመሆኑ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፯ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>

አንቀጽ ፯፻፶፰ <u>የመልካም ጠባይ ዋስትና</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፰ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ዋስትና" ይል የነበረው ተሻሽሎ "የመልካም ጠባይ ዋስትና" እንዲል ተደርጓል::

ይዘቱንም በሚመለከት በሁለቱም ንዑስ ቁጥሮች ላይ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎ አንቀጹ የተሻሻለ ሲሆን የንዑስ ቁጥር ሁለት የሁለተኛው ፓራግራፍ አሳብ በመጀመሪያው ፓራግራፍ ውስጥ የተካተተ በመሆኑ ተሰርዟል::

አንቀጽ ፯፻፶፱ <u>መውረስ እና ለመንግሥት ገቢ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፱ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ስለመውረስ" ብቻ ይል ነበር ሆኖም ንዑስ ቁጥር አንድ በአንቀጽ ፲፰ በተደነገገው መሠረት ስለመውረስ የሚደነግግ ቢሆንም ንዑስ ቁጥር ሁለት በአንቀጽ ፲ መሠረት በደንብ ተላላፊነት የተገኙ ዕቃዎች ወይም መሣሪያዎች ለመንግሥት ገቢ እንዲደረግ የሚያዝዝ በመሆኑ ሁለቱን አሳቦች ባካተተ መልኩ ስያሜው ተስተካክሏል::

በተጨማሪም በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያ በማድረግ አንቀጹ ተረቋል::

 www.abyssinialaw.com

ነቀጽ ፫፻፷ ድርጅቶችን መከልከልና የሥራ ፈቃድን ማገድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜውም ሆነ ይዘቱ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ የተደረገበት ሲሆን ሁለተኛውና ሶስተኛው ፓራግራፎች ተቀራራቢ አሳቦችን የያዙ በመሆኑ በአንድ ፓራግራፍ እንዲዋሃዱ ተደርጓል።

ንቀጽ ፫፻፷፩ መውረስና ማገድ ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ "ዓይነተኞቹ የአፈጻጸም ሁኔታዎች" ይል የነበረው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተስተካክሎአል።
ይዘቱን በሚመለከትም ለውጥ ተደርጓል። በድንጋጌው መግቢያ ላይ ".... የመውረስ" ከሚለው ቃል ቀጥሎ "ወይም ለመንግሥት ገቢ የማድረግ" የሚል ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሁለቱም እርምጃዎች በአንቀጽ ፫፻፶፱ እንዲሁም በአንቀጽ ፺፰ እና ፺ የተካተቱ በመሆናቸው ነው። ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ ፊደል ተራ (ሠ) ድረስ በተመለከቱት ሀረጎች ላይም የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል።

ንቀጽ ፫፻፷፪ የግል ነፃነትን መከላከልና መቀነስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌውም ግልፅ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

በተለይም "ወንጀልን ወይም ተጨማሪ ወንጀሎችን ለመፈጸም" የሚለው ተሰርዞ "የደንብ ተላላፊነት ተግባሮችን ለመፈጸም" የሚለው ሀረግ እንዲገባ ተደርጓል፤ ምክንያቱም ይህ መጽሐፍና ርዕስ የሚመለከተው ደንብ ተላላፊነትን ከመሆኑም በላይ ወንጀሎችን በተመለከተ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ ፻፵፪ የተደነገገ በመሆኑና እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ባለመሆኑ ነው።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የማሳወቅ እርምጃዎች</u>

አንቀጽ ፫፻፷፫ ይግባኝ ሳለው ባለሥልጣን ማስታወቅና ፍርድን ለሕዝብ መግለጽ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፫ ሆኖ ገብቷል። ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፷፬ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ መመዝገብ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፳ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፷፬ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው በስያሜውም ሆነ በይዘቱ ላይ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያና ለውጥ ተደርጎበታል።

 www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሁለት
## የቅጣት አፈጻጸም

አንቀጽ ፩፻፹፮ ቅጣትን ማገድ እና በአመክሮ መፍታት የማይቻል መሆኑ

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፩፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጽ ፩፻፹፬ እና ተከታዮቹ ደንብ የተላለፈው ሰው እንደሚቀጣ የሚደነግጉ ሆኖ ሳለ፣ ተመሳሳይ ሃሳብ በየድንጋጌው የመጀመሪያ ፓራግራፍ ውስጥ እንደገና ማስቀመጡ ድግግሞሽ ስለሆነ የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተሰርዟል።

የድንጋጌው ሁለተኛ ፓራግራፍ፣ ቅጣትን ማገድ የማይቻል ስለመሆኑ ይደነግጋል። ሆኖም በአንቀጽ ፩፻፺፯ (፪) መሠረት አስቀድሞ በአመክሮ መፈታትም ለደንብ ተላላፊነት ተፈጻሚ ሊሆን ስለማይገባ፣ ቅጣት ማገድም ሆነ በአመክሮ መፍታት እንደማይቻል በሚያሳይ መልክ የድንጋጌው ስያሜም ሆነ ይዘት ተስተካክሎ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፩፻፹፯ ቅጣትን ማቅለል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፯ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፩፻፹፰ መደበኛ የሆነ የቅጣት ማክበጃ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፰ ሆኖ ገብቷል።

የመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። ሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር ግን ድግግሞሽ በመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

አንቀጽ ፩፻፹፱ ጥፋት ሲደራረብ ቅጣትን ማክበድ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፩፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፹፱ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ሁለት ፓራግራፎች ያሉት ሲሆን አላስፈላጊ ሀረጎች ተሰርዘው ፓራግራፎቹ የተዋሃዱ ሲሆን ንዑስ ቁጥር (፩) የቅጣቱ መደራረብ ጣራ እንደሚያስፈልገው ስለታመነ የማረፊያ ቤቱ እስራት ከአንድ ዓመት፣ እንደማይበልጥ፤ መቀጮው የተፈጥሮ ሰውን በሚመለከት ከአንድ ሺ ሁለት መቶ ብር፣ የሕግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት በሚመለከት ከአምስት ሺ ብር ለመብለጥ እንደማይችል ተገልጾ ተረቅቋል።

በተጨማሪም በንዑስ ቁጥር (፩) ሆነ በንዑስ ቁጥር (፪) ላይ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን አደራርቦ ሲፈጽም፣ የመቀጮው መጠን እስከ አምስት ሺህ ብር ሊደርስ እንደሚችል የሚገልጽ አዲስ ሐረግ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሁለተኛው ፓራግራፍ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል።

ንቀጽ ፯፻፷፱ <u>በደጋጋሚነት ጊዜ ቅጣትን ማክበድ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፷፱ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በተለይም የተፈረደው ቅጣት <u>ከተሰረዘበት</u> ጊዜ አንስቶ የሚለውን ሀረግ፣ <u>በይቅርታ ቀሪ ከሆነበት</u> ጊዜ አንስቶ በሚል በመተካት አነጋገሩ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል።

አንቀጹ በተጨማሪ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ንቀጽ ፯፻፸ <u>መደራረብና መደጋገም</u>

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፯፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፸ ሆኖ ገብቷል።

ድንጋጌው የእስራቱን ጣራ ሲገልጽ የመቀጮውን ጣራ አልደነገገም። በመሆኑም መቀጮው ግለሰብን በሚመለከት ከሁለት ሺህ አራት መቶ ብር፣ የህግ ሰውነት የተሰጠውን ድርጅት ከሆነ ከአስር ሺህ ብር ለመብለጥ እንደማይችል ሆኖ ተሻሽሏል። ይህም የሆነበት ምክንያት የማረፊያ ቤቱ ቅጣት ጣራና የገንዘብ መቀጮ ጣራ የንጽጽር ስሌት ተሰርቶለት ነው።

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>

<u>ክስ የሚቀርብባቸው፣ ክስና ቅጣት የሚታገድባቸውና ቀሪ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች</u>

አንቀጽ ፯፻፸፩ <u>የክስ አቀራረብ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፸፩ ሆኖ ገብቷል።

ይህ አንቀጽ በቀድሞ ህግ መሠረት የምዕራፍ ሁለት የመጀመሪያው ድንጋጌ ነበር፤ በዚህ ህግ ግን የዚህ ምዕራፍ አካል ሆኖ ገብቷል። ምዕራፍ ሁለት የሚደነግገው ስለቅጣት አፈጻጸም በመሆኑና የዚህ አንቀጽ ይዘት ግን ከክስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ ከነበረበት ቦታ ተሰርዞ ክሶችን በሚመለከተው በዚህ በሶስተኛው ምዕራፍ ስር ሊገባ ችሏል።

በቁጥር ፯፻፷፩ (፩) ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚለው ተሰርዟል። ምክንያቱም አንቀጹ የሚደነግገው ደንብ መተላለፍን በተመለከተ ክሱ እንዴት እንደሚቀርብ ስለሆነና የእንግሊዝኛው ቅጂ the provisions of this Code የሚለው Code of petty offences ለማለት ስለሆነ ነው።

በተጨማሪም ድንጋጌው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፯፻፷፪ <u>የግል አቤቱታ የሚቀርብባቸው ሁኔታዎች</u>

የቀድሞው ሕግ ቁጥር ፯፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

<u>የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፱ ድንጋጌ መሰረዝ</u>

ይህ ድንጋጌ በደንብ ተላላፊነት የተከሰሰ ወይም ቅጣት የተፈረደበት ጥፋተኛ መሞቱ ስለሚያስከትለው ውጤት የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ ፩፻፲፬ እና ፩፻፲፭ ስለተከሳሽ መሞት የተጻፈው ድንጋጌ ለደንብ ተላላፊም ተፈጻሚነት እንዳለው ከአንቀጽ ፯፻፶፬ መረዳት ስለሚቻል ተሰርዟል።

አንቀጽ ፯፻፷፫ <u>የይርጋ ዘመን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፷፫ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌውም ላይ የቃላት ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን በሁለተኛው ፓራግራፍ ስለ ፍጹም የይርጋ ዘመን አስፈላጊው ሀረግ እንዲገባና አስፈላጊ ያልሆነ አጣቃሽ ቁጥር እንዲሰረዝ ተደርጓል።

አንቀጽ ፯፻፷፬ <u>ይቅርታና ምህረት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፷፬ ሆኖ ገብቷል።

በቀድሞው ድንጋጌ ስያሜም ሆነ ይዘት ላይ ምህረትና የአዋጅ ምህረት የሚሉት ቃላት ይገኛሉ። ሆኖም በአንቀጽ ፪፻፳፱ እና ፪፻፴ ላይ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ይቅርታና ምህረት በሚሉት ቃላት እንዲተኩ ተደርጓል። ድንጋጌውም መሰየምን የማያካትት በመሆኑ መሰየምን አስመልክቶ የተገለጹት አጣቃሽ ቁጥሮች እንዲሰረዙ ተደርጓል።

አንቀጽ ፯፻፷፭ <u>መሰየም</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፷፭ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው መሠረት አንድ ደንብ ተላላፊ ለመሰየም የሚችለው ቅጣቱን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ቢያንስ አምስት ዓመት ያለፈ እንደሆነ ነው። ነገር ግን የተጠቀሰው ጊዜ መርዘሙ ደንብ ተላላፊን እንደወንጀለኛ የሚቆጥር በመሆኑ ወደ አንድ ዓመት ዝቅ እንዲል ተደርጓል። የተጠቀሰው ጊዜም ካለፈ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንጹህ ስሙ እንዲመለስለት ተደርጎ ተረቋል። ከዚህም በላይ የአንድ ዓመቱ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጥፋተኛው ቅጣቱን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ብቻ ሳይሆን ቅጣቱ በይርጋ ወይም በይቅርታ ቀሪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል።

www.abyssinialaw.com

ከዚህም በላይ ደንብ ተላላፊው ወይም ወኪሉ ለፍርድ ቤት ካላመለከተ በስተቀር እንደማይሰየም በድንጋጌው ሁለተኛው ፓራግራፍ ላይ ተገልጾ ነበር:: ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ሥነ-ሥርዓት ከጥፋቱ ቀላል መሆን አንጻር ሲታይ በጥፋተኛውም ሆነ በፍርድ ቤቱ ላይ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር ስለሆነ ሁለተኛው ፓራግራፍ ተሰርዟል::

## ስምንተኛ መጽሐፍ

## ልዩ ክፍል

## ርዕስ አንድ

## በሕዝባዊና በማኅበራዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

## ምዕራፍ አንድ

## ወቅሳሳ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፯፻፸፮ በዚህ ርዕስ ስር በግልጽ ያልተሸፈኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን የሚመለከት ወቅሳሳ ድንጋጌ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፸፮ ሆኖ ገብቷል:: በድንጋጌው ላይ የቃላት ማስተካከያና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበታል::

### አንቀጽ ፯፻፸፯ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በደንብ መተላለፍ ቅጣት ያለው ተካፋይነት

ይህ ድንጋጌ በቀድሞው ሕግ ያልነበረ አዲስ አንቀጽ ነው:: ድንጋጌው ሁለት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅትም ሆነ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በዚህ ርዕስ ስር በሚገኙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ተካፋይ በሚሆኑበት ጊዜ ስለሚጠየቁበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው::

## ምዕራፍ ሁለት

## በመንግሥትና በሕዝብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች

## ክፍል አንድ

## በመንግሥትና በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች

### አንቀጽ ፯፻፸፰ ሕጋዊ ገንዘብን አለመቀበል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፸፰ ሆኖ ገብቷል::

በማዕድንና በወረቀት የሚለው በሁለቱም መሠረት ያለባቸው ስለሚመስል "ና" የሚለው ተሰርዞ "ወይም" ሆኖ ተሻሽሏል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፸፱ ሀሰተኛ ገንዘብ በእጅ መኖሩን አለማስታወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፸፱ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "ወደ ሀሰት የተለወጠ ገንዘብ በእጅ መኖሩን ሳያስታውቅ ስለመቅረት" ይል የነበረው ተለውጦ ከላይ የተመለከተው ስያሜ ሆኗል::

አንቀጽ ፫፻፹ ሕገወጥ በሆኑ መስፈሪያዎችና ሚዛኖች መገልገል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ ፫፻፹ ሆኖ ገብቷል::

አስፈላጊ ያልሆኑ አንዳንድ ቃላት ተሰርዘው አንቀጹ በመጠኑ ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፫፻፹፩ ጊዜያቸው ባለፈ ወይም ወደሀሰት በተለወጡ የመመላለሻ ወረቀቶች መገልገል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፩ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ ውድቅ በሆኑ ወይም ወደ ሀሰት በተለወጡ የመመለሻ ወረቀቶች ስለመገልገል ይል የነበረው ተስተካክሎ ከላይ እንደተመለከተው ሆኗል::
ድንጋጌው መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፹፪ የማዕረግ ስምና የምስክር ወረቀትን በማጭበርበር መቀበልና መገልገል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፪ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፹፫ ከሕግ ውጭ የሲቪል ኒሻኖችና የማዕረግ ምልክቶችን መስራት፣ በነዚህ መነገድና እነዚህን ነገሮች ማድረግ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፫ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው በፊደል (ሀ) ላይ "ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው" የሚል ሀረግ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን አንዳንድ የቃላት ለውጥ ተደርጎ አንቀጹ ተሻሽሏል::

## ክፍል ሁለት
## በቀረጥና በግብር ገቢዎች፣ በፋይናንስ እና አስተዳደር ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

አንቀጽ ፫፻፹፬ የቀረጥና የግብር ሕጎችን መጣስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፹፬ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፯፻፹፭ <u>በወርቅ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ምንዛሪ ሕገ ወጥ ስራ መስራትን አስመልክቶ የወጣ ሕግን መጣስ</u>

ይህ አዲስ አንቀጽ ሲሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ ፫፻፵፯ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ በአንቀጹ ስያሜ ላይ ስለተመለከቱት ነገሮች የንግዱን ወይም የምንዛሬ ጉዳይ በአንድ በተወሰነ ህጋዊ መስመር ውስጥ የሚጠበቀውን ወይም የመቆጣጠር፣የመከላከልና የልዩ ጥበቃ ስርዓት የሚፈጸምበትን ደንብ የሚጥስ ማንኛውም ሰው እንደሚቀጣ የሚደነግግ ነው።

አንቀጽ ፯፻፹፮ <u>ስለከበሩ ማዕድኖች አጠባበቅ የወጡ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞ ሕግ የቁጥር ፯፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፹፮ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ አጭርና ግልጽ ሆኖ ተስተካክሏል። ይዘቱም ግልጽ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል።

አንቀጽ ፯፻፹፯ <u>የሚተላለፉ ሰነዶችን፣ አክሲዮኖችን ወይም የግዴታ ወረቀቶችን የሚመለከቱ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፹፯ ሆኖ ገብቷል።

የድንጋጌው ስያሜ አጭርና ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፯፻፹፰ <u>ቁጠባና ባንኮችን የሚመለከቱ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፹፰ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ የአደራ ገንዘብ ማስቀመጫ ቤቶች ይል የነበረው ቁጠባ በሚል ተሻሽሏል።

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት መቃናት ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፯፻፹፱ <u>ሎተሪዎችንና ውርርዶችን የሚመለከቱ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፯፻፹፱ ሆኖ ገብቷል።

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ ዕጣዎች የሚለው ሎተሪዎች ላይ የሚካተት ስለሆነ ተሰርዟል።

የእንግሊዝኛው ቅጂ ግልጽ ስለሆነ አንቀጹ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። በተለይ በንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) የእንግሊዝኛው ቅጂ ላይ የሎተሪና ውርርዶችን ተሳታፊ የሆኑት አድራጊዎች እንደሚቀጡ /ቁማር ላይ ተሳታፊም ይቀጣል/ ብሎ ሲደነግግ የአማርኛው ግን እዚህ ነጥብ ላይ የተገለጸ ነገር የለውም። ስለዚህ ንዑስ ቁጥር (፩) (ለ) እንግሊዘኛው 'or participates in such games or betting' የሚለው "እንደዚህ ባለ ጨዋታ ወይም ውርርድ ተሳታፊ የሆነ፤ ወይም" በሚል ተተርጉሞ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) ውስጥ ገብቷል።

አንቀጹ በዚህ መልኩ ተስተካክሏል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፶ <u>የዋጋ ቁጥጥርን የሚመለከቱ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፺፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶ ሆኖ ገብቷል::

በድንጋጌው ውስጥ እንደ "ርስት" ያለው እና ሌሎች አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ተሰርዘው፣ የቃላት ማስተካከያ እና የአቀማመጥ ለውጥ ተደርጎበት ይህ አንቀጽ ተሻሽሏል::

አንቀጽ ፰፻፶፩ <u>የንግድና የሙያ ስራዎችን ስለማቋቋም፣ ማካሄድና መቆጣጠር የወጡ ህጎችን መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፩ ሆኖ ገብቷል::

የአንቀጹ ይዘት ስለሙያ ስራዎች ብቻ የሚደነግግ ሳይሆን የንግድ ሥራዎችንም የሚያካትት ስለሆነ ስያሜውም ንግድን ባካተተ መልኩ ተሻሽሏል:: ንዑስ ቁጥር ሁለት ስለ ጥብቅ ሁኔታዎችና ስለመቆጣጠር እንጂ ጠበቅ ስላለ ቅጣት ስለማያወሳ ይህም ስለአንዳንድ አስፈላጊ ሁኔታዎች በሚደነግግ ደንብ ወይም አዋጅ የሚወጣ ስለሆነና ትርጉም የማይሰጥ ስለሆነ ተሰርዟል::

አንቀጹ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>
<u>ወታደራዊ ግዴታዎችን መጣስ እና በመከላከያ ሠራዊት እንዲሁም</u>
<u>በፖሊስ ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

ስያሜው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለት በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት የቃላት መቃናት ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፪ <u>ወታደራዊ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶችን መወሰን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የወታደራዊ ደንብን መተላለፍ የሚለይበት ሁኔታ" ይል የነበረው ከላይ እንደተመለከተው ተሻሽሏል:: በድንጋጌው ይዘት ላይም የቃላት ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን፣ አጣቃሽ ቁጥሮች በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ መሆናቸው ቀርቶ በትክክለኛው ቦታቸው እንዲቀመጡ ሆኗል::

አንቀጽ ፰፻፶፫ <u>ወታደራዊ የዲሲፕሊን ቅጣቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜም ሆነ ይዘቱ ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ቃላት ተሰርዘውና የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት ተሻሽሏል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፺፬ <u>በመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፷፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፬ ሆኖ ገብቷል።

አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፺፭ <u>ደንቡ ለፖሊስ ሠራዊት ተፈጻሚ መሆኑ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፭ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>
## <u>በመንግሥት የሥራ ግዴታዎች እና በመንግሥት መሥሪያ ቤት (ባለሥልጣን) ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>
## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>በመንግሥት የሥራ ግዴታዎች ላይ የሚደረጉ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

ርዕሱ በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት ተስተካክሏል።

አንቀጽ ፫፻፺፮ <u>በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፮ ሆኖ ገብቷል።

ስያሜው ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ቁጥር ፫፻፶፮ ውስጥ ባለሥልጣን የሚለው ቃል የመንግሥት ሠራተኛ ላይ የተጠቃለለ ስለሆነ ባለሥልጣን የሚለው ቃል ተሰርዟል።

አንቀጽ ፫፻፺፯ <u>የማስገደድ መብትን ከመጠኑ ማሳለፍ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፯ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፺፰ <u>ሀቀኛነትን ማጓደል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፺፰ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ውስጥ "የውስልትና" የሚለው ቃል ሌላ ተግባርን የሚገልጽ ስለሆነ ተሰርዞ የእምነት ማጉደልን በሚል ተሰውጧል። የቃላት መቃናትም ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፬፻፺፱ የአድልዎ እርዳታ መስጠት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፬፻፺፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሰጡትን ኦፊሴላዊ ወረቀቶችን በግዴለሽነት መስጠት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻ ሆኖ ገብቷል::
የድንጋጌው ስያሜ በይዘቱ መሠረት ተስተካክሏል::

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፩ አነስተኛ የሆኑ ጉዳዮች፣ የሥነ-ሥርዓት /የዲሲፒሊን/ ቅጣቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፩ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## ክፍል ሁለት
## በመንግሥት መሥሪያ ቤት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

አንቀጽ ፭፻፪ ኦፊሴላዊ ማስታወቂያዎችን መጉዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፪ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፭፻፫ አስገዳጅ የሆኑ የፊሴል መግለጫዎችን ወይም የሚመዘገቡ ነገሮችን አለመስጠት ወይም አለማስመዝገብ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፶፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፫ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ በይዘቱ መንፈስ ተስተካክሏል:: በዚህ የደንብ መተላለፍ ሕግ ውስጥ ቸልተኝነት አያስቀጣም ካልተባለ በቀር ባይገለጽም የሚያስቀጣ ስለሆነ እዚህ በግልጽ መናገሩ የሚጨምረው ነገር ስለሌለና መርሁን መድገም ስለሆነ "ቸልተኝነት" የሚለው ቃል ተሰርዟል::

በተጨማሪም አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com



ንቀጽ ፫፻፬ ተገቢ ያልሆነ ማስታወቂያ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፶፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

ንቀጽ ፫፻፭ በሌለው ስልጣን መገልገል

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ የሚደነግገው መብት እያለው አለአግባብ የተጠቀመበትን ሳይሆን መብት ሳይኖረው እንዳለው አድርጎ የተጠቀመበትን ስለሆነ ስያሜው ይህንን በሚገልጽ መልኩ ተሻሽሏል፡፡

በተጨማሪም አንቀጹ ይበልጽ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፫፻፮ ባለሥልጣንን የመርዳት እንቢታ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፫፻፯ ትዕዛዝን አለመፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌ ተሻሽሎ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ ገብቷል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የፊደል ተራ (ሀ) የመጨረሻው አነጋገር "ሀሰተኛ ቃል የሰጠ" የሚለው ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ የሰጠ ሰው በደንብ ተላላፊነት እንደሚጠየቅ በመደንገግ ራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሆኖ አዲስ አንቀጽ ተረቅቋል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## በሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ተረጋግቶ መኖር ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

### ክፍል አንድ
### በሕዝብ ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

አንቀጽ ፫፻፰ የጦር መሣሪያዎችንና ጥይቶችን መቆጣጠር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፪፻፷፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፫፻፱ <u>የተከለከለ የጠር መሣሪያን መያዝና በዚሁ መገልገል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፫፻፲ <u>የውጭ አገር ዜጎችን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን በማለት አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: እንዲሁም የጉዞ ሰነድና ቪዛ ስለመስጠትና የውጭ ዜጎችን ስለመመዝገብ ከወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፩/፷፩ እና ወደፊት ሊወጣ ከሚችለው ጉዳዩን ከሚመለከት የተሻሻለ ሕግ ጋር እንዲገናዘብ ለማድረግ እነዚሁኑ ባጣቀሰ መልኩ ተቀርጿል::

አንቀጽ ፫፻፲፩ <u>ያለፈቃድ ስምን መለወጥ ወይም በሌላ ስም መጠራት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፩ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>በሕዝብ ሰላም፣ ጸጥታና ሥርዓት ላይ የሚፈጸሙ</u>

<u>የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

አንቀጽ ፫፻፲፪ <u>መገናኛ ብዙኃንንና ማስታወቂያን ስለመጠበቅ የወጣውን ሕግ መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፪ ሆኖ ገብቷል::

የድንጋጌው ስያሜ "የጋዜጣንና የማስታወቂያን መታተም ጉዳይ ስለ መጠበቅ" የሚል ነበር:: ነገር ግን አንቀጹ ጋዜጣንና ማስታወቂያን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም መገናኛ ብዙኃን የሚመለከት መሆን ስለሚገባው ስያሜው በዚህ መሠረት ተስተካክሏል:: በቀድሞ ሕግ ድንጋጌ ይዘትም ላይ የሰፈረው ዝርዝር ከጽሁፍ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ብቻ ይመለከታል:: ይህ ግን በቂ ባለመሆኑ "በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት ወይም በሌላ መገናኛ ብዙኃን" የሚከናወነውንም ልዩ ልዩ ድርጊት እንዲያጠቃልል ተደርጎ አንቀጹ ተደንግጓል::

አንቀጽ ፫፻፲፫ <u>አስደንጋጭ መግለጫዎች፣ ወሬዎች ወይም ማስታወቂያዎች</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፲፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፲፬ <u>ሀሰተኛ የአደጋ ምልክት መስጠት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፷፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፬ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፲፭ <u>የሌሎችን ሥራ፣ ሰላምና ዕረፍት ስለማወክ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፭ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፲፮ <u>ሐይማኖትን የመስደብና የማዋረድ ንግግር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፮ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፲፯ <u>የበዓል ቀናቶችን መጠበቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጹ ፰፻፲፰ <u>አልኮል የሚያደርሰውን አደጋ መከላከል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፲፱ <u>ሰክሮ ወይም አእምሮ የሚያናውጥ ነገር ቀምሶ ሕዝብን ማወክ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፲፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፳ <u>የምግብና የመጠጥ ቤቶችን መጠበቅና መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፳ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፴፩ <u>የቲያትር ቤቶችንና የሕዝብ መደሰቻ ሥፍራዎችን መጠበቅ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፩ ሆኖ ገብቷል::

የቀድሞው ሕግ ድንጋጌ ፊደል ተራ (ለ) የሚደነግገው ስለሳንሱር ወይም ቅድመ ምርመራ በመሆኑና ይህም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ቀሪ የሆነ በመሆኑ፣ ይህ ተሰርዟል፤ በመሆኑም አንቀጹ ሁለት ንዑስ ፊደል እንዲኖረው ሆኖ በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ተቀርጿል:: በሽግሽጉ መሠረት ፊደል ተራ (ሐ) የነበረው ፊደል ተራ (ለ) እንዲሆን ተደርጓል::

አንቀጽ ፰፻፴፪ <u>እንስሳትን በሚያስቅቅ ሁኔታ ማንገላታት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፪ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>በሕዝብ ጸጥታ ላይ የሚፈጸም ደንብ መተላለፍ</u>

አንቀጽ ፰፻፴፫ <u>የሰዎችን ሰላማዊ ኑሮ መንካት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፴፬ <u>በአደገኞች ሰዎች ወይም በእንስሳት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፸፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፬ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፴፭ <u>የሰዓት እላፊ እና በሌሊት መዘዋወርን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፭ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው የአንቀጹን ይዘት በሚገልጽ መልኩ ተስተካክሏል::

አንቀጽ ፰፻፴፮ <u>የህንጻ ሥራዎችን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፮ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ይዘቱም በይበልጥ ግልጽነት እንዲኖረው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፭፻፳፯ <u>መንገዶችና የሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎችን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፯ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት መቃናት ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፭፻፳፰ <u>የመገናኛ ደህንነትን አደጋ ላይ መጣል</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፰ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፭፻፳፱ <u>እሳት፣ ፈንጂዎችንና አደገኛ ንጥረ ነገሮችን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፳፱ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>
## <u>በሕዝብ ጤና እና በጽዳት ጥበቃ ላይ የሚፈጸሙ</u>
## <u>የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

አንቀጽ ፭፻፴ <u>የሕዝብ ጤናና ጤናማነትን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴ ሆኖ ገብቷል።

የቀድሞው ድንጋጌ ይዘት በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተከፈለ ሲሆን ይህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሐ) ስር የአካባቢ ብክለትን የሚመለከት አዲስ ድንጋጌ እንዲገባለት ተደርጓል።

አንቀጽ ፭፻፴፩ <u>መርዛማና አደንዛዥ ንጥረ ነገሮችንና መድኃኒቶችን መቆጣጠር</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፩ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል። እንዲሁም ባሁኑ ጊዜ በዓለም-ዓቀፍ ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የናርኮቲክና ሳይትኮሮፒክ መድኃኒቶች እንዲካተቱ ሆኗል።

አንቀጽ ፭፻፴፪ <u>ሌላው ሰው ህሊናውን እንዲስት ወይም እንዲፈዝ ማድረግ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፭፻፴፪ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፰፻፵፫ ምግቦችን፣ መጠጦችንና ሌሎች ሸቀጦችን መቆጣጠር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል:: እንዲሁም ስለ ጽዳት የሚያወሳው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፯፻፹፰ (ለ) በዚህ አንቀጽ ፰፻፴፰ (ሀ) ውስጥ የተመለከተ ስለሆነ ወጥቷል::

አንቀጽ ፰፻፵፬ የሕክምናና የመፈወስ ሙያዎችንና ሆስፒታሎችን መቆጣጠር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፹፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፬ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፵፭ የማስታወቅ ግዴታን አለመፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ፰፻፵፭ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፵፮ የማከምን ተግባር አለመፈጸም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፮ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፵፯ አስከሬን ስለመቅበርና ስለማቃጠል የወጣውን ደንብ መጣስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፯ ሆኖ ገብቷል::

ስያሜው የአንቀጹን ይዘት ይበልጥ በሚገልጽ መልኩ ተሻሽሏል::

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## ርዕስ ሁለት
## በሰዎችና በንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች
## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፰፻፵፰ በዚህ ርዕስ ስር በግልጽ ባልተሸፈኑ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለውን ተካፋይነት የሚመለከት ጠቅላላ ድንጋጌ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፰ ሆኖ ገብቷል::

መሠረቱ /መርህ/ የሚለው በአረቃቀቅ ሂደት ባብዛኛው መርሆችን የሚያስቀምጥ አንቀጽ ስያሜ እንጂ ቅጣትን የሚደነግግ የአንቀጽ ስያሜ ስለማይሆን የቀድሞው

www.abyssinialaw.com

የድንጋጌው ስያሜ ተሰርዟል:: ጠቅላላ ድንጋጌ ግን በሌላ የተለየ አንቀጽና የሕግ ድንጋጌ የማይቀጣ ድርጊት ሳይቀጣ እንዳያመልጥ የሚያዝበት መንገድ ስለሆነ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ስያሜው መስተካከሉ የተሻለ ነው::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

ንቀጽ ፰፻፴፱ <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ርዕስ ስር በተመለከቱት የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ያለው ተካፋይነት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፱ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው በቀድሞው ህግ መሠረት የምዕራፍ ሶስት የመጨረሻው ነበር:: ሆኖም አነጋገሩ የሚመለከተው ምዕራፍ ሶስትን ብቻ ሳይሆን በርዕሱ (Title) ያሉትን ምዕራፎች ሁሉ በመሆኑ ከነበረበት ቦታ ተሰርዞ ከምዕራፎቹ ሁሉ በፊት እንዲገባና የርዕሱ (Title) የመጀመሪያው አንቀጽ እንዲሆን ተደርጓል::

በድንጋጌው ስያሜ ውስጥ "ላይ" የሚለው ቃል መኖሩ በስያሜውና በይዘቱ ላይ መሠረታዊ ልዩነት ያስከትላል:: "ላይ" የሚለው ቃል መኖሩ በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ማህበር ወይም ድርጅት ላይ በደል እንደሚፈጸምበት ያመለክታል:: ሆኖም የአንቀጹ አሳብ አንድ ማኅበር ወይም ድርጅት የደንብ ተላላፊነት ተግባር መፈጸሚያ መሣሪያ ሲሆን ድርጅቱም ሆነ የእርሱ ኃላፊዎች ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው:: ይህም ሃሳብ በአንቀጽ ፯፻፲፮ ላይ በግልጽ ሰፍሮ ስለሚገኝ በዚሁ መሠረት ድርጅቱም ሆነ የድርጅቱ ኃላፊዎች መጠየቅ እንዲችሉ "ላይ" የሚለው ቃል ተሰርዟል::

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ አዲስ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ (፪) የቀድሞውን ሕግ የቁጥር ፰፻፰ን ድንጋጌ ሃሳብ የያዘ ነው:: ንዑስ አንቀጽ ፩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ርዕስ ስር ባሉ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ተካፋይ የሚሆንበትን ሁኔታ ይመለከታል:: ንዑስ አንቀጽ (፪)ደግሞ የአንድ ድርጅት ባለሥልጣኖች ወይም ሠራተኞች ከድርጅት ስራ ጋር በተያያዘ የደንብ መተላለፍ ቅጣት ሲፈጽሙ እነርሱም ተጠያቂ እንደሚሆኑ ይደነግጋል::

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>በሰዎች ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ለሰውነት ጥበቃ የወጡ ደንቦችን መተላለፍ</u>

አንቀጽ ፰፻፵ <u>የእጅ እልፊትና ቀላል የኃይል ድርጊት</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ለግልጽነት ሲባል የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፵፯ አስከሬን ወይም ቁስለኛን አለማስታወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፯ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አስፈላጊው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፵፰ በግል ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፰ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ለግልጽነት ሲባል የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፵፱ የግል ምሲጢር የመጠበቅ መብትን መንካት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵፱ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶ በክብር ላይ የሚፈፀሙ ቀላል ጥፋቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

## ክፍል ሁለት
## በመልካም ጠባይ/ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

አንቀጽ ፰፻፶፩ በመልካም ሥነ-ምግባርና መልካም ጠባይ /ሞራሊቲ/ ላይ የሚፈጸሙ ጥፋቶች

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፺፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፩ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ለግልጽነት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፪ አስነዋሪ የዝሙት ጥያቄ እና የብልግና ተግባር

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

ጥፋቱ ከበድ ያለ ስለሆነና ደንብ ተላላፊዎች ከዚህ ድርጊት እንዲቆጠቡ ሌሎችም ወደፊት ይህንን እንዳይፈጽሙ ለመግታት ቅጣቱ እስከ አንድ ወር እንዲደርስ ሆኗል::

ለበለጠ ግልጽነት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፴፯ ለብልግና ተግባር የሚያነሳሳ ማስታወቂያና መግለጫ ማውጣት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፯ ሆኖ ገብቷል፡፡

ቅጣቱ የመግታት ኃይል እንዲኖረውና ደንብ ተላላፊዎች ወደዚህ ድርጊት እንዳይመለሱ ለማድረግ ሲባል እስከ መደበኛው ከፍተኛ የማረፊያ ቤት እሥራት እንዲደርስ የእስከ አንድ ወር ገደቡ ተነስቷል፡፡ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፴፰ የማስወረጃ ዘዴዎችን ማስተዋወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፷፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፰ ሆኖ ገብቷል፡፡

የቀድሞው ድንጋጌ በፊደል ተራ (ሀ) ውስጥ የተጠቀሰው የጽንስ መከላከያ ማስታወቅ ብሎም መጠቀም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በአሰራር የማያስቀጣና የተሰረዘ ሆኖ ስለተቆጠረ /disuse/ ከዚያም በላይ ከስነ ሕዝብ ፖሊሲው ጋር እንዲጣጣም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር ፱ ስለተሻረ ከዚህ አንቀጽ እንዲወጣ ሆኗል፡፡

የቀድሞው የፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበት በአንድ ፓራግራፍ ያለ ፊደላት ተራ ተረቅቋል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

በንብረት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

ይህ ምዕራፍ በአዲሱ የወንጀል ህግ ላይ ምዕራፍ አራት የተባለው በስህተት ነው፤ ምዕራፍ ሶስት ተብሎ ሊጻፍ ይገባ ነበር፡፡

ክፍል አንድ

ብሔራዊ ሀብቶችን መጠበቅ

አንቀጽ ፰፻፴፱ ታሪካዊ፣ ከኑ-ጥበባዊ እና የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፴፱ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

አንቀጽ ፰፻፵ እጽዋትንና እንስሳትን መጠበቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፬፻፸፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፵ ሆኖ ገብቷል፡፡

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ክፍል ሁለት
## ሌሎች ንብረቶችን መጠበቅ

በምዕራፍ ሁለት እና በክፍል ሁለት ስያሜዎች መካከል ሊከሰት የሚችለውን መምታታት ለማስወገድ ሲባል ክፍል ሁለት "ሌሎች ንብረቶችን መጠበቅ" ተብሏል::

አንቀጽ ፰፻፶፩ የመንግሥት እና የግል ንብረቶችን መጠበቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፩ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፪ ቀላል ስርቆት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፪ ሆኖ ገብቷል::

መደናገርን ለማስቀረት የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፫ እሸት መቅጠፍና ከማሳ መቃረም

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፫ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፬ አጠራጣሪ የሆኑትን አንዳንድ ዕቃዎች ያለምክንያት መያዝ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፬ ሆኖ ገብቷል::

ድንጋጌው አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፭ ንብረቶችን መሰወርና አግባብ ላለው ባለሥልጣን አለማስታወቅ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፭ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

አንቀጽ ፰፻፶፮ የሌላ ሰውን ንብረት ማበላሸት ወይም ዋጋው እንዲቀንስ ማድረግ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፯፻፲ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፮ ሆኖ ገብቷል::

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል::

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፰፻፶፯ በሕዝብ ሐውልቶች ላይ ጉዳት ማድረስ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፩ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፯ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

## ክፍል ሶስት

## በንብረት ላይ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በጠቅላላው

አንቀጽ ፰፻፶፰ የሌላውን ሰው ጥቅም በተንኮል መጉዳት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፪ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፰ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፰፻፶፱ ወስላታነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፫ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፶፱ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፰፻፷ ሌሎች ጥቅሞችን በማጭበርበር ማግኘት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፬ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፷ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፰፻፷፩ አውቃለሁ ባይነት

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፭ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፷፩ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ በይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፰፻፷፪ ያለፈቃድ ገንዘብ መሰብሰብ

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፰፻፲፮ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፰፻፷፪ ሆኖ ገብቷል።

አንቀጹ ግልጽነት እንዲኖረው የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አራት
## በኢኮኖሚ፣ ንግድና የባህር አስተዳደር ጉዳዮች ላይ
## የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች

አንቀጽ ፫፻፴፫ <u>የንግድና የሂሳብ መዛግብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መተላለፍ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፯ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፫ ሆኖ ገብቷል። አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፴፬ <u>በግዴታ የፍርድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ እምቢተኛ መሆን</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፰ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፬ ሆኖ ገብቷል። አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።

አንቀጽ ፫፻፴፭ <u>ስለንግድ መርከቦች የወጡትን ደንቦች መጣስ</u>

የቀድሞው ሕግ የቁጥር ፫፻፲፱ ድንጋጌ የዚህ ሕግ አንቀጽ ፫፻፴፭ ሆኖ ገብቷል። አንቀጹ ግልጽ እንዲሆን የቃላት ማስተካከያ ተደርጎበታል።